# ኰኵሐ ፡ ሃይማኖት ።

ወጣቲ ፡ ተመልከቲ ፡ እንዳትሳሳቲ ።



ጥንታዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ነፋስ ፡ ነፈሰ ፤ ዝናም ፡ ዘነመ ፤ ጎርፉም ፡ ጎረፈና ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ሊያናውጠው ፡ ቃጣ ። ቤት ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግን ፡ በጽኑ ፡ መሠረት ፡ በተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፤ በመንፈሳዊ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፤ በጾም ፡ በጸሎት ፡ የተመሠረተ ፡ ስለኾነ ፡ ሊያንዋውጸው ፡ አልቻለም ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፭ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ጥር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ፡ ም፡

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ፡ ኰኵሐ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ወጣት ፡ ተመልከት ፡ እንዳትሳሳት ፡ የተባለ ፡ መጽሐፍ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ከባቶቻቸው ፡ የወረሷት ፡ ሃይማኖት ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፤ በድቡሽት ፡ ላይ ፡ ሳይኾን ፡ በጽኑ ፡ ጭንጫ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መኾኑን ፡ እንዲረዱበት ፤

ከውስጡ ፡ የሚመነጭ ፡ ምንጭ ፡ ሳይኖረው ፡ በድንገተኛ ፡ ዝናም ፡ ከሚ ንቧቧ ፡ ጎርፍ ፡ ከሐሰተኛ ፡ ሰባኪ ፡ ሊድኑበት ፡ ከመልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀንበሬ ፡ ተዘጋጀ ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በነገሡ ፡ በ፴፮ኛው ፡ ዓመት ።
ብፁዕ ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በኾኑ ፡ በ፳ኛው ፡ ዓመት ።
በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

## መቅድም ።

መቅድም ፡ ማለት ፡ ከመጽሐፉ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ የሚገኝ ፡ ጽሐ
የነገሩ ፡ መሪ ፡ ፊታውራሪ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ይደልዎ ፡
ያነብብ ፡ ቅድመ ፡ ይዝክር ፡ ስሞ ፡ ለበዓለ ፡ መጽሐፍ ፡ ወእምዝ ፡ ያንብብ ፡ ወ
ሀር ፡) መጽሐፍ ፡ የሚመለከት ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ የደራሲውን ፡ ስምና ፡ ታሪ
ማወቅና ፡ መረዳት ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ መጽሐፉን ፡ ማንበብ ፤ መተርጐም ፡ ይገባዋ
ብሎ ፡ እንደነገረን ፡ የመቅድም ፡ አጻጻፍ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሊጠ
ይገባል ። እኔም ፡ በዚሁ ፤ መሠረት ፡ አስቀድሜ ፡ ስሜንና ፡ አድራሻዬን ፡ ቀጥየ
ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሰብኩበትን ፡ ምክንያት ፡ እያከታተልኩ ፡ እጽፋለ



እኔ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀንበሬ ፡ የተወለድኩበትና ፡ የተማርኩበት ፡ ሀገሬ ፡ ዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ የተባልኩበት ፡ ፀገሬ ፡ ብቸና ፡ ጊዮርጊስ ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሰብኩበት ፡ እኔ ፡ የማውቀውን ፡ ሌላ ፡ አ
ቀውም ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ማነንም ፡ ሰው ፡ ለመንቀፍ ፡ ወይም ፡ የማነንም ፡ ስም ፡
ጥፋት ፡ አደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

በ፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታተመ ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ የተባለ ፡ ጽሑፍ ፡ በ፵፫ ፡ ዓ፡ ም፡ አየሁ ። ምሥጢሩም ፡ እንደ ፡ ስሙ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መስሎኝ፡ እስክመለከተው ፡ ቸኰልኩ ።

ብመለከተው ፡ ግን ፡ ሐሳቡ ፡ ኹሉ ፡ የተዘበራረቀ ፤ ጥቅሱ ፡ ከሐሳብ ፡ የተራራቀ ፤ ራሱን ፡ በበጎ ፡ ስም ፡ የተከናነበ ፤ ውስጡ ፡ በማስመሰል ፡ ቡትት ፡ የተተበተበ ፡ በሰውም ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ የተጠላ ፤ ስድብን ፡ ብቻ ፡ የተመላ ፤ ጥንታዊት ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የሚነቅፍ ፤ ቅዱሳን ፡ መላእክትን ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታትን ፡ የሚዘልፍ ፤ የሰው ፡ ስም ፡ የሚያጠፉ ፤ ሕገ ፡ ምንኵስናን ፡ የሚያክፋፋ ፡ ኾኖ ፡ አገኘሁት ።

ለእግዚአብሔር ፡ በጎ ፤ መሥዋዕት ፡ ያቀረብን ፡ እየመሰላቸው ፡ እናንተን ፡ የሚገሉበት ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ፡ ያለውን ፡ ሳይገነዘበው ፡ ቀርቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የሠራሁ ፡ መስሎት ፡ ይኸን ፡ ብዬ ፡ በጣም ፡ ተገረምኩ ፡ ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፩ ።

ይህን ፡ በማውጣት ፡ በማውረድ ፡ ሳለሁ ፡ እሱ ፡ ሐሳቡ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ በማታለል ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመሸለግ ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ጉዳት ፡ የማያሳዝነው ፡ ኖሮ ፡ ለመጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ተቃራኒነቱ ፡ በሕግ ፡ የታወቀውን ፡ ሐተታ ፡ መናፍስት ፡ ዐውደ ፡ ነገሥት ፡ መጽሐፈ ፡ ጥንቆላ ፡ አሳትሞ ፡ በግልጽ ፡ ለሕዝብ ፡ ይሸጥ ፡ ጀመረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለካንስ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ወእምፍሬሆሙ ፡ ተአምርዎሙ ፡ ያለን ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አታላይነቱን ፡ በእርግጥ ፤ ተረዳሁት ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፮ ።

በሊህ ፡ በኹለቱ ፡ መጻሕፍቶቹም ፡ ምክንያት ፡ በሕዝቡ ፤ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ተመለከትኩ ። በሕዝብ ፡ ከደረሱ ፡ ጉዳቶችም ፡ ጥቂቶችን ፡ አስታውሳለሁ ።

፩ኛው ፡ ከእስራኤል ፡ በቀር ፡ ተቀዳሚ ፡ ሳይኖረው ፡ ለዓለም ፡ ተቀዳሚ ፡ ኾኖ ፡ ብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ በሰሎሞን ፡ ጊዜ ፡ ተቀብሎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖረውን ፤ ኋላም ፡ ወንጌልን ፡ በፈቃዱ ፡ ተቀብሎ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ሕገ ፡ ጣዖትን ፡ ለይቶ ፡ የሚኖረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እውነተኛውን ፡ ቀጥተኛውን ፡ ያባቶቹን ፡ ግብ ፡ አስለቅቆ ፡ ወሰን ፡ ወደሌለው ፡ መድረሻው ፡ ወደማይታወቅ ፡ የተውሶ ፡ ባህል ፡ መርቶ ፡ ባክኖ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ መሞከሩ ፡ ነው ።

፪ተኛውም ፡ የጥንቆላ ፡ መጽሐፍ ፡ በመሸጡ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተገኘ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕውቀት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ ወደማወቅ ፡ የተመራውን ፡ ሕዝብ ፡ ከሰይጣን ፡ በተገኘ ፡ ዕውቀት ፡ እየተመራ ፡ እነአካአብ ፡ እነ ፡ አካዝያስ ፡ በወደቁበት ፡ ጉድጓድ ፡ እንዲወድቅ ፡ ማድረጉ ፡ ነው ፡ ነገ ፡ ቀዳ ፡ ፳፪ ፡ ፳-፴፱ ። ነገ ፡ ካል ፡ ፩ ፡ ፪-፯ ።

፫ተኛ ፡ ወሎሙ ፡ በሙሴናሆሙ ፡ ዐሰበ ፡ ዓመፃ ፡) ፪ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ፡ በጥፉ ፡ ትምህርታቸው ፡ አስተምረናል ፡ ብለው ፡ ዋጋ ፡ ይቀበላሉ ፡ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ በሊህ ፡ በጥፉዎች ፡ መጻሕፍቶቹ ፡ የሕዝቡን ፡ ገንዘብ ፡ መሸለጉ ፡ ነው ።



ይህንም ፡ ሥራውን ፡ ትኩር ፡ አድርጌ ፡ ስመለከት ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወተለውዋ ፡ ለፍኖተ ፡ በለዓም ፡ ወልደ ፡ ባሶር ፡ ዘአፍቀራ ፡ ለዐስበ ፡ ዓመፃ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡ የቀናውን ፡ መንገድ ፡ ትተው ፡ (የዐመፅ ፡) የግፍ ፡ ዋጋ ፡ የወደደ ፡ የባሶር ፡ ልጅ ፡ የበለዓምን ፡ መንገድ ፡ ተከተሉ ፡ ብሎ ።

ይሁዳም ፡ አሌ ፡ ሎሙ ፡ እስመ ፡ በፍኖተ ፡ ቃየል ፡ ሖሩ ፡ ወበዐስበ ፡ ጌጋዩ ፡ ለበለዓም ፡ ውዕዩ ፡ ወበክህዱ ፡ ለቆሬ ፡ ተኀጕሉ ፤ ይሁ ፡ ፲፩ ።

ወዮላቸው ፡ በቃየል ፡ መንገድ ፡ ሔደዋልና ፡ የበለዓምንም ፡ የዐመፅ ፡ ዋጋ ፡ በመውደድ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ተቃጥለዋልና ፡ በቆሬ ፡ ክህደት ፡ ጠፉ ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ፡ ስለሱና ፡ እሱን ፡ ስለመሰሉ ፡ ሰዎች ፡ መኾኑን ፡ በርግጥ ፡ አምናለሁ ።

ይህም ፡ እምነቴ ፡ በእውነት ፡ እንጂ ፡ በሐሰት ፡ አለመኾኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ከበለዓም ፡ ታሪክ ፡ ዘጭሩ ፡ እጽፋለሁ ። በለዓም ፡ ሀብተ ፡ መርገም ፤ ሀብተ ፡ በረከት ፡ ተሰጥቶት ፡ እሱ ፡ የረገመው ፡ ይረገም ፤ እሱ ፡ የባረከው ፡ ይባረክ ፡ ነበረ ። እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ሲወጡ ፡ አሕዛብን ፡ ድል ፡ እየነሡ ፡ ሲመጡ ፡ በባላቅ ፡ ወልደ ፡ ሶፎር ፡ ሀገር ፡ አጠገብ ፡ በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ሰፈሩ ።

እስራኤል ፡ በአሞራውያን ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ኃይል ፡ ሰምቶ ፡ ባላቅ ፡ ወልደ ፡ ሶፎር ፡ ፈራ ፡ ተንቀጠቀጠ ።

አንተ ፡ የረገምከው ፡ ይጠፋልና ፡ መጥተህ ፡ ርገምልኝ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እሰጥሃለሁ ፤ ብሎ ፡ ከበለዓም ፡ ዘንድ ፡ ላከበት ።

በለዓምንም ፡ እግዚአብሔር ፤ እስራኤል ፡ የተባረከ ፡ ሕዝብ ፡ ነውና ፡ አትሒድ ፡ አትራገም ፡ አለው ። በለዓምም ፡ መላክተኞችን ፡ አይኾንም ፡ ብሎ ፡ አሰናበታቸው ። መላክተኞችም ፡ ተመልሰው ፡ ለባላቅ ፡ ነገሩት ።

ባላቅ ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ አነሰኝ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ መስሎት ፡ ከፊተኞች ፡ የከበሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ መርጦ ፡ ያልከውን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ እሰጥሃለሁና ፡ አደራህን ፡ ናልኝ ፡ ብሎ ፡ ዳግም ፡ ላከበት ።

በዚች ፡ ሌሊት ፡ በራእይ ፡ መሔዱን ፡ ሒድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጠልህን ፡ ተናገር ፡ እንጂ ፡ አትራገም ፡ አለው ።

ሲነጋ ፡ አኅያውን ፡ ጭኖ ፡ ወደ ፡ ባላቅ ፡ ሲሔድ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመንገዱ ፡ ላይ ፡ ላኅያይቱ ፡ ሰይፉን ፡ መዞ ፡ ታያት ። ሸሽታ ፡ ወደ ፡ ሜካ ፡ ይዛው ፡ ገባች ። ደብድቦ ፤ ከመንገዱ ፡ መለሳት ። መልአኩም ፡ ከዚያ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ከማያሰኝ ፡ ከጠባብ ፡ ጎዳና ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ታያት ። እሸሻለሁ ፡ ስትል ፡ እግሩን ፡ ከግንብ ፡ አጣብቃ ፡ አቈሰለችው ፡ ይደበድባት ፡ ጀመረ ፡ የምትሔድበት ፡ መንገድ ፡ ስላጣች ፡ በሦስተኛው ፡ ተኛች ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አብዝቶ ፡ መታት ። አኅያይቱ ፡ እንደሰው ፡ አንደበት ፡ አውጥታ ፡ ምነው ፤ ምን ፡ ባልኩህ ፡ እንዲህ ፡ አብዝተህ ፡ ትመታኛለህ ፡ አለችው ። በለዓምም ፡ እንዲህ ፡ ስታላግጪብኝ ፡ በጄ ፡ ሰይፍ ፡ ኖሮስ ፡ ቢኾን ፡ በገደልኩሽ ፡ ነበረ ፡ አላት ። ካንተ ፡ የበለጠ ፡ ግሩም ፡ መልአክ ፡ ቢታየኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ካሰብከው ፡ ሳደርስህ ፡ የኖርኩ ፡ አኽያህ ፡ አይደለሁምን ፡ አለችው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መልአኩ ፡ ለርሱም ፡ ተገለጠለት ። በለዓም ፡ በግንባሩ ፡ ወድቆ ፡ሰገደለትና ፡ ጌታዬ ፡ ባላውቅ ፡ ነው ፡ ፈቃድህ ፡ እንዳይደለ ፡ ልመለስ ፡ አለው ። መልአኩም ፡ መሔዱን ፡ ሒድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የምገልጽልህን ፡ ብቻ ፡ ተናገር ፡ እንጂ ፡ እንዳትራገም ፡ አለው ። እሺ ፡ ብሎ ፡ ሔደ ።

በማግስቱ ፡ ባላቅ ፡ በለዓምን ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ወደሚታዩበት ፡ ተራራ ፡ አወጣው ፡ በለዓምም ፡ ባላቅን ፡ ፯ ፡ መሠዊያ ፡ አዘጋጅልኝ ፡ ፯ ፡ ላም ፡ ፯ ፡ ዳንግሌ ፡ አቅርብልኝ ፡ አለው ። ባላቅም ፡ እንዳለው ፡ አደረገለት ፡ ፯ቱን ፡ ላሞችና ፡ ፯ቱን ፡ ዳንግሌ ዎች ፡ አርዶ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ያሟርት ፡ ጀመረ ። ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መርገሙን ፡ ወደ ፡ በረከት ፡ ስለመለሰበት ፡ በመርገሙ ፡ ፈንታ ፡ የሶፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡ እስራ ኤልን ፡ ርገምልኝ ፡ ብሎ ፡ ጠራኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልረገመውን ፡ ምን ፡ አግዶኝ ፡ ረግማለሁ ። ከተራሮች ፡ ራስ ፡ አየዋለሁ ፡ ከኮረብታውም ፡ እመለከተዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋቸውን ፡ ነገረው ።

ባላቅም ፡ ርገምልኝ ፡ አልኩህ ፡ እንጂ ፡ መርቅልኝ ፡ አልኩህን ፡ ቢለው ። እግዚአብሔር ፡ የገለጸልኝን ፡ እናገራለሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ላደርግ ፡ እችላለሁ ፡ አለው ። ባላቅም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ይዞት ፡ ገባ ።

በማግስቱ ፡ ገሚሶቹ ፡ ከሚታዩበት ፡ ገሚሶቹ ፡ ከማይታዩበት ፡ ተራራ ፡ ወስዶ ፡ እንደዚያው ፡ ፯ ፡ ላም ፡ ፯ ፡ ዳንግሌ ፤ ሠዋለት ። በለዓምም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ያሟርት ፡ ጀመረ ። እንደዚያው ፡ መራገም ፡ ስላልተቻለው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሐሰት ፡ አይናገርም ፡ በሠራውም ፡ ሥራ ፡ አይጸጸትም ፡ እኔ ፡ እስራኤልን ፡ እንድመርቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብያለሁና ። በያዕቆብ ፡ ክፋት ፡ አላይበትም ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አምላክ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነውና ። በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ አስማት ፡ የለም ፡ በእስራ ኤልም ፡ ላይ ፡ ሟርተኝነት ፡ አይቻልም ። ይህ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ደቦል ፡ ነው ፤ ያንበሳ ፡ ደቦል ፡ የሰበረውን ፡ ሥጋውን ፡ ሳይበላ ፡ ደሙን ፡ ሳይጠጣ ፡ እንዳ ይመለስ ፡ ይህ ፡ ሕዝብም ፡ አሕዛብን ፡ ሳያጠፋ ፡ አይመለስም ፡ አለው ።

ባላቅም ፡ መራገም ፡ ቢቀር ፡ እንኳ ፡ ባይኾን ፡ መመረቁን ፡ አትተውምን ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ለምን ፡ ትመርቀዋለህ ፡ አለው ። እግዚአብሔር ፡ ያዘዘኝን ፡ አደርጋለሁ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አግዛለሁን ፡ አለው ።

ባላቅም ፡ ኹሉም ፡ ወደማይታዩበት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ይዞት ፡ ሒዶ ፡ ፯ ፡ መሠዊያ ፡ ፯ ፡ ላም ፡ ፯ ፡ ዳንግሌ ፡ አዘጋጀለት ። በለዓም ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ እግዚ. አብሔር ፡ እስራኤልን ፡ እንዲመርቅ ፡ እንጂ ፡ እንዲረግም ፡ እንዳልፈቀደለት ፡ ስላ ወቀ ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ሊያሟርት ፡ አልሔደም ፤ በዚያው ፡ ባለበት ፡ ኾኖ ፡ እስ ራኤል ፡ በየነገዳቸው ፡ ሲጓዙ ፡ በዓይኑ ፡ ሕሊና ፡ አይቶ ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፡ ሰፈ ርህና ፡ ድንኳንህ ፡ ምን ፡ ያምር ? እስራኤል ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ተኝቷል ፡ እንደ ፡ ብርቱይቱ ፡ እንስት ፡ አንበሳም ፡ አንቀላፍቷል ፡ ማን ፡ ሊያስነሣው ፡ ይችላል ፡



ጠላቶቹን ፡ አጥንታቸውን ፡ ይሰብራቸዋል ፡ በፍላጻ ፡ እየወጋ ፡ ይጥላቸዋል ። ያዕቆብ ፡ ሆይ ፡ የሚባርክህ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ የሚረግምህም ፡ የተረገመ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባላቅ ፡ ወልደ ፡ ሶፎር ፡ በበለዓም ፡ ተቆጥቶ ፡ እኔ ፡ ልትረግ ምልኝ ፡ ጠራኹህ ፡ እንጂ ፡ ልትመርቅልኝ ፡ ኖሯልን ፡ እነሆ ፡ ስትመርቃቸው ፡ ሦስተኛህ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ አንተን ፡ ላከብርህ ፡ አስቤ ፡ ነበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከከለ ከለህ ፡ ሒድ ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ አቃጥሎት ፡ ባልራገም ፡ ምን ፡ ቸገረህ ፡ እነሱን ፡ ላጥፋልህ ፡ እንጂ ፡ ገንዘቡን ፡ ስጠኝ ፡ አለው ።

ባላቅም ፡ እነሱ ፡ ከጠፉ ፡ ባትራገም ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡ አለው ። እንግዲ ያስ ፡ ያገርህን ፡ ሴቶች ፡ ባዋጅ ፡ አሰብስበህ ፡ መልካካሞችን ፡ ጠርተህ ፡ ሽልመህ ፡ አስጊጠህ ፡ ለጣዖቱ ፡ ከተሠዋው ፡ ተረፈ ፡ መሥዋዕት ፡ አስይዘህ ፡ ስደዳቸው ፡ እስራኤል ፡ ሴትነታቸውን ፡ ሲያውቁ ፡ እየተነጣጠቁ ፡ ፈቃዳችንን ፡ ፈጽሙልን ፡ ይሏቸዋል ፤ ፍቅር ፡ የጋራ ፡ አይደለምን ፡ እናንተም ፡ ይህን ፡ ብሉልን ፡ ይበሏቸው ፡ ያንጊዜ ፡ ተረፈ ፡ መሥዋዕቱን ፡ ሲበሉ ፡ አምላካቸው ፡ ቀናዒ ፡ ነው ፡ ተበቅሎ ፡ ያጠፋልሃል ፡ ብሎ ፡ ጥልቅ ፡ ምክር ፡ መክሮ ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀብሎ ፡ ሒዷል ፡ ዘኍል ፡ ፴፩ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ።

ባላቅ ፡ ወልደ ፡ ሶፎርም ፡ በለዓም ፡ እንደመከረው ፡ ያገሩን ፡ ሴቶች ፡ ሰብስቦ ፡ ተረፈ ፡ ጣዖቱን ፡ አስይዞ ፡ ሰደዳቸው ። እስራኤልም ፡ እየተነጣጠቁ ፡ በየፈረፈሩ ፡ ይዘዋቸው ፡ ገቡ ፤ ለሴቶች ፡ ፍቅር ፡ ሲሉ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡ በሉ ፡ ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ አመነዘሩ ፡ ከዚያው ፡ ላይ ፡ መቅሠፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈጽማቸው ፡ ጀመረ ፤ ዘምሬና ፡ ክስቢ ፡ በአውታረ ፡ ደብተራ ፡ አጠገብ ፡ ሲያመነዝሩ ፤ ፊንሐስ ፡ በቀጭን ፡ ጦር ፡ ኹለቱንም ፡ አጣምሮ ፡ ወግቶ ፡ መቅሠፍቱን ፡ ጸጥ ፡ እስኪያደር ግላቸው ፡ ድረስ ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ ፳፬ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ አልቋል ፡ ዘኍል ፡ ፳፪ ፡ ፩ -፳፭ ፡ ፲ ፡ ተመልከት ።

በለዓም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ መጥራቱ ፡ ኮከብ ፡ ይሠርቅ ፡ እምያዕቆብ ፡ ብሎ ፡ ደገኛውን ፡ ትንቢት ፡ መናገሩ ፡ ሳይቀር ፤ ለገንዘብ ፡ ሲል ፡ በረቂቅ ፡ ምክሩ ፡ ክህሊ ፡ ከመ ፡ አምላኩ ፡ የተባለውን ፡ ሕዝብ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ ለይቶ ፡ እንዳስጠፋው ።

ይህም ፡ ሰው ፡ ለማስመሰል ፡ ያህል ፡ ባፉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመልካለሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ እሰብካለሁ ፡ እያለ ፡ በረቂቅ ፡ ተንኮል ፡ የሕዝቡን ፡ ገንዘብ ፡ ለመሸለግ ፡ ዳንግሌ ፡ በግ ፡ ዳለቻ ፡ ፍየል ፡ ገብስማ ፡ ዶሮ ፡ ለሰይጣን ፡ ረዱ ፡ በደሙ ፡ ተቀበሉ ፡ በፈርሱ ፡ ታጠቡ ፡ የሚል ፤ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትሞ ፡ እየሸጠ ፡ የመ ሐፍ ፡ ጣዖት ፡ አቁሞ ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ ታጥቦ ፡ ከኃጢአት ፡ የነጻውን ፡ ሕዝብ ፡ በበጎች ፡ በፍየሎች ፡ ደምና ፡ ፈርስ ፡ እየተለወሰ ፡ ለሰይጣን ፡ እንዲገዛ ፡ ከእግዚአ ብሔር ፡ አንድነት ፡ እንዲለይ ፡ ስላደረገው ፡ በዐስበ ፡ ጌጋዩ ፡ ለበለዓም ፡ ውዕዩ ፡ ወበከህዱ ፡ ለቆሬ ፡ ተኀጕሉ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረ ፡ ስለርሱ ፡ ነው ፡ አልኩ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምናልባት ፡ አቶ ፡ ዘመንፈስ ፡ . . . በዚሁ ፡ በጥንቄላ ፡ መጽሐፉ ፡ ከጠንቋይነት ፡ ንጹሕ ፡ ለመምሰል ፡ ጥንቄላ ፡ ሐሰት ፡ መኾኑን ፡ ሰዎች ፡ እንዲያውቁት ፡ ጻፍኩት ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አልሠራውም ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ እውነት ፡ አድርጎ ፡ የሚቀበለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ጣዖት ፡ እየጠረበ ፡ የሚሸጥ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ጣዖት ፡ አላመልክም ፤ ቢል ፡ ጣዖት ፡ አላመልክም ፡ ማለቱ ፡ አጭበርባሪ ፡ አታላይ ፡ አስመሳይ ፡ መባልን ፡ ከሚደርብለት ፡ በቀር ፡ ከመምለኬ ፡ ጣዖትነት ፡ እንዳያነጻው ፡ ይልቁንም ፡ ለሕዝብ ፡ የጥፋት ፡ መሪ ፡ በመኾኑ ፡ ዕፅፍ ፡ ድርብ ፡ ቅጣት ፡ ያለበት ፡ መኾኑን ፡ ይገንዘብ ።

ይህንም ፡ ለማድረግ ፡ ያስደፈረው ፡ በጥንተ ፡ ተፈጥሮ ፡ ዲያብሎስ ፡ ከበላዩ ፡ የሚያሰማው ፡ ድምጽ ፡ ቢያጣ ፡ መላእክትን ፡ እኔ ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ እንዳላቸው ፡ አቶ ፡ ዘመንፈስም . . . ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ያደረገውን ፡ ስሕተትና ፡ ጉድለት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ዘርዝሮ ፡ ለራሱ ፡ ያስረዳው ፡ ለሕዝብም ፡ ያስታወቀበት ፡ ስላልኖረ ፡ ቆማጣን ፡ ቆማጣ ፡ ካላሉት ፡ ገብቶ ፡ ይፈተፍታል ፡ እንደተባለው ፡ ይህን ፡ የጥንቆላ ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ መድፈሩን ፡ ተገንዘብኩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገሥጾ ፡ በባሕቲቱ ፡ በባሕቲትከ ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ ተመርቶ ፡ የነበረው ፡ ሐሳቤ ፡ ዝልፍዎ ፡ በግህደት ፡ ወደሚለው ፡ መንገድ ፡ ተመለሰ ።

ስጽፍም ፡ የጥንቄላ ፡ መጽሐፍ ፡ ስሕተትነቱ ፡ በርግጥ ፡ የታወቀ ፡ ስለኾነ ፡ ስለሱ ፡ ከመጻፍ ፡ ይልቅ ፡ ራሱን ፡ እብነ ፡ ማዕዘንት ፡ በተባለው ፡ በታላቁ ፡ ደንጋይ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ቀብሮ ፡ ሳይታወቅ ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ እግረ ፡ ልቡና ፡ ማስመሰል ፡ በተባለ ፡ መርዝ ፡ እየነደፈ ፡ የጣለበትን ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ የተባለ ፡ እባቡን ፡ በበትረ ፡ ጽድቅ ፡ ቀጥቅጦ ፡ መጣልና ፡ ሬሳነቱን ፡ ለሕዝብ ፡ ማሳየትን ፡ መረጥሁ ።

ይህነንም ፤ የመረጥኩበት ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥጋዊ ፡ አስተዳደር ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ ማንም ፡ አጥቅቷትና ፡ ደፍሯት ፡ የማታውቅ ፡ በነፃነቷና ፡ በመንግሥቷ ፡ ኮርታ ፡ የምትኖር ፡ ሀገር ፡ እንደመኾኗ ፤ በመንፈሳዊም ፡ በኩል ፡ እንዲሁ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ በአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ባሕር ፡ ሲዋኝ ፡ ሳለ ፤ እንደ ፡ ርእሰ ፡ አበው ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ በተፈጥሮ ፡ እውቀቷ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ህልዎቱን ፡ አውቃ ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየንና ፤ ሌሎችንም ፡ ትእዛዛት ፡ የጠበቀች ፤ መጻሕፍተ ፡ ነቢያትንም ፡ የተቀበለች ። ክርስቶስም ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ሕግ ፡ የተጻፈላቸው ፡ ትንቢት ፡ የተነገረላቸው ፡ ሱባኤ ፡ የተቈጠረላችው ፡ አይሁድና ፡ ሕግ ፡ ያልተጻፈላቸው ፡ አሕዛብ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ወንጌልን ፡ አንቀበልም ፡ ብለው ፡ ሐዋርያትን ፡ ሲገርፏቸው ፡ ሲወግሯቸው ፡ ሲሰቅሏቸው ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረው ፡ ሱባኤ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አውቃ ፡ በፈቃዷ ፡ መምህር ፡ ፈልጋ ፡ (ነዋ ፡ ማይ ፡ መኑ ፡ ይከልአኒ ፡ ተጠምቆ ፡) ወኀ ፡ እነሆ ፡ አለ ፡ መጠመቅን ፡ ማን ፡ ይከለክለኛል ፡ ብላ ፡ ያመነች ፡ የተጠመቀች ፤ የክርስቶስን ፡ መድኀ



ኒትነት ፡ ጠንቅቃ ፡ ያወቀች ፡ ስትኾን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ዛሬ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ተነሥቶ ፤ በተለየም ፡ ለወጣቱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወንድሜ ፡ ክርስቶስን ፡ በማመንና ፡ በእውነተኛውም ፡ ጥምቀት ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ተቀብለህ ፡ ኹለተኛ ፡ ከመንፈስ ፡ የተወለድህና ፡ ከቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ጋራም ፡ የተዋወቅህ ፡ ትኾናለህ ፡ በማለት ፡ ጻፍኩልህ ፡ በማለቱ ፤ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ያልበሰሉትን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ መርምረው ፡ ያልተረዱትን ፡ ወጣቶች ፡ ሊያጠምድበት ፡ የዘረጋው ፡ አሽክላ ፡ መኾኑን ፡ ስለተረዳሁት ፡ ለወጣቶች ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ እንዲኾን ፡ በማለት ፡ ነው ።

እናንተ ፡ ወንድሞቼ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶችም ፡ በሥጋዊ ፡ በኩል ፡ ለባዕድ ፡ ተገዝቶ ፡ ነፃነትን ፡ አጥቶ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከመኖር ፡ ስለነፃነታችሁና ፡ ስለመንግሥታችሁ ፡ ደማችሁን ፡ አፍሳችሁ ፡ ዕለቱን ፡ መሞትን ፡ እንድትመርጡ ፡ አምናለሁ ።

ስለነፃነታችሁና ፡ ስለመንግሥታችሁ ፡ ደማችሁን ፡ ለማፍሰስ ፡ ቈራጦች ፡ መኾናችሁም ፡ እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ ውርደትንና ፡ ጥቃትን ፡ ጠልታችሁ ፡ አባቶቻችን ፡ ደማቸውን ፡ አፍሰው ፡ አጥንታቸውን ፡ ከስክሰው ፡ ያወረሱንን ፡ መንግሥታችንንና ፡ ነፃነታችንን ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ከማየት ፡ መሞት ፡ ይሻለናል ፡ ብላችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፤ ኹሉ ፡ በግዛትም ፡ ቢኖሩ ፡ በመገዛትም ፤ ቢኖሩ ፡ በመጨረሻው ፡ ኹሉንም ፡ አንድ ፡ ሞት ፡ እንዲገናኛቸው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ኹሉም ፡ እንዳልነበሩ ፡ እንዲኾኑ ። ይልቁንም ፡ እንደ ፡ አልዓዛርና ፡ እንደ ፡ ነዌ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ከኖሩ ፡ ሰዎች ፤ በመከራ ፡ በመገዛት ፡ የኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ የተሻለ ፡ ኑሮ ፡ ማግኘታቸውን ፡ አጥታችሁት ፡ አደለም ።

በመንፈሳዊም ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ በማወቅና ፡ በሃይማኖት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ብልጫና ፡ ቅድሚያ ፡ ያላችሁ ፡ እናንተን ፡ አዲስ ፡ ቅኝዎች ፡ አዲስ ፡ አማኞች ፡ ላድርጋችሁ ፡ ብሎ ፡ መቃጣቱ ፡ ያንኑም ፡ ደፍሮ ፡ ሳያፍር ፡ ሳይፈራ ፡ ጽፎ ፡ በእጃችሁ ፡ መስጠቱ ፡ የውርደት ፡ ውርደት ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ መኾኑን ፡ አሳስባችኋለሁ ።

ይህነንም ፡ ሳሳስባችሁ ፡ ይህ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ለጻፈላችሁ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ ሰጥቼ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ አይደለምና ፡ ይህን ፡ የጻፍኩላችሁን ፡ መልስ ፡ በጥንቃቄ ፡ ባለመሰልቸት ፡ እንድትመለከቱልኝና ፡ ሬሳነቱን ፡ እንድትረዱት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደራ ፡ ጥየባችኋለሁ ።

ይህንም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደራ ፡ ስጥልባችሁ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በኦርቶዶክሳዊ ፡ ተዋህዶ ፡ ሃይማኖቷ ፡ በጥንታዊ ፡ ሕጓና ፡ ሥርዓቷ ፡ አጽንተው ፡ ሊጠብቋት ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ በተቀቡ ፡ ጊዜ ፡ ከቅዱሳን ፡ ነገሥታት ፡ ከአብርሀና ፡ ወአጽብሐ ፡ ጀምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ የእስክንድርያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ተዋህዶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ የወሰነችውን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ በለማፍረስ ፡ እጠብቃታለሁ ፡ ብለው ፡ የሰጡት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እስከፍጻሜ የማይፈርስባቸው ፤ አስተዋዩ ፤ ጠንቃቃው ፡ መሪያችን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የጎደለባትን ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንድታሟሉላት ፡ በማይወሰን ፡ ልግስናቸው ፡ በያይነቱ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ከፍተው ፡ በሀገራችሁም ፡ ውስጥ ፡ ቢኾን ፤ ለትምርት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሀገር ፡ ስትላኩም ፡ ቢኾን ፡ የሀገራችሁን ፡ ሃይማኖት ፡ ጠብቁ ፡ ሀገራችን ፡ በሃይማኖት ፡ ከጥንት ፡ ጀምራ ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ስለኾነች ፡ መዋስ ፡ አትፈልግም ፡ የሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ የሚታይ ፡ አደለምና ፡ አጥብቃችሁ ፡ አስቡበት ፡ እያሉ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያስጠነቅቋችሁን ፡ ኹሉ ፡ እንዳትረሱት ፡ ከማሳሰብ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

ምን ፡ አልባት ፡ ይህን ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚዘነጋ ፡ ወጣት ፡ ቢገኝ ፡ አባት ፡ ቀፎ ፡ ቢያበጅ ፡ ልጅ ፡ ማንጉዛ ፡ (ቀፎ ፡ ደፊ ፡) ገዛ ፡ የሚባለው ፡ ያባቶቻችን ፡ ተረት ፡ እንደሚደርስበት ፡ አይጠረጠርም ።

በሉ ፡ ያባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ ለእኔም ፡ እውነተኛውን ፡ ቀጥተኛውን ፡ መልስ ፡ ይግለጽልኝ ፡ ለናንተም ፡ ሰሚ ፡ ጆሮ ፡ አስተዋይ ፡ አእምሮ ፡ ይስጣችሁ ።

አሜን ።

---

## መግቢያ ።

መግቢያ ፡ ማለት ፡ መሪ ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ። አንዱን ፡ ሰው ፡ ወደማያውቀው ፡ ሀገር ፡ ልክ ፡ የሚሰድ ፡ ሰው ፤ ቢያገኝ ፡ አንድ ፡ መሪ ፡ ጨምሮ ፤ ቢያጣ ፡ የመንገዱን ፡ አኳኋንና ፡ የሀገሩን ፡ አቀማመጥ ፡ የሚደርስበትንም ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ ምልክት ፡ አስጠንቶ ፤ ወይም ፡ የዚህኑ ፡ ካርታ ፡ ሰጥቶ ፡ ቢሰደው ፡ መላክተኛው ፡ ያለችግር ፡ ካሰበው ፡ ቦታ ፡ ይደርሳል ። እንግዲ ፡ ድርሰት ፡ የሚጽፍም ፡ ሰው ፡ ተመልካቾች ፡ ከመካከሉ ፡ ሲገቡ ፡ የመጽሐፉን ፡ አኳኋን ፡ ለማወቅ ፡ እንዳይቸገሩ ፡ መግቢያ ፡ በተባለው ፡ አርእስት ፡ ላይ ፡ የመጽሐፉን ፡ ጠባይ ፡ ያጻጻፉን ፡ ድርጅት ፡ ብቻ ፡ ዘርዝሮ ፡ ማሳየት ፡ ይገባል ። እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ተመልካቾች ፡ ያላንድ ፡ ችግር ፡ የመጽሐፉን ፡ ጠባይ ፡ ሊረዱት ፡ ይችላሉ ።

እኔም ፡ ይህን ፡ በመገንዘብ ፡ ተመልካቾች ፡ ያላንድ ፡ ችግር ፡ ከግቡ ፡ እንዲደርሱልኝ ፡ በማለት ፡ የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ያጻጻፉን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ ፡ መግቢያ ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ዘርዝሬ ፡ አሳያለሁ ።

፩ኛ ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አካሔድና ፡ ጠቅላላ ፡ ድርጅቱ ፡ የፊተኛው ፡ ደራሲ ፡ አቶ ፡ ዘመንፈስ . . . ለጻፈው ፡ ጽሑፍ ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፤ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ እያለ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፪ኛ ፡ ተመልካቾች ፡ መልሱ ፡ ልክ ፡ ነው ፤ ወይም ፡ ልክ ፡ አደለም ፡ ብሎ ፡ ለማመዛዘን ፡ እንዲመቻቸው ፡ አስቀድሜ ፡ ያቶ ፡ ዘመንፈስ ፡ . . ን ፡ ጽሑፍ ፡ በምሉ ፡ ጽፌ ፡ የኔን ፡ መልስ ፡ አስከትላለሁ ።

፫ኛ ፡ ከሐሳቡ ፡ ጋራ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ያህል ፡ የተራራቁ ፡ ሲኾኑ ፡ ለማስመሰል ፡ በምዕራፍና ፡ በቍጥር ፡ ብቻ ፡ የደረደራቸውን ፡ ጥቅሶች ፡ ፍሬ ፡ ነገራቸውን ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌ ፡ መልስ ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ።

፬ኛ ፡ ያቶ ፡ ዘመንፈስ . . . ንግግርና ፡ መልሱ ፡ ባንድ ፡ መልክ ፡ የታተመ ፡ እንደኾነ ፡ ንባቡ ፡ ተሰባጥሮ ፡ ተመልካቾችን ፡ እንዳያስቸግር ፡ በማለት ፡ የፊተኛውን ፡ ድርሰት ፡ በረቂቅ ፤ መልሱን ፡ በጉልህ ፡ አሳትሜዋለሁ ።

፭ኛ ፡ የፊተኛው ፡ ደራሲ ፡ ለመጽሐፉ ፡ ከምዕራፍ ፡ በቀር ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ስላልሰጠው ፡ ቍጥር ፡ የለሽ ፡ በመኾኑ ፡ ለመመልከት ፤ ወይም ፡ ከውስጡ ፡ ለመጥቀስ ፡ አይመችም ፡ ነበረ ። እኔ ፡ ግን ፡ ደራሲው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በሚለው ፡ አርእስት ፡ ብዙ ፡ ጸያፍና ፡ ጉድለት ፡ እንደምታገኝበት ፡ እተማመናለሁና ፡ የጎደለውን ፡ መልተህ ፡ የጠመመውን ፡ አቅንተህ ፡ የደፈረሰውንም ፡ ቃላት ፡ አጣርተህ ፡ ታነብልኝ ፡ ዘንድ ፡ በማክበር ፡ አሳስብሀለሁ ፡ ብሎ ፡ አደራ ፡ ስለጣለብኝና ፡ ለያንዳንዱ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ቍጥር ፡ ስለሰጠሁት ፡ ለመመልከትም ፡ ለመጥቀስም ፡ ቢኾን ፡ የተሻለ ፡ መልክ ፡ አግኝቷል ።

፮ኛ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ የምሰጣቸው ፡ መልሶች ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ኾነው ፡ ቍጥር ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ሲኾን ፡ በሀ ፡ በለ ፡ በሐ ፡ ወይም ፡ ቍጥሮች ፡ በጕልህ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ፊደል ፡ ታትመው ፡ ይገኛሉ ። የፊተኛውንም ፡ ድርሰት ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የሚገልጹ ፡ ቍጥሮች ፡ ከኔ ፡ የተገኙ ፡ እንደመኾናቸው ፡ በጉልህ ፡ ታትመዋል ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ፪ዓይነት ፡ ቍጥሮች ፡ መገኘታቸው ፡ ነውና፡ ተከታዩ ፡ ረቂቅ ፡ ፊደል ፡ ሲኾን ፡ የፊተኛውን ፡ ድርሰት ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፤ ተከታዩ፡ ጉልህ ፡ ፊደል ፡ ሲኾን፡ የመልሱን፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የሚቈጥሩ ፡ መኾናቸውን ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ፡ ነው ።

፯ኛ ፡ የመቅድምንና ፡ የመግቢያን ፡ አጻጻፍ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደገለጽኩት ፡ መኾኑን ፡ ደራሲው ፡ ሳይረዳው ፡ ቀርቶ ፡ መቅድም ፤ መግቢያ ፡ መባልን ፡ ስሙን ፡ ብቻ ፡ አስጨብጧቸዋል ፡ እንጂ ከስድብ ፡ በቀር ፡ የሚገባ ቸውን ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ አላገኙም ።

እኔም ፡ በጠቅላላው ፡ ፪ቱም ፡ አርእስቶች ፡ የተበላሹ ፡ በመኾናቸው ፡ ላር ማቸው ፡ ስላልቻልኩ ፡ ደራሲው ፡ እንደጻፋቸው ፡ መልስ ፡ ሰጥቼባቸዋለሁ ። አን ባቢዎች ፡ ግን ፡ ምንም ፡ በሌሎችም ፡ አናቅጽ ፡ ይህን ፡ የመሰሰለ ፡ ጉድለት ፡ ባይ ታጣ ፡ ይልቁንም ፡ መቅድምና ፡ መግቢያ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፋቸውን ፡ ያልያዙ ፤ ያላገኙ፡ መኾናቸውን ፤ እንዲገነዘቡት ፡ አሳስባቸዋለሁ ።

፰ኛ ፡ አቶ ፡ ዘመንፈስ ፡ አሥራው ፡ መጻሕፍትን ፡ እንኳኖክን ፡ የብሉይ ፡ አዋልድ ፡ አፖክሪፌ ፡ ስለኾኑ ፡ ለምስክርነት ፡ አይበቁም ፡ ብሎ ፡ ሲነቅፍ ኢትዮ ጵያ ፡ ለምስክርነት ፡ ከተቀበለቻቸው ፡ ከመጻሕፍተ ፡ ሊቃውንት ፡ አልፎ ፡ ለጸሎ ትና ፡ ለታሪክ ፡ ማወቅ ፤ ለኃዘንና ፡ ለጨዋታ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የምታደርጋቸውን ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ በቂ ፡ ምስክሮች ፡ እያደረገ ፡ ጠቅሱዋቸዋል ።

እኒኽውም የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) አፖክሪፌ ፡ ብሎ ፡ ከነቀፋቸው ፡

ጥበበ ፡ ሰሎሞን ፡
ተግሣጽ ፡ ሰሎሞን ፡
ሲራክ ፡

(ለ) ከጸሎት ፡ መጻሕፍት ፡

ግንዘት ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎት ፡
መልክዐ ፡ ማርያም ፡
ድጓና ፡ ጾመ ፡ ድጓ ፡ አዋልድ ሳይቀር ፡

(ሐ) ከሊቃውንት ፡

ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡
ሃይማኖተ ፡ አበው ፡
ቅዳሴ ፡

(መ) ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርሰቶች ፡

መጽሔት ፡
ቅኔዎች ፡
ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡
ወዳጄ ፡ ልቤ ፡ የብላቴን ፡ ጌታ፡ኅሩይ ፡
ምክሐ ፡ ምእመናን ፡ ያለቃ ፡ ታዬ ፡
ያዝማሪዎች ፡ ግጥም ፡
ያልቃሾች ፡ ግጥም ፡ ናቸው ።

በዚህ ፡ አያያዝ ፡ ሌሎችን ፡ መጻሕፍት ፡ አለመጥቀሱ ፡ ባይደርስባቸውና ፡ ባያውቃቸው ፡ እንጂ ፡ ነቀፋዋቸው ፡ አይደለም ፡ ቢባል ፡ የሚያሳፍር ፡ ነገር ፡ የለበ ትም ። እኔም ፡ እንዲሁ ፡ ለተጠየቁት ፡ ጥያቄ ፡ ተመሳሳዩን ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝቤ ፡ እንደሱው ፡ በያይነቱ ፡ መልስ ፡ ጽፌለታለሁና ፡ ከስሕ ተት ፡ እንዳትቈጥሩብኝ ፡ አሳስባችኋለሁ ።

## ጸ ሎ ት ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ፡ እንዘ ፡ አአምን ፤ ወእትመኀፀን ፡ እክህደከ ፡ ሰይጣን ፡ በቅድመ ፡ ዛቲ ፡ እምየ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

በልዩ ፡ ሦስትነት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚኾን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አምኜና ፡ ተማጽኜ ፡ በዚች ፡ በናቴ ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፊት ፡ ሰይጣን ፤ ክጀሃለሁ ።

እንተ ፡ ይእቲ ፡ ስምዕየ ፡ ማርያም ፡ ጽዮን ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዚህም ፡ ምስክሬ ፡ ለዓለሙ ፡ ዓለም ፡ ለሚኾን ፡ ለጌታ ፡ እናት ፡ የኾነች ፡ ማርያም ፡ ናት ።

፩ ፡ ጸሎት ፡ ዘእምአረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ድር ፡ ፩ ።

ከአረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ የተገኘ ፡ ጸሎት ፡ ፩ኛ ፡ ድርሳን ።

አክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ክሥት ፡ አዕይንተ ፡ አልባቢነ ፡ ወአብርህ ፡ አዕይንተ ፡ ሕሊናነ ፡ ከመ ፡ ንለቡ ፡ አንብቦ ፡ መጻሕፍቲከ ፡ ቅዱሳት ።

የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ሕያው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍቶችህን ፡ ስንመለከት ፡ አስተዋዮች ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ ዐይነ ፡ ልቡ ናችንን ፡ ግለጽልን ፡ ዐይነ ፡ ነፍሳችንን ፡ አብራልን ።

አሜን ፡ ይኹንልን ፡ ይደረግልን ።

አንተ ፡ በኃይልከ ፡ ዘታነሥእሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ጠባይዓት ፡ ነባብያን ፡ በበመዓ ርጊሆሙ ፡ ወህላዌሆሙ ፡ እንተ ፡ ኢትማስን ፡ ወእንተ ፤ እምኀቤከ ፡ ተሠርዐት ።

አቤቱ ፡ በከሀሊነትህ ፡ አእኳትያን ፡ መላእክትን ፡ በየመዓርጋቸው ፡ ካንተ ፡ በተ ገኘች ፤ በሕማም ፡ በሞት ፡ በማትለወጥ ፡ ባሕርያቸው ፤ ለቅዳሴ ፡ የምታነቃቃቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ወእምኔከ ፡ ያዔንዉ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለተድላሆሙ ፤ ወብከ ፡ ይረክቡ ፡ ኃይለ ፡ ለጽንዖሙ ፡ ሀበነ ፡ ለነኒ ፡ ኃይለ ፡ ለድኩማን ፡ ወለኅጡኣነ ፡ አእምሮ ፡ ከመ ፡ ንጽሐፍ ።

ተድላ ፡ ነፍስ ፡ የሚኾናቸው ፡ መዓዛ ፡ ጸጋን ፤ ጽንዐ ፡ ነፍስ ፡ የሚኾናቸው ፡ ኃይልን ፡ የሚያገኙ ፡ ካንተ ፡ ነውና ፤ ድኩማን ፡ ለምንኾን ፤ እውቀት ፡ ለሌለን ፡ ለእኛም ፡ ለዚህ ፡ ለተሳዳቢ ፡ መልስ ፡ እንጽፍለት ፡ ዘንድ ፡ ኃይለ ፡ ቃልን ፡ ግለጽልን ።

ወጸግወነ ፡ መንፈሰከ ፡ ከመ ፡ ንቅልም ፡ በጸሎታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ንጽሕት ፡ ወስብሕት ፡ ወድንግልት ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ማርያም ፡ ወበጸሎተ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ አሥመሩ ፡ ፈቃደከ ።

ክህደቱን ፤ ስሕተቱን ፤ ድፍረቱን ፤ ሐሰቱን ፤ በጽሕፈት ፡ እንገልጥበት ፡ ዘንድ ፡ ኹልጊዜ ፡ ንጽሕት ፡ ስብሕት ፡ በምትኾን ፤ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በእመቤታችን፡

www.ethiopianorthodox.org

በድንግል ፡ ማርያም ፡ አማላጅነት ፤ ፈቃድህን ፡ ፈጽመው ፡ ደስ ፡ በሰኙህ ፡ በቅዱሳ ንም ፡ ኹሉ ፡ አማላጅነት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳድርብን ።

አሜን ፡ ይኹንልን ፡ ይደረግልን ።

ክልእ ፡ ጸሎት ፡ ዘእምአረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ በእንተ ፡ ሰይጣን ፡ ጸሪፍ ፡ ድር ፡ ፫ ።

ስድብን ፡ ስለሚያስተምር ፡ ስለ ፡ ሰይጣን ፡ ጸሪፍ ፡ የሚጸለይ ፡ ከአረጋዊ ፡ መን ፈሳዊ ፡ የተገኘ ፡ ኹለተኛ ፡ ጸሎት ፡ (፫ኛ ፡ ድርሳን ።)

አገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ወመሠረተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ዘበጥበብከ ፤ ፈጠርከ ፡ ኵሎ ፡ ለሕይወተ ፡ ዚአነ ፤ ወለምሥጢራቲከ ፡ ረሰይከነ ፡ ሐዲሳነ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ውሉደ ፡ ለእግዚአብሔርናከ ፤ ቅድስት ፡ ይእቲ ፡ ቅድሳቲከ ፡ ፀመቅደስ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ዘበ ስብሐቲከ ፡ ነባቢት ።

ኻያ ፡ ኹለቱን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ የፈጠርክ ፤ የዓለም ፡ ኹሉ ፡ መገኛ ፤ ለእኛ ፡ ሕይወት ፡ ሊኾን ፡ በባሕርይ ፡ ጥበብህ ፡ ኹሉን ፡ የፈጠርክ ፤ እግዚአብሔርነትህን ፡ የምናገለግል ፡ ልጆች ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ በጥምቀት ፤ በሥጋው ፡ በደሙ ፡ እንድን ታደስ ፡ ያደረግኸን ፡ አቤቱ ፡ ከከበሩ ፡ የከበረች ፡ ከተለዩ ፡ የተለየች ፡ በምትኾን ፡ በመቅደስህ ፡ በመስጋኞችህ ፡ በመላእክት ፤ በደቂቀ ፡ አዳም ፡ አንደበት ፡ የምትመ ሰገናት ፡ ምስጋና ፡ ክብርት ፡ ንጽሕት ፡ ልዩ ፡ ናት ።

አእግዚኦ ፡ በኃይልከ ፡ ዐቢይ ፡ ዘይመውዕ ፡ ኵሎ ፡ ዕፁ ፡ አፉሁ ፡ ለፀማዒ ፡ ከመ ፡ ኢይንብብ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሰ ፡ አግብርቲከ ፡ ሐሜተ ፡ ወፀሪፈ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ላዕሌከ ፡ ወላዕለ ፡ ምሥጢራቲከ ፡ ወላዕለ ፡ አግብርቲከኒ ።

አቤቱ ፡ ሰይጣን ፡ ጸሪፍ ፡ አድሮበት ፡ አንተን ፡ ከባሕርይ ፡ አባትህ ፡ ከአብ ፤ ከባሕርይ ፡ ሕይወትህ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለይቶ ፤ አሳንሶ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስ ቀድሞ ፡ አእግዚኦ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ ለእስራኤል ፡ ይጸልይ ፡ ያማልድ ፡ ነበረ ። ዛሬም ፡ ከትንሣኤና ፡ ከዕርገት ፡ በኋላ ፡ ሲጸልይ ፡ ሲያማልድ ፡ ይኖራል ፡ እያለ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ የማይገባ ፡ ክህደትን ፡ የሚናገር ።

(ወላዕለ ፡ አግብርቲከ ፡) በባሮችህ ፡ በቅዱሳን ፡ መላእክትም ፡ ላይ ፡ አእግዚኦ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያሉ ፡ አያማልዱም ፡ ብሎ ። (ወላዕለ ፡ ምሥጢራቲከ ፡) በሥ ጋህ ፡ በደምህም ፡ ላይ ፡ ምሳሌ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተለውጦ ፡ ፍጹም ፡ ሥጋ ፡ ፍጹም ፡ ደም ፡ አይኾንም ፡ አማናዊ ፡ አደለም ፡ ብሎ ። (ወላዕለ ፡ አግብር ቲከኒ ፡) ቅዱሳን ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ ደናግል ፡ መነኰሳትም ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፤ አስ ተምረው ፤ አጥምቀው ፡ አቍርበው ፡ ሀብት ፡ ሥርየት ፡ ልጅነት ፡ አስጥተው ።

ካረቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሰውነታቸው ፡ አነሳሥቷቸው ፡ ኃጢአት ፡ የሠሩ ትንም ፡ በንስሐ ፡ አማልደው ።

በዐፀደ ፡ ነፍስም ፡ ዘአስተየ ፡ ጽዋዐ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ፡ በስመ ፡ ረድእየ ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ኢየኀጕል ፡ ዐስቦ ። ዘተወክፈ ፡ ጻድቀ በስመ ፡ ጻድቅ ፡ ዐስበ ፡ ጻድቅ ፡ ይነሥእ ፡ ባልከው ፡ መሠረት ፡ ስለወላዲተ ፡ አምላክ ፤ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፤ ስለቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ስለ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብለው ፡ ለርሁባን ፡ ያበሉ ፡ ለጽሙዓን ፡ ያጠጡ ፡ ለዕሩቃን ፡ ያለበሱ ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ፡ ቅዱ



ሳንም ፡ አያማልዷቸውም ፡ እያለ ፡ ሐሜትን ፡ ስድብን ፡ የሚናገር ፡ ይህነን ፡ (አፉን ፡ ዝጋው ፡ ማለት ፡) ምላሽ ፡ አሳጣው ።

ወአዕርግ ፡ ሕሊናሁ ፡ ኀበ ፡ ሀገርከ ፡ ሀገረ ፡ አእምሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንተ ፡ ኢይ ነፍሐ ፡ በውስቴታ ፡ መናፍስተ ፡ ኑፋቄ ።

ሕሊናውንም ፡ በውሥጧ ፡ ክህደትን ፡ ስሕተትን ፡ የሚያስተምሩ ፡ መናፍቃን ፡ ወደማይሾሙባት ፡ ወደማይሠለጥኑባት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ መልስ ።

አሜን ፡ ይኹን ፡ ይደረግ ።

---

፩ኛ ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ።

ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ እውነትን ፡ ከሐሰት ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ ለሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ተጻፈ ፡ ለምትለው ።

ለሰው ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ራሱን ፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ፡ ራሱንም ፡ ማወቅ ፡ ማለት ፡ አላዋቂነቱን ፡ ማወቅ ፡ ማለት ፡ ነው ። አላዋቂነትንም ፡ አለማወቅ ፡ ያላዋቂ ነት ፡ የድንቁርና ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ፤ ራስን ፡ ከለማወቅ ፡ በታች ፡ የሚገኝ ፡ ሌላ ፡ ድን ቁርና ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ አንተ ፡ ራስህን ፡ ባለማወቅህ ፡ ተምረህ ፡ በቂ ፡ ትምህርት ፡ ሳይኖርህ ፤ ወይንም ፡ በትሩፋት ፡ ደክመህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የማስተማር ፡ ሀብት ፡ ሳይሰጥህ ፡ በድፍረት ፡ አስተምረኝ ፡ ያለህ ፡ ሳይኖር ፡ ላስተምራችሁ ፡ ማለትህ ፤ አኃው ፡ ፊልክስዩስን ፡ ጠይቀውት ፡ የተረገመላቸውን ፡ ነገር ፡ ይመስላል ።

ይቤሉ ፡ አኃው ፡ ይቤ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ እስመ ፡ ዘይሜህር ፡ ቢጾ ፡ እምቅ ድመ ፡ ይስአሎ ፡ መዐርይ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ ዘይዛለፎ ።

አኃው ፡ ፊልክስዩስን ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ አስተምረኝ ፡ ሳይለው ፡ ወንድሙን ፡ ላስተምርህ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ከተሰዳቢ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ልዩነት ፡ የለ ውም ፡ ብሏል ፡ ምን ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፡ ዘኢኮነ ፡ ራእሰ ፡ ወኢተረሰየ ፡ መምህረ ፤ ወፍጹመኒ ፡ ዘኢያጥረየ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኢእመዓርጊሁ ፡ ወኢእምአእምሮቱ ፡ ወኢእ ምግባራቲሁ ፡ ወኢእመክራቲሁ ፡ በውስተ ፡ ልህቅና ፡ ዓመታቲሁ ፡ ወይደፍር ፡ ለምህሮ ፡ ኢይደልመሮ ፡ ለትምህርቱ ፡ ግብረ ፡ ጸጋ ።

ትምሮ ፡ ለማስተማር ፡ ሳይሾም ፤ ይልቁንም ፡ የትምህርትን ፡ ዘዴ ፡ ሳያውቅ ፤ ከመዓርጉ ፡ ማዓርግ ፡ ከእውቀቱ ፡ እውቀት ፡ ከትሩፋቱ ፡ ትሩፋት ፡ ሳይኖረው ፤ ወይም ፡ እስኪያረጅ ፡ ድረስ ፡ በመከራ ፡ ተፈትኖ ፡ ጣዕመ ፡ ጸጋ ፡ ሳይቀምስ ፡ ላስተምር ፡ በሚል ፡ ሰው ፡ ትምርት ፤ ጸጋ ፡ አይገኝበትም ።

ወኢይረብህ ፡ ተመሀሪኒ ፡ እምኔሁ ።

ከሱ ፡ የሚማርም ፡ ሰው ፡ ረብ ፡ ጥቅም ፡ አያገኝም ።

ወዝኬ ፡ ዘይሜህር ፡ ዘእንበለ ፡ ይኅሥሡ ፡ እምኔሁ ፡ ወዘእንበለ ፡ ምክንያተ ፡ ድልወት ፡ ለበቍዔተ ፡ ሰማዕያን ፡ ውእቱኬ ፡ አብድ ፡ ወአኮ ፡ ጠቢብ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸውም ፡ አስተምረን ፤ ሳይሉት ፡ ሰማዕያኑን ፡ የሚጠቅምበት ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ ላስተምራችሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አላዋቂ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አዋቂ ፡ አይባልምና ፡ አስተምረን ፡ ሳይሉት ፡ ላስተምራችሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ከተሳዳቢ ፡ ይቆጠራል ፡ ብሎ ፡ ተርጉሞላቸዋል ። ይህም ፡ ጽሑፍህ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጥቅም ፡ የማይገኝበት ፡ ስድብን ፡ የሚያስተምር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነትን ፡ ከሐሰት ፡ ለይቶ ፡ የሚያሳይ ፡ አይደለም ።

እንዲያውም ፡ በጠቅላላው ፡ ጸጋ ፡ አይገኝበትም ፡ የተባለ ፡ ይህ ፡ አንተ ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ ብለህ ፡ ያቀረብከው ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አላዋቂ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አዋቂ ፡ አይባልም ፡ የተባልክ ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ ነህ ፡ ብል ፡ የሚያሳፍረኝ ፡ ነገር ፡ አደለም ፡ አንተም ፡ ሐሰት ፡ ብለህ ፡ ልትቃወም ፡ አይገባህም ።

## ፪ተኛ ፡ አዋጅ ።

፩ ወካልአስ ፡ መሠረተ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ሣርሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተሣረረ ፡ ወመሠረቱሂ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ ፩፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፩። ስለምትለው ።

ይህን ፡ ዐዋጅ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በጥንተ ፡ ስብከቱ ፡ ነግሮን ፡ በጥንቃቄ ፡ የምንጠብቀው ፡ ዐዋጅ ፡ መኾኑን ፡ ሳታውቅ ፡ ቀርተህ ፡ አዲስ ፡ አሰመስለህ ፡ በመናገርህ ፡ እናዝናለን ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የተቀበልነው ፡ በጥንቃቄ ፡ የምንጠብቀው ፡ የክርስቲያንነታችን ፡ መሠረት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መሠረትነት ፡ ወጥቶ ፡ ፍጡር ፡ የሚያመልክ ፡ ለጣዖት ፡ የሚሰግድ ፡ የለም ።

፪ አንተ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ልልክህ ፡ ነኝና ፡ ተነሥተህ ፡ ወገብህን ፡ ታጠቅ ፡ በፊታቸውም ፡ እንዳላሳፍርህ ፡ ብላቴና ፡ ነኝ ፡ ብለህ ፡ አትፈር ፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ ይህንን ፡ ሕዝብ ፡ ካንተ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ እንጨት ፡ ነገሬንም ፡ ባአፍህ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ አደርገዋለሁና ፡ ትበላውማለች ፡ ኤር ፡ ፩ ፬—፲፯ ፡ አለኝ ።

በማለትህ ፡ ኤርምያስ ፡ እንደ ኾንክ ፡ ትናገራለህ ።

፫ ሕዝ ፡ ፫፩—፳፩ ፡ የጠቀስከው ፡ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ይህን ፡ መጣፍ ፡ ብላ ፡ አለኝ ፡ አፌን ፡ ከፈትሁ ፡ ያንንም ፡ መጣፍ ፡ አበላኝ ። በላሁት ፡ ባፌ ፡ እንደማር ፡ ጣፋጭ ፡ ኾነ ። መንፈስ ፡ አንግኝ ፡ ወሰደኝ ፡ አገዤ ፡ ኼድኩ ፡ የእግዚኦብሔር ፡ ነገር ፡ ወደእኔ ፡ መጣ ፡ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ለእስራኤል ፡ ወገን ፡ ጠባቂ ፡ አድርጌሃለሁ ፡ ካፌ ፡ ነገር ፡ ትስማ ፡ ዘንድ ፤ እኔንም ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ ትመክራቸው ፡ ዘንድ ፡ አለኝ ፡ ይላል ።

በዚህም ፡ አነጋገርህ ፡ ሕዝቅኤል ፡ እንደ ኾንክ ፡ ትናገራለህ ።

፬ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳፮ ፡ ፲፬—፲፰ ፡ የጠቀስከው ።

በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ሳውል ፡ ሳውል ፡ ለምን ፡ ታሳድደኛለህ ፡ በችንካር ፡ ላይ ፡ ብትቆም ፡ ላንተ ፡ ይብስሃል ፡ አለኝ ፡ ይላል ። በዚህም ፡ አጠቃቀስህ ፡ አንተ ፡ ሳውል ፡ እንደ ኾንክ ፡ ትናገራለህ ።

ሀ) በዚህ ፡ አነጋገርህስ ፡ የዋህ ፡ ብእሲ ፡ ኵሎ ፡ ዘነገርዎ ፡ የአምን ።

የዋህ ፡ ሰው ፤ ኹሉ ፡ እውነት ፡ ይመስለዋል ፡ የነገሩትን ፡ ኹሉ ፡ ያምናል ፡ ተብሎ ፡ እንደተነገረ ፡ ባንተና ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ የማያውቁትን ፡ ሰዎች ፡ አታልበት ፡ እንጂ ፡ እኛንስ ፡ ኤርምያስ ፡ በም ፡ ፳፫ ፡ በቍ ፡ ፳፭—፴፫ ፡ እኒህን ፡



ነቢያትን ፡ እኔ ፡ አላክኋቸውም ፡ እርሳቸው ፡ ይሮጣሉ ፡ እንጂ ፤ እኔ ፡ አልተናገርኋቸውም ፡ እርሳቸው ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ። እነሆ ፡ እኔ ፡ በሐሰታቸውና ፡ በድፍረታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ላከን ፡ እያሉ ፡ በሕዝቤ ፡ በሚጫወቱበት ፡ በነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ እኔ ፡ አላክኋቸውም ፡ አላዘዝኋቸውም ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እነዚህ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ አይረቡም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ።

ለ) ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ እንዲሁ ፡ ሲያስጠነቅቀን ፡ በቆሮ ፡ በ፪ተኛ ፡ ክታቡ ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ በቍ ፡ ፲፫ ፡ እስመ ፡ ሀለዉ ፡ ሐሳውያን ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ፡ እለ ፡ ይትሜየኑ ፡ ወይትሜሰሉ ፡ ሐዋርያተ ፡ ክርስቶስ ። ወዝኒ ፡ አኮ ፡ ለአንክሮ ፡ እስመ ፡ ለሊሁ ፡ ሰይጣን ፡ ይትሜሰል ፡ ከመ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ።

ሀመስን ፡ እየሠሩ ፡ የሚተናኰሉ ፡ የክርስቶስ ፡ መላክተኞች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሐሰተኞች ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤ ይህም ፡ አያስደንቅም ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ሰይጣን ፡ ቅሉ ፡ እኔ ፡ የብርሃን ፡ መላክ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ በመልአከ ፡ ብርሃን ፡ ራሱን ፡ ይመስላልና ፡ ብሎ ።

ሐ) ለጢሞቴዎስ ፡ በጻፈለት ፡ በ፪ተኛ ፡ ክታቡም ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፩—፮ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ክፉ ፡ ጊዜ ፡ እንዲኾን ፡ ዕወቅ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፡ የሚወዱ ፡ ገንዘብም ፡ የሚወዱ ፡ ትምክህተኞች ፡ ዕቡዮች ፡ ተሳዳቦች ፤ ላባቶቻቸው ፡ ለቅዱሳን ፡ ለመምህራን ፡ የማይታዘዙ ፡ የማያመሰግኑ ፡ ያልተቀደሱ ፤ ፍቅር ፡ የሌላቸው ፡ መሐላ ፡ የሚያፈርሱ ፡ ምለው ፡ የሚከዱ ፡ ሐሜተኞች ፡ ራሳቸውን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ የማይጠብቁ ፡ ደስ ፡ የማያሰኙ ፡ መልካምን ፡ የማይወዱ ፡ በደለኞች ፤ ችኩሎች ፤ ትቢተኞች ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከማገልገል ፡ ይልቅ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ማድረግን ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ይነሣሉ ። በኒህም ፡ የአምልኮት ፤ መልክ ፡ ይታይባቸዋል ፤ የአምልኮትን ፡ ኃይል ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ የከዱ ፡ ናቸው ። እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሽሻቸው ፡ ራቃቸው ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቆናልና ፡ ካንተ ፡ ተንኰል ፡ አጥብቀን ፡ እንሸሻለን ፡ እንጂ ፡ አንቀበልህም ።

ተጋፍተህ ፡ እሳት ፡ ኸነህ ፡ ብትመጣም ፡ ዕንጨት ፡ ሳንኾን ፡ ወኃ ፡ ኾነን ፡ እንቆይሃለን ።

መ) እውነተኞችንና ፡ ደጋጎችን ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ ለይተን ፡ አንጠርጥረን ፡ እናውቃቸዋለንና ፡ ቀደስኩክ ፡ እምከርሥ ፡ እምከ ፡ የተባለ ፡ ኤርምያስንና ፡ ኤር ፡ ፩ ፡ ፭ ።

ረሰይኩከ ፡ ሰብአ ፡ ዓይን ፡ ለእስራኤል ፡ ከመ ፡ ትስማዕ ፡ ቃለ ፡ እምአፉየ ፡ ወትገሥጾሙ ፡ በቃልየ ፡ የተባለ ፡ ሕዝቅኤልንም ፡ ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

ንዋየ ፡ ኅሩየ ፡ ረሰይክዎ ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡ ይፁር ፡ ስምየ ፡ በቅድመ ፡ አሕዛብ ፡ የተባለ ፡ ጳውሎስንም ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ፡ እናከብራቸዋለን ፤ እንወዳቸዋለን ።

ሠ) ጸሎታችን ፡ ወደፊታችሁ ፡ ይድረስ ፡ ለእኛም ፡ ወደ ፡ አምላካችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩልን ፡ እንላቸዋለን ።

ረ) እነሱም ፡ ጸሎታችሁን ፡ በሱ ፡ ፊት ፡ እናቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደርሱ ፡ የላካችሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ እናንተ ፡ በሠራችሁት ፡ ኃጢአት ፡ ከደነገጣችሁበት ፤ እኔም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ባደረግሁብችሁ ፡ ክፋት ፡ እጠጠታለሁ ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ብትቀመጡ ፡ እሠራችኋ ለሁ ፡ አላፈርሳችሁም ፡ እተክላችኋለሁ ፡ አልነቅላችሁም ፡ አለ ፡ ብለው ፡ በረድ ኤት ፡ ይመልሱልናል ኤር ፡ ፵፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፲ ።

፩ ፡ ኤርምያስ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ። የጠቀስከው ።

እኔን ፡ ስለተውኝ ፡ ለእንግዶች ፡ አማልክት ፡ ዕጣን ፡ ዐጠኑ ፤ ለእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ሰገዱ ፡ ይላል ።

ኤርምያስ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የጻፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሱ ፡ አድሮ ፡ ሊመለክበት ፡ ሊሰገድበት ፡ በእጁ ፡ ቀርፆ ፡ ለሙሴ ፡ የሰጠው ፡ ታቦት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ለሰይጣን ፡ ማደሪያ ፡ ለጣዖት ፡ የሰገዱ ፡ እስራኤልን ፡ ሲዘልፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለታ ቦት ፡ እግዚአብሔር ፡ መስገዳቸውን ፡ ነቅፎ ፡ አይደለም ።

፯ ፡ ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፭—፰ ። የጠቀስከው ።

በሰው ፡ የሚታመን ፡ ሥጋ ፡ የለበስንም ፡ ክንዱ ፡ የሚያደርግ ፡ ልቡም ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ የሚመለስ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔርም ፡ እምነቱ ፡ የሚኾን ፡ ይላል ።

፯ ፡ ከዳዊትም ፡ መዝሙር ። የጠቀስከው ።

ማዳን ፡ በማይቻላቸው ፡ በመላእክትና ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ አትታመኑ ። በሰው ፡ በመላእክት ፡ ከመታመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መታመን ፡ ይበልጣል ። በሰው ፡ መታ መን ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ይላል ።

የእምነት ፡ ዐይነቱ ፡ ፪ ወገን ፡ ነው ።

ሀ) ከሰዎች ፡ ወገን ፡ አምላክ ፡ ሳይኾኑ ፡ አምላክ ፡ ነን ፡ እንመለክ ፡ እንሰገድ ፡ የሚሉ ፡ እንደነአርጤምስ ፤ እንደነዜውስ ፤ እንደነይሁዳ ፡ ዘገሊላ ፤ እንደነቴውዳስ ፡ ዘግብጽ ፤ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፴፮ ፡ ፴፰ ።

የነሱንም ፡ ቃል ፡ አምነው ፡ አምላክነትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አውጥተው ፡ እነሱን ፡ አምልከው ፡ የተጎዱ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ዘያመልክ ፡ በፍጡር ፡ ርጉም ፡ ውእቱ ፡ የተባሉ ፡ እኒህን ፡ የመሰሉ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

ለ) ደግሞ ፡ አምላክነትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አውጥተው ፡ ለፍጡር ፡ ሳይሰጡ ፡ ለጊዜው ፡ ጠላት ፡ ሲነሣባቸው ፡ ችግር ፡ ሲያገኛቸው ፡ ዘመን ፡ ያነሣቸውን ፡ ባለጸጎችና ፡ ጉልበታሞችን ፡ ርዱን ፡ ብለው ፡ የሚጠጉቸው ፤ እገሌ ፡ ሳለ ፡ ብለው ፡ የሚመኩባቸው ፡ አሉ ።

አካዝ ፤ ራዓሶንና ፡ ፋቁሄ ፡ ወልደ ፡ ሮሜልዩ ፡ በጠላትነት ፡ በተነሡበት ፡ ጊዜ ፡ ና ፡ ርዳኝ ፡ ሲል ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገንዘብ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አድርጎ ፡ ለቴልጌልቴልፌልሶር ፡ እንደላከ ፡ ነገ ፡ ካል ።

ዐሣም ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ለባዓስ ፡ ለእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ረዳብህ ፡ ቢሉት ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገንዘብ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አየ ርጎ ፤ ኀድ ግአ ፡ ኪዳነ ፡ ዘምስለ ፡ ባዓስ ፡ ወግበር ፡ ሰላመ ፡ ምስለ ፡ ገብርከ ፡ እንዳለ ፡ ዜና ፡ መዋ ፡ ፲፯ ፡ ፩—፱ ።

ይህ ፡ ግብራቸው ፡ ምንም ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ ባያሰኛቸው ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለተጠራጠሩ ፡ ተወቅሰውበታል ፤ ዐሣን ፡ ሐናኒ ፡ የተባለ ፡ ነቢይ ፡ ባምላ



ክህ ፡ መታመንህን ፡ ትተህ ፡ በሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ስለታመንክ ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ጭፍራ ፡ ከጅህ ፡ አመለጠ ። ኢትዮጵያውያንና ፡ ሊቢያውያን ፡ ይልቅ ፡ በፈረስና ፡ በሠረገላ ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ አልነበረምን ፤ በእግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ስለታመንህ ፡ በጅህ ፡ ጣላቸው ። ልቡ ፡ ወደርሱ ፡ ፍጹም ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአ ሔር ፡ ዐይኖች ፡ በምድሩ ፡ ኩሉ ፡ ይዘራሉና ። አሁንም ፡ በዚህ ፡ ስንፍና ፡ አደረግህ ፡ ስለዚህም ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ሰልፍ ፡ ይነሣብሃል ፡ ብሎታል ፡ ዜና ፡ መዋ ፡ ካል ፡ ፲፮ ፡ ፯—፲፫ ።

ዳዊትና ፡ ኤርምያስም ፡ እኒህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሲመክሩ ፡ ሲገሥጹ ፡ የሐናኒን ፡ ንግግር ፡ አስመስለው ፡ ተናግረውታል ፡ እንጂ ፡ የጻድቅ ፡ ሰው ፡ ጸሎት ፡ ግዳጅ ፡ ትፈጽማለች ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ።

ቅዱሳን ፡ ጻድቃንን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩልን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አማል ዱን ፡ ብለው ፡ በቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ የሚማጸኑትን ፡ ሰዎች ፡ ሲነቅፉ ፡ አልተናገሩትም ።

አንተ ፡ ግን ፡ መጻሕፍትን ፡ ከፍ ፡ ብለህ ፡ አርእስታቸውን ፡ ዝቅ ፡ ብለህ ኅዳጋቸውን ፡ ሳትመለከት ፡ አፍህ ፡ እንዳመጣ ፡ ልጥቀስ ፡ እያልክ ፡ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ ታማታቸዋለህ ፡ እንጂ ፡ ቅዱሳን ፡ አምላክ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ከመመለክ ፤ እኛም ፡ ፍጡራንን ፡ ከማምለክ ፡ ንጹሐን ፡ ነን ። በእኛ ፡ ውስጥ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ክዶ ፡ በፍጡር ፡ የሚያመልክ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ካለስ ፡ ርጉም ፡ ነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ የሚታመን ፡ ግን ፡ ቡሩክ ፡ ነው ።

፰ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ፡ የጠቀስከው ።

ወንድምህ ፡ ከሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢወጣ ፡ ብቻውን ፡ ይዘህ ፡ ምከረው ፡ ባይሰማህ ፡ ፪ ፡ ሰው ፡ ፫ ፡ ሰው ፡ ይዘህ ፡ ምከረው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በ፪ ፡ በ፫ ፡ ምስክ ሮች ይጸናልና ፤ እነዚህም ፡ መክረውት ፡ ባይመለስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንገራት ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከስሕተቱ ፡ ባይመለስ ፡ እንደ ፡ ዓረማዊ ፡ እንደ ፡ መጸብሐዊ ፡ ይኹን ፡ ይላል ።

ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ተፈጻሚነቱ ፡ ከአበው ፡ ሲያያዝ ፡ ከመጣው ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርሰቲያን ፡ ወጥቶ ፡ በተገኘ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነው ።

አንተም ፡ ከሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጥተህ ፡ ተገኝተህ ፡ ተፈጽሞብሃል ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ መፈጸሙንም ፡ በዚሁ ፡ በስድብ ፡ መጽሐፍህ ፡ በ፲፫ተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ከ፩-፰ ፡ በሚገኙት ፡ መሥመሮች ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ የሰውን ፡ ሥርዓትና ፡ የፍጡ ራን ፡ አማላጅነት ፡ ተባሕትዎና ፡ ምንኵስና ፡ የሚሉትም ፡ አንዘግዝጎ ፡ ስለጣለ ፡ ርሱና ፡ ተማሪዎቹ ፡ በሮማ ፡ ጳጳስ ፡ ዘንድ ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ ጽሉዓንና ፡ ውጉዛን ፡ ዕሡራን ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡ መስክረሃል ።

የኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባህልና ፡ ሥርዓትም ፡ ካንተ ፡ ባህልና ፡ ሥርዓት ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ መኾኑንም ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ አንዘግዝጎ ፡ ጣለው ፡ በማለትህ ፡ አረጋግጠሃል ።

ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምንም ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ በማለትና ፡ ባንድ ፡ አንድ ፡ ሥርዓትና ፡ ልማድ ፡ ልዩነት ፡ ቢኖራቸውም ፡ አንተ ፡ ተወግዘህ ፡ በተለየህበት ፡ ሥርዓት ፡ ቅዱሳንን ፡ በማክበር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ተባሕትዎንና ፡ ምንኵስናን ፡ በማፍቀር ፡ ጾም ፡ ሕግ ፡ መኾኑን ፡ በማመን ፡ ልዩነት ፡ ስለሌላቸው ፤ አንተን ፡ በማውገዝና ፡ በመለየት ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም ። ኹለቱ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ስላወገዙህም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በኹለት ፡ ምስክር ፡ ይጸናል ፡ የተባለው ፡ ተፈጽሞብሃል ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ።

እንግዲህ ፡ በንተ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመብህን ፡ ቅጣት ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ልታወረው ፡ ስትቃጣ ፡ አታፍርምን ? ተው ፤ በዚህ ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ ልታፍርበት ፡ እንጂ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ልትጠቅሰው ፡ አይገባህም ።

፱ ሉቃስ ፡ ፱ ፤ ፳፫ ፡ ፳፯ ። የጠቀስከው ።

እኔን ፡ ሊከተለኝ ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ ሰውነቱን ፡ ይጥላት ፤ ጨክኖ ፡ መስቀሉን ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ፤ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የወደደ ፡ ይጥላታል ፤ ነፍሱንም ፡ ስለኔ ፡ የጣለ ፡ ያድናታል ፤ ለሰው ፡ ነፍሱን ፡ ካጠፋ ፡ ዓለሙን ፡ ኹሉ ፡ ቢገዛ ፡ ቢነዳ ፡ ምን ፡ ይረባዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ። በዚህ ፡ በነገሬም ፡ ያፈረብኝም ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ባባቱ ፡ ጌትነት ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ያፍርበታል ፡ ይላል ።

ክርስቶስን ፡ መከተል ፡ በግብር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ ነውን ፡ አይደለም ። ክርስቶስን ፡ በግብር ፡ መምሰልም ፡ በሚከተለው ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ፡ መገኘት ፡ ነው ።

ሀ) ክርስቶስ ፡ በድንግልና ፡ እንደኖረ ፡ በድንግልና ፡ መኖር ።

ለ) ክርስቶስ ፡ በገዳም ፡ ፵መዓልት ፡ ፵ሌሊት ፡ እንደ ፡ ጾመ ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርጎ ፡ ጾመ ፡ ፵ንና ፡ ሌሎችንም ፡ አጽዋማት ፡ መጾም ።

ሐ) ለቈናጽልኒ ፡ ግበብ ፡ በሙ ፡ ወለአዕዋፈ ፡ ሰማይኒ ፡ ምጽላል ፡ በሙ ፡ ለወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያውሰ ፡ አልቦ ፡ ኀበ ፡ ያሰምክ ፡ ርእሶ ፡ እንዲል ፡ ማቴ ፡ ፰ ፡ ፳ ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርጎ ፡ ቤት ፡ ሳይሠሩ ፡ ዘር ፡ ሳይዘሩ ፡ በበረሃ ፡ ወድቆ ፡ ዳዋ ፡ ጥሶ ፡ ደንጊያ ፡ ተንተርሶ ፡ መኖር ።

መ) ወመነና ፡ ለኀፍረት ፡ እንዲል ፡ ክርስቶስ ፡ ጨርቅ ፡ አጠርቅሞ ፡ ግንድ ፡ ተሸክሞ ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ሲወቀስ ፡ ራቁቱን ፡ በመስቀል ፡ ሲሰቀል ፡ ኀፍረትን ፡ ከምንም ፡ እንዳልቈጠሩት ፡ አስበ ፤ የላመ ፡ የጣመ ፡ ልቅመስ ፤ የሞቀ ፡ የደመቀ ፡ ልልበስ ፡ ሳይሉ ፤ ዳባ ፡ ለብሶ ፤ ቋርፍ ፡ መኰረፊያ ፡ ኀርሶ ፤ ጥሬ ፡ በልቶ ፤ ውኃ ፡ ጠጥቶ ፤ መኖር ፡ ነው ። ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ባሕታውያንና ፡ መነኮሳት ፡ ክርስቶስን ፡ መስለው ፡ የሚሠሩት ፡ ብዙ ፡ የትሕትና ፡ ሥራ ፡ አለ ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፡ ባለ ፡ ዐቅሙ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ሲነሣ ፡ ሲወድቅ ፡ ይታያል ። አንተ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ኃጢአት ፡ ቈጥረህ ፡ አንዘግዝገህ ፡ ጥለኸዋል ። እንግዲህ ፡ ክርስቶስን ፡ መምሰል ፡ ከግብሩ ፡ ሳይገኙ ፡ መጻሕፍትን ፡ አፍ ፡ እንዳመጣ ፡ እየጠቃቀሱ ፡ የክርስቶስን ፡ ዐሠር ፡ ይዞ ፡ በሚደክም ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በማፋቸል ፡ የሚገኝ ፡ ይመስልሃልን ።? ከሥራው ፡ ሳይገኙ ፡ በማፊቸል ፡ ብቻ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንዳትገኝ ፡ ሲያስጠነቅቀን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡



በማቴ ፡ ወንጌል ፤ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፳፩ ፡ የሰማይ ፡ አባቴን ፡ ፈቃድ ፡ ከሚፈጽም ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ እግዚኦ ፡ እግዚኦ ፡ የሚለኝ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ መንግሥተ ፤ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አደለም ፡ ያለንን ፡ ረሳኸውን ፤ ? እንቢ ፡ ብለህ ፡ ተጋፍተህ ፡ እጠቃ ሳለሁ ፡ ብትልም ፡ አንተ ፡ ተግሣጼን ፡ ጠልተኸዋል ፡ ሕጌን ፡ ትእዛዜን ፡ ወደ ላህ ፡ አንዘግዝገህ ፡ ጥለኸዋል ፡ መጽሐፍ ፡ እየጠቃቀስክ ፡ ላስተምር ፡ ለምን ትላለህ ፡ እያለ ፡ በቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ ቃል ፡ ይዘልፍሃል ፡ መዝ ፡ ፶ ፡ ፲፯–፳ ።

በፍርድ ፡ ቀንም ፡ አቤቱ ፡ በስምህ ፡ ትንቢት ፡ የተናገርን ፡ አደለንምን በስምህ ፡ ጋኔን ፡ ያወጣን ፡ ብዙ ፡ ተአምራትስ ፡ ያደረግን ፡ አደለንምን ፡ ብትለው ከቶ ፡ እኔ ፡ አላውቅህም ፡ አንተ ፡ ዐመፀኛ ፡ ከኔ ፡ ራቅ ፡ ያሰኝሃል ፡ እንጂ ፡ የጠቅምህ ፡ አደለምና ፡ አፍህ ፡ እንዳመጣ ፡ እየጠቃቀስክ ፡ ማፊቸልህን ፡ ተው ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፪ ።

፲ ሕዝቅኤል ፡ ፫ ፡ ፳፯ ፡ የጠቀስከው ፡ የሚሰማ ፡ ይስማ ፡ እንቢ ፡ የሚልም ፡ እንቢ ይበል ፡ ይላል ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ መጻሕፍትን ፡ ለዐሳብህ ፡ እንደሚስማማህ ፡ አድርገህ ጠቅሰኻቸዋል ፤ እኔም ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ እያልኩ መልሼልሃለሁ ፤ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የኹለታችንንም ፡ ነገር ፡ አመዛዝኖ ሰምቶ ፡ እሺ ፡ የሚለውን ፡ እሽ ፡ ይበል ፤ እንቢ ፡ የሚለውን ፡ እንቢ ፡ ይበል

፲፩ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፪ ፡ ፲፤፲፪ ፡ የጠቀስከው ።

የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ትንቢት ፡ ነገር ፡ አትቈልፍ ፡ ዘመኑ ፡ ቀርቡዋልና ግፍ ፡ የሚሠራ ፡ ግፍ ፡ ይሥራ ፡ ርኵስም ፡ የሚኾን ፡ ርኵስ ፡ ይኹን ፡ ጻድቁም ይጽደቅ ፡ ቅዱሱም ፡ ይቀደስ ። እነሆ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣለሁ ፡ ዋጋዬም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ነው ፡ ለኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ይላል ።

በዚህ ፡ ነገር ፡ እንዳንፈካከርበት ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክታቡም ፫ ቍ ፬ ዛሬ ፡ በሃይማኖት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ኾነናል ፡ ፍጻሜያችን ግን ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ገና ፡ አልታወቀልንም ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቆናልና ፡ ኹላችንም ፡ ወደፊት ፡ በሚቆየን ፡ ነገር ፡ መፈካከራችንን ፡ ትተን ፡ በደላችንን ፡ ኃጢአታችንን ፡ ሳይቆጣጠር ፡ ሕጉን ፡ በመቀበላችን ፡ በስሙ ፡ በመጠራታችን ፡ ብቻ ዓለሙን ፡ ላድነው ፡ እንጂ ፡ ልፈርድበት ፡ አልመጣሁም ፡ ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ በማይጠብቀው ፡ ሰው ፡ የምፈርድበት ፤ አደለሁም ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ በቀኝ ፡ ያቆመን ፡ ዘንድ እንለምነው ፡ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፵፯ ።

## ፫ ተ ኛ ፡ ማ ስ ጠ ን ቀ ቂ ያ ።

### ማስጠንቀቂያ ፡ ብለህ ፡ ስለጻፍከው ፡ መልስ ።

፩ የተወደድክ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ይህች ፡ ትንሽ ፡ የሐሳቤ ፡ መግለጫ ፡ መጽሐፍ ፡ ስዕፍ ፡ መጀመሪያ የሚበቃ ፡ ትምህርት ፡ አልተማርኩም ፡ ብለሃል ።

ሀ) በዚህ ፡ ንግግርህ ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ እኔ ፡ በወልድ ፡ ውሉድ ፡ በክርስቶስ ክርስቲያን ፡ የተባልን ፡ እኛን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጆች ፡ ቅዱሳንን ፡ ብንወድ ፡ ብናከብር ፡ መምለክያን ፡ ጣዖት ፡ በማለትህ ።

www.ethiopianorthodox.org

ለ) በክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ ቅዱሳንን ፡ ጣዖታት ፡ ብለህ ፡ ስትሳደብ ፡ በመድፈርህ ።

ሐ) ኢይብለክሙ ፡ አግብርትየ ፡ አላ ፡ አዕርክትየ ፡ ብሎ ፡ ወዳጆቹ ፡ መኾናቸውን ፡ የመሰከረላቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍቀሬ ፡ ጣዖት ፡ ያሰኝብኛል ፡ ባለማለትህ ፡ የበቃ ፡ ትምህርት ፡ አለመማርክን ፡ ተረድቸው ፡ ሳለ ፡ አንተም ፡ እንዲሁ ፡ እንደኔ ፡ ተረድተኸው ፡ የበቃ ፡ ትምርት ፡ የለኝም ፡ በማለትህ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

፱ ፱ተኛ ፡ በልዩ ፤ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ ሳይኾን ፡ አጻጻፉ ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ ከማገኝበት ፡ የንግድ ፡ ሥራዬ ፡ ላይ ፡ ተደራቢ ፡ ሆነብኝ ። ስለምትለው ።

እውነት ፡ ነው ፡ ስንኳንስ ፡ ጾም ፡ የማያሳርፈው ፡ ሰዓት ፡ የማያልፈው ፡ ኾኖ ፡ ሲገኝ ፡ ውሎ ፡ ለሚመገብ ፡ እንኳ ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ ማግኘት ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ነው ። አንተም ፡ እንዲሁ ፡ በየሰዓቱ ፡ ምግብ ፡ ለማግኘት ፡ በምትደክመው ፡ ድክምህ ፡ ላይ ፡ ተደራቢ ፡ ስለኾነብህ ፡ ራስህ ፡ መዞሩን ፡ ጥቅስህ ፡ ያለአገባብ ፡ በመውደቁ ፡ ንባቡ ፡ ከምሥጢሩ ፡ በመራራቁ ፡ ተረድቼዋለሁ ።

፲ እኔ ፡ ላማርኛው ፡ ባዕዱ ፡ ትግሬ ፡ በመኾኔ ፡ ብዙ ፡ ጉድለትና ፡ ጸያፍ ፡ እንደምታገኝበት ፡ እተማመናለሁ ፡ ስለምትለው ።

ብዙ ፡ ጉድለትና ፡ ጸያፍ ፡ ያገኘሁበት ፡ በጠቅላላው ፡ ሐሳብህ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባማርኛው ፡ አሰካክ ፡ ላይስ ፡ ያገኘሁት ፡ ጉድለትና ፡ ፀያፍ ፡ ዐጭር ፡ ነው ። ቢኖርም ፡ የታወቀ ፡ ነውና ፡ አያስቀይምም ። ትግሬስ ፡ ዛሬ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ አንተ ፡ ተወልደህ ፡ የብድር ፡ ባህል ፡ እስክትሰብክበት ፡ ድረስ ፡ ለግእዝ ፡ ቋንቋችን ፡ ለኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታችን ፡ መሠረት ፤ ለ፱ቅዱሳን ፡ አባቶቻችን ፡ ምኔት ፡ ስለኾነ ፡ የትግሬ ፡ ተወላጅነትህ ፡ የሚያኰራህ ፡ እንጂ ፡ የሚያሳፍርህ ፡ አለመኾኑን ፡ ስገልጽልህ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

፲፩ የጐደለውን ፡ መልተህ ፡ የጠመመውን ፡ አቃንተህ ፡ የደፈረሰውንም ፡ ቃል ፡ አጣርተህ ፡ ታነብልኝ ፡ ዘንድ ፡ በማክበር ፡ አሳስብሃለሁ ፡ ስላልከኝ ።

በእውነት ፡ የጠመመውን ፡ አቅንቼ ፡ የጐደለውን ፡ መልቼ ፡ የደፈረሰውን ፡ ቃል ፡ አጣርቼ ፡ እመልስልህ ፡ ዘንድ ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ቅን ፡ ሕሊና ፡ ሰጥቶ ፡ በልቡናዬ ፡ ምሥጢሩን ፡ በአንደበቴ ፡ ንግግሩን ፡ ያከናውንልኝ ፡ ዘንድ ፡ ያባቶቼ ፡ የቅዱሳንን ፡ ፈጣሪ ፡ አጥብቄ ፡ እለምነዋለሁ ።



፪ተኛ ፡ መግቢያ ።

መግቢያ ፡ ብለህ ፡ ለጻፍከው ፡ መልስ ።

፩ አንተ ፡ ይህችን ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ የሐሳቤ ፡ መግለጫ ፡ የምታነብ ፡ በተለይም ፡ ለወጣቱ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ወንድሜ ፡ ክርስቶስን ፡ በማመንና ፡ በእውነተኛው ፡ ጥምቀትም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ተቀብለህ ፡ ኹለተኛ ፡ ከመንፈስ ፡ የተወለድክና ፡ ከቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ጋራም ፡ የተዋወቅህ ፡ ትኾናለህ ፡ በማለት ፡ ወንድሜ ፡ እያልከኝ ፡ ደፍሬ ፡ መጻፌ ፡ ይህነኑ ፡ ትልቅ ፤ እምነትህና ፡ ስጦታህ ፡ እምኜ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ በመጻሕፍት ፡ ለሚያላግጡ ፡ ከህዲዎችና ፡ ተጠራጣሪዎች ፡ አህርው ፡ ለኾኑ ፡ ሰዎች ፡ እንዳልጻፍኩት ፡ አስቀድሜ ፡ ልገልጽልህ ፡ እወዳለሁ ፡ ብለሃል ።

፩ ፡ እግዲህ ፡ አንተ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ የምታውቀው ፡ እንደታጠፈ ፡ በገበታው ፡ ላይ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የሚለውን ፡ ማስታወቂያ ፤ ብቻ ፡ ይመስለኛል ፡ እንጂ ፡ ስንኳን ፡ ምሥጢሩን ፡ ትመረምረው ፡ ንባቡንም ፡ ያነበብከው ፡ አይመስለኝም ። አንብበኸውስ ፡ ቢኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ ጀምራ ፡ በንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ የተዋወቀች ፡ መኾኗን ፡ ፩ኛ ፡ ነገ ፡ ቀዳ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ብትመለከት ፡ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ወሬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የመጣለቱን ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ በእንቆቅልሽ ፡ ትፈትነው ፡ ዘንድ ፡ መጣች ። አንተን ፡ የወደደ ፡ አምላክህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ። በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ያስቀመጠህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ወዷልና ፡ ለዘላለም ፡ ቅን ፡ ፍርድም ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ አሳነሣህ ፡ አለችው ፡ እያለ ፡ ይተርክልህ ፡ ነበረ ።

ይህንንም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቁርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ተነሥታ ፡ ቤተ ፡ አይሁድን ፡ ትፋረዳታለች ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ልትሰማ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ መጥታለችና ፡ ብሎ ፡ መስክሮላታል ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፵፪ ።

፪ተኛም ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፳፮—፵ ፡ ብትመለከት ፤ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ጀንደረባ ፡ ከህንደኬ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ ከሹማምቶቿ ፡ የበለጠ ፡ በከብቷ ፡ ኹሉ ፡ የሠለጠነ ፡ ነበረ ። እንደ ፡ አሪቱ ፡ ሥራት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሊሰግድ ፡ ሔዶ ። ሰግዶ ፡ ሲመለስ ፡ በሠረገላው ፡ ተቀምጠ ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ መጽአ ፡ ከሙ ፡ በግዕ ፡ ይጠባሕ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ የተናገረውን ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ እያነበበ ፡ ሲሔድ ፤ ፊልጶስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዞ ፡ ይህ ፡ ትንቢት ፡ መፈጸሙን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ተርጒሞ ፡ ተርኮ ፡ ቢነግረው ፡ እኔ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደኾነ ፡ አምናለሁ ፤ ብሎ ፡ እንደተጠመቀና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋ ፡ እንደተቀበለ ፡ ይተርክልሃል ።

ይህ ፡ ታሪክ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ጀምራ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መተዋወቋን ፡ ከሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ጀምራ ፡ በጥምቀት ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋ ፡ መቀበሏን ፡ ገልጦ ፡ ያስረዳል ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ዛሬ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ተነሥተህ ፡ እንደገና ፡ ባንተ ፡ ሐዋርያነት ፡ ጸጋ ፡ ጥምቀትን ፡ እንድታገኝልህ ፡ ባንተ ፡ መምህርነት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ እንድትተዋወቅልህ ፡ ስታስብ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ስሙን ፡ ከመጥራት ፡ በቀር ፡ ንባቡን ፡ ተመልክተኸው ፡ ምሥጢሩን ፡ ተገንዝበኸው ፡ አታውቅም ፡ ብልህ ፡ የሚያሳፍረኝ ፡ አለመኾኑን ፡ እወቅልኝ ፡ ተረዳልኝ ።

www.ethiopianorthodox.org

ደግሞስ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከንደበታችሁ ፡ አይውጣ ፡ ሳሙ ፡ ቀዳ ፡ ፱ ፡ ፫ ።

(ሀ) ለቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ አትግደል ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችሁ ፡ ነበረ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ወንድሙን ፡ በከንቱ ፡ የሚያስቀይም ፡ ሰው ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድ በታል ፡ ወንድሙን ፡ ጨርቀ ፡ ለባሽ ፡ አባተ ፡ ታናሽ ፡ ብሎ ፡ የተሳደበ ፡ በሸንጎ ፡ ባደባባይ ፡ ይፈረድበታል ። ዲዳ ፡ ደንቆሮ ፡ ብሎ ፡ ቢሳደብም ፡ በገሃነም ፡ ይፈረድ በታል ፤ ጠላቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፡ የሚረግሟችሁን ፡ ሰዎች ፡ መርቋቸው ፡ ለሚጠ ልዋችሁም ፡ መልካም ፡ አድርጉ ፡ እያለ ፡ ይመክረናል ፡ ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፲፫ ፡ ዘሌዋ ፡ ፳፬ ፡ ፲፯ ፡ ማቴ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ፡ ፴፬ ፡ ፩ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ጠላትህን ፡ መውደድ ፡ ይቅርና ፡ በማይገባህ ፡ በሀገረ ፡ ስብከቷ ፡ ገብተህ ፡ ስትባልቅ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ በትዕግሥት ፡ የምትመለከትህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ዕሪያ ፡ ከሀዲ ፡ ተጠራጣሪ ፡ በመጻሕፍት ፡ የምታላግጥ ፡ እያልክ ፡ ትሰድ ባታለህ ፡ እንግዲህ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ ተሳደቡ ፡ የሚል ፡ ከምን ፡ መጽ ሐፍ ፤ በስንት ፡ ምዕራፍ ፤ በስንት ፡ ቍጥር ፤ አግኝተህ ፡ ይኾን ።

መጽሐፍ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ አትተማሙ ፡ አትነቃቀፉ ፡ ወንድሙን ፡ የነቀፈ ፡ የሰደበ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መንቀፉ ፡ መስደቡ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ይመክረናል ፡ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ይህን ፡ ዘለህ ፡ ይልቁንም ፡ በሐሰት ፡ በማስመሰል ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እያልክ ፡ ከተሳደብክ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መንቀፍህ ፡ ነው ፤ ሕገ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ከነቀፍክ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ እንጂ ፡ ፈጻሚ ፡ ሕግ ፡ አት ባልም ፡ ስለዚህ ፡ በመጻሕፍት ፡ የምታላግጥ ፡ ከሀዲ ፤ ተጠራጣሪ ፤ ዕሪያ ፤ አንተ ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለመኾኗን ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ።

በሐሰት ፡ በማስመሰል ፡ እየጠቀስክ ፡ ያልኩትንም ፡ ጥቅሶችህን ፡ እየዘረዘርኩ ፡ አስረዳሃለሁ ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ አውርቼ ፡ አልሔድም ።

፱ ሕዝቅ ፡ ፴፮ ፡ ፳፭ ፡ ፳፯ ፡ የጠቀስከው ።

የጸራ ፡ ወኅ ፡ አፈስባችኋለሁ ፡ ትጸሩማላችሁ ፡ ከርኩሰታችሁም ፡ ከጣዖቶቻችሁም ፡ ኹሉ ፡ አነጻችኋለሁ ፡ ይላል ።

ኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ ትንቢት ፡ ገና ፡ በትንቢትነቱ ፡ ሳለ ፡ ያወቀችው ፡ የተረዳ ችው ፡ ኾና ፤ ትንቢቱ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ፣ነዋ ፡ ማይ ፡ መኑ ፡ ይክልአኒ ፡ ተጠምቆ ፡ ብላ ፡ አምና ፡ ተጠምቃ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በተቀበለች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ዐዲስ ፡ አስመስሎ ፡ መጥቀስ ፡ ማስመሰል ፡ ማጭበርበር ፡ ነው ።

፲ ምሳ ፡ ፳፫ ፡ ፱ ፡ የጠቀስከው ።

በሰነፍ ፡ ጆሮ ፡ አንዳች ፡ አትናገር ፡ የነገርህን ፡ ጥበብ ፡ ያፌዝብሃል ፡ ይላል ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንንና ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ልትዘልፍበት ፡ የጻፍከው ፡ መኾኑን ፡ ላቶ ፡ ማመን ፡ ብቻ ፡ ብለህ ፡ የጻፍከው ፡ አድራሻ ፡ እየመሰከረብህ ፡ ለነሱ ፡ አልጻፍኩትም ፡ ማለትህ ፡ ሐሰትህ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ጥበብህን ፡ የምናፌዝብህ ፡ ሰነፎች ፡ መኾናችንን ፡ ስታውቅ ፡ ለምን ፡ ጻፍከው ፡ አንተ ፡ ማንበብ ፡ እንጂ ፡ ማስተዋል ፡ እንደሌለብህ ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ።



ከዚህስ ፡ ይልቅ ፡ ቀጥሎ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ አስቀድሞ ፡ የተደረገውን ፡ ድንበር ፡ አታርቅ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ተመልክተህ ፡ ከባቶችህ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ውን ፡ ሕግ ፡ ፈቀቅ ፡ ሳታደርገው ፡ ብትኖር ፡ የተሻለ ፡ ነበር ።

፲፩ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፮ ፡ የጠቀስከው ።

የተቀደሰውን ፡ ለውሾች ፡ አትስጡ ፡ ዕንቋችሁንም ፡ በዕሪያዎች ፡ ፊት ፡ አትጣሉ ፡ በእግሮቻቸው ፡ እንዳይረግጡት ፡ ተመልሰውም ፡ እንዳይነክሷችሁ ፡ ይላል ።

ስድብ ፡ ለተሳዳቢው ፡ መልክና ፡ ግብር ፡ ተስማሚ ፡ ኾኖ ፡ ሲገኝ ፡ እንደ ፡ ምስጋ ናና ፡ እንደሙገሳ ፡ ይቆጠራል ፡ እንጂ ፡ ስድብ ፡ አይባልም ፡ አለመልኩ ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ ተሳዳቢውን ፡ ሽፋጭ ፡ አስመሳይ ፡ ያሰኘዋል ፡ እንጂ ፡ ስድብን ፡ እውነት ፡ ብሎ ፡ የሚቀበልለት ፡ አያገኝም ፡ ተሰዳቢውንም ፡ አያሳፍረውም ።

ይህ ፡ ጥቅስ ፡ ዕሪያን ፡ ንጹሕ ፡ ቅዱስ ፡ ምግብ ፡ አድርጎ ፡ በሚመገበው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ቢጠቀስ ፡ ኖሮ ፡ የበሉት ፡ የጠጡት ፡ አካል ፡ ኾኖ ፡ ገዝፎ ፡ የሚታይ ፡ ስለ ሆነ ፡ አዳሪን ፡ በማደሪያው ፡ መጥራት ፡ አገባብ ፡ በመኾኑ ፡ ተስማሚ ፡ ተገቢ ፡ ጥቅስ ፡ ኾኖ ፡ በተገኘ ፡ ነበረ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ከዕሪያ ፡ ጠባይ ፡ የራቀች ፤ ዕሪያ ፡ መብ ላትን ፡ የተጸየፈች ፤ ስትኾን ፡ ዕሪያዎች ፡ ብለህ ፡ ብትሳደብ ፡ አንተን ፡ አስመሳይ ፡ ሽፋጭ ፡ ያሰኝሃል ፡ እንጂ ፡ በርሱዋ ፡ ምንም ፡ አይደርስባትም ፤ ነገርክንም ፡ እው ነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚቀበልልህ ፡ አይገኝም ።

እስኪ ፡ ያሳይህ ፡ ዕሪያ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ይመነኵሳልን ፤ ይጾማልን ፤ በዓል ፤ ያከብራልን ፤ ለጽላት ፡ ይሰግዳልን ፡ ቅዱሳንን ፡ ይወዳልን ፤ በየትኛው ፡ ግብሩ ፡ ይኾን ፡ እኛን ፡ የሚመስለን ። በእውነቱ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የዕሪያ ፡ ጨማ ፡ ከምትቈርጥ ፡ በየስዓቱ ፡ ከምታላምጥ ፡ የዕሪያ ፡ ግብር ፡ ይዞህ ፡ ከምትገኝ ፡ ካንተ ፡ ልንጠበቅበት ፡ ተጻፈ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ከኛ ፡ ጠባይ ፡ ልትጠበቅበት ፡ አልተጻፈም ።

ይኸውም ፡ ዕንቍ ፡ የኾነች ፡ ያባቶችህን ፡ ሕግ ፡ ተመልሰህ ፡ ስትረግጣትና ፡ ስትነክሣት ፡ በመገኘትህ ፡ ይታወቃል ።

፲፪ ፡ ፪ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩—፱ ፡ የጠቀስከው ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፡ የሚወዱ በት ፡ ጊዜ ፡ እንዲመጣ ፡ እወቅ ፡ ብር ፡ ወዳጆች ፤ ተመኪች ፤ ዕቡዮች ፤ ተሳዳቦች ፤ ላባቶ ቻቸው ፡ የማይታዘዙ ፤ የማያመሰግኑ ፤ ያልተቀደሱ ፤ ፍቅር ፡ የሌላቸው ፤ መሐላ ፡ የሚያፈርሱ ፤ ሐሜተኞች ፤ ራሳቸውን ፡ ከክፉ ፡ የማይጠብቁ ፤ ደስ ፡ የማያሰኙ ፤ መልካም ፡ የማይወዱ ፤ በደለኞች ፤ ችኩሎች ፡ ትቢተኞች ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከመ ውደድ ፡ ይልቅ ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡ የሚወዱ ። በርሳቸውም ፡ የአምልኮት ፡ መልክ ፡ አለባቸው ፡ ኃይሏ ፡ ምግባርን ፡ ትሩፋትን ፡ ግን ፡ የካዱ ፡ ናቸው ። እሊህንም ፡ ሽሻቸው ። ከነዚህ ፡ አሉና ፡ ቤት ፡ ለቤት ፡ የሚዞሩ ፡ ኃጢአት ፡ የመላባቸውን ፡ ሴቶች ፡ ይገነትታሉ ፡ ወደ ፡ ተላ ለፈች ፡ ፍትወት ፡ የሚቀዳደሙ ፡ ኹለጊዜም ፡ ይማራሉ ፡ ወደ ፡ እውነትም ፡ እው [illegible] ከቶ ፡ አይችሉም ። ኢያኔስና ፡ ኢያንበሬስም ፡ ሙሴን ፡ እንደተ

www.ethiopianorthodox.org

ቃወሙት ፡ እንዲሁ ፡ እሊህም ፡ እውነትን ፡ ይቃወማሉ ፡ አእምሮዋቸው ፡ የጠፉ ፡ ሰዎች ፡ ከሃይማኖታቸው ፡ የወጡ ፡ ይላል ።

እንግዲህ ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፤ የሚወዱበት ፡ ክፉው ፡ ጊዜ ፡ የመጣ ፡ ከመቼ ፡ ጀምሮ ፡ ይመስልሃል ። ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ከ፫፻ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ አንዘግዝጎ ፡ ከጣለበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ አደለምን ። በርግጥ ፡ ከዚያ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(ሀ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንስ ፡ ይህ ፡ ትንቢት ፡ እንዳይደርባት ፡ ፈርታ ፡ ተንቀጥቅጣ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሑር ፡ ወሚጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ ፡ ብሎ ፡ ባስተማራት ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ጠፊ ፡ ነው ፡ ምን ፡ ይረባችኋል ፡ ምን ፡ ይጠቅማችኋል ፡ ገንዘባችሁን ፡ ሽጣችሁ ፡ ለውጣችሁ ፡ ሰጥታችሁ ፡ መጽውታችሁ ፡ መንኑ ፡ እያለች ፡ ሥርዓተ ፡ ብሕትውና ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ ታስተምራለች ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በዚሁ ፡ ክታብ ፡ በ፫ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፫ ፡ ቍጥር ፡ የሕይወት ፡ ትምርት ፡ ሕገ ፡ ትሩፋትን ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ የሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ። በጆሮዋቸው ፡ ቀበዝባዛነት ፡ ለጆሮዋቸው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ የሚነግሯቸው ፡ መምህራንን ፡ ይሰበስባሉ ፡ ጆሮዋቸውን ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ከመስማት ፡ ተረት ፡ ወደመስማት ፡ ይመልሳሉ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ይፈጸምብህ ፡ ዘንድ ፡ ምንኵስና ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ አይረባም ፡ አይጠቅምም ፡ እያልክ ፡ ታስተምራለህ ።

(ለ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ገቢረክሙ ፡ በሉ ፡ አግብርት ፡ ዕሩዓን ፡ ንሕነ ፡ ያለውን ፡ ተከትላ ፡ ሕጉን ፡ ብትፈጽሙም ፡ እኛ ፡ ኃጢአተኞች ፡ ነን ፡ አንገታችንን ፡ አቅንተን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተን ፡ ልንጸልይ ፡ አይገባንም ፡ አባቶቻችን ፡ ቅዱሳን ፡ ጸልዩልን ፡ ለምኑልን ፡ ብላችሁ ፡ በቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ ተማፀኑ ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ፡ ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ፡ ፱-፲፬ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ማን ፡ ከማን ፡ አንሶ ፡ ጸልዩልኝ ፡ እላለሁ ፡ ሥራዬ ፡ ይበቃኛል ፡ በሥራዬ ፡ እጸድቃለሁ ፡ እያልክ ፡ ትታበያለህ ፡ እኛ ፡ ሠርተን ፡ ለመጽደቅ ፡ አንችልምና ፡ አባቶቻችን ፡ አማልዱን ፡ እንደሚሉ ፡ እንደነዚህ ፡ ያላደረገኸኝ ፡ እያልክ ፡ ትመካለህ ።

(ሐ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተዘከሩ ፡ መኳንንቲክሙ ፡ ዘነገሩክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ትሬእዩ ፡ ሠናየ ፡ ግእዘሙ ።

ወንጌልን ፡ ያስተማሯችሁ ፡ መምህራኖቻችሁን ፡ እርዱ ፡ በጎ ፡ ምግባራቸውንም ፡ አይታችሁ ፡ በሃይማኖት ፡ ምሰሏቸው ፡ ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮ ።

ተአዘዙ ፡ ለመኳንንቲክሙ ፡ ወተኰነኑ ፡ ሎሙ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይተግሁ ፡ በእንተ ፡ ነፍስክሙ ፡ ከመ ፡ ዘይትሐሰብዎሙ ፡ በእንቲአክሙ ፡ ከመ ፡ በፍሥሐ ፡ ይግበርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወኢይንህኩ ።

www.ethiopianorthodox.org



ፍትሐ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ ስለናንተ ፡ የሚቆጣጠሯቸው ፡ እንደመኾናቸው ፡ መምህሮቻችሁ ፡ ነፍሳችሁን ፡ ሊማጻን ፡ ተግተው ያስተምሯችኋልና ፡ ይህን ፡ ማስተማሩን ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እንዲሠሩት ፡ እንዳያገዙ ፡ ርዷቸው ፡ አክብሯቸው ፡ ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ።

ወበኀቤየሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ክቡራን ፡ አዕርክቲከ ፤ እግዚኦ ። መዝ ፡ ፻፴፱ ፡ ፲፯ ።

አቤቱ ፡ ወዳጆችህ ፡ ቅዱሳን ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ የከበሩ ፡ ናቸው ፡ ያለውን ፡ ተከትላ ፡ መምሮቻችሁ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያትን ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታትን ፡ ከክርስቶስ ፡ በታች ፡ አክብሯቸው ፡ ውደዷቸው ፡ ታዘዙላቸው ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ የቀደሙ ፡ መምህራን ፡ ነቢያትን ፡ ሐዋርያትን ፡ ሊቃውንትን ፡ ጣዖታት ፤ ዛሬ ፡ ያሉ ፡ መምህራንን ፡ እነመምሬ ፡ አታለሉ ፡ እያልክ ፡ ትሰድባቸዋለህ ።

(መ) የኢትዮጵያ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ አንተ፡ በማያገባህ ፡ በሀገረ ፡ ስብከቷ ፡ ገብተህ ፡ በጆሮህ ፡ ቀበዝባዛነት ፡ ያመጣሃውን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ባህል ፡ ስትሰብክ ፡ እያየችህ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ዕድውክሙ ፡ ቢጽክሙ ፡ ውእቱ ። በኛ ፡ ላይ ፡ ያልኾነ ፡ ኹሉ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፡ አትከልክሉት ፡ ያለውን ፡ ተከትላ ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ካመነ ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ከጠራ ፡ ተውት ፡ አትከልክሉት ፡ እያለች ፡ ልጆቿን ፡ ትመክራለች ፡ ሉቃ ፡ ፱ ፤ ፶ ።

አንተ ፡ ግን ፡ አለስሟ ፡ ስም ፡ ያለግብሯ ፡ ግብር ፡ እየሰጠህ ፡ ታማታለህ ፡ ትጠላታለህ ፡ ትነቅፋታለህ ፡ ትሰድባታለህ ።

ሠ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይርህቡ ፡ ወይጸምዑ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ያለውን ፡ ይዛ ፡ ገንዘባችሁንማ ፡ ጨርሳችሁ ፡ ከበላችሁት ፡ ከጠጣችሁት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ምን ፡ ሠርታችሁ ፡ ደስ ፡ ልታሰኙት ፡ ነው ፡ ገንዘባችሁን ፡ ሰጥታችሁ ፡ መጽውታችሁ ፡ እየጾማችሁ ፡ ደስ ፡ አሰኙት ፡ እያለች ፡ ትመክራለች ፡ ታስተምራለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ወአስባሕክሙ ፡ ልበክሙ ፡ ከመ ፡ ዘያሰብሕ ፡ ላህመ ፡ ለዕለተ ፡ ጥብሐት ፡ ያለውን ፡ (ተግሣጽ ፡) ያዕ ፡ ፭ ፡ ፭ ፡ ትሩፋት ፡ እንደመሥራት ፡ ቈጥረኸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፤ ሰውነታችሁ ፡ ለምን ፡ ይከሣል ፤ ብሉ ፡ ጠጡ ፤ ሆድ ፡ ይሙላ ፤ ደረት ፡ ይቅላ ፤ ጾም ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፤ አይረባም ፤ አይጠቅምም ፤ እያልክ ፡ ታስተምራለህ ።

ረ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻዋን ፡ እንዳትረባ ፡ እንዳትጠቅም ፡ አውቃ ፡ በሃይማኖታችሁ ፡ ላይ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሥሩ ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ። ያዕ ፡ ፪ ፡ ፲፬-፳፮ ።

አንተ ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ አምኛለሁ ፡ እምነቴ ፡ ብቻ ፡ ይበቃኛል ፡ ትላለህ ፡ እንጂ፡ የሃይማኖት ፡ ኃይል ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ ፈጽመህ ፡ ክደሃል ፡ ያዕ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።

ሰ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሰንበት ፡ ጋራ ፡ በያመት ፡ በያመቱ ፡ የጌታን ፡ [illegible]ችንን ፡ የነቢያት ፡ የሐዋርያትን ፡ የጻድቃን ፡ የሰማዕታትን ፡ በዓል ፡ ምክን

www.ethiopianorthodox.org

ያት ፡ በማድረግ ፡ ከሴት ፡ ራቁ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቁ ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሔዳችሁ ፡ እጅ ፡ ንሱ ፡ ቤት ፡ ለቤት ፡ አትልከስከሱ ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ። ሕዝቡም ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ሲሠራው ፡ ይታያል ።

አንተ ፡ ግን ፡ በዓል ፡ ማክበር ፡ በሕግ ፡ ያልታዘዘ ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ ነውና ፡ በዓል ፡ አታክብሩ ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አትድረሱ ፡ ቤት ፡ ለቤት ፡ ተልከስከሱ ፡ እያልክ ፡ ታስተምራለህ ። ኹል ፡ ጊዜ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ እመለከታለሁ ፡ ትላለህ ፡ ወደ ፡ እውነተኛው ፡ ጽድቅ ፡ ለመምጣት ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ አትችልም ፤ ኢያኔስና ፡ ኢያንበሬስ ፡ ሙሴን ፡ እንደተቃወሙት ፡ አንተም ፡ ሙሴንና ፡ ሌሎችንም ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያትንና ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታትን ፡ ትቃወማለህ ። ከሃይማኖት ፡ የወጡ ፡ አእምሯቸው ፡ የጠፋ ፡ ሰዎች ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ይነሣሉ ፡ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የጻፈ ፡ ስላንተ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኦልጻፈም ፡ ብንል ፡ ባስተዋዮችና ፡ በተመልካቾች ፡ ዘንድ ፡ እውነት ፡ እንጂ ፡ ሐሰት ፡ ኾኖ ፡ አይገኝም ።

ይልቁንም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ አእግዚአ ፡ መሀሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ ለእስራኤል ፡ ይጸልይ ፡ ነበረ ፡ በማለትህ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፍጡር ፡ ደኃራዊ ፡ እያልክ ፡ የምትክደው ፤ መጻሕፍትን ፡ እንደ ፡ ፈቃድህ ፡ እየጠቃቀስክ ፡ የምታላግጥባቸው ፡ አንተ ፡ (ምዕ ፡ ፺ ፡ ገጽ ፡ ፵፬ ፡ መሥመር ፡ ፲፩-፲፪ ፡) መጻሕፍትን ፡ መርምረን ፡ ጠንቅቀን ፡ ፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተወልደ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ ወልድ ፡ ዋህድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ (አመክንዮ ፡ ዘሐዋ ፡) ወነአምን ፡ በ፩ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ (ጸሎ ፡ ሃይ ፡ ዘ፫ ፲ ፡) ብለን ፡ የምናምን ፡ እኛን ፡ ከሀዲዎች ፡ በመጻሕፍት ፡ የሚያላግጡ ፡ ብለህ ፡ መሳደብህ ፡ ባስተዋዮች ፡ ዘንድ ፡ ይገርማል ፡ ይደንቃል ። ቢኾንም ፡ ይህ ፡ አጠቃቀስህና ፡ አነጋገርህ ፡ ያንተን ፡ በሽህ ፡ ውረድነት ፡ ይገልጽብሃል ፡ እንጂ ፡ የሚጐዳን ፡ አይደለም ።

፺ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እንደዚህ ፡ ብየ ፡ ስነግርህ ፡ ለጊዜው ፡ ትንቅፈኝ ፡ ይኾናል ። እያልክ ፡ እያጠራጠርክ ፡ ትናገራለህ ።

እኔስ ፡ የምነቅፍህ ፡ ለጊዜው ፡ ብቻም ፡ አይደለም ፡ ለዘለቃው ፡ ነው ፡ ምክንያቱንም ፡ በሚከተለው ፡ መሥመርና ፡ እንዲሁም ፡ በየደጁ ፡ በምታመጣቸውም ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ አስረዳሃለሁ ።

፺ በመንፈሳዊ ፡ ሐሳብ ፡ ልብ ፡ ዳኛ ፡ አድርገህ ፡ በዚህ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃላት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ በየምዕራፉና ፡ ቍጥሩ ፡ አውጥተህ ፡ እየለየህ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ብቻ ፡ ብታነብ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከልቤ ፡ አውጥቼ ፡ ከሕሊናየ ፡ አንቅቼ ፡ እንዳልጻፍኩት ፡ ትረዳዋለህ ። ትላለህ ።

ጥቅሶችህን ፡ ኹሉ ፡ በምዕራፍና ፡ በቍጥር ፡ እያወጣሁ ፡ ብመለከታቸው ፡ ከላይ ፡ መነሻቸውን ፡ ከታች ፡ መድረሻቸውን ፡ ሳትመለከት ፤ ለምን ፡ ምክንያት ፡ እንደተጻፉ ፡ ምሥጢራቸውን ፡ ሳትረዳ ፤ ከሕሊናህ ፡ ለነቃው ፡ መጥፎ ፡ ሐሳብ ፡ ደጋፊ ፡ እያደረግህ ፡ አላገባብ ፡ መጥቀስህ ፡ ያሳዝናል ፡ እንጂ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ቅዱሳት ፡ መሆናቸው ፡ አይከድም ።



፰ ገንዘብ ፡ ብታገኝ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አማርኛውን ፡ ገዝተህ ፡ አሹተውለህ ፡ እያመሳከርህ ፡ አንብብ ፤ አማርኛ ፡ በመኾኑ ፡ ምሥጢሩን ፡ በቶሎ ፡ እንዲገባህ ፡ ብየ ፡ ነኝ ። ስለ ፡ ምትለው ።

መጽሐፍ ፤ ቅዱስ ፡ ምሥጢሩ ፡ ጥልቅ ፡ ከመኾኑም ፡ በላይ ፡ ወደአማርኛ ፡ ሲመለስ ፡ ያማርኛውን ፡ ሕግ ፡ ተከትሎ ፡ በደንብ ፡ ያልተጻፈ ፡ በመኾኑ ፡ ከግእዙ ፡ ይልቅ ፡ ዐማርኛው ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። አንተም ፡ ምሥጢሩን ፡ ሳትረዳው ፡ የተረዳሁት ፡ መስሎህ ፡ የተሳሳትክ ፡ አማርኛ ፡ በመኾኑ ፡ ይመስለኛል ።

፱ ገንዘብ ፡ ብታጣ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ ያለው ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ከዕቃ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ዝም ፡ በል ፡ አትናገር ፡ ተብሎ ፡ የኋሊት ፡ ተቈልፎ ፡ ታገኘዋለህ ። ስለ ፡ ምትለው ።

አንተ ፡ ከጉባኤ ፡ ቤት ፡ ደርሰህ ፡ ባታውቅ ፡ መምህራንን ፡ ባትወድ ፡ ዝም ፡ በሉ ፡ ተብሎ ፡ ተቈለፈባቸው ፡ እያልክ ፡ ታወራለህ ፤ እንጂ ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ ቤት ፡ ብትሔድስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ባልተሳሳተ ፡ መንገድ ፡ ፍልፍል ፡ አድርገው ፡ አንብበው ፡ ተርጕመው ፡ ሲያስረዱ ፡ ባገኘሃቸው ፡ ነበረ ።

፲ ቋንቋው ፡ ግዕዝ ፡ ኾኖ ፡ ስለማይሰማልህ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ተርጓሚ ፡ ካህን ፡ ይዘህ ፡ ማንበብና ፡ መመርመር ፡ ማስተዋልም ፡ ያስፈልግሃል ። ስለምትለው ።

ከተናገርከው ፡ ኹሉ ፡ አለአሁን ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ አልተናገርክም ፤ ይህን ፡ ምክር ፡ ለራስህም ፡ የምታደርገው ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ኖሯል ? ከመምህራን ፡ ዘንድ ፡ ደርሰህ ፡ ቢኾን ፡ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ ባልደረስክም ፡ ነበረ ። አሁንም ፡ ይህን ፡ ምክር ፡ ለራስህም ፡ እንድታደርገው ፡ አደራ ፡ እልሃለሁ ።

፲፩ ጀምረኽ ፡ ሳትጨርስ ፡ አስቀድመህ ፡ ብትነቅፍ ፡ ፍሬ ፡ ሳታገኝበት ፡ መቅረትህን ፡ እወቀው ፡ ስለ ፡ ምትለው ።

እንዲህ ፡ ያልከውን ፡ ይገፅ ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ መላልሼ ፡ ብመለከተው ፡ ከስድብ ፡ በቀር ፡ አንድም ፡ የሚጠቅም ፡ ፍሬ ፡ አላገኘሁበትም ።

፲፪ መንቀፍ ፡ ወይም ፡ ማቀፍ ፡ ከባሕረ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ዋኝቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በውጭ ፡ ኾኖ ፡ አይደለም ። ስለምትለው ።

ባሕረ ፡ መጻሕፍት ፡ የምትለው ፡ ይህ ፡ መጽሐፍህ ፡ በውስጡ ፡ ማስመሰል ፡ የተባለ ፡ ዓሣ ፡ የላሰው ፡ ደንጋያ ፡ (ጥቅስ ፡) ሞልቶበት ፡ ከማሙለጭለጭ ፡ በቀር ፡ ጥልቅነት ፡ የሌለው ፡ በመኾኑ ፡ ሊያስዋኝ ፡ አልቻለም ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተመላለስኩበት ።

፲፫ ብትነቅፍም ፡ እርሱን ፡ በሚያህል ፡ ጽሑፍ ፡ ካልኾነ ፡ በቃል ፡ አይበቃም ። ስለ ፡ ምትለው ።

እውነትህን ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ነገሩን ፡ ተረድቼው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ መልሱን ፡ ባጠፌታ ፡ ጽፌልሃለሁ ።

፲፬ ይልቁንስ ፡ አባታችን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ኵሎ ፡ አመክሩ ፡ ወዘሠናይ ፡ አጽንዑ ። ከመ ፡ ትፍትኑ ፡ ወታመክሩ ፡ ዘይኄይስ ፡ ግብረ ፡ እያለ ፡ ይመክርሃልና ፡ ያባትህን ፡ ምክርና ፡ ትምህርት ፡ አጽንተህ ፡ ይዘህ ፡ ኹሉን ፡ መመርመር ፡ ያስፈልግሃል ፡ ፩ ተሰ ፡ ፭ ፡ ፳፩ ፡ ፊል ፡ ፩ ፡ ፲ ። ስለ ፡ ምትለው ።

አንተ ፡ ባታውቅ ፡ እንግዳ ፡ አስመስለህ ፡ እንዲህ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያስ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ ምክር ፡ ከመጻፉ ፡ አስቀድማ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ተመራምራ ፡ ዐውቃ ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅን ፡ መርጣ ፡ ይዛለች ።

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስም ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ከሃይማኖተ ፡ አሪት ፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፤ ከሕገ ፡ አሪት ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ መርጣ ፡ ይዛለች ።

ሃይማኖትም ፡ ያለምግባር ፡ እንዳይረባ ፡ እንዳይጠቅም ፡ ዐውቃ ፡ መብልዕሰ ፡ ኢያሠልጠነ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሊዕኒ ፡ ኢያረብሐነ ፡ ወኢያነክየነ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፰ ፰ ፡ ያለውን ፡ ተመልክታ ፡ ንበላዕ ፡ ወንስተይ ፡ ወጌሠመ ፡ ንመውት ፡ ከማለት ፡ ንጹም ፡ ወንጸሊ ፡ ወጌሠመ ፡ ንመውት ፡ ማለትን ፡ መርጣ ፡ አጥብቃ ፡ ይዛለች ። ፩ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፴፪ ።

፲፬ አስቀድመህ ፡ ግን ፡ ራስህን ፡ በራስህ ፡ መርምረህ ፡ ስታበቃ ፡ በጠባቡ ፡ መንገድ ፡ ወደሕይወት ፡ በሚያገባው ፡ በሰፊው ፡ ጎዳና ፡ ወደሞት ፡ በሚያገባው ፡ በየትኛው ፡ ላይ ፡ የምትኼድ ፡ እንዳለህ ፡ ስልቱህ ፡ በልብህ ፡ ታዘበው ፡ ብለህ ፡ ሰቆቃ ፡ ኤር ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፴፱ ፡ ፵ ፡ ሕያው ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ ያንጐራጕራል ፡ ሰው ፡ ስለኃጢአቱ ፡ ያንጐራጕር ፡ መንገዳችንን ፡ እንመርምር ፡ እንሻ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንመለስ ፡ ያለውን ።

፲፭ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ በ፪ ቆሮ ፲፫ ፭ ፡ በሃይማኖት ፡ ቆማችሁም ፡ እንደ ኾነ ፡ ወይም ፡ ክርስቶስ ፡ አድሮባችሁ ፡ እንዳለ ፡ አታውቁም ፡ እንደ ኾነ ፡ ራሳችሁን ፡ ፈትኑ ፡ መርምሩ ፡ ያለውን ።

፲፮ ማቴዎስም ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፬ ፡ ባኡ ፡ እንተ ፡ ጸባብ ፡ አንቀጽ ፡ እስመ ፡ ርኂብ ፡ አንቀጽ ፡ ወስፉሕት ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡ ኃጕል ፡ ወብዙኃን ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ይበውእዋ ፡ ውስቴታ ፡ ወጥቀ ፡ ጸባብ ፡ አንቀጽ ፡ ወዕፅብት ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ወኅዳጣን ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ይበውዑ ያለውን ፡ ጠቅሰሃል ።

(ሀ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለኒህ ፡ ጥቅሶች ፡ እንግዳ ፡ አደለችም ፡ ልጆቿን ፡ ቢቻል ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ ባይቻልም ፡ ጧትና ፡ ማታ ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሔዳችሁ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቢርቃችሁ ፡ ክመኝታችሁ ፡ ላይ ፡ ኾናችሁ ፡ ጧዋት ፡ ምን ፡ ስትሠሩ ፡ እንደአደራችሁ ፡ ማታ ፡ ምን ፡ ስትሠሩ ፡ እንደዋላችሁ ፡ ሰውነታችሁን ፡ በመቈጣጠር ፡ ጸሎት ፡ አቅርቡ ፡ ትላለች ።

(ለ) ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፤ በፈቃደ ፡ ነፍስ ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋችሁን ፡ አትሥሩ ፡ ሥጋ ፡ ነፍስ ፡ የማትወደውን ፡ ይወዳል ፡ ነፍስም ፡ ሥጋ ፡ የማይወደውን ፤ ትወዳለችና ፡ የምትወዱትን ፡ እንዳትሠሩ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣሉባችኋል ፡ ገላ ፡ ፭ ፲፮ ፡ ፳፫ ፡ ያለውን ፡ አጥብቃ ፡ ተመርጉዛ ፡ ጾም ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፡ ብሉ ፡ ጠጡ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ምንኵስና ፡ ሕግ ፡ አደለም ፡ ፈቃደ ፤ ሥጋችሁን ፡ ፈጽሙ ፡ የሚለውን ፡ ወደጥፋት ፡ የሚያደርሰውን ፡ ሰፊውን ፡ በር ፡ ሰፊውን ፡ ጐዳና ፡ ትታችሁ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ አላፊ ፡ ጠፊ ፡ ስለኾነ ፡ ያገቡ ፡ እንዳላገቡ ፡ ያለቀሱ ፡ እንዳላለቀሱ ፤ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ደስ ፡ እንዳላላቸው ፤ የገዙ ፡ እንዳልገዙ ፤ የበሉ ፡ የጠጡ ፡ እንዳልበሉ ፡ እንዳልጠጡ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፳፱—፴፪ ፡ ይኾናሉና ፡ ከሴት ፡ ርቃችሁ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቃቸሁ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋችሁን ፡ አሸንፉችሁ ፡ በፈቃደ ፡ ነፍስ



ጸንታችሁ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ተወስናችሁ ፡ ወደሕይወት ፡ በምትወስዲቱ ፡ በጠባቧ ፡ በር ፡ ግቡ ፤ በምታስጨንቂቱ ፡ መንገድ ፡ ሒዱ ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ጠባብ ፡ ጠባብ ፡ በሮች ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ኃጢአት ፡ የቈጠርካቸው ፡ ስትኾን ፡ ባኡ ፡ እንተ ፡ ጸባብ ፡ አንቀጽ ፡ እያልክ ፡ በመጥቀስህ ፡ መጻሕፍትን ፡ ለሰው ፡ መዝለፊያ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ልትጠቀምባቸው ፡ የምትሻቸው ፡ አልመሰልከኝም ። ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ በአፍዓ ፡ ያሉ ፡ አሕዛብስ ፡ አንተ ፡ ከምትሠራው ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይሠሩ ፡ መሰለህ ። እንዳንተ ፡ ጾም ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፤ እንደ ፡ ከብቶች ፡ መብላትን ፤ መጠጣትን ፤ መጋባትን ፤ ሕግ ፡ አድርጎ ፡ ተግባረ ፡ ነፍስ ፡ የሚያዝባቸው ፡ ዕለታተ ፡ በዓላትን ፡ ሳይለዩ ፡ ዘወትር ፡ ለተግባረ ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ ጽሙድ ፡ ኾኖ ፡ መኖርን ፡ አይደለምን ? ፈጣሪ ፡ አለ ፡ ማለትን ፡ ግን ፡ ኹሉም ፡ በየቋንቋቸው ፡ የሚክዱ ፡ አይምሰልህ ።

፲፯ ነገር ፡ ግን ፡ በሰው ፡ ያለው ፡ መንፈስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ነው ፡ አስተዋይ ፡ የሚያደርግ ፡ ብለህ ፡ ኢዮ ፡ ፴፪ ፡ ፰ ፡ የጠቀስከው ።

እውነት ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ አስተዋይ ፡ የሚያደርግ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ የለውም ።

፲፰ ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ የጠቀስከው ፡ መዝ ፡ ፵፱ ፡ ፳ ። ሰውስ ፡ ክቡር ፡ ፍጥረት ፡ ሲኾን ፡ አላወቀም ፤ አእምሮ ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደ ፡ እንስሶች ፡ ኾነ ፡ እንስሶችን ፡ መሰለ ፡ ይላል ።

ቅዱስ ፡ ዳዊት እንስሳትን ፡ መሰሉ ፡ ማለቱ ፤ ቀርጻቸው ፡ ተለውጦ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ቀንድ ፤ ጅራት ፤ ጋማ ፤ ጭራ ፡ አወጡ ፡ ማለቱ ፡ አደለም ። ግእዘ ፡ መላእክትን ፡ ጾምን ፤ ጸሎትን ፤ ትሕርምትን ፤ ንጽሕናን ፡ ትተው ፡ ግእዘ ፡ እንስሳትን ፡ ያዙ ፡ በግእዘ ፡ እንስሳት ፡ ጸኑ ፡ ሲል ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ካንተና ፡ ከኛ ፡ በግእዘ ፡ እንስሳት ፡ ጸንቶ ፡ መብላት ፡ መጠጣትን ፡ መጋባትን ፡ ብቻ ፡ ተግባር ፡ አድርጎ ፡ የሚኖር ፡ ማነው ፡ አንተ ፡ አይደለህምን ።

ይህ ፡ ትንቢት ፡ ስላንተ ፡ የተነገረ ፡ መኾኑን ፡ ራስህን ፡ በራስህ ፡ መርምርበት ። ራስህን ፡ ታዘብበት ፡ እንጂ ፡ እኔን ፡ ምን ፡ በል ፡ ትለኛለህ ።

፲፱ ከዚህ ፡ ቀጥለህ ፡ የጠቀስከው ፡ ፪ቆሮ ፡ ፲-፲፭ ፡ ከሐሳብህ ፡ ጋራ የተራራቀ ፡ በመኾኑ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የሌለበት ፡ ስለኾነ ፡ አልፌዋለሁ ። ይህን ፡ ሐሳብ ፡ የሚደግፍ ፡ አለመኾኑንም ፡ አይቼ ፡ ልረዳ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በምዕራፉና ፡ በቍጥሩ ፡ አውጥቶ ፡ ይመልከት ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ተኛ ፡ መቅድም ፡ ከለምትለው ፡ መልስ ።

፩ የተወደድክ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ቅር የሚያሰኝህ ፡ ቃላት ፡ አታጣ በትም ፡ ይኾናል ፡ ብለህ ፡ አጠራጥረህ ፡ ተናግረሃል ።

፩ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ያልተማሩ ፡ የማያስተውሉ ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎችን ፡ መጻሕፍት ፡ ለባህላቸው ፡ እንዲስማማ ፡ አድርገው ፡ እንደለዋወጧቸው ፡ እንደአጠመሟቸው ፡ ዛሬም ፡ የመጽሐፉን ፡ ቃል ፡ ይለዋውጡታል ፡ ተብሎ ፡ እንደተነገረ ፡ ፪ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ከላይ ፡ አርእስታቸውን ፡ ከታች ፡ ኅዳጋቸውን ፡ ተመልክተህ ፡ የሚሰጡትን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ሳትረዳ ፤ አፋህ ፡ እንዳመጣ ፡ በዘፈቀደ ፡ በመጥቀስህ አጠቃቀስህ ፡ ኹሉ ፡ በጣም ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፪ ነገር ፡ ግን ፡ በውነተኛው ፡ ብርሃናዊ ፡ ሕሊናህ ፡ ብትመረምረው ፡ የኛው ፡ አምልኮና ፡ የአምላካችን ፡ ትእዛዝ ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ መኾኑን ፡ ስላየሁ ፡ ለኔም ፡ እንዳንተ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቅር ፡ ብሎኛል ። እንደምን ፡ ብትለኝ ፡ ግን ፡ ክርስቲያንነታችን ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሕግና ፡ በምግባር ፡ አይደለም ፡ ስለምትለው ።

፪ ፡ በአንተ በኩል ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ ከራሱ ፡ በመነጨው ፡ ሐሳብ ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አምዘግዝጎ ፡ ከጣለው ፡ ወዲህ ፡ አኳኼዳችሁ ፡ ኹሉ ፡ ከአምላክ ፡ ትእዛዝ ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ ኾኗል ፡ ስለዚህ ፡ ክርስቲያንነታችሁ ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ በሕግና ፡ በምግባር ፡ አለመኾኑን ፡ መልካም ፡ ተመልክተኸዋል ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ ሳትለውጥ ፡ ሳትክድ ፡ ባለ ፡ ዓቅሟ ፡ ኹሉ ፡ ለመፈጸም ፡ ትጣጣራለች ፡ በሰብአዊ ፡ ባሕርይዋ ፡ ደክማ ፡ በኃጢአት ፡ ብትሰነካከልም ። ስብዐ ፡ ይወድቅ ፡ ወስብዐ ፡ ይትነሣእ ጻድቅ ። ኢይብለከ ፡ እስከ ፡ ስብእ ፡ አላ ፡ ፸ ፡ በበስብዕ ፡ ያለውን ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ አጥብቃ ፡ ይዛ ፡ ተስፋ ፡ ሳትቈርጥ ፡ በንስሐ ፡ መንገዷን ፡ ወደዚያው ፡ ትቀጥላለች ፡ እንጂ ፡ ሕጉን ትእዛዙን ፡ አትክድም ፡ አትነቅፍምና ፡ ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርቃለች ፡ አትባልም ።

፫ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የባሰውና ፡ የከፋው ፡ ግን ፡ ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ የክርስቶስን ፡ መድኃኒትንት ፡ ከነ ወንጌሉ ፡ ጥሎ ፡ ለአባ ፡ እገሌ ፡ ጻድቅ ፡ ብሎ ፡ ከነመጽሐፈ ፡ ሐሰቱ ፡ አምኖ ፡ ለማያድነው ፡ መድኃኒት ፡ መስሎት ፡ ተቀብሎ ፡ በስሙ ፡ ግን ፡ የክርስቶስ ፡ ወገን ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ ይላልና ፡ ነገሩ ፡ ቅር ፡ ያሰኛል ፡ በጣምም ፡ ያሳዝናል ፡ ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ፡ ኤር ፡ ፳፰ ፡ ፱ ፡ ፯ ፡ ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ፡ ማለትህ ፡

አቡሃ ፡ ለሐሰት ፤ ዓመፃ ፡ ወጽአት ፡ እመዛግብቲሃ ፡ ክተባለው ፡ ከግብር ፡ አባትህ ፡ ከሰይጣን ፡ የተማርኸው ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

፫ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የክርስቶስን ፡ መድኃኒትነት ፡ ከነወንጌሉ ፡ ጥላ ፡ አንዱን ፡ ጻድቅ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ አታምንም ። ይህ ፡ ንግግርህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ መኾኑንም ፡ በጠቀስካቸው ፡ ጥቅሶች ፡ አስረዳሃለሁ ።

(ሀ ፡) ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ፡ የጠቀስከው ፡ እግዚአብሔር ፡ የንቅልፍ ፡ መንፈስ ፡ አፍሶባችኋልና ፡ ዐይናችሁን የሚጨፍን ፡ ነቢያታችሁንም ፡ አለቆቻችሁንም ፡ ራእይ ፡ የሚያዩትንም ፡ ይጋርዳቸዋል ፡ ራእዩም ፡ ኹሉ ፡ እንደታተመ ፡ መጽሐፍ ፡ ይኾንባቸዋል ፡ ፊደል ፡ ለሚያወቅ ፡ ይህን ፡ አንብብ ፡ ብለው ፡ ይሰጡ



ታል ። እርሱም ፡ ተዘግቷልና ፡ አልችልም ፡ ይላቸዋል ። ደግሞም ፡ ያነን ፡ መጽሐፍ ፡ ጽሕፈት ፡ ለማያውቅ ፡ ይሰጡታል ። ይህነን ፡ አንብብ ፡ ይሉታል ። እርሱም ፡ ማንበብ ፡ አላውቅም ፡ ይላቸዋል ፡ ይላል ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እመኒ ፡ ክዱን ፡ ትምህርትነ ፡ ክዱን ፡ ውእቱ ፡ ለኅርቱማን ፡ ወለንፉቃን ፡ ብሎ ፡ እንደነገረን ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፫ መጻሕፍት ፡ ስውርነታቸው ፡ የተሰወረውን ፡ ገልጠው ፡ የረቀቀውን ፤ አጕልተው ፡ ተርጕመው ፡ የሚያስረዱ ፡ መምህራንን ፡ በሚንቁ ፡ በሚያቃልሉ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያስ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የተሰወረውን ፡ ገልጠው ፡ የረቀቀውን ፡ አጕልተው ፡ ተርጕመው ፡ የሚያስረዱ ፡ በትርጓሜ ፡ የተቀረጹ ፤ በምሥጢር ፡ የተጌጹ ፡ በሃይማኖት ፡ የተመደኑ ፤ በምግባር ፡ የተፈተኑ ፤ እንደነዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤ እንደነቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ያሉ ፡ የተጣሩ ፡ መምህራኖች ፡ ስላሏት ፡ አንብባ ፡ ተርጕማ ፡ ታስረዳለች ፡ እንጂ ፡ አላውቅም ፡ አትልምና ፡ ይህ ፡ ጥቅስህ ፡ ከንቱ ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

ይህንስ ፡ ጥቅስ ፡ ስለ ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በጻፍከው ፡ በ፬ተኛው ፡ አንቀጽ ፡ በ፳፬ ፡ ገጽ ፡ በ፬ተኛው ፡ መሥመር ፤ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ሕሊናየ ፡ የማይደርስበት ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ስለኾነ ፡ ከማውቀው ፡ ይልቅ ፡ የማላውቀው ፡ ይበዛል ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ በመሰከርክበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብትጠቅሰው ፡ የማያጠራጥር ፡ ተስማሚ ፡ ኾኖ ፡ በተገኘ ፡ ነበረ ።

(ለ ፡) በ፲፫ ፡ ቍ ፡ የጠቀስከው ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ባፉ ፡ ያቀርበኛል ፡ በከንፈሩ ፡ ያከብረኛል ፡ በልቡ ፡ ግን ፡ ከኔ ፡ እጅግ ፡ ይርቃል ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ።

እስራኤል ፡ ባፋቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ፡ ለታቦተ ፡ ጽዮን ፡ እንሰግዳለን ፡ እያሉ ፡ በልባቸው ፡ ጣዖት ፡ ሲያመልኩ ፡ አሮን ፤ ወይም ፡ ኢዮርብዓም ፡ ወልደ ፡ ናባጥ ፡ ላቆማቸው ፡ ዕጓላተ ፡ ላሕም ፡ ሲሰግዱ ፡ ቢገኙ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለነሱ ፡ ተናገረው ፡ እንጂ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያን ፡ አልተናገረውም ፡ ዘፀአ ፡ ፴፪ ፡ ፩ ፡ ፱ ። ነገ ፡ ቀዳ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰—፴፩ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አፍኒ ፡ ወልብ ፡ ኅቡረ ፡ ይእመኑ ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ፡ እንጂ ፡ ፈጣሪዋን ፡ በአፏ ፡ አምና ፡ በልቧ ፡ የምትክድ ፡ አደለችምና ፡ ሊጠቀስባት ፡ አይገባም ።

(ሐ ) በኤር ፡ ፳፰ ፡ ፱—፯ ፡ የጠቀስከው ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሮቹን ፡ ነቢያትን ፡ ማልዶ ፡ ወደናንተ ፡ ላከ ፡ እናንተ ፡ ከክፉታችሁ ፡ ትመለሱ ፡ ዘንድ ፤ ሌሎችንም ፡ አማልክት ፡ ታመልኳቸውና ፡ ትሰግዱላቸው ፡ ዘንድ ፡ አትከተሉ ። በእጃችሁም ፡ ሥራ ፡ አታስቆጡኝ ፡ ክፉ ፡ እንዳላደርግባችሁ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ በጃችሁ ፡ ሥራ ፡ ታስቆጡኝ ፡ ዘንድ ፡ አልሰማችሁም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ።

(መ ፡) ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፬ ፡ የጠቀስከው ፡ በማን ፡ አፌዛችሁ ፡ አፋችሁን ፡ በማን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከፊታችሁ ፡ ምላሳችሁን ፡ አስረዘማችሁ ፡ እላንተ ፡ የዓመፃ ፡ ልጆች ፡ አይደላችሁምን? አሰተኛ ዘር ። በጽኑ ፡ ምኞት ፡ ወደ ፡ አማልክት ፡ ትሮጣላችሁ ፡ ከለመለመው ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ሕፃናቱን ፡ የምታርዱ ፤ በፈሳሽ ፡ ወኃ ፡ አጠገብ ፡ ከደንጊያ ፡ ስንጣቂ ፡ በታች ። በፈሳሽ ፡ አጠገብ ፡ ያሉ ፡ ልዝብ ፡ ደንጎች ፡ ፈንታሽ ፡ ናቸው ። ርሳቸው ፡ ዕፃሽ ፡ ናቸው ። ለርሳቸውም ፡ የመጠጥ ፡ መሥዋዕት ፡ አፈሰሽ ፡ የእህልንም ፡ ቍርባን ፡ አቀረብሽ ፡ በዚህ ፡ ደስ ፡ ይበለኝን?አለ፡እግዚአብሔር ፤ ይላል ። የሚከተሉትም ፡ ቃላት ፡ ይህኑ ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ።

ምነው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ሐሰት ፡ ስትናገር ፡ አታፍርምን ፤ የእግዚአብሔርስ ፡ መንግሥት ፡ በስብቅ ፡ የሚወረስ ፡ መሰለኽን ። እስቲ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ምእመናን ፡ ልጆቻቸውን ፡ በየትኛው ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ለጣዖት ፡ ሲያርዱ ፡ አየህ ፤ በየትኛውስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፤ መጽአ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ ይጠባሕ ፡ ተብሎ ፡ ከተነገረለት ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀር ፡ የማን ፡ ጻድቅ ፡ ሥጋ ፡ የማን ፡ ጻድቅ ደም ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ ሲቀርብ ፡ የት ፡ አየህና ፤ ትዋሻለህ ፡ ይህንም ፡ በመናገርህ ፡ ወሰበሂ ፡ ይነብብ ፡ ሐሰተ ፡ እምዚአሁ ፡ ይነብብ ፡ እስመ ፡ ሐሳዊ ፡ ውእቱ ፡ ወአቡሃ ፡ ለሐሰት ፡ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፬ ፡ የተባልክ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ብል ፡ ቅር ፡ ይልሃልን ፤ አይልህም ።

እነ ፡ ኢሳይያስ ፡ ይህን ፡ በጻፉበት ፡ ዘመን ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ነበረች ፡ እስራኤልም ፡ ያከብሯት ፡ ይሰግዱላት ፡ ነበረ ፡ ለምን ፡ ለታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ሰገዳችሁ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ ለምን ፡ አከበራችሁ ፡ ሲሉ ፡ የጻፉት ፡ መሰለህን ? ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ የሚያናግርህ ፡ በታቦተ ፡ እግዚአብሔርና ፡ በጣዖታት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ባታውቀው ፡ ባትረዳው ፡ ነውና ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ፡ ብትመለከት ፡ ወመኑ ፡ ዘይዴምር ፡ ታቦተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ሲል ፡ ታገኘው ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ማንበብ ፡ እንጂ ፡ ማስተዋል ፡ አትችልም ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንስ ፡ ነቢያትን ፡ ሐዋርያትን ፡ በታቦተ ፡ እግዚአብሔርና ፡ በጣዖት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ዘርዝረው ፡ አስረድተው ፡ ፍጡር ፤ ከማምለክ ፡ ለጣዖት ፡ ከመስገድ ፡ ስላዳኗት ፡ ትወዳቸዋለች ፡ ታከብራቸዋለች ፡ እንጂ ፡ አማልክት ፡ ናቸው ፡ ብላ ፡ አታምንባቸውም ።

(ሠ ፡) በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፲፫ ፡ ቍጥር ፡ የጠቀስከው ፡ ወዳንቺ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ኹሉን ፡ ነፋስ ፡ ይወስዳቸዋል ፡ ነፋስ ፡ ይነጥቃቸዋል ፡ ይላል ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፤ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ጉባኤ ፡ ዘሐዋርያት ፡ የተባለችቱ ፡ ጉባኤ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ጉባኤ ፡ አደለችም ። ይች ፡ ጉባኤ ፡ የምትበተን ፡ ከኾነ ፡ ወዲበ ፡ ዛቲ ፡ ኰኵሕ ፡ አሐንፃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንየ ፡ ወአናቅጸ ፡ ሲኦልኒ ፡ ኢይኄይልዋ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ታበለ ፤ ፈረሰ ፡ ማለት ፡ ነዋ ፡ ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፡ ኢሳይያስም ፡ ከተበታኞች ፡ አንዱ ፡ እርሱ ፡ ስለኾነ ፡ ይህን ፡ ትንቢት ፡ የተናገረ ፡ ስለራሱ ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ማለትህ ፡ ነው ። የምትናገ



ረው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በእውነት ፡ እንዲህ ፡ ፈራሽ ፡ ኸኖ ፡ ይገኛል ፡ እንጂ ፡ ቀዋሚ ፡ ኸኖ ፡ አይገኝም ።

፬ ስለዚህ ፡ አትናቴዎስ ፡ በቅዳሴው ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ገሥጽዎ ፡ ለኃጥእ ፡ ከመ ፡ እኩከሙ ፡ ዝልፍዎ ፡ በግኅደት ፡ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ፡ መዐድዎ ፡ ለዘጌገየ ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ ኪያሃ ፡ ፍኖተ ፡ ወይትጋነይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይስረይ ፡ ሎቱ ፡ ይላል ፡ ብለህ ፡ ጠቅሰሃል ።

፬ ፡ አትናቴዎስ ፡ አንተ ፡ ጣዖታት ፡ እያልክ ፡ ከምትሰድባቸው ፤ እኛ ፡ አባቶቻችን ፡ አማላጆቻችን ፡ እያልን ፡ ከምናከብራቸው ፡ ከቅዱሳን ፡ አንዱ ፡ ነው ።

(ሀ) እርሱ ፡ ቅዱሳን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ እንዲያማልዱ ፡ ሲያስረዳ ፡ አሜሃ ፡ ሰአሉ ፡ ለነ ፡ አስተምሕሩ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይምሐረነ ፡ ወይሣሃለነ ፡ አኮ ፡ በሥጋነ ፡ አላ ፡ በሥጋከሙ ፡ አኮ ፡ በከመ ፡ ምግባሪነ ፡ ርኵስት ፡ አላ ፡ በከመ ፡ ምሕረቱ ፡ ለአምላክነ ፡ ብሏል ፡ ቍ ፡ ፺ ።

(ለ) ሕያዋንም ፡ ለሙታን ፡ መጸለይ ፡ እንደሚገባቸው ፡ ሲያስረዳ ፡ ንስእለከ ፡ እግዚኦ ፡ ወናስተበቍዓከ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ አበዊነ ፡ ወአኃዊነ ፡ ወፈለሱ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፤ ኃላፊ ፡ ከመ ፡ ታዕርፎሙ ፡ ሠናየ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ንጹሕ ፡ እምርስሐት ፡ በቅድሜከ ፡ ብሏል ፡ ቍ ፡ ፺፪ ።

(ሐ) ከሰንበትም ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ በዓላት ፡ እንዳሉ ፡ ሲያስረዳ ፡ ንዑ ፡ ናዕብያ ፤ ንዑ ፡ ንወድሳ ፤ ንዑ ፡ ናክብራ ፡ ንዑ ፡ ናብዕላ ፡ ለበኵረ ፡ በዓላት ፡ ብሏል ፡ ቍ ፡ ፶፭ ።

ይህንን ፡ ቃሉን ፡ የምትቀበለው ፡ ከኾንክ ፡ አንተም ፡ አንድ ፡ ልጁ ፡ መኾንህ ፡ ነውና ፡ በውነት ፡ ጥፋት ፡ ካየህብን ፡ ልትገሥጸን ፡ ልትመክረን ፡ ይገባሃል ፡ ይህን ፡ የማትቀበል ፡ ከኾንክ ፡ ግን ፡ ገሥጽዎ ፡ ዝልፍዎ ፡ መዐድዎ ፡ የተባልን ፡ ሕጉን ፡ የተከተልን ፡ እኛ ፡ ነን ። ለኀጥእ ፤ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ፤ የተባልክ ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ ይህችን ፡ ሥራህን ፡ ትተው ፡ ዘንድ ፡ እንመክርሃለን ፡ እናስተምርሃለን ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ግን ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይትቃረንዋ ፡ ለሕግነ ፡ ሠሩ እምድር ፡ ዝክሮሙ ፡ ወኢትጽሐፍ ፡ ስሞሙ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኢየኀብሩ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንከ ፡ ቅድስት ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ስቅል ፡ ውስተ ፡ ክሣውዲሆሙ ፡ ጋጋ ፡ ዘእሳት ፡ ወቦቱ ፡ ይስሐቡ ፡ ውስተ ፡ ዐቢይ ፡ ሰይል ፡ እያለ ፡ ይጸልይብሃል ፡ እኛም ፡ እንደርሱ ፡ እንጸልይብሃለን ፡ እንጂ ፡ አንቀበልህም ።

እርሱም ፡ ገሥጽ ፤ ዝልፍ ፤ አይልህምና ፡ ይህ ፡ አጠቃቀስህ ፡ አጭበርባሪ ፡ ያሰኛሃል ፤ ሰራቂ ፡ ሐሳዊ ፡ ቍ ፡ ፰ ፡ ከተባሉት ፡ ያስቈጥርሃል ።

፭ ፮ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፳ ፡ የጠቀስከው ፡ በቁሱ ፡ ላይ ፡ ፪ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ምስክር ፡ ካልመሰከሩበት ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፡ ሰምተህ ፡ አትፍረድበት ፡ ከመሰከሩበት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በድሎ ፡ ቢገኝ ፡ ሌላው ፡ ይፈራ ፡ ዘንድ ፡ በጉባኤ ፡ ፍረድበት ፡ ይላል ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፣ ፪ ፣ ተሰሎ ፣ ፫ ፣ ፲፬–፲፭ ፣ የጠቀስከውም ፣ ካላንተ ፣ በዚህ ፣ ክታብ ፣ ለጻፍነው ፣ ነገር ፣ የማይታዘዝ ፣ ሰው ፣ ቢኖር ፣ ያፍር ፣ ዘንድ ፣ ተለዩት ፣ አትገናኙት ። ነገር ፣ ግን ፣ እንደ ፣ ወንድም ፣ ገሥጹት ፣ እንጂ ፣ እንደ ፣ ጠላት ፣ አትዩት ፣ ይላል ።

ቅዱስ ፣ ጳውሎስ ፣ ይህነን ፣ የጻፈ ፣ ራሳቸው ፣ ከመዘለፍ ፣ ከመገሠጽ ፣ ወጥተው ፤ ሌላውን ፣ ለመገሠጽ ፣ ለመዝለፍ ፣ በቅተው ፣ ለተገኙ ፣ ለነጢሞቴዎስ ፣ ነው ፤ እንጂ ፣ አንተማ ፣ ባንደኛ ፣ አንቀጽ ፣ (ሀዋ፳ ፣ ፳፯–፴፪ ፣ እንደጻፍኩልኽ ፣ ለመገሠጽ ፣ ለመዘለፍ ፣ በቅተህ ፣ ተገኝተህ ፣ ተፈጽሞብሃልና ፣ ልትጠቀሰው ፣ አይገባህም ።

፯ ያገሬ ፣ ሕዝብ ፣ የተሰቀለውን ፣ ክርስቶስን ፣ ብቻ ፣ እውነተኛው ፣ መድኃኒት ፣ አምኖ ፣ እንዲድንልኝ ፣ በማለት ፣ ነኝ ፣ እስከዚህ ፣ ድረስ ፣ ደፍሬ ፣ የጻፍኩኝ ፣ እንጂ ፣ ልስድብ ፣ ብዬ ፣ ወይም ፣ ልነቅፍ ፣ ብዬ ፣ እንዳል ጻፍኩት ፣ ጀምረህ ፣ እስከ ፣ መጨረሻው ፣ ብታነበው ፣ ቅዱስ ፣ ዳዊት ፣ ቅንዓት ፣ ቤትከ ፣ በልዐኒ ፣ እንዳለ ፣ እኔንም ፣ እንዲሁ ፣ የጤፍ ፣ ፍሬ ፣ በማያህል ፣ በትንሹ ፣ በቅሜ ፣ የቤቱ ፣ ቅንዓት ፣ አስገድዶ ፣ እንዳጻፈኝ ፣ ትረዳዋለህ ፣ ትላለህ

እንግዲህ ፣ በመጻሕፍት ፣ የሚያላግጡ ፣ ከሐዲዎች ፣ ተጠራጣሪዎች ፣ ዕረያዎች ፣ ማለትን ፣ ከምስጋና ፣ ቆጠርከውን ።

ይልቁንም ፣ ደግሞ ፣ ከዚህ ፣ የባሰ ፣ እውነተኛ ፣ መድኃኒት ፣ ክርስቶስ ፣ ብቻ ፣ መኾኑን ፣ በማመን ፣ ከዓለም ፣ ቅድሚያ ፣ ያለውን ፣ ሕዝብ ፣ የክርስቶስን ፣ መድኃኒትነት ፣ ያላመነ ፣ አይሁዳዊ ፤ ወይም ፣ ዐረማዊ ፣ አድርገኸው ፤ እውነተኛው ፣ መድኃኒት ፣ ክርስቶስን ፣ አምኖ ፣ እንዲድንልኝ ፣ የክርስቶስ ፣ የወንጌሉ ፣ ጣዕም ፣ በቀምሳቸው ፣ የልማድና ፤ የድንቁርና ፣ መጋረጃ ፣ ብገልጽላቸው ፣ ከማለት ፣ የበለጠ ፣ ስድብ ፣ አለን ?

በእውነት ፣ የቤቱ ፣ ቅንዓት ፣ አድሮብህስ ፣ ቢኾን ፣ የያዕቆብ ፣ ፈጣሪ ፣ የእግዚአብርሔርን ፣ ማደሪያ ፣ እስካገኝ ፣ ድረስ ፣ ወደቤቴ ፣ ውስጥ ፣ አልገባም ፣ ወደአልጋየ ፣ ወደ ፣ ምንጣፌ ፣ አልወጣም ፣ ላይኖቼ ፣ ዕንቅልፍን ፣ ለቅንድቦቼ ፣ ሽልብታን ፣ ለሰውነቴ ፣ ዕረፍትን ፣ አልሰጥም ፣ እያልክ ። ወቀፃዕክዋ ፣ በጾም ፣ ለነፍስየ ፣ እስከማለት ፣ ደርሰህ ፣ የታቦተ ፣ እግዚአብሔርንና ፤ የቅዱሳንን ፣ ክብር ፣ ተረድተኸው ፣ አቤቱ ፣ አንተ ፣ ከኀይልህ ፣ ታቦት ፣ ጋራ ፣ ወደ ፣ ዕረፍትህ ፣ ተነሣ ፣ ካህናቶችህ ፣ ጽድቅ ፣ ይልበሱ ፣ ቅዱሳንኽም ፣ ዕልል ፣ ይበሉ ፣ እያልክ ፤ ባመሰገንክ ፣ ነበረ ፣ እንጂ ፣ እንዲህ ፣ በመንፈስ ፣ ጽርፈት ፣ እየተመራህ ፣ የስድብ ፣ መጽሐፍ ፣ እንድትጽፍ ፣ ባላስገደደህም ፣ ነበረ ። መዝ ፣ ፻፴፩ ፣ ፲ ፣ ፪፴፪ ፣ ፫-፲ ።

ሰው ፣ በፈቃዱ ፣ ከሚፈተነው ፣ በቀር ፣ እግዚአብሔር ፣ ማንንም ፣ ቢኾን ፣ በክፉ ፣ ሐሳብ ፣ አይፈትንምና ። ያዕ ፣ ፩ ፣ ፲፫ ።

፰ ወንድሞቼ ፣ ሆይ ፣ እስከዚህ ፣ ድረስ ፣ በድፍረት ፣ እያማረርኩኝ ፣ መጻፌ ፣ ግን ፣ አባቶቻችን ፣ ፫፻ ፲ወ፰ ፣ ርቱዓን ፣ ሃይማኖት ፣ በፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ በኹለተኛው ፣ አንቀጽ ፣ መጻሕፍት ፣ ፹ወ፩ ፣ አምላካውያት ፣ የተውልንን ፣ ጠፍተው ፣ በመጻሕፍት ፣ ፈጠራ ፣ ተቀብረው ፣ ተረስተው ፣ ስላየሁ ፣ ነው ፣ ስለምትለው ።

አሁን ፣ እልፍ ፣ ብለህ ፣ በሚከተለው ፣ መሥመር ፣ አንዳንድ ፣ እያልክ ፣ ከቍጥር ፣ እስክታኀላቸው ፣ ድረስ ፤ ሰማንያ ፣ አንድ ፤ መጻሕፍት ፣ ቀድሞ ፣ መኖራቸውን ፣ ኋላም ፣ ፫፻ ፣ ቈጥረው ፣ ማስረከባቸውን አምነሃልና ፣ በማመንህ ፣ አመሰግንሃለሁ ።



፱ ቸሩ ፣ እግዚአብሔር ፣ የጨለማውን ፣ ዘመን ፣ በቃህ ፣ በኀይለ ፣ ሥላሴ ፣ ብርሃን ፣ ሰጥቸሃለሁ ። ሐሰት ፣ ውጣ ፣ እውነት ፣ ግባ ፣ ብሎ ፣ ዐውጆ ፣ ምሕረቱን ፣ በኢትዮጵያ ፣ ስለዘረጋልን ፣ ነው ። ስለምትለው ፣

አንተ ፣ በዚህ ፣ አንቀጽ ፣ ጨለማ ፣ ሐሰት ፣ የምትላቸው ፣ ነገሮች ፣ ለታቦት ፣ ለሥዕል ፣ ለመስቀል ፣ መስገድን ፤ ጻድቃን ፣ ሰማዕታትን ፣ ማክበርን ፤ አዋልድ ፣ መጻሕፍትን ፣ መቀበልን ፣ ነው ።

ግርማዊ ፣ ቀዳማዊ ፣ አፄ ፣ ኃይለ ፣ ሥላሴ ፣ በመንግሥቱ ፣ አስተዳደር ፣ በኩል ፣ ሕዝብና ፣ መንግሥት ፣ ብዙ ፣ ደም ፣ ካልተፋሰሰ ፣ በቀር ፣ በሰላማዊ ፣ መንገድ ፣ ሊቋቋም ፣ አይችል ፣ የነበረውን ፣ ሕገ ፣ መንግሥት ፣ በፈቃዳቸው ፣ አቋቁመው ፤ በያይነቱ ፣ ብዙ ፣ ተማሪ ፣ ቤት ፣ ከፍተው ፤ ወገን ፣ ባለመለያየት ፣ የኢትዮጵያ ፣ ወጣቶችን ፣ ኹሉ ፣ ወደ ፣ እውቀት ፣ ደረጃ ፣ አድርሰው ፣ የኢትዮጵያን ፣ መንግሥት ፣ ከሠለጠኑ ፣ መንግሥታት ፣ ጋራ ፣ ስላስተካከሏትና ፣ በማናቸውም ፣ ረገድ ፣ ራሷን ፣ እንድትችል ፣ ስላደረጓት ፣ ቸሩ ፣ እግዚአብሔር ፣ የጨለማ ፣ ዘመን ፣ በቃህ ፣ ሐሰት ፣ ውጣ ፣ እውነት ፣ ግባ ፣ ብሎ ፣ የምሕረት ፣ ዐዋጅ ፣ መስጠቱ ፣ በእርግጥ ፣ የታመነ ፣ ነው ።

በመንፈሳዊ ፣ አስተዳደር ፣ ግን ፣ ካባቶቻቸው ፣ በወረሷት ፣ በኦርቶዶሳዊት ፣ ሃይማኖት ፣ ጸንተው ፣ ካባቶቻቸው ፣ ሲያያዝ ፣ የመጣውን ፣ የኢትዮጵያን ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ሥርዓት አጽንተው ፣ ቀድሞ ፣ የተተከሉ ፣ ታቦታትን ፣ ያከብራሉ ፤ ታቦት ፣ ባልተተከለባቸው ፣ አውራጃዎች ፣ በጻድቃን ፣ በሰማዕታት ፣ በቅዱሳን ፣ መላእክት ፣ ስም ፣ ይተክላሉ ፤ መጻሕፍተ ፣ ሊቃውንትን ፣ መጻሕፍተ ፣ መነኰሳትን ፣ እስከ ፣ ትርጓሜያቸው ፣ በእጅ ፣ ያጽፋሉ ፤ በማኅተም ፣ ያሳትማሉ ፤ ለታቦት ፤ ለሥዕል ፣ ለመስቀል ፣ እንደሚገባቸው ፣ የጸጋ ፣ ሰጊድ ፣ ይሰግዳሉ ፣ እንጂ ፣ ከቶ ፣ ያንተን ፣ ሐሳብ ፣ የደገፉበት ፤ የቤተ ፣ ክርስቲያናችንን ፣ ሥርዓት ፣ የለወጡበት ፣ ጊዜ ፣ አይገኝም ።

ይህ ፣ አነጋገርህ ፣ የለበጣ ፣ የማታለል ፣ የማስመሰል ፣ መኾኑ ፣ ለማንም ፣ ያልተሰወረ ፣ ጉልህ ፣ ኸኖ ፣ እንደሚታይ ፣ ሌላውም ፣ ጥቅስህ ፣ ኹሉ ፣ እንደዚሁ ፣ የማስመሰል ፣ የማታለል ፣ መኾኑን ፣ አስተዋይ ፣ ልቡና ፣ ሊረዳው ፣ ይችላል ።

፲ እንዲሁም ፣ ዲሞክራሲ ፣ (ሐሳብን ፣ በጽሑፍ ፣ መግለጥ ፣) አዲስ ፣ ዘመን ፣ አመጣሽ ፣ ሳይኾን ፣ በሀገራችን ፣ ጥንታዊ ፣ መኾኑን ፣ አሳስባለሁ ፣ በማለትህ ።

አጻጻፍህ ፣ ያንተን ፣ ሐሳብ ፣ ብቻ ፣ ለመግለጽ ፣ እንጂ ፣ ከመጻሕፍት ፣ ምሥጢር ፣ ግብ ፣ ለመድረስ ፣ አለመኾኑን ፣ አስረድተሃል ። እንግዲህ ፣ ሰው ፣ ሐሳቡን ፣ በጽሑፍ ፣ መግለጡ ፣ ከሱ ፣ የተሻለ ፣ ተመልካች ፣ አይቶ ፣ መልካም ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ቢቀበለው ፣ ሊጸናበት ፣ መጥፎ ፣ ሐሳብ ፣ ነው ፣ ተው ፣ ቢለው ፣ ሊመለስ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በስሕተቱ ፣ እንደጸና ፣ ሊቀር ፣ አደለምና ፣ ይህ ፣ አጻጻፍህ ፣ መጻሕፍትን ፣ መንገዳቸውን ፣ አስለቅቆ ፣ ምሥጢራቸውን ፤ አጥፍቶታል ። የሰው ፣ ሐሳብ ፣ መጻሕፍትን ፣ ሊከተል ፣ እንጂ ፣ መጻሕፍት ፣ የሰውን ፣ ሐሳብ ፣ ሊከተሉ ፣ አገባብ ፣ አደለምና ፣ ይህን ፣ መጥፎ ፣ ሐሳብክን ፣ ተውው ፣ ይቅርብህ ።

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ ስሥዕልና ፡ ምስልን ፡ ሲነቅፍ ፡ ዐይን ፡ ቦሙ ፡ ወኢይሬእዩ ። እዝነ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይሰ ምዑ ። አንፍ ፡ ቦሙ ፡ ወኢያጼንዉ ። እድ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይገሥሡ ። ወኢይነቡ ፡ በጎራዒቶሙ ፡ ወአልቦ ፡ መን ፈስ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡ ከማሆሙ ፡ ለይኩኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ገብርዎሙ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይትዌከሉ ፡ ቦሙ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ፻፴፭፡ ጠቅሰሃል ።

አንተ ፡ ነገር ፡ ጐንጭሮ ፡ መነሣት ፡ ልማድህ ፡ በመኾኑ ፡ ጐንጭፈህ ፡ ተነ ሥተህ ፡ ስለ ፡ ሥዕል ፡ አድርገህ ፡ ትጠቅሰዋለህ ፡ እንጂ ፡ እሱስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ መሥመር ፡ ከፍ ፡ ብለህ ፡ ብትመለከተው ፡ አማልክቲሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ብሎ ፡ ለይቶ ፡ ስለ ፡ ጣዖታት ፡ እንደተናገረው ፡ ስለ ፤ ሥዕል ፡ እንዳልተናገረው ፡ ትረዳው ፡ ነበረ ።

ለእግዚአብሔርና ፡ ለወዳጆቹ ፡ ለቅዱሳን ፡ መታሰቢያ ፡ ተብሎ ፡ የተሠራ ፡ ምስል ፤ የተሣለ ፡ ሥዕል ፡ እንዳይነቀፍ ፡ ልታውቅ ፡ አትወድም ፡ እንጂ ፡ ብትወ ድስ ፡ (ዘፀአት ፡ ፴፯ ፡ ፯ ፡) ኹለቱንም ፡ ኪሩቤል ፡ ከተመታ ፡ ወርቅ ፡ አደረገ ፤ በመ ክደኛው ፡ ፪ወገን ፡ አንዱን ፡ ኪሩብ ፡ ከአንዱ ፡ ዳር ፤ ኹለተኛውንም ፡ ኪሩብ ፡ ከኹለተኛው ፡ ዳር ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ኹለቱንም ፡ ኪሩቤል ፡ ከሥርየቱ ፡ መክ ደኛ ፡ በላይ ፡ ሠራ ። በ፪ቱ ፡ ወገን ኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸውን ፡ በላይ ፡ ዘርግ ተው ፡ የሥርየቱን ፡ መክደኛ ፡ በክንፎቻቸው ፡ ሰወሩ ። ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ መክ ደኛው ፡ አዘንብለው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይታያዩ ፡ ነበሩ ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ።
አሁን ፡ ከዚህ ፡ ኪሩቤል ፡ የሚላቸው ፡ ለሕያዋን ፡ ኪሩቤል ፡ መታሰቢያ ፤ ሊኾኑ ፡ በሕያዋን ፡ ኪሩቤል ፡ አምሳል ፡ ባስልኤል ፡ የቀረፃቸው ፡ ምስሎች ፤ የሣ ላቸው ፡ ሥዕሎች ፡ አደሉምን ።

ኹለተኛም ፡ ነገ ፡ ቀዳ ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፳፫ ፡ በራእዩም ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ከወይራ እንጨት ፡ ኹለቱን ፡ ኪሩቤል ፡ ሠራ ፤ ቁመታቸውን ፡ ፲ ፡ ክንድ ፡ አደረገ ፤ የኪሩ ብም ፡ አንድ ፡ ክንፍ ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ እርሱም ፡ አሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ካንዱ ፡ ክንፍ ፡ ዳር ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኹለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ዳር ፡ ድረስ ። ለኹለተ ኛው ፡ ኪሩብ ፡ ደግሞ ፡ ፲ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፡ የኪሩቤልም ፡ ልክና ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ልክና ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ነበረ ። ያንዱ ፡ ኪሩብ ፡ ቁመቱ ፡ ፲ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፡ የኹለተኛውም ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ። ኪሩቤልንም ፡ በውስጥ ፤ ባለው ፡ ቤት ፡ መሃ ከል ፡ አደረገ ። ኪሩቤልም ፡ ክንፋቸው ፡ የተዘረጋ ፡ ያንዱም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ናሱን ፡ የነካ ፡ ነበረ ። የኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ኹለተኛውን ፡ ናስ ፡ የነካ ፡ ነበረ ። ኹለቱም ፡ ክንፎቻቸው ፡ በመቅደሱ ፡ መካከል ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተቃረቡ ፡ ነበሩ ። ኪሩቤልንም ፤ በወርቅ ፡ ለበጠ ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኪሩቤል ፡ የሚላቸው ፡ ለሕያዋን ፡ ኪሩቤል ፡ መታሰቢያ ፡ ሊኾኑ ፡ በሕያዋን ፡ ኪሩቤል ፡ አምሳል ፡ ሰሎሞን ፡ ጠቢባኑን ፡ ያስቀረፃቸው ፡ ምስሎች ፡ ያሣላቸው ፡ ሥዕሎች ፡ አደሉምን ። ሕያዋን ፡ ኪሩቤልስ ፡ በኒህ ፡ ቅር ፆች ፡ ላይ ፡ በረድኤት ፡ ከማደር ፡ በቀር ፡ ሰማያዊ ፡ ቦታቸውን ፡ ለቀው ፡ መጥተው ፡ በአካል ፡ የሚታዩ ፡ ይመስልሃልን ።



ዳዊትም ፡ ሥዕለ ፡ ኪሩብ ፡ የተሣለባትን ፡ ታቦት ፡ ያከብር ፡ እንደነበረ ፡ ልታውቅ ፡ ብትወድ ፤ ሳሙ ፡ ካል ፡ ፯ ፡ ፪—፲፯ ፡ ተመልከት ፡ ዳዊት ፡ ከርሱ ፡ ጋራም ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ዕፃ ፡ ካለች ፡ ከባዕሌ ፡ ሀገር ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተጠራባትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ተነሡ ። የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ በዲሱ ፡ ሠረገላ ፡ ጫኑ ። ከአሚናዳብ ፡ ቤት ፡ በኮረፍታ ፡ ላይ ፡ ከነበረው ፡ አመጡት ። የአሚናዳብም ፡ ልጆች ፡ ዑዛና ፡ አሂዮ ፡ አዲሱን ፡ ሠረገላ ፡ ይነዱ ፡ ነበረ ።

በኮረፍታ ፡ ላይ ፡ ከሚኖረውም ፡ ከአሚናዳብ ፡ ቤት ፡ ባነሡት ፡ ጊዜ ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ አጠገብ ፡ ሔዱ ። አሂዮም ፡ በታቦት ፡ ፊት ፡ ይሔድ ፡ ነበረ ። ዳዊትና ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥድ ፡ በተሠራ ፡ ዕቃ ፤ በበገና ፤ በመሰንቆ ፤ በነጋሪትና ፡ በጸናጽልም ፡ ይጫወቱ ፡ ነበረ ። ወደናኮንም ፡ ዐውድማ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ዑዛ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፤ የእግዚአ ብሔርንም ፡ ታቦት ፡ የያዙ ፡ ላሞች ፡ ይፋንኑ ፡ ነበረና ። እግዚአብሔርም ፡ በዑዛ ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ፡ ስለድፍረቱም ፡ ቀሠፈው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ዘንድ ፡ ከዚያው ፡ ሞተ ። ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ ዑዛን ፡ ስለሰበረው ፡ አዘነ ። ያንም ፡ ስፍራ ፡ የዑዛ ፡ ስብራት ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። ዳዊትም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ እንዴት ፡ ወደኔ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈራ ፡ እያለ ፡ መላልሶ ፡ ያስረዳሃል ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ተጨንቆ ፡ ተጠበ ፡ የሚፈራውን ፡ የሚያከብረውን ፡ የቅዱሳንን ፡ ሥዕል ፡ አፍ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይነቡ ፡ ብሎ ፡ ነቀፈ ፡ እያልክ ፡ የጣዖታቱን ፡ ዘለፋ ፡ ለጌታችን ፡ ለእመቤታችን ፡ ሥዕል ፡ ሰጥተህ ፡ ስትናገር ፡ አታፍርምን ።?

እንዲህስ ፡ ያልኾነውን ፡ ኾነ ፤ ያልተደረገውን ፡ ተደረገ ፡ እያልክ ፡ በማስመ ሰል ፡ ብትናገር ፤ ምንተ ፡ ይሁብከ ፡ ወምንተ ፡ ይዌስኩከ ፡ በእንተ ፡ ከናፍረ ፤ ጕሓ ሉት ። በከዳተኛ ፡ ከንፈር ፡ ከዳት ፡ ሽንገላ ፡ ብትናገር ፡ ሥላሴ ፡ ምን ፡ ይሰጡሃል ? ምንስ ፡ ይጨምሩልሃል ? እያሰኘ ፡ ያስወቅስሃል ፡ እንጂ ፡ ዋጋ ፡ የሚያሰጥህ ፡ መሰ ለህን ? መዝ ፡ ፻፳፫ ። የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በማስመሰል ፡ የሚገባበት ፡ አይደለም ።
፱ ሰው ፡ ደግሞ ፡ እውነት ፡ መስሎት ፡ ሥዕል ፡ አፍ ፡ አውጥቶ ፡ ይናገራል ፡ ላብና ፡ ደምም ፡ ይወጣዋል ፡ ብሎ ፡ ጽፏል ፡ እያልክ ።

እመቤታችን ፡ ጼዴንያ ፡ በምትባል ፡ ሀገር ፡ ያደረገችውን ፡ ተአምራት ፡ ትነቅ ፋለህ ፡ ታስተባብላለህ ። ንባብ ፡ ግእዛን ፡ የሌላቸው ፡ ፍጥረቶች ፡ ኹሉ ፡ በተአም ራት ፡ እንዲነጋገሩ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ተናግረዋል ።

ከነዚኽውም ፡ አንዱ ፡ የበለዓም ፡ አህያ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አፍ ፡ አውጥታ ፡ ተና ግራ ፡ በለዓምን ፡ ዘልፋዋለች ፡ ዘኊ ፡ ፳፪ ፡ ፳፰ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።
፪ተኛም ፡ በዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ ንጽሐ ፡ ጠባይዕ ፡ ያላደፈባቸው ፡ ቅናት ፡ ምቀ ኛት ፡ የሌለባቸው ፡ ሕፃናት ፡ ሆሣዕና ፡ በዓርያም ፡ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ፣ እያሉ ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ሰምተው ፡ ቅናት ፡ ምቀኝነት ፡ የተመሉ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ የሕፃናቱ ፡ ምስጋና ፡ ደስ ፡ አላሰኛቸው ፡ ብሎ ፡ ምነው ፡ አትቈጣቸውምን ፡ ቢሉት ፡ ንባብ ፡ ግእዛን ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ዝም ፡ ይበሉ ፡ ካላችሁ ፡ እኒህ ፡ ደንጋዮች ፡ ያመስግኑ ፡ ብሎ ፡ ቢያዝዝ ፡ ደንጋዮች ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ አመስግነዋል ፡ ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፵ ።

እንግዲህ ፡ አኽያና ፡ ደንጋይ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አፍ ፡ አውጥተው ፡ ሲናገሩ ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡ የወላዲተ ፡ አምላክ ፡ የእመቤታችን ፡ መታሰቢያ ፡ ሥዕለ ፡ ማርያም ፡ አፍ ፡ አውጥታ ፡ ተናገረች ፡ ቢባል ፡ ብርቁ ፡ ድንቁ ፡ ምንድን ፡ ነው ፤ የእመቤታችን ፡ ሥዕል ፡ ከበለዓም ፡ አህያና ፡ ከቢታንያ ፡ ደንጋይ ፡ ታንሣለችን ።

ይህም ፡ ተአምራት ፡ የተደረገ ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ ተግባር ፡ አድርጎ ፡ ለሚኖር ፡ አባ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለሚባል ፡ መነኰሴና ፤ እንደ ፡ አብርሃም ፡ ተወክፎ ፡ ነግድን ፡ ተግባር ፡ አድርጋ ፡ ለምትኖር ፡ ማርታ ፡ ለምትባል ፡ ሴት ፡ ነው ፡ ስንክሳር ፡ መስከረም ፡ ፲ ።

ጾም ፡ ጸሎትስ ፤ ወዝንቱ ፡ ዘመድ ፡ ኢይወፅእ ፡ ዘእንበለ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ። ተብሎ ፡ የተነገረለት ፡ ደገኛ ፡ ሥራ ፡ አይደለምን ፤ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ፡ ተወክፎ ፡ ነግድስ ፤ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ይልቅ ፡ ሥላሴን ፡ በአብርሃም ፡ ቤት ፡ እንግዳ ፡ ኹኖ ፡ ለማደር ፡ ያደረሰ ፡ ደገኛ ፡ ሥራ ፡ አይደለምን ፤ ዘፍ ፡ ፲፰ ፡ ፩-፲፰ ።

በጾም ፡ በጸሎት ፡ በተወክፎ ፡ ነግድ ፡ ጸንተው ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ተአምራት ፡ ቢደረግላቸው ፡ ብርቁ ፡ ድንቁ ፡ ምንድን ፡ ነው ።

በዚያውስ ፡ ላይ ፡ በማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ታህል ፡ ሃይማኖት ፡ ካለቻችሁ ፡ ይህነን ፡ ተራራ ፡ ከዚህ ፡ ወደዚያ ፡ ተነሣ ፡ ብትሉት ፡ ይነሣል ፡ የሚሳናችሁ ፡ የለም ፡ ተብሎ ።

በ፳፩ ፡ ም ፡ በ፳፩ ፡ ቍጥርም ፡ እንደዚሁ ፡ ሃይማኖት ፡ ካላችሁ ፡ ካልተጠራጠራችሁ ፡ ተአምራት ፡ የሚደረግላችሁ ፡ በበለስ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ይህነን ፡ ተራራ ፡ ተነሥተህ ፡ ወደባሕር ፡ ግባ ፡ ብትሉት ፡ ይደረግላችኋል ፡ ተብሎ ።

በማርቆስም ፡ ፲፮ ፡ በስሜ ፡ ያመኑትን ፡ ሰዎች ፡ ይች ፡ ተአምራት ፡ ትከተላቸዋለች ፡ ትደረግላቸዋለች ፡ ተብሎ ።

በሉቃስም ፡ ፲፯ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ተሃክል ፡ ሃይማኖት ፡ ብትኖራችሁ ፡ ይችን ፡ ሾላ ፡ ዛፍ ፡ ከሥርሽ ፡ ተነቅለሽ ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ተተከይ ፡ ብትሏት ፡ ትታዘዝላችኋለች ፡ ተብሎ ።

በዮሐንስም ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ፡ በኔ ፡ ያመነ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ ከዚያም ፡ የሚበልጥ ፡ ያደርጋል ፡ ተብሎ ፡ በጌታ ፡ ቃል ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታበለን ።

እኛስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማይታበል ፡ ቃሉ ፡ በነገረን ፡ ኹሉ ፡ እናምናለንና ፡ ይህ ፡ ታምራት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ እናምናለን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በሱ ፡



ስም ፡ አምኖ ፡ ያለመነው ፡ ኹሉ ፡ እንዲደረግለት ፡ እናምናለን ። አንተ ፡ ግን ፡ ስለሃይማኖትህ ፡ ጐደሎነት ፡ አይደረግልህም ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ።

፲ እኔም ፡ እንደዚሁ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ከልኹነ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ የለም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀርም ፡ ሌላ ፡ የሚያድን ፡ የለም ፡ ብዬ ፡ ሐሳቤን ፡ ብገልጥ ፡ ድፍረት ፡ ወይም ፡ ስሕተት ፡ የሚቈጠርብኝ ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም ፡ ስለምትለው ።

ድፍረትህና ፡ ስሕተትህ ፡ ነቢያት ፡ በትንቢት ፤ ሐዋርያት ፡ በስብከት ፤ የደከሙበትን ፤ እኛም ፡ በስሙ ፡ አምነን ፡ ወልድ ፡ በመባሉ ፡ ውሉድ ፤ ክርስቶስ ፡ በመባሉ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብለን ፡ የተጠራንበትን ፤ የክርስቶስን ፡ ሕይወትነት ፡ ከአንተ ፡ ሐሳብ ፡ የመነጨ ፡ አስመስለህ ፡ ከክርስቶስም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚያድን ፡ የለም ፡ ብዬ ፡ ሐሳቤን ፡ ብገልጥ ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከክርስቶስ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሕይወት ፡ የለም ፡ ማለትህ ፡ ከድፍረት ፡ ከስሕተት ፡ ገብቶ ፡ አይቈጠርብህም ።

፲፩ ግባ ፡ ሐዋ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ፡ የጠቀስከውም ፡

በደንብ ፡ የተጠቀሰ ፡ ነው ፡ እኛም ፡ ከክርስቶስ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ ብለን ፡ ለራሳችንም ፡ አናምንም ፡ ለሌላውም ፤ አናስተምርም ። ቅዱሳንንም ፡ ብናከብራቸውና ፡ ብንወዳቸው ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ኢይብለክሙ ፡ አግብርትየ ፡ አላ ፡ አዕርክትየ ፡ ብሎ ፡ የሰጣቸውን ፡ ክብር ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ የጸጋ ፡ ክብር ፡ እናከብራቸዋለን ። እንጂ ፡ የባሕርይ ፡ አማልክት ፡ ብለን ፡ አናከብራቸውም ።

በችግራችንም ፡ ጊዜ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ አምላከ ፡ አብርሃም ፡ ወአምላከ ፡ ይስሐቅ ፡ ወአምላከ ፡ ያዕቆብ ፡ ብሎ ፡ በነገረን ፡ መሠረት ፤ በእንተ ፡ አብርሃም ፡ ፍቁርከ ፤ ወበእንተ ፡ ይስሐቅ ፡ ቍልዔከ ፤ ወበእንተ ፡ እስራኤል ፡ ቅዱስከ ። አምላከሙ ፡ ለአበዊነ ፡ ርድአነ ፤ ስምዐነ ፡ እያልን ፡ የነሱን ፡ ስም ፡ እየጠራን ፡ እሱን ፡ እንለምነዋለን ፡ እንጂ ፡ ቅዱሳንን ፡ የክርስቶስ ፡ ተወዳጆች ፡ አድርገን ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ ናቸው ፤ ብለን ፡ አናመልካቸውም ፤ የአምልኮት ፡ ስግደት ፡ አንሰግድላቸውም ።

፲፪ ከብሉያትና ፡ ከሐዲሳት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ የለም ፡ ስለምትለውም ።

ብሉያት ፡ ሐዲሳት ፡ የሚባሉ ፡ አንተ ፡ በሐሳብህ ፡ የወደድካቸውን ፡ ብቻ ፤ መርጠህ ፡ በጥራዝ ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ብለህ ፡ የምትጠራቸው ፡ ፷፯ቱ ፡ ብቻ ፡ አደሉም ።

አንቀጽ ፡ በገጽ ፡ ፪ ፡ መሥመር ፡ ፲፰ ፡ አባቶቻችን ፡ ፫፻፲ወ፰ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በ፪ተኛው ፡ አንቀጽ ፡ መጻሕፍት ፡ የተውልን ፡ ፹ወ፩ዱ ፡ አምላካውያት ፡ መጻሕፍት ፡ ብለህ ፡ ያስታወስካቸው ፡ ፹፩ዱ ፡ ኹሉ ፡ እና ፡ ሌሎችም ፡ ከብሉያት ፡ ከሐዲሳት ፡ ግብ ፡ ሳይወጡ ፡ በብሉያት ፡ በሐዲሳት ፡ የተሰወረውን ፡ ገልጠው ፡ የረቀቀውን ፡ አጕልተው ፡ የሚያስረዱን ፡ የሊቃውንት ፡ መጻሕፍትም ፡ አምላክ ፡ ያጻፋቸው ፡ የአምላክን ፡ ነገር ፡ የሚናገሩ ፡ ስለኾኑ ፡ የሕይወት ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ከብሉያት ፡ ከሐዲሳት ፡ ልዩ ፡ አይደሉም ።

ስለዚህም ፡ የጠቀስከው ፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ። መጻሕፍትም ፡ ተከፈቱ ፡ ሌላውም ፡ መጽሐፍ ፡ ተከፈተ ፡ እርሱም ፡ የሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ብሎ ፡ ኹሉንም ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ ከፍሎ ፡ አልተዋቸውም ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስም ፡ ላገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሳት ፡ ከአምላክ ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ ተጀምሮ ፡ የማይፈጸም ፡ ከንቱ ፡ የኾነ ፡ ምንኩስና ፡ የሚባል ፡ የሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ።

ብለህ ፡ ሕገ ፡ ምንኩስናን ፡ ትነቅፋለህ ፡ ትሰድባለህ ፡ አምላክ ፡ ያልፈቀደው ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሕግ ፡ እንደ ኾነ ፡ ትናገራለህ ፡ ለዚሁም ፡ ምስክር ፡

ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፩—፲፪ ። ፩ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፰—፲፪ ። ጠቅሰሃል ።

ማቴ ፲፱ ፩ ፲፪ የጠቀስከው ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሊፈታተኑት ፡ መምህር ፤ ሰው ፤ ሚስቱን ፡ በበደለችው ፡ ጊዜ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ሊፈታት ፡ ይገባልን ፡ ቢሉት ፤ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ስለፈጠራቸው ፡ ወንድ ፡ ሚስት ፡ ካገባ ፡ በኋላ ፡ እናት ፡ አባቱን ፡ ትቶ ፡ ሚስቱን ፡ ተከትሎ ፡ ይሔዳል ። ስለዚህ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ይባላሉ ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ አይባሉምና ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ያደረጋቸውን ፤ ሰው ፤ ሊለያቸው ፡ አይገባውም ፡ አላቸው ።

እነሱም ፡ መልሰው ፡ እንኪያ ፤ መፍታት ፡ የማይገባ ፡ ከኾነ ፡ ሙሴ ፡ ሚስቱን ፡ የሚፈታ ፡ ሰው ፡ ነውሯን ፡ የሚነግር ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ሰጥቶ ፡ ይፍታት ፡ ለምን ፡ አለ ፡ ቢሉት ፤ ሙሴስ ፡ እንደ ፡ ክፋታችሁ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ሚስታችሁን ፡ እንድትፈቱ ፡ አዘዛችሁ ፡ እንጂ ፡ በተፈጥሮስ ፡ መፋታት ፡ አልነበረም ፤ እኔም ፡ ሚስቱን ፡ ሳትሰስንበት ፡ ሰነፈች ፡ ደረቀች ፡ ብሎ ፡ የፈታ ፤ ስትሰስን ፡ ተገኝታ ፡ በነውር ፡ የተፈታችትንም ፡ ያገባ ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድበታል ፡ ብዬ ፡ እንዲፈረድበት ፡ እውነት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ በባልና ፡ በሚስት ፡ መከከል ፡ ያለውን ፡ የመጋባትን ፡ የመፋታትን ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ፡ እንጂ ፡ የምንኵስናን ፡ ነገር ፡ እነሱም ፡ አልጠየቁት ፡ እሱም ፡ አልመለሰላቸውም ።

እንደዚሁም ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፰-፲፪ ፡ የጠቀስከው ።

ሴት ፡ ለባሏ ፡ ክብሩ ፡ ናት ፡ ሴት ፡ ከወንድ ፡ ተገኝታለች ፡ እንጂ ፡ ወንድ ፡ ከሴት ፡ አልተገኘምና ፡ ሴት ፡ ስለወንድ ፡ ተፈጠረች ፡ እንጂ ፡ ወንድ ፡ ስለሴት ፡ አልተፈጠረም ። ስለዚህ ፡ ለሴት ፡ ሥልጣን ፡ በራስዋ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። አሁንም ፡ ሴት ፡ ከባልዋ ፡ አትለይ ፡ ባልም ፡ ሚስቱን ፡ አይፍታ ፡ እያለ ፡ የባልና ፡ የሚስትን ፡ ተፈጥሯቸውንና ፡ አኗኗራቸውን ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ምንኵስና ፡ ከአምላክ ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ ከንቱ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ መኾኑን ፡ አይናገርም ።

፲፬ ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ ለአዳም ፡ ከፈጠረው ፡ በኋላ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናይ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይንበር ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ ንግበር ፡ሎቱ ፡ ቢጸ ፡ ዘትረድኦ ፡ ብሎ ፡ የምትረዳው ፡ ሔዋንን ፡ ፈጥሮ ፡ ስጠውና ፡ ሙሉ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ ብቻውስ ፡ ጐደሎ ፡ እንደነበረ ፡ ጽሑፍ ፡ ይነግረናል ፡ ብለህ ፡ አዳም ፡ በተፈጥሮ ፡ ሕፀፀ ፡ አካል ፡ ኖሮበት ፡ ሔዋን ፡ ተፈጥራ ፡ ምልዐተ ፡ አካል ፡ የኾነችው ፡ አስመስለህ ፡ ከልብህ ፡ አንቅተህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ትናገራለህ ።

ስለዚህም ፡ የጠቀስከው ፡ ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ አይደለም ፡ የምትረዳው [illegible]



የምትስማማውን ፡ ልፍጠርለት ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ሔዋን ፡ ለአዳም ፡ የኑሮ ፡ ረዳቱ ፡ መኾኗን ፡ እንጂ ፡ በአካሉ ፡ ጐደሎነት ፡ ኖሮበት ፡ እርሷ ፡ ምልዐተ ፡ አካል ፡ እንደኾነችው ፡ አይነግረንም ።

፲፭ ፪ተኛም ፡ ስለዚሁ ፡ ተጨማሪ ፡ አድርገህ ፡ የጠቀስከው ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ።

ሴት ፡ ከባሏ ፡ አትለይ ፡ ባልም ፡ ሚስቱን ፡ አይፍታ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ አዳም ፡ በተፈጥሮው ፡ ሕፀፀ ፡ አካል ፡ ኖሮበት ፡ ሔዋን ፡ ምልዐተ ፡ አካል ፡ እንደኾነችው ፡ አይነግረንም ። ቢኾንም ፡ ሕፀፅህን ፡ አንተው ፡ ራስህ ፡ ተገንዝበኸው ፡ በ፪ተኛው ፡ አንቀጽ ፡ በ፮ ፡ ቍ ፡ በንግግሬ ፡ ብዙ ፡ ጕድለት ፡ ፀያፍ ፡ እንደምታገኝበት ፡ እተማመናለሁና ፡ የጠመመውን ፡ አቅንተህ ፡ የጐደለውን ፡ ሞልተህ ፡ እንድታነብልኝ ፡ አሳስብሃለሁ ፡ ያልከኝን ፡ ባለመዘንጋት ፡ አዳም ፡ ብቻውን ፡ ኸኖ ፡ ሳለ ፡ ኑሮው ፡ ጐደሎ ፡ እንጂ ፡ የተሟላ ፡ ባለመኾኑ ፡ ረዳት ፡ ሔዋንን ፡ ፈጥሮለት ፡ ኑሮው ፡ የተሟላ ፡ ኾኖለት ፡ ብዬ ፡ አርሜ ፡ አንብቤልሃለሁ ።

እንግዲህ ፡ ወደፍሬ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ።

ምንኵስና ፡ ከአምላክ ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ ከንቱ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ፀመፀኛ ፡ ሰው ፡ ከፀመፅ ፡ መዝገብ ፡ ልቡናው ፡ ዓምፅን ፡ አውጥቶ ፤ ይናገራል ፡ ተብሎ ፡ እንደተነገረ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፴፭ ፡ በሞራ ፡ ከተመረገ ፡ ከተለሰነ ፡ ልቡናህ ፡ አንቅተህ ፡ ባልታረመ ፡ አንደበትህ ፡ ትናገራለህ ፡ እንጂ ፡ ከጠቀስካቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ይህንን ፡ መጥፎ ፡ ንግግርህን ፡ የመሰከረልህ ፡ አልተገኘም ። ምንኵስና ፡ ከአምላክ ፡ የተፈቀደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ለማገልገል ፡ የታቀደ ፡ ሕገ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ያስገኘችው ፡ ሕገ ፡ ፍጹማን ፡ መኾኑን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እየጠቀስኩ ፡ በምንኵስና ፡ የተጠቀሙ ፡ አባቶችን ፡ ታሪክ ፡ እየተረክሁ ፡ አስረዳህ ፡ ዘንድ ፡ አለኝና ፡ ልብ ፡ አድርገህ ፡ በማስተዋል ፡ ስማኝ ።

፩ኛ ፡ ክፍል ፡ ስለጥቅሶች ።

ሐዋርያት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ሳትሰስንበት ፡ ሰነፈች ፡ ደረቀች ፡ ብሎ ፡ የፈታ ፤ በነውር ፡ የተፈታችውንም ፡ ያገባ ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድበታል ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ ሰነፈች ፡ ደረቀች ፡ ብሎ ፡ መፍታት ፤ በነውር ፡ የተፈታችቱንም ፡ ማግባት ፡ የማይገባ ፡ ከኾነ ፡ ጥንቱን ፡ አለማግባት ፡ ይሻላል ፡ ቢሉት ፤ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ መኖርስ ፡ ለኹሉ ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ አላመቻሉን ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ አይገባም ፡ አላለም ።

በሚከተለውም ፡ መሥመር ፡ ንጽሕና ፡ ሀብት ፡ ኾኖ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ወይም ፡ ከናታቸው ፡ ማኅፀን ፡ ኅፅዋን ፡ ኾነው ፡ የተወለዱ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ።

ደግሞ ፡ ሰዎች ፡ በግድ ፡ ሰልበው ፡ ኅፅዋን ፡ ያደረጓቸው ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ብሎ ፡ በግድ ፡ የሚከለክሉትን ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ በፈቃዳቸው ፤ የሚከለክሉ ፡ መንከሳትንም ፡ [illegible]ት ፡ ሰማያት ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ ኅፃዋን ፡ ያደረጉ ፡ አሉና ፡ ይህን ፡

www.ethiopianorthodox.org

መፈጸም ፡ የሚቻለው ፡ ይፈጽም ፡ በማለቱ ፡ ምንኵስና ፡ የተገባ ፡ ሕግ ፡ መኾኑን ፡ አስረድቷል ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፫–፲፰ ።

፬ተኛም ፡ ፩ ፡ ባለጸጋ ፡ መጥቶ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ የምወርስበት ፡ ምን ፡ ልሥራ ፡ ቢለው ፡ አትግደል ፡ አትስረቅ ፤ አታመንዝር ፤ በሰት ፡ አትመስክር ፤ አባት ፡ እናትክን ፡ አክብር ፤ በልንጀራህን ፡ እንደራስህ ፡ ውደድ ፡ ብሎ ፡ ሕገ ፡ ርትዕን ፡ አስተማረው ፤ ይህንንስ ፡ ኹሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሬ ፡ ጠብቄዋለሁ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ቀረኝ ፤ ቢለው ፡ ከዚህስ ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ የለም ፡ ሕግን ፡ ፈጽመሃል ፡ ሳይል ፡ ፍጹም ፡ ልትኾን ፡ ከወደድክስ ፡ ያለህን ፡ ኹሉ ፡ ሽጠህ ፡ ለውጠህ ፡ ለነዳያን ፡ መጽውተህ ፡ እኔን ፡ ምሰለኝ ፡ በማለቱ ፡ ሕገ ፡ ፍጹማን ፡ ምንኵስናን ፡ አስተማረው ።

፫ኛ ፡ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ባለጸጋ ፡ ገንዘቡን ፡ ሰጥቶ ፡ መጽውቶ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቆ ፡ ትቶ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይገባል ፡ ከማለት ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ቻልፋለች ፡ ማለት ፡ ይቀላል ፡ ብሎ ፡ በንዳንተ ፡ ያለው ፡ እንቢተኛ ፡ ሲመስልበት ፡ ሕገ ፡ ፍጻሜ ፡ ምንኵስናን ፡ የፈጸመ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እነሆ ፡ እኛ ፡ ኹሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንህ ፡ እንግዲህ ፡ የምናገኘው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ቢለው ፡ ዛሬ ፡ ሰው ፡ በኾንኩ ፤ ጊዜ ፡ የተከተላችሁኝ ፡ እናንተ ፤ ወልደ ፡ አኃለ ፡ እመሕያው ፡ እኔ ፡ ባባቴ ፡ ጌትነት ፡ በተገለጥኩ ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ ኹለት ፡ ወንበር ፡ ተቀምጣችሁ ፡ በሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ትፈርዳላችሁ ፡ ብሎ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ተከፋይነትን ፡ የሚያመለክት ፡ ተስፋ ፡ ሰጠው ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ ስለኔ ፡ ስም ፡ ብሎ ፡ ቤቱን ፡ ንብረቱን ፡ እናቱን ፡ አባቱን ፡ ሚስቱን ፡ ልጆቹን ፡ እኅቶቹን ፡ ወንድሞቹን ፡ ትቶ ፡ የመነነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዕፅፍ ፡ ድርብ ፡ ዋጋ ፡ ያገኛል ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትንም ፡ ይወርሳል ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ለሚነሡ ፡ መናንያን ፡ መነኰሳት ፡ ተስፋውን ፡ ሰጥቷል ።

፩ተኛም ፡ ክርስቶስን ፡ መከተል ፡ በግብር ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ አለመኾኑን ፡ እንዳንተ ፡ ያላወቀ ፡ አንድ ፡ ዓለማዊ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ልከተልህ ፡ ቢለው ፡ ለቀበሮዎች ፡ ጕድጓድ ፤ ለወፎችም ፡ መጠጊያ ፡ ዛፍ ፡ አላቸው ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ራሴን ፡ የማስጠጋበት ፡ የለኝም ፡ በግብር ፡ ላትመስለኝ ፡ ለምን ፡ ትከተለኛለህ ፡ በማለቱ ፡ በኋረ ፡ መናንያን ፡ መኾኑን ፡ አስረድቶ ፡ ካሰናበተው ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስን ፡ መከተል ፡ በግብር ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ አለመኾኑን ፡ ያወቀ ፡ ዓለሙን ፡ የናቀ ፡ በፍቅረ ፡ ክርስቶስ ፡ የተጨነቀ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ አሰናብተኝና ፡ አባቴን ፡ ቀብሬ ፡ መጥቼ ፡ ልከተልህ ፡ ቢለው ምዉታን ፡ ዘመዶችህን ፤ ምውታን ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ይቀብሩዋቸዋል ፡ አንተስ ፡ ኺድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አስተምር ብሎ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስናን ፡ አስተምሮታል ።

እንዲሁም ፡ ፫ተኛ ፡ አንድ ፡ ልቡ ፡ በፍቅረ ፡ ክርስቶስ ፡ የተነካ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቼን ፡ በዚህ ፡ ዋሉ ፡ በዚህ ፡ እደሩ ፡ ብየ ፡ አደራጅቻቸው



ልምጣና ፡ ልከተልህ ፡ ቢለው ፡ ዕርፍ ፡ ይዞ ፡ ወደኋላው ፡ የሚያርስ ፡ የለም ፡ (ከመነኑ ፡ ከመነኰሱ ፡ በኋላ ፡ ሚስት ፡ ላግባ ፡ ቤት ፡ ልሥራ) ፡ ማለት ፡ የለም ብሎ ፡ ሥርዓተ ፡ ምንኵስናን ፡ አስተምሮታል ፡ ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፶፯ ።

፰ተኛም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለልጁ ፡ ሠርግ ፡ ያደረገ ፡ ንጉሥን ፡ ትመስላለች ፡ ብሎ ፡ ምሳሌ ፡ መስሎ ፡ በተናገረበት ፡ አንቀጽ ፡ ለሠርጉ ፡ የተጠሩትን ፡ ሰዎች ፡ ጥራ ፡ ብሎ ፡ መላክተኛውን ፡ ቢልከው ፡ ፩ኛው ፡ ዐዲስ ፡ እርሻ ፡ ገዝቼ ፡ ያንን ፡ ላይ ፡ እሔዳለሁ ፡ ስለዚህ ፡ ልመጣ ፡ አልቻልኩም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደመጣሁ ፡ ያህል ፡ ቁጠርልኝ ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ቀረ ።

፪ተኛውም ፡ ሰው ፡ ፭ ፡ ያህል ፡ ወይፋፍኖች ፡ ገዝቼ ፡ እኒያን ፡ አስጠምጄ ፡ ላስፈትን ፡ ልሔድ ፡ ነኝ ፡ ስለዚህ ፡ መምጣት ፡ አልተቻለኝም ፡ ቢኾንም ፡ እንደመጣሁ ፡ ቁጠርልኝ ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ቀረ ።

፫ተኛውም ፡ ዐዲስ ፡ ሚስት ፡ አግብቻለሁና ፡ እሷን ፡ ጥዬ ፡ ልመጣ ፡ አልቻልኩም ፡ ቢኾንም ፡ እንደመጣሁ ፡ ቁጠርልኝ ፡ እንጂ ፡ እንደቀረሁ ፡ አትቁጠርብኝ ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ቀረ ።

ንጉሡም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በነሂ ፡ ሰዎች ፡ ተቈጥቶ ፡ ሒዱ ፡ ወደ ፡ ገባያም ፡ ወደ ፡ አደባባይም ፡ ሔዳችሁ ፡ ያገኛችሁትን ፡ ኹሉ ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ጥሩልኝ ፡ ብሎ ፡ አስጠርቶ ፡ ለበዓሉ ፡ ተካፋይ ፡ አደረጋቸው ፡ ብሎ ፡ ቤት ፤ ንብረት ፤ ልጅ ፡ ሚስት ፡ ያላቸው ፡ ሰብአ ፡ ዓለምን ፡ ሐልዮ ፡ መንበርት ፡ ትካዘ ፡ ዓለም ፡ ፍቅረ ፡ ብእሲት ፡ ምክንያት ፡ ኾኖ ፡ ከበዓሉ ፡ እንዳስቀራቸው ፤ ቤት ፤ ንብረት ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ የሌላቸው ፡ መነኰሳትን ፡ ባሕታውያንን ፡ ሐልዮ ፡ መንበርት ፡ ትካዘ ፡ ዓለም ፡ ፍቅረ ፡ ብእሲት ፡ ሳይከለክላቸው ፡ ለበዓሉ ፡ ተካፋይ ፡ መኾናቸውን ፡ በምሳሌ ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ ሰብአ ፡ ዓለምና ፡ ስለ ፡ መነኰሳት ፤ ስለ ፡ መናንያን ፡ መኾኑን ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ እኔን ፡ ሊመስል ፡ ወዶ ፡ ወደኔ ፡ የሚመጣ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ እናቱን ፡ አባቱን ፡ ሚስቱን ፡ ልጆቹን ፡ እኅቶቹን ፡ ወንድሞቹን ፡ ራሱን ፡ ሰውነቱን ፡ ሳይቀር ፡ ጠልቶ ፡ መስቀሉን ፡ ተሸክሞ ፡ በግብሩ ፡ እኔን ፡ ካልመሰለኝ ፡ የኔ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ሊባል ፡ አይችልም ፡ ብሏል ፡ ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፬–፲ ፡ ሉቃ ፡ ፲፬ ፡ ፲፮–፳፷ ።

፺ተኛ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በቆሮ ፡ ክታቡ ፡ በም ፡ ፯ ፡ በቍ ፡ ፩ ፡ ስለጻፋችሁልኝ ፡ ነገር ፡ ለሰው ፡ ሴት ፡ ሳይነካ ፡ በንጽሕና ፡ ቢኖር ፡ በተሻለው ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ዝሙት ፡ ድል ፡ እንዳይነሣችሁ ፡ ወንዶችም ፡ አንዳንድ ፡ ሴት ፤ ሴቶችም ፡ አንዳንድ ፡ ባል ፡ ሊያገቡ ፡ ይገባል ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ድንግልና ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፡ አላለም ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አይለያዩ ፡ እያለ ፡ የነገራቸውን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ መጥቶ ፤ ይህንም ፡ ማለቴ ፡ ስለባሕርያችሁ ፡ ደካማነት ፡ ሰይጣን ፡ ድል ፡ እንዳይነሣችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ አግብተው ፡ የፊቱ ፡ ማዓስባንና ፡ ያላገቡ ፡ ደናግልም ፡ እንደኔ ፡ በድንግልና ፡ ቢኖሩ ፡ በተሻላቸው ፡ ነበረ ፡ ብሏል ።

www.ethiopianorthodox.org

በ፳፱ኛውም ፡ ቍጥር ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ንብረት ፡ ሊያልፍ ፡ ቀርቧል ፡ ያንጊዜ ፡ ያገቡ ፡ እንዳላገቡ ፡ የበሉ ፡ የጠጡ ፡ እንዳልበሉ ፡ እንዳልጠጡ ፡ ይኹኑ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ኹሉ ፡ ያልፋል ፡ ይጠፋልና ፡ እኔስ ፡ ያለኃዘን ፡ እንድትኖሩ ፡ እመኝላችኋለሁ ። ሚስት ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኘው ፡ ገንዘብ ፡ ደስ ፡ ያሰኘው ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝበትን ፡ ሥራ ፡ ያስባል ። ያገባ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ሚስቱን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኛት ፡ ገንዘብ ፡ ደስ ፡ ያሰኛት ፡ ዘንድ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ንብረት ፡ ያስባል ።

እንደዚሁም ፡ ባል ፡ ያላገባች ፡ ሴት ፡ በነፍሷም ፡ በሥጋዋም ፡ የተቀደሰች ፡ ትኾን ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ በምታሰኘው ፡ ገንዘብ ፡ ደስ ፡ የምታሰኝበትን ፡ ሥራ ፡ ታስባለች ።

ባል ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ግን ፡ ባሏን ፡ ደስ ፡ በምታሰኘው ፤ ገንዘብ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ንብረት ፡ ታስባለች ። ይህንም ፡ ማለቴ ፡ ያለጥርጥር ፡ እግዚአብሔርን ፡ በትክክል ፡ እንድታገለግሉትና ፡ እንድትጠቀሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አጠምዳችሁ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ። የማግባት ፡ ፈቃድ ፡ ያለበትም ፡ ቢያገባ ፡ ኃጢአት ፡ የለበትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ላግባ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ልመንኵስ ፡ በማለት ፡ ልቡናው ፡ የማይታወከበት ፡ ሰው ፡ የወደደውን ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ። ልመንኵስ ፡ የሚለውን ፡ አግባ ፤ ላግባ ፡ የሚለውን ፡ መንኵስ ፡ ብለው ፡ አያገብሩት ፡ ድንግልናውን ፡ ጠብቆ ፡ ሊኖር ፡ ቢጨክን ፡ በጎ ፡ አደረገ ፤ ያገባውም ፡ በጎ ፡ አደረገ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ካገባው ፡ ያላገባው ፡ የበለጠ ፡ የተሻለ ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ እያለ ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ ከመኖር ፡ ክሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ የበለጠ ፡ የተቀደሰ ፡ መሆሪያ ፡ መኾኑን ፡ መላልሶ ፡ ይነግረናል ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፳፱–፴፬።

፪ተኛ ፡ በምንኵስና ፡ ስለተጠቀሙ ፡ አባቶች ፡ ታሪክ ።

፩ኛ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ በብሕትውና ፡ ይኖር ፡ ነበረ ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ አብርሃም ፡ ነገሥት ፡ ከሎዶጎሞርን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ሲመለስ ፡ ከያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ኹሉ ፡ ከ፲ ፡ አንድ ፡ አውጥቶ ፡ ገብሮለታል ፤ ከሱ ፡ ተባርኮ ፡ በረከቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ተመልሷል ። በዚኸውም ፡ በግብሩ ፡ ንጉሠ ፡ ጽድቅ ፡ ንጉሠ ፡ ሰላም ፡ ተብሎበታል ። ለንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ለመኾን ፡ በቅቶበታል ።

ምሳሌነቱንም ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ። እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ያለሹመት ፡ ተሾመህ ፡ የዓለሙ ፡ አገልጋይ ፡ አንተ ፡ ነህ ብሎ ፡ መስክሮለታል ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወ መልከ ፡ ጼዴቅሰ ፡ ንጉሠ ፡ ሳሌም ፡ ካህኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ በአምሳሊሁ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነብር ፡ ክህነቱ ፡ ለዝሉፉ ። ትሬእዩኑ ፡ ዕበዮ ፡ ለዝንቱ ፡ ዘወሀቦ ፡ አብርሃም ፡ ዓሥራተ ፡ እምኵሉ ፡ ዘይኄይስ ፡ ወርእሰሙ ፡ ለአበው ።



መልከ ፡ ጼዴቅስ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ የሳሌሙ ፡ ንጉሥ ፤ ነው ፡ ክህነቱም ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ ምሳሌ ፡ በመኾን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። የአበው ፡ ጥንታቸው ፡ የሚኾን ፡ አብርሃም ፡ ከገንዘቡ ፡ ኹሉ ፡ መልከካሙን ፡ የገበረለትን ፡ የመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ደግነቱን ፡ ታያላችሁን ፡ ብሎ ፡ መስክሮለታል ፡ መዝ ፡ ፻፲ ፡ ፬ ፡ ዕብ ፡ ፯ ፡ ፩–፬ ።

፪ተኛም ፡ ኤልያስ ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ድንግል ፡ ንጹሕ ፡ ነበረ ፡ በዚሁም ፡ ተጠቅሞበት ፡ ዝናም ፡ እንዳቆመ ፡ ሰማይ ፡ እንደለጐመ ፡ ሙት ፡ እንዳነሣ ፡ በሠረገላ ፡ እሳት ፡ ወደሰማይ ፡ እንዳረገ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይነግረናል ። ፩ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ፡ ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ፡ ፩ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፵፬ ። ፲፯ ፡ ፲፱–፳፬ ፡ ነገ ፡ ካል ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፫ተኛ ፡ ኤልሳዕ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ ንብረት ፡ ገዝቶ ፡ ይኖር ፡ ነበረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ በተመረጠ ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ በርኖሱን ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ተከተለኝ ፡ ቢለው ፡ ከ፲፪ ፡ ጥንድ ፡ በሬዎች ፡ ፪ቱን ፡ በሬዎች ፡ አርዶ ፡ በሞፈሩና ፡ በቀንበሩ ፡ ቀቅሎ ፡ አብልቶ ፡ ፲፩ዱን ፡ ጥማዶች ፡ ትቶ ፡ ኤልያስን ፡ ተከትሎ ፡ ሔደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሎ ፡ ፪ ፡ ምውት ፡ እስከ ፡ ማንሣት ፡ ደርሷል ፡ ፩ ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲፮–፳፩ ።

፬ተኛ ፡ ገና ፡ ከመወለዱ ፡ አስቀድሞ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በመወለዱ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ታላቅ ፡ ይኾናል ፡ ወይን ፤ ጠጅ ፤ ዐረቄ ፡ አይጠጣም ፡ ከናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ጀምሮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮበታል ፡ ተብሎ ፡ በመልአኩ ፡ ቃል ፡ የተመሰከረለት ። ከተወለደም ፡ በኋላ ፡ ኢተንሥአ ፡ እምትውልደ ፡ አንስት ፡ ዘየዐብዮ ፡ ለዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ተብሎ ፡ በጌታ ፡ ቃል ፡ የተመሰከረለት ፡ መጥምቀ ፡ መለኮት ፡ ዮሐንስ ፡ ንጹሕ ፡ ድንግል ፡ ነው ። ኑሮውም ፡ በመምህርነት ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ በረሀ ፡ ነበረ ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ፡ ፹ ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ።

እንግዲህ ፡ እንዳንተ ፡ አነጋገር ፡ እኒህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ አባቶች ፡ ኹሉ ፡ ከአምላክ ፡ ሕግ ፡ በተለየ ፡ ከንቱ ፡ በኾነ ፡ የሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጽድቅ ፡ ሲደክሙ ፡ መኖራቸው ፡ ነው ።

ለሕግ ፡ ተላላፎች ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ብለህ ፡ ታስባለህን ፡ ወይንስ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ አልተሰጣቸውም ፡ ብለህ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ልታሳብላቸው ፡ ታስብ ፡ ይኾን ።

አንተ ፡ ካልሠራሁት ፡ ብለህ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ የሚገኝበትን ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ ከአምላክ ፡ ያልተፈቀደ ፡ ጥቅም ፡ የለሽ ፡ ከንቱ ፡ ግብር ፡ እያስመሰልክ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነገር ፡ ባልታረመ ፡ አንደበትህ ፡ እየተናገርክ ፡ እግረ ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደምንኵስና ፡ በሚያቀኑ ፡ ሰዎች ፡ ዕንቅፋት ፡ ብትኾንባቸው ፤ ያጸድቅን ፡ አያጸድቅን ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ ብታሳድርባቸው ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እናንተ ፡ አትገቡም ፡ የሚገቡትንም ፡ ምክንያት ፡ እየፈጠራችሁ ፡ እንዳይገቡ ፡ ትከለክሏቸዋላችሁ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በር ፡ ትዘጉባቸዋላችሁና ፡ እናንት ፡ ግብዞች ፡ ወዮ

www.ethiopianorthodox.org

ላችሁ ፡ ከተባሉት ፡ ያስቈጥረሃል ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ይጠቅምሃል ፡ ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፩ ፡ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፶፪ ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ መቸም ፡ ይሉኝታ ፡ ቢስ ፡ ነህና ፡ ምንኵስናን ፡ ነቀፍኩ ፤ እንጂ ፡ ድንግልናን ፡ መች ፡ አልኩ ፡ ትለኝ ፡ ይኾናል ። ቆብ ፡ ምንም ፡ ለአክሊለ ፡ ሦክ ፡ ምሳሌ ፡ መኾኑ ፡ ባይዘነጋ ፡ የምንኵስና ፡ ዋናው ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ እየኖሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ።

፲፮ ፍጡር ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ከሰው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡ ደቃቁ ፡ ትል ፡ የሩካቤን ፡ ጠባይና ፡የዘር ፡ ማድረጊያ ፡ ካለው ፡ አምሳያውን ፡ ተደራጊ ፡ ባሕርይ ፡ እንደሚያስፈልገውና ፡ የገዛ ፡ ገንዘቡ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፡ ስለምትለው ።

ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልዕዋ ፡ ለምድር ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳፰ ፡ ያለው ፡ ትእዛዝ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ተግባር ፡ እንደመኾኑ ፡ መጠን ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ያላቸው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ፍጥረት ፡ እንኳ ፡ ኹሉ ፡ ለባሕርዩ ፡ ተስማሚ ፡ ኾኖ ፡ አግኝቶት ፡ ዐውቆ ፡ ይሠራዋል ፡ እንጂ ፡ መምህር ፡ አይሻለትም ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ይህን ፡ ለሰው ፡ ደንበኛ ፡ ትምርት ፡ አድርገህ ፡ ስታስተምረው ፡ የሰው ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀቱ ፡ ከእንስሳ ፡ ያንሣል ፡ እንስሳት ፡ የሚያውቁትን ፡ ሊያውቅ ፡ አይችልም ፡ ማለትህ ፡ አይደለምን ?

የመምህርነትህ ፡ ግምትና ፡ ለሰው ፡ የምታስብለት ፡ ጥቅም ፡ ግምቱ ፡ ይህ ፡ መኾኑ ፡ ለአስታዋይ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ይገርማል ፡ ያስደንቃል ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንስ ፡ ይህን ፡ የሩካቤን ፡ ተግባር ፡ እንስሳትን ፡ በሚመስልበት ፡ በደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ፈቃድ ፡ ተሸንፎ ፡ የሚሠራው ፤ መምህር ፡ የማያሻው ፡ መኾኑን ፡ ዐውቃ ፡ ከልክ ፡ አልፎ ፡ አብዝቶ ፡ ሥርቶት ፡ በሰብአ ፡ ትካት ፡ በሰብአ ፡ ሰዶም ፡ በሰብአ ፡ ገሞራ ፡ የደረሰ ፡ መዓት ፡ እንዳይደርስበት ፡ ከማስጠንቀቅ ፡ በቀር ፡ ብሉ ፤ ጠጡ ፤ ዝሙት ፡ ሥሩ ፡ ማለትን ፡ ጉባኤ ፡ አድርጋ ፡ አታስተምረውም ።

እንስሳዊ ፡ ግብር ፡ እንስሳዊ ፡ ዕውቀት ፡ ባላት ፡ በደማዊት ፡ ነፍስ ፡ እንስሳትን ፡ እንደመሰለ ፤ መልአካዊ ፡ ዕውቀት ፡ መልአካዊ ፡ ግብር ፡ ባላት ፡ በነባቢት ፡ ነፍስም ፡ መላእክትን ፡ መምሰል ፡ አለበትና ፡ እንስሳትን ፡ ከመምሰል ፡ መላእክትን ፡ መምሰል ፡ የበለጠ ፡ ተግባር ፡ መኾኑን ፡ እያስረዳች ፡ መላእክትን ፡ የሚመስልበትን ፡ ተግባር ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ ድንግልንና ፡ ንጽሕናን ፤ ቅድስናን ፡ ታስተምራለች ።

፲፯ ይህን ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ ሊያደርጉት ፡ የማይኾንላቸው ፡ ግን ፡ ማድረጊያ ፡የሌላቸው ፡ ሕፅዋን ፡ ጃንደረቦች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ስለምትለው ።

አንተ ፡ የእውቀትህ ፡ መጠኑ ፡ ከዚህ ፡ ድረስ ፡ ስለኾነ ፡ ጃንደረቦች ፡ በግድ ፡ ከሩካቤ ፡ መከልከላቸውን ፡ የማያውቅ ፡ አለ ፡ መስሎህ ፡ እንዲህ ፡ ማለትህ ፡ ያሳዝናል ። ይህስ ፡ የግድ ፡ ነው ፡ አያስደንቅም ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ከሚመሰገኑ ፡ ይልቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይመሰገኑ ፡ ዘንድ ፡ ዐባለ ፡ ዘ



ፈቃዱን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምላጭነት ፡ ቈርጠው ፡ ጥለው ፡ ሩካቤን ፡ ሊያደርጉ ፡ የማይቻላቸው ፡ ብዙ ፡ ቅዱሳን ፡ አሉ ፡ ብዬ ፡ እንዳሉ ፡ እውነት ፡ እነግርሃለሁ ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ፡ ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፳፱ ።

ኾኖም ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ የዘር ፡ ማድረጊያ ፡ ካለው ፤ አምሳያው ፡ ተደራጊ ፡ ባሕርይ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፡ ያልከውንና ፡ ሩካቤን ፡ ሊያደርጉት ፡ የማይቻላቸው ፡ ጃንደረቦች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ ያልከውን ፡ ሲያመዛዝኑት ፡ ሩካቤን ፡ በሥዒን ፡ የተውት ፡ ጀንደረቦች ፡ ዕዳ ፡ አይኾንባቸውም ፡ ሲቻላቸው ፡ ለጽድቅ ፡ ብለው ፡ የተውት ፡ ዕዳ ፡ ይኾንባቸዋል ፡ ማለትህ ፡ እንደኾነ ፡ በግልጥ ፡ ታውቋል ።

እንግዲህ ፡ በሩካቤ ፡ በዘርዕ ፡ ልጅ ፡ ወልደው ፡ ከከበሩ ፡ አባቶች ፡ በብሕትውና ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ በቅድስና ፡ ጸንተው ፡ ኖረው ፡ በአምሳሊሁ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነብር ፡ ክህነቱ ፡ ለዝሉፉ ፡ ኢተንሥአ ፡ እምትውልደ ፡ አንስት ፡ ዘየዐብዮ ፡ ለዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ለመባል ፡ የበቁ ፡ የነመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ የነዮሐንስ ፡ መጥምቅን ፡ ታሪክ ፡ ተመልከት ፡ ዕብ ፡ ፯ ፡ ፫ ፡ መገ ፡ ፻፲፥፬ ፡ ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ።

፲፰ የማይሳሳተው ፡ ቸሩ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ በጥበቡ ፡ አውቆ ፡ በምሥጢሩ ፡ ተረቅቆ ፡ ለፈጠረው ፡የሩካቤ ፡ ሕግ ፡ ማድረጊያ ፡ ስጥቷቸው ፡ ሳሉ ፡ በትምክህታቸው ፡ እሳትን ፡ በጨርቅ ፡ የሚቋጥሩ ፡ መላእክት ፡ ምድር ፡ ማለት ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ የሚከበሩ ፡ መነኵሴዎች ፡ ባገራችን ፡ ሞልተዋል ። ስለምትለው ።

መነኰሳት ፡ የሚመነኵሱ ፡ እመሰ ፡ ፈቀድከ ፡ ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሑር ፡ ወሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ለፍቅሩ ፡ ከመሳሳታቸው ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሚስት ፡ አግብተው ፡ ቤት ፡ ሠርተው ፡ ከሚያገለግሉት ፡ አገልግሎት ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ሊያገለግሉት ፡ ወደው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰብሳብ ፡ ርኩስ ፡ ብለው ፡ ሩካቤን ፡ ተጸይፈው ፡ አይደለም ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፫ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፳፱-፴፩ ።

እሳትን ፡ በጨርቅ ፡ የምንቋጥር ፡ መላእክተ ፡ ምድር ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ተመክተው ፡ ይመነኵሳሉ ፡ ማለትን ፡ አንተ ፡ ፈጥረህ ፡ ትናገረዋለህ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚመሰክርልህ ፡ አይገኝም ። ሰብሳብ ፡ ርኩስ ፡ ብለው ፡ ሩካቤን ፡ ተጸይፈው ፡ እሳትን ፡ በጨርቅ ፡ የምንቋጥር ፡ መላእክተ ፡ ምድር ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ተመክተው ፡ የሚመነኵሱ ፡ የሉም ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ካሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማትቀበላቸው ፡ መኾኗን ፡ በእርግጥ ፡ እነግርሃለሁ ።

፲፱ አምላክ ፡ የፈጠረውንና ፡ የወሰነውን ፡ ሕግ ፡ ሊያፈርሱና ፡ ሊሽሩ ፡ ሲሞክሩ ፡ ኹሉም ፡ በጥበባቸው ፡ ተሸረው ፡ በተጸየፉት ፡ በዓለማዊ ፡ ጭቃ ፡ ወድቀው ፡ ተጥለቅልቀው ፡ መገኘታቸውን ፡ ስላየሁ ፡ በትዕቢታቸውና ፡ በበሕተታቸው ፡ አዝናለሁኝ ፡ ስለምትለው ።

አንተ ፡ ፈረሰ ፡ ብለህ ፡ የምትቈረቈርበት ፡ ሕግ ፤ ሰው ፡ እንስሳትን ፡ መስሎ ፡ የሚሠራውን ፡ መብላትን ፡ መጠጣትን ፡ ሩካቤን ፡ ነው ፤ ይህንም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በተፈጥሮው ፡ ካባቱ ፡ ከቀዳማዊ ፡ አዳም ፡ ወርሶት ፡ መምህር ፡ ሳይሻ ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ አውቆት ፡ አብዝቶ ፡ ሠርቶት ፡ እሱን ፡ የመጠበቁ ፡ ዋጋ ፡ በንፍር ፡ ውኃ፡

www.ethiopianorthodox.org

መደምሰስን ፡ ከሰማይ ፡ በዘነመ ፡ እሳት ፡ መቃጠልን ፡ አግኝቷል ፡ ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ። ም ፡ ፯ ፡ ፲ ፡ ፳፬ ። ዘፍ ፡ ፲፱ ፡ ፩-፲ ። ፳፬ ፡ ፳፯ ።

ሕገ ፡ መላእክት ፡ ድንግልና ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ከሱም ፡ በፊት ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ተገልጦላቸው ፡ ጠብቀውት ፡ የተጠቀሙ ፡ ባይታጡ ፤ ከዳግማዊ ፡ አዳም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተወርሶ ፡ አብዝተው ፡ ለሠሩት ፡ ሰዎች ፡ ዋጋቸውን ፡ በጸጋ ፡ ላይ ፡ ጸጋ ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ አሰጥቷል ።

ስለዚህ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ኀዳግን ፡ አበ ፡ ቀዳማየ ፡ ዘቦቱ ፡ ማሰነ ፡ ዘውእቱ ፡ አዳም ።

የተገኦዳንበትን ፡ የቀደመ ፡ አባታችንን ፡ ተውን ፡ ይኸውም ፡ አዳም ፡ ነው ። እያሉ ፡ (ቄርሎ ፡) ወንትልዎ ፡ ለፍጹም ፡ መልአክነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ፍጹም ፡ አበጋዛችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንምሰለው ፡ ወደማለት ፡ ተመል ሰው ፡ እግረ ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ መላእክት ፡ አቅንተዋል ። ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ። እንግዲህ ፡ እኒህ ፡ አንተ ፡ የምታዝንላቸው ፡ መነኮሳት ፡ ይህን ፡ ተመልክተው ፡ ከሕገ ፡ እንስሳት ፡ ወጥተው ፤ ሕገ ፡ መላእክትን ፡ ቢይዙ ፤ አምላክ ፡ የወሰነውን ፡ ሕግ ፡ አፈ ረሱ ፡ ሻሩ ፡ ተብለው ፡ ሊወቀሱ ፡ ሥራቸው ም ፡ ከድፍረት ፡ ከስሕተት ፡ ገብቶ ፡ ሊቆ ጠርባቸው ፡ ይገባልን ፤ አይገባም ። በውነቱ ፡ ካዘንክስ ፡ ከግእዘ ፡ እንስሳ ፡ ነፃ ፡ የሚ ያደርጉ ፡ ጾምን ፡ ትሕርምትን ፡ ብሕትውናን ፡ ምንኵስናን ፡ ነቅፎ ፡ በግእዘ ፡ እንስሳ ፡ ታሥሮ ፡ ተተብትቦ ፡ ለቀረ ፡ ለራስህ ፡ ብታዝን ፡ እንዴት ፡ በተሻለ ፡ ነበር ።

፳ ሕግ ፡ ሊያጠፉ ፡ የሚሞክር ፡ ኹሉ ፡ ለራሱ ፡ ይጠፋል ፤ ብለህ ፡ ለዚሁ ፡ ምስክር ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፱—፲፪ ፡ ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፯—፲፯ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፱ — ፴፩ ፡ ጠቅሰሃል ።

እውነት ፡ ነው ፡ ሕግን ፡ ሊያጠፋ ፡ የሚሞክር ፡ ለራሱ ፡ መጥፋቱ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ በሰብአ ፡ ትካት ፤ በሰብአ ፡ ሰዶም ፤ በሰብአ ፡ ገሞራ ፡ ታውቋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቢጠብቁት ፡ የሚጠብቅ ፡ ቢያጠፉት ፡ የሚያጠፋ ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ መላእ ክት ፡ ጾም ፤ ጸሎት ፤ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፤ ነው ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ እንደምት ለው ፡ ሕገ ፡ እንስሳት ፡ መብላት ፤ መጠጣት ፡ መንጠላጠል ፡ አይደለም ።

አንተ ፡ የምታስተምረውንስ ፡ ሕግ ፡ ተጠንቅቆ ፡ ከመጠበቅ ፡ ፈጽሞ ፡ መተው ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ የሚያሰጥ ፡ መኾኑን ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተረክ ሁልህን ፡ የነመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ የነኤልያስን ፡ የነዮሐንስ ፡ መጥምቅን ፡ ታሪክ ፡ ተመ ልከት ፡ በዚሁ ፡ ም ፡ በቍ ፡ መግ ፡ ፻፲፬ ። ዕብ ፡ ፯ ፡ ፩-፬ ። ፩ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፵፱ ። ፲፯ ፡ ፲፱—፳፬ ፡ ነገ ፡ ካል ፡ ፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ፲፯ ፡ ፳፩ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ፡ ፹ ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ።

፳፩ ስለዚህም ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፱—፲፪ ፡ የጠቀስከው ፡ ፍትወት ፡ እንስሳዊ ፡ ለሰው ፡ ተስማ ሚው ፡ ስለኾነ ፡ ከጃንደረቦች ፡ በቀር ፡ ኹሉ ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ጽኑ ፡ ከባድ ፡ ጦር ፡ መኾኑን ፡ ከተናገረ ፤ በኋላ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚችል ፡ ግን ፡ ይፈጽመው ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ሚስት ፡ አለማግባት ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ አላለም ቍ ፡ ፲፪ ፡ ተመልከት ።



፳፪ ሮሜ ፡ ፪ ፡ ከ፯ — ፲፯ ፡ የጠቀስከውም ።

በእውነተኛ ፡ ፍርዱ ለኹሉም ፡ እንደየሥራው ፡ ይከፍለዋልና ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ የታገሡ ፡ ሰዎች ፡ ክብርን ፡ ጌትነትን ፡ ይሻሉ ። እሱም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጣቸዋል ፡ የከሐዲዎችና ፡ የጽድቅ ፡ እንቢተኞች ፡ ዐመፅን ፡ የሚወዱ ፡ ግን ፡ አይሁዳዊም ፡ ቢኾን ፡ ዓረማዊም ፡ ቢኾን ፡ ሥራው ፡ ክፉ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ፍዳው ፡ መቅሠፍት ፤ መንሡት ፤ ቍጥዓ ፤ ገዓር ፤ ምንዳቤ ፡ ነው ።

ሥራው ፡ መልካም ፡ ለኾነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ አይሁዳዊም ፡ ዐረማዊም ፡ ቢኾን ፡ ዋጋው ፡ ክብር ፤ ጌትነት ፡ ሰላም ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ አያደላምና ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ልጅ ፡ የወለደ ፡ ፈጻሚ ፡ ሕግ ፡ ኾኖ ፡ ዋጋውን ፡ ያገኛል ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ የኖረ ፡ ሕግ ፡ ተላላፊ ፡ ተብሎ ፡ ይቀጣል ፡ አላለም ።

፳፫ ይልቁንም ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፱—፴፩ ፡ የጠቀስከው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፤ መጽሐፍ ፡ የጥ በበኞችን ፡ ጥበባቸውን ፡ አጠፋለሁ ፤ የመካሮችንም ፡ ምክራቸውን ፡ እንቃለሁ ፡ ብሏልና ፡ እንግዲህ ፡ ጠቢብ ፡ ማነው ፤ ፀዋቂስ ፡ ማነው ፤ ይህን ፡ ዓለምስ ፡ የሚሻው ፡ ማነው ። የዚህን ፡ ዓለም ፡ ጥበብማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስንፍና ፡ ያደረገው ፡ አይደለ ምን ፡ የሚል ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ዓለም ፡ በተፈጥሮው ፡ ያውቀው ፡ የነበረ ፡ ጥበብ ፡ ምን ፡ ይመስለ ሃል ፡ መብላት ፡ መጠጣት ፡ ሚስት ፡ ማግባት ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ አይደለምን ? ጌታ ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስስ ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ከስንፍና ፡ የቈጠረው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ ምንድን ፡ ነው ፤ ዛሬ ፡ አንተ ፡ ጠቃሚ ፡ ቀዋሚ ፡ ሕግ ፡ አስመስ ለህ ፡ የምታስተምረውን ፡ መብላትን ፡ መጠጣትን ፡ ሚስት ፡ ማግባትን ፡ ቤት ፡ መሥ ራትን ፡ አይደለምን ።

ይኸውም ፡ እውነት ፡ መኾኑ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ እንዳንተ ፡ ትካዘ ፡ ዓለም ፡ ሐልዮ ፡ መንበርት ፤ ብዕል ፡ ሰፋጢት ፤ ፍቅረ ፡ ብእሲት ፡ አጫንቆ ፡ የያ ዘው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እወርስ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ልሥራ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወትን ፡ ልትወርስ ፡ ከወደድክስ ፡ በአሪት ፡ የተጻፉ ፡ ትእዛዛትን ፡ ጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ሕገ ፡ ርትዕን ፡ ካስተ ማረው ፡ በኋላ ፡ ይህንንስ ፡ ከልጅነቴ ፡ ጀምሬ ፡ ጠብቄያለሁ ፡ ቢለው ፡ ፍጹም ፡ ልት ኾን ፡ ከወደድክስ ፡ ያለህን ፡ ኹሉ ፡ ሸጠኽ ፡ ለውጠኽ ፡ ለነዳያን ፡ መጽውተህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ ብሎ ፡ ሕገ ፡ ትሩፋት ፡ ምንኵስናን ፡ ያስተማረው ፡ አይደለምን ። ከጠቀስካቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ኹሉ ፡ ሚስት ፡ ሳያገቡ ፡ ልጅ ፡ ሳይወልዱ ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ፡ ሕግ ፡ መተላለፍ ፡ መኾኑን ፡ አንዱም ፡ አልመሰከረልህም ። እንግዲህ ፡ ምዕራፍና ፡ ቍጥር ፡ ብቻ ፡ እየጠቃቀስክ ፡ እውነቱን ፡ ሐሰት ፡ ጽድቁን ፡ ኃጢአት ፡ በማስመሰልኽ ፡ ውሥጡን ፡ ገብተው ፡ ያልመረመሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሕሊና ፡ ብታሸብር ፤ በእግዚአብሔርም ፡ መናኒ ፡ ብትከለክልበት ፡ የምታገኘው ፡ ጥቅም ፡ ምን ፡ ይኾን ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፬ እንመምሬና ፡ እነአባቴ ፡ ግን ፡ ከዓለም ፡ ሞተናል ፡ ዓለምም ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ የሞተች ፡ ናት ፡ ገላ ፡ ፮ ፡ ፲፬—፲፯ ፡ ብለው ፡ ሲያበቁ ለተጸየፉቱ ፡ ዓላም ፡ እንደገና ፡ ጌቶቹ ፡ ዋኖቹ ፡ ኾነው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሳይሠሩ ፡ ከሠራተኛ ፡ ኹሉ ፡ በግድ ፡ እያስገበሩ ፡ በጠጅና ፡ ጠላ ፡ ባረቂና ፡ ጮማ ፡ በሐርና ፡ ኩፍ ፡ ጫማ ፡ ተንከረው ፡ ምውታኖቹ ፤ ከሕያዋን ፡ በላይ ፡ ክብረው ፡ የሐላፊው ፡ የሥጋ ፡ ምቾት ፡ ይዘው ፡ ለስማያዊና ፡ ለሥጋዊ ፡ ዳኛ ፡ ሳይገዙ ፡ መክሊታቸውን ፡ ሳያራቡና ፡ በሕግ ፡ ሕፃናት ፡ ወልደው ፡ ዘርዐ ፡ አዳም ፡ ሳያበዙ ፡ በሥጋና ፡ ነፍስ ፡ ሸፍተው ፡ ከዓለም ፡ ዱር ፡ ገብተው ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ተሸሽገው ፡ ይኖራሉ ፡ ስለምትለው ።

ለነገርህ ፡ ሥር ፡ መሠረት ፡ አድርገህ ፡ የተነሣህ ፡ በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ምንኵስናን ፡ ለመንቀፍ ፡ ነበረ ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ሐሳብህ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስናን ፡ ከመንቀፍ ፡ ወጥቶ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ወደ ፡ መቆርቆር ፡ አዘንብሏል ፤ አንተ ፡ መጻሕፍትን ፡ ባለመመርመርህ ፡ መስሎህ ፡ አፍህ ፡ እንዳመጣ ፡ ትቀባጥራለህ ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ አንተ ፡ እንደምትናገረው ፡ አይደለም ።

(ሀ) ከዓለም ፡ ሞተናል ፡ ዓለምም ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ የሞተች ፡ ናት ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ለተጸየፉቱ ፡ ዓለም ፡ እንደገና ፡ ጌቶቹና ፡ ዋኖቹ ፡ ኾነዋል ፡ ስለምትለው ፤ ይህ ፡ ምውትነት ፡ በሕሊና ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ አይፈጸምም ። ይህም ፡ ሊታወቅ ፡ ለዚህ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ መደበኛው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ነው ። ምውትነቱ ፡ በሕሊናው ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ ስላልኾነ ፡ ከዕለተ ፡ ሞት ፡ አስቀድሞ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሊለይ ፡ አልቻለም ።

ቅዱስ ፡ ዳዊትም ፡ ፈላሲ ፡ አነ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወነግድ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ አበውየ ፡ ብሏል ፡ መዝ ፡ ፴፱ ፡ ፲፪ ። ዳዊት ፡ እንግዳና ፡ መጻተኛነቱ ፡ በሕሊና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ ነውን ? በኑሮውማ ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ በመንግሥት ፡ መኖሩ ፡ የታወቀ ፡ አይደለምን ? እንግዲህ ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊትና ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መጻተኛ ፡ ስደተኛ ፡ ምውት ፡ ኾኖ ፡ መኖር ፡ በሕሊና ፡ እንጂ ፡ በእግር ፡ አለመኾኑን ፡ በአነጋገራቸውና ፡ በኖኗሯቸው ፡ ካስረዱ ፤ አንተ ፡ ስንኳንስ ፡ የሰውን ፡ ሕሊና ፡ የራስህን ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ የማትችል ፡ መኾንህን ፡ ተገንዝበህ ፡ የሕሊናውን ፡ ፍርድ ፡ ለሕሊና ፡ ዳኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለቀህ ፡ በማታውቀው ፡ ነገር ፡ ከመፍረድ ፡ አፍህን ፡ ዝጋ ፡ ላንደበትህ ፡ መዝጊያ ፡ አብጅለት ፡ ሢም ፡ እግዚኦ ፡ ዐቃቤ ፡ ለአፉየ ፡ ወማዕፆ ፡ ዘዐቅም ፡ ለከናፍርየ ፡ በል ፡ መዝ ፡ ፻፵፩፡፫ ።

፳፭ (ለ) አንድ ፡ ቀን ፡ ሳይሠሩ ፡ ከሠራተኛ ፡ ኹሉ ፡ በግድ ፡ እያስገበሩ ፡ በጠጅና ፡ ጠላ ፡ ባረቂና ፡ ጮማ ፡ ተንከረው ፡ በሥጋ ፡ ምቾት ፡ ይኖራሉ ፡ ስለምትለው ።

እነኚህ ፡ መነኰሳት ፡ አስተምሮ ፡ ማጥመቅን ፤ ቀድሶ ፡ ማቍረብን ፤ ሥራ ፡ አድርገው ፡ የተቀመጡ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በሥራ ፡ ፈትነት ፡ የተቀመጡ ፡ አይደሉም ። ፩ኛ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሉቃስ ፡ ወን ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ ወውእተ ፡ ቤተ ፡ ንበሩ ፡ ወብልዑ ፡ ወስትዩ ፡ ዘእምኀቤሆሙ ፡ እስመ ፡ ይደልዎ ፡ ዐስቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ ወኢትፍልሱ ፡ እምቤት ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ወሀገርኒ ፡ ኀበ ፡ ቦእክሙ ፡ ወተወክፉሙ ፡ ብልዑ ፡ ዘአቅረቡ ፡ ለክሙ ፡ ባለው ፡ ትእዛዝ ።

፪ተኛም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ አስተምሮ ፡ ዋጋ ፡ ይበላል ፡ ብለው ፡ ቢያሙት ፡ ቀዳ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፯ ፡ ማነው ፡ ከ



ደር ፡ የሚኾን ። ደግሞስ ፡ ወይን ፡ ተክሎ ፡ አርሞ ፡ ኰትኵቶ ፡ ከአዕዋፍ ፡ ጠብቆ ፡ ፍሬውን ፡ የማይበላ ፡ ማነው ። መንጋውንስ ፡ ከአራዊት ፡ ጠብቆ ፡ ለምለም ፡ ሣር ፡ ጥሩ ፡ ወኀ ፡ መግቦ ፡ ወተቱን ፡ የማይጠጣ ፡ ማነው ። እንደዚህስ ፡ ኹሉ ፡ እኛ ፡ አስተምረን ፡ አጥምቀን ፡ አቍርበን ፡ ለቊመተ ፡ ሥጋ ፡ ያህል ፡ የዕለት ፡ ራት ፡ መመገብ ፡ አይገባንምን ።

አሪትስ ፡ እኽልህን ፡ በምታሔድበት ፡ ጊዜ ፡ የበሬውን ፡ አፍ ፡ አታፍነው ፡ ብሎ ፡ የለምን ? ። በውኑ ፡ እግዚአብሐር ፡ የበሬውን ፡ አፍ ፡ አትዝጋ ፡ ማለቱ ፡ በሬው ፡ አሳዝኖት ፡ ነውን ? ፤ እኛ ፡ ስናስተምር ፡ ውለን ፡ የዕለት ፡ ራት ፡ ይገባናልና ፡ እንዲገባን ፡ ሲያስረዳ ፡ የጻፈ ፡ አይደለምን ? ። እንዲሁም ፡ የሚያርስ ፡ ገበሬ ፡ እምሾየን ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ያርሳል ፤ የሚያሔድም ፡ የቆሎየን ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ያሔዳል ። እኛስ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምርት ፡ አስተምረናችሁ ፤ አጥምቀን ፡ ልጅነት ፡ አሰጥተናችሁ ፤ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ አቀብለናችሁ ፤ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ ብልት ፡ አድርገናችሁ ፡ ሥጋዊ ፡ ምግብ ፡ ብንመገብ ፡ ቊም ፡ ነገር ፤ ነውን ? ። ለደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ያገለግሉ ፡ የነበሩ ፡ ካህናተ ፡ ኦሪት ፡ ምግባቸው ፡ ተረፈ ፡ መሥዋዕቱ ፤ ልብሳቸው ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሐር ፡ የሚገባው ፡ መባዕ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ ዛሬም ፡ ጌታችን ፡ ወንጌልን ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ ማግኛቸው ፡ ወንጌልን ፡ ማስተማራቸው ፡ ይኹን ፡ ሲል ፡ አዝዟል ፡ ብሎ ፡ በጻፈው ፡ መሠረት ።

አስተዋጽኦም ፡ ማወጣጣት ፡ እንዲገባቸው ፡ በጻፈው ፡ መሠረት ። ፩ ቆሮ ፲፮ ፡ ፩—፬ ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፲—፲፯ ፡ ፱ ፡ ፩-፲፭ ። ምእመናን ፡ ያስገደዳቸው ፡ ሳይኖር ፡ በፈቃዳቸው ፡ በሚሰጧቸው ። ወይም ፡ መንግሥት ፡ በችሮታው ፡ የካህናት ፡ ማደሪያ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ከሰጠው ፡ ርስት ፡ በሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ይተዳደራሉ ፡ እንጂ ፡ ማንንም ፡ ሠራተኛ ፡ አስገድደው ፡ አይቀበሉም ። እውነት ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

፳፮ (ሐ) ለስማያዊና ፡ ለሥጋዊ ፡ ዳኛ ፡ ሳይገዙ ፡ ይኖራሉ ፡ ስለምትለው ። መነኰሳት ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ በጸሎተ ፡ ማኅበርም ፡ በግል ፡ ጸሎታቸውም ፡ ቢኾን ፡ ዕቀብ ፡ ንግሦ ፡ ወሠራዊቶ ፡ አግርር ፡ ፀሮ ፡ ወጸላዕቶ ፡ ለንጉሥነ ፡ እያሉ ፡ ከመጸለይ ፡ የሚያቋርጡበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ። ለንጉሥ ፡ መገዛት ፡ ሌላን ፡ አለው ፤ ወይስ ፡ ይህን ፡ ከሽፍትነት ፡ ቈጠርከው ። ለሰማያዊ ፡ ዳኛ ፡ መገዛትስ ፡ ከሴት ፡ ርቀው ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቀው ፤ ገሚሶቹ ፡ በማስተማር ፤ ገሚሶቹ ፡ በማጥመቅ ፡ በማቍረብ ፤ ገሚሶቹ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ተወስኖ ፡ መኖር ፡ አይደለምን ? ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መገዛት ፡ ጾም ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፡ እያሉ ፡ እያወሩ ፡ ልጓም ፡ እንደ ፡ ወለቀላት ፡ አጋሰስ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ማላመጥ ፡ መሰለህ ? ።

፳፯ መክሊታቸውን ፡ ሳያራቡና ፡ በሕግ ፡ ሕፃናት ፡ ወልደው ፡ ዘርዐ ፡ አዳም ፡ ሳያበዙ ፡ ቀሩ ፡ ስለምትለው ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ መክሊትን ፡ ማራባትና ፡ ገብር ፡ ኄር ፡ መባል ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ሕፃናት ፡ ወልዶ ፡ እኒያን ፡ አበርክቶማ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ታላቅ ፡ የምሥራች ፡ አልነበረምወይ ። እንዲህማ ፡ ቢኾን ፡ ለዚህ ፡ ምን ፡ ሰነፍ ፡ ተገኝቶ ፡ ገብር ፡ ሀካይ ፡ ለምንት ፡ ኢያገብእከ ፡ ወርቅየ ፡ ውስተ ፡ ማዕድየ ፡ ተብሎ ፡ ማን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይወቀስ ፡ ነበረ ፤ እንዲህ ፡ ከኾነስ ፡ በክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ባንዲት ፡ ሴት ፡ ተወስኖ ፡ ካንዲት ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ጥቂቶች ፡ ልጆች ፡ ወልዶ ፡ ጥቂቶችን ፡ ከማበርከት ፡ ከክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ በአፍአ ፡ እንዳሉ ፡ ሰዎች ፡ የቻሉትን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ አግብቶ ፤ ከብዙ ፡ ሴቶች ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ወልዶ ፡ ማበርከት ፡ በተሻለ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ አይደለም ። መክሊትን ፡ ማራባትና ፡ ገብር ፡ ኄር ፡ መባልስ ፡ የሚገኘው ፡ እንደ ፡ መነኮሳት ፡ የሐዋርያትን ፡ ዐሠር ፡ ተከትሎ ፤ መስቀል ፡ ሞትን ፡ ተሸክሞ ፤ ቤትን ፡ ንብረትን ፡ ሚስትን ፤ ልጅን ፡ ትቶ ፤ ለዕለት ፡ ምግብ ፡ የተገኘውን ፡ በልቶ ፤ ዘሮ ፡ ተንከራቶ ፡ ወንጌልን በአገዛ ፡ ሰማዕያን ፡ ዘርቶ ፡ የክርስቶስን ፡ ቤተ ፡ ሰብአች ፡ አባዝቶ ፡ አበርክቶ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፯–፵ ። ፲፯ ፡ ፳፬–፳፯ ፡ ሉቃ ፡ ፲፬ ፡ ፳፯–፳፰ ። ማር ፡ ፰ ፡ ፴፬–፴፰ ፡ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

ሰነፉና ፡ ልባሙም ፡ ተለይቶ ፡ የሚታወቅበት ፡ ጊዜው ፡ ገና ፡ ነው ። በጊዜውም ፤ ጊዜ ፡ ቢኾን ፡ ገብር ፡ ኄር ፡ ወምእመን ፡ ዘበኅዳጥ ፡ ምእመነ ፡ ኮንከ ፡ ዲበ ፡ ብዙኅ ፡ እሠይመከ ፡ ብሎ ፤ ዋጋ ፡ መክፈል ፤ ገብር ፡ ሀካይ ፡ ለምንት ፡ ኢያግባእከ ፡ ወርቅየ ፡ ውስተ ፡ ማዕድየ ፡ እሥሩ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ብሎ ፡ መፍረድ ፤ የክርስቶስ ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ ስለ ኾነ ፡ አንተን ፡ የሚያገባህ ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ዝም ፡ በል ።

፳፫ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ባሥረኛው ፡ አንቀጽ ፡ መነኮሳት ፡ የደነገጉት ፡ ሕጋቸው ፡ ግን ፡ መነኮስ ፡ ፅድሜ ፡ ልኩ ፡ ከተማ ፡ ሳይገባ ፡ በረሃ ፡ ሊኖር ፡ ሥጋና ፡ መጠጥም ፡ ለዘወትር ፡ እንዳይቀምስ ፤ የጠጉር ፡ ሠቅና ፡ የቀርበት ፡ ልብስም ፡ ካልኾነ ፡ የሐር ፡ የጥጥ ፡ ጨርቅ ፡ እንዳይለብስ ፡ ከወገቡም ፡ ሰንዝር ፡ ወፍራም ፡ የቁርበት ፡ መታጠቂያ ፤ እንዳይለይ ፡ በመሬት ፤ ካልኾነም ፡ ምንጣፍ ፡ አንጥፎ ፡ በመደብና ፡ አልጋ ፡ እንዳይተኛ ፤ ውሎ ፡ ማታ ፡ በመጠን ፡ በጨው ፡ በልቶ ፡ ወን ፡ ሊጠጣ ፡ ይህንንና ፡ ሌላውም ፡ የመሰለው ፡ ኹሉ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ሕጋቸው ፡ ሲያደርጉና ፡ ሲሔዱ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አይተናቸው ፡ አናውቅም ፡ በስሕተትና ፡ በድፍረት ፡ ስተናገርኩት ፡ ይቅርታ ፡ እለምናለሁ ፡ ስለምትለው ።

ከፍ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ አምላክ ፡ በጥበቡ ፡ አውቆ ፡ ለፈጠረው ፡ የኑካቤ ፡ ሕግ ፡ ማድረጊያ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ሳሉ ፡ በትምክህታቸው ፡ እሳትን ፡ በጨርቅ ፡ የሚቋጥሩ ፡ መላእክተ ፡ ምድር ፡ እኛ ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ መክሊታቸውን ፡ ሳያራቡና ፡ በሕግ ፡ ሕፃናት ፡ ወልደው ፡ ዘርዐ ፡ አዳም ፡ ሳያበዙ ፡ የቀሩ ፡ መነኰሴዎች ፡ አሉ ፡ ብለህ ፡ የጻፍከው ፡ ስሕተት ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበህ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ ባለመፈጸሙ ፡ የምትቆረቆር ፡ ከኾንክስ ፡ በነገሩ ፡ ያልደረስክበት ፡ መኾንህን ፡ አስረዳሃለሁና ፡ በቅን ፡ አስተያየት ፡ ተመልከትልኝ ።

ምንኵስና ፡ ማለት ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ማንም ፡ ሳያስገድደው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ብዕዓት ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ተቀደሰ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መስጠት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሥርዓተ ፡ ምንኵስናውን ፡ አድርሶ ፡ ቆቡን ፡ የሚጭንለት ፡ ቅናቱን ፡ የሚያስርለት ፡ አስኬማውን ፡ የሚያደርግለት ፡ አበ ፡ ምኔቱ ፤ የጀመረውን ፡ እንዲያስፈጽመው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸልይለታል ፤ ከጸብዐ ፡ አጋንንት ፡ የሚድንበትን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሰልፍ ፡ ያስተምረዋል ፡ እንጂ ፡ አያስገድደውም ። የሚያስገድደው ፡ ሕሊናው



ብቻ ፡ ነው ። አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ፫፻ ፡ አባቶቻችን ፡ በአንቀጸ ፡ መነኮሳት ፡ መጻፋቸው ፡ ሰይጣን ፡ በገዝሙት ፡ ድል ፡ እንዳይነሣቸው ፡ በታ ፡ ይዘው ፡ እንዲዋጉት ፡ ሲመክሯቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የጠቀስከውን ፡ ግብር ፡ ኹሉ ፡ ኅሩም ፡ ርኩስ ፡ ብለው ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ የዝሙት ፡ ጦር ፡ ሲቃወማቸው ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋቸውን ፡ ለመግታት ፡ እንዲመቻቸው ፡ በበአት ፡ ተቈተው ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሰው ፡ በመድ ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ ሥጋ ፡ ከመብላት ፡ ወይን ፡ ከመጠጣት ፡ ተከልክለው ፡ ይኖራሉ ።

በዚህ ፡ ድል ፡ ሲነሡት ፡ ሰይጣን ፡ ጦሩን ፡ ለውጦ ፡ በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ሲዋጋቸው ፤ አባ ፡ አባ ፡ ሲያሰኛቸው ፤ እነሱም ፡ እንደሱ ፡ ሰልፋቸውን ፡ ለውጠው ፡ ከበአታቸው ፡ ወጥተው ፡ አእምሮውን ፡ ያጣ ፡ እብድ ፡ መስለው ፡ ልብሳቸውን ፡ ጥለው ፡ የውሻ ፡ ሬሣ ፡ እስከመጐተት ፡ ደርሰው ፡ ማንም ፡ በማያውቀው ፡ ጦርነት ፡ ድል ፡ ይነሡታል ፡ (ስንክሳር ፤) ነሐሴ ፡ ፲፬ ።

ወይም ፡ በውስጥ ፡ ፍጹም ፡ መናንያን ፡ ሲኾኑ ፡ ዝሙትን ፡ የሚሹ ፡ ዓለማውያን ፡ እየመሰሉ ፡ ቤተ ፡ ዘማት ፡ እየገቡ ፡ በዝሙት ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙ ፡ ሴቶችን ፡ ወደ ፡ ንጽሕና ፡ የሳቡ ፡ አሉ ፡ (ስንክ ።) ፡ መጋ ፡ ፲፬ ፡ ፳፲ ።

ወይም ፡ ብቻቸውን ፡ ከመኖራቸው ፡ የተነሣ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ባለማየታቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደነሱ ፡ አድርጎ ፡ የሚያገለግል ፡ የሌለ ፡ እየመሰላቸው ፡ ሲታበዩ ፡ ከገዳሙ ፡ ይልቅ ፡ በዓለሙ ፡ ውስጥ ፡ የበለጡ ፡ የበለጡ ፡ አገልጋዮች ፡ እንዳሉት ፡ በመግለጽ ፡ ለመገሠጽ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጠርቶ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ የሚልካቸው ፡ ይገኛሉ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ።

ዮኾውም ፡ እንጦንዮስን ፡ ከአስካፍ ፤ መቃርዮስን ፡ ወደ ፡ ክልኤቲ ፡ አንስት ፡ ብብኑዳን ፡ ወደ ፡ ፊያታይ ፡ መዓንዝር ፤ አዩጳን ፡ ወደ ፡ ኖላዊ ፡ ትሩፍ ፡ እንደላካቸው ፡ ነው ፡ ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ፊልክ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ ተስእሎ ፡ ፴፯ ፡ ተመልከት ።

ወይም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ምውት ፡ አነ ፡ በኀበ ፡ ዓለም ፡ ወዓለምኒ ፡ ምውት ፡ በኀቤየ ፡ እያለ ፡ በዓለሙ ፡ ውስጥ ፡ ተገኝቶ ፡ ሲያስተምር ፡ እንደኖረ ፡ ሀብተ ፡ ንጽሕ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ማስተማር ፡ ክፍላቸው ፡ ኾኖ ፡ በከተማ ፡ እያስተማሩ ፡ እያጠመቁ ፡ እያቈረቡ ፡ የሚኖሩ ፡ አሉ ።

በዚያም ፡ በዚያም ፡ ቢኾን ፡ ድካማቸው ፡ ብፅዓታቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ መሥዋዕትነታቸውን ፡ የተቀደሰ ፤ መሥዋዕት ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ እነሱ ፡ ብፅዓታቸውን ፡ በተመቻቸው ፡ መንገድ ፡ ቢፈጽሙ ፡ ምን ፡ ቸገረህና ፡ በማታውቀው ፡ ነገር ፡ ገብተህ ፡ ትደክማለህ ። ይህንስ ፡ ትተህ ፡ አንደኛ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማይታበል ፡ ቃሉ ፡ በሰፈራችሁበት ፡ ላዳን ፡ ሳይሰፈርላችሁ ፡ በፈረዳችሁበት ፡ ሳይፈረድባችሁ ፡ አይቀርምና ፡ እንዳይፈረድባችሁ ፡ አትፍረዱ ። ባይንህ ፡ ያለውን ፡ ምሰሶ ፡ ሳትመለከት ፡ በወንድምህ ፡ ዐይን ፡ ያለውን ፡ ጉድፍ ፡ ለምን ፡ ትመለከታለህ ፡ (ማለት ፡) ባንተ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ታላቁን ፡ ኃጢአት ፡ ሳታስብ ፡ በወንድምህ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ታናሹን ፡ ስሕተት ፡ ለምን ፡ ትመለከታለህ ። ባንተ ፡ ዐይን ፡ ምሰሶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሳለ ፡ ወንድምህን ፡ ተወኝ ፡ ከይንህ ፡ ጉድፍ ፡ ላውጣልህ ፡ እንዴት ፡ ትለዋለህ ፡ (ማለት ፡) ባንተ ፡ ታላቅ ፡ ከባድ ፡ ኃጢአት ፤ እያለብህ ፡ ወንድምህን ፡ ስሕተትህን ፡ ላርቅልህ ፡ እንደምን ፡ ትለዋለህ ። አንት ፡ ግብዝ ፡ አስቀድመህ ፡ የራስህን ፡ ኃጢአት ፡ በንስሐ ፡ አርቅ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በወንድምህ ፡ ያለውን ፡ ስሕተት ፡ እንድታርቅለት ፡ ትኽናለህ ፡ ያለውን ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፭፫ ።

፪ተኛም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለኹሉም ፡ ሥራቸውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቅላቸዋል ፡ ጌታውን ፡ ሲያገለግል ፡ ሳለ ፡ የሰው ፡ ምንደኛ ፡ የምትነቅፍ ፡ አንተ ፡ ምንድን ፡ ነህ ፤ ቢሰንፍም ፡ ሐሳቡና ፡ ምኞቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነውና ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሶ ፡ ሊያጸናው ፡ ይችላል ። እንዲህ ፡ መልሶ ፡ ሊያጸናው ፡ የሚችል ፡ ሲኽን ፡ ወንድምህን ፡ የምትነቅፍ ፡ አንተ ፡ ምንድን ፡ ነህ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ተበላላጭ ፡ ተፈካካሪ ፡ ኽነሃልን ። ከክርስቶስ ፡ ፊት ፡ ለፍርድ ፡ እንቀርብ ፡ ዘንድ ፡ በኹላችን ፡ እያለብን ፡ ከዚያ ፡ አስቀድመህ ፡ የምትፈርድ ፡ አንተ ፡ ምንድን ፡ ነህ ። እግዚአብሔር ፡ ጉልበት ፡ ኹሉ ፡ ለኔ ፡ ይንበረከካል ፡ አንደበትም ፡ ኹሉ ፡ ለኔ ፡ ይገዛልና ፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፡ ስላለ ፡ ኹላችንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትሬ ፡ ቀርበን ፡ እንመረመር ፡ ዘንድ ፡ እንዳለን ፡ የታወቀ ፡ የተረዳ ፡ ነውና ፡ ወንድማችንን ፡ በማንነቅፍ ፡ ገንዘብ ፡ የማንነቅፍበትን ፡ ግብር ፡ እንያዝ ፡ እናስብ ፡ እንጂ ፡ ወንድማችንን ፡ አንንቀፍ ፡ ያለውን ፡ ተመልከተህ ፡ ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፬ ፡ ፲–፲፬ ። ፊልክስዩስ ፡ ወለእመ ፡ ርኢከ ፡ ፊያታየ ፡ አው ፡ ቀታሌ ፡ በል ፡ በአይቴ ፡ አአምር ፡ ለእመ ፡ ከነ ፡ ይበድረኒ ፡ በዊአ ፡ ኀበ ፡ ገነት ፡ ከመ ፡ ፈያታዊ ፡ ዘየማን ።

ሥርዓተ ፡ አበውን ፡ ተከትለው ፡ ያሉትን ፡ መንቀፍህ ፡ ይቅርና ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ወንበዴ ፡ ብታይ ፡ ፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ አዳምን ፡ ቀድሞት ፡ ገነት ፡ እንደገባ ፡ እኔንስ ፡ ይህ ፡ ወንበዴ ፡ ቀድሞኝ ፡ ይገባ ፡ እንደኾነ ፡ ምን ፡ ዐውቃለሁ ፡ በል ።

ወለእመ ፡ ርኢከ ፡ ዘማዌ ፡ ወኀጥአ ፡ በል ፡ በአይቴ ፡ አአምር ፡ ለእመ ፡ ከነ ፡ ዝንቱ ፡ ሀለዎ ፡ ያፍቅሮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወይብክ ፡ በአንተ ፡ ኃጠውኢሁ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ።

ኃጥእ ፡ ዘማዊም ፡ ብታይ ፡ ይህስ ፡ ምንአልባት ፡ ክርስቶስን ፡ ይወደው ፡ እንደኾነ ስለኃጢአቱስ ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ያዝን ፡ ያለቅስ ፡ እንደኾነ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ ፡ በል ፡ እንጂ ፡ ማንንም ፡ አትንቀፍ ።

ወዘይሔሊኬ ፡ ከመዝ ፡ ለዓለም ፡ ኢይወድቅ ፡ እምፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ። ኹልጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ከፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተለይቶ ፡ አይወርድም ።

እመሰ ፡ ፀነ ፡ ኀበ ፡ ትዝኅርት ፡ ይወድቅ ፡ እመልዕልት ።

ወደ ፡ ትዕቢት ፡ ቢሳብ ፡ ግን ፡ ከመዓርጉ ፡ ይወርዳል ፡ ያለውንና ፡ ክፍ ፡ ፫ ፡ ተስ ፡ ፴፩ ።

እስመ ፡ አበ ፡ አጋቶን ፡ ከነ ፡ ሰበ ፡ ርእየ ፡ ለእኍ ፡ እንዘ ፡ የኀጥእ ፡ ወየአብድ ፡ ለእመ ፡ ኰነኖ ፡ በሕሊናሁ ፡ ይብላ ፡ ለነፍሱ ፡ [illegible]



ጉኩ ፡ ወመኑ ፡ ረሰየከ ፡ ኰናኔተ ፡ ሎቱ ፡ ቦኑ ፡ አንቲ ፡ ትትኀሠሚ ፡ በእንተ ፡ ኃጣውኢሁ ፡ ተገኀሚ ፡ እንከ ፡ እምኔሁ ፡ እስመ ፡ ዘይትኀሠሠኪ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኃጣውእኪ ፡ ወእበድኪ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወትሰበር ፡ እንከ ፡ ሕሊናሁ ።

አባ ፡ አጋቶን ፤ ከአኃው ፡ አንዱ ፡ ሲበድል ፡ አይቶ ፡ ሕሊናው ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ የፈረደ ፤ ያነን ፡ ሰው ፡ የነቀፈበት ፡ እንደኾነ ፤ ነፍሱን ፡ ወንድምሽን ፡ የነቀፍሽው ፡ ስለምንድነው ፤ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ፈራጅ ፡ አድርጎ ፡ ማን ፡ ሾሞሻል ፤ በውኑ ፡ ሥላሴ ፡ በርሱ ፡ ኃጢአት ፡ አንችን ፡ በፍዳ ፡ ይመራመሩሻልን ፤ ነቀፋሽን ፡ ተዪ ፤ በሰው ፡ ከመፍረድ ፡ ተከልከዪ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚመራመርሽ ፡ በአንች ፡ ኃጢአት ፡ በድንቁርናሽ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሌላው ፡ ኃጢአት ፡ አይመራመርሽምና ፡ እያለ ፡ ሕሊናውን ፡ ከነቀፋ ፡ የመልሳት ፡ ነበረ ፡ የተባለውን ፡ ብትሰማ ፡ እንዴት ፡ በተሻለ ፡ ነበረ ፡ ከስንት ፡ ስሕተትስ ፡ በዳንክ ፡ ነበር ፡ ፊልክ ፡ ክፍ ፡ ፯ ፡ ተስ ፡ ፱፱ ።

በስሕተትና ፡ ድፍረት ፡ ለተናገርኩት ፡ ይቅርታ ፡ እለምናለሁ ፡ ስለምትለው ።

ይቅርታ ፡ የሚለምን ፡ ሰው ፡ ስሕተቱንና ፡ ድፍረቱን ፡ ዐውቆ ፡ ባለፈው ፡ ተጠጥቶ ፡ ከሚመጣው ፡ ተጠብቆ ፡ ሥርየት ፡ ቢለምን ፡ ይቅርታ ፡ ያገኛል ፡ እንጂ ፡ በስሕተቱና ፡ በድፍረቱ ፡ እንደጸና ፡ ኾኖ ፡ ይቅርታ ፤ እያለ ፡ ቢቀልድ ፡ ያዋቂ ፡ በዳይ ፡ ተብሎ ፡ ከሚፈረድበት ፡ በቀር ፡ ይቅርታ ፡ የሚያሰጥ ፡ አይመስለኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ እድግተ ፡ በለዓምን ፡ እብን ፡ ቢታንያን ፡ በተአምራት ፡ ያናገረ ፡ ጌታ ፡ አን ንም ፡ በ፤ አምራት ፡ ስላናገርህ ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ በ፰ተኛው ፡ ድርሳን ፡ ከሰይጣናት ፡ ይልቅ ፡ መልኩ ፡ የከፋ ፡ መዓዛው ፡ የከረፋ ፡ ሰይጣን ፡ ፀሪፍ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ሲጸልይ ፡ ይሰማኝ ፡ ይመስልሃልን ፤ ሥጋ ፡ ወደሙንም ፡ በሚለውጥበት ፡ ጊዜ ፡ የሚለምጥ ፡ ይመስልሃልን ፡ እያለ ፡ ሲሳደብ ፡ አየሁት ፡ ያለውን ፡ ሰይጣን ፡ ፀሪፍ ፡ ከንተ ፡ አርቆ ፡ ይቅር ፡ ይበልህ ፡ አረ ፡ መን ፡ ድር ፡ ፰ ።

፳፱ ስለዚህ ፡ ከመንኰሱ ፡ አይሠሩም ፡ ካልሠሩም ፡ አይብላምና ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ሊቆጠርላቸው ፡ በማለት ፡ ለምውታን ፡ ጽድቅ ፡ ለናንተም ፡ ክብር ፡ ሊኾናችሁ ፡ ሳትሠሩ ፡ ለኛ ፡ መግቡን ፡ የሚል ፡ አግራምቢጥ ፡ የኾነ ፡ በዓላትን ፡ ብቻ ፡ የሚቆጥር ፡ አትሥሩ ፡ የሚል ፡ መጻሕፍተ ፡ ማታለያ ፡ አዋልድ ፡ የተባለ ፤ (ልበ ፡ ወልድ ፡) መነኰሴዎች ፡ ሰበኩትና ፡ ደብተሮችም ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ እያጋነኑ ፡ ውሸትን ፡ ጨምረው ፡ እየጻፉ ፡ ከሰከሱት ፡ ስለምትለው ።

ከመነኰሱ ፡ አይሠራም ፡ ማለትህ ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ። ምንኵስና ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራበት ፡ የተመደበ ፡ ሕገ ፡ ትሩፋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሥራ ፡ ፈትነት ፡ የተመደበ ፡ ሕግ ፡ አይደለም ።

ላንተ ፡ ሥራ ፡ የሚመስልህ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ። በእንተ ፡ ዘበላዕክሙ ፡ ኀብስተ ፡ ወጸገብክሙ ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ መከተል ፡ ስለኾነ ፡ ባይመስልህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መነኰሳትስ ፡ ተገበሩ ፡ እንከ ፤ አከ ፡ ለመብልዕ ፡ ኃላፊ ፡ አላ ፡ ለመብልዕ ፡ ዘይነብር ፡ ለሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘይሁበክሙ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ያለውን ፡ ተመልከተው ፡ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፳፮ ፡ ወጣንያኑ ፡ በ፮ቱ ፡ [illegible] ፡ ከሚያደርሱት ፡ ጸሎትና ፡ ሰጊድ ፡ ጋራ ፡ ዘር ፡ እየዘሩ ፡ ተክል ፡

www.ethiopianorthodox.org

እየተከሉ ፡ ሰሌን ፡ እየታተ ፡ እንቅብ ፡ እየሰፉ ፡ በመርዳት ። ፍጹማኑም ፡ ከ ወ ፡ ተለይተው ፡ ከበዓታቸው ፡ እግራቸውን ፡ በቀዊም ፡ እጃቸውን በሰፊሕ ፤ አንገታቸውን ፡ በአንቃዕድዎ ፡ ሠርተው ፡ ቀጥተው ፤ ወይም ፡ በሰጊድ ፡ ሲነሡ ፡ ሲወድቁ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ተወስነው ፡ ይገኛሉ ።

በዓለም ፡ የሚገኙ ፡ መነኮሳትም ፡ በማስተማር ፤ በማጥመቅ ፤ በማቍረብ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በማገልገል ፡ ጽሙዳን ፡ ኾነው ፡ ይገኛሉ ፡ እንጂ ፡ ምንኵስና ፡ የሥራ ፡ ፈትነት ፡ ሞያ ፡ አይደለም ።

ካልሠሩ ፡ አይበላም ፡ ማለትህ ፡ እውነትህ ፡ ነው ። የኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጌታ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ያለውን ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ዘኢይፈቅድ ፡ ይትቀነይ ፡ ኢይሴሰይ፡ በዕምውነ ፡ ይትገበሩ፡ ተግባሮሙ፡ ወይሴሰዩ፡ ሲሳዮሙ፡ ያለውን፡ ቃሎቃልችና ፡ ፪ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ልጆቿን ፡ ሠርተው ፡ ራሳቸውንና ፡ ሌላውንም ፡ እንዲረዱ ፡ ታዝዛለች ፡ እንጂ ፡ በሥራ ፡ ፈትነት ፡ እንዲኖሩ ፡ አታዝዝም ። በሕጓ ፤ የሚተዳደሩ ፡ ልጆቿም ፡ በላይኞች ፡ መስመሮች ፡ በዘረዘርኩልህ ፡ ሥራዎች ፡ ተሰማርተው ፡ ይገኛሉ ፡ እንጂ ፡ ሳትሠሩ ፡ እኛን ፡ መግቡን ፡ የሚል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አይገኝም ። ይህ ፡ ንግግር ፡ አንተ ፡ ከዐመፅ ፡ መዝገብ ፡ ልቡናህ ፡ አንቅተህ ፡ የተናገርከው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አይደለም ።

ሳትሠሩ ፡ ለኛ ፡ መግቡን ፡ ይላሉ ፡ ማለትህ ፡ ውሸትህ ። እናንተ ፡ ሠርታችሁ ፡ እኛን ፡ መግቡን ፡ ይላሉ ፡ ብትል ፡ እንኳ ፡ እውነትን ፡ ይኾን ፤ ሐሰትን ፡ ይኾን ፡ ብሎ ፡ የሰሚን ፡ ልቡና ፡ ባጠራጠረ ነበረ ፤ ካልሠሩማ ፡ ምኑን ፡ ይመግቧቸዋል ፡ እንደነሱ ፡ ድኖች ፡ መሆናቸው ፡ አይደለምን ። ንግግርህ ፡ ኹሉ ፡ ገብቶ ፡ ሲመረምሩት ፡ እንደዚህ ፡ መጨበጫ ፡ የሌለው ፡ ሐሰት ፡ ብቻ ፡ ኾኖ ፡ ይገኛል ።

ለምውታን ፡ ጽድቅ ፡ ለናንተም ፡ ክብር ፡ ሊኾናችሁ ፡ ስለምትለውና ፡ በዓላትን ፡ ብቻ ፡ የሚቆጥር ፡ ስለምትለው ። ለበዓላትና ፡ ለተዝካር ፡ ለዝክር ፡ አርእስት ፡ ሰጥተህ ፡ አንቀጽ ፡ ለይተህ ፡ ስለጻፍክ ፡ መልሱን ፡ በየቦታቸው ፡ እጽፍልሃለሁና ፡ በያንቀጹ ፡ ተመልከት ።

መጻሕፍተ ፡ ማታለያ ፡ አዋልድ ፡ ስለምትለው ፡ በጠቅላላው ፡ የመጻሕፍትን ፡ እውነተኞችናና ፡ ሐሰተኞችን አሥራው ፡ መጻሕፍትና ፡ አዋልድ ፡ መጻሕፍትን ፡ ስልት ፡ ስልታቸውን ፡ ለይቼ ፡ እጽፍልሃለሁና ፡ ስለ ፡ ፃ ዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በጻፍከው ፡ አርእስት ፡ ተመልከት ።

ስለዚህም ፡ የጠቀስከው ፡ ኤር ፡ ፳፫ ፡ ፴–፴፪ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ በነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገሬን ፡ በሚሰርቁ ፡ ላይ ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከባልንጀራው ፡ እነሆ ፡ በነቢያት ፡ ላይ ፡ ቆምሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ምላሳቸውን ፡ የሚወስዱ ፡ የሚሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ ፡ ይላል ።

እንግዲህ ፡ በእኛ ፡ ውስጥ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አየሁት ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ላከኝ ፡ የሚል ፡ የለብንምና ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ መጥቀስህ ፡ በከንቱ ፡ ነው ፡ ይህስ ፡ ጥቅስ ፡ አንተ ፡ ዐዋጅ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ እኔ ፡ ልልክህ ፡ ነኝና ፡ ተነሥተህ ፡ ወገብህን ፡ ታጠቅ ፡ በፊታቸውም ፡ እንዳላሳፍርህ ፡ ብላቴና ፡ ነኝ ፡ ብለህ ፡ አትፈር ፡ አለኝ ፡ ባልክ ፡ ጊዜ ፡ በሚገባ ፡ ተጠቅሶልሃልና ፡ ያነን ፡ ተመልከት ።

፴፩ ርኅሩኅ ፡ ሕዝባችንም ፡ በባሕርዩ ፡ አጸድቅ ፡ ባይ ፡ በለኾነ ፡ ጕደሎዎቹ ፡ ምሉዎቹ ፡ (ጻድቃን) መበለው ፡ ሰለታዩት ፡ ጽፈው ፡ የሰጡትን ፡ ውሸት ፡ ተቀብሎ ፡ ገዝቶ ፡ የነገሩትን ፡ ብቻ ፡ ሰምቶ ፡ እንዳዘዙት ለነሱ ፡ ፈርቶ ፡ በዓላትን ፡ እየቈጠረ ፡ ለሥጋውና ፡ ለነፍሱ ፡ የሚጠቀምበትን ነገር ፡ ሳያገኝ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ኾኖ ፡ በንዝኅላል ፡ አጉል ፡ ይኖራል ፡ ስለምትለው ።

(ሀ) ርኅሩኅ ፡ ሕዝባችን ፡ ገንዘብ ፡ ከማከማቸት ፡ መስጠት ፤ ከመብላት ፡ መጾም ፡ ዘወትር ፡ በተግባረ ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ ጽሙድ ፡ ከመኾን ፡ በዓላትን እየቈጠሩ ፡ ለተግባረ ፡ ነፍስም ፡ ጽሙድ ፡ መኾን ፡ የታዘዘ ፡ ሕግ ፡ የተሠራ ፡ ሥራት ፡ መኾኑን ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ያወቀ ፡ የተረዳ ፡ ስለኾነ ፤ ዐውቆ ፡ ወዶ ፡ ይሠራዋል ፡ እንጂ ፡ እነሱን ፡ ፈርቶ ፡ አይሠራውም ፡ ሐሰትህ ፡ ነው ። ባንተ ፡ አፍ እንኳ ፡ ርኅሩኅ ፡ ሕዝባችን ፡ ያሰኘው ፡ ይህን ፡ ዐውቆ ፡ ቢሠራው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሳያውቅማ ፡ ተገዶ ፡ የሚሠራው ፡ ከኾነ ፡ ምን ፡ ርኅሩኅ ፡ ያሰኘው ፡ ነበረ ። አንተ ፡ ግን ፡ ለእስራኤል ፡ ኹለተኛ ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ተቀዳሚ ፡ ኾኖ ፡ ከሰሎሞንና ፡ ከንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ጀምሮ ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖረውን ፡ ሕዝብ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ እንደሚነዳ ፡ ከብት ፡ ወይም ፡ እንደሚዘወር ፡ መኪና ፡ አድርገኸው ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ እየተመራ ፡ ለሥጋውና ፡ ለነፍሱ ፡ የሚጠቅመውን ፡ ሳያውቅ ፡ በንዝኅላል ፡ አጉል ፡ ይኖራል ፡ እያልክ ፡ ለመሳደብ ፡ የደፈርክበት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ድንቁርና ፡ ቢሰፍርብህ ፡ ይኾን ፡ ይገርማል ፡ ይደንቃል ።

(ለ) ጕደሎቹ ፡ ምሉዎች ፡ መስለው ፡ ታይተውት ፡ ስለምትለው ።

ምሉውና ፡ ጐደሎው ፤ ኃጥኡና ፡ ጻድቁ ፡ ተለይቶ ፡ የሚታወቅበት ፡ ጊዜው ፡ ገና ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ወዓዲ ፡ ኢተዐውቀ ፡ ለነ ፡ ምንተ ፡ ንከውን ፡ ፩ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፪ ብሎ ፡ አስጠንቅቆናልና ፡ ኹላችንም ፡ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡ ውስተ ፡ መንሡት እያልን ፡ በፍርሃት ፡ ከመጠባበቅ ፡ በቀር ፡ ልንመጻደቅበት ፡ አይገባንም ።

ለዚሁ ፡ ምስክር ፡ አድርገህ ፡ የጠቀስከው ፡ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ፡ ኤልያስም ፡ ወደ ሕዝቡ ፡ ቀርቦ ፡ እስከመቼ ፡ በኹለት ፡ ልባችሁ ፡ ባንጕል ፡ ስታነክሱ፡ ትኖራላችሁ ፡ እግዚአብሐር ፡ አምላክ ፡ እንደኾነ ፡ እርሱን ፡ ተከተሉ ፤ ብዔልም ፡ አምላክ ፡ እንደኾነ ፡ ተከተሉት ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ አልመለሱለትም ፡ ይላል ። ኤልያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የተናገራቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ክደው ፡ ብዔል ፡ የሚባል ፡ ጣዖትን ፡ ያቆሙትን ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አልተናገረውም ። እኛም ፡ ኤልያስ ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፴፮ ፡ ቍ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሐር ፡ ሆይ ፡ ብሎ ፡ የእሊህን ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶች ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ ለምኖ ፡ ልመናው ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ደረሰለት ፡ አውቀን ፡ የኒህን ፡ ቅዱሳንና ፡ የሌሎችንም ፡ ቅዱሳን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ስም ፡ ጠርተን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምናለን ፡ እንጂ ፡ ብዔልን ፡ አናመል ክም ፡ እንግዲህ ፡ ጣዖት ፡ ሳናመልክ ፡ በሃይማኖትና ፡ በምግባር ፡ ኤልያስን ፡ መስለን ፡ በምንገኞች ፡ሰዎች ፡ ላይ ፡ ጽፈህ ፡ ከተገኘህ ፡ አስመሳይ ፡ አታላይ ፡ጎደሎ ፡ ሙባል ፡ ላንተ ፡ የተገባ ፡ ስምህ ፡ መኾኑን ፡ ተረዳ ።

(ሐ) ከዚህ ፡ ቀጥለህ ፡ መልክዐ ፡ ማርያም ፡ ለክግደኪን ፡ ሕይወትየ ፡ በንዝኅላል ፡ እመ ፡ ተሠልጠ ፡ ወኅልቀን ፡ ጠቅሰሃል ።

ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ መስመር ፡ መጻሕፍት ፡ ማታለያ ፡ አዋልድ ፡ የተባሉ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መነከሳቱ ፡ ሰበኩት ፡ ብለህ ፡ አዋልድ ፡ መጻሕፍትን ፡ ስት ነቅፍ ፡ ተናግረህ ፡ ነበረ ። እኛ ፡ ከጸሎት ፡ በቀር ፡ ለሃይማኖትና ፡ለምግባር ፡ ምስ ክር ፡ አድርገን ፡ የማንጠቅሳቸውን ፡ መልክ ፡ መልኮችን ፡ በቂ ፡ ምስክሮች ፡ አድር ገህ ፡ ከጠቀስክልኝ ፡ ከላይ ፡ የተናገርከው ፡ አዋልድ ፡ መጻሕፍት፡ ማታለያ ፡ መባላቸው ፡ ቀርቶ ፡ ባንተው ፡ ቃል ፡ ተሠይመው ፡ ለምስክርነት ፡ የበቁ ፡ እውነተኞች ፡ መጻሕፍት ፡ መኾናቸውን ፡ ማረጋገጥህን ፡ አስተውል ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ የጠቀስካቸውን ፡ አዋልድ ፡ ምናልባት ፡ እኔ ፡ የጠቀስኩ ልህ ፡ እንደኾነ ፡ ቅር ፡ እንዳይልህና ፡ ሰው ፡ እንዳይታዘብህ ፡ አደራ ።

ወደ ፡ ሥር ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ፡ ሕይወትየ ፡ በንዝኅላል ፡ እመ ፡ ተሠልጠ ፡ ወኅልቀ ፡ ወስክኒ ፡ ክራማተ ፡ እስከ ፡ እገብር ፡ ጽድቀ ፡ ማለት ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ እስመ ፡ ኖኅ ፡ እምሥዕርተ ፡ ርእስየ ፡ ጌጋይየ ፡ ከመ ፡ ጾር ፡ ክቡድ ፡ ከብደ ፡ ላዕ ሌየ ። ኃጢአትየ ፡ ዘበንዕስየ ፡ ወዕበድየ ፡ ኢትዝክር ፡ ሊተ ። ወሥረይ ፡ ሊተ ፡ ኵሎ ፡ ኃጢአትየ ፡ እስመ ፡ ብዙኅ ፡ ውእቱ ። ንግረኒ ፡ ውኁዶን ፡ ለመዋዕልየ ፡ ወኢ ትሰደኒ ፡ በመንፈቀ ፡ ዓመትየ ። ብሎ ፡ የጸለየውን ፡ ጸሎት ፡ የመሰለ ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መዝ ፡ ፴፫ ፡ ፺፩ ፡ ንዝኅላልነት ፡ አይደለም ፡ ንዝኅላልነትስ ፡ እንዳንተ ፡ በማያው ቁት ፡ ነገር ፡ ገብቶ ፡ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ እያማቱ ፡ መጻሕፍትን ፡ እያገለባበጡ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ የተጠሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ጥንቆላ ፡ እየጻፉ ፡ ባታላይነት ፡ የሕዝብን ፡ ገንዘብ ፡ መሸለግ ፡ ነው ።

፴፩ ለአዋልድ ፡ አውራቸው ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ፡ የሚባለው ፡ ደግሞ ፡ መላእክት ፡ ወደ ፡ምድር ፡ ወርደው ፡ ሴቶችን ፡ እየመረጡ ፡ አግብተው ፡ ፪ሺ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ቁመታቸው ፡ ከነፋስ ፡ ጋራ ፡ የሚጋጩ ፡ አንድ ፡ ዝኆን ፡ ባንድ ፡ እጃቸው ፡ አንሥተው ፡ በፀሐይ ፡ አቅርበው ፡ ጠብሰው ፡ የሚውጡ ፡ ወንዶች ፡ ልጆችን ፡ ወለዱ ፡ ስመ ፡ ነገዳቸውም ፡ አዛሄልና ፡ አዛዛሄል ፡ ይባሉ ፡ ነበረ ፡ ይላል ። ሄኖክ ፡ ግን ፡ ከአዳም ፡ ፯ተኛው ፡ ነው ፡ ሄኖክ ፡ ማቱሳላ ፡ ላሜኅ ፡ ኖኅ ፡ በኖኅ ፡ ዘመን ፡ የማየ ፡ አይኅ ፡ ጥፋት ፡ሲኾን ፡ በአምላክ ፡ ትእዛዝ ፡ ከተፈጠረው ፡ ፍጥ ረቱ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ በዘመዱ ፡ ከኖኅ ፡ መርከብ ፡ ገብቶ ፡ ለዘር ፡ ቀርቶ ፡ ስለ ፡ ዳነ ፡ ኹሉም ፡ እስካ ሁን ፡ ድረስ ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፮ ፡ ፲፫—፳፪ ፡ ፯ ፡ ፩—፳፬ ። ፰ ፡ ፲፭—፳፪ ። የነአዛሄልና ፡ አዛዛሄል ፡ ዘር ፡ ግን ፡ በዓ ለም ፡ ላይ ፡ ስሌለ ፡ ፍጹም ፡ የውሸት ፡ ውሸትና ፡ የባልቴቶች ፡ ተረት ፡ መኾኑን ፡ በዚሁ ፡ ጭር ፡ ማስረጃ ፡ ይታወቃል ፡ ስለምትለው ።

አንተ ፡ ባታውቅ ፡ የአዋልድ ፡ ብቻ ፡ አውራ ፡ ትለዋለህ ፡ እንጂ ፡ ሄኖክስ ፡ ለትውልድ ፡ ተቀዳሚ ፡ እንደመኾኑ ፡ መጠን ፡ ምሥጢረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማየ ትና ፡ ትንቢት ፡ በመናገር ፡ መጻሕፍትንም ፡ በመጻፍ ፡ ለነቢያትና ፡ ለሐዋርያትም ፡



መሪ ፡ ፈ ታውራሪ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ የሚያሳፍር ፡ አይደለም ። ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ሄኖክ ፡ ከደረሰበት ፡ ማዕርግ ፡ ደርሰው ፡ ሄኖክ ፡ ያየውን ፡ ምሥጢር ፡ አይተው ፡ የሱን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ተናገሩ ፡ እንጂ ፡ ሄኖክ ፡ ከተናገረው ፡ ቃል ፡ ወጥ ተው ፡ አልጻፉም ። ይህነኑም ፡ ኃይለ ፡ ቃሉን ፡ ከኃይለ ፡ ቃላቸው ፡ ትንቢቱን ፡ ከትንቢታቸው ፡ ምሥጢሩን ፡ ከምሥጢራቸው ፡ እያስማማህ ፡ በሰፊው ፡ አስረዳሃለ ሁና ፡ ከዐይኅ ፡ ልቡናህ ፡ ላይ ፡ ተጋርዶ ፡ ያለውን ፡ የእንቢተኝነትና ፡ የድንቁርና ፡ መጋረጃ ፡ ገለጥ ፡ አድርገህ ፡ ተመልከት ።

፩ኛ ፡ ጌታ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ለእስራኤል ፡ በግሩም ፡ ራእይ ፡ መታየቱን ፡ ወእ ምህየ ፡ ይከይድ ፡ ዲበ ፡ ሲና ፡ ደብር ፡ ወያስተርኢ ፡ በትዕይንቱ ፡ ወያስተርኢ ፡ በጽንዐ ፡ ኃይሉ ፡ እምሰማይ ፡ ወይፈርህ ፡ ኵሉ ፡ ወያድለቀልቁ ፡ ትጉሃን ፡ ወይነሥ ኦሙ ፡ ፍርሃት ፡ ወረዓድ ፡ ዐቢይ ፡ እስከ ፡ አፅናፈ ፡ ምድር ።

ከዚያም ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ በከተማው ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በጌትነቱ ፡ ይገለጣል ። ኹሉ ፡ ይፈራል ፡ ትጉሃንም ፡ ይነዋወጻሉ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ታላቅ ፡ ፍርሃትና ፡ እንቅጥቅጥ ፡ ይይዛቸዋል ፡ ብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ ተናገረል ። ፩ ፡ ፬፱ ።

ይህ ፡ ትንቢት ፡ በሙሴ ፡ ጊዜ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሙሴ ፡ ያይን ፡ ምስክር ፡ ኾኖ በ፫ተኛው ፡ ቀን ፡ በማለዳ ፡ ጊዜ ፡ ነጐድጓድና ፡ መብረቅ ፡ ኾነ ከባድም ፡ ደመና ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ኾነ ። የመለከቱም ፡ ድምፅ ፡ እጅግ ፡ ይበረታ ፡ ነበረ ። በሰፈ ሩም ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ተንቀጠቀጡ ። የሲናም ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፡ ይጤስ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔር ፡ በእሳት ፡ ስለወረደበት ፡ ከርሱም ፡ ጢስ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። እንደ ፡ እቶን ፡ ጢስ ። ተራራውም ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ ይናወጥ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ የሄ ኖክ ፡ ትንቢት ፡ መፈጸሙን ፡ መስክሯል ፡ ዘፀአ ፡ ፲፱ ከ፲፮–፳፰ ዳን ፯ ፱–፲፩ ።

በሐዲስም ፡ ቅዱስ ፡ጳውሎስ፡ እስመ ፡ ኢመጻእክሙ ፡ኀበ ፡ እሳት ፡ ዘያስተርኢ ፡ ዘይነ ድድ ፡ ወጽልመት ፡ ግፍትዕት ፡ ወቆባር ፡ ወዐውሎ ፡ ወጣቃ ፡ ወድምፀ ፡ መጥቅዕ ፡ ወቃለ ፡ ነገር ፡ ዘሰምዑ ፡ እሙንቱ ፡ ወኢፈቀዱ ፡ ይድግሙ ፡ ተናግሮቶሙ ፡ እስመ ፡ ስእንዎ ፡ አጽምዖቶ ፡ ለዘተናገሮሙ ፡ ወእመኒ ፡ እንስሳ ፡ ቀርበ ፡ ለውእቱ ፡ ደብር ፡ ይዌግርዎ ፡ ወከመዝ ፡ ግሩም ፡ ውእቱ ፡ ዘአስተርአዮሙ ፡ ወሙሴኒ ፡ ይቤ ፡ ርዑድ ፡ ወድን ጉጽ ፡ አነ ።

የሚነድ ፡ እሳት ፡ ወደሚታይበት ፤ ጽጋግና ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ይያዝ ፡ የመለሰ ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ የቆመ ፡ ጨለማ ፡ ወደሚታይበት ፤ የነጋሪት ፡ ድምፅ ፡ ወደተሰማበት ፤ እስራኤል ፡ የተነጋገራቸው ፡ እሱን ፡ መስማት ፡ ስላልተ ቻላቸው ፡ ኹለተኛ ፡ ሊናገራቸው ፡ ያልወደዱት ፡ ቃል ፡ ወደተሰማበት ፡ ወደ ፤ ደብረ ፡ ሲና ፡ አልወጣችሁም ። ከብትም ፡ ወደተራራው ፡ ቢቀርብ ፡ ወግረው ፡ ይገሉት ፡ ነበረ ። ይህ ፡ ኹሉ ፤ ግሩም ፡ ነገር ፡ ስለታያቸው ፡ ነው ። ሙሴም ፡ ርዑድ ፤ ድንጉፅ ፡ ነኝ ፡ አለ ፡ ብሏል ፡ ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፲፰–፳፪ ።

ከሊቃውንትም ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ እምደብረ ፡ ሲና ፡ ወዕአ ፡ እሳት ፡ ወጢስ ፡ ወእምኔኪሰ ፡ ኮነ ፡ አምላክ ፡ ወሰብአ ። እምደብረ ፡ ሲና ፡ ኮነ ፡ ድንጋፄ ፡ ወሐውክ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ላዕለ ፡ አይሁድ ፡ ወእምኔኪ.ሰ ፡ ከነ ፡ ድንጋፄ ፡ ወሐውክ ፡ ላዕለ ፡ ሄሮድስ ፡ ወላዕለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ላዕለ ፡ ዲያብሎስ ፡ ወላዕለ ፡ አጋንንቲሁ ።

ከደብረ ፡ ሲና ፡ እሳትና ፡ ጢስ ፡ ወጣ ፤ ካንቺ ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ክርስቶስ ፡ ተወለደ ። በደብረ ፡ ሲና ፡ ከታየው ፡ እሳትና ፡ ጢስ ፡ የተነሣ ፡ በአይሁድ ላይ ፡ ድንጋፄና ፡ ሁከት ፡ ተደረገ ። ካንቺም ፡ የተነሣ ፡ በሄሮድስና ፡ በሠራዊቱ ፡ በዲያብሎስና ፡ በአጋንንቱ ፡ ላይ ፡ ድንጋፄና ሁከት ፡ ኾነ ።

ቃለ ፡ አብ ፡ ሕያው ፡ ዘወረደ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ወወሀበ ፡ ሕገ ለሙሴ ወከነ ፡ ርዕሰ ፡ ደብር ፡ በጊሜ ፡ ወጢሰ ፡ በጽልመት ፡ ወነፋስ ፡ ወበድምፀ ፡ ቃለ ፡ አቅርንት ፡ ይጌሥጽ ፡ ለእለ ፡ ይቀውሙ ፡ በፍርሃት ፡ ውእቱኬ ፡ ዘወረደ ፡ ኀቤኪ ፡ አደብር ፡ ነባቢት ።

ነባቢት ፡ ደብር ፡ ሆይ ፡ ወዳንቺ ፡ የወረደው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ወርዶ ፡ ለሙሴ ፡ ሕግን ፡ የሰጠው ፤ የተራራውን ፡ ራስ ፡ በጉምና ፡ በጢስ ፡ በጨለማና ፡ በነፋስ ፡ የጋረደው ፤ ፈርተው ፡ የቆሙትንም ፡ በነጋሪት ፡ ድምፅ ፡ የገሠጸው ፡ የአብ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ነው ። ብሎ ፡ ወስዶታል ። እንግዲህ ፡ ለብሉያትም ፡ ለሐዲሳትም ፡ ለሊቃውንትም ፡ መሠረት ፡ ሄኖክ ፡ እንደ ኾነ ፡ ተመልከት ።

፪ተኛም ፡ ዕፀ ፡ ሕይወትን ፡ አይቶ ፡ ወርኢኩ ፡ ፯ተ ፡ አድባረ ፡ ክቡራነ ፡ ወኵሎ ፡ ፩እምነ ፡ ፩ወየዐውድዎ ፡ ዕፀወ ፡ መዓዛ ፡ ወሀሎ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ዕፅ ፡ አልቦ ፡ ግሙራ ፡ አመ ፡ ፄነወኒ ፡ ወአ.፩ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ወበዕዳንሂ ፡ ዘከማሁ ፡ ኢኮነ ፡ ዘይምዕዝ ፡ እምኵሉ ፡ መዓዛ ፡ ወቈጽሉ ፡ ወጽጌሁ ፡ ወዕፀ ፡ ኢይፀመሂ ፡ ለዓለም ፡ ወፍሬሁኒ ፡ ሠናይ ፡ ወፍሬሁሰ ፡ ከመ ፡ አስካለ ፡ በቀልት ። ወውእተ ፡ጊዜ ፡ እቤ ፡ ነዋ ፡ ዝንቱ ፡ ሠናይ ፡ ዕፅ ፡ ወሠናይ ፡ ለርእይ ፡ ወአዳም ፡ ቈጽሉ ፡ ወፍሬሁኒ ፡ ሞገስ ፡ ጥቀ ፡ ለርእየ ፡ ገጽ ።

ወአውሥአኒ ፡ ሚካኤል ፡ ፩እመላእክት ፡ ቅዱሳን ፡ ወይቤለኒ ፡ ሄኖክ ፡ ምንተ ፡ ትሴአል ፡ በእንተ ፡ መዓዛሁ ፡ ለዝ ፡ ዕፅ ፡ ወአውሣእክዎ ፡ እንዘ ፡ እብል ፡ እፈቅድ ፡ አእምር ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ዕፅ ፡ ወአውሥአኒ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዝንቱ ፡ ደብር ፡ ዘርኢከ ፡ ነዊኀ ፡ ዘርእሱ ፡ ይመስል ፡ መንበሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንበሩ ፡ ውእቱ ፡ ኀበ ፡ ይነብር ፡ ቅዱስ ፡ ወዐቢይ ፡ እግዚአ ፡ ስብሐት ፡ ወዝንቱኒ ፡ ዕፀ ፡ መዓዛ ፡ ሠናይ ፡ ወአ.፩ ፡ ዘሥጋ ፡ አልቦ ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡ ይግሥሦ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ዐቢይ ፡ ኰነኔ ፡ አመ ፡ ይትቤቀል ፡ ኵሎ ፡ ወይትፌጸም ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

የከበሩ ፡ የከበሩ ፡ ፯ ተራራዎች ፡ አየሁ ። ኹሉም ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ልዩ ልዩ ፡ የኾኑ ፡ ዕንጨቶች ፡ ከበዋቸዋል ፡ ከውስጣቸውም ፡ መቸም ፡ ቢኾን ፡ እንደ ርሱ ፡ አርነ ፡ የሸተተኝ ፡ ሌላ ፡ ዕፅ ፡ የሌለ ፡ ከሽቱ ፡ ኹሉ ፡ የበለጠ ፡ የሽቱ ፡ ዕንጨት ፡ አለ ። ዛፉም ፡ ቅጠሉም ፡ አበባውም ፡ ለዘለዓለም ፡ አይጠወልግም ። ፍሬውም ፡ ያማረ ፡ ነው ። ያውም ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ፍሬ ፡ ያለ ፡ ነው ። ያንጊዜ ፡ ይህ ፡ ዕንጨት ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ቅጠሉም ፡ ያማረ ፡ ነው ። ፍሬውም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡



ለማየት ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነው ፡ አልኩ ። ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሄኖክ ፡ ስለዚህ ፡ ዕንጨት ፡ ሽታ ፡ ምን ፡ ትጠይቃለህ ፡ አለኝ ። ስለ ርሱ ፡ ላውቅ ፡ እወዳለሁ ፡ ይልቁንም ፡ የዚህን ፡ ዕንጨት ፡ ነገር ፡ ላውቅ ፡ እወዳለሁ ፡ ብዬ ፡ መለስኩለት ። ጫፉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዙፋን ፡ መስሎ ፡ የምታየው ፡ ይህ ፡ ረዢም ፡ ተራራ የክብር ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቀመጥበት ፡ ዙፋኑ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ሽታው ፡ ያማረ ፡ እንጨት ፡ እስከ ፡ ቁ..ጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ይነካው ፡ ዘንድ ፡ ከሥጋዊ ፤ ከደማዊ ፡ ሰው ፡ ወገን ፡ ላንዱ ፡ እንኳ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ ሲል ፡ መለሰልኝ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ ፯ ፮–፲፮ ።

ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ሙሴ ፡ ይህን ፡ ሄኖክ ፡ ያየውን ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ አይቶ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ከምድር ፡ ዛፍን ፡ ኹሉ ፡ አወጣ ፡ መልኳ ፡ ያማረውን ፡ መብልዋም የጣፈጠውን ፡ የሕይወትንም ፡ ዛፍ ፡ በገነት ፡ መኻከል ፡ ተከለ ፡ ብሎ ፡ ከሄኖክ ፡ አምጥቶ ፡ ተናግሯል ፡ ዘፀአ ፡ ፪ ፡ ፱ ።

ከዐበይት ፡ ነቢያት ፡ አንዱ ፡ ሕዝቅኤልም ፡ ሄኖክ ፡ ያየውን ፡ ዕፀ ፡ ሕይወትን፡ አይቶ ፡ በወንዙም ፡ ዳር ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ የሚያፈራው ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይበቅላል ፡ ቅጠሉ ፡ የማይረግፍ ፡ ፍሬው ፡ የማይጐድል ፡ በየወሩ ፡ ኹሉ ፡ ዐዲስ ፡ ፍሬ ፡ ያፈራ ወኀዎች ፡ ከመቅደስ ፡ ይወጣሉና ፡ ፍሬውም ፡ ለመብል ፡ ይኾናል ፡ ቀጥሉም ፡ ለመድኀኒት ፡ ብሏል ፡ ሕዝ ፡ ፵፯ ፡ ፲፪ ።

ከሐዋርያትም ፡ አንዱ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ይህንኑ ፡ ሄኖክ ፡ ያየውን፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ አይቶ ፡ ድል ፡ ለነሣው ፡ በአግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የሕይወት፡ ዛፍ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ እሰጠዋለሁ ፡ አለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሏል ፡ ራእ ፡ ፪ ፯ ።

ደግሞም ፡ በደባባዩዋም ፡ መካከል ፡ በፈሳሹ ፡ ወንዝም ፡ ዳር ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ አለች ፡ አሥራ ፡ ኹለት ፡ ፍሬም ፡ ትሰጣለች ፡ በወር ፡ በወርም ፡ ታፈራለች ፡ የዛፊቱም ፡ ቅጠል ፡ የአሕዛብ ፡ ፈውስ ፡ ነው ፡ ብሏል ፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፪ ፡ ፪ ፡

ይህንንም ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት ፡ በአዳም ፡ በደል ፡ ምክንያት ፡ በቀጥታ ፡ ማገኘት ፡ ስላልተቻለ ፡ ሊቃውንት ፡ እንዳስተያየታቸው ፡ አንዱ ፡ ፍቅር ፣ አንዱ ትንሣኤ ፤ አንዱም፡ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ እያሉ ፡ ተርጕመውታል ። እንግዲህ ፡ ለነዚህ ፡ ኹሉ ፡ መሠረታቸው ፡ ሄኖክ ፡ እንደ ኾነ ፡ አስተውል ።

፫ተኛም ፡ ሞት ፡ ያስፈረደችብን ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ አይቶ ፡ ወመጻእኩ ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡ ጽድቅ ፡ ወርኢኩ ፡ በክሀቲሆሙ ፡ ለእሉ ፡ ዕፀው ፡ ዕፀወ ፡ ብዙኃነ ፡ ወዕፀ ፡ ጥበብ ፡ ዘእምኔሁ ፡ በሊዖሙ ፡ የአምርዋ ፡ ለጥበብ ፡ ዐባይ ፡ ወይመስል ፡ ሐመረ ፡ ጽራዕ ፡ ወፍሬሁኒ ፡ ከመ ፡ አስካለ ፡ ወይን ፡ ጥቀ ፡ ሠናይ ፡ ወፄናሁ ፡ ለውእቱ ፡ ዕፅ ፡ የሐውር ፡ ወይበጽሕ ፡ ነዋኀ ፡ ወእቤ ፡ ዝ ፡ ዕፅ ፡ ሠናይ ፡ ወፍሡሕ ፡ ርእየቱ ፡ ወአውሥአኒ ፡ መልአክ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ዘምስሌየ ፡ ሀሎ ፡ ወይቤለኒ ፡ ዝ ውእቱ ፡ ዕፀ ፡ ጥበብ ፡ ዘእምኔሁ በልዑ ፡ አቡከ ፡ አረጋዊ ፡ ወእምከ ፡ ዕቤራዊት ፡ እለ ፡ ቀደሙ ፡ ወአእመርዋ ለጥበብ ፡ ወተፈትሐ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ወአእመሩ ፡ ከመ ፡ ዕራቃኒሆሙ ፡ ወተሰዱ እምገነት ።

www.ethiopianorthodox.org

ጽድቅ ፡ ወደሚሠራበት ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ከኒህ ፡ ዕንጨቶች ፡ ወደዚያ ፡ ሲል ፡ ብዙ ፡ ዕንጨቶች ፡ አየሁ ፡፡ ከርሱ ፡ በልተው ፡ ጥበብን ፡ የሚያውቁበትን ፡ ዕፀ ፡ ጥበብንም ፡ አየሁ ፡፡ እርሱም ፡ ተረር ፡ ቃሞ ፡ ይመስላል ፡፡ ፍሬውም ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ፍሬ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነው ፡፡ የዚህም ፡ እንጨት ፡ ሽታው ፡ ከሩቅ ፡ ይሸታል ፡፡ ይህ ፡ ዕንጨት ፡ እጅግ ፡ መልከም ፡ ነው ፡ አሱን ፡ ማየትም ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ አልኩ ፡፡ የቀደሙ ፡ አባቶችህ ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ከርሱ ፡ በልተው ፡ ጥበብን ፡ ያወቁበት ፤ ዐይናቸው ፡ ተገልጦ ፡ ራቁትነታቸውን ፡ አውቀው ፡ ከገነት ፡ የወጡበት ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ መለሰልኝ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ ም ፴ ቀ ፡ ፳፩–፳፱ ፡፡

ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ሙሴ ፡ የዚህን ፡ ዕፅ ፡ ነገር ፡ በገነት ፡ መሃከል ፡ መልካምና ፡ ክፉን ፡ የምታሳውቅ ፡ ዛፍ ፡ አለች ፡፡

እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሰውን ፡ አዘዘው ፡ ከገነት ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ትበላለህ ፤ መልካምንና ፡ ክፉን ፡ ከምታስታውቀው ፡ ከገነት ፡ ዛፍ ፡ ግን ፡ ከርስዋ ፡ በበላህ ፡ ቀን ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ ትሞታለህ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ጽፏል ፡ ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡፡

ከዚህም ፡ ገዝቅ ፡ ብሎ ፡ እባብ ፡ ተንኰለኛ ፡ ነበረችና ፡ ሴቲቱን ፡ በውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገነት ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ እንዳትበሉ ፡ አዘዛን ፡ አለቻት ፡፡ ሴቲቱም ፡ እባቢቱን ፡ በገነት ፡ ካለችው ፡ ዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ብቻ ፡ አትብሉ ፡ እንዳትሞቱ ፡ አትንኳት ፡ አለን ፡ እንጂ ፡ በገነት ፡ ካለችው ፡ ዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ እንበላለን ፡ አለቻት ፡፡ እባብም ፡ ለሴቲቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርስዋ ፡ በበላችሁ ፡ ጊዜ ፡ ዐይናችሁ ፡ እንድትከፈት ፡ ያውቃልና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አትሞቱም ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ትኾናላችሁ ፤ መልካምና ፡ ክፋውንም ፡ ታውቃላችሁ ፡ አለቻት ፡፡ ሴቲቱም ፡ ዛፊቱ ፡ መብልነቷ ፡ መልካም ፡ እንደኾነች ፤ ለማየትም ፡ እንድታስጐመጅ ፡ ዛፊቱም ፡ ጥበብ ፡ ለመስጠት ፡ ያማረች ፡ እንደኾነች ፡ አየች ፡፡ ከፍሬዋ ፡ ወስዳ ፡ በላች ፡፡ ለባልዋም ፡ ደግሞ ፡ ወስዳ ፡ ሰጠች ፡፡ ከርስዋ ፡ ጋራ ፡ ርሱም ፡ በላ ፡፡ የኹለቱም ፡ ዐይናቸው ፡ ተከፈተች ፡፡ ዕራቁት ፡ መኾናቸውንም ፡ ዐወቁ ፡ የበለሲቱንም ፡ ቅጠል ፡ ሸልለው ፡ ግልድም ፡ አደረጉ ፡ ብሎ ፡ የነገሩን ፡ ኹኔታ ፡ አስፋፍቶ ፡ ተናግሯል ፡ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፩–፯ ፡ ይህነንም ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ የዕፀ ፡ በለስን ፡ ነገር ፡ ያልተናገረ ፡ የለም ፡፡

፬ተኛ ፡ የማየ ፡ አይኅን ፡ ነገር ፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ይወፅእ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ወይትረኀወ ፡ ኵሎሙ ፡ መዛግብተ ፡ ማያት ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ ወዲበ ፡ አንቅዕት ፡ እለ ፡ መትሕተ ፡ ሰማያት ፡ ወዘመልዕልተ ፡ ምድር ፡ ወይደመሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ማያት ፡ ዘምስለ ፡ ማያት ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ ማይሰ ፡ ዘመልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ ተባዕታይ ፡ ውእቱ ፤ ወማይ ፡ ዘመትሕተ ፡ ምድር ፡ አንስታይ ፡ ይእቲ ፡ ወይደመሰሱ ፡ ኵሉ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ የብስ ፡ ወእለ ፡ የኀድሩ ፡ መትሕተ ፡ አፅናፈ ሰማይ ፡ ወበእንተዝ ፡ አእመርዋ ፡ ለዓመፃሆሙ ፡ እንተ ፡ ገብሩ ፡ በዲበ ምድር ፡ ወበእንተዝ ፡ ይትኀጐሉ ፡፡



በዚያ ፡ ወራት ፡ መቅሠፍት ፡ ከመናፍስት ፡ ጌታ ፤ ይታዘዛል ፡ ከሰማይ ፡ በላይ ያሉ ፡ ውኆዎች ፡ ይዘንማሉ ፡፡ በምድርም ፡ ያሉ ፡ ውኆዎች ፡ ይፈላሉ ፡፡ ከሰማይ ፡ የወረዱ ፡ ውኆዎችና ፡ ከምድር ፡ የፈሉ ፡ ውኆዎች ፡ ይገናኛሉ ፡፡ ከሰማይ ፡ የወረደው ፤ ውኀ ፡ ተባዕታይ ፡ ነው ፡ (ማለት) ፡ ንፍር ፡ ውኀ ፡ ነው ፡፡ ከምድር ፡ የመነጨችቱ ፡ ውኀ ፡ ግን ፡ እንስት ፡ ናት ፡ (ማለት ፡) ቀዝቃዛ ፡ ናት ፡፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ፍጥረቶች ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋሉ ፡ ስለዚህ ፡ በምድር ፡ የሠሯትን ፡ ጥፋት ፡ ያውቋታል ፡ ብሏል ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፴ ፡ ፴፰ ፡፡

ይህም ፡ ትንቢት ፡ ለኄኖክ ፡ ፫ተኛ ፡ ትውልድ ፡ በኾነው ፡ በኖኅ ፡ ጊዜ ፡ ተፈጽሟል ፡፡

መፈጸሙንም ፡ ሊቀ ፡ ነቢያት ፡ ሙሴ ፡ ፲ቀን ፡ ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፡ የጥፋት ፡ ውኀ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኾነ ፡ በኖኅ ፡ ዕድሜ ፡ በ፮፻ ዓመት ፡ በ፪ተኛው ፡ ወር ፡፡ ከወሩም ፡ በ፲፯ ሰባት ፡ ቀን ፡፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ የታላቁ ፡ የቀላይ ፡ ምንጮች ፡ ኹሉ ፡ ተቀደዱ ፡ የሰማይም ፡ መስኮቶች ፡ ኹሉ ፡ ተከፈቱ ፡፡ ዝናሙም ፡ ኾነ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ፵ቀንና ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ ብሎ ፡ ጽፏል ፡ ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፲ ፡፡

ይህንም ፡ ጌታ ፡ ከጥፋት ፡ ውኀ ፡ ዘመን ፡ ፊት ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ኖኅ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ እስከሚገባበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ ሲያገቡ ፡ ሲጋቡ ፡ የጥፋት ፡ ውኀ ፡ መጥቶ ፡ እስኪያጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ እንዳላወቁ ፡ የወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ የክርስቶስም ፡ አመጣጡ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አረጋግጦታል ፡ ማቴ ፡ ፳፬ ፴፰ ፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቀሩት ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ሊቃውንትም ፡ ሌሎች ፡ አዋልድም ፡ ቢኾኑ ፡ የማየ ፡ አይኅን ፡ ነገር ፡ አምልተው ፡ አስፍተው ፡ ተናግረዋል ፡፡

፭ተኛ ፡ ኖኅ ፡ መርከብ ፡ ሠርቶ ፡ ፫ቱን ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ በሠራት ፡ መርከብ ፡ ከማየ ፡ አይኅ መዳኑን ፡ ውእቱ ፡ ላሕም ፡ ተወልደ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወፀረበ ፡ ሎቱ ፡ መስቀረ ፡ ዐቢየ ፡ ወነበረ ፡ ዲቤሃ ፡ ወ፫አልሕምት ፡ ምስሌሁ ፡ ነበሩ ፡ በይእቲ ፡ መስቀር ፡ ወተከድነ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወርኢኩ ፡ ናኅሰ ፡ ልዑለ ፡ ወ፯ቱ ፡ አስራብ ፡ ዲቤሁ ፡ ወእልኩ ፡ አስራብ ፡ በ፩ዐፀድ ፡ ያውኅዙ ፡ ማየ ፡ ብዙኀ ፡፡ ወነዋ ፡ አንቅዕታት ፡ ተርኅዉ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወአኀዘ ፡ ውእቱ ፡ ማይ ፡ ይፍላሕ ፡ ወይትነሣእ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወኢያርአዮ ፡ ለውእቱ ፡ ዐፀድ ፡ እስከ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ተከድነ ፡ በማይ ፡ ወበዝኀ ፡ ማይ ፡ ዲቤሁ ፡ ወኵሎሙ ፡ አልሕምት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ወፀድ ፡ ተጋብኡ ፡ እስከ ፡ ርኢክዎሙ ፡ ይሠጥሙ ፡ ወይትወሐጡ ፡ ወይትኀጐሉ ፡ በውእቱ ፡ ማይ ፡ ወውእቱ ፡ መስቀር ፡ ይፀቢ ፡ ዲበ ፡ ማይ ፡ ወኵሎሙ ፡ አልሕምት ፡ ወነጌያት ፡ ወአግማል ፡ ወአእዱግ ፡ ተሠጥሙ ፡፡ ወካዕበ ፡ ርኢኩ ፡ በራእይ ፡ እስከ ፡ ሰሰላ ፡ እልኩ ፡ አስራብ ፡ እምዝኩ ፡ ናኅስ ፡ ልዑል ፡ ወንቅዐተ ፡ ምድር ፡ ዐረየ ፡ ወማዕምቅታት ፡ ካልአት ፡ ተፈትሑ ፡ ወአኀዘ ፡ ማይ ፡ ይረድ ፡ ውስቴቶሙ ፡ እስከ ፡ ተከሥተ ፡ ምድር ፡ ወውእቱ ፡ መስቀር ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወተገኅሠ ፡ ጽልመት ፡ ወኮነ ፡ ብርሃን ፡ ወውእቱ ፡ ላሕም ፡ [illegible] ሴ ፡ ወፅአ ፡ እምዝኩ ፡ መስቀር ፡ ወ፫ ፡ አልሕምት ፡ ምስሌሁ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

አንድ ፡ ላም ፡ ተወልዶ ፡ ሰው ፡ ኸነና ፡ ትልቅ ፡ መርከብ ፡ ሠራ ፤ በውስጡም ፡ ተቀመጠ ፡ ፫ላሞችም ፡ አብረውት ፡ በዚያች ፡ መርከብ ፤ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ። ፯መኸረቦች ፡ በንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ወኀዎችን ፡ ሲያፈሱ ፡ አየሁ ። ቦታው ፡ ለመታየት ፡ እስከማይቻል ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ ብዙ ፡ ምንጮች ፡ እየመነጩ ፡ ብዙ ፡ ወኀ ፡ ሲያጥለቀልቀው ፡ አየሁ ። በዚያ ፡ ቦታ ፡ የነበሩ ፤ ላሞችም ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ወኀ ፡ ሠጥመው ፡ ሲጠፉ ፡ አየሁ ። ያ መርከብ ፡ ግን ፡ በወኀው ፡ ላይ ፡ ይንሳፈፍ ፡ ነበር ፡ ወኀው ፡ ሲደርቅ ፡ ግን ፡ ኖኅ ፡ ከነልጆቹ ፡ ከመርከብ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ ፹፩ ፡ ፲፫–፳፱ ።

ይህም ፡ ትንቢት ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሙሴ ፡ አሪትን ፡ ሲጽፍ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኖኅን ፡ የሥጋ ፡ ኹሉ ፡ ጥፋት ፡ በፊቴ ፡ ደርሷል ፡ ምድር ፡ ኃጢአትን ፡ መልታለችና ፡ እኔም ፡ ከርሳቸው ፡ የተነሣ ፡ ምድርን ፡ አጠፋታለሁ ። ላንተ ፡ ግን ፡ ከጽድ ፡ እንጨት ፡ መርከብ ፡ ሥራ ፡ በመርከቡም ፡ ጉርጆቹን ፡ አድርግ ። ውሥጡንም ፡ ሜዳውንም ፡ በዝፍት ፡ ለቅልቀው ። የመርከቡም ፡ ርዝመቱ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ወርዱ ፡ አምሳ ፡ ክንድ ፡ ከፍታው ፡ ፴ ፡ ክንድ ፤ ይኹን ። ለመርከቡም ፡ መስኮት ፡ አውጣለት ፡ ከከፍታውም ፡ ክንድ ፡ ምሉ ፡ ትተህ ፡ ጨርሰው ፡ የመርከቡንም ፡ ደጅ ፡ ባጠገቡ ፡ አድርግ ፡ ታችኛውንም ፡ ኹለተኛውንም ፡ ሦስተኛውንም ፡ ደርብ ፡ ታደርግለታለህ ፡ አለው ። ኖኅም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አድርጎ ፡ ዳነ ፡ ሲል ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሮ ፡ ጽፏል ። ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፯ ፡ ፲፫–ም ፡ ፰ ፲፰ ፤ ድረስ ፡ ተመልከት ።

ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያትም ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለኖኅ ፡ አመ ፡ ይገብር ፡ ታቦተ ፡ ወድኀኑ ፡ ባቲ ፡ ስማኒቱ ፡ ነፍስ ፡ ኅዳጣን ፡ እምነ ፡ ማይ ፡ ብሏል ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፳ ።

፯ተኛ ፡ ዳግመኛ ፡ ሰውን ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ አላጠፋውም ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዲሰጠው ፡ ለዚኸውም ፡ ምልክት ፡ ቀሥተ ፡ ደመና ፡ እንዲተክል ። ወእምድኅረዝ ፡ ነስሐ ፡ ርእሰ ፡ መዋዕል ፡ ወይቤ ፤ በከ ፡ አኀጐልክዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ የብስ ፡ ወመሐለ ፡ በስሙ ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ እምይእዜ ፡ ኢይገብር ፡ ከመዝ ፡ በኵሎሙ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ የብስ ፡ ወትእምርተ ፡ እወዲ ፡ በሰማይ ፡ ወይከውን ፡ ማዕከሌየ ፡ ወማዕከሌሆሙ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፤ መጠነ ፡ መዋዕለ ፡ ሰማይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ጌታ ፡ ሰውን በከንቱ ፡ አጠፋሁት ፡ ብሎ ፡ ተጠጠተ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በምድር ፡ በሚኖር ፡ ፍጥረት ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ አላደርግበትም ፡ ብሎ ፡ በገናና ፡ ስሙ ፡ ማለ ። ይህ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ በነሱና ፡ በኔ ፡ መከከል ፡ የሙተማመኛ ፡ ምልክት ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ ፲፭ ፡ ፩–፱ ።

ይህም ፡ ትንቢት ፡ በኖኅ ፡ ዘመን ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ሙሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኖኅን ፡ እንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ፍጥረትን ፡ ኹሉ ፡ በንፍር ወኀ ፡ አላጠፋውም ። ምድርን ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ ኹለተኛ ፡ የጥፋት ፡ ወኀ ፡ አላዘንምም ። በናንተና ፡ በኔ ፡ መከከል ፡ ያለው ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ምልክት ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡



መከከል ፡ ፫ ፡ ኅብር ፡ ያላት ፡ ቀሥተ ፡ ደመና ፡ አደርጋለሁ ። ሰማይንም ፡ በደመና ፡ በጋረድሁ ፡ ጊዜ ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ቀሥቴ ፡ በደመናው ፡ ይታያል ። በኔና ፡ በናንተ ፡ መከከል ፡ ያለውን ፡ ኪዳኔን ፡ አስባለሁ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ እየተረከ ፡ ጽፏል ፡ ዘፍጥ ፡ ፲፩ ፡ ፰–፲፰ ።

ይህን ፡ የሄኖክን ፡ ትንቢት ፡ የሙሴን ፡ ታሪክ ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ተናግረውታል ። ቀሥተ ፡ ደመናውን ፡ በማየቱ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚነሣው ፡ ትውልድ ፡ ኹሉ ፡ ባይኑ ፡ ሲአየው ፡ የሚኖር ፡ ስለኾነ ፡ ለዚህ ፡ ትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያይን ፡ ምስክር ፡ ነው ።

፰ተኛ ፡ ያንድነትን ፡ የሦስትነትንም ፡ ነገር ፡ እስመ ፡ ቆመ ፡ ኅሩይ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ወስብሐቲሁ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ወኃይሉ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ወቦቱ ፡ የኀድር ፡ መንፈሰ ፡ ጥበብ ፡ ወመንፈሰ ፡ ዘያሌቡ ፤ ወመንፈሰ ፡ ትምህርት ፡ ወኃይል ፡ ወመንፈሰ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ በጽድቅ ።

ኅሩይ ፡ ክርስቶስ ፡ በመናፍስት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ቆመ ፡ ጌትነቱ ፡ ለዘለዓለም ፤ ኃይሉም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ። መንፈሰ ፡ ጥበብ ፡ መንፈሰ ፡ አእምሮ ፡ ያድርበታል ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ ፲፫ ፡ ፲፱ ፳፱ ።

እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ብሎ ፡ እግዚብሔር ፡ አብን ፤ ኅሩይ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድን ። መንፈሰ ፡ ጥበብ ፡ መንፈሰ ፡ ዘያሌቡ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አስተውል ።

ሄኖክ ፡ ቆመ ፡ ኅሩይ ፤ ያለውንም ፡ ኢሳይያስ ፡ ናሁ ፡ ቍልዔየ ፡ ኅሩይየ ፡ ዘሠምረቶ ፡ ነፍስየ ፡ ወወሀብኩ ፡ መንፈስየ ፡ ዲቤሁ ፡ ያመጽእ ፡ ፍትሐ ፡ ለአሕዛብ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ፡ ኢሳይ ፡ ፵፪ ፡ ፩–፫ ።

ይህን ፡ የኢሳይያስንም ፡ ቃል ፡ ጌታ ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ መፈጸሙን ፡ ወንጌላዊ ፡ ወገሠጾሙ ፤ ከመ ፡ ኢያግኅድዎ ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ዘተብህለ ፡ በኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ናሁ ፡ ወልድየ ፡ ዘኀረይኩ ፡ ፍቁርየ ፡ ዘሠምረቶ ፡ ነፍስየ ፡ አነብር ፡ መንፈስየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኵነኔየ ፡ ለአሕዛብ ፡ ይነግር ፡ ኢይደምፅ ፡ ወኢይጸርሕ ፡ ወአልበ ፡ ዘይሰምዕ ፡ በጽጐ ፡ ቃሎ ፡ ብርዐ ፡ ቅጥቁጠ ፡ ኢይሰብር ፡ ወሡዐ ፡ ዘይጠይስ ፡ ኢያጠፍዕ ፡ እስከ ፡ ያገብእ ፡ ፍትሐ ፤ ለመዊዕ ፡ ወበስመ ፡ ዚአሁ ፡ አሕዛብ ፡ ይትአመኑ ፡ ብሎ ፡ አስረድቷል ፤ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ፡ -፳፪ ።

ሄኖክ ፡ ወቦቱ ፡ የኀድር ፡ መንፈሰ ፡ ጥበብ ፡ ያለውንም ፡ ኢሳይያስ ፡ ትወፅእ ፡ በትር ፡ እምሥርወ ፡ ዕሤይ ፡ ወየዐርግ ፡ ጽጌ ፡ እምጕንዱ ፡ ወየዐርፍ ፡ ዲቤሁ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሰ ፡ ጥበብ ፡ ወአእምሮ ፡ መንፈሰ ፤ ኃይል ፡ ወምክር ፡ መንፈሰ ፡ ልቡና ፡ ወጽድቅ ፡ ወይመልዕ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ። መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌየ ፡ ቀብዐኒ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ፡ ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፩–፬ ። ፷ ፡ ፩–፬ ።

ይህ ፡ የሄኖክና ፡ የኢሳይያስም ፡ ትንቢት ፡ በጌታ ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ መፈጸሙን ፡ ወወሀብዎ ፡ መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ ወከሠቶ ፡ መጽሐፈ ፡ ረከበ ፡ መካነ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኀበ ፡ ጽሑፍ ፡ ዘይብል ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌየ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ቀብዐኒ ፡ እዜንዎሙ ፡ ለነዳያን ፡ ፈነወኒ ፡ እስብክ ፡ ሎሙ ፡ ግእዛነ ፡ ለፄዉዋን ፡ ወይርአዩ ፡ ዕውራን ፡ ወአንግሮሙ ፡ ለግፉዓን ፡ ወእስብክ ፡ ዐመተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኅሪተ ፡ ወከደኖ ፡ መጽሐፈ ፡ ወመጠዎ ፡ ለላእክ ፡ ወነበረ ። ወአንሥኡ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ምኵራብ ፡ ወነጸርዎ ፡ ወአኀዘ ፡ ይበሎሙ ፡ ዮም ፡ በጽሐ ፡ ቃለ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ወተሠልጠ ፡ ውስተ ፡ እዘኒክሙ ። ብሎ ፣ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቃሉ ፡ አስረድቶናል ፡ ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፲፯ -፳፪ ።

፳ተኛ ፡ ይባርኩክ ፡ እለ ፡ ኢይነውሙ ፡ ወይቀውሙ ፡ በቅድመ ፡ ስብሐቲከ ፡ ወይባርኩ ፡ ወይሴብሑ ፡ ወያሌዕሉ ፡ እንዘ ፣ ይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአ መናፍስት ፡ ይመልዕ ፡ ምድረ ፡ መናፍስተ ።

የማያንቀላፉ ፡ በጌትነትህ ፡ ፊት ፡ የሚቆሙ ፡ መላእክት ፡ ጽኑዕ ፡ ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ ልዩ ፡ የሚኾን ፡ ጌታ ፡ በምድርም ፡ በመናፍስትም ፡ ዘንድ ፡ ምሉዕ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ቃላቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ያመሰግኑሃል ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ ፱ ፡ ፴፰ ።

ኢሳይያስም ፡ ሄኖክ ፡ ከደረሰበት ፡ ማዕርግ ፡ ደርሶ ፡ ባንድነት ፡ በሦስትነት ፡ ሲሠለስ ፡ ሲቀደስ ፡ አይቶ ፡ ወእምዝ ፡ በዓመተ ፡ ሞተ ፡ ዖዝያን ፡ ርኢክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ልዑል ፡ ወነዋኅ ፡ ወምሉዕ ፡ ቤተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወሱራፌል ፡ ይቀውሙ ፡ ዐውዶ ፡ ለለ ፡ ፮፮ ፡ ፮ቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡ በ፪ ፡ ይደድኑ ፡ ገጾሙ ፡ ወበ፪ ፡ ይከድኑ ፡ እግሮሙ ፡ ወበ፪ ፡ ይሠሩ ፡ ወይኬልሑ ፡ ፩ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ወይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ መልዐ ፡ ኵሎ ፡ ምድረ ፡ ስብሐቲከ ፡ ብሏል ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩ ፡ -፬ ።

ከዚህ ፡ አያይዘው ፡ አሥራው ፡ መጻሕፍትም ፡ አዋልድ ፡ መጻሕፍትም ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፤ እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ እያሉ ፡ ተናግረዋል ፡ ለኹሉም ፡ መሠረት፡ ሄኖክ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ።

፱ነኛ ፡ ወይቤለኒ ፡ ዝቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ መሀሪ ፡ ወርኁቀ ፡ መዓት ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ።
ወለውእቱ ፡ መቅድመ ፡ ቃል ፡ ይባርክዎ ፡ ወያሌዕልዎ ፡ ወይሴብሕዎ ፡ በጥበብ ።

ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ መሀሪ ፡ ርኁቀ ፡ መዓት ፡ ነው ፡ አለኝ ። ይህነንም ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ ቡሩክ ፡ ልዑል ፡ ስቡሕ ፡ ጠቢብ ፡ እያሉ ፡ ያመሰግኑታል ፡ ብሎ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃልነቱን ፡ ተናግሯል ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ፲፯ ፡ ፲፩ ።

ይህንም ፡ ይዞ ፡ ሰሎሞን ፡ በመኀልዩ ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ እኁየ ፡ ናሁ ፡ ውእቱ ፡ መጽአ ፡ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ ቃል ፤ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ እኁየ ፤ ወልደ ፡ አብ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ እንደመኾኑ ፡ ወልድ ፤ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ (መኀልይ ፡ ፪ ፡ ፳።)

ይህንም ፡ ይዞ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቀዳሚሁ ፡ ቃል ፡ ውእቱ ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብሎ ፡ አጕልቶ ፡ ተናግሯል ። ዮሐ ፡ ፩፩ ፡ ፲፬ ።



ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሄኖክ ፡ መሠረትነት ፡ ዮሐንስ ፡ ቃል ፣ ቀዳማዊ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ማለቱን ፡ ይዘው ፡ መጻሕፍት ፣ ኹሉ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፣ ኮነ ፤ ቃለ ፡ አብ ፡ ወቃለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ አካላዊ ፡ ቃልነቱን ፡ አምልተው ፡ አስፍተው ፡ አጕልተው ፡ ተናግረዋል ፡ ጥንታቸው ፡ ግን ፡ ለኹሉም ፡ ሄኖክ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ።

፲ኛም ፡ ስለምድራዊ ፡ ልደቱ ፡ ወርኢኩ ፡ ከመ ፡ ተወልደ ፡ ፩ ፡ ላሕም ፡ ፀዓዳ ፡ ወአቅርንቲሁ ፡ ዐበይት ፡ ወኵሎሙ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ይፈርህዎ ፡ ወያስተበቍዕዎ ፣ በኵሉ ፡ ጊዜ ፣ ወርኢኩ ፡ እስከ ፣ ተወለጡ ፣ ኵሎሙ ፡ አዝማዲሁ ፡ ወኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ አልሕምተ ፡ ፀዐድዋነ ።

አንድ ፡ ነጭ ፡ በሬ ፡ ሲወለድ ፡ አየሁ ፡ ቀንዶቹም ፣ ትልልቆች ፣ ናቸው ፣ የዱር ፡ አራዊትና ፣ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ይፈሩታል ፡ ኹልጊዜ ፡ ይማልዱታል ፡ ዘመዶቹ ፡ ኹሉ ፡ ተለውጠው ፡ እንደርሱ ፡ ነጫጭ ፡ ከብቶች ፣ ሲኾኑ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፣ በምሳሌ ፡ ተናግሯል ፡ ፴፬ ፣ ፳፩ ።

ይህም ፡ ትንቢታዊ ፡ ምሳሌ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ሲያስተምር ፡ አምጽኡ ፡ መግዝዐ ፡ ላሕም ፡ ንጹሐ ፡ ንጥብሖ ፡ ወንበልዖ ፡ ወንትፈሣሕ ፡ በቱ ፣ ብሎ ፡ ገልጾታል ። ሉቃ ፣ ፲፭ ፡ ፳፪ ።

ይህንም ፡ ይዘው ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ አላሕም ፡ ዘኢይትኄየል ፡ በቀርኑ ፡ ለእለ ፡ ይስሕብዎ ፡ ወያጸንን ፣ ክሣዶ ፡ ለእለ ፡ ይጠብሕዎ ፡ እያሉ ፡ ጽፈዋል ።

፲፩ኛ ፣ በሌላም ፡ አንቀጽ ፡ ወአቅርንቲሁ ፡ ዐበይት ፡ ያለውን ፣ የመሰለ ፡ ንባብ ፡ ወርኢኩ ፡ እስከ ፡ በቄለ ፣ ፩ ፡ ቀርን ፡ ዐቢይ ፡ ፩ ፡ እምእልኩ ፡ አባግዕ ፡ ወተከሥታ ፡ አዕይንቲሆሙ ።

ከኒያ ፡ ከበጎችም ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ቀንድ ፡ ሲበቅል ፡ አየሁ ፡ የበጎችም ፡ ዐይናቸው ፡ ተገለጸ ፡ ብሎ ፡ ጌታን ፡ በቀርን ፡ መስሎ ፡ ተናግሯል ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ።

ይህነንም ፡ የሄኖክን ፡ ምሳሌ ፡ ዘካርያስ ፡ አንሥአ ፡ ለነ ፡ ቀርነ ፡ መድኃኒትነ ፡ እምቤተ ፣ ዳዊት፡ ገብሩ ፡ በከመ ፡ ነበበ ፡ በአፈ ፡ ነቢያቲሁ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ እምዓለም ፡ ብሎ ፡ ገልጾ ፡ ተናግሯል ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፷፱ ። ነቢያት ፤ እለ ፡ እምዓለም ፡ ለተባሉት ፡ ፊታውራሪያቸው ፡ መጀመሪያቸው ፡ ሄኖክ ፡ እንደኾነ ፡ አስተውል ።

፲፪ተኛ ፣ ጌታ ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረገው ፣ ተድላ ፡ ደስታም ፡ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ይዘፍኑ ፡ አድባር ፡ ከመ ፡ ሐራጊት ፡ ወአውግርኒ ፡ ያንፈርዕፁ ፡ ከመ ፡ መሐስዕ ፡ ጽጉባነ ፡ ሐሊብ ።

በዚያ ፡ ወራት ፡ ተራራዎች ፡ እንደ ፡ ጊደሮች ፡ ይዘፍናሉ ፡ ኮረብታዎችም ፣ ወተት ፡ እንደጠገቡ ፣ ጠቦቶች ፣ ይዘላሉ ፡ ብሎ ፣ ተናግሯል ፡ ፲፫ ፡ ፴፪ ።

ይህነንም ፡ቅዱስ ፣ ዳዊት ፡ አድባር ፡ አንፈርዐፁ ፡ ከመ ፡ ሐራጊት ፡ ወአውግርኒ ፡ ከመ ፡ መሐስዐ ፡ አባግዕ ፡ ብሎ ፡ ወሰዶታል ። መዝ ፡ ፻፲፬ ፡ ፬ ፡ ፯ ።

ኢዩኤልም ፣ በዚያም ፡ ቀን ፡ ተራሮች ፤ በተሐ ፣ ጠጅ ፡ ያንጠባጥባሉ ፡ ኮረፍቶችም ፡ ወተትን ፡ ያፈሳሉ ፣ በይሁዳም ፡ ያለ ፡ ወንዝ ፡ ኹሉ ፡ ወኃ ፡ ያጎር

www.ethiopianorthodox.org

ፋል ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ምንጭ ፡ ትፈልቃለች ፡ የሺጢሚንም ፡ ሜዳ ፡ ታጠጣለች ፡ ብሏል ፡፡

የኢትዮጵያውም ፡ ሊቅ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ በእንተ ፡ ልደቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ አድባር ፡ ኮኑ ፡ ኀብስተ ፡ ሕይወት ፡ ወዕፀወ ፡ ገዳምኒ ፡ ፈረዩ ፡ አስካለ ፡ በረከት ፡ ማየ ፡ ባሕርኒ ፡ ኮነ ፡ ሐሊበ ፡ ወመዓረ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ፡፡ ዝማሬ ፡ ዘልደት ፡ ተመልከት ፡፡

፲፫ተኛ ፡ የዕርገትንና ፡ የነቢር ፡ በየማንንም ፡ ነገር ፡ ወእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ አንበሮ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለኅሩይ ፡፡

የመናፍስት ፡ ጌታም ፡ ኅሩይ ፡ክርርቶስን ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ አስቀመጠው ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡፡

ቅዱስ ፡ ዳዊትም ፡ ለኄኖክ ፡ የገለጠ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገልጦለት ፡ ዐርገ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይባቤ ፡ ወእግዚእነ ፡ በቃለ ፡ ቀርን ፡፡ ዐረገ ፡ ውስተ ፡ ዓርያም ፡ ፄዊወከ ፡ ፄዋ ፡፡ ይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንበር ፡ በየማንየ ፡ ብሏል ፡ መዝ ፡ ፵፯ ፡ ፷ ፡ ፷፰ ፡ ፻፰ ፡፡ ፻፲፩ ፡፡

ይህም ፡ ትንቢት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡፡ ወእግዚእነሰ ፡ ኢየሱስ ፡ እምድኅረ ፡ ተናገሮሙ ፡ ዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡፡ ወእንዘ ፡ ይባርኮሙ ፡ ተራኀቆሙ ፡ ወዐርገ ፡ ሰማየ ፡ ብለው ፡ ወንጌላውያን ፡ አረጋግጠው ፡ ጽፈዋል ፡፡ ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፡፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፶ ፡፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፩ ፩—፲፬ ፡፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ ዕበዩ ፡ በሰማያት ፡ ብሏል ፡፡ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያት ፡ ጴጥሮስም ፡ ዘሀለዎ ፡ ይነብር ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወተኰነኑ ፡ ሎቱ ፡ መላእክት ፡ ወሥልጣናት ፡ ወኵሉ ፡ ኃይል ፡ ብሏል ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ፡፡ ከሊቃውንትም ፡ ፫፻ ፡ ዐርገ ፡ በስብሐት ፡ ውስተ ሰማያት ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ አቡሁ ፡ ብለዋል ፡ ሃይ ፡ አበ ፡፡

፲፬ተኛ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚደረገው ፡ ምሥጢረ ፡ ዘመናትም ፡ ተገልጦለት ፡፡ ወሎቱ ፡ ወሀብኩ ፡ ስብሐተ ፡ ወአምኔሁ ፡ በከይኩ ፡ ብካየ ፡ ዐቢየ ፡ ወአንብዕየ ፡ ኢቆመ ፡ እስመ ፡ ኢክህልኩ ፡ ተዐግሦተ ፡ ሶበ ፡ እሬኢ ፡ እንዘ ፡ ይወርዱ ፡ ዲበ ፡ ዝኩ ፡ ዘርኢኩ ፡፡ ፹፬ ፡ ፹፪ ፡፡

ወርኢኩ ፡ መንበር ፡ ተሐንጸ ፡ በምድር ፡ ሐዋዝ ፡ ወነበረ ፡ ዲቤሁ ፡ እግዚአ ፡ አባግዕ ፡ ወነሥአ ፡ ኵሎን ፡ መጻሕፍተ ፡ ኅቱማተ ፡ ወፈትሖን ፡ ለእማንቱ ፡ መጻሕፍት ፡ በቅድመ ፡ እግዚአ ፡ አባግዕ ፡፡

ለጌትነቱ ፡ ምስጋና ፡ አቀረብኩ ፡ ካየሁትም ፡ ምሥጢር ፡ የተነሣ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አለቀስኩ ፡ ወደዚያ ፡ ወዳየሁት ፡፡ ቦታ ፡ ሲወርዱ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ልታገሥ ፡ አልቻልኩምና ፡ እንባየ ፡ አልተገታም ፡ ፹፬ ፡ ፹፪ ፡ ባማረ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ዙፋን ፡ ተዘረጋ ፤ የበጎች ፡ ጌታ ፡ በላዩ ፡ ተቀመጠ ፤ የተቈለፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ ወሰደ ፡፡ እኒያንም ፡ መጽሐፎች ፡ በበጎች ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ዘረጋቸው ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፡ ፹፬ ፡ ፩ ፡፡

ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊም ፡ በደሴተ ፡ ፍጥሞ ፡ ይህ ፡ የኄኖክ ፡ ራእይ ፡ ተገልጾለት ፡ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ ውስተ ፡ የማኑ ፡ ለውእቱ ፡ ዘይነ[illegible]



ጽሕፍተ ፡ እንተ ፡ ውስጣ ፡ ወእንተ ፡ አፍአሃ ፡ ወኅትምት ፡ በ፯ቱ ፡ ማኅተም ፡፡ ወርኢኩ ፡ መልአከ ፡ ዐቢይ ፡ ይጸርሕ ፡ ወይብል ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ለመኑ ፡ ይደልዎ ፡ ይክሥታ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወይፍታሕ ፡ ማኅተሚሃ ፡፡ ወአልቦ ፡ ዘክህለ ፡ ከሢቶታ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወኢርእዮታ ፡ ኢበሰማይ ፡ ወኢበምድር ፡ ውበዙኃን ፡ እለ ፡ በከዩ ፡ ወአነኒ ፡ ምስሌሆሙ ፡፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘተረክበ ፡ ዘይደልዎ ፡ ይክሥታ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወይርአያ ፡፡ ወይቤለኒ ፡ እምውስተ ፡ እልክቱ ፡ ሊቃናት ፡ ኢትብኪ ፡ ናሁ ፡ ሞዐ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ዘእምውስተ ፡ ሥርው ፡ ለዳዊት ፡ ከመ ፡ ይፍትሓ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ወለማኅተሚሃ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡፡ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ዝክቱ ፡ በግዕ ፡ ፩ደ ፡ እምነ ፡ ፯ቱ ፡ ማኅተሚሃ ፡ ወዕአ ፡ ፈረስ ፡ ፀዓዳ ፡፡ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ካልአ ፡ ማኅተመ ፡ ወዕአ ፡ ፈረስ ፡ ቀይሕ ፡፡ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ሣልሰ ፡ ማኅተመ ፡ ወፅአ ፡ ፈረስ ፡ ጸሊም ፡፡ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ራብዐ ፡ ማኅተመ ፡ ወዕአ ፡ ፈረስ ፡ ሐመልሚል ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚደረገውን ፡ ምሥጢረ ፡ ዘመን ፡ ተናግሯል ፡፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፡፡ ፯ ፡ ፩--፲፯ ፡፡ ፰ ፡ ፩—፳፩ ፡ ተመልከት ፡፡

፲፭ተኛ ፡ የዳግም ፡ ምጽአትም ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ ወናሁ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአእላፊሁ ፡ ቅዱሳን ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ፍትሐ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወያኅጒሎሙ ፡ ለረሲዓን ፡ ፩ ፡ ፱ ፡

ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ታገብዕ ፡ ምድር ፡ ማኅፀንታ ፡ ወሲኦል ፡ ታገብእ ፡ ማኅፀንታ ፡ ዘተመጠወት ፡ ወኀጕል ፡ ያገብእ ፡ ዘይፈዲ ፡ ወየኅሪ ፡ ጻድቃነ ፡ ወኅሩያነ ፡ እምኔሆሙ ፡ እስመ ፡ ቀርበት ፡ ዕለት ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይድኃኑ ፡፡ ወኅሩይ ፡ በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ይነብር ፡ ወኵሎ ፡ ኅቡዓተ ፡ ጥበብ ፡ እምሕሊና ፡ አፉሁ ፡ ያወፅእ ፤ እስመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ወሀቦ ፡ ወሰብሖ ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ረሲዓንን ፡ ፈርዶ ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ አእላፍ ፡ መላእክትን ፡ አስከትሎ ፡ ይመጣል ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ምድር ፡ (መቃብር ፡) የተቀበለችውን ፡ ዐደራ ፡ (ማለት ፡) የተቀበረባትን ፡ ሥጋ ፡ ትመልሳለች ፡፡ ሞትም ፡ የወሰደውን ፡ ይመልሳል ፡፡ ጻድቃን ፡ የሚድኑበት ፡ ቀን ፡ ስለደረሰ ፡ ጻድቃንን ፡ ከኃጥአን ፡ ይለያል ፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ኅሩይ ፡ ክርስቶስም ፡ የመናፍስት ፡ ጌታ ፡ ስለሰጠው ፡ ስላከበረው ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ማለትን ፡ ካንደበቱ ፡ አውጥቶ ፡ ይናገራል ፡ ብሏል ፡ ፲፫ ፡ ፳፱ ፡፡

ይህንም ፡ ጌታ ፡ ወአመ ፡ ይመጽእ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ በስብሐተ ፡ አቡሁ ፡ ወኵሎሙ ፡ መላእክቲሁ ፡ ምስሌሁ ፡ አሜሃ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ብሎ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውንም ፡ ተናግሯል ፡ ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፩—፵፯ ፡ ፳፬ ፡ ፴፯-፵፫ ፡፡

ያዕቆብ ፡ ዘሥሩግም ፡ በቅዳሴ ፡ ይህነን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ ተናግሯል ፡፡

እስመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ወሀቦ ፡ ወሰብሖ ፡ ያለውንም ፡ የመሰለ ፡ እስመ ፡ [illegible]ን ፡ ወኢመነሂ ፡ አላ ፡ ኵሎ ፡ ኵነኔሁ ፡ አወፈዮ ፡ ለወልዱ ፡፡ እስመ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ትመጽእ ፡ ሰዓት ፡ በዘይሰምዕዎ ፡ ቃሎ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ወይወፅኡ ፡ እለ ፡ ሠናየ ፡ ገብሩ ፡ ውስተ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለሕይወት ፡ ወእለሰ ፡ እኩየ ፡ ገብሩ ፡ ውስተ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለደይን ፡ ብሏል ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ።

፲፮ኛ ፡ ወይከውኑ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክተ ፡ በሰማይ ፡ ወገጾሙ ፡ ይበርህ ፡ በፍሥሐ ። ኹሉም ፡ በሰማይ ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ይኾናሉ ፡ ፊታቸውም ፡ በደስታ ፡ ያበራል ፡ ብሎ ፡ ዕሜተ ፡ ጻድቃንን ፡ ተናግሯል ።

ይህንም ፡ አሚሃ ፡ ይበርሁ ፡ ጻድቃን ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ በመንግሥተ ፡ አቡሆሙ ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ መስክሮለታል ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፵፫ ፡ ዳን ፡ ፲ ፡ ፳፪ ።

፲፯ኛ ፡ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ርኢክዎ ፡ ለርእሰ ፡ መዋዕል ፡ ይነብር ፡ በመንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወመጻሕፍተ ፡ ሕያዋን ፡ ተከሥቱ ፡ በቅድሜሁ ።
በዚያ ፡ ወራት ፡ ከቀኖች ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ክርስቶስን ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ አየሁት ፡ የሕያዋን ፡ መጻሕፍትም ፡ በፊቱ ፡ ተገለጡ ፡ ብሏል ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ።

ይህንንም ፡ ዳንኤል ፡ የእሳት ፡ ፈሳሽ ፡ ከፊቱ ፡ ይፈልቅ ፡ ይወጣም ፡ ነበረ ። ሺህ ፡ ጊዜ ፡ ሺህ ፡ ያገለግሉት ፡ ነበረ ። እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍም ፡ በፊቱ ፡ ቆመው ፡ ነበረ ። ለፍርድ ፡ ተቀመጠ ፡ መጻሕፍትም ተገለጡ ፡ ብሏል ፡ ፯ ፡ ፲ ።

ዮሐንስም ፡ በራእዩ ፡ ሙታንን ፡ ታናሾችንም ፡ ታላቆችንም ፡ አየሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆመው ። መጻሕፍትም ፡ ተከፈቱ ። ሌላውም ፡ መጽሐፍ ፡ ተከፈተ ፡ እርሱም ፡ የሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ሙታንም ፡ ፍርዳቸውን ፡ ተቀበሉ ፡ በመጻሕፍት ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ሥራት ፡ መጠን ፡ ብሏል ፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ።

፲፰ተኛ ፡ ስለ ፡ ኃጥአንም ፡ አይቴ ፡ ማኅደረ ፡ ኃጥኣን ፡ ወአይቴ ፡ ምዕራፎሙ ፡ ለእለ ፡ ክህድዎ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ እምኅየሰሙ ፡ ሰበ ፡ ኢተወልዱ ፡ ወሰበ ፡ ይትከሠታ ፡ ኅቡዓቲሆሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ይትኴነኑ ፡ ኃጥአን ፡ ወይትሀወኩ ፡ ረሚዓን ፡ እምገጸ ፡ ጻድቃን ፡ ወኅሩያን ፡ ወእምይእዜሰ ፡ ኢይከውኑ ፡ አዚዛነ ፡ ወኢልዑላነ ፡ እለ ፡ ይእኅዝዋ ፡ ለምድር ።

የመናፍስት ፡ ጌታን ፡ የካዱ ፡ የኃጥአን ፡ ማረፊያቸው ፡ ማደሪያቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ። ባልተወለዱ ፡ በተሻላቸው ፡ ነበረ ። ጻድቃን ፡ ተሰውረው ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ በክብር ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ኃጥአን ፡ ይቀጣሉ ። ከጻድቃን ፡ ባለሟልነት ፡ የተነሣ ፡ ረሚዓን ፡ ይታወካሉ ። ከዚያች ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ምድርን ፡ ይገዟት ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ አዛዦች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አይኾኑም ፡ ብሏል ፡ ፱ ፡ ፲፩–፲፬ ።

ይህንም ፡ የሄኖክን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ ፡ በምክረ ፡ ረሚዓን ፡ ብሎ ፡ የጻድቃንን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ አኮ ፡ ከመዝ ፡ ኃጥአንሰ ፡ አኮ ፡ ከመዝ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ መሬት ፡ ዘይግሕፎ ፡ ነፋስ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፡ ወበእንተዝ ፡ ኢትነሥኡ ረሚዓን ፡ እምደይን ። ወኢኃጥአን ፡ ውስተ ፡ ምክረ ፡ ጻድቃን ። እስመ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍኖቶሙ ፡ ለጻድቃን ። ወፍኖቶሙሰ ፡ ለኃጥአን ፡ ትጠፍዕ ፡ ብሏል ፡ መዝ ፡ ፩ ፡ ፩-፮ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፳፱—፴፫ ።



፲፱ነኛ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ እንዲያልፍና ፡ የማያልፈው ፡ ሐዲስ ፡ ዓለም ፡ እንዲተካ ፡ ያንጊዜ ፡ ጻድቃን ፡ ከፀሐይ ፡ ፯ ፡ እጅ ፡ እንዲያበሩ ። ወሰማይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ይወፅእ ፡ ወየሐልፍ ፡ ወሰማይ ፡ ሐዲስ ፡ ይትረአይ ፡ ወኵሉ ፡ ኃይለ ፡ ሰማያት ፡ ያበርሁ ፡ ለዓለም ፡ ፯ተ ፡ ምክዕቢተ ።

የቀደመው ፡ ሰማይ ፡ ያልፋል ፡ ዐዲስ ፡ ሰማይ ፡ ይታያል ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ኃይላትም ፡ ሰባት ፡ ዕዕፍ ፡ ድርብ ፡ ለዓለም ፡ ያበራሉ ፡ ብሏል ፡ ፵፭ ፡ ፯ ።

ይህንም ፡ የሄኖክን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ኢሳይያስ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ አዲስ ፡ ሰማይ ፡ እፈጥራለሁና ፡ አዲስም ፡ ምድር ፡ የቀደሙትም ፡ አይታሰቡም ፡ ወደ ፡ ልብም ፡ አይገቡም ። አዲስ ፡ ሰማይና ፡ አዲስ ፡ ምድርም ፡ እኔ ፡ የምሠራቸው ፡ በፊቴ ፡ እንዲቆሙ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሏል ፡ ኢሳ ፡ ፷፭ ፡ ፲፯ ። ፷፮ ፡ ፳፪ ።

ሊቀ ፡ ሐዋርያት ፡ ጴጥሮስም ፡ የአምላክን ፡ ቀን ፡ መምጣት ፡ ስትጠብቁ ፡ ወደርሱም ፡ ስትቸኩሉ ፡ ስለርሱ ፡ ሰማዮች ፡ ተቃጥለው ፡ ይፈታሉ ፡ የፍጥረትም ፡ ሥር ፡ በትኩሳት ፡ ይቀልጣል ። እኛ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተስፋው ፡ አዲሱን ፡ ሰማይ ፡ አዲሲቱንም ፡ ምድር ፡ ጽድቅ ፡ የሚኖርባትን ፡ እንጠብቃለን ፡ ብሏል ፡ ፪ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።

ዮሐንስም ፡ በራእዩ ፡ አዲስ ፡ ሰማይ ፡ አዲስ ፡ ምድር ፡ አየሁ ፡ የፊተኛይቱ ፡ ሰማይ ፡ የፊተኛይቱ ፡ ምድር ፡ አልፋለችና ። ባሕርም ፡ እንግዲህ ፡ አይገኝም ፡ ብሏል ፡ ራእ ፡ ፳፩ ፡ ፩ ።

፳ኛ ፡ ስለራሱም ፡ ወእምቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ነገር ፡ ተከብተ ፡ ሄኖክ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየአምር ፡ እምውሉደ ፡ ሰብእ ፡ በኀበ ፡ ተከብተ ፡ ወኀበ ፡ ሀሎ ፡ ወምንተ ፡ ኮነ ። ወኵሉ ፡ ግብሩ ፡ ምስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ወምስለ ፡ ትጉሃን ፡ በመዋዕሊሁ ። ወአነ ፡ ሄኖክ ፡ ከንኩ ፡ እባርኮ ፡ ለእግዚእ ፡ ዐቢይ ፡ ወለንጉሥ ፡ ዘለዓለም ። ወናሁ ፡ ትጉሃን ፡ ይጼውዑኒ ፡ ሊተ ፡ ለሄኖክ ፡ ጸሐፌ ፡ ጽድቅ ፡ ሑር ፡ አይድዕ ፡ ለትጉሃን ፡ ሰማይ ፡ ፲ ፡ ፩-፯ ።

ከነገሩ ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ሄኖክ ፡ ተሰወረ ፡ የተሰወረበትም ፡ ቦታና ፡ ያለበትም ፡ የት ፡ እንደኾነ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ። በዘመኑ ፡ ሥራው ፡ ኹሉ ፡ ከቅዱሳንና ፡ ከትጉሃን ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ ኾነ ። እኔ ፡ ሄኖክ ፡ ገናና ፡ ጌታ ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ እሱን ፡ የማመሰግነው ፡ ኾንኩ ። እነሆ ፡ ትጉሃን ፡ መላእክት ፡ እውነት ፡ ነገርን ፡ የምጽፍ ፡ እኔ ፡ ሄኖክን ፡ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡ ሔደህ ፡ አስተምር ፡ እያሉ ፡ ጠሩኝ ፡ ፲ ፡ ፩-፲ ።

ወመጽአ ፡ ኀቤየ ፡ ዝኩ ፡ መልአክ ፡ በቃሉ ፡ አምኀኒ ፡ ወይቤለኒ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ብእሲ ፡ ዘተወለድከ ፡ ለጽድቅ ፡ ኀደረ ፡ ላዕሌከ ፡ ወጽድቁ ፡ ለርእሰ መዋዕል ፡ ኢየኀድገከ ፡ ብሏል ፡ ፳ ፡ ፵፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

ያ ፡ መልአክ ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ በቃሉ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠኝ ። ለጽድቅ ፡ የተፈ ጠርክ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ጽድቅም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አድሯል ፤ የዘመናት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ አይለይህ ፡ አለኝ ፡ ብሏል ፡ ፳ ፡ ፵፫ ።

ይህነንም ፡ ሊቀ ፡ ነቢያት ፡ ሙሴ ፡ ሄኖክ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ዓመት ፡ ተቀምጦ ፡ ማቱሳ ላን ፡ ወለደ ። ሄኖክ ፡ አካሔዱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አደረገ ። ማቱሳላን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ ኖረ፡ወንዶችንና ፡ሴቶችን ፡ልጆችም ፡ ወለደ ።የሄኖክም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ሄኖክም ፡ አካሔዱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስላደረገ ፡ አልተገኘም ፤ እግዚአብሔር ፡ ወስዶታልና ፡ ብሎ ፡ መስክሮለታል ፡ ዘፍጥ ፡ ፭ ፡ ፳፩-፳፭ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ሄኖክ ፡ በሃይማኖት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ወጣ ። ሞትንም ፡ አላየም ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አልተገኘም ። እግዚአብሔር ፡ አውጥቶታልና ። እግዚአ ብሔርን ፡ ደስ ፡ እንዳሰኘው ፡ ገና ፡ ሳያወጣው ፡ ተመስክሮለት ፡ ነበረና ፡ ብሎ ፡ መስክሮለታል ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፭ ።

አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ፫ቱ፻ት ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፩ዱ ፡ መጽሐፈ ፡ ሲራክ ፡ ብለው ፡ የቆጠሩት ፡ ሲራክም ፡ ወድሶሙ ፡ ንለእደው ፡ ክቡራን ፡ ብሎ ፡ አበውን ፡ በተራ ፡ እያነሣሣ ፡ መጥቶ ፡ ወአልቦ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ዘከመ ፡ ሄኖክ ፡ ወሎቱኒ ፡ ነሥእዎ ፡ እምነ ፡ ብሔር ፡ ብሎ ፡ መስክሮለታል ፤ ሲራ ፡ ፵፱ ፡ ፲፮ ።

ስለትንቢቱም ፡ እውነተኛነትና ፡ ደገኛነት ፡ እሊህ ፡ ኹሉ ፡ ነቢያትና ፡ ሐዋርያት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሳይቀር ፡ ትንቢቱን ፡ በመጥቀሳቸው ፡ ከመመስከራ ቸው ፡ በላይ ፡ ከሐዋርያት ፡ አንዱ ፡ ይሁዳ ፡ ከአዳም ፡ ሰባተኛው ፡ ትውልድ ፡ ሄኖክ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከአእላፍ ፡ ቅዱሳን ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ በእነዚህ ፡ ትንቢት ፡ ተናግ ሮባቸዋል ፡ ሲል ፡ መስክሮለታል ፡ ይሁ ፡ ፲፬ ።

፳፩ኛ ፡ ስላንተና ፡ እንዳንተ ፡ በማስመሰል ፡ የሐሰት ፡ መጽሐፍ ፡ ለሚጽፉ ፤ ለሰው ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ ለሚሰጡ ፡ ሰዎችም ፤ አሌ ፡ ለክሙ ፡ እለ ፡ ትጽሕፉ ፡ ነገረ ፡ ሐሰት ፡ ወነገረ ፡ ረሚዓን ፡ እስመ ፡ ውእቶሙ ፡ ይጽሕፉ ፡ ሐሰቶሙ ፡ ከመ ፡ ይስም ዕዋ ፡ ወኢይርስዕዋ ፡ ለእበድ ።

ስንፍናን ፡ እንዲያጠኗት ፡ እንዳይዘነጓት ፡ ሐሰታቸውን ፡ እውነት ፡ አስመስ ለው ፡ ይጽፋሉና ፡ የዝንጉዎችን ፡ ሐሰት ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ አስመስላችሁ ፡ ለምት ጽፉ ፡ ወዮላችሁ ፤ ፴፯ ፡ ፴፩ ።

አሌ ፡ ለክሙ ፡ እለ ፡ ትዌልጥዎሙ ፡ ለነገራተ ፡ ርትዕ ፡ ወሥርዓት ፡ እንተ ፡ ለዓለም ።

ለዘለዓለሙ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ እውነተኞችን ፡ ነገሮች ፡ በሐሰት ፡ ለምትለ ውጡ ፡ ወዮላችሁ ።

የዐልዉ ፡ ወይሬስዩ ፡ ርእሰሙ ፡ ዘኢኮኑ ፡ ኃጥአነ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ሀለዉ ፡ ይትከየዱ ።



ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ አልሠራንም ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ይፈረድባቸው ፡ ዘንድ ፡ አላቸውና ፡ ብሎ ፡ ተናግሮብሃል ። ፺፯ ፡ ፴፱ ።

ይህነንም ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይጽሕፉ ፡ መጽሐፈ ፡ እኩየ ።

አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይብልዎ ፡ ለእኩይ ፡ ሠናየ ፡ ወለሠናይ ፡ እኩየ ፡ እለ ፡ ይብልዎ ፡ ለብርሃን ፡ ጽልመተ ፡ ወለጽልመት ፡ ብርሃነ ፡ እለ ፡ ይብልዎ ፡ ለጥዑም ፡ መሪረ ፡ ወለመሪር ፡ ጥዑመ ። አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይጠበቡ ፡ ለእከይ ፡ ወይብሉ ፡ ንሕነ ፡ ከመ ፡ ጠቢባን ፡ ብሏል ፡ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳ ፡ -፳፪ ፡ ፲፩ ።

ጌታም ፡ ወያወፅኡ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ስመ ፡ እኩየ ፡ በእንተ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመ ሕያው ፡ ብሏል ፡ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፪ ።

ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ወእለሰ ፡ አልቦሙ ፡ ትምህርት ፡ እለ ፡ ኢለበዉ ፡ ይመይ ጥዎ ፡ ለቃለ ፡ መጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ሜጥዎን ፡ ለብዙኃት ፡ መጻሕፍት ፡ ለግእዘሙ ፡ ወያማስኑ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

፳፪ተኛ ፡ የመምለክያነ ፡ ጣዖትን ፡ ነገር ፡ በሴሩህ ፡ ጊዜ ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ከመጀመሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ወሃይማኖቶሙ ፡ ከነ ፡ ለአማልክት ፡ እለ ፡ ገብሩ ፡ በእደዊ ሆሙ ፡ ወይክህዱ ፡ ስሞ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ወይሰደዱ ፡ እምአብያተ ፡ ምስት ጉቡአ ፡ ዚአሁ ፡ ወለመሃይምናን ፡ እለ ፡ ስቁላን ፡ በስሙ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ወይሰግዱ ፡ ለእብን ፡ ወእለ ፡ ይገድፉ ፡ ምስለ ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ፡ ወዘዕፅ ፡ ወዘል ሕኵት ።

ሃይማኖታቸውም ፡ የመናፍስት ፡ ጌታን ፡ ስሙን ፡ ክደው ፡ በእጃቸው ፡ የተሠሩ ፡ ጣዖታትን ፡ ያመልካሉ ፡ በመናፍስት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ የተጠሩ ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ የርሱ ፡ ወገኖች ፡ ምእመናን ፡ ከሚሰበሰቡባት ፡ ከመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ይሰደዳሉ ።

ከወርቅ ፡ ከብር ፡ ከእንጨት ፡ ከሸክላ ፡ ከደንጋይ ፡ ለተሠሩ ፡ ጣዖታት ፡ ይሰግ ዳሉ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ። ፵፮ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ፡ ፵ ።

ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ በሴሩህ ፡ ዘመን ፡ ጣዖት ፡ መሥራት ፡ ከተጀመረ ፡ ወዲህ ፡ የተ ነሡ ፡ ነቢያትም ፡ ያይን ፡ ምስክሮች ፡ ኾነው ፡ ሄኖክ ፡ በትንቢት ፡ የተናገረውን ፡ አማልክቲሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ አፍ ፡ በሙ ፡ ወኢይነቡ ፡ እያሉ ፡ ተናግረዋል ፡ መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ፻፴፭ ።

በአርእስቱ ፡ አንተ ፡ ባታውቅ ፡ ሄኖክን ፡ ለአዋልድ ፡ ብቻ ፡ አውራቸው ፡ ትለዋለህ ፡ እንጂ ፡ እሱስ ፡ ለብሉያትና ፡ ለሐዲሳትም ፡ መሪ ፡ ፊታውራሪ ፡ ነው ፤ ያልኩህን ፡ እነኾ ፡ ከ፩—፳፪ ፡ ቍ ፡ ንባቡን ፡ ከንባባቸው ፡ ኀይለ ፡ ቃሉን ፡ ከኀ ይለ ፡ ቃላቸው ፡ ምሥጢሩን ፡ ከምሥጢራቸው ፡ እያስማማሁ ፡ አስረዳሁህ ። አንባ ብያንና ፡ ሰማዕያን ፡ ይሰለቹብኛል ፡ ብዬ ፡ ታገሥኩት ፡ እንጂ ፡ ቃለ ፡ በረከት ፡ ዘሄኖክ ፡ ካለው ፡ ጀምረህ ፡ ተፈጸመ ፡ በዝየ ፡ ራእየ ፡ ኀቡዓት ፡ ዘሄኖክ ፡ እስኪል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ድረስ ፡ ብትመለከተው ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ ባገኘኸው ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይኾናል ፡ አታደርገውም ።

እኔ ፡ ግን ፡ ወደፊትም ፡ አስፈላጊ ፡ በኾነበት ፡ ቦታ ፡ ኹሉ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጋራ ፡ እያስማማሁ ፡ እጠቅስልሃለሁና ፡ በያንቀጹ ፡ ተመልከት ።

እንግዲህ ፡ ዐበይት ፡ ነቢያት ፤ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፤ ሐዋርያት ፡ ፸ ፡ አርድእት ፡ ከአሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ እስከ ፡ አቡቀለምሲስ ፡ ለጻፉዋቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ያደረጉትን ፡ ሄኖክን ፡ ስትነቅፍ ፡ እነዚያን ፡ ኹሉ ፡ መንቀፍህ ፡ እንደ ኾነ ፡ አስተውል ። ሥሩ ፡ ጣፋጭ ፡ ከልኾነ ፡ ሚፉ ፡ አይጣፍጥምና ፡ ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ። ለዚኸውም ፡ መረጃ ፤ ይኾንህ ፡ ዘንድ ፡ ስለዚሁ ፡ ከደረሰው ፡ የተዘጋጀ ፡ አንድ ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ እጽፍልሃለሁ ።

ሥርወ ፡ መጻሕፍት ፡ ዕፀው ፡ እለ ፡ ነቢያት ፤ ወዘሐዋርያት ፡ አዕፁቅ ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ፡ ልብው ።

መዓዛ ፡ ትሥልስት ፡ ስኂን ፡ ወመዓዛ ፡ ትስብእት ፡ አፈው ።
ዘእምጽጌ ፡ ቃሉ ፡ አጌነዉነ ፤ ነፋሳት ፡ ጸሐፍት ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ አበው ።
ኢይትከሀል ፡ ይትሐሰው ፤ ወይትነሣት ፡ ሕቀ ፡ በአፈ ፡ ብእሲ ፡ ቅብው ።
ልሱሐሰ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ጣዕመ ፡ ቃለ ፡ ሄኖክ ፡ ፄው ።
ተሰምዮ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ጣዕመ ፡ መጻሕፍት ፡ ይትሔሰው ።
እምጥንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ሥርው ።
እምጣነ ፡ አዕፁቅ ፡ ኢይትቄደሱ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ መዚንው ።

## የነአዛሔልና ፡ አዛዛሔል ፡ ዘር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለመኖሩ ፡

፴፪ መላእክት ፡ ወደምድር ፡ ወርደው ፡ ሴቶችን ፡ እየመረጡ ፡ አገቡ ፡ አለ ፡ ስትል ፡ የነአዛሔል አባቶቻቸው ፡ መላእክት ፡ ቢኾኑ ፡ እናቶቻቸው ፡ ሰዎች ፡ መኾናቸውን ፡ አረጋግጠሃል ። እንግዲህ ፡ በናቶቻቸው ፡ ሰዎች ፡ ከኾኑ ፤ የሰውም ፡ ዘር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ካለ ፤ ዘራቸው ፡ ጠፋ ፡ እያልክ ፡ ለምን ፡ ትዋሻለህ ። እንዲህም ፡ ስላልኩህ ፡ ቢኾኑስ ኖሮ ፡ ማለቴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አባቶቻቸው ፡ በቁሙ ፡ መላእክት ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ ያመንኩልህ ፡ አይምሰልህ ። ይህስ ፡ አንተ ፡ ተስአሎ ፡ ለአቡከ ፡ ወይነግረከ ፡ ወሊቃውንቲከ ፡ ይዜንዉከ ፡ ያለውን ፡ ባለማወቅህ ፡ ሊቃውንትን ፡ መምህራንን ፡ ጠይቆ ፡ መረዳት ፡ ነውር ፡ መስሎህ ፡ አፍህ ፡ እንዳመጣ ፡ ትዘባርቃለህ ፡ እንጂ ፡ በቁሙ ፡ መላእክት ፡ አደሉም ። በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ከሴት ፡ ርቀው ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቀው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ናቸው ። መላእክት ፡ ማለቱ ፡ ሰለኹለት ፡ ነገር ፡ ነው ።

አንደኛ ፡ ስለአለቅነታቸው ፤ ኹለተኛ ፡ ስለንጽሕናቸውና ፡ ስለ ፡ ቅድስናቸው ፡ ነው ።

ስለአለቅነታቸው ፡ ላልኩህ ፡ ግሥ ፡ ተመልአክ ፡ አለቃ ፡ ኾነ ፡ ብሎ ፤ መልአክ ፡ አለቃ ፤ መላእክት ፡ አለቆች ፡ ይላል ፡ የግእዙ ፡ ጠባይዕ ፡ ይህ ፡ ነው ። የመጻሕፍት



፩ኛ ፡ ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ ። ወሕዝብኒ ፡ ነበቡ ፡ ከንቶ ። ወተንሥኡ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ። ብሎ ፡ ወመላእክትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ ፡ ይላል ፡ መዝ ፡ ፪ ፡ ፪ ።

አሁን ፡ መላእክት ፡ ያለ ፡ መኳንንቱ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እነቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እነቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ከአይሁድ ፡ ጋራ ፡ በጌታ ፡ መስቀል ፤ ተባበሩ ፡ ማለት አይደለም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ በግእዙ ፡ ወመላእክትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ኅቡረ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወላዕለ ፡ መሲሑ ፡ የሚለውን ፡ ንባብ ፡ ባማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መኳንንቱም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በመሲሑ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ባንድ ፡ ተማከሩ ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ።

፪ተኛም ፡ መላእክተ ፡ ይሁዳ ፡ መሳፍንቲሆሙ ። መላእክተ ። ዛብሎን ፡ ወመላእክተ ፡ ንፍታሌም ፡ ይላል ፡ መዝ ፡ ፷፰ ። ፳፯ ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የይሁዳ ፡ የቤት ፡ አለቆች ፡ የዛብሎን ፡ የቤት ፡ አለቆች ፡ የንፍታሌም ፡ የቤት ፡ አለቆች ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የይሁዳ ሚካኤል ፡ የዛብሎን ፡ ገብርኤል ፡ የንፍታሌም ፡ ሩፋኤል ፡ ማለቱ ፡ አይደለም ።

ይህንም ፡ እንደዚያው ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ በግእዙ ፡ መላእክተ ፡ ይሁዳ ፡ መሳፍንቲሆሙ ። መላእክተ ፡ ዛብሎን ፡ ወመእላክተ ፡ ንፍታሌም ፡ ያለውን ፤ ያማርኛው መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የይሁዳ ፡ አለቆች ፡ ከሠራዊታቸው ፡ ጋራ ፡ የዛብሎን ፡ አለቆችና ፡ የንፍታሌም ፡ አለቆች ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ።

፫ተኛ ፡ ረስዮሙ ፡ ለመላእክቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ሔሬብ ፡ ወዜብ ፡ ወዜብሔል ፡ ወስልማና ፡ ወኵሎሙ ፡ መላእክቲሆሙ ፡ ይላል ፡ መዝ ፡ ፹፫ ፡ ፲፩ ።

እንዲህ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የጠላቶችህ ፡ የኤዶምያስን ፡ የእስማዔላውንን ፡ የሞዓብንና ፡ የዐጋራውያንን ፡ አለቆቻቸውን ፡ እንደ ፡ ሔሬብ ፡ እንደ ፡ ዜብ ፡ አድርጋቸው ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሚካኤልን ፡ ገብርኤልን ፡ ማለቱ ፡ አይደለም ።

፬ተኛ ፡ ወጸሐፍ ፡ ሎቱ ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘኤፌሶን ፡ ለመልአከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሰምርኔስ ፡ ይላል ፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩ ፡ ፰ ፡ ፲፪ ፲፰ ። ም ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ።

አሁን ፡ ጻፍላቸው ፡ የሚለው ፡ ለየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አለቆች ፡ ለኤጲስ ፡ ቆጶሳቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለነሚካኤል ፡ ለነገብርኤል ፡ አይደለም ።

፭ተኛ ፡ ወይእዜኒ ፡ አኃውየ ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ በኢያእምሮ ፡ ገበርክምዎ ፡ ለዝ ፡ ከመ ፡ ገብሩ ፡ መላእክቲክሙ ፡ ይላል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

መላእክቲክሙ ፡ ማለቱ ፡ አለቆቻችሁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሚካኤሎቻችሁ ፡ ገብርኤሎቻችሁ ፡ ማለቱ ፡ አለመኾኑን ፡ አስተውል ።

## ኹለተኛ ፡ ስለንጽሕናቸው ።

ሰው ፡ ስለንጽሕናው ፡ መልአክ ፡ እንዲባል ፡ ሲያስረዳ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ። [illegible] ፡ [illegible]ይዉ ፡ ምውታን ፡ ኢያወስቡ ፡ ወኢይትዋሰቡ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ መላእክት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይከውኑ ፡ በሰማያት ፡ ብሏል ። ማቴ ፤ ፳፪ ፡ ፴ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይልቁንም ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ሰው ፡ በግብሩ ፡ መጠራት ፡ እንዲገባው ፡ ሲያስረዳ ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ አንሰ ፡ እቤ ፡ አማልክት ፡ አንትሙ ። ወደቂቀ ፡ ልዑል ፤ ኵልክሙ ፡ ብሏል ። መዝ ፡ ፹፪ ፡ ፮ ።

ይህንንም ፡ ጌታ ፤ አኮኑ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ኦሪትክሙ ፡ አንሰ ፡ እቤ ፡ አማልክት ፡ አንትሙ ። ወሰበ ፡ ለእልክቱ ፡ አማልክት ፡ ይቤሎሙ ፡ እለ ፡ ከነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤሆሙ ፡ ኢይትከሀል ፡ ይትሐሰው ፡ ወይትነሠት ፡ ቃለ ፡ መጽሐፍ ፡ እፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘቀደሶ ፡ አብ ፡ ወፈነዎ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ትብሉኒ ፡ ትፀርፍ ፡ ለእመ ፡ እቤለክሙ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አነ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፴፫–፴፮

በኦሪታችሁ ፡ እኔስ ፡ አማልክት ፡ ናችሁ ፡ ብዬ ፡ ነበረ ፡ የሚል ፡ ተጽፎ ፡ የለምን ። የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሊታበል ፡ አይቻልምና ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተላከላቸው ፡ እኒያን ፤ አማልክት ፡ ካላቸው ፤ አብ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የላከኝ ፡ እኔንማ ፤ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ብላችሁ ፡ ትሳደባለህ ፡ እንደምን ፡ ትሉኛላችሁ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ።

ሄኖክም ፡ እንደዚሁ ፡ መላእክት ፡ ያላቸው ፡ ከሴት ፡ ርቀው ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቀው ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በቁሙ ፡ መላእክት ፡ አይደሉም ።

ሰዎች ፡ መኾናቸው ፤ መላእክት ፡ አለመኾንቸውም ፡ ፍትወት /እንስሳዊ ፡ ተስማሚነቱ ፡ ለግዙፋን ፡ ፍጥረቶች ፡ ለሥጋውያን ፡ ለደማውያን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለረቂቃን ፡ ፍጥረቶች ፡ ለመላእክት ፡ አይደለምና ፤ እኒህ ፡ መላእክት ፡ መልከ ፡ መልካሞች ፡ ሴቶችን ፡ አይተው ፡ ፍትወት ፡ ተነሣሣባቸው ፤ በሐፀ ፡ ዝሙት ፡ ተነደፉ ፡ በማለቱ ፡ ይታወቃል ። ፍትወት ፡ እንስሳዊስ ፡ ለመላእክት ፡ በሕርይ ፡ ተስማሚ ኾኖ ፡ ቢኾን ፡ ዲያብሎስ ፡ ሔዋንን ፡ በሳተ ፡ ጊዜ ፡ በዚህም ፡ ዐይነት ፡ ስሕተት ፡ እሱም ፡ በሳተበት ፡ እሷንም ፡ ባሳታት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ አስበልቶ ፡ አምላክነትን ፡ እንድትሻ ፡ ማድረጉ ፡ ብቻ ፡ ባልበቃውም ነበረ ።

በሌላም ፡ አንቀጽ ፡ ዛቲ ፡ ኵነኔ ፡ እንተ ፡ ይትኴነኑ ፡ መላእክት ፡ ሰማዕት ፡ ይእቲ ፡ ለነገሥት ፡ ወለአዚዛን ፡ እለ ፡ ይእኅዝዎ ፡ ለየብስ ፡ እስመ ፡ እሉ ፡ ማያተ ፡ ኵነኔ ፡ ለፈውሰ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለመላእክት ፡ ወለሞተ ፡ ሥጋሆሙ ። ይህች ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ የሚቀጡት ፡ ቅጣት ። ዓለምን ፡ ለመግዛት ፡ ሥልጣን ፡ ላላቸው ፡ ለነገሥታት ፡ ምስክር ፡ ትኾንባቸዋለች ። እሊህ ፡ የጥፋት ፡ ወኃዎች ፡ ከኃጢአት ፡ ለተጠበቁ ፡ ለነኖኅ ፡ ድኅነት ፤ ላልተጠበቁ ፡ ለሰብአ ፡ ትካት ፡ ጥፋት ፡ ኾነውባቸዋልና ፡ ብሎ ፡ ገልጾታል ። ፲፰ ፡ ፱

መላእክትማ ፡ ምን ፡ ሥጋ ፡ አላቸውና ፡ ለፈውሰ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለመላእክት ፡ ወለሞተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ይላል ። እንግዲህ ፡ ሰዎች ፡ መኾናቸውን ፤ መላእክት ፡ አለመኾናቸውን ፡ በዚህ ፡ ተረዳ ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ወነዋ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለእልክቱ ፡ [illegible] ዚአሆሙ ፡ ስምያዛ ፡ ወካልእ ፡ አርስጢኬፋ ፡ ወሣልሱ ፡ አርሚን ።



የነዚያም ፡ አለቆች ፡ ስማቸው ይህ ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ስማያዛ ፤ ኹለተኛው ፡ አርስጢኬፋ ፤ ሦስተኛው ፡ አርሚን ፡ ይባላሉ ፡ እያለ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ እስከ ፡ ፳ ፡ ቍጥር ፡ ዘርዝሮ ፡ ከቈጠረ ፡ በኋላ ፡ ፲፱ ፡ ፲ ፤ እኒህኑ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ አስተው ፡ ከልዑል ፡ ማዓርጋቸው ፡ ያወረዷቸውን ፤ በአዋልደ ፡ ቃየል ፡ እንዲሰስኑ ፡ ያደረጓቸውን ፡ አጋንንትን ፡ ለይቶ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘአስሐተ ፡ ኵሎሙ ፡ ደቂቀ ፡ መላእክት ፡ ወአውረዶሙ ፡ ዲበ ፡ የብስ ፡ ወአስሐቶሙ ፡ በአዋልደ ፡ ሰብእ ፡ ወካልእ ፡ ስሙ ፡ አስብኤል ፡ ዝንቱ ፡ አመሮሙ ፡ ምክረ ፡ እኩየ ፡ ለደቂቀ ፡ መላእክት ፡ ቅዱሳን ፡ ወአስሐቶሙ ፡ ከመ ፡ ያማስኑ ፡ ሥጋሆሙ ፡ በአዋልደ ፡ ሰብእ ፤ ወሣልስ ፡ ስሙ ፡ ጋድራኤል ፡ ዝውእቱ ፡ ዘአርአየ ፡ ኵሎ ፡ ዝብጠታተ ፡ ሞት ፡ ለውሉደ ፡ ሰብእ ፤ ወውእቱ ፡ አስሐታ ፡ ለሔዋን ።

ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ አስቶ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ፋይድ ፡ ያወረዳቸው ፤ በቃየል ፡ ልጆች ፡ እንዲያመነዝሩ ፡ ያደረጋቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ኹለተኛው ፡ ስሙ ፡ አስብኤል ፡ ይባላል ። ርሱ ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ መክሮ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ በቃየል ፡ ልጆች ፡ እንዲያመነዝሩ ፡ ያሳታቸው ፡ ነው ፤ ሦስተኛውም ፡ ስሙ ፡ ጋድራኤል ይባላል ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ መደባደብንና ፡ መጋደልን ፡ ያስተማረ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ ሔዋንንም ፡ ያሳተ ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ ፲፭ ፡ ፲፯—፳፩ ።

ሥጋውያን ፡ ደቂቀ ፡ ሴትንና ፤ ረቂቃን ፡ አጋንንትን ፡ መላእክት ፤ መላእክት ፡ በማለት ፡ ቢያስተባብራቸው ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ የተፈጠሩ ፡ እነስማዝያን ፡ ከመዓርጋቸው ፡ ወረዱ ፤ በሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሳቱ ፤ ሰውነታቸውን ፡ በሴቶች ፡ ልጆች ፡ አሳደፉ ፤ ብሎ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ የተፈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ መኾናቸውን ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ። ተፈጥሯቸው ፡ ከመላእክት ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ እነአስብኤልንና ፡ እነጋድራኤልን ፡ ሔዋንን ፡ እንዳሳቱ ፡ እኒህንም ፡ አሳቷቸው ፡ ብሎ ፡ በየግብራቸው ፡ እንደለያቸው ፡ አስተውል ።

ይህንም ፡ ነገር ፡ ሄኖክ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ሊቀ ፡ ነቢያት ፡ ሙሴም ፡ የመላእክትን ፡ ተፈጥሮ ፡ ሳይኾን ፡ የአዳምን ፡ ትውልድ ፡ መብዛት ፡ በሚናገርበት ፡ አንቀጽ ፡ ሰዎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መብዛት ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፤ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ በተወለዱላቸው ፡ ጊዜ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ የሰውን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ መልካሞች ፡ እንደኾኑ ፡ አዩ ። ከነዚያም ፡ የመረጡ ፡ የመረጧቸውን ፡ ለሚስትነት ፡ ወሰዱ ። እግዚአብሔርም ፡ መንፈሴ ፡ ለዘለዓለም ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ አደለም ። እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ሥጋ ፡ ነውና ፡ ዘመናቸው ፡ ግን ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ይኹን ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሏል ፤ ዘፍ ፡ ፮ ፡ ፩—፬ ።

እንግዲህ ፡ ሄኖክ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ከበዙ ፡ በኋላ ፡ [illegible]ሞች ፡ ቆነጃጅት ፤ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ተወለዱላቸው ። የሰማይ ፡ ልጆች ፡ መላእክት ፡ እነሱን ፡ አይተው ፡ ወደዷቸው ። ከሰማይም ፡ ወርደው ፡ አገ

www.ethiopianorthodox.org

ቧቸው ፡ ያለውና ፡ ሙሴ ፡ የሰው ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ መልከ ፡ መልካሞች ፡ እን ደኾኑ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ሚስቶች ፡ አደረጓቸው ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ እንደ ኾነ ፡ አስተውል ።

ስለቁመታቸው ፡ መርዘምና ፡ ማጠር ፡ እንደ ኾነም ፡ እነሆ ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ረገርምና ፡ ዐጭር ፡ ሰው ፡ ሲፈጠር ፡ ይኖራል ፡ ይልቁንም ፡ ጎልያድ ፡ ፯ ፡ ክንድ ፡ ተስንዝር ፡ ቁመት ፡ እንደነበረው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይነግረናል ፡ ሳሙ ፡ ቀዳ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ፡ ፰ ። እንግዲህ ፡ እርሱ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ አደለም ፡ ሊባል ፡ ነውን ? ፡ አይባልም ።

እንግዲህ ፡ ኄኖክ ፡ ከሰማይ ፡ ወርደው ፡ ሚስት ፡ አገቡ ፡ ያላቸው ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ መኾናቸውን ፤ በቁሙ ፡ መላእክት ፡ አለመኾናቸውን ፡ በሚበቃ ፡ ምስክር ፡ መላልሼ ፡ ካስረዳሁህ ፤ የነአዛሔል ፡ የነአዛዝሔል ፡ ዘር ፡ የአዳም ፡ ዘር ፡ ነውና ፡ ዛሬ ፡ በምሉ ፡ እዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳለ ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ።

ይህንም ፡ ከተረዳህልኝ ፡ ፍጹም ፡ የውሸት ፡ ውሸት ፡ የባልቴቶች ፡ ተረት ፡ ያንተ ፡ ሐሳብና ፡ ያንተ ፡ ንግግር ፡ መኾኑን ፤ የኄኖክ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ፩ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ካጸፋት ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ይልቅ ፤ የጸራ ፤ እውነተኛ ፤ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አንዱ ፡ ደገኛው ፡ እሱ ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ፤ አልረዳም ፡ ብትል ፡ ግን ፡ አስተዋይ ሚዛናዊ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ተመልካች ፡ ኹሉ ፡ ይፍረደኝ ፡ ይፈርደዋል ።

፹፫ ለመጽሐፈ ፡ ኄኖክ ፡ ጓደኛውና ፡ ምስክሩ ፡ ቁርዓን ፡ ወይም ፡ ማሕዱስ ፡ ከሚባለው ፡ ዋናው ፡ የመሐመዳውያን ፡ መጽሐፍ ፡ መላእክት ፡ ወርደው ፡ ሚስቶች ፡ አግብተው ፡ ሃሩትና ፡ ማሩት ፡ አዛሄልና ፡ አዘዛሔል ፡ የሚባሉ ፡ ረጃጅሞች ፡ ሰዎች ወለዱ ፡ ይላል ፡ ስለምትለው ።

እኛ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድም ፡ ሦስትም ፡ ነው ። አንዱ ፡ አካል ፡ ወረደ ፡ ተወለደ ፡ ስንል ፤ ሙሐመዳውያን ፡ አላህ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አይወርድም ፡ አይወለድም ፡ በማለታቸው ፡ እንለያያለን ፡ እንጂ ፡ ፩ እግዚአብሔር ፡ በማለትና ፡ ስነ ፡ ፍጥረትንም ፡ በማመን ፡ እንገናኛለን ። ከመጻሕፍትም ፡ ሙሳ ፡ ተውራትን ፡ (ሙሴ ፡ ኦሪትን) ዳውድ ፡ ዜቡርን ፡ (ዳዊት ፡ መዝሙርን) ነቢዩ ፡ ኢሳ ፡ እንጅልን ፡ (ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌልን ፡) መጻፋቸውን ፡ እናምናለን ፡ ይላሉ ። እንደዚሁ ፡ የኄኖክንም ፡ መጽሐፍ ፡ ተቀብለው ፡ ጠቅሰው ፡ ጽፈው ፡ እንደ ኾነ ፡ የሚነቀፍ ፡ አደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ቁርዓን ፡ ስላልተማርኩና ፡ ስላልተመለከትኩ ፡ እውነት ፤ ወይም ፡ ሐሰት ፡ ብዬ ፡ ዕርግጠኛውን ፡ ልጽፍልህ ፡ አልቻልኩም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሚያውቁትን ፡ አውቃለሁ ፡ የማያውቁትን ፡ አላውቅም ፡ ማለት ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ መኾኑን ፡ እንድትገነዘብልኝ ፤ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፤ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡ ያለውን ፡ እንድትመለከት ፡ አሳስብሃለሁ ፡ ማቴ ፡ ፭ ፴፯ ።

፹፬ ለመጽሐፈ ፡ ኄኖክ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብቻዋ ፡ ለምስክርነት ፡ ትቀበለዋለች ፡ እንጂ ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ያሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የብሉይ ፡ አዋልድ ፡ (አፖግራፌ ) ስለ ኾኑ ፡ ከ፹ወ፩ ፲፱ቱን ፡ ትሩፋት ፡ ብለው ፡ ለምስክርነት ፡ አይቀበሏቸውም ፡ ብለህ ፡ ምስክር ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎ ትቍ ፪፻፱ ፡ ፺ ስለጠቀስከው ።



ይህ ፡ የጠቀስከው ፡ የጸሎት ፡ መጽሐፍ ፡ ከኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ እስከ ፡ ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፡ ያሉትን ፡ ፵ውን ፡ እኒህን ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ ለምስክርነት ፡ ተቀብሏቸዋል ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ቄጥሮ ፡ ከኄኖክ ፡ እስከ ፡ መቃብያን ፡ ካልእ ፡ ፲፬ ፡ መጻሕፍት ፡ ቄጥሮ ፡ እኒህ ፡ ፲፬ቱን ፡ የኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ አድርጋ ፡ ስትቀበላቸው ፡ ሌሎች ፡ የፕሮቴስታንት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የብሉይ አዋልድ ፡ አፖክሪፌ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ አዋልድ ፡ ያገቧቸዋል ፡ እንጂ ፡ ለምስክርነት ፡ አይቀበሏቸውም ፤ አፖክሪፌ ፡ ማለትም ፡ የተሰወሩ ፡ ያልተገለጹ ፡ መጻሕፍት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ይተርካል ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ክህደት ፡ አለባቸው ፡ ብሎ ፡ አልመሰከረም ።

አይቀበሏቸውም ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ እንኳ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ እንደ ፡ አዋልድ ፡ መጻሕፍት ፡ አድርገው ፡ ያገቧቸዋል ፡ እንጂ ፡ ለምስክርነት ፡ አይቀበሏቸውም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ተገኝቶባቸዋል ፡ ተብሎ ፡ ለምስክርነት ፡ የማያበቃ ፡ ነውር ፡ እንደጻፉባቸው ፡ አልገለጸልንም ።

ኢትዮጵያ ፡ ብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ ለመቀበል ፡ ተቀዳሚዋ ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ብቻ ፡ ነበረች ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡ ተቀዳሚ ፡ አልነበራትም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ ስትቀበል ፡ ሌላው ፡ ዓለም ፡ ጣዖት በማምለክ ፡ ውስጥ ፡ ይገኝ ፡ ነበረ ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ በመቀበል ፡ የተከተላት ፡ ሕዝብ ፡ ከብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ግሚሱን ፡ ተቀብሎ ፡ ግሚሱን ፡ አልቀበልም ፡ ቢል ፡ ለራሱ ፡ ይባሰው ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያስ ፡ መሪዪቱ ፡ ተመሪ ፡ ተቀዳሚዪቱ ፡ ተከታይ ፡ ኾና ፡ እነዚያን ፡ አብነት ፡ ልታደርጋቸው ፡ አትሻም ። ቀድሞ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ጣዖት ፡ ሲያመልክ ፡ ርሷ ፡ ብቻዋን ፡ ኦሪትን ፡ በመቀበሏ ፡ እንዳላፈረች በትና ፡ እንዳልተዋረደችበት ፡ ዛሬም ፡ ርሷ ፡ የተቀበለቻቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ የፕሮቴስታንት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባትቀበላቸው ፡ ርሷ ፡ አታፍርበትም ፡ አትዋረድበትም ።

በዚያውም ፡ ላይ ፡ አፖክሪፌ ፡ ማለት ፡ የተሰወሩ ፡ ያልተገለጹ ፡ መጻሕፍት ፡ ማለት ፡ ከኾነ ፡ የተሰወሩባቸው ፡ ያልተገለጹላቸው ፡ ሰዎች ፡ ባይቀበሏቸው ፡ ከጥንት ፡ ጀምረው ፡ ያልተሰወሩባት ፡ የተገለጹላት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በቂ ፡ ምስክር ፡ አድርጋ ፡ ብትቀበላቸው ፡ የሚያስነቅፋት ፡ አለመኾኑን ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ይስማ ዐይነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ያስተውል ።

፹፭ ውድ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቅ ፡ የጨለማው ፡ ፋና ፡ ጌታዬ ፡ ብላታ ፡ ኅሩይ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የስሜን ፡ ሀገር ፤ ሰዎች ፤ (መጽሐፈ ፡ ሊቃውንት ፡) ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተጣሉ ፡ ይካሰሳሉ ፡ የደቡብ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ (አዋልድን ፡) ከእውነተኞች ፤ ሐሰተኞች ፡ ይልቅ ፡ ይበዛሉ ፡ (ወዳጄ ፡ ልቤ ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ገጽ ፡ ፹፪ ፡) ብለው ፡ አስተምረውናልና ፡ ስለምትለው ።

የኄኖክን ፡ ከቍጥር ፡ አለመግባት ፡ በምትናገርበት ፡ ጊዜ ፡ ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ በአዋልድ ፡ መጻሕፍት ፡ ከእውነተኞች ፡ ሐሰተኞች ፡ ይበዛሉ ፡ አሉ ፡ ብለህ ፡ መጥቀስህ ፡ የትኛውን ፡ ሐሳብህን ፡ እንዲገድፍልህ ፡ ነው ፡ ይኾን ።

www.ethiopianorthodox.org

ርሳቸውስ ፡ ከእውነተኞች ፡ ሐሰተኞች ፡ ይበዛሉ ፡ ማለታቸው ፡ አንተ ፡ እን ደጻፍክቻው ፡ ያሉትን ፡ መጻሕፍተ ፡ ፈጠራ ፡ ሲነቅፉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሄኖክን ፡ ሲነቅፉ ፡ አይደለም ።

ሄኖክንስ ፡ ጎሀ ፡ ጽባሕ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ የብሉይ ፡ መጻሕፍትን ፡ በቈጠሩበት ፡ አንቀጽ ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ፡ አንድ ፡ ብለው ፡ ቈጥረውታል ።

ከዚህም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ መስመር ፡ የሄኖክ ፡ መጽሐፍ ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ከተጻፈው ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ ቀድሞ ፡ የተጻፈ ፡ አልተገኘም ። ብዙ ፡ የዓለም ፡ ሊቃውንቶች ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ለማግኘት ፡ ፈልገው ፡ ሳያገኙት ፡ ቀሩ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈውን ፡ በየቋንቋቸው ፡ የእንግሊዝ ፡ የፈረ ንሳይ ፡ የጀርመን ፡ የኢጣልያ ፡ ሊቃውንት ፡ ተርጒመውታል ፡ ይባላል ፡ በእንግ ሊዝ ፡ የተተረጐመውን ፡ እኔ ፡ በዓይኔ ፡ አይቸዋለሁ ፡ ብለው ፡ ሄኖክን ፡ ከማጣቱ ፡ በቀር ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ተካክሎ ፡ እንዲፈልገው ፡ መስክረውለታል ፡ እንጂ ፡ መቸም ፡ ቢኾን ፡ ሄኖክን ፡ የነቀፉበት ፡ ጽሑፍ ፡ አይገኝም ።

ይህንም ፡ የክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይን ፡ ቃል ፡ ታላቁ ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ መዝገበ ፡ ፊደል ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ገጽ ፡ ፶፬ ፡ የአሪት ፡ ትምህርት ፡ አበጋዞች ፡ የብሉይ ፡ የሐዲስ ፡ መሐንድሶች ፡ እነጳውሎስ ፡ እነእስጢፋኖስ ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ኹሉ ፡ ሱባዔ ፡ ትውልድ ፡ ከሄኖክ ፤ ሱባዔ ፡ ዘመን ፡ ከዳንኤል ፤ ሱባዔ ፡ ዕለት ፡ ከኤርምያስ ፡ በስፍር ፡ በቍጥር ፡ እያመጡ ፡ ከኦሪትና ፡ ከነቢያት ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ እየሰጡ ፡ ትውልዱን ፡ ከዘመን ፡ ትንቢቱን ፡ ከመድኅን ፡ እያስማሙና ፡ እየተረጐሙ ፡ ኦሪትስኬ ፡ መርሐ ፡ ክነተነ ፡ ለኅበ ፡ ክር ስቶስ ፡ እንከሰ ፡ ኢንፈቅድ ፡ መርሐ ፡ እያሉ ፡ በክርክርና ፡ በሙግት ፡ ወዲህም ፡ በአምላካዊ ፡ ኃይል ፡ በተአምራት ፡ በ፪ቱም ፡ ወገን ፡ የማይገፉ ፡ የማይሸነፉ ፡ ስለኾ ኑባቸው ፡ አይሁድ ፡ ከኀፍረትና ፡ ከብስጭት ፡ ከቍጣ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ወንጌልን ፡ ያጠፉን ፡ ኦሪትን ፡ ያሰፉን ፡ መስሏቸው ፡ ሐዋርያት ፡ የሚጠቅሷቸው ፡ ደረቅ ፡ ትን ቢትና ፡ ሱባዔ ፡ ራእይ ፡ ያላቸውን ፡ የክርስቶስን ፡ አምላክነትና ፡ ሰውነት ፡ ድካሙ ንና ፡ ኃይሉን ፡ መከራ ፡ መስቀሉን ፡ በሕማሙና ፡ በሞቱ ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ መኾኑን ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ገልጠው ፡ አፍርጠው ፡ የሚናገሩትን ፤ ቃላቸው ፡ ከብሉይ ፡ ንባብ ፡ የተለየ ፡ ፍጹም ፡ ደረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ስለኾነ ፡ ከቍጥር ፡ ከቀመር ፡ ሳይገቡ ፡ ለምስክርነት ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ብሌን ፡ እንዳደራ ፡ ምናን ፡ በፍጹም ፡ ጥን ቃቄ ፡ ተጠብቀው ፤ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩትን ፡ የብሉይ ፡ አዋልድ ፡ ኹሉ ፡ ጭራሽ ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ዕልም ፡ ድርግም ፡ አድርገው ፡ አጠፉቸው ።

ኋላ ፡ ግን ፡ በዕርው ፡ ምላሽ ፡ ተገኝተው ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ከተተረጐሙት ፡ አዋልድ ፡ ኩፋሌና ፡ ሄኖክ ፡ ተረፈ ፡ ኤርምያስ ፡ ዕርገተ ፡ ኤልያስ ፡ እሊሀ ፡ ዐረቱ ፡ ከግእዝ ፡ በቀር ፡ በኹሉ ፡ ስላልተገኙ ፡ ሄኖክን ፡ ብቻ ፡ ከግእዝ ፡ ተርጒመው ፡ አይሁድ ፡ ሳይቀሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ይዘውታል ፡ ከግእዝ ፡ ጋራ ፡ በዕብራይ ስጥ ፡ የታተመውን ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ደብረ ፡ ገነት ፡ በለው ፡ በአይሁድ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ እኛ ፡ ባይናችን ፡ አይተናል ፡ ብለው ፡ አረጋግጠው ፡ ነገረ



ውናል ። እንግዲህ ፡ ሐዋርያት ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ የረ ቱበቻውን ፡ አይሁድ ፡ የተረቱባቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ስትሰድብና ፡ ስትነቅፍ ፡ ከተገ ኘህ ፡ የአይሁድ ፡ ተባባሪ ፡ የክርስቶስ ፡ ተጻራሪ ፡ መኾንህን ፡ እወቅ ፡ ተመልካ ችም ፡ ይወቅልህ ።

ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ኅሩይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጥምቀት ፡ ወልዳ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ፪ት ፡ ልደት ፡ ማለት ፡ ጡቶ ቿን ፡ እያጠባች ፡ ያሳደገቻቸው ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ስለኾኑ ፡ አንተ ፡ የምትነ ቅፈውን ፡ ለታቦት ፡ ለሥዕል ፡ ለመስቀል ፡ የሚገባውን ፡ የጸጋ ፡ ስግድ ፡ ሳያቋርጡ ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክትንም ፡ እንዲሁ ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ እያከበሩ ፡ የኖሩና ፡ በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ ዐፅማቸው ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ውስጥ ፡ ዐርፎ ፡ የሚገኝ ፡ ፍጹም ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ናቸው ።

እንግዲህ ፡ በሃይማኖትና ፡ በባህል ፡ ልዩነት ፡ ከሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በሀብትና ፡ በመዓርግ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ የምታከብር ፡ የምታመሰግን ፡ በሀብትና ፡ በመዓርግ ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ያሉትን ፡ የምትነቅፍ ፡ የምትሰድብ ፡ ከኾንክ ፡ በገጽ ፡ ፱ ፡ በቁልምጫ ፡ መናገር ፡ አላውቅም ። ለሰው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መናገርን ፡ ከፈለግሁ ፡ የክርስቶስ ፡ ባርያ ፡ ባልኾንኩም ፡ ነበረ ፡ ያልከው ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ መኾኑ ፡ ወዴት ፡ አለ ። አንተ ፡ አታላይ ፡ ለማታለል ፡ የተሠራ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ሳይገለጥ ፡ አይቀርምና ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በጽሑፎችህ ፡ ኹሉ ፡ ቃዝ በሃል ፡ ወደፊትም ፡ የሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ ሲታዘብህ ፡ ይኖራል ።

፴፯ ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥትም ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ፡ አልተቈጠረምና ፡ ማመን ፡ አይገባም ፡ ስለምትለው ።

ስለእእምሮህ ፡ ደካማነት ፡ ያልቈጠሩት ፡ መስሎህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፫፻ትስ ፡ ፩ ፡ መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ፡ ብለው ፡ ባይቈጥሩትም ፡ በላይኛዎች ፡ መሥመሮች ፡ ንባባቸ ውን ፡ ከንባቡ ፡ ምሥጢራቸውን ፡ ከምሥጢሩ ፡ አስማምቼ ፡ የሱን ፡ ተቀዳሚ ነት ፡ የነሱን ፡ ተከታይነት ፡ ያስረዳሁህን ፡ ብሉያትንና ፡ ሐዲሳትን ፡ ሲቈጥሩ ፡ ዐብ ረው ፡ በምሥጢር ፡ ቈጥረውታል ።

ደግሞ ፡ የስሙ ፡ መጠሪት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ከታየህ ፡ ከ፫፻ ፡ ብልጫ ፡ ያላ ቸው ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ በየመጽሐፋቸው ፡ ስሙን ፡ ከነግብሩ ፡ ትንቢቱን ፡ እስከ ፡ ትሩፋቱ ፡ አምልተው ፡ አስፍተው ፡ ጽፈውለታል ፡ ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፲፰–፳፭ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፴፯ ። ሲራ ፡ ፲፱ ፡ ፵፯ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፭ ። ይሁ ፡ ፲፬ ፡ ተመልከት ፡ ።

ያዝማሮችንና ፡ ያልቃሾችን ፡ ግጥም ፡ ለምስክርነት ፡ ስትጠቅስ ፡ ሄኖክ ፡ ለምስክርነት ፡ አይበቃምና ፡ ሊቀበሉት ፡ አይገባም ፡ በማለትህ ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የእውቀትህንና ፡ ያስተዋዩነትህን ፡ ደረጃ ፡ በዚሁ ፡ ብቻ ፡ ሊረዳው ፡ ችሏል ።

፴፰ አባቶቻችን ፡ ፫፻ ፡ ፲ወ፰ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ የጻፉልን ፡ ፹ወ፩ ፡ ብቻ ፡ ይበቁናል ፡ እንጂ ፡ እውነትና ፡ ሐሰት ፡ እምነትና ፡ ክህደት ፡ ደበላልቀን ፡ ብናምን ፡ ዋጋችን ፡ ምናምንነት ፡ መኾኑን ፡ እንገንዘብ ፡ ኢዮ ፡ ፲፩ ፡ ፴፩ ፡ ስለምትለው ።

፫፻ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልትቀበላቸው ፡ የሚገባ ፡ መጻሕ ፍት ፡ ቊጥራቸው ፡ ፹፩ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቊጥራቸውን ፡ ካረጋገጡ ፡ በኋላ ፡ ዘዚ.ዘ. ቊጥራቸውን ፡ ሲጽፉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

| ተራ ቍ | ብ ሉ ያ ት ። | ዝርዝር | ድምር |
|---|---|---|---|
| ፩ | አሪት ፡ | ፭ | ፭ |
| ፪ | ዘኢያሱ ፡ | ፩ | ፮ |
| ፫ | ዘመሳፍንት ፡ | ፩ | ፯ |
| ፬ | ዘሩት ፡ | ፩ | ፰ |
| ፭ | ዘዮዲት ፡ | ፩ | ፱ |
| ፮ | ነገሥት ፡ | ፬ | ፲፫ |
| ፯ | ሕፁፃን ፡ | ፪ | ፲፭ |
| ፰ | ዕዝራ ፡ | ፪ | ፲፯ |
| ፱ | አስቴር ፡ | ፩ | ፲፰ |
| ፲ | ጦብያ ፡ | ፩ | ፲፱ |
| ፲፩ | ነገረ መቃብያን ፡ | ፪ | ፳፩ |
| ፲፪ | ኢዮብ ፡ | ፩ | ፳፪ |
| ፲፫ | መዝሙረ ዳዊት ፡ | ፩ | ፳፫ |
| ፲፬ | መጻሕፍተ ሰሎሞን ፡ | ፭ | ፳፰ |
| ፲፭ | ዐበይት ነቢያት ፡ | ፬ | ፴፪ |
| ፲፮ | ደቂቀ ነቢያት ፡ | ፲፪ | ፵፬ |
| ፲፯ | ጥበበ ሲራክ ፡ | ፩ | ፵፭ |
| ፲፰ | ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን | ፩ | ፵፮ |

በ፵፮ቱ ፡ ላይ ፡ ሄኖክ ፡ ኩፋሌ ፡ ሱቱኤል ፡ ዕዝራ ፡ ቢጨመሩ ፡ ፵፱ ፡ ይኾናሉ ፤ ስለሄኖክ ፡ የፅጠነው ፡ ሐተታ ፡ በቂ ፡ ነው ። ኩፋሌ ፡ ዘተከፍለ ፡ እም አሪት ፡ ማለት ፡ ነው ። ሱቱኤልም ፡ ያው ፡ ከላይ ፡ የተቈጠረው ፡ ዕዝራ ፡ ነው ፡ እኒህም ፡ አስቀድማ ፡ የተቀበለቻቸው ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ያመጣቻቸው ፡ አይደሉም ። ይህነንም ፡ አንተ ፡ የጨለማው ፋና ፡ የኢትዮጵያው ፡ ሊቅ ፡ ብለህ የመሰከርክላቸው ፡ ክቡር ፡ ብላቴን ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ መጻሕፍትን ፡ ሲቆጥሩ በጎህ ፡ ጽባሕ ፡ ቈጥረዋቸዋል ።

| ተራ ቍ | ሐ ዲ ሳ ት ። | ዝርዝር | ድምር |
|---|---|---|---|
| ፲፱ | ወንጌል ፡ | ፬ | ፬ |
| ፳ | ግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ | ፩ | ፭ |
| ፳፩ | መልእክታተ፡ጳውሎስ ፡ | ፲፬ | ፲፱ |
| ፳፪ | መልክክታተ ፡ ሐዋርያት ፡ | ፯ | ፳፮ |
| ፳፫ | ራእ ዮሐንስ ፡ | ፩ | ፳፯ |

ጠቅላላ ፡ ድምር ፸፫

www.ethiopianorthodox.org



፹፩ ፡ ለማድረግ ፡ ፰ ይጎድላል ፡ ፪ መጽሐፈ ፡ ኪዳን ፡ ፬ ሲኖዶስ ፡ አንድ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ፩ ቀሌምንጦስ ፡ ፰ስትን ፡ ከ፸፫ ፡ ቢጨምሩ ፤ ፹፩ ፡ ይሆናል ። ፹፩ ፡ መጻሕፍት ፡ እሊህ ናቸው ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳን ፡ ጌታ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ ያስተማረው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስተዳደር ፡ ሥርዓት ፡ ጸንቶበት ፡ የሚኖር ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በወንጌሉ ፡ መጨረሻ ፡ ወቦ ፡ ባዕዳትኒ ፡ ብዙኃት ፡ ግብራት ፡ ዘገብረ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ በቅድመ ፡ አርዳኢሁ ፡ ዘኢተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ነው ።

ሲኖዶስም ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መቅድም ፡ መጻሕፍተ ፡ ቀኖናትሰ ፡ ቀዳሚ ሆሙ ፡ ቀኖና ፡ ዘሠርዕዎ ፤ ሐዋርያት ፡ ወእሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ጉቡአን ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ እምድኅረ ፡ ዕርገት ፡ ወርደተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረው ፡ የሐዋርያት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ፬ክፍል ፡ ነው ፡ ሥርዓተ ፡ ጽዮን ፤ አብጥሊስ ፤ ግጽው ፤ ትእዛዝ ፤ ይባላል ። ሥርዓተ ፡ ጽዮን ፡ ፴ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ መሪ ፡ ምልክቱ ፡ ዓይን ። አብጥሊስ ፡ ፹፫ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ መሪ ፡ ምልክቱ ፡ ረስጦአ ። ግጽው ፡ ፸፬ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ መሪ ፡ ምልክቱ ፡ ረስጠብ ። ትእዛዝ ፡ ፵፮ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ መሪ ፡ ምልክቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ይባላል ። ጠቅላላ ፡ ስሙ ፡ ግን ፡ ሲኖዶስ ፡ ነው ፡ ሲኖዶስም ፡ ማለት ፡ ጉባኤ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፫፻፯ትም ፡ ፹፩ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ አግኝተው ፡ ረስጣ ፡ ፹ወ፪ ። ረስጠብ ፡ ፵ወ፭ ፡ ብለው ፡ ከአብጥሊስና ፡ ከግጽው ፡ ጠቅሰው ፡ ጽፈውልናል ፡ እንጂ ፡ ከልቡናቸው ፡ አንቅተው ፡ አልጻፉም ።

ዲድስቅልያም ፡ በዚሁ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መቅድም ፡ ወሣልስ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘዕውቅ ፡ በኀበ ፡ ግብጻውያን ፡ ዲድስቅልያ ፡ ዘውእቱ ፡ ትምህርት ፡ ብሂል ፡ ወይነ ግር ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ተጋብኡ ፡ በእንተ ፡ አንብሮቱ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ፲ ወ፪ቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ወጳውሎስ ፡ ኅሩይ ፡ ወያዕቆብ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘኢየሩ ሳሌም ፡ ተብሎ ፡ የተቈጠረ ፡ የሐዋርያት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። መሪ ፡ ምልክት ፡ ድስቅ ፡ ተብሎ ፡ ተሰጥቶታል ። አንቀጹም ፡ ፵፫ ፡ ነው ።

ቀሌምንጦስም ፡ ወራብዕኒ ፡ መልእክተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀበ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ወት እምርቱ ፡ ጴጥ ፡ ዘውእቱ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተብሎ ፡ የተቈጠረው ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፫፻፯ ፡ በአንቀጸ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ልትቀበላቸው ፡ የታዘዘ ፡ አምላክ ፡ ያጻፋቸው ፡ የአምላክን ፡ ነገር ፡ የሚ ናገሩ ፡ መጻሕፍት ፡ ፹፩ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ዘርዝረው ፡ ደምረው ፡ በግልጽና ፡ በም ሥጢር ፡ የቈጠሩዋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ ጠንቅቃ ፡ ቈጥራ ፡ ታምናለች ፡ እውነትና ፡ ሐሰትን ፡ እምነትና ፡ ክህደትን ፡ ደበላልቃ ፡ አታምንም ።

ኢትዮጵያ ፡ ፫፻፯ ፡ በግልጽ ፡ የቈጠሩዋቸውንና ፡ በምሥጢር ፡ የቈጠሩዋቸውን ፡ ፹፩ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ አስማምታ ፡ ይዛ ፡ ስትገኝ ፡ እነሆ ፡ አንተ ፡ በምሥ ጢር ፡ የተቈጠሩትን ፡ ከብሉይ ፡ ሄኖክን ፤ ኩፋሌን ፤ ሱቱኤል ፡ ዕዝራን ።

ከሐዲስ ፡ ኹለቱን ፡ መጻሕፍተ ፡ ኪዳንን ፤ ሲኖዶስን ፤ ዲድስቅልያን ፤ ቀሌም ጦስን ፡ ፰ቱን ፡ ማወቅህ ፡ ይቅርና ፡ በግልጽ ፡ ከቈጠሯቸውም ፡ እንኳ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዮዲትን ፤ ጦቢትን ፡ ነገረ ፡ መቃብያንን ፡ ኹለቱን ፤ ካምስቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሰሎሞን ፡ ጥበብንና ፡ ተግሣጽን ፤ ጥበበ ፡ ሲራክን ፤ ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ኮርዮንን ፡ ፷ቱን ፡ በድ ምር ፡ ፲፷ቱን ፡ ከቍጥር ፡ አውጥተህ ፡ ፫፻ ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ የቈጠሩትን ፡ ኤርም ያስን ፡ ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፤ ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ፡ ብለህ ፡ ከኹለት ፡ ከፍለህ ፡፡

ከዚህም ፡ ላይ ፡ ከኤርምያስ ፡ ባሮክንና ፡ ተረፈ ፡ ኤርምያስን ፤ ከዳንኤል ፡ ሶስ ናንና ፡ ተረፈ ፡ ዳንኤልን ፡ ገንጥለህ ፡ ጥለህ ፡ ከ፹፩ዱ ፡ ፲፯ቱን ፡ አጕድለህ ፡ ፷፭ቱን ፡ ብቻ ፤ ጠርዘህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ ታወራለህ ፡፡

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጉድ ፡ በጉያህ ፡ ደብቀህ ፡ ፫፻ ፡ የጻፉልን ፡ ፹ወ፩ብቻ ፡ ይበቁናል ፡ እያልክ ፡ በሰው ፡ የምታላግጥ ፡ በ፷፭ትና ፡ በ፹፩ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የቁጥር ፡ ብልጫ ፡ ባታውቅ ፡ ነውን ፤ ወይስ ፡ ይህን ፡ የቍጥር ፡ ብልጫ ፡ አመዛዝኖ ፡ ማወቅ ፡ የሚችል ፡ አይገኝም ፡ ብለህ ፡ ይኾን ፡፡ ወይ ፡ ጉድ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መጠ ንን ፡ አለማወቅ ፡ አጥብቆ ፡ ይገርማል ፡ እኮ !! ፡፡

ማናቸውም ፡ ነገርህ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ገብቶ ፡ ሲመረምሩት ፡ በዝርዝርነቱ ፡ ፍሬ ፡ ሳይጨብጥ ፡ ብርድ ፡ የመታው ፡ አዝመራ ፡ ኾኖ ፡ ይገኛል ፡፡

እንግዲህ ፡ እውነትና ፡ ሐሰት ፡ እምነትና ፡ ክህደት ፡ ደበላልቆ ፡ ማመን ፡ ማለት ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ ከ፹፩ ፡ መጻሕፍት ፡ ፲፮ቱን ፡ ገንጥሎ ፡ ጥሎ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘነሥአ ፡ እመጻሕፍቲ ፡ ሐሰት ፡ እንተ ፡ አንበርዋ ፡ ከህ ድያን ፡ ወአብአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ በእንተ ፡ ሙስና ፡ ሕዝብ ፡ ይሰደድ ፡፡

የምእመናንን ፡ ልቡና ፡ በመጥፎ ፡ ሐሳብ ፡ ለማበላሸት ፡ መናፍቃን ፡ ጠን ቋዮች ፡ ከጻፏቸው ፡ የሐሰት ፡ መጻሕፍቶች ፡ ጽሮ ፡ ለምእመናን ፡ የሚያድል ፡ ቢኖር ፡ ከምእመናን ፡ ይለይ ፡ (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ሩብ ፡) ተብሎ ፡ የታወጀበትን ፡ ዐውደ ፡ ነገሥት ፡ ሐተታ ፡ መናፍስት ፡ የተባለ ፡ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍ ፡ ተክቶ ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ ፈንታ ፡ ነጭና ፡ ዳንግሌ ፡ በግ ፡ ጥቁርና ፡ ዳለቻ ፡ ፍየል ፡ ነጭና ፡ ገብስማ ፡ ዶሮ ፡ ደም ፡ አፍሱ ፤ ደሙን ፡ ተቀቡ ፡ በፈርሱ ፡ ታጠቡ ፡ እያሉ ፡ ማስተማር ፡ ነው ፡፡ ኢዮብም ፡ ሰው ፡ በምናምን ፡ ነገር ፡ አይመን ፡ ርሱ ይስታል ፡ ዋጋውም ፡ ምናምንነት ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ፡ እንዲህ ፡ በሚ ያደርግ ፡ ሰው ፡ ነው ፡፡ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፤ እምነት ፡ የፈጸምክ ፡ አንተ ፡ ስለኾንክ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ያገኘኸው ፡ ዋጋ ፡ ኹሉ ፡ የምናምንነት ፡ ዋጋ ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ፡፡ ዘመሳ ፡ ፯ ፡ ፩ ፡ ፲፰–፳፯ ፡፡ ነገ ፡ ካል ፡ ፮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ፳–፳፯ ፡፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፩ ፡ ፩–፲፱ ፡፡

፴፰ ለምስክርነት ፡ የማይበቃው ፡ አዋልድ ፡ የተባለው ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ የሐሰትና ፡ የማታለያ ፡ ቃላት ፡ መንፈስ ፡ የሌለው ፡ ሬሳ ፡ መኾኑን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቃላት ፡ በመንፈስ ፡ መርምረህ ፡ መዝነህ ፤ ከንቱና ፡ ውሸት ፡ መኾኑን ፡ አይተህ ፡ አንዘግዝገህ ፡ ጥለህ ፡ በእሳት ፡ አቃጥለህ ፡ አጥፍተህ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ አጽንተህ ፡ ያዝና ፡ ለነፍስህም ፡ ዕረፍት ፡ ታገኛለህ ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፳፰–፴ ፡፡ ሥራ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫–፳ ፡ ስለምትለው ፡፡

ከግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ የጠቀስከውን ፡ ብመለ... አድሮ ፡ ደጋግ ፡ ተአምራት ፡ አደረገ ፡ ከጳውሎስ ፡ መጠምጠሚያ ፡ ቀደው ፡ በበ



ሽተኞች ፡ ላይ ፡ ሲያኖሩባቸው ፡ በሺተኞች ፡ ይድኑ ፡ አጋንንትም ፡ እየጮሁ ፡ ይወጡ ፡ ነበረ ፡፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ በክርስቶስ ሳያምኑ ፡ ጳውሎስ ፡ ስሙን ፡ ፀሚ ያስተምርለት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አማፅነናችኋል ፡ አጋንንት ፤ ውጡ ፡ እያሉ ፡ ረጪቸው ፡፡ እንዲህም ፡ ያደረጉ ፡ በአይሁድ ፡ ካህናት ፡ አለቃ ፡ የኹኑ ፡ የአስቄዋ ፡ ልጆች ፡ ፯ቱ ፡ ናቸው ፡፡ በበሽተኛው ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ጋኔንም ፡ በኢ የሱስ ፡ አምናለሁ ፡ ጳውሎስንም ፡ አውቀዋለሁ ፡ ረ ፡ እናንተ ፤ እነማን ፡ ናችሁ ፡ እናንተማ ፡ ከኔ ፡ ልዩ ፡ ናችሁን ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፡፡ በሽተኛውም ፡ ወዲያው ፡ ተቈጥቶ ፡ ተነሥቶ ፡ ግንበር ፡ ግንባራቸውን ፡ ገምሶ ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ አበረራቸው ፡ ይህም ፡ ነገር ፡ በኤፌሶን ፡ ባሉ ፡ በአይሁድም ፡ በዓረማውያንም ፡ ዘንድ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፈርተው ፡ ኹሉም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አመኑ ፡፡ ካመኑትም ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ እየመጡ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ተናዘዙ ፡፡ የጥንቈላ ፡ የክህደት ፡ መጽሐፎቻቸውንም ፡ እያመጡ ፡ በኹሉ ፡ ፊት አቃጠሉ ፡፡ የተቃጠሉት ፡ መጻሕ ፍትም ፡ ዋጋ ፡ ቢገመት ፡ ፶ሽ ፡ ብር ፡ ኾነ ፡ ይላል ፡፡

አንተ ፡ የጻፍካቸው ፡ የክህደትና ፡ የጥንቈላ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ተቀምጠው ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፤ እነኄኖክ ይቃጠሉ ፡ ለማለት ፡ ይረዳኛል ፡ ብለህ ፡ ይህን ፡ ጥቅስ ፡ በመጥቀስህ ፡ እየተገረምኩ ፡ ከላይም ፡ ከታችም ፡ የተጠቀሱትን ፡ ቃላት ፡ በመንፈሴ ፡ ብመረምር ፡ ለምስክርነት ፡ የማይበቁ ፡ ከንቱና ፡ ውሸት ፡ የሚናገሩ ፡ የሐሰትና ፡ የማታለያ ፡ ቃላት ፡ የመላባቸው ፡ መንፈስ ፡ የሌላቸው ፡ ሬሶች ፡ አንተ ፡ የጻፍካቸው ፡ መጻሕፍቶች ፡ ብቻ ፤ ኾነው ፡ ስላገኘኋቸው ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፳፰–፴ ፡ እንደ ጠቀስከው ፡ ያንተን ፡ ትብትብ ፡ አምዘግዝጌ ፡ ጥዬ ፡ በእሳት ፡ አቃጥዬ ፡ ከየዋሁ ፡ መምህር ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተምሬ ፡ ቀላሏን ፡ ሸክም ፡ ልዝቧን ፡ ቀንበር ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብዬ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ተመለከትኩ ፡ ዕረ ፍተ ፡ ነፍስ ፡ አግኝቻለሁ ፡፡

፴፱ ወዳጆቼ ፡ ሆይ ፡ አዋልድ ፡ የሚባል ፡ ኹሉ ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ስላችሁ ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ መጽሐፈ ፡ መነኮ ሳት ፡ ደግሞ ፡ አርድእት ፡ የሚባል ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ ሲዋሽ ፡ ለስደምና ፡ ገሞራ ፡ ሐዋርያት ፡ አቃጠሉት ፡ ይላል ፡ አርድእት ፡ ዘንሙስ ፡ ተመልከት ፡ ከሎጥ ፡ እስከ ፤ ዘመን ፡ ሐዋርያት ፡ ፪ሽ ፡ ዓመት ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዘመን እየዋሸ ፡ ግን ፡ መነኰሴዎች ፡ እውነተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ብለው ፡ ለጸሎታቸው ፡ ተቀብለው ፡ ከመ ጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ አምነው ፡ ይዘውት ፡ ይኖራሉ ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፩–፳፭ ፡ ስለምትለው ፡፡

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን በሕግ ፡ ተቀብላ ፡ የምታውቃቸውና ፡ የምትሠ ራባቸው ፡ መጻሕፍተ ፡ መነከሳት ፡ በጉባኤ ፡ የሚነበቡ ፡ የሚተረጐሙ ፤ ፊልክስዩስ ፤ ማር ፡ ይስሐቅ ፤ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ናቸው ፡፡ ፩ኛ ጸሎትም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ ፡ አንትሙሰ ፡ ሶበ ፡ ትጼልዩ ፡ ከመዝ ፡ በሉ ፡ ብሎ ፡ የሠራልን ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡፡ ፪ተኛ ፡ ወአንብቡ ፡ መዝሙረ ፡ ወስብሐተ ፡ ወማኅሌተ ፡ ቅድሳት ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ቈላ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ፡ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ያዘዘን ፤ ፫፻ትም ፡ በአንቀጸ ፡ ጸሎት ፡ የለዩ ልን ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ፲፭ቱ ፡ መኃልየ ፡ ነቢያት ፡ ኪዳን ፡ ሊጦን ፡ መስተብቍዕ ፡ ... ፡ ለሙታን ፡ የሚጸለይ ፡ ግንዘት ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ውዳሴ ፡ ማርያምና ፡ መልካ ፡ መልኮች ፤ ናቸው ፡ እንጂ ይህን ፡ አንተ ፡ የምትለውን ፡ መጽሐፍ ፡ በጉባኤ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሚነበብ ፡ የሚተረጐም ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ገድለ ፡ ቅዱሳንና ፡ እንደ ፡ ተአምር ፡ በሐዋርያት ፡ በዓል ፡ ለሕዝብ ፡ የሚነበብ ፡ የሚተረጐም ፡ ባለመሆኑ ፡ በሕግ ፡ የምታውቀውና ፡ በሕግ ፡ የምትጸልይበት ፡ መጽሐፍ ፡ አደለም ፤ በጭራሽ ፡ አታውቀውምና ፡ በግል ፡ ሲጸልይበት ፡ ያየኸውን ፡ ሰው ፡ ጠይቀው ፡ እንጂ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አትወቅስበትም ። ለዚህም ፡ ምስክር ፡ የጠቀስከው ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፩—፳፫ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፤ እግዚአብሔርን ፡ ሲያውቁት ፡ ከዱት ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔርነቱ ፡ ያመሰገኑት ፡ አደሉም ፡ በሳባቸው ፡ ረከሱ ፡ ልቡናቸው ፡ ባለማወቅ ፡ ተሸፈነ ፡ ሊራቀቁ ፡ ሲወዱ ፡ ሰነፉ ፡ የማይጠፋውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ በሰው ፡ መልክ ፡ ምሳሌ ፡ ለወጡ ፡ በወፎችና ፡ በእንስሶች ፡ በተንቀሳቃሾችም ፡ አምሳል ፡ ለወጡ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ ፈቃድ ፡ ለርኵስነት ፤ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ ራሳቸው ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሥጋቸውን ፡ ያጐሳቍሉ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እውነት ፡ በሐሰት ፡ ለውጠው ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ቡሩክ ፡ አምላክ ፡ የሚኾን ፡ ኹሉን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ጣዖት ፡ አምልከዋልና ፡ ፍጥረቶቹ ፡ በሞት ፡ እንስንስ ፡ አሉ ፡ ይላል ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ይህን ፡ የጻፈ ፡ አይሁዳዊና ፡ ዓረማዊ ፡ ፀሕግ ፡ ተጠላልተው ፡ ሲነጋገሩ ፡ አይሁዳዊ ፡ ዓረማዊን ፡ ያንተ ፡ አባት ፡ ለእንጨት ለደንጋይ ፡ ሲሰግድ ፡ የኔ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመልክ ፡ ነበረ ፡ ቢለው ፡ ዓረማዊ ሲመልስ ፡ የኔ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የካደ ፡ ለጣዖት ፡ የሰገደ ፡ መምህር ፡ ባይናረው ፡ መጻሕፍት ፡ ባይጻፉለት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ ስለሰጠ ፡ እግዚአብሔርስ ስነ ፡ ፍጥረትን ፡ በመመርመር ፡ ይታወቅ ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዓረማውያን ፡ በተፈጥሯቸው ፡ አዋቂዎች ፡ ሲኾኑ ፡ ሰንፈው ፡ ጣዖት ፡ አመለኩ ፡ እያለ ፡ ሲተርክ ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አርድእት ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ስለመቀበሏ ፡ የጻፈው ፡ አደለም ።

በእውነቱ ፡ ሲመረምሩትስ ፡ ይህ ፡ ጥቅስ ፡ አውቃለሁ ፡ ስትል ፡ ስትራቀቅ ፡ ለሰነፍክ ፤ የማይጠፋውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በዳንግሌ ፡ በግና ፡ በዶሮ ፡ ደም ፡ ለለወጥክ ፤ በወፎችና ፡ በተቃንሳቃሾች ፡ ምልክት ፡ እንዲመሩ ፡ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈህ ፡ ለሕዝብ ፡ ለምታድል ፡ ላንተ ፡ ቢጠቀስ ፡ በውነት ፡ ያለጥርጥር ፡ ተስማሚህ ፡ ነው ።

፴ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጥፋት ፡ ያደረሰን ፡ በባዕድ ፡ ሕዝብ ፡ መመሬት ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ በባዕድ ፡ ሕዝብ ፡ መመራት ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ አንተ ፡ አባቶችህን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፡ ንቀህ ፡ አቃለህ ፡ በባዕድ ፡ ልማድና ፡ ባህል ፡ እመራለሁ ፡ ባትል ፡ ፈጣሪህ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደ ፡ አርዮስ ፡ ፍጡር ፡ ባላልክም ፡ ቅዱሳንንም ፡ ጣዖታት ፡ ባላልክም ፡ ነበረ ፡ (ገጽ ፴፬ ፡ መሥመር ፡ ፳፯ ፡ ተመልከት) ።

በባዕድ ፡ መሪ ፡ ተመርተህ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ክህደት ፡ ጉድጓድ ፡ የወደቅህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ በባዕድ ፡ ሕዝብ ፡ ከመመራት ፡ ነፃ ፡ ነን ።

ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ የጠቀስከው ፡ ዘዳግ ፡ ፲፯ ፡ ፲፭ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ የመረጠውን ፡ ከወንድሞችህ ፡ መካከል ፡ በንተ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አንግሥ ፡ ከወንድሞችህ ፡

www.ethiopianorthodox.org



ያልኾነውን ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ የኾነውን ፡ ግን ፡ በበላይህ ፡ ልታነግሥና ፡ ንጉሥ ፡ ልታደርግ ፡ አትችልም ፡ ይላል ።

ኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሯ ፡ በእናቱ ፡ ከንግሥተ ፡ አዜብ ፡ በአባቱ ፡ ከሰሎሞን ፡ ከተወለደ ፡ ከቀዳማዊ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ሳይቋረጥ ፡ የወረደ ፡ ወገኗን ፡ ታነግሣለች ፡ እንጂ ፡ መቸም ፡ ቢኾን ፡ ባዕድ ፡ አንግሣ ፡ አታውቅም ፤ ዛሬም ፡ ወገኗን ፡ ጠብቂዋን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ አንግሣለች ።

በ፲፰፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዕርሚን ፡ ጣሊያን ፡ በግፈኝነትና ፡ በወራሪነት ፡ ገብታ ፡ እንግሣለሁ ፡ ብትል ፡ በጸሎት ፡ ነዝንዞ ፡ በጥይት ፡ ጠዝጥዞ ፤ በምንሽር ፡ አባውዞ ፡ ድምጥማጧን ፡ እንዳጠፋቻት ፡ ስታውቅ ከኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ማንኛው ፡ ንጉሥ ፡ ባዕድ መስሎ ፡ ታየህና ፡ ጠቀስከው ። ይህ ፡ አጠቃቀስህ ፡ ሳታውቀው ፡ ከታላቁ ፡ ጉድጓድ ፡ ከመንግሥት ፡ ፖለቲካ ፡ ውስጥ ፡ ወርውሮ ፡ ጥሎሃልና ፡ የመንግሥት ፡ ፖለቲካ ፡ ተጠባባቂዎች ፡ የተከታተሉህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወዮልህ ።

፴፩ ከዚህም ፡ ቀጥለህ፡ ለምንት ፡ ተሐውሪ ፡ በፍኖተ ፡ ግብጽ ፡ ከመ ፡ ትስተዪ ፡ ማየ ፡ ሕሙገ ፡ ኤር ፪ ፡ ፲፰ ። ፪ተኛ ኢሳ ፡ ፴፩ ፡ ፩-፫ ፡ ምስር ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አምላክ ፡ አይደለም ። ፫ተኛም ፡ ሕዝ ፡ ፳፯ ፳ ወይቤሎሙ ፡ ግድፉ ፡ ኵልክሙ ፡ ርኵሰክሙ ፡ እምቅድመ ፡ አዕይንቲክሙ ፡ ወኢትርኩሱ ፡ በጣዖቶሙ ፡ ለግብጽ ፡ አነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ፡ ወዐለዉኒ ፡ ወዐበዩ ፡ ስሚዖትየ ፡ ወኢገደፉ ፡ ርኵሰ ፡ እምአዕይንቲሆሙ ፡ ወኢኀደጉ ፡ ጣዖቶሙ ፡ ለግብጽ ፡ ወእቤ ፡ እሠውጥ ፡ መዓትየ ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ብለህ ፡ ጠቅሰሃል።

እነዚህን ፡ የጠቀስካቸውን ፡ ጥቅሶች ፡ ኹሉ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ነቢያት ፡ የተናገሯቸው ፡ ግብጽ ፡ ጣዖት ፡ ታመልክ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜና ፡ እስራኤልም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የግብጽን ፡ ጣዖት ፡ ለማምለክ ፡ ይሳቡ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ እስራኤልን ፡ ሲመክሩ ፡ ሲያስተምሩ ፡ የተናገሩት ፡ ነው ። ይህ ፡ ትንቢት ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ሠርቶ ፡ አልፏል ።

ዛሬ ፡ ግብጽ ፡ ስንኳንስ ፡ ሌላውን ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ልትስብ ፡ እሷ ፡ ራሷም ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ስብከት ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላ ፡ አምና ፡ ወልድ ፡ ዋህድ ፡ የምትል ፡ አርቶዶክሳዊት ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ መምለኪተ ፡ ጣዖት ፡ አይደለችም ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ፍሬ ፡ አድርገህ ፡ የያዝከው ፡ ኤኖክንና ፡ ሌሎችንም ፡ አዋልድ ፡ መጻሕፍት ፡ ለመንቀፍ ፡ ነበረ ፤ እንግዲህ ፡ እኒህ ፡ ጥቅሶች ፡ በየትኛው ፡ መንገድ ፡ ሐሳብህን ፡ ሊደግፉልህ ፡ ጠቀስካቸው ፡ ይኾን ፤ ስድብ ፡ አይረባም ፡ አይጠቅምም ፡ እንጂ የሚጠቅም ፡ ቢኾን ፡ እንኳ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ብቻ ፡ መስደብ፡ በበቃህ ፡ ነበረ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስድብ ፡ አልበቃህ ፡ ብሎ ፡ አልፈህ ግብጽንና ፡ ምስርን ፡ መስደብህ ፡ ይገርማል ፡ ይደንቃል ! ።

፴፪ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ለወደ ፡ ፊቱ ፡ ግን ለኢትዮጵያዊ ፤ ሕዝቤ ፡ እንደ ፡ ክህነተ ፡ አሮንና ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘፀ ፡ ፳ ፳፫ ። አንዲት ፡ ምሽት ፡ የለችው ፡ የቤቱን ፡ ሥርዓትና ፡ የልጆቹንም ፡ አቀጣጥ ፡ ያሳመረ ፡ በኑሮውም ፡ ፍጹም ፡ የኾነ ፡ ጳጳስ ፡ ሐሊብ ፡ ነባቤ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ቱስሕት ፡ ብሎ ፡ እንደቃዘዘው ፡ ረዐዩ ፡ ሐሀ ፡ [illegible]ቤክሙ ፡ መርዔቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ተዐቅብዎሙ ፡ ወኢትቅንይዎሙ ፡ በኵርህ ፡ አላ ፡ በጽድቅ ፡ እንዘ ፡ ኢትትኴየሉ ፡ ሕዝበ ፡ አላ ፡ አርአያ ፡ ኩንዎሙ ፡ ለመርዔቱ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፩—፱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንደሚለውም ፡ ለሕዝቡ ፡ ድብላቂ ፡ የሌለው ፡ የክርስቶስን ፡ የጸጋውን ፡ ወንጌል ፡ ተግቶ ፡ የሚመግበውና ፡ የሚገሥጸው ፡ ወደ ፡ ሕይወትም ፡ የሚመራው፡እውነተኛ ፡ እረኛ ፡ ባርያውን ፡ እንዲልክለት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየለመንኩ ፡ እመኝለታለሁ ። ጢሞ ፡ ፫ ፩—፲፫ ። ቲቶ ፩ ፩—፱ ። ጴጥ ፡ ፪ ፩ ፫ ። ስለምትለው ።

እንደ ፡ ክህነተ ፡ አሮን ፡ ያለ ትል ፡ ዘንድማ ፡ አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የተባለ ፡ ክርስቶስ ክህነተ ፡ አሮንን ፡ መሥዋዕት ፡ አሪትን ፡ እንዳሳለፋቸው ፡ አልሰማህምን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስስ ፡ በዕብራውያን ፡ ክታቡ ፡ እመሰ ፡ ይትፌጸም ፡ በክህነቶሙ ፡ ለሌዋውያን ፡ ዘይገብሩ ፡ ለሕዝብ ፡ በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ ለምንት ፡ እንከ ፡ ይትፈቀድ ፡ ይሠየም ፡ ካልእ ፡ ካህን ፡ ዘከመ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሢመቱ ።

እንደ ፡ ታዘዘው ፡ ለሕዝቡ ፡ የሚሠዉት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርቡት ፡ ጸሎት ፡ በሌዋውያን ፡ ክህነት የሚፈጸምማ ፡ ቢኾን ፡ (ማለት) በሌዋውያን ፡ ክህነት ፡ ኃጢአት ፡ የሚሠረይማ ፡ ከኾነ ፤ ሹመቱ ፡ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ካህን ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ባስፈለገ ፡ ነበር፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሕጋቸው ፡ ስታልፍ ፡ ክህነታቸውም ፡ አብራ ፡ የምታልፍ ፡ ስለኾነ ፤ ሹመቱ ፡ እንደ ፡ አሮን ፡ ሹመት ፡ ያለ ፡ ካህን ፡ ይሾማል ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ክህነቱ ፡ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ካህን ፡ ይሾማል ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡ የክህነተ ፡ አሮንን ፡ ማለፍ ፡ አረጋግጦ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አልሰማህምን ። ዕብ ፡ ፯ ፲፩—፲፯ ።

አንተስ ፡ በወንጌል ፡ አሙንኩ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ተማርኩ ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቆየህ ፡ በመኾንህ ፡ መምህር ፡ መኾን ፡ የሚገባህ ፡ ስትኾን ፡ ጆሮህ ፡ ኰመስ ማት ፡ ደንዝዟልና ፡ ሰውነቱ ፡ ያልጠነከረ ፤ ጥርስ ፡ ያላወጣ ፡ ሕፃን ፡ ዳቦ ፤ ቆሎ ፤ ፍትፍት ፤ መረቅ ፤ ከሚሰጡት ፡ ይልቅ ፡ ወተት ፡ ቢግቱት ፡ እንዲወድ ፤ ለአንተም ፡ የፍጹማን ፡ ትምህርት ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ከመንገር ፡ የሕፃናት ፡ ትምርት ፡ ፊደልን ፤ የወጣኒ ፡ ትምርት ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከነን ፡ ሊያስተምሩህ ፡ ይገባል ዕብ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።

ብሉ ፡ ጠጡ ፡ ደም ፡ አፍሱ ፡ ስብ ፡ አጢሱ ፡ የምትል ፡ ሕግ ፡ ምንም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ገና ፡ ብትኾን ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ክህነተ ፡ አሮን ፡ አልፋለች ፡ ተሽራለች ፤ ሊቀ ፡ ካህናታችንም ፡ ዘከመዝኬ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይደልወነ ፡ ጻድቅ ፡ ወየዋህ ፡ ወንጹሕ ፡ ወርኁቅ ፡ እምኵሉ ፡ ኃጢአት ፡ የተባለ ፡ ዕብ ፡ ፯ ፡ ፳፮ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ነው ። ክህነታችንም ፡ ቤት ፡ ሥሩ ፡ ሚስት ፡ አግቡ ፡ ልጅ ፡ ውለዱ ፡ የማትል ፡ ሥጋዊት ፡ ያይደለች ፡ መንፈሳዊት ፡ ወኩኑ ፡ ታቦተ ፡ መንፈሳዌ ፡ ለክህነት ፡ ቅድስት ፡ ወንጽሕት ፡ ከመ ፡ ታቅርቡ ፡ ወታዕርጉ ፡ መሥዋዕተ ፡ መንፈሳዌ ፡ ዘይሰጠወክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእደዊሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተባለች ፡ ንጽሕት ፡ ቅድስት ፡ የኾነች ፡ ክህነት ፡ ናት ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፭ ።

፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ የጠቀስከውም ፡ እሙን ፡ ነገር ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳሰ ፡ ሠናየ ፡ ግብረ ፡ ፈተወ ፡ ብሎ ፡ ዘአሐተ

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ፡ ላንተ ፡ ጳጳስነት ፡ ሊሾም ፡ የወደደ ፡ ያለ ፡ መስሎሃል ። አይደለም ። ይህስ ፡



አምላክ ፡ በባሕርዩ ፡ የሚያደርገውን ፡ ኃይል ፡ ሰዎች ፡ በጸጋ ፡ የሚሠሩት ፡ ስለ ኾነ ፡ አንሰ ፡ እቤ ፡ አማልክት ፡ አንትሙ ፡ ወደቂቀ ፡ ልዑል ፡ ኵልክሙ ፡ እንዳላቸው ፡ መዝ ፡ ፹፪ ፡ ፮ ፡ ዮሴፍም ፡ ለፈርዖን ፡ ቢትወደድ ፡ ኾኖ ፡ በግብፅ ፡ ሲኖር ፡ የንጉሥ ፡ ሥራ ፡ ከሠራ ፡ ብሎ ፡ እንዘ ፡ ንጉሥ በግብጽ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው ። በማስተማር በማጥመቅ በማቍረብ ፡ ጳጳሳትን ፡ ስለመሰሏቸው ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ቅስና ፡ ሊሾም ፡ የወደደ ፡ ሲል ፡ ነው ። ይህንንም ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ አስረዳሃለሁና ፡ አስተውል ።

፩ኛ ፡ የጢሞቴዎስ ፡ ማዓርግ ፡ የጳጳስነት ፡ ማዓርግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ማዓርግ ፡ አይደለም ። ጵጵስና ፡ የሚሾም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጳጳስን ፡ ጳጳስ ፡ የማይሾመው ፡ ስለኾነ ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ።

፪ኛ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በ፰ተኛው ፡ ቍጥር ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ ከማሁ ፡ ንጹሐን ፡ ይላል ። ዲያቆናት ፡ ተከታታይነታቸው ፡ ለቀሳውስት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለጳጳሳት ፡ አይደለምና ፡ ጳጳስ ፡ ያለው ፡ በቁሙ ፡ ጳጳስ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ወከማሁ ፡ ቀሳውስትኒ ፡ ሳይል ፡ አልፎ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ አይልም ፡ ነበረ ።

፫ኛ ፡ አንተ ፡ በጠቀስከው ፡ ለቲቶ ፡ በጻፈው ፡ ክታቡ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ኀደጉከ ፡ ውስተ ፡ ቀርጤስ ፡ ከመ ፡ ትሢም ፡ ቀሲሳነ ፡ ለአህጉር ፡ ዘአሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ፡ ብሎ ፡ ሚስት ፡ ማግባትን ፡ ለቀሳውስት ፡ ሰጥቶ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ወርቱዕ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ ዘአልቦ ፡ ሐሜት ፡ ዘኢያደሉ ፡ ከመ ፡ መጋቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ዘአሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ፡ ባለማለቱ ፡ ይታወቃል ።

፬ኛ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ክታቡ ፡ ፯ ፡ ፴፪ ፡ እስመ ፡ ዘኢያውሰበ ፡ ይሔልዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዘያሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወዘሰ ፡ አውሰበ ፡ ይሔሊ ፡ ንብረተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ በዘያሠምራ ፡ ለብእሲቱ ። እፈቅድ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ይኩን ፡ ከማየ ፡ በማለቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ መኾኑን ፡ አስረድቷል ።

፭ኛ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐሊብ ፡ ነባቤ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ቱስሕት ፡ ማለቱ ፡ መምህራን ፡ እንደሚተረጕሙት ፡ ቱሳሔ ፡ ዘርዕ ፡ የሌለበት ፡ ክርስቶስን ፡ ውደዱ ፡ ማለቱ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ጳጳሳት ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ ለጳጳሳት ፡ ሰጥቶ ፡ የሚተረጐም ፡ ከኾነ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ቱስሕት ፡ ማለት ፡ ለኑሮው ፡ ተጨማሪ ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ የሌለው ፡ ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ መነኵሴ ፡ ማለትን ፡ ያመለክታል ፡ እንጂ ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ ያለው ፡ ማለት ፡ አለመኾኑን ፡ አስተውል ።

እንግዲህ ፡ ለዚህ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ክህነት ፡ ጀማሪ ፡ ከኾኑት ፡ አባቶች ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፤ ቤት ፡ ሠርቶ ፤ ልጅ ፡ ወልዶ ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ነው ? ሐዋርያት ፡ ናቸውን ? ፫፻ናቸውን ? ማነው ፡ ይኾን ! ።

እግዚአብሔር ፡ በትውልዳቸው ፡ በሃይማኖታቸው ፡ በባህላቸው ፡ በኑሯቸው ፡ ድብላቂ ፡ የሌላቸው ፡ ጳጳሳትን ፡ ሾሞላት ፡ ሳለ ፡ ለቤቷ ፡ ለንብረቷ ፡ ለሚስቴ ፡ ለልጆቼ ፡ የሚል ፡ ጳጳስ ፡ እንዲሾምላት ፡ መመኘትህ ፡ ከንቱ ፡ ምኞት ፡ ነው ።

፵፫ እንደ ፡ ልቤም ፡ ጠባቆች ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ በእውቀትና ፡ በማስተዋል ፡ ይጠብቋችኋል ፡ ኤር ፡ ፲፭—፲፯ ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ ዛሬ ፡ ሊፈጸምልን ፡ ኹላችን ፡ ባንድነት ፡ ለቸሩ ፡ አምላካችን ፡ እንለምነው ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ስለምትለው ።

እግዚአብሔር ፡ ካመንበት ፡ ጀምሮ ፡ ይህን ፡ ቸርነቱን ፡ አላጎደለብንም ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ አሳጥቶን ፡ አያውቅም ፡ ለወደፊቱም ፡ እንዳያሳጣን ፡ እንጸልያለን ።

## ልዩ ፡ መግለጫና ፡ ምክር ።

፩ የተኛህ ፡ ንቃ ፡ ከሙታንም ፡ ተነሣ ፡ ክርስቶስ ፡ ያበራልሃል ፡ ብለህ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ። ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ስለ ፡ ጠቀስከው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የተኛህ ፡ ንቃ ፡ ብሎ ፡ አልቀረም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ዘመኑ ፡ ጥቂት ፡ ስለ ኾነ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ተድላ ፡ ደስታ ፡ ኹሉ ፡ ኃላፊ ፡ ጠፊ ፡ ነውና ፡ ይህንን ፡ ዓለም ፡ ንቃችሁ ፤ አቃላችሁ ፡ እንደ ፡ ጠባባት ፡ ደናግል ፡ ኑሩ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሰነፎች ፡ ደናግል ፡ አትኑሩ ፡ ብሎ ።

በሮም ፡ ክታቡም ፡ ከእንቅልፍ ፡ የሚነቁበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ምሰሉት ፡ እንጂ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋችሁን ፡ አታስቡ ፡ ብሎ ፡ ከእንቅልፍ ፡ መንቃት ፡ መጾም ፡ መጸለይ ፡ በጠቅላላው ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ መተው ፡ መኾኑን ፡ መላልሶ ፡ አስረድቷል ።

ኢትዮጵያም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ ከመጻፉ ፡ አስቀድማ ፡ ዓለም ፡ በፍቅረ ፡ ጣዖት ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ በንዋመ ፡ ሐኬት ፡ ሠጥሞ ፡ ሳለ ፡ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀቷ ፡ ነቅታ ፡ ሃይማኖተ ፡ አሪትን ፡ ተቀብላ ፡ ወልድየ ፡ ዘበኵርየ ፡ ለተባለ ፡ ለእስራኤል ፡ ተባባሪ ፡ ኾና ፡ እንደ ፡ ኖረች ፤ ዛሬም ፡ ከአሪት ፡ እንቅልፍ ፡ ነቅታ ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረው ፡ ሱባኤ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አውቃ ፡ በፈቃዷ ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ጠፊ ፡ ነውና ፡ ክርስቶስን ፡ መስላችሁ ፡ ኑሩ ፡ ብላ ፡ ስላስተማረች ፤ ከልጆቿ ፡ ብዙዎቹ ፡ ለወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያውሰ ፡ አልቦ ፡ ኀበ ፡ ያሰምክ ፡ ርእሶ ፡ ያለውን ፡ በመገንዘብ ፡ ማቴ ፡ ፰ ፡ ፲ ፡ ቤት ፡ ሳይሠሩ ፡ ጎመን ፡ ሳይዘሩ ፡ የማቅ ፡ ጉሬንዳ ፡ የፍየል ፡ ሌጦ ፡ ለብሰው ፡ ረሃቡን ፡ ጽሙን ፡ ታግሠው ፡ በየገዳማቱና ፡ በየዋሻው ፡ በየፍርኵታው ፡ ሲዞሩ ፡ ሲንከራተቱ ፡ ይገኛሉ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፴፯ ።

ዓለማውያን ፡ ተብለው ፡ ሚስት ፡ አግብተው ፡ ቤት ፡ ሠርተው ፡ የሚኖሩትም ፡ እግዚአብሔር ፡ የወሰነላቸውን ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ለሥጋዊ ፡ ሥራና ፡ ለሥጋ ፡ መደሰቻ ፡ ብቻ ፡ ሳያደርጉ ፡ ተግባረ ፡ ሥጋ ፡ ከማይዙባቸው ፡ ዕለታት ፡ ተግባረ ፡ ነፍስ ፡ የሚይዙባቸውን ፡ ዕለታት ፡ በዓላትን ። መብል ፡ መጠጥ ፡ ከሚየደርጉባቸው ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋቸውን ፡ ከማፈጸሙባቸው ፡ ዕለታት ፡ በተዘክሮት ፡



እግዚአብሔር ፡ ኾነው ፡ ንጽሕናን ፡ ትሕርምትን ፡ ጾም ፡ ጸሎትን ፡ የሚይዙባቸው ፡ አጽዋማትን ፡ ለይተው ፡ ጉዟቸውን ፡ ወደ ፡ ሕጉ ፡ ወደ ፡ ትእዛዙ ፡ አቅንተው ፡ ሲጓዙ ፡ ይታያሉ ። ከዕንቅልፍ ፡ መንቃት ፡ የክርስቶስን ፡ ብርሃን ፡ ማየት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ፡ የጠቀስከውም ፡ አሮጌው ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ ሔደ ፡ እነሆ ፡ ኹሉ ፡ ታደሰ ፡ ይላል ።

ኢትዮጵያም ፡ አሮጌ ፡ ሥራ ፡ የተባለው ፡ ክርስቶስ ፡ ያሳለፈው ፡ በክህነተ ፡ አሮን ፡ ጸንቶ ፡ ይሠራ ፡ የነበረው ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ስብ ፡ ማጤስ ፡ ዘወትር ፡ ተድላ ፡ ሥጋ ፡ ማድረግ ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝባ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ አፍአዊ ፡ ሰውነታችን ፡ በሕማም ፡ በሞት ፡ ይለወጣል ፡ ውሳጣዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ግን ፡ ኹልጊዜ ፡ በተሐድሶ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ስለ ኾነ ፡ ለጥቂት ፡ ሰዓት ፡ የሚኾን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ መከራ ፡ ክብርን ፡ የክብር ፡ ክብርን ፡ አብዝቶ ፡ የሚያመልጠን ፡ ነውና ፡ መከራ ፡ መቀበልን ፡ አንሰልች ፡ አንሰቀቅ ፤ አንመረር ፤ ምግባር ፤ ትሩፋት ፡ መሥራትን ፡ ቸል ፡ አንበል ፤ ይህ ፡ ምድራዊ ፡ ቤታችን ፡ ቢፈርስ ፡ በሰማይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ያልሠራው ፡ ሕንፃና ፡ ቤት ፡ አለንና ፡ ስለርሱ ፡ የምንደክምለት ፡ ሰማያዊ ፡ ቤታችንን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፡ ብሎ ፡ ያስተማራትን ፡ አጽንታ ፡ ይዛ ። ፪ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፮-፲፰ ፡ ፭ ፡ ፩ ። የምታውቀውን ፡ ዓለም ፡ በማታውቀው ፡ ዓለም ፡ ለውጣ ፤ ከተድላ ፡ ሥጋ ፡ ተድላ ፡ ነፍስን ፡ መርጣ ፤ ከሴት ፡ ርቆ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቆ ፡ ዳባ ፡ ለብሶ ፤ ዳዋ ፡ ጥሶ ፤ ጤዛ ፡ ልሶ ፤ ጸብዐ ፡ አጋንንትን ፡ ግርማ ፡ ሌሊትን ፡ ድምፀ ፡ አራዊትን ፡ ችሎ ፡ ታግሦ ፡ መኖርን ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባረ ፡ ነፍስ ፡ አድርጋ ፡ ትኖራለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ተድላ ፡ ሥጋን ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲመችህ ፡ ዘከመዝኬ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይደልወነ ፡ የተባለ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሊቀ ፡ ካህናትነት ፡ ክደህ ፡ የአሮንን ፡ ሊቀ ፡ ካህናትነት ፡ በመመኘት ፡ እንደ ፡ ዴማስ ፡ ሆዴ ፡ ይምላ ፡ ደረቴ ፡ ይቅላ ፡ ብለህ ፡ ከመኝታ ፡ ተነሥቶ ፡ ፋርኖ ፡ መብላትን ፡ ሻይ ፡ መጠጣትን ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቀን ፡ ሳይለዩ ፡ ተጣጥቆ ፡ ወደ ፡ ሥጋዊ ፡ ሥራ ፡ መሠማራትን ፤ ከጥቂት ፡ ሰዓትም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መብል ፡ መመለስን ፡ ተግባር ፡ አድርገህ ፡ ትገኛለህ ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ዐውደ ፡ ነገሥት ፡ የተባለ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጣዖት ፡ አቁመህ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገንዘቡን ፡ ስትሸልገው ፡ በአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ዐዘቅት ፡ ስታሰርገው ፡ ትገኛለህ ። እንግዲህ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ግብር ፡ የምትኖር ፡ ስትኾን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መጥቀስ ፡ ይገባሃልን ። ወይስ ፡ አሮጌው ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሔደና ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ታደሰ ፡ ዐውቆ ፡ ከእንቅልፍ ፡ መንቃት ፡ ይህ ፡ መሰለህን ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ዛሬ ፡ አንተ ፡ ከምትሠራው ፡ የባሰ ፡ ምን ፡ ይሠሩ ፡ ኖሯል ፡ ይኾን ።

በእውነቱ ፡ አኖኋርህንና ፡ አጠቃቀስክን ፡ አመዛዝኖ ፡ ሲመለከቱት ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ በእንቅልፉ ፡ ሳለ ፡ የሚቃዠውን ፡ ቅዠት ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ ከእንቅልፉ ፡ የነቃ ፡ ሰው ፡ የማነገገረው ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ ይመስላል ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ እናንተ ፡ ያገሬ ፡ ልጆች ፡ ፀወን ፡ ጥግት ፡ የተጠቃችሁ ፡ ስለምን ፡ አልኮል ፡ (አዋልድ ) ትጠጣላችሁ ፡ ሊጎዳችሁ ፡ ላያረካችሁ ፡ ስለምትለው ።

ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ አሁንስ ፡ ትኩር ፡ አድርጌ ፡ ብመለከትህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ማለትንና ፡ አዋልድ ፡ ማለትን ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ያጠናህ ፡ እንጂ ፡ ለይተህ ፡ የምታውቃቸው ፡ አልመሰልከኝም ፡ እነሆ ፡ አንተ ፡ ያልደረስክባቸውና ፡ ያላየሃቸው ፡ ሲቀሩብህ ፡ በቀር ፡ በጥራዝ ፡ ነጠቅነት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ የሰማሃቸው ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ከሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ከቅዳሴም ፡ የምትጠቃቀሳቸው ፡ አላረካህ ፡ ብለው ፡ እኛ ፡ ለምስክርነት ፡ በቂ ፡ አድርገን ፡ የማንጠቅሳቸውን ፡ መልካ ፡ መልኮችንና ፡ ቅኔዎችን ፡ ያዝማሪዎችንና ፡ ያልቃሾችን ፡ ግጥም ፡ ሳይቀር ፡ ለሃይማኖትና ፡ ለምግባር ፡ ምስክር ፡ አድርገህ ፡ ትጠቅሳለህ ።

እኛስ ፡ እንዲሁ ፡ እንዳንተ ፡ ጠቃሚነታቸውን ፡ አውቀን ፡ ለምስክርነት ፡ እንጠቅሳቸዋለን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ እናደርጋቸው ፡ መሰለህ ፡ ይህስ ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ ይሁኑ ፡ ያልክ ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ የነቀፍካቸው ፡ አይመስልም ።

እንግዲህ ፡ አልኮል ፡ መባል ፡ የሚገባቸው ፡ ጠቃሚነታቸውን ፡ አንተም ፡ እኛም ፡ የመሰከርንላቸው ፡ መጻሕፍተ ፡ ሊቃውንት ፡ ሳይሆኑ ፡ የሰውን ፡ አንጎል ፡ እየበጠበጡ ፡ ከጥፋት ፡ የሚያደርሱ ፡ አልኮሎች ፡ ያንተ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸውን ፡ እወቅ ።

፲ ለምን ፡ ገንዘብ ፡ ትሰበስባላችሁ ፡ ለማይጠቅማችሁ ፡ ስለምትለው ።

እነሆ ፡ አንተ ፡ ኑሮህ ፡ ሱቅ ፡ ከፍተህ ፡ በታላቅ ፡ ንግድ ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በጻፍከው ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ ገልጸህልናል ። ይኸው ፡ በሸቀጦችህ ፡ የምታገኘው ፡ ገቢ ፡ አልበቃህ ፡ ብሎ ፡ ክህደት ፤ ስሕተት ፤ ውሸት ፤ ድፍረት ፤ ብቻ ፡ የተመላበትን ፡ ይህን ፡ መጽሐፍና ፡ ዐውደ ፡ ነገሥት ፡ አሳትመህ ፡ የሕዝቡን ፡ ገንዘብ ፡ ያላገባብ ፡ ትሰበስባለህ ፡ ያለሕግ ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ የማይጠቅም ፡ መኾኑን ፡ ከተረዳኸውማ ፡ ቢጠቅምስ ፡ ባይጠቅምስ ፡ ይችን ፡ ትንሺ ፡ መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ ፡ ገዝታችሁ ፡ ከማለት ፡ በብላሺ ፡ ወስዳችሁ ፡ ተመልከቱ ፡ አትልም ፡ ነበረን ፤ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቢኾን ፡ አታላይነትህ ፡ በምንም ፡ አስተዋይ ፡ ዘንድ ፡ ሊሰወር ፡ አልቻለም ።

፲፩ ልምክራችሁ ፡ ይችን ፤ ትንሺ ፡ መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ ፡ ገዝታችሁ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍና ፡ ወደ ፡ የሱስ ፡ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ መግቢያና ፡ መድረሻ ፤ እንድትኾናችሁ ፡ እውነትን ፡ ከሐሰት ፡ እየለያችሁ ፡ ወተት ፡ ወተትዋን ፡ (ጥቅስ ፡ ጥቅሷን ፡) በዚች ፡ ቋጫ ፡ ብትጠጧት ፡ (ብታነቧት) ፡ ከጥግት ፡ ረክታችሁ ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ሥርየት ፡ አግኝታችሁ ፡ አግላኛችሁም ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ካመናችሁ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በሰማይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትነግሣላችሁ ፡ ስለምትለው ።

ኢትዮጵያ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በያንቀጹ ፡ መላልሽ ፡ እንዳስረዳሁኽ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሬ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ጋራ ፡ የተዋወቀች ። በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አስታራቂነት ፤ ሥርየት ፡ አግኝታ ፡ ከሱ ፡ በተገኘ ፡ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ከጽምዐ ፡ ነፍስ ፡ የረካች ። አማላጅነቱም ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞና ፡ ዐርገ ፡ በስብሐት ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ፡



አቡሁ ፡ ማር ፡ ፲፮ ፡ ፳ ። ወእመኒ ፡ አእመርናሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ እምይእዜሰ ፡ አልቦ ፡ ዘነአምሮ ፡ እንከ ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ። ወገብአ ፡ ኀበ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወክብሩ ፡ ዘቀዳሚ ። ከተባለ ፡ ወዲህ ፡ ሳይኾን ፡ ከጽንስ ፡ እስከ ፡ ዕርገት ፡ በሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ብቻ ፡ የተፈጸመ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ከዕርገትም ፡ በኋላ ፡ ከመማለድ ፡ በቀር ፡ አማላጅነት ፡ የሌለበት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ መኾኑን ። እውነትን ፡ ከሐሰት ፡ ለይታ ፡ ጠንቅቃ ፡ ያወቀች ፡ ናት ።

በሰማይ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ መንገሥም ፡ ንዑ ፡ ትልዉኒ ፡ እንዳለው ፡ በሥራ ፡ ካልተከተሉት ፡ እንዳንተ ፡ ከሥራው ፡ ሳይገኙ ፡ በማፈቸል ፡ ብቻ ፡ የማይገኝ ፡ መኾኑን ፡ አውቃ ፡ የሱን ፡ ዐሠር ፡ ተከትላ ፡ ትደክማለች ፡ እንጂ ፡ ያንተን ፡ መጽሐፈ ፡ ክህደትና ፡ መጽሐፈ ፡ ጥንቄላ ፡ አትሻም ።

፲፪ ወተት ፡ ወተትዋን ፡ በዚች ፤ ቋጫ ፡ ብትጠጧት ፡ (ጥቅስ ፡ ጥቅሱዋን ፡ ብታነቧት ፡ ስለምትለው ፡ የሚታለቡትና ፤ ወተት ፡ የሚሰጡት ፡ ላሞች ፤ ምን ፡ ያማሩ ፡ የተወደዱ ፡ ቢኾኑ ፡ ወተቱ ፡ የሚታለብበትን ፡ ዕቃ ፡ አጥቦ ፡ አጥኖ ፡ መክደኛ ፡ አበጅቶ ፡ በጥንቃቄ ፡ አልቦ ፡ ምንም ፡ ቄሻሻ ፡ ሳይወድቅበት ፡ ቢጠጡት ፡ ሕይወት ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ባልታጠበ ፡ ባልታጠነ ፡ ቋጫ ፡ አልቦ ፡ ክፍቱን ፡ አስቀምጦ ፡ ትንኞች ፡ ገብተውበት ፡ ዝንቦች ፡ ተንሳፈውበት ፡ ቄሻሻ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ተጠራቅሞበት ፡ ቢጠጡት ፡ ደዌ ኾኖ ፡ ይገላል ፡ እንጂ ፡ በላሞች ፡ መልካምነት ፡ ብቻ ፡ ሕይወት ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። ስለዚህም ፡ ሊያፈሱት ፡ እንጅ ፡ ሊጠጡት ፡ አይገባም ።

እንዲሁም ፡ ያንተ ፡ ጥቅሶች ፡ ምንም ፡ መጻሕፍቶቹ ፡ ንጹሓን ፡ ክቡራን ፡ ቢኾኑ ፡ ባልተቃና ፡ ነገር ፡ ባልተጣራ ፡ ምሥጢር ፡ ሰብስበህ ፡ ጠቅሰህ ፡ ክህደትን ፡ ውሸትን ፤ ማስመሰልን ፤ ማታለልን ፤ ማጭበርበርን ፡ ስለከሰከስክበት ፡ መርዝ ፡ ስለበጠበጥክበት ፡ ቢመለከቱት ፡ ስቦ ፡ ጐትቶ ፡ እነአርዮስ ፡ በወደቁበት ፡ ጕድጓድ ፡ የሚጥል ፡ በመኾኑ ፡ ስንኳንስ ፡ በገንዘብ ፡ ገዝቶ ፡ ሊመለከቱት ፡ በብላሽ ፡ ወድቆ ፡ ቢገኝም ፡ አምዘግዝጎ ፡ ሊጥሉት ፡ እንጂ ፡ ሊያዩት ፡ አይገባም ።

ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ ይህን ፡ ያንተን ፡ ማታለያ ፡ ገዝቶ ፡ መመልከት ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ለመኾኑ ፡ ምስክር ፡ ሊኾኑኽ ፡ ምሳ ፡ ፰ ፲ ፡ ፴፮ ። ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ዮሐ ፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬ ። ኤፌ ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ ፮ ። ጠቅሰሃል ። ምሳ ፡ ፰ ፲ ፤ ፴፮ ። የጠቀስከው ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ጥበብ ፡ ከሉል ፡ ትበልጣለች ፤ ያማረ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አይተካከላትም ፤ እኔ ፡ ጥበብ ፡ በምክር ፡ ተቀምጫለሁ ፡ የዕውቀትንም ፡ አሳብ ፡ አግኝቻለሁ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ነበርኩ ፤ ነገሥታት ፡ በኔ ፡ ይነግሣሉ ፤ ሹማምትም ፡ የቀናውን ፡ ነገር ፡ በኔ ፡ ያደርጋሉና ፡ ተግሣጼን ፡ ውሰዱ ፡ ብርም ፡ አደለ ፤ ከምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ ይልቅ ፡ እውቀትን ፡ ምረጡ ፡ አለች ፡ ጥበብ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ የዘመንፈስን ፡ ውሸትና ፡ የስድቡን ፡ መጽሐፍ ፡ ገዝታችሁ ፡ ተመልከቱ ፡ አይልም ። ምኑን ፡ ሊያስረዳልህ ፡ ጠቀስከው ፡ ይኾን ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የነበርኩ ፡ ጥበብ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ማለትህ ፡ ይኾን ።

ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፩ ፫ ፡ የጠቀስከውም ፡ እናንተ ፡ የተጠማችሁ ፡ ኹሉ ፡ ወደውኃ ፡ ገንዘብም ፡ የሌላችሁ ፡ ያለብር ፡ ያለዋጋ ፡ ጠጅና ፡ ወተት ፡ ጠጡ ፡ ይላል ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንጂ ፡ ያንተን ፡ መጽሐፈ ፡ ሐሰት ፡ ገዝታችሁ ፡ ተመልከቱ ፡ አይልም ። ይልቁንም ፡ ሰሎሞንና ፡ ኢሳይያስ ፤ አንተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሐሰትህን ፡ በብር ፡ ገዝታችሁ ፡ ተመልከቱ ፡ ስትል ፤ ሰሎሞን ፡ ከብርና ፡ ከምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ እውቀትን ፡ ምረጡ ፡ በማለቱ ፡ ኢሳይያስም ፡ ገንዘብ ፡ የሌላችሁ ፡ ያለዋጋ ፡ ጠጅና ፡ ወተት ፡ ጠጡ ፡ በማለቻቸው ፡ አታላይነትህን ፡ ይመሰክሩብሃል ፡ መፈራረጃ ፡ ይኾኑብሃል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አይረዱህም ።

፲ ዮሐንስ ፡ ፬ ፡ ፳ ፲፬ ፡ የጠቀስከው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ሠማርያ ፡ አልፎ ፡ ሲሔድ ፡ ያዕቆብ ፡ ለልጁ ፡ ለዮሴፍ ፡ በሰጠው ፡ በወይን ፡ ቦታ ፡ አጠገብ ፡ ከምትገኝ ፡ የወኀ ፡ ጉድጓድ ፡ ተቀመጠ ፤ ከዚያም ፡ አንዲት ፡ የሠማርያ ፡ ሴት ፡ ወኀ ፡ ልትቀዳ ፡ መጣች ። ጌታችን ፡ ወኀ ፡ አጠጭኝ ፡ ቢላት ፤ አንተ ፡ አይሁዳዊ ፡ ነህ ፡ እኔ ፡ ሣምራዊት ፡ ነኝ ፡ ከእኔ ፡ ወኀ ፡ እንደምን ፡ ትለምናለህ ፡ አለችው ። ጌታም ፡ መልሶ ፡ አሁን ፡ ወኀ ፡ የሚለምንሽ ፡ ማን ፡ እንደኾነ ፡ ብታውቂ ፡ ኖሮ ፡ ማየ ፡ ሕይወትን ፡ በለመንሺው ፡ ነበረ ። እሱም ፡ በሰጠሽ ፡ ነበረ ፡ አላት ። እሱዋም ፡ ወኀው ፡ ጥልቅ ፡ ጉድጓድ ፡ ነው ፡ መቅጃ ፡ እንኳ ፡ የሬህም ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ ወዴት ፡ አለህ ፡ ብትለው ። ከዚህ ፡ ወኀ ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዳግመኛ ፡ ይጠማል ፡ እኔ ከምሰጠው ፡ ወኀ ፡ የሚጠጣ ፡ ግን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ከሱ ፡ ሲመነጭ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ ዳግመኛ ፡ አይጠማም ፡ አላት ። እሱዋም ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳል ጠማና ፡ ወኀ ፡ ለመቅዳት ፡ ወደዚህ ፡ ጉድጓድ ፡ እንዳልመጣ ፡ ከዚያ ፡ ወኀ ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ፡ እያለ ፡ ይተርካል ። ምሥጢሩም ፡ በኔ ፡ ያመነ ፡ ልጅነትን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ልጅነትንም ፡ ያገኘ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ያገኛል ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ላንተ ፡ እንደመሰለህ ፡ የጉድጓድ ፡ ወኀ አይደለም ። እንግዲህ ፡ ለምን ፡ እንዲጠቅምህ ፡ ጠቀስከው ፡ ይኾን ፡ ወይስ ፡ ያንተን ፡ የማታለያ ፡ መጽሐፍ ፡ ገዝቶ ፡ በመመልከት ፡ ልጅነት ይሰጣል ፡ መስሎህ ፡ ይኾን ።

፲፩ እናንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ያመናችሁ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በርሱ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዳላችሁ ፡ ይህችን ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፍኩላችሁ ፡ ብለህ ፡ ለዚሁ ፡ ምስክር ፡ ፩ ዮሐ ፡ ፭ ፲ ፲፫ ። ስለጠቀስከው ።

ዮሐንስ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍና ፡ ቍጥር ፡ የጻፈው ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያመነ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክርነት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አለ ። በልጁ ፡ የማያምን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለልጁ ፡ የመሰከረውን ፡ ምስክርነት ፡ አላመነምና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሐሰተኛ ፡ አደረገው ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ሰጥቶናልና ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ምስክርነቱ ፡ ይች ፡ ናት ፤ ወልድ ፡ አድሮበት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ አለው ፤ ልጁ ፡ ያላደረበት ፡ ግን ፡ ሕይወት ፡ የለውምና ፡ በልጁ ፡ የምትገኝ ፡ ሕይወት ይች ፡ ናት ። በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ያመናችሁ ፡ እናንተ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዳላችሁ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ጻፍኩላችሁ ፡ ይላል ፡ ኢትዮጵያም ፡ አብ ፡ ለልጁ ፡ የመሰከረለት ፡ ምስክርነት ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ዘአፈቅር ፡ ዘኪያሁ ፡ ሠመርኩ ፡ ወለቱ ፡ ስምዕዎ ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ያለው ፡ [illegible]



ቃል ፡ መኾኑን ፡ አውቃ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ በለው ፡ መሠረት ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋህድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ እያለች ፡ አምላክነቱን ፡ ታምናለች ። አንተ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ክደህ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑም ፡ አስቀድሞ ፡ ከዕርገቱም ፡ በኋላ ፡ ቢኾን ፡ በማላጅነት ፡ መድበኸዋል ።

ወለሱ ፡ ስምዕዎ ፡ ያለውንም ፡ ትእዛዝ ፡ ሰምታ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘኢተወልደ ፡ እማይ ፡ ወእመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይበል ፡ በዊዐ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በለው ፡ መሠረት ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፫–፱ ፡ ጥምቀትን ፡ ከሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ጀምራ ፡ ተቀብላለች ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፳፯–፵ ።

፪ተኛ ፡ እመ ፡ ኢበላዕክሙ ፡ ሥጋሁ ፡ ለወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ አልብክሙ ፡ ሕይወት ፡ ላዕሌክሙ ፡ ዘበልዐ ፡ ሥጋየ ፡ ወሰትየ ፡ ደምየ ፡ ቦ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፶፫–፶፬ በለው ፡ መሠረት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የሚሠዋው ፡ መሥዋዕት ፡ አማናዊ ፡ ሥጋው ፡ አማናዊ ፡ ደሙ መኾኑን ፡ አምና ፡ ትቀበላለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ክደህ ፡ ቍርባን ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አማናዊ ፡ ሥጋ ፡ ደም ፡ አይደለም ፡ ትላለህ ።

፫ተኛ ፡ ሑር ፡ ወሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ ፡ በለው ፡ መሠረት ፡ ለምናኔ ፡ ትሸቀዳደማለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ ክደህ ፡ ምናኔን ፡ ትንቃለህ ፡ መናንያንን ፡ ትነቅፋለህ ።

፬ተኛ ፡ ዘኪያክሙ ፡ ተወክፈ ፡ ኪያየ ፡ ተወክፈ ፡ ወዘኪያየ ፡ ተወክፈ ፡ ተወክፎ ፡ ለዘፈነወኒ ፡ በለው ፡ መሠረት ፡ ሐዋርያትን ፡ ፸ ፡ አርድእትን ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚነሡ ፡ መምህራንን ፡ አክብራ ፡ ተቀብላለች ፡ ወደፊትም ፡ ትተበላለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ክደህ ፡ ነቢያትን ፡ ሐዋርያትን ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታትን ፡ ትንቃለህ ፡ ታቃልላለህ ።

፭ተኛ ፡ ዘተወክፈ ፡ ነቢየ በስመ ፡ ነቢይ ፡ ዐስበ ፡ ነቢይ ፡ ይነሥእ ፡ ወዘተወክፈ ፡ ጻድቀ ፡ በስመ ፡ ጻድቅ ፡ ዐስበ ፡ ጻድቅ ፡ ይነሥእ ፡ በለው ፡ መሠረት በነቢያት ፡ በሐዋርያት ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ ስም ፡ ምጽዋት ፡ ትመጸውታለች ፡ ዝክር ፡ ትዘክራለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ክደህ ፡ ዝክርን ፡ ተዝካርን ፡ ትነቅፋለህ ።

ስለዚህ ፡ የክርስቶስን ፡ አምላክነት ፡ እንዲህ ፡ አጣርታ ፡ የምታውቅና ፡ የምታምን ፡ ትእዛዙን ፡ ተጠንቅቃ ፡ የምትጠብቅ ፡ ኢትዮጵያ ። ተዐቀቡ ፡ እምሐሰውያን ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ በልብሰ ፡ አባግዕ ፡ ወእንተ ፡ ውስጦሙሰ ፡ ተኵላት ፡ መሠጥ ፡ ወእምፍሬሆሙ ፡ ተአምርዎሙ ፡ ያለውንም ፡ የምታውቅ ፡ ስለሆነች ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ጉድ ፡ በጉያህ ፡ ደብቀህ ፡ በዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ ተጠግተህ ፡ መርዝህን ፡ ልትነዛበት ፡ በመቃጣትህ ፡ ከመገረም ፡ በቀር ፡ ያንተን ፡ ጽሑፍ ፡ በፍጹም ፡ አትቀበልህም ።

፲፪ እኔ ፡ ግን ፡ በእውነት ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ደንቆሮ ፡ ነኝ ፡ ጥበብ ፡ አልተማርሁም ፡ የቅዱሳንም ፡ እውቀት ፡ የለብኝም ፡ ምሳ ፡ ፴፰ ፡ ፫ ። ፩ ቆሮ ፫ ፡ ፲፰ ፡ ስለምትለው ።

ፊትህን ፡ ጸፍቶ ፡ አፍህን ፡ ከፍቶ ፡ ይህንን ፡ እውነተኛ ፡ ቃል ፡ ያናገረህን ፡ [illegible] ለክ ፡ ኃይልህ ፤ ምን ፡ ይረቅ ፤ ምን ፡ ይደንቅ እያልኩ ፡ እያደነ

www.ethiopianorthodox.org

ቅሁ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አንተ ፡ እንደተናገርከው ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልቃወመውም ፡፡

፲ እኔ ፡ የማላስተውለውን ፡ ነገር ፡ ተናገርኩ ፡ ይህንንም ፡ አለመዋቂ ፡ ግሩም ፡ ነው ፡ ኢዮ ፡ ፵፪ ፡ ፫ ፡ ስለምትለው ፡፡

እውነት ፡ ነው ፡ ቀድሞ ፡ የማታስተውለውን ፡ ያልተረዳኸውን ፡ መናገርህ ፡ ኋላም ፡ ያልተረዳኸውንና ፡ የማታስተውለውን ፡ ነገር ፡ መናገርህን ፡ ስታውቅ ፡ ወደ ፡ አስተዋይነት ፡ ልመለስ ፡ ማለት ፡ ጠቃሚ ፡ መኾኑን ፡ አለማወቅህ ፡ ይገርማል ፡፡

ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ አስታውስሃለሁና ፡ እሺ ፡ በለኝ ፡፡ የቅዱሳን ፡ እውቀት ፡ የሌለብህ ፡ ያልተማርክ ፡ ደንቆሮ ፡ የማታስተውል ፡ መኾንህን ፡ እያወቅኸው ፡ እንቢ ፡ ብለህ ፡ በእልክ ፡ ወድቆ ፡ ከማይነሱበት ፡ ገደል ፡ አትግባ ፤ ለሚከተሉህም ፡ ሰዎች ፡ ዕውር ፡ ዕውርን ፡ ቢመራ ፡ ተያይዞ ፡ ገደል ፡ እንደተባለው ፡ የዕውር ፡ መሪ ፡ አትሁንባቸው ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬ ፡፡ ይህነንስ ፡ ትተህ ፡ ከድንቁርና ፡ ነፃ ፡ እንድትወጣ ፡ ተማር ፤ አስተዋይ ፡ እንድትኾን ፡ ከመ ናገር ፡ በፊት ፡ መምህራንን ፡ ጠይቅ ፤ የቅዱሳን ፡ እውቀት ፡ እንዲያድርብህ ፡ ተባሕትዎን ፡ ከምንኵስና ፡ ጾምን ፡ ከቀኖና ፡ ትሕርምትን ፡ ከጸሎት ፡ ሰጊድን ፡ ከቁመት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ ያዝ ፡፡ እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፤ ይኸ ፡ ልጄ ፡ ሞቶ ፡ የነበረው ፡ ዳነ ፤ ጠፍቶ ፡ የነበረው ፡ ተገኘ ፡ ብሎ ፡ ይቀበልሃል ፡ ሉቃ ፡፡ ፲፭ ፡ ፳፫ ፤ ከድንቁርና ፡ ነፃ ፡ ትወጣለህ ፤ አስተዋይ ፡ ትኾናለህ ፤ ቅዱሳን ፡ ከደረሱበት ፡ እውቀት ፡ ትደርሳለህ ፡፡ በጠቅላላው ፡ አንተ ፡ ትድናለህ ፡ እንቢ ፡ ብት ለኝ ፡ ግን ፡ ከፍዳህ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭ ፡ ያዕ ፡ ፭ ፲፱ ፡፡

፲፩ እኔ ፡ በዕድሜ ፡ ታናሽ ፡ ነኝ ፡ ስለምትለው ፡፡

ይህ ፡ የግል ፡ ጉዳይህ ፡ ነው ፡ የሚያገባኝ ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ መልስ ፡ ልሰ ጥበት ፡ አልፈቅድም ፡፡

፲፪ ስለዚህ ፡ ስጋሁ ፡ እውቀቴንም ፡ እገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ፈራሁ ፡ ስለምትለው ፡፡

ባለመማርህና ፡ ደንቆሮ ፡ በመኾንህ ፡ እውቀት ፡ እንደሌለህ ፡ ስታውቀው ፡ መጻሕፍትን ፡ እንዲህ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ አድርገህ ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ ከማስቀየም ፡ እንደ ፡ ፈራህ ፡ ቀርተህ ፡ ቢኾን ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ኖሯል ፡፡

፲፫ ነገራችሁን ፡ ጠበቅሁ ፡ እንዲሁም ፡ ተመለከትኋችሁ ፡ ነገር ግን ፡ ልማድንና ፡ ስንፍናን ፡ የሚገሥጽ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አላገኘሁም ፡ ስለምትለው ፡፡

ነገራችንንስ ፡ ብትጠብቀው ፡ እኛንም ፡ ከገባንበት ፡ ገብተህ ፡ ከወጣንበት ፡ ወጥተህ ፡ ብትመለከተን ፡ ኖሮ ፡ ልማድንና ፡ ስንፍናን ፡ የሚገሥጹ ፡ መምህራ ንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍትንም ፡ ባገኘህ ፡ ነበረ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እውቀትህ ፡ እንዳ ይ ስፋፋ ፡ በጭሩ ፡ ወስነኸዋልና ፡ ልታገኝ ፡ አትችልም ፡፡

፲፬ ነገር ፡ ሞልቻለሁና ፡ እናገራለሁ ፡ ጥቂትም ፡ እተነፍሳለሁ ፡ ከንፈሬንም ፡ ገልጬ ፡ እመልሳለሁ ፡ ስለምትለው ፡፡

ነገር ፡ ክፉም ፡ በጎም ፡ ቢኾን ፡ ከሕሊና ፡ እየመነጨ ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ መምላቱ ፡ የማይካድ ፡ ነው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አስተዋይ ፡ ሰ[illegible]



ውን ፡ አስቀርቶ ፡ በጎውን ፤ አስቀያሚውን ፡ ትቶ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፤ መርጦ ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ያሰበውን ፡ ኹሉ ፡ አይናገርም ፡፡ ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፵፭ ፡፡

አንተም ፡ እንደዚሁ ፡ ማድረግ ፡ ይገባህ ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይኸ ናል ድንቁርናህን ፤ አስተዋይ ፡ አለመኾንህን ፡ አንተ ፡ አስቀድመህ ፡ ተናግረኸዋ ልና ፡ አይፈረድብህም ፡፡

፲፭ ነገር ፡ ግን ፡ በቁልምጫ ፡ መናገር ፡ አላውቅም ፡ ያለዚያስ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ከሕይወቴ ፡ ፈጥኖ ፡ ይቈ ርጠኛል ፡ ኢዮ ፡ ፴፪ ፡ ፩ – ፳፩ ፡፡ ለሰው ፡ (ዓለምን ፡) ደስ ፤ የሚያሰኝ ፡ መናገርን ፡ ከፈለግሁ ፡ ግን ፡ የክርስቶስ ፡ ባርያ ፡ ባልኾንኩኝም ፡ ነበረ ፡ ገላ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ስለምትለው ፡፡

የዚህን ፡ መልስ ፡ ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይን ፡ በጠቀስክበት ፡ አንቀጽ ፡ በገጽ ፡ ፳፫ ፡ በቍ ፡ ፴፫ ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ ጠቅሼ ፡ ጽሑፍህ ፡ ኹሉ ፡ በሀብትና ፡ በመዓርግ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የታየህን ፡ በመለማመጥ ፡ በመሽቈጥቈጥ ፡ መኾኑን ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌል ሃለሁና ፡ ያነን ፡ ተመልከት ፡፡

፲፮ በክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ አላፍርም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ኃይል ፡ ለሚያምን ፡ ኹሉ ፡ መድኃኒት ፡ ነውና ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ፡፡ ፩ ቆሮ ፡ ፲፰ ፡ ስለምትለው ፡፡

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ኢየኀፍር ፡ ምህሮ ፡ ወንጌሉ ፡ ቢል ፡ በረኀብ ፡ በጽምዕ ፡ እየተንገላታ ፡ በዱላ ፤ እየተመታ ፡ እየታሠረ ፡ እየተፈታ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አይነት ፡ ፈተና ፡ እየተቀበለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ እየተደላደለ ፡ እየተቀማጠለ ፡ አይ ደለምና ፡ ከሥራው ፡ ገብቶ ፡ ሳይገኙ ፡ ሌላ ፡ የሠራውን ፡ እየጠቀሱ ፡ ማፈቸል ፡ አይገባምና ፡ ተው ፡፡

፲፯ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ክስው ፡ ስሕተት ፡ ከብረት ፡ ዝገት ፡ አይታጣምና ፡ በተሳሳትኩት ፡ ይቅርታ ፡ እን ድታደርጉልኝ ፡ እለምናችኋለሁ ፡ መዝ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ፡ ስለምትለው ፡፡

መሳሳትህን ፡ አውቀኸው ፡ በእውነቱ ፡ ይቅርታ ፡ የምትለምን ፡ ከኾነ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበልህ ፡፡

## የሃይማኖት ፡ ወይም ፡ የእምነት ፡ ትርጓሜ ፡ ፡፡

### ምዕራፍ ፡ ፩ ፡፡

፩ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ባንድ ፡ አምላክ ፡ ፫ ፡ አካላት ፡ በ፫ት ፡ አካላትም ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ መኖሩን ፡ አምነን ፡ እንናገራለን ፡፡

፪ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ አምነህ ፡ የምትሔድበት ፡ መንገድ ፡ ሒደህም ፤ በእርግጥ ፡ የምትገባበት ፡ ሀገር ፡ ወይም ፡ ሕያው ፡ መኖርያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ወይም ፡ ገና ፡ ያልታየውን ፡ መንግሥት ፡ ስማያት ፡ በዓይነ ፡ ልቡና ፡ አይቶ ፡ በእደ ፡ ሕሊና ፡ በተስፋ ፡ ጨብጦ ፡ መያዝ ፡፡ ወይም ፡ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ አምላክህን ፡ ኋላም ፡ እግዚአብሔር ፡ አባትህ ፡ የወለደልህን ፡ አዳማዊ ፡ ወንድምህን ፡ እንደ ፡ ነፍስህ ፡ መውደድ ፡ ፍቅር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ማቴ ፡ ፳ ፡ ፱ ፡ ፵፫ ፵፰ ፡ ፳፪ ፡ ፴፯ – ፵ ፡፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፱–፳፳ ፡፡ [illegible] ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ፡ ስለጠቀስካቸው ፡ ጥቅሶች ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

መጻሕፍት ፡ በያንቀጹ ፡ የሃይማኖትንና ፡ የምግባርን ስልት ፡ ስልታቸውን ለይተው ፡ ጽፈውልናል ፤ ይልቁንም ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ያዘባ ቅኸው ፡ ሃይማኖት ፤ ተስፋ ፤ ፍቅር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መኾናቸውን ፤ ወይእዜሰ እሉ ፡ ፫ቱ ፡ ዘይነብሩ ፡ እሙንቱ ፡ ሃይማኖት ፤ ወትውክልት ፤ ወተፋቅሮ ፡ ወእም ኵሉ ፡ የዐቢ ፡ ተፋቅሮ ፡ ብሎ ፡ ለይቶ ፡ ለይቶ ፡ ጽፎልን ፡ ነበረ ። አንተ ፡ ግን በሃይማኖትና ፡ በምግባር ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ እንኳ ፡ ለይተህ ፡ ሳታ ውቅ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በሃይማኖት ፡ የተመሠረተውን ፡ በምግባር ፡ የታነጸውን በትሩፋት ፡ የተጌጸውን ፡ የኢትዮጵያን ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ላስተምር ፡ በማለትህ እኛ ተገረምኩ ፡ የሃይማኖትንና ፡ የምግባርን ፡ ስልት ፡ ስልታቸውን ፡ ለይቼ ፡ አሳይሃለሁና በማስተዋል ፡ ኾነህ ፡ ተመልከት ።

(ሀ) ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ብለህ ፡ የጻ ፍከው ፡ እርግጥ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ዘይነብሩ ፫ቱ ፡ ካላቸው ፡ አንዱ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ፡ ሃይማኖት ፤ ተስፋ ፡ ለሚያ ደርጋት ፡ የተረዳች ፡ የታመነች ፡ ናት ፡ ይላልና ፡ ስለሃይማኖት ፡ ቢጠቀስ ፡ መልካም ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ በሃይማኖትና ፡ በተስፋ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩ ነት ፡ ገልጦ ፡ እንዳስረዳህ ፡ አስተውል ።

(ለ) ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ አምነህ ፡ የምትሔድበት ፡ መንገድ ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለምትለው ።

አምኖ ፡ የሚሔዱበት ፡ መንገድ ፡ ጌታ ፡ ተጠምቆ ፡ ዕለቱን ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ገዳም ፡ ሔዶ ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ጾመና ፡ የትሩፋትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ እንዳስተማረን ፡ እኛም ፡ ካመን ፡ ከተጠመቅን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጾም ፡ ወደ ፡ ጸሎት ወደ ፡ ቀዊም ፡ ወደ ፡ ሰጊድ ፤ በጠቅላላው ፡ ወደ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትሩፋት ፡ መሠማራት ነው ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ አምነህ ፡ የምትሔድበት ፡ መንገድ ፡ ማለት ፡ ነው ያልከው ፡ የተሰሳተ ፡ ንግግር ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፱ ፡ የጠቀስከው ፡ ብፁዓን ገባርያነ ፡ ሰላም ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰመዩ ። እነሱ ፡ የእግ ዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉና ፡ ሰውን ፡ ከሰው ፡ የሚያስታርቁ ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ናቸው ፡ ይላል ። ወደላይም ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ በሚገኙት ፡ መሥመሮች ፡ ከብ ዕል ፡ ከእውቀት ፡ ነዳያን ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ብሎ ፡ ትሕትናን ፤ ዛሬ ፡ የሚያለቅሱ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው , ብሎ ውኂዘ ፡ አንብዕን ፤ ስለጽድቅ ፡ ብለው ፡ የሚራቡ ፡ የሚጠሙ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ጾምን ፤ ለሰው ፡ የሚያዝኑ ፡ የሚራሩ ፡ ንዑዳን ፡ ክቡ ራን ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ምጽዋትን ፤ ስለጽድቅ ፡ ብለው ፡ የሚሰደዱ ፡ ንዑዳን ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ምናኔን ፡ አስተምሮናል ። ይህ ፡ አንቀጸ ፡ ምግባር ፡ ነው እንጂ ፡ አንቀጸ ፡ አሚን ፡ አደለም ፤ አምኖ ፡ የሚሔዱበት ፡ መንገድ ፡ በጎ ፡ ምግ ባር ፡ መኾኑን ፡ ለይተህ ፡ አውቀህ ፡ ይህን ፡ ጥቅስ ፡ ብትጠቅስለት ፡ ተስማሚ ፡ ነው ።

(ሐ) ሒደህ ፡ በእርግጥ ፡ የምትገባበት ፡ ሀገር ፡ ወይም ፡ ሕያው ፡ መኖሪያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ያልከውም እንዲሁ ፡ የተሳሳተ ፡ ንግግር ፡ ነው ።



ከላይ ፡ እንደ ፡ ነገርኩህ ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ ከላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ምግባ ራት ፡ መንገድ ፡ አድርገን ፡ ብንጓዝ ፡ የምንገባበት ፡ ሀገራችን ፡ ሕያው ፡ መኖሪያ ችን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ራሱ ፡ ሃይማ ኖት ፡ አደለም ።

(መ) ወይም ፡ ገና ፡ ያልታየውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በዓይን ፡ ልቡና ፡ አይቶ ፡ በእደ ፡ ሕሊና ፡ በተስፋ ጨብጦ ፡ መያዝም ፡ ትምጻእ ፡ መንግሥትከ ፡ እያልን ፡ የምንጠባበቀው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ካላቸው ፡ አንዱ ፡ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይባላል እንጂ ፡ ሃይማኖት ፡ አይባልም ።

ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፬—፳፭ ፡ የጠቀስከውም ፡ የሚታየውን ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፡ ተስፋ አይባልም ፡ የሚያየውንማ ፡ እንደምን ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ ደጅ ፡ ይጠናዋል ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተስፋ ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ አይናገርም ።

፪ ቆሮ ፡ ፬ ፲፰ ፡ የጠቀስከውም ፡ የሚታይ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ጠፊ ፡ ነው ፡ የማትታይ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ የማታልፍ ፡ ቀዋሚ ናትና ፡ የማትታይ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፡ እንጂ ፡ የሚታይ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ተስፋ ፡ አናደርገውም ፡ ብሎ ፡ ስለተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይና ገራል ፡ እንጂ ፡ ስለሃይማኖት ፡ አይናገርምና ፡ ለይተህ ፡ ስለተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ ያት ፡ ብትጠቅሰው ፡ መልካም ፡ ነው ።

(ሠ) ወይም ፡ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ አምላክህን ፡ ኋላም ፡ እግዚአብሔር ፡ አባትህ ፡ የወለደልህ ፡ አዳማዊ ፡ ወን ድምህን ፡ እንደ ፡ ነፍስህ ፡ መውደድ ፡ ማፍቀር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ያልከውም ።

ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፤ ፍቅረ ፡ ቢጽ ፡ ይባላሉ ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖት ፡ አይባሉም ። አፍቅሮ ፡ ለእግዚአሔር ፡ አምላክከ ፡ በኵሉ ፡ ልብከ ፡ በሚለው ፡ ትእዛዝና ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ፡ ባለው ፡ ትእዛዝ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ አስተውል ። ኢታምልክ ፡ ለጣዖት ፡ አልሰግድም ፡ በሰማይም ፡ በምድርም ፡ ፈጣሪ ፤መግደል ፡ ማዳን ፡ የሚቻለው ፡ አምላክ ፤ እግዚአብሔር ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በማመን ፡ ይፈጸማል ። ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሖር ፡ ወሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ሰውነትን ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ አሳልሮ ፡ እስከ መስጠት ፡ ደርሶ ፡ በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናዶ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ኹሉ ፡ በፍጹም ፡ ቆርጦ ፡ በመጣል ፡ ይፈጸማል ፡ እንጂ ፡ በቃል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አምላክነት ፡ አውቃለሁ ፡ አምናለሁ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ የሚፈጸም ፡ አደለም ።

ይኸውም ፡ የሰማይ ፡ አባቴን ፡ ፈቃድ ፡ ከሚፈጽም ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ የሚለኝ ፡ ኹሉ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አደለም ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አቤቱ ፡ በስምህ ፡ ትንቢት ፡ ተናግረን ፡ አልነበረምን ፤ በስምህ ፡ ጋኔን ፡ አስወጥተን ፡ አልነበረምን ፤ በስምህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተአምራት ፡ አድርገን ፡ አልነበረምን ፡ ይሉኛል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ ዐመፀኞች ፡ ኹሉ ፡ ከኔ ፡ ራቁ ፡ አላ [illegible] ፡ እላቸዋለሁ ፡ በማለቱ ፡ ይታወቃል ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

አዳማዊ ፡ ወንድምን ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ አድርጎ ፡ መውደድም ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ፡ ተብሎ ፡ የታዘዘ ፡ ከ፲ሩ ፡ ትእዛዛት ፡ አንዱ ፡ ነው ።

(ረ) ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፫–፵፰ ፡ የጠቀስከውም ፡ ከናንተ ፡ አስቀድመው ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዳጃችሁን ፡ ውደዱ ፡ ጠላታችሁን ፡ ጥሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ጠላታችሁን ፡ ውደዱ ፡ እላችኋለሁ ፡ የሰማይ ፡ አባታችሁ ፡ ለጻድቃንም ፡ ለኃጥአንም ፡ ዝናምን ፡ በማዝነም ፡ ፀሐይን ፡ በማውጣት ፡ ፍጹም ፡ እንደ ኾነ ፡ እናንተም ፡ ኹሉን ፡ አስተካክሎ ፡ በመውደድ ፡ ፍጹማን ፡ ኹኑ ፡ ይላል ። እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ዘይነብሩ ፡ ፫ቱ ፡ ካላቸው ፡ አንዱ ፡ ተፋቅሮ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖት ፡ አደለም ።

(ሰ) ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴፯–፵ ፡ የጠቀስከውም ፡ በአሪት ፡ መጀመሪያይቱ ፡ ደገኛይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እሷን ፡ የምትመስላት ፡ ኹለተኛይቱም ፡ ትእዛዝ ፡ ባልንጀራህን ፡ እንደራስህ ፡ አድርገህ ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡ አቆራኝቶ ፡ አነጻጽሮ ፡ ተናግሯል ። እንዲህም ፡ አነጻጽሮ ፡ መጻፉ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በሮም ፡ ክታቡ ፡ ወንድሙን ፡ ከወደደው ፡ አይገለውም ፤ አይሰርቀውም ፤ በሐሰት ፡ አይመክርበትም ፤ ሚስቱንና ፡ ለሱ ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ አይመኝበትምና ፤ ሰው ፡ ወንድሙን ፡ ከወደደ ፡ ሕጉን ፡ ኹሉን ፡ መፈጸሙ ፡ ነው ። ወንድሙን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልምና ፡ የ፲ቱ ፡ ትእዛዛት ፡ ኹሉ ፡ አበጋዛቸው ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንዳስረዳን ፡ አፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከም ፡ ኢታምልክን ፡ ከሚቃወሙ ፡ ዳንግሌ ፡ በግ ፡ ጥቁር ፡ ፍየል ፡ ገብስማ ፡ ዶሮ ፡ ረዱ ፡ ከሚሉ ፡ አንተ ፡ ከጻፍከው ፡ ስሕተት ፡ ኹሉ ፡ የሚጠብቅ ፡ ስለ ኾነ ፡ ነው ።

እነሆ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ሃይማኖት ፤ ተስፋ ፤ ፍቅር ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንደ ኾኑ ፡ ለይተው ፡ ለይተው ፡ ጽፈውልናል ። ሃይማኖትና ፡ ምግባርም ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ተዋህደው ፡ በንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ካልተገኙ ፡ ለየብቻቸው ፡ ከኾኑ ፡ የማይጠቅሙ ፡ ምውታን ፡ መኾናቸውን ፡ ጽፈውልናል ። ይልቁንም ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ ወንድሞቻችን ፤ ሃይማኖት ፡ አለኝ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ የለኝም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ምን ፡ ይረባል ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፤ ሃይማኖቱ ፡ ብቻዋን ፡ ልታድነው ፡ ትችላለችን ፤ በጎ ፡ ምግባር ፡ የሌላት ፡ ሃይማኖት ፡ የሞተች ፡ ናትና ፡ ብቻዋን ፡ ልታድነው ፡ አትችልም ። አምላክ ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ በማመንህ ፡ በጎ ፡ አድርገህ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ካልጨመርክበት ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተስ ፡ አጋንንትም ፡ በግድ ፡ ያምኑበታል ፡ ስሙ ፡ ሲጠራም ፡ ይደነግጣሉ ፡ ዳሩ ፡ ምን ፡ ይኾናል ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ የላቸውምና ፡ አይድኑም ፤ አንተ ፡ ግብዝ ፡ ሃይማኖት ፡ ያለምግባር ፡ የሞተች ፡ እንደ ኾነች ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለህን ፡ ከወደድክስ ፡ የአብርሃም ፡ ሃይማኖቱ ፡ ፍጽምት ፡ ኾና ፡ የታወቀችለት ፡ ልጁን ፡ ይሥሐቅን ፡ ለመሥዋዕትነት ፡ በማቅረቡ ፡ እንደ ኾነ ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ፡ ብሎ ፡ ጽፎልናል ። ያዕ ፡ ፪ ፡ ፲፬–፳፮ ።



አንተ ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ወደ ፡ ምንመስልባቸው ፡ ወደ ፡ ጾም ፡ ወደ ፡ ትሕርምት ፡ ወደ ፡ ሰጊድ ፡ ወደ ፡ ቁመት ፡ መሠማራት ፡ ሲያዳግትህ ፡ ጊዜ ፡ የእምነት ፡ ትርጓሜው ፡ ፍቅር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ምግባርንና ፡ ትሩፋትን ፡ ሠርዘሃቸዋል ። እንዲህማ ፡ ከኾነ ፡ ከሃይማኖተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአፍኣ ፡ ያሉ ፡ አሕዛብም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይፋቀራሉና ፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ አላቸው ፡ ማለት ፡ ነዋ ። ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ ሃይማኖት ፡ ለሚባል ፡ ኹሉ ፡ ዋናው ፡ ፍሬ ፡ ነገሩና ፡ የመንገዱ ፡ ትርጓሜ ፡ ፍቅር ፡ እንደ ኾነ ፡ አንዳንድ ፡ አዝማሪዎችም ፡ በሚከተለው ፡ ግጥም ፡ ገልጸውታል ፡ ብለህ ፡ ለዚህ ፡ ምስክር ፡ በዕርጥቡ ፡ ተጠርበ ፡ ሲደርቅ ፡ የተወላገደ ፡ ሳንቃ ፡ የመሰለ ፡ ያዝማሪ ፡ ግጥም ፡ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ቃል ፡ ትምህርት ።

መዝገበ ፡ ቅዳሴ ፡ ሳታት ።
ድጓ ፡ ዝማሬ ፡ መዋሥዕት ።
ትንሽ ፡ ፍሬ ፡ አጣሁበት ።
የጋላን ፡ ሃይማኖት ፡ ይዤለሁ ።
ወንድሜን ፡ እወዳለሁ ።

ብለህ ፡ ጠቅሰሃል ። ለሃይማኖትህ ፡ ምስክር ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አጥተህ ፡ ለት ፡ ያዝማሪዎችን ፡ ግጥም ፡ የምትጠቅስስ ፡ ከኾንክ ፡ ያማርኛው ፡ ሊቅ ፡ ነጋድራስ ፡ በረናው ። ገሎ ፤ ማስነሣት ፡ ታውቃለህ ። ወልድ ፡ አብነት ፡ አለህ ። ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፴–፲፪ ፡ የሴት ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብለህ ። ወልድ ፡ በራስህ ፡ ተኰራህ ። ዮሐ ፡ ፳፯ ፡ ፴ ፡ አብ ፡ አይበልጥምዎይ ፡ አባትህ ። ተለማኝቱ ፡ እናትህ ። ያሉትን ፡ ምሥጢራዊ ፡ ግጥም ፡ ጠቅሰኸው ፡ ቢኾን ፡ እንዴት ፡ ባማረ ፡ ነበረ ፤ ዳሩ ፡ ምን ፡ ይኾናል ፡ ዕቅምህ ፡ አልፈቀደልህም ። እንግዲህ ፡ ያንተ ፡ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ በንብላው ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ ስለ ኾነ ፡ ምንም ፡ አንተ ፡ ትሰማለህ ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ ባላደርግ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ ጥብቅ ፡ ዐደራ ፡ የጣልኩባቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ይረዱት ፡ ዘንድ ፡ እጽፍላችዋለሁ ።

ሃይማኖት ፡ በዓይን ፡ የማይታይ ፡ በእጅ ፡ የማይዳሰስ ፡ በጆሮ ፡ ብቻ ፡ ሰምቶ ፡ ይህ ፡ ሊደረግ ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ማለትን ፡ ትቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ኹሉ ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ በሕሊና ፡ የሚታመን ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። ለዚኸውም ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፤ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፤ ምሥጢረ ፡ ጥምቀት ፤ ምሥጢረ ፡ ቍርባን ፤ ምሥጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የተባሉ ፡ አምስት ፡ አዕማድ ፡ አሉት ፡

## ፩ኛ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ።

ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ማለት ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ ያለው ፡ መለኮት ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ በነበሩ ፡ ዛሬም ፡ ባሉ ፡ ኋላም ፡ ዓለሙን ፡ አሳልፈው ፡ በሚኖሩ ፡ አብ ፤ ወልድ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በተባሉ ፡ በሦስቱ ፡ አካላት ፡ እንዳለ ፡ መርምሮ ፡ አውቆ ፡ እግዚአብሔር ፡ በስም ፡ በገጽ ፡ በአካል ፡ ሦስት ። በባሕርይ ፡ በህልውና ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፤ ሦስት ፡ ሲኾን ፡ አንድ ፡ መኾኑንም ፡ መጻሕፍት ፡ በያንቀጹ ፡ ነግረውናል ።

፩ኛ ፡ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ግንብ ፡ መሥራት ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ እኒህ ፡ ሰዎች ፡ ቋንቋቸው ፡ አንድ ፡ ስለ ኾነ ፡ ግንብ ፡ ሊሠሩ ፡ ጀመሩ ፡ ግንባቸው ፡ እንዲ

www.ethiopianorthodox.org

ከለከልባቸው ፡ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ንግግር ፡ እንዳይሰማ ፡ በቋንቋ ፡ እንለያያቸው ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ እንውረድ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሏል ፡ ዘፍ ፡ ፲፩ ፡ ፯--፰ ።

አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ አንድነቱን ፤ ኑ ፡ እንውረድ ፡ ብሎ ፡ ሦስትነቱን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አስተውል ።

፪ተኛም ፡ አብርሃም ፡ በዐዐደ ፡ መምሬ ፡ ድንኳኑን ፡ ተክሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገለጠለት ፡ ዐይኑን ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ ቢመለከት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ወደርሱ ፡ ሲመጡ ፡ አየ ። ባያቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበላቸው ፡ ሮጦ ፡ ሔዶ ፡ ሰገደላቸው ፡ አቤቱ ፡ በፊትህስ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ኸንኩ ፡ ባርያህን ፡ እንዳታልፈኝ ፡ እለምንሃለሁ ፤ ጥቂት ፡ ውኀ ፡ ይምጣላችሁ ፤ እግራችሁንም ፡ ታጠቡ ፤ ከዚህ ፡ ችም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ዕረፉ ፤ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ ላምጣላችሁ ፤ ልባችሁንም ፡ ደግፉ ፡ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ትሔዳላችሁ ፡ አላቸው ። ሥላሴም ፡ እንዳልክ ፡ አድርግ ፡ አሉት ፡ ይላል ። ዘፍ ፡ ፲፰ ፩-፯ ።

ከዚህም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ አመ ፡ ከመ ፡ ዮም ፡ እገብእ ፡ ኀቤከ ፡ ወትረክብ ፡ ሣራ ፡ ወልደ ።

የዛሬ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ወዳንተ ፡ እመጣለሁ ፡ ሚስትህ ፡ ሣራም ፡ ልጅ ፡ ትወልዳለች ፡ አለው ፡ ይላል ።

አሁን ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ጌታ ፡ ሦስት ፡ ኸኖ ፡ በመታየቱ ፡ ሦስትነቱን ፤ የዛሬ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ወዳንተ ፡ እመጣለሁ ፡ በማለቱ ፡ አንድነቱን ፡ መስክሯል ።

አብርሃምም ፡ ፫ቱን ፡ አካል ፡ አቤቱ ፡ በፊትህስ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኸነ ፡ ባርያህን ፡ እንድታልፈኝ ፡ እለምንሃለሁ ፡ በማለቱ ፡ አንድነቱን ።
ጥቂት ፡ ውኀ ፡ ይምጣላችሁ ፡ እግራችሁንም ፡ ታጠቡ ፡ ከዚች ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ዕረፉ ፡ በማለቱ ፡ ሦስትነቱን ፡ መስክሯል ።

ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ ተገለጠለት ፡ በማለቱ ፡ አንድነቱን ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ወደርሱ ፡ ሲመጡ ፡ አየ ፡ በማለቱ ፡ ሦስትነታቸውን ፡ መስክሯል ።

የእግዚአብሔር ፤ የአብርሃም ፤ የሙሴ ፡ ምስክርነት ፡ የማይታበል ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ።

፫ተኛም ፡ ኄኖክ ፡ የማያንቀላፉ ፡ ትጉሃን ፡ መላእክት ፡ በጌትነትህ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የመናፍስት ፡ ጌታ ፡ አቤቱ ፡ (ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ) ጽኑዕ ፡ በአምልኮት ፡ ልዩ ፡ እምአማልክተ ፡ ሐሰት ፤ ባዕል ፡ እምንዴት ፤ ንጹሕ ፡ እምኃጢአት ፤ እኵት ፡ በአፈ ፡ ሰብእ ፡ ወመላእክት ፡ ነህ ፡ እያሉ ፡ ያመሰግናሉ ፡ ብሏል ። ፱ ፡ ፴፰ ፡ ይባርኩከ ፤ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ብሎ ፡ አንድነቱን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ ሦስትነቱን ፡ እንደ ፡ መሰከረ ፡ አስተውል ።

ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፩-፱ ። መዝ ፡ ፳ ፯ ፰ ። ፴፫ ፡ ፯ ፡ ጥልቅ ፡ በኸነ ፡ አስተያየት ፡ ተመልከት ። ይህንም ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ ባላቸው ፡ በነፍስ ፡ በቀላይ ፡ በእሳት ፡ በፀሐይ ፡ ... በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋህድ ፡ በመለኮት ፡ ዘይሜለስ ፡ በአካላት ፡ ወኩነታት ።



በመለኮት ፡ አንድ ፡ በአካላትና ፡ በኩነታት ፡ ሦስት ፡ በሚኾን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እናምናለን ፡ ብለው ፡ ነግረውናል ።

እንዲህ ፡ ግን ፡ ስለኾነ ፡ የአካላት ፡ ሦስትነትና የኩነታት ፡ ሦስትነት ፡ አንድ ፡ አይደለም ። አካላት ፡ መጠቅለልና ፡ መቀላቀል ፡ ሳይኖርባቸው ። በተከፍሎ ፤ በተፈልጦ ፤ በፍጹም ፡ ገጽ ፤ በፍጹም ፡ መልክዕ ፤ በየራሳቸው ፡ የቆሙ ፡ ሲኾኑ ፤ ኩነታት ፡ ተከፍሎ ፡ ተፈልጦ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ በተዋህዶ ፤ በተጋብኦ ፤ ባንድነት ፤ አካላትን ፡ በህልውና ፡ እያገናዘቡ ፡ ባንድ ፡ መለኮት ፡ የነበሩ ፤ ያሉ ፤ የሚኖሩ ፡ ናቸው ።

እሊኸውም ፡ ከዊነ ፡ ልብ ፡ ከዊነ ፡ ቃል ፡ ከዊነ ፡ እስትንፋስ ፤ ናቸው ።

ከዊነ ፡ ልብ ፡ በአብ ፡ መሠረትነት ፡ ለራሱ ፡ ለባዊ ፡ ኸኖ ፡ ለወልድና ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እውቀት ፡ መኾን ፡ ነው ።

ከዊነ ፡ ቃል ፡ በአብ ፡ መሠረትነት ፡ ለራሱ ፡ ነባቢ ፡ ኸኖ ፡ ለአብ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንባብ ፡ መኾን ፡ ነው ።

ከዊነ ፡ እስትንፋስ ፡ በአብ ፡ መሠረትነት ፡ ለራሱ ፡ ሕያው ፡ ኸኖ ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ሕይወት ፡ መኾን ፡ ነው ። ሦስት ፡ ኩነታት ፡ ያልናቸው ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

የሊህም ፡ የሦስቱ ፡ ኩነታት ፡ ምሥጢር ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርዓያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ የነፍስን ፡ የአካሏን ፡ አንድነት ፡ ለሥላሴ ፡ ባሕርይና ፡ መለኮት ፤ የባሕርይዋን ፡ ከዊን ፡ ለሥላሴ ፡ አካል ፡ ሰጥቶ ፡ ቢመረምሩት ፡ ይታወቃል ።

ነፍስ ፡ በአካሏ ፡ ከሦስት ፡ የማትከፈል ፡ አንዲት ፡ ስትኾን ፡ በባሕርይዋ ፡ እንደ ፡ ሥላሴ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አላት ፤ ይኸውም ፡ ከዊነ ፡ ልብ ፤ ከዊነ ፡ ቃል ፤ ከዊነ ፡ እስትንፋስ ፡ ነው ። በባሕርይዋ ፡ ያለ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አካሏን ፡ ከሦስት ፡ እንዳይከፍለው ፡ በሥላሴ ፡ ባሕርይ ፡ ያለ ሦስት ፡ ከዊንም ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴን ፡ መለኮተ ፡ ሥላሴን ፡ ከሦስት ፡ አይከፍለውም ።

በባሕርይዋ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ ያላት ፡ ነፍስ ፡ አንዲት ፡ ብትባል ፡ እንጂ ፡ ሦስት ፡ እንዳትባል ፤ ሦስት ፡ ከዊን ያላት ፡ መለኮተ ፡ ሥላሴ ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴም ፡ አንዲት ፡ ብትባል ፡ እንጂ ፡ ሦስት ፡ አትባልም ።

ለፀሐይም ፡ እንደዚሁ ፡ ክበብ ፤ ብርሃን ፤ ዋዕይ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፡ በክበቡ ፡ አብ ፤ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፤ በዋዕዩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላሉ ፤ ሦስት ፡ ከዊን ፡ ያለው ፡ ፀሐይ አንድ ፡ ፀሐይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ሦስት ፡ ፀሐይ ፡ እንዳይባል ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ ያላት ፡ ባሕርየ ሥላሴ ፡ መለኮተ ፡ ሥላሴም ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ሦስት ፡ አትባልም ።

የእሳትም ፡ ምሳሌነት ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፬ተኛም ፡ ቀላይ ፡ ለቀላይ ፡ ስፍሐት ፡ ርጥበት ፤ ሑከት ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፡ በስፍሐቱ ፡ አብ ፤ በርጥበቱ ፡ ወልድ ፡ በሁከቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላሉ ፡ ይህ ፡ ሦስት

www.ethiopianorthodox.org

ከዊን ፡ ያለው ፡ ቀላይ ፡ አንድ ፡ ቀላይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ሦስት ፡ ቀላይ ፡ እንዳይባል ሦስት ፡ ከዊን ፡ ያላት ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴ ፡ መለኮት ፡ ሥላሴም ፡ አንዲት ፡ ብትባል እንጂ ፡ ሦስት ፡ አትባልም ።

የነፍስ ፡ የልብነቷ ፡ ከዊን ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ ወደ ፡ መኾን ፤ የቃልነቷ ከዊን ፡ ልብ ፡ እስትንፋስ ፡ ወደ ፡ መኾን የእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ልብ ፡ ቃል ወደ ፡ መኾን ፡ እንዳይለወጥ ፡ የመለኮት ፡ ሥላሴም ፡ የልብነቱ ፡ ከዊን ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ ወደ ፡ መኾን ፤ የቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ልብ ፡ እስትንፋስ ፡ ወደ ፡ መኾን ፤ የእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ ልብ ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ አይለወጥም ።

የቀሩት ፡ ምሳሌዎች ፡ ከዊንም ፡ እንደዚሁ ፡ አይለዋወጥም ።
ከምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ስትገባ ፡ እንደትተገር ፡ እኒህን ፡ ምሳሌዎች ፡ ጠንቅቀህ ፡ መርምርና ፡ ተረዳ ። እኒህ ፡ ምሳሌዎች ፡ የሚገኙባቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ዘፍጥ ፡ ፩ ፳፮ ፡ ቀሌምንጦስ ። የ፫፻ ፡ ቅዳሴ ፡ ግሩም ። ያባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ። አረጋዊ መንፈሳዊ ።

ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በቂጥቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ኹለተኛ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ።

በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ አብ ፡ መለኮት ፡ ወልድ ፡ መለኮት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ መለኮት ፡ ፩ዱ ፡ መለኮት ፡ ብለን ፡ ካመንባቸው ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ከአብ ፡ ያለእናት ፡ የተወለደው ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ማርያም ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ከኹለት ፡ አካል አንድ ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፡ ብለን ፡ እናምናለን ። ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ እንዲል ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፲፬ ።

መለኮት ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ስንልም ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ አልኾኑም በማለታችን ፡ መለኮት ፡ በተከፍሎ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ የምንል ፡ አደለንም ። ዘላዕሌሁ ኀደረ ፡ ኵሉ ፡ መለኮቱ ፡ በሥጋ ፡ ሰብእ ፡ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደጻፈልን ። ቈላስ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ፍጹም ፡ መለኮት ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ በከፊል ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ አንልም ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ካላችሁ ፡ በኋላ ፍጹም ፡ መለኮት ፤ ሰው ፤ ኾነ ፡ ብላችሁ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ አልኾኑም ካላችሁ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመለኮትነት ፡ በአፍአ ፡ ናቸው ፡ ወይም ፡ መለኮት ፡ እንደ ፡ አካላት ፡ ከሦስት ፡ ይከፈላል ፡ ያሰኝባችኋል ፡ የሚለን ፡ ሰው ፡ ቢኖር ሊቃውንት ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ የመሰሉለትን ፡ ምሳሌዎች ፡ ያስተውል ።

## ፩ኛ ፡ ነፍስ ።

በአካሏ ፡ አንድ ፡ ስትኾን ፡ በከዊን ፡ ሦስት ፡ የምትኾን ፡ ነፍስ ፤ በልብነቷ ከዊን ፡ በእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፤ በተለየ ፡ በቃልነቷ ፡ ከዊን ፡ ብቻ ፡ ከሥጋ ምላስ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዳ ፡ ንባብን ፡ በሰጠች ፡ ድምፅን ፡ ባሰማች ፡ ጊዜ ፡ አካሏ ፡ ከሦስት ፡ እንዳይከፈል ፤ መለኮትም ፡ ከሦስት ፡ የሚከፈል ፡ አይደለም ፡ የልብነቷ ፡ ከዊንና የእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ነፍስ ፡ ከመባል ፡ ከነፍስነት ፡ በአፍአ ፡ ናቸው ፡ እንዳይባሉ



በልብነት ፡ ከዊንና ፡ በእስትንፋስነት ፡ ከዊን ፡ ያሉ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መለኮት ፡ ከመባል ፡ ከመለኮትነት ፡ በአፍአ ፡ ናቸው ፡ አይባሉም ፤ ከመለኮትነት ፡ በአፍአ ፡ አይደሉም ።

## ፪ተኛ ፡ ፀሐይ

ፀሐይ ፡ በአካሉ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ። ይኸውም ፡ ክበብ ፤ ብርሃን ፤ ዋዕይ ፤ መኾን ፡ ነው ፡ ፀሐይ ፡ በክበብነቱና ፡ በዋዕይነቱ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በብርሃንነቱ ፡ ከዊን ፡ ብቻ ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዐይንን ፡ ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ እንዲያይ ፡ ያደርገዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክበብና ፡ ዋዕይ ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ስላልተዋሐዱ ፡ ከፀሐይነት ፡ በአፍዓ ፡ ናቸው ፡ አይባሉም ፡ ወይም ፡ ፀሐይ ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለ ፡ አይባልም ። እንደዚኸውም ፡ መለኮት ፡ በብርሃንነቱ ፡ ከዊን ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡ ስንል ፡ በክበብነትና ፡ በዋዕይነት ፡ ከዊን ፡ የተመሰሉ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አልተዋሐዱም ፡ ብንል ፡ መለኮት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለ ፡ ወይም ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመለኮትነት ፡ በአፍአ ፡ ናቸው ፡ አያሰኝብንም ።

## ፫ተኛ ፡ እሳት ።

እሳት ፡ በአካሉ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ። ይኸውም ፡ ፍሕም ፤ ብርሃን ፤ ዋዕይ ፤ መኾን ፡ ነው ። እሳት ፡ በፍሕምነቱና ፡ በዋዕይነቱ ፡ ሳይኾን ፡ በብርሃንነቱ ፡ ከዊን ፡ ብቻ ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ሲዋሐድ ፡ ፍሕምና ፡ ዋዕይ ፡ ባለመዋሐዳቸው ፡ ከእሳትነት ፡ በአፍአ ፡ ናቸው ፡ እንዳይባሉ ፡ ወይም ፡ እሳት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለ ፡ እንዳይባል ፤ መለኮትም ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ብቻ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ብንል ፡ በልብነትና ፡ በእስትንፋስነት ፡ ከዊን ፡ ያሉ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመለኮትነት ፡ በአፍአ ፡ ናቸው ፡ አያሰኝም ፡ ወይም ፡ መለኮት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለ ፡ አያሰኝብንም ።

## ፬ተኛ ፡ ቀላይ ።

ቀላይ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፤ ይኸውም ፡ ስፍሐት ፡ ርጥበት ፡ ሁከት ፤ መኾን ፡ ነው ። ሰው ፡ ከባሕር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ቀላይ ፡ በስፍሐትና ፡ በሁከት ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በርጥበት ፡ ከዊን ፡ ብቻ ፡ ከአካል ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ ስፍሐትና ፡ ሁከት ፡ ባለመገኘታቸው ፡ ከቀላይነት ፡ በአፍዓ ፡ ናቸው ፡ እንዳይባሉ ፤ ወይም ፡ ቀላይ ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለ ፡ እንዳይባል ፡ መለኮትም ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ብቻ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ብለን ፡ በልብነቱና ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ አልተዋሐደም ፡ ብንል ፡ መለኮት ፡ ከሦስት ፡ ተከፈለ ፡ ወይም ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመለኮትነት ፡ በአፍዓ ፡ ናቸው ፡ አንልም ።

እንዲህ ፡ አድርገን ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለናት ፡ የተወለደ ፡ ወልድ ፡ አብ ፤ ድኅረ ፡ ዓለምም ፡ ከእመቤታችን ፡ ያለአባት ፡ የተወለደ ፡ ወልድ ፡ ማርያም ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ልደት ፡ በተዋሕዶ ፡ ከበረ ፡ ብለን ፡ እናምናለን ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ሦስተኛ ፡ ምሥጢረ ፡ ጥምቀት ።

ምሥጢረ ፡ ጥምቀት ፡ ማለት ፡ አዳም ፤ በተፈጠረ ፡ በ፵ቀኑ ፡ ከሥላሴ ፡ የጸጋ ልደት ፡ ተወልዶ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኾኖ ፡ ነበረ ። ምክረ ፡ ሰይጣንን ፡ ሰምቶ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በበላ ፡ ጊዜ ፡ ልጅነቱን ፡ አስወሰደ ። ጌታ ፡ ሰው ፡ የኾነበት ፡ ምሥ ጢሩ ፡ ያነን ፡ የሔደብንን ፡ ልጅነት ፡ ሊያስመልስልን ፡ ነው ። ስለዚህ ያነን ፡ ልደት ለማግኘት ፡ ምክንያት ፡ የሚኾነን ፡ ማየ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ለመቀደስና ፡ ለመባረክ በእደ ፡ ዮሐንስ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ተጠመቀ ። ከተጠመቀም ፡ በኋላ ፡ ሳይውል ሳያድር ፡ ዕለቱን ፡ ገዳም ፡ ሔዶ ፡ ፵መዓልት ፡ ፵ሌሊት ፡ ጾሞ ፡ ከሰይጣን ፡ ተፈትኖ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ትምህርት ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ለኒቆዲሞስ ፡ ዳግመኛ ያልተወለደ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አያይም ፡ ብሎ ፡ ነግሮታል ። ኒቆዲሞ ስም ፡ ነገሩ ፡ ቢረቅበት ፤ ሰው ፡ ተወልዶ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ ሊወለድ እንደምን ፡ ይቻላል ። ከተወለደ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ ተመልሶ ፡ ወደናቱ ማኅፀን ፡ ሊገባና ፡ ዳግመኛ ፡ ሊወለድ ፡ ይቻላልን ፡ ቢለው ፤ ዳግመኛ ፡ ከውኃና ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያልተወለደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሊገባ ፡ አይችልም ፡ ብዬ ፡ በእ ውነት ፡ እነግርሃለሁ ፡ ብሎ ፡ በጥምቀት ፡ የምናገኘውን ፡ ረቂቅ ፡ ልደት ፡ አረጋግጦ ፡ ነግሮ ታል ። ዮሐ ፡ ፫ ፫-፯ ። የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ በረገ ፡ ጊዜም ወእንዘ ፡ ታጠምቅዎሙ ፡ በሉ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ሐዋርያ ትን ፡ አዝዙዋቸዋል ። ምሥጢረ ፡ ጥምቀት ፡ ማለት ፤ ሰው ፡ ተወልዶ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ዳግመኛ ፡ ሊወለድ ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ሳይጠራጠር ማንም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ አምኖ ፡ በተጠመቀ ፡ ጊዜ ፡ ከሥላሴ ፡ በዓይን ፡ የማይ ታይ ፡ ረቂቅ ፡ ልደትን ፡ እንዲወለድ ፡ ማመን ፡ ነው ። ምሥጢረ ፡ ጥምቀት ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፬ተኛ ፡ ምሥጢረ ፡ ቍርባን ።

ምሥጢረ ፡ ቍርባን ፡ ማለት ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ኅብስተ ፡ ሕይወት ይህ ፡ ነው ፡ ከርሱ ፡ የበላ ፡ አይሞትም ። ከሱ ፡ የበላ ፡ ለዘለዓለም ፡ የማይሞት ሕያው ፡ ኾኖ ፡ የሚኖር ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ኅብስት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ይህ ፡ እኔ የምሰጠው ፡ ኅብስትም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የሚኾን ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ የወ ልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ክርስቶስን ፡ ሥጋውን ፡ ካልበላችሁ ፡ ደሙን ፡ ካል ጠጣችሁ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የላችሁም ። ሥጋዬን ፡ የበላ ፡ ደሜን ፡ የጠጣ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ያገኛል ። ሥጋዬ ፡ እውነተኛ ፡ ምግብ ፡ ደሜም ፡ እው ነተኛ ፡ መጠጥ ፡ ነውና ፡ ሥጋዬን ፡ የበላ ፡ ደሜን ፡ የጠጣ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሕያው ኾኖ ፡ ይኖራል ፤ እኔም ፡ አድሬበት ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎ ፤ በነገረን ፡ መሠረት ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በምሴተ ፡ ሐሙስ ፡ ተርታውን ፡ ኅብስት ፡ በርክ ቶ ቀድሶ ፡ አክብሮ ፡ ለውጦ ፡ ፍጹም ፡ ሥጋውን ፡ አድርጎ ፡ ይህ ፡ ነገ ፡ በመልዕ

www.ethiopianorthodox.org



ቸው ፤ ተርታውንም ፡ ወይን ፡ አክብሮ ፡ ለውጦ ፡ ይህ ፡ ነገ ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ የሚፈሰው ፡ ደሜ ፡ ነው ፡ እንኩ ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ እንደሰጣቸው ፡ ዛሬም ፡ ቀሳውስት ፡ ተርታውን ፡ ኅብስት ፡ ተርታውን ፡ ወይን ፡ ፩ዱ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ ባርከው ፡ ሀበነ ፡ ንኅበር ፡ በዘዚአከ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ ሲፈትቱት ፡ ፍጹም ፡ የአምላክ ፡ ሥጋ ፡ የአምላክ ፡ ደም ፡ እንዲኾን ፡ ማወቅና ፡ ማመን ።

ይህ ፡ ኅብስት ፡ የፈጣሪያችን ፡ የአማኑኤል ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ጽዋዕ ፡ የአማኑኤል ፡ ደም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሲያቀብሉ ፡ ባይናችን ፡ የምናየው ፡ ኅብስት ፡ ወይን ፡ ሲኾን ፡ ሥጋ ፡ ደም ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ ሳይ ጠራጠሩ ፡ አምን ፡ በእውነት ፡ የአማኑኤል ፡ ሥጋ ፡ የአማኑኤል ፡ ደም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መቀበል ፡ ነው ። ከምሉ ፡ በክፍሉ ፤ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ምሥጢረ ፡ ቍር ባን ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ፭ተኛ ፡ ምሥጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ።

እግዚአብሔር ፤ ሰውን ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ እየኖረ ፡ ስሙን ፡ ሊቀድስ ፡ ክብሩን ፡ ሊወርስ ፡ ፈጥሮታል ፡ እንጂ ፡ እንዲታመም ፡ እንዲሞት ፡ አድርጎ ፡ አልፈጠረውም ፡ ነበረ ። ሞት ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ያመጣው ፡ ዕዳ ፡ ነው ። እግዚአብሔርሰ ፡ ኢገብረ ፡ ሞተ ፡ አላ ፡ ረሲዓን ፡ ጸውዕዎ ፡ በቃሎሙ ፡ ወዐርከ ፡ አምሰልዎ ። ሞትን ፡ ረሲዓን ፡ በቃላቸው ፡ ጠርተው ፡ አምጥተው ፡ ወዳጅ ፡ አስመሰሉት ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ሰውን ፡ ሊሞት ፡ አልፈጠረውም ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ነገረን ። ጥበ ፡ ፩ ፡ ፲፰-፳፫ ።

ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በልቶ ፡ መሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብእ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ክሰማ ፡ ወዲህ ፡ የሚሞት ፡ ሆኗል ። ይኸውም ፡ በአቤል ፡ ተገሆምሯል ። በዚህም ፡ አቤል ፡ በሖረ ፡ ምውታን ፡ ተብ ሎበታል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚነሡ ፡ ሰዎች ፡ ሞተን ፡ ፈርሰን ፡ በስብሰን ፡ እንቀራለን ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ እንዳይቆርጡ ፡ ሄኖክን ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በማሳረጉ ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤን ፡ ሰጥቷቸዋል ፡ ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፳፬ ፡ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፭ ።

ይህነንም ፡ ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በ፳፬ተኛው ፡ ድርሳን ፡ (በአቤል ፡ አፍርሆሙ ፡ ወበሄኖክ ፡ አንቅሆሙ ፡) ሞት ፡ እንዳለ ፡ በአቤል ፡ ነግሮ ፡ አሳዘናቸው ፡ ትንሣኤም ፡ እንዳለ ፡ በሄኖክ ፡ ነግሮ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ፡ ብሎ ፡ ተርጕሞታል ።

ይህንም ፡ አበው ፡ በምሥጢር ፡ ያውቁት ፡ የነበረውን ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ ጌታ ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ በመቃብር ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ቃሉን ፡ የሚሰሙበት ፡ ጊዜ ፡ ትመጣለች ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጎ ፡ የሠሩ ፡ ኹሉ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለክብር ፡ ይነ ሣሉ ። ክፉ ፡ የሠሩ ፡ ግን ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለኀሣር ፡ ይነሣሉ ፡ ብሎ ፡ ገልጦ ፡ ነግሮናል ። ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፰ ።

ይህንም ፡ በቃል ፡ ያስተማረንን ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ ፫ ፡ መዓልት ፡ ፫ ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጥፍቶ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡

የማይከተለው ፡ ረሃብ ፡ ጽምዕ ፡ ድካም ፡ የማይስማማው ፡ ኃያል ፡ ሕያው ፡ ኾኖ በመኖሩ ፡ በገቢር ፡ አሳይቶናል ።

አቤል ፡ አስቀድሞ ፡ በመሞቱ ፡ በኋላ ፡ ምውታን ፡ እንደተባለ ፡ ጌታም አስቀድሞ ፡ በመነሣቱ ፡ በኋላ ፡ ትንሣኤ ፡ ኾኗል ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ከእመቤታችን ፡ በቀር ፡ የርሱን ፡ ትንሣኤ ፡ የመሰለ ፍጹም ፡ ትንሣኤ ፡ የተነሣ ፡ የለም ። እነአልዓዛር ፡ እነወልደ ፡ መበለት ፡ እነ ለተ ፡ ኢያኢሮስን ፡ ቢያስነሣቸው ፡ ረኃብ ፡ ጽምዕ ፡ ድካም ፡ በሚስማማው ሕማም ፡ ሞት ፡ በሚከተለው ፡ ቡሩድ ፡ በግዙፍ ፡ ሥጋ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ለገ ዜው ፡ ቢነሡ ፡ ወዲያው ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ እየተመለሱ ፡ ሞተዋል ።

ይህ ፡ ባተሰፋ የምንጠባበቀው ፡ ደገኛው ፡ ትንሣኤ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደ ለም ። ደገኛውስ ፡ ትንሣኤ ፡ ማንም ፡ በማያውቃት ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ በሚያውቃት ዕለትና ፡ ሰዓት ፡ በክበበ ፡ ትስብእት ፡ በግርማ ፡ መለኮት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ኃጥእ ፡ ጻድቅ ፡ አማኒ ፡ መናፍቅም ፡ ቢኾን ፡ በወርድ ፡ በቁመት ፡ ሳይበላለጥ ተካክሎ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ በማይከተሉት ፡ እውነትና ፡ ሐሰት ፡ ጽድቅና ፡ ኃጢ አት ፡ በማይፈራረቁበት ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ በሐዲስ ፡ ሥጋ ፡ ተነሥቶ ፡ እንደ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ዋጋን ፡ ተቀብሎ ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ጋራ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ኾኖ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያዩ ፡ ሲደሰቱ ፡ መኖር ፡ ነው ምሥጢረ ፡ ትንሣኤ ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

እናንተ ፡ ወንድሞቼ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ እነሆ ፡ ሃይማኖትና ፡ የ ምነት ፡ ትርጓሜ ፤ አምኖ ፡ የሚሔዱበት ፡ መንገድና ፡ ሔዶም ፡ የሚገቡበት ሀገር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መኾናቸውን ፡ ሃይማኖት ፡ ፰ቱ ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር የእምነት ፡ ትርጓሜ ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ መሠዋት ፡ ደርሶ ሃይማኖትን ፡ በሥራ ፡ መግለጽ ፤ አምኖ ፡ የሚሔዱበትም ፡ መንገድ ፡ ጾም ፡ ጸሎት ሰጊድ ፡ ቁመት ፡ በጠቅላላው ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ መሥራት ፤ ሔዶም ፡ የሚ ገቡበት ፡ ሕያው ፡ መኖሪያ ፡ ሀገርም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መኾኗን ፡ ለይቼ ለይቼ ፡ ጽፌላችኋለሁ ። እንዲህ ፡ ከዘር ፡ የወረደ ፡ የተጣራ ፡ ሃይማኖትና ምግባር ፤ የታረመ ፡ የተወሰነ ፡ ሕግና ፡ ባህል ፡ እያላችሁ ፡ በማይረባ ፡ በማ ጠቅም ፡ በእንብላው ፡ ብቻ ፡ በተመሠረተ ፡ እርሱ ፡ ራሱም ፡ መዳረሻውን ፡ አ ውቀው ፡ ብሎ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ በየቀኑ ፡ ሲፈራቀቅና ፡ ሲለያይ ፡ በሚኖር የተውሶ ፡ ባህል ፡ ተጠልፋችሁ ፡ ከጽኑ ፡ አንባችሁ ፡ እንዳትወድቁ ፡ አደራ እላችኋለሁ ።

ለምድራዊው ፡ መንግሥታችሁና ፡ ለኃላፊው ፡ ርስታችሁ ፡ ደማችሁን ፡ ለ ፍሰስ ፡ ቆራጦች ፡ እንደመኾናችሁ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተ ኝታ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ከ፫፻፲፰ ፡ ከባቶቻችሁ ፡ ተያይዞ ፡ ለመጣች ፡ የ ታልፍ ፡ ሰማያዊት ፡ ርስት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ለምታወርሳችሁ ፡ ለጸናች ለቀናች ፡ ሃይማኖታችሁና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለተወደደች ፡ ምግባራችሁ ደማችሁን ፡ ልታፈሱላት ፡ የሚገባ ፡ መኾኑን [illegible]



## እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ሥረ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ።

፩ ፡ የፍቅር ፡ አባት ፡ መምህራችን ፡ ክርስቶስ ፡ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ፍቅር ፡ ቢኖራችሁ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቼ ፡ መኾናችሁ ፡ በርሷ ፡ ትታወቃላችሁና ፤ እኔ ፡ በሔድኩበት ፡ መንገድ ፡ ተከተሉኝ ፡ ብሎናል ፡ ብለህ ፡ ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴፬–፴፯ ፡ ጠቅሰሃል ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሔደበቸውና ፡ ተከተሉኝ ፡ ያለባ ቸው ፡ መንገዶች ፡ ጥምቀት ፤ ተባሕትዎ ፡ ምንኵስና ፤ ከዊነ ፡ ሰማዕት ፤ ተአ ምኖ ፡ ኃጣውእ ፡ መኾናቸውን ፡ ሊቁ ፡ ወሐዮን ፡ እግዚእ ፡ ለኵምስ ፡ ግብራት ፡ ብሎ ፡ አስረድቶናል ። ጥምቀት ፡ በጥምቀት ፡ የሚሻው ፡ የሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ሳይኖረው ፡ ጥምቀትን ፡ ሊአኛ ፡ ባርከ ፡ ቀድሶ ፡ ለመስጠት ፡ በእደ ፡ ዮሐንስ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጠመቅ ፡ ነው ። ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ጌታዋን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ተከትላ ፡ ልጆቿን ፡ ወንዶችን ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ ሴቶችን ፡ በ፹ ቀን ፡ ታጠምቃለች ።

ያንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የምትከተለው ፡ በፉና ፡ በንዳንድ ፡ በማይጠቅሙ ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ ጌታችን ፡ በ፴ ፡ ዘመኑ ፡ ተጠምቋልና ፡ ጥምቀት ፡ በ፴ ፡ ዘመን ፡ ትላለች ።

እነሆ ፡ ከመንፈስና ፡ ከወኃ ፡ ያልተወለደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አያያ ትም ፡ ብሎ ፡ በማይታበል ፡ ቃሉ ፡ ነግሮናል ። ለሰውም ፡ ዕድሜው ፡ ዐጭር ፡ ስለኾነ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ሳይሞላው ፡ የሚሞተው ፡ ብዙ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አያያዝ ፡ ጥምቀት ፡ በ፴ ፡ ዘመን ፡ ከሆነ ፡ ያልተጠመቀም ፡ የማይድን ፡ ከኾነ ፡ ጌታ ፡ በሞቱ ፡ ያዳነ ፡ ከ፴ ፡ ዘመን ፡ በላይ ፡ የሞቱትን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚበልጥ ፡ ማነው ፡ ብለው ፡ በጠየቁት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ ጠርቶ ፡ ከመካከላቸው ፡ አቁሞ ፡ ተመልሳችሁ ፡ እንደዚህ ፡ ሕፃን ፡ ካልኾናችሁ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አትገቡም ፡ ያለው ፡ ቃሉና ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለእንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ሕፃናት ፡ ናትና ፡ አትከልክ ሏቸው ወደኔ ፡ ይምጡ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ታበለ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፩-፯ ። ፲፱ ፡ ፲፬ ።

ይህነንም ፡ ስልህ ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ ያንተ ፡ ዘርፍና ፡ ቅርንጫፍ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለጥምቀትና ፡ ስለቊርባን ፡ ብለህ ፡ በጻፍከው ፡ አንዳንድ ፡ ማኅበሮች ፡ ጥምቀት ፡ በ፴ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ እንደሚሉት ፡ ሳይኾን ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ፡ ማለትህን ፡ ሳልዘነጋ ፡ ነው ።

፪ ፡ ተባሕትዎ ፤ ተባሕትዎ ፡ ተጠምቆ ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ ዕለቱን ፡ ገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሔዶ ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ ብቻውን ፡ ኾኖ ፡ መጾምና ፡ መብል ፡ ያመጣውን ፡ የስስት ፡ ፈተና ፡ በትሕርምት ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ በመዋዕለ ፡ ስብ ከቱም ፡ ቀን ፡ ሲያስተምር ፡ እየዋለ ፡ ሌሊት ፡ ብቻውን ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ማደር ፡ [illegible] ፡ ፴፯ ።

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ልጆቿን ፡ በ፵ ፡ በ፹ ፡ ቀን ፡ አ[illegible] ምቃ ፡ ዕለቱን ፡ ሳይውሉ ፡ ሳያድሩ ፡ ተጠምቀው ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ እስኪ[illegible] በሉ ፡ ድረስ ፡ የናቶቻቸውን ፡ ጡት ፡ በመከልከል ፡ ጾምን ፡ ታስጀምራቸዋለች ፣ ፯ ፡ ዓመት ፡ ከመላቸው ፡ በላይ ፡ ዐርብና ፡ ረቡዕን ፡ ጾመ ፡ ገሃድን ፡ ጾመ ፍልሰታን ፡ እንዲጾሙ ፡ ታዝዛቸዋለች ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ፲፫ቱ፯ ፡ በፍትሐ ፡ ነ[illegible] ሥት ፡ የወሰኑላትን ፡ ፯ቱን ፡ አጽዋም ፡ እንዲጾሙ ፡ ታስገድዳቸዋለች ።

ያንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ልጆቿን ፡ በ፵ም ፡ ቀን ፡ ሆነ ፡ በ፹ም ዘመን ፡ ሆነ ፡ አጥምቃ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ አታቀብላቸውም ። አዳም ፡ ልጅነትን ካገኘ ፡ በኋላ ፡ መልሶ ፡ ልጅነቱን ፡ ወዳስወሰደበት ፡ ሚዳ ፡ ወደ ፡ ሙብል ወደመጠጥ ፡ ታሰማራቸዋለች ፡ እንጂ ፡ ዲያብሎስ ፡ ድል ፡ ወደተነሣበት ፡ ወደ ጾም ፡ ወደ ፡ ትሕርምት ፡ አትመራቸውም ። አካለ ፡ መጠን ፡ ካደረሱም ፡ በኋላ በተባሕትዎ ፡ መኖር ፡ እንደ ፡ ኃጢአት ፤ የሚቆጠር ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እያለች ታስተምራቸዋለች ።

፫ተኛ ፤ ምንኵስና ፡ ምንኵስናም ፡ ማለት ፡ በድንግልና ፡ ኖሮ ፡ አክሊለ ፡ ሦክ[illegible] መሸከም ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በድንግልና ፡ ኖሮ ፡ አክሊለ ፡ ሦክን እንደተሸከመ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በድንግልና ፡ እየኖሩ ፡ ለአክሊለ ሦክ ፡ ምሳሌ ፡ የሚኾን ፡ ቆብዕን ፡ መሸከም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያስመስል ፡ ደግ[illegible] ሥራ ፡ መኾኑን ፡ ታስተምራለች ።

ያንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ምንኵስና ፡ ከእምላክ ፡ ሕግ ፡ የተለየ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ።

፬ተኛ ፡ ከዊነ ፡ ሰማዕት ፤ ከዊነ ፡ ሰማዕት ፡ ማለት ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ቆሞ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እውነተኛ ፡ ምስክር ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም መጥቼ ፡ ተወለድኩ ፡ ብሎ ፡ መመስከር ፡ ነው ።

ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይህ ፡ ምስክርነት ፡ የሚፈጸመው በላውያን ፡ ነገሥታት ፡ በላውያን ፡ መኳንንት ፡ በተነሡበት ፡ ዘመን ፡ ሳያፍሩ ሳይፈሩ ፡ ወእነግር ፡ ስምዐከ ፡ በቅድመ ፡ ነገሥት ፡ ወኢይትኃፈር ፡ እያሉ ሰውነትን ፡ ለተሳለ ፡ ስለት ፡ ለነደደ ፡ እሳት ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ።

ዘመነ ፡ ሰላምም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መስለ[illegible] በብሕትውናና ፡ በግብረ ፡ ምንኵስና ፡ ተወስኖ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ በ[illegible] መት ፡ ጸንቶ ፡ ተገኝቶ ፡ በስስት ፡ ሲመጣ ፡ በትሕርምት ፤ በትዕቢት ፡ ሲመጣ በትሕትና ፤ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ሲመጣ ፡ በጸሊዐ ፡ ንዋይ ፡ ድል ፡ በመንሣት ነው ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ።

ያንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በ[illegible] ዘንድ ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን ፡ ታገኛላችሁ ፡ [illegible] ልዩ ፡ መከራ ፡ ያገኛችኋልና ፡ እኔ ፡ ድል ፡ እንደነሣሁት ፡ እናንተም ፡ ጠን[illegible]



ችሁ ፤ ድል ንሡ ። ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፴፬ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አንዘግዝጋ ፡ ጥላ ፡ በቃል ፡ በማፈቻል ፡ ብቻ ፡ የሚዳን ፡ መስሏት ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ ከኃጢአታችን ፡ ያነጻናል ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ ስታወራ ፡ ትኖራለች ።

፭ተኛ ፡ ተአምኖ ፡ ኃጣውእ ፤ ተአምኖ ፡ ኃጣውእ ፡ ማለት ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ ሲኾን ፡ ራሱን ፡ ከተአማንያን ፡ ኃጣውእ ፡ እንደአንዱ ፡ አድርጎ ፡ በምእመናን ፡ ተገብቶ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፡ ለምንት ፡ ኀደገኒ ፡ ብሎ ፡ መጸለይ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በስሙ ፡ አምናችሁ ፡ ሕጉን ፡ ጠብቃችሁ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለባችሁ ፡ ብትኾኑም ፤ ኃጢአት ፡ የለብንም ፡ ንጹሓን ፡ ነን ፡ አትበሉ ፤ እኛ ፡ አንገታችንን ፡ አቅንተን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ማየት ፡ የማይቻለን ፡ ኃጢአተኞች ፡ ነንእና ፡ አባቶቻችን ፡ ቅዱሳን ፡ ጸልዩልን ፡ አማልዱን ፡ በሉ ፡ እያለች ፡ ታስተምራለች ።

ያንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ከመጠመቅ ፡ በቀር ፡ አንዱን ፡ ሳትነካ ፡ በስሙ ፡ አምነው ፡ ርሱን ፡ ተከትለው ፡ ትእዛዙን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ ኢይብለክሙ ፡ አግብርትየ ፡ አላ ፡ አዕርክትየ ፡ ያላቸው ፡ ሐዋርያትንና ፡ ተከታዮቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ የማይረቡ ፡ ሬሶች ፡ እያለች ፡ ትሳደባለች ፡ በሥራዬ ፡ እጸድቃለሁ ፡ እያለች ፡ ትመካለች ።

እንግዲህ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በየትኛው ፡ አካሔድህ ፡ ነው ፡ የተከተልከው ፡ ከሥራው ፡ ሳይገኙ ፡ ክርስቶስ ፡ ለቤዛ ፡ ዓለም ፡ ሞተ ፡ በማለት ፤ ብቻ ፡ የሚዳን ፡ መሰለህን ? ይህስ ፡ ታሪክ ፡ ዐዋቂ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ አያሰኝምና ፡ ሕግህን ፡ አርም ።

፳ ከዚህ ፡ ቀጥለህ ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፯ ። ዕብ ፡ ፯ ፳፭ ። ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፱ ። ፳ ፳፬ ። ፲፬ ፡ ፳፭ ። ፫ ፡ ፶፬ ። ፲ ፡ ፯—፲፭ ። ፲ ፳፫—፴ ። ፫ ፡ ፲፱ ። ፯ ፡ ፴፭ ። ፫ ፡ ፴፯ ። ፯ ፡ ፶፬ ። ፯ ፡ ፴፫ ። ፯ ፡ ፵፯ ። ፲፱ ፡ ፵፯ ። ፲፬ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ፡ ፴፯ ። ፳ ፡ ፲፱ ። ፲፬ ፡ ፳፯ ። ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፬ ፡ ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፴ ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፩-፲ ። ፲፬ ፡ ፩-፬ ፡ ዕብ ፡ ፬ ፡ ፲፬-፲፯ ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ፲፬ ፡ ፫ ። በተስፋ ፡ ነቅታችሁ ፡ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ጠብቁኝ ፡ ብሎ ፡ አዘናል ፡ እስከሚለው ፡ ቃል ፡ ድረስ ፡ በነሂ ፡ ምዕራፎችና ፡ ቍጥሮች ፡ የሚገኙትን ፡ ቃላት ፡ በግእዝም ፡ በማርኛም ፡ ጠቀስሃቸዋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሽህ ፡ ፮፻ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ወንጌልን ፡ የተቀበለችና ፡ ያመነች ፡ የወንጌልን ፡ ምሥጢር ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ያወቀች ፡ የተረዳች ፡ መኾኗን ፡ አላውቅ ፡ ብለህ ፡ እንግዳ ፡ አስመስለህ ፡ በመጥቀስህ ፡ እያዘንኩ ፡ ጌታ ፡ የተናገረው ፡ በወንጌል ፡ የተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምሰጥህ ፡ መልስ ፡ የለኝም ።

ስለዚህ ፡ አማላጃችን ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ አምነን ፡ ካልከው ፡ ጀምሮ ፡ ለሚሰማው ፡ ማረኝ ፡ ማለት ይበልጣል ፡ እስከምትለው ፡ ድረስ ፡ በኻያው ፡ መሥመ[illegible] ተጻፈው ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ አማላጅነት ፡ እንጂ ፡ ስለሃይማኖት ፡ አይናግርም ።

www.ethiopianorthodox.org

ድራሲ ፡ ለድርሰቱ ፡ አንቀጽ ፡ ለይቶ ፡ አርእስት ፡ ሰጥቶ መጻፉ ፡ አሳቦቹ ፡ ኹለ
በየፈርጃቸው ፡ በየመልካቸው ፡ ኾነው ፡ በንዳንድ ፡ ፊት ፡ እንዲገኙለት ፡ ነበረ ፡ እን
በየገጹ ፡ አንቀጽ ፡ በእንተ ፡ እገሌ ፡ ብሎ ፡ መጻፍ ለመጽሐፉ ፡ ጌጥ ፡ ይኾነዋል
ብሎ ፡ አልነበረም ።

አንተ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ባለማወቅህ ፡ ስለሃይማኖት ፡ ስለአማላጅነት ፡ እያልክ
ከመጻፍ ፡ በቀር ፡ ነገሮችን ፡ በያንቀጻቸው ፡ ሳትሰበስብ ፡ አንዱን ካንዱ ፡ አማተህ
አዘበራርቀህ ፡ ጽፈሃቸዋል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነገርህ ፡ ኹሉ ፡ ሳይታሠር ፡ ቀርቶ
ነፋስ ፡ እንደበተነው ፡ ነዶ ፡ በያንቀጹ ፡ በየገጹ ፡ ተበትኖ ፡ ተልከስክሶ ፡ ይገኛል
እኔ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እንዳይደርስብኝ ፡ የዚህን ፡ መልስ ፡ ስለአማላጅነት ፡ ብለህ ፡ ባ
ፍከው ፡ አንቀጽ ፡ ለመጻፍ ፡ አቆይቼ ፡ ስለሃይማኖት ፡ ነክነት ፡ ላላቸው ፡ ነገሮች
ብቻ ፡ መልስ ፡ ልጽፍልህ ፡ አስቤ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በአንቀጾች ፡ መለያየት
ጥቅሱንና ፡ መልሱን ፡ ማገናዘብ ፡ የማይቻልህ ፡ በመኾኑ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጠው ፡ የቀረ
ይመስልሃል ፡ ብዬ ፡ መልሱን ፡ ያለቦታው ፡ ከቅርታ ፡ ጋራ ፡ እጽፋለሁ ።

፮ ስለዚህ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ አማላጃችን ፡ መኾኑን ፡ አምነን ፡ ሌሎች ፡ የማይጠቅሙ ፡ የፍጡራን ፡ አ
ላጆች ፡ ትተን ፡ እነሆ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣለሁ ፡ ለኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ዋ
ዬም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፪ ፡ ፲፪ ፡ ስላለን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ የሱስ ፤ ና ፤ እያልን ፡ የርሱን ፡ ት
ዛዝ ፡ ብቻ ፡ እየፈጸምን ፡ በኃጢአታችን ፡ እያዘን ለርሱ ፡ መቈየትና ፡ መጠበቅ ፡ ይገባናል ፡ ስለምትለው

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አማላጃችን ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ አንተ ፡ ከልቡናህ ፡ አንቅተህ
ጽፈሃል ፡ ላማላጅነቱ ፡ ምስክር ፡ አድርገህ ፡ የጠቀስከው ፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፪ ፡ ፲፪
ግን ፡ ለኹሉም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እከፍለው ፡ ዘንድ ፡ ፈጥኜ ፡ እመ
ለሁ ፡ ዋጋዬም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ጌትነቱን ፡ አምላክነቱን ፡ ይናገራል
እስኪ ፡ ያሳይህ ፡ አማላጅ ፡ አማልዶ ፡ ተማላጁ ፡ እሺ ፡ ቢለው ፡ እሺ ፡ አሰኝቸል
ለሁ ፡ አስደርጌልሃለሁ ፤ ባይኾንለት ፡ አልኾነልኝም ፡ ብሎ ፡ ለላከው ፡ መልስ ፡ ይሰ
ጣል ፡ እንጂ ፡ ዋጋ ፡ የሚገኝ ፡ ከኔ ፡ ነው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ዋጋውን ፡ እከፍለዋለሁ
ይላልን ፤ ከራሱ ፡ በሥልጣኑ ፡ እንደየሥራው ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ የሚቻለው ፡ ከ
ነስ ፡ ተማላጅ ፤ ጌታ ፤ ሰጪ ፤ ነሺ ፤ ይባላል ፡ እንጂ ፡ አማላጅ ፡ ይባላልን ፡ ኣንተ
ደፋር ፡ እረኛ ፡ ምነው ፡ ንግግርህን ፡ ብታርመው ፡ በዘፈቀደ ፡ መናገርህን
ብትተው ።

ለእኛስ ፡ አማላጆቻችን ፡ በራሳቸው ፡ መብትና ፡ ሥልጣን ፡ ለማንም ፡ ዋጋ ፡ ሊ
ፍሉ ፡ የማይቻላቸው ፡ ለማማለድ ፡ የሚያበቃ ፡ የባለሟልነት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው
ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ ናቸው ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስስ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ዕሩየ ፡ መንግሥት
ዕሩየ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በአብ ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጦ ፡ እንደ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥ
ችን ፡ ዋጋችንን ፡ የሚከፍለን ፡ አምላካችን ፡ ንጉሣችን ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እናምን
ቃለን ፡ እንጂ ፤ ያስታራቂነቱን ፡ ተግባር ፡ በ
በኋላ ፡ አማላጅ ፡ ስንለው ፡ አንኖርም ።



፯ አሁን ፡ ግን ፡ ያማላጅነቱን ፡ ነገር ሽማግሌው ፡ ሐዋርያ ፡ ዮሐንስ ፡ የነገረን ፡ ኡነተኛ ፡ ምክር ፤ እን
ስማ ። ልጆቼ ፡ ሆይ ኃጢአት ፡ እንዳትሠሩ ፡ ክናንተ ፡ ማኝም ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፡ ግን ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጻድቅ ፡ አማላጅ ፡ አለን ፡ ይለናል ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ወይም ፡ እናቴ ፡ አለንላችሁ ፡ አይልም ።
፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፩ ። ፪ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፬—፳፩። ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፭—፳፯ ። ስለምትለው ።

ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወእመቦ ፡ ዘአበሰ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ብነ ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰጥተህ ፡ ያለትርጓሜው ፡
አማላጅ ፡ ብለህ ፡ ጽፈሃል ። ይህ ፡ ንግግርህ ፡ በፍጹም ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ። ጰራቅሊ
ጦስ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የወልድ ፡ ስም ፡ አይደለም ፡ የመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ስም ፡ መኾኑንም ፡ ይኸው ፡ ሐዋርያ ፡ በጻፈው ፡ ወንጌል ፡ ለዘላለሙ ፡ ከናንተ ፡
ጋራ ፡ እንዲኖር ፡ እንደኔ ፡ ያለ ፤ ለኔ ፡ ኹለተኛ ፡ የሚኾን ፡ ጰራቅሊጦስን ፡ ይሰድላችሁ ፡
ዘንድ ፡ አብን ፡ እለምንዋለሁ ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ።

ይህነን ፡ እኔ ፡ የነገርኳችሁን ኹሉ ፡ አብ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ የሚልክላችሁ ፡ ጰራቅ
ሊጦስ ፡ ያስተምራችኋል ፡ ያሳስባችኋል ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ።

እኔ ፡ የምልክላችሁ ፡ ከአብ ፡ የሠረፀ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ በመጣ ፡
ጊዜ ፡ ምስክሬ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ።

እኔ ፡ ካልሔድኩ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ወደናንተ ፡ አይመጣምና ፡ እኔ ፡ ብሔድ ፡
ይሻላችኋል ፡ ብሎ ፡ መላልሶ ፡ አስረድቶናል ፡ ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ።

፫ቱም ፡ አካላት ፡ በየራሳቸው ፡ ቅውማን ፡ እንደኾኑ ፡ በስም ፡ አጠራርም ፡
በየራሳቸው ፡ የጸኑ ፡ እንጂ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ስም ፡ እንዳይጠራ ፤ ኢይፈልስ ፡ ስመ ፡
አብ ፡ ለከዊነ ፡ ስመ ፡ ወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወኢይፈልስ ፡ ስመ ፡ ወልድ ፡
ለከዊነ ፡ ስመ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወኢይፈልስ ፡ ስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለከ
ዊነ ፡ ስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ እያሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ነግረውናል ፡ ሃይ ፡ አበ ። በስም ፡
መፋለስ ፡ ካለም ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴም ፤ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌም ፤ መፋለሱ ፡ የማይጠ
ረጠር ፡ ነው ። ጰራቅሊጦስ ፡ ማለትም ፡ መጽንዒ ፡ መንጽሒ ፡ ናዛዚ ፡ ከሣቲ ፡ ማለት ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ አማላጅ ፡ ማለት ፡ አይደለም ።

የዚህም ፡ ንባብ ፡ ትርጓሜው ፡ የበደለ ፡ ሰውም ፡ ቢኖር ፡ በንስሐ ፡ ከተመ
ለሰ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ የሚሰድልን ፡ የሚያነጻና ፡ የሚያጸና ፡
ምሥጢርን ፡ የሚገልጽ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አለልን ፡ ማለት ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ አማላጅ ፡ ማለት ፡ አይደለም ።

ይህ ፡ አነጋገር ፡ በፍጹም ፡ የተሳሳተ ፡ ፈጠራ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ንግግር ፡ ነውና ፡
ተው ፡ አስተውል ፤ ከመጻሕፍት ፡ ከመምህራን ፡ ያልተገኘ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነገር ፡ ብት
ናገር ፡ ምን ፡ ይጠቅምሃል ።

፰ እኔ ፡ ወይም ፡ እናቴ ፡ አለንላችሁ ፡ አይለንም ። ስለምትለው ።

ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በዚሁ ፡ አንተ ፡ በጠቀስከው ፡ በመጀመሪያው ፡ ክታቡ ፡
ፍ ፡ ባ፲፬ ፡ ቍ ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ ወደርሱ ፡ ያቀረብነውን ፡ ልመና ፡ ይሰ
ማናልና ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያለችን ፡ ባለሟልነት ፡ ይች ፡ ናት ። የለመንውንም ፡ እንዲ

www.ethiopianorthodox.org

ሰማን ፡ ካወቅን ፡ ኹልጊዜ ፡ ወደርሱ ፡ የምናቀርባት ፡ ልመና ፡ እንዳለች ፡ እናውቃለን ፡ ስለዚህ ፡ ለሞት ፡ የማያበቃ ፡ ኃጢአት ፡ ሲሠራ ፡ ወንድሙን ፡ ያየው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ለሞት ፡ የማያበቃ ፡ ኃጢአት ፡ የሠራ ፡ ወንድሙን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡ የጸልይለት ። ነገር ፡ ግን ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ኃጢአት ፡ አለና ፡ ይጸል ዩለት ፡ ያልኩ ፡ ስለርሱ ፡ አደለም ፡ ብሎ ፡ ጻድቃን ፡ ለተነሳሕያን ፡ ኃጥአን ፡ መጸለይ ፡ እንዲገባቸው ፤ ንስሐን ፡ ለማትፈልግ ፡ ጸልዩልኝ ፡ ለማትል ፡ ላንተ ፡ መጸለይ ፡ እንዳይገባ ፡ ለይቶ ፡ ጽፎልናል ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ወይም ፡ እናቴ ፡ አናማልዳችሁም ፡ አላለንም ።

፱ ፤ ስለዚህ ፡ የጠቀስከው ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፬–፳፩ ፡ ክርስቶስ ፡ ለኹሉ ፡ ቤዛ ኾኖ ፡ ስለሞተ ፡ ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ የሚነሡ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ስለርሳቸው ፡ ሞቶ ፡ የተነሣ ፡ ክርስቶስን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ራሳቸውን ፡ ለማገልገል ፡ አደለም ፡ ክርስቶስንም ፡ ከትንሣኤ ፡ አስቀድሞ ፡ በግዘፍ ፡ ብናውቀው ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ በግዘፍ ፡ የምናውቀው ፡ አደለንም ። ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ በባቱ ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ፡ ወደቀደመ ፡ ጌትነቱ ፡ ወደቀደመ ፡ ክብሩ ፡ ተመለሰ ፡ ያለውን ፡ ንባብ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ተናግሮ ፡ በአብ ፡ ቀኝ ፡ መቀመጡን ፡ ጌትነቱን ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ የኾነው ፡ ኹሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ታድሷል ፤ ብሉይ ፡ ግብር ፡ አልፏል ፤ እነሆ ፡ በክርስ ቶስ ፡ አቅራቢነት ፡ ወደርሱ ፡ ባቀረበን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፤ ኹሉ ፡ ታድሷል ፡ የዓለሙን ፡ ኃጢአት ፡ ንቆ ፡ አቃሎ ፤ ዕዳ ፡ አልልም ፡ ብሎ ፡ ዓለሙን ፡ በክርስቶስ ፡ ዋጅቶታልና ፡ ፈቃዱን ፡ የምንፈጽምበት ፡ ልጅነትን ፡ ሰጠን ። ወዶ ፡ የሠራት ፡ ወን ጌልን ፡ እንድናስተምር ፡ አደረገን ፡ ይቅርታውን ፡ የምናገኝበት ፡ ሐዋርያነትን ፡ ሾሞ ናልና ፡ እንግዲህስ ፡ እኛ ፡ በክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ በክርስቶስ ፡ ፈንታ ፡ እንጸልይላች ኋላን ፡ እግዚአብሔርም ፡ በኛ ፡ ጸሎት ፡ ልጅነትን ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጣችኋል ፡ እናን ተም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ታሰኙት ፡ ዘንድ ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ጠርቼ ፡ እማል ዳችኋለሁ ፡ እያለ ፡ የክርስቶስን ፡ ጌትነት ፡ የራሱን ፡ አማላጅነት ፡ ይጽፋል ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ ያማልዳችኋል ፡ እኛ ፡ አናማልዳችሁም ፡ አላለንም ።

፲ ዑነትኞቹ ፡ አማላጆቹ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ፲ቃላተ ፡ኦሪትንና ፡ ፮ቱ ፡ ቃላተ ፡ ወንጌልን ፡ አጥንቶ ፡ ፈጣሪውን ፡ ብቻ ፡ በሃይማኖት ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ እያዘኑ ፡ ዘወትር ፡ ወደርሱ ፡ እየጮሁ ፡ ምሕረትን ፡ ከመሀሪው ፡ እየለመኑ ፡ በጸሎት ፡ ተግቶና ፡ ነቅቶ ፡ መኖር ፡ ነው ። ስለምትለው ።

፲ቃለተ ፡ ኦሪትና ፡ ፮ቱ ፡ ቃላተ ፡ ወንጌል ፡ ቢጠብቋቸው ፡ ዋጋ ፡ የሚያሰጡ ፡ ባይጠብቋቸው ፡ ፍዳ ፡ የሚያመጡ ፡ በገሃነም ፡ የሚያስቀጡ ፡ሕጎች ፡ ይባላሉ ፡ እንጂ ፡ አማላጆች ፡ አይባሉም ።

በሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ እነሱን ፡ ጠብቆ ፡ የኖረ ፡ ሰው ፡ ለሌላው ፡ አማላጅ ፡ ይኾ ናል ፡ እንጂ ፡ አማላጅ ፡ አይሻም ፡ ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ።

፲፩ ለማይሰሙ ፡ አስምሩኝ ፡ ከማለት ፡ ለሚሰማው ፡ ማረኝ ፡ ማለ...

የዚህነን ፡ መልስ ፡ ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ ብለህ ፡ በጻፍከው ፡ በ፯ተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ተመልከት ፡ ሰማዕያን ፡ መኾናቸው ...



፲፪ ሥታያቸውና ፡ ጩኸታቸውን ፡ ሰማሁ ፡ ላድናቸውም ፡ ወረድሁ ፡ ዘጸአ ፡ ፫ ፡ ፱ ፡ ፰ ፡ ወደኋም ፡ የጮኸ ፡ እንደኾነ ፡ መሀሪ ፡ ነኝና ፤ እኔ ፡ እሰማዋለሁ ፡ ዘፀአ ፡ ፳፪ ፡ ፳፯ ። ስለምትለው ።

ኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ከንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ጀምራ ፡ የተቀበለችና ፡ ያወ ቀች ፡ ናት ፡ ላላወቀ ፡ ይጠቀስለታል ፡ እንጂ ፡ ለሚያውቅ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ አስ መስሎ ፡ የሚያውቀውን ፡ ነገር ፡ መጥቀስ ፡ ሞኝ ፡ ቂል ፡ ያስመስላል ። ለምንም ፡ አይጠቅምም ።

፲፫ አንቺ ፡ የሰበሰብሻቸው ፡ ኹሉ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይወስዳቸዋልና ፡ በጮህሽ ፡ ጊዜ ፡ ሊያድኑሽ ፡ አይችሉም ፡ ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፫ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትጮሃለህ ፡ ርሱም ፡ እነሆኝ ፡ እቤት ፡ ይል ሃል ። ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፱ ፡ ስለምትለው ።

ኢሳይያስ ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ የተናገረው ። እግዚአብሔርን ፡ ክደው ፡ ጣዖት ፡ በሚያመልኩ ፤ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ጠልተው ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰትን ፡ ካህናተ ፡ ጣዖ ትን ፡ በሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ነው ። ኢትዮጵያም ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ አም ልኮተ እግዚአብሔርን ፡ መርጣ ፡ ከነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ከካህናተ ፡ ጣዖት ፤ ነቢያተ ፡ ጽድቅን ፡ ካህናተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለይታ ፡ ዐውቃ ፡ የምትወድ ፡ የምታከብር ፡ ሀገር ፡ ናት ።

የሰበሰበቻቸውም ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ሲያስተምሩ ፡ ከተሳለ ፡ ስለት ፤ ከነደደ ፡ እሳት ፡ ገብተው ፡ የሞቱ ፡ የሰማዕታትንና ፡ በፍቅሩ ፡ ተናደው ፡ ከዓለም ፡ ወጥተው ፡ በየዋሻው ፡ በየፍርክታው ፡ ወድቀው ፡ የቀሩ ፡ የቅዱሳንን ፡ ዐፅማቸውን ፡ ወይም ፡ ዜና ፡ ገድላቸውን ፡ ዜና ፡ ዕረፍታቸውን ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ በጣዖት ፡ ብትመስላቸው ፡ ኢይብለክሙ ፡ አግብርትየ ፡ አላ ፡ አዕርክትየ ፡ ያላቸው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መፍቀሬ ፡ ጣዖት ፡ ማለትህ ፡ አይደለምን ።

በዚያውስ ፡ ላይ ፡ እነሱን ፡ ነፍስ ፡ የሚበትናቸው ፡ ከኾነ ፡ ወኢትወድቅ ፡ አሐቲ ፡ እምሥዕርተ ፡ ርእስክሙ ፡ ወለክሙሰ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስክሙኒ ፡ ኍለቍን ፡ ኍሉቃት ፡ እማንቱ ።

የናንተስ ፡ የራስ ፡ ጠጕራችሁ ፡ ኹሉ ፡ የተቈጠረ ፡ ነው ፤ የተቈጠረ ፡ እንዳ ይጠፋ ፡ አይጠፋም ፡ ያላቸው ፡ ቃሉ ፡ ታበለ ማለትህ ፡ አይደለምን ፤ እኛስ ፡ ጣዖት ፡ እንዳናመልክ ፡ ስታውቀው ፡ እንዲህ ፡ እያልክ ፡ የምትጽፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሰብቅ ፡ የሚገባ ፡ መስሎሃልን ፡ እባክህ ፡ ንግግርህን ፡ አርም ። መዝ ፡ ፳፭ ፡ ፲፩ ።

፲፬ እንግዲህ ፡ ሃይማኖት ፡ ከመስማት ፡ ነው ፡ መስማትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ስለምትለው ።

ማመን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ከመስማት ፡ መኾኑ ፤ አሰሚዎችም ፡ መም [illegible] ፡ የማይካድ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ካወቅህ ፡ የረቀቀውን ፡ አጕልተው ፡ የተሰወረውን ፡ ገልጸው ፡ የሚያስረዱ ፡ የሊቃውንትን ፡ ቃል ፡ እንዳትሰማ

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ማይ ፡ ንዝጸምዑ ፡ ምኽሪ ፡ ንዝሰምዑ ።

፪ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በትግሬኛ ፡ የተጻፈ ፡ ስለኾነ ፡ እኔም ፡ ትግሬኛ ፡ አጣርቼ ፡ የማላውቅ ፡ ስለኾንኩ ፡ በማያውቁት ፡ ቋንቋ ፡ ገብቶ ፡ እየዘባረቁና ፡ እየተጨማለቁ ፡ የተ መልከቾችን ፡ ወርቅ ፡ ጊዜያቸውን ፡ ከማባከን ፤ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ሊረዳ ፡ የሚሻ ፡ አእምሯቸውን ፡ ከማበሳጨትና ፡ ከማስመረር ፡ መተው ፡ ይሻላል ፡ ብዬ ፡ በዚሮ ፡ አልፌዋለሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ልዩ ፡ ድብዳቤ ።

ላቶ ፡ ማንበብ ፡ ብቻ ፡ እጅጉን ፡ ለጤናህ ፡ እንደምን ፡ ነህ ። እኔ ፡ ግን ፡ ኪዳን ፡ ተከየድኩ ፡ ምስለ ፡ ኅሩያንየ ፡ ብሎ ፡ ላባቶቹ ፡ ለነቢያት ፡ ለሐዋርያት ፡ ለጻድቃን ፡ ለሰማዕታት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የሰጣቸው ፡ አምላክ ፡ ይክበር ፡ ይመስገንና ፡ ደኅና ፡ ነኝ ።

፩ ለማክብርህ ፡ ወንድሜ ፡ ላቶ ፡ ማመን ፡ ብቻ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥተህ ፡ እጅጉን ፡ ለጤናህ ፡ እንደምን ፡ ትኾናለህ ። እኔ ፡ ግን ፡ ኪዳኑን ፡ የማይከዳ ፡ በጭንቅ ፡ የሚረዳ ፡ ያባቶቹ ፡ የአብርሃምንና ፡ የይስሐቅን ፡ የያዕቆብንና ፡ የዮሴፍን ፡ አምላክ ፡ ሕዝቡ ፡ እስራኤልን ፡ ከምስር ፡ ባርነት ፡ አውጥቶ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራን ፡ በእደ ፡ ሙሴ ፡ አሻግሮ ፡ በእደ ፡ ኢያሱ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ከነዓንን ፡ ያወረሰ ፡ ዑንቶኛው ፡ አምላክ ፡ ይክበርና ፡ ይመስገን ፡ በጣም ፡ ደኅና ፡ ነኝ ። ውድ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ በዓለም ፡ ተገናኝተን ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ እስክንጫወት ፡ ድረስ ፡ ይህችን ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ የተባለች ፡ ትንሽ ፡ ደብዳቤ ፡ እጽፍልህ ፡ ዘንድ ፡ ሕሊናየ ፡ አነሳሣኝ ፡

ብለህ ፡ የጻፍክልኝ ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ ፤ ተመለከትኩት ። ይልቁንም ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ በዓለም ፡ ተገናኝተን ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ እስክንጨዋወት ፡ ድረስ ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ የትባለች ፡ ይችን ፡ ትንሽ ፡ ደብዳቤ ፡ እጽፍልህ ፡ ዘንድ ፡ ሕሊናዬ ፡ አነሳሣኝ ፡ የሚለውን ፡ ጽሑፍ ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ። ወንድሜ ፡ ምን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ሊጽፍልኝ ፡ ምን ፡ መንፈስ ፡ አነሳሥቶት ፡ ይኾን ፡ በማለት ፡ ደብዳቤህን ፡ እስካነባትና ፡ ካንተ ፡ እስክንገናኝ ፡ በጣም ፡ ቸኩዬ ፡ ነበረ ። ብመለከተው ፡ ግን ፡ እንዳሰብኩት ፡ ሳይኾን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደ ፡ አርዮስ ፡ ፍጡር ፡ ደኅራዊ ፤ ወዳጆቹ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክትን ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታትን ፡ ጣዖታት ፤ ወበኀቤየሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ክቡራን ፡ አዕርክቲከ ፡ እግዚኦ ፡ የምትል ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምለኪተ ፡ ጣዖት ፡ የሚል ፡ ከእውነት ፡ ጋራ ፡ ያልተያያዘ ፡ ሐሰትን ፡ ብቻ ፡ የተመረገዘ ፡ ኾኖ ፡ ባገኘው ፡ በጣም ፡ አዘንኩ ፤ ያነሳሣህም ፡ መንፈስ ፡ ጽርፈት ፡ እንደኾነ ፡ ተገነዘብኩ ።

ስለዚህ ፡ ተገናኝተን ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ መነጋገራችንስ ፡ ይቅርና ፡ ጽሑፍህንም ፡ መመልከቱ ፡ አሰቀቀኝ ። ቢኾንም ፡ የሀገራቸውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክና ፡ የተቀደሰ ፡ ተዋህዶ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ንጹሕ ፡ ምግባራቸውን ፡ ያልተረዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ወጣቶች ፡ ምንአልባት ፡ አሉ ፡ እንደኾነ ፤ ያንተን ፡ ሐሰት ፡ ያባቶቻቸውን ፡ እውነተኛነት ፡ ይረዱበት ፡ ዘንድ ፡ መልሱን ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፤ ሐሰቱን ፤ ሐሰት ፡ እያልኩ ፡ እጽፍልሃለሁና ፡ ጠንቅቀህ ፡ ተመልከት ።

www.ethiopianorthodox.org



፪ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ እምነትን ፣ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚመስሳትና ፡ የሚተካከላት ፡ ነገር ፡ (ጥበብ) ፡ እንደሌለ ፡ ኹላችንም ፡ ማወቅ ፡ ያገባናል ፡ ሰውም ፡ የተፈጠረው ፡ የእምነት ፡ ባለቤትና ፡ አገልጋይ ፡ እንዲኾን ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

አንተ ፡ አላወቅሃትም ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚተካከላት ፡ የለም ፡ ስለዚህም ፡ የጠቀስከው ፡ ኢዮ ፡ ፳፰ ፡ ፲፪—፳፰ ፡ ጥበብ ፡ ወዴት ፡ ትገኛለች ፤ የማስተዋልስ ፡ ቦታ ፡ ወዴት ፡ ነው ፤ እያለ ፡ መጥቶ ፡ በመጨረሻው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ጥበብ ፡ ነው ፡ ከኀጢአትም ፡ መራቅ ፡ ማስተዋል ፡ ነው ፡ ይላል ።

አንተ ፡ ከፍሬ ፡ ነገሩና ፡ ከሥራው ፡ አልደረስክበትም ፡ እንጂ ፡ ኢዮብ ፡ የተናገረውስ ፡ እውነት ፡ ነው ።

፫ ስለዚህ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደሚነግሩን ፡ የሚታመነው ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ የፈጠረው ፡ አምላክ ፡ ብቻው ፡ ከልኾነ ፡ ክርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ክቶ ፡ የሚታመን ፡ የለም ፡ ማር ፡ ፲፪ ፡ ፳፰—፴፪ ፡ ስለጠቀስከው ።

አንተ ፡ ከሥራውና ፡ ከፍሬ ፡ ነገሩ ፡ አልደረስክበትም ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ እህል ፡ ተቋጥሮ ፡ ቢቀመጥ ፡ እስካልከው ፡ ድረስ ፡ አንተ ፡ አልፈጸምከውም ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ።

፬ እህል ፡ ተቋጥሮ ፡ ቢቀመጥ ፡ አይጠቅምም ፤ ተፀጥሮና ፡ ተፈጭቶ ፡ ተነፍቶና ፡ ተቦክቶ ፡ ተጋግሮ ፡ ቢበላ ፡ ግን ፡ ሕይወትነቱ ፡ ይታወቃል ፡ እንደዚሁ ፡ እምነትም ፡ መኖሯ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ፡ ህላዌዋን ፡ የሚያስታውቅ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ የሚታይ ፡ የሚበላ ፡ ሕያው ፡ ምግባር ፡ ሊኖርባትና ፡ ሊገኝባት ፡ ይገባል ፡ ያልሆውና ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ እምነት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ከእንስሳት ፡ ጸታ ፡ ካልኾነ ፡ በሰብእነት ፡ ጸታ ፡ ገብቶ ፡ ሊቈጠር ፡ ክቶ ፡ አይቻልም ። መዝ ፡ ፵፱ ፡ ፳ ፡ ስለምትለው ።

እነሆ ፡ ሃይማኖት ፡ መኖሯን ፡ የሚያሳውቅ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ሕያው ፡ ምግባር ፡ ማለት ፡ ድውይ ፡ መፈወስ ፡ ሙት ፡ ማስነሣት ፡ ጋኔን ፤ ማስወጣት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ማዓርግም ፡ የሚደረሰው ፡ በርሱ ፡ አምኘ ፡ እኖራለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ እንደሔደው ፡ ሊሔድ ፤ እርሱ ፡ እንደ ፡ ኖረው ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ እንዳስረዳን ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፯ ፤ ሆድ ፡ ማምለክን ፡ ትቶ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ሳይሹ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ በቁመት ፡ ተወስኖ ፡ በመኖር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ልጄን ፡ ጋኔን ፡ እየጣለ ፡ ያመዋል ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቶችህ ፡ ዘንድ ፡ ብወስደው ፡ ሊያድኑት ፡ አልቻሉምና ፡ አንተ ፡ አድንልኝ ፡ ብሎ ፡ በለመነው ፡ ጊዜ ፤ እላንት ፡ ተጠራጣሪዎች ፤ እናንት ፡ አሉተኞች ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ከናንት ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ፤ እስከመቼ ፡ ድረስስ ፡ እታገሣችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ተቈጥቶ ፡ ሕፃኑን ፡ አስመጥቶ ፡ ካዳነው ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ቀርበው ፡ እኛ ፡ ጋኔኑን ፡ ማስወጣት ፡ ያቃተን ፡ ስለምንድን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ ስለሃይማኖታችሁ ፡ ጐደሎነት ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ነቅ ፡ የሌለበት ፡ ፍጽምት ፡ ሃይማኖት ፡ ካለቻችሁ ፡ ይህነን ፡ ተራራ ፡ ከዚህ ፡ ተነሥተህ ፡ ወደዚያ ፡ ሒድ ፡ ብትሉት ፡ ይደረግላችኋል ፡ የሚሳናችሁ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ባላጋራ ፡ ሰይጣን ፡ ካልጾሙ ፡ ካልጸለዩ ፡ አይወጣም ፡ በማለቱ ፡ የሃይማኖት ፡ መገለጫው ፡ ሕያው ፡ ምግባር ፤ ጾም ፡ ጸሎት ፡ መኾናቸው ፡ ታውቋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ከዚህ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ለኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖቷ ፡ መታወቂያና ፡ መገለጫ ፡ ጾምን ፤ ጸሎትን ፤ ሰጊ ድን ፤ ቁመትን ፤ ሕግ ፡ ሥርዓት ፡ አድርጋ ፡ በዚያው ፡ ስትጓዝ ፡ ትታያለች በዚህም ፡ ሥራዋ ፡ ከግእዘ ፡ እንስሳ ፡ ወጥታ ፡ በግእዘ ፡ መላእክት ፡ ጸንታ ፡ ት ኝበታለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ የሃይማኖትን ፡ ህላዌዋን ፡ የሚያስታውቅ ፡ የሚበላ ፡ ምግባር ሊኖርበት ፡ ይገባል ፡ ብለህ ፡ እንደተናገርከው ፤ ጾምን ፤ ጸሎትን ፤ ሰጊድን ፤ ቁመ ትን ፤ ንጽሕናን ፤ ድንግልናን ፡ ብሕትውናን ፡ ምንኵስናን ፤ አምዘግዝገህ ፡ ጥለህ መብላትን ፤ መጠጣትን ፤ መጋባትን ፤ ወደሥራ ፡ መሠማራትን ፤ ብቻ ፡ ሕግ ፡ አድ ርገህ ፡ በመያዝህ ፡ በግእዘ ፡ እንስሳ ፡ ጸንተህ ፡ ትታያለህ ።

እንግዲህ ፡ ከሥራው ፡ ሳይገኙ ፡ እየተሻሙ ፡ ጥቅሶችን ፡ ያለአገባብ ፡ በመ ጠቃቀስ ፡ ክርስቲያን ፡ መኾን ፡ አይገኝምና ፡ በእውነቱ ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖት ካለችህ ፤ ብቻዋን ፡ አትጠቅምህምና ፡ የሚያንቀሳቅሳት ፡ ሕያው ፡ ምግባር ፡ ልት ሠሩላት ይገባሃል ።

፮ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ በእምነት ፡ ከዓለም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ የፈተና ፡ ወጥመድ ፡ አምልጠ ፡ በሞት ጊዜም ፡ የተስፋና ፡ የደስታ ፡ ዕረፍት ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላል ፡ ስለምትለው ፡

እምነትን ፡ በበጎ ፡ ምግባር ፡ ካልገለጹዋት ፡ በእምነት ፡ ብቻ ፡ የተስፋና የደስታ ፡ ዕረፍት ፡ ሊገኝ ፡ አይቻልም ። እንዲህማ ፡ ከኾነ ፡ ጻድቃንን ፡ በቀኙ አቁሞ ፡ ብራብ ፡ አብልታችሁኛል ፡ ብጠማ ፡ አጠጥታችሁኛል ፡ ብታረዝ ፡ አል ብሳችሁኛል ፡ ወደኔ ፡ ኑ ፡ ይላቸዋል ። ኃጥአንን ፡ በግራ ፡ አቁሞ ፡ ብራብ ፡ አላ በላችሁኝም ፡ ብጠማ ፡ አላጠጣችሁኝምና ፡ ከኔ ፡ ወግዱ ፡ ይላቸዋል ፡ ለምን አለን ፤ አምናችሁብኛልና ፡ ወደኔ ፡ ኑ ። ክዳችሁኛልና ፡ ከኔ ፡ ራቁ ፡ ወግዱ ፡ ይለ ቸዋል ፡ አይለንም ፡ ኖሯልን ፡ ተው ፤ አስተውል ። ማቴ ፡ ፳ ፳፭ ። ያዕ ፡ ፪ ፡ ፲-፳፯ ።

፯ የተዋደድህ ፡ ወንድሜ ፡ ምእመን ፡ ሆይ ፡ የዘመኑ ፡ ልጆች ፡ ዕድላችን ፡ ኾኖ ፡ እግዚአብሔር ፩ሳላ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ግን ፡ ማሠርና ፡ መፍታት ፡ በሚለው ፡ አርእስት ፡ በ፲፫ተኛው ፡ ምዕራፍ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ቊጥሩና ፡ ባህሉ ፡ ስሙም ፡ ከጽ ፡ እስከ ፡ ፴፬ይነት ፡ ይኾናል ። ስለምትለው ።

የማሠርንና ፡ የመፍታትን ፡ ነገር ፡ በቦታው ፡ እጽፍልሃለሁ ። ቊጥሩና ፡ ባህሉ ፡ እየ በዛ ፡ የሔደበት ፡ ምክንያት ፡ ግን ። ልዩንና ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ከአበው ፡ ከነቢያት ተያይዞ ፡ የወረደውን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያዘዘውን ፡ ሐዋርያት ፸ አርድእት ፤ ፫፻፲፰ ፤ ሊቃውንት ፤ የወሰኑትን ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ሳያፋልሱ ፡ በትርጓሜ ፡ አስተያየት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ አካል ፤ ፪ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ቢለያዩም ፡ በየሊቃነ ፡ ጳጳሳቶቻቸው ፡ ሥር ፡ በሕገ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽር ፡ ውስጥ ፡ ተሰብስበው ፡ ይገኛሉ ። ልባቸው ፡ ባሰበው መንገድ ፡ እንዳይሔዱም ፡ አበው ፡ የደነገጉት ፡ ሕግ ፡ የወሰኑት ፡ ሥራት ፡ እንዳጥር እንደ ፡ ቅጥር ፡ ይወስናቸዋል ፡ ይገታቸዋል ። ም[illegible]



በሕርያቸው ፡ ደክሞ ፡ ሕጉን ፡ ተላልፈውና ፡ ተረማምደው ፡ ቢገኙ ፡ ኃጢአት ፡ መኾኑን ፡ አውቀው ፡ ይጸጸቱበታል ፡ ንስሐ ፡ ይገቡበታል ፡ እንጂ ፡ በጎ ፡ እንደሠሩ ፡ አድርገው ፡ አይመኩበትም ፡ በዚያው ፡ አይጸኑበትም ።

ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ እንደተናገርከው ፡ በ፲፭፻፲፪ ፡ ዓ. ም. ከመምህር ፡ ሳያ ገኝ ፡ ከራሱ ፡ አንቅቶ ፡ በሕግ ፡ ሳይኾን ፡ በድፍረት ፡ ከአበው ፡ ከነቢያት ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ውን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የፈጸመውን ፤ ሐዋርያት ፤ ፸አርድእት ፤ ፫፻፲፰ ፤ ሊቃው ንት ፤ የወሰኑትን ፡ የደነገጉትን ፡ 1512 ፡ ዘመን ፡ የተሠራበትን ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነቅሮ ፡ አምዘግዝጎ ፡ ጥሎ ፡ መዳን ፡ በእምነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ምግባር ፡ ለእምነት ፡ መግለጫ ፡ የምልክት ፡ ያህል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለምንም ፡ አይረባም ፡ አይጠቅምም ። በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በልታ ችሁ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ጹሙ ፤ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተግባረ ፡ ሥጋችሁን ፡ ሠርታችሁ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተግባረ ፡ ነፍሳችሁን ፡ ያዙ ፤ የሚቻላችሁ ፡ ከኾነ ፡ ከሴት ፡ ርቃ ችሁ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቃችሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መስላችሁ ፤ በንጽሕና ፡ በድንግ ልና ፡ በተባሕትዎ ፡ በምንኵስና ፡ ብትኖሩ ፡ የበለጠ ፡ ክብር ፡ ታገኛላችሁ ፡ የምትል ፡ ጠባቧን ፡ በር ፡ ጠባቧን ፡ ጐዳና ፤ ወደቀኝ ፡ ትታችሁ ፡ ማጣትና ፡ ጥጋብ ፡ ካልከለከ ላችሁ ፡ ጊዜ ፡ ሳትወስኑ ፡ ዘወትር ፡ ብሉ ፡ ጠጡ ። ድካም ፡ ካልከለከላችሁ ፡ ዘወትር ፡ ተግባረ ፡ ሥጋችሁን ፡ ያዙ ፤ በምትል ፡ በስተግራ ፡ ባለችቱ ፡ በሰፊይቱ ፡ በር ፡ ግቡ ፡ ለዘ ርዕ ፡ ማድረጊያ ፡ ዐባለ ፡ ዘርዕ ፡ እያለችሁ ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ በተባሕትዎ ፡ በምንኵስና ፡ ብትኖሩ ፡ ዕዳ ፡ ይኾንባችኋል ፡ ብሎ ፡ ካስተማረ ፡ ወዲህ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ጠባቡን ፡ በርና ፡ ሰፊውን ፡ በር ፡ ቀኙንና ፡ ግራውን ፡ መንገድ ፡ ለይታችሁ ፡ የምታውቁበት ፡ አእምሮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሳይነሳችሁ ፡ የሉተር ፡ ትምህርት ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ለመፈጸም ፡ ተስማሚ ፡ ኾኖ ፡ ስላገኛችሁት ፡ ወደዚያው ፡ አዘንብላችሁ ፤ ራሳችሁን ፡ አታለላችሁ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽርና ፡ ክልል ፡ ወጥታችሁ ፡ የሕግ ፡ ክልል ፡ የሥርዓት ፡ ወሰን በሌለው ፡ ሜዳዊ ፡ ሕግ ፡ ዐውታሩዋን ፡ እንደበ ጠሰች ፡ በቅሎ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋችሁ ፡ እንዳዘዛችሁ ፡ ስትፈልሉ ፡ ትታያላችሁ ። የሚወስናችሁ ፡ የሥርዓት ፡ ዐጥር ፡ ቅጥር ፡ የሚገታችሁ ፡ የሕግ ፡ ልጓም ፡ ከማጣ ታችሁ ፡ የተነሣ ፡ የማኅበራችሁና ፡ የባህላችሁ ፡ ቊጥር ፡ በየቀኑ ፡ እየበዛ ፡ ሲሔድ ፡ ይታያል ።

ወደሀገራችን ፡ ያልመጡት ፡ እኛ ፡ የማናውቃቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህል ፡ ያላቸው ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ማኅበሮች ፡ ይቅርና ፡ ወደ ፡ ሀገራችን ፡ የገቡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህል ፡ ያላቸው ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ማኅበሮች ፡ ቊጥር ፡ እየበዛ ፡ ሔዷል ፡ እኒ ኸውም ።

፩ ሠራዊተ ፡ ክርስቶስ ፡ ሚሲዮን ።
፪ ስዊድን ፡ ወይም ፡ ከነሻ ፡ ሚሲዮን ።
፫ ሱዳን ፡ እንተሪዮር ፡ ሚሲዮን ።
፬ ፡ መኖሚኒት ፡ ሚሲዮን ፡
[illegible] ኖርዌጅን ፡ ሚሲዮን ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፡ አሜሪካን ፡ ሚሲዮን ።
፯ ፡ ወችታዎር ፡ ሚሲዮን ። ወይም ፡ ጆሆባ ።
፰ ፡ አድቤንቲስት ፡ ሚሲዮን ።
፱ ፡ የ፯ ፡ ቀን ፡ አድቤንቲስት ፡ ሚሲዮን ።
፲ ፡ ከሙኒስት ፡ ሚሲዮን ።
፲፩ ፡ ባፕቲዝም ፡ ሚሲዮን ፡ እሊህንም ፡ የመሳሰሉ ፡ ናቸው ።

እንግዲህ ፡ መምህሩ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲኾን ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማ ኖት ፡ ቀኖናንና ፡ ባህሉን ፡ ያብዛዘው ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ከተደነገገው ፡ ሕግ ከተወሰነው ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ እየኖሩ ፡ እንደልብ ፡ መዝናናት ፡ መኾኑ ፡ ከታ ወቀ ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ ወቅሶና ፡ መክሮ ፡ በሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽር ውስጥ ፡ ከመወሰን ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ መድኃኒት ፡ የሌለው ፡ መኾኑ ፡ የታ መነ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ነው ።

፰ ሌሎች ፡ የፈጠራ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ደግሞ ፡ ከህደት ፤ ጥንቈላ ፡ ፊሎሶፊ ፤ አስትሮኖሚ ፤ ማተማቲክ ሳይንስ ፤ ፖለቲካ ፡ ናቸው ። መጨረሻው ፡ ወይም ፡ ዋናቸው ፡ እነራስ ፡ አቶማቲክ ፡ የሚባሉ ፡ ዓለምን ፡ ሲ ሳልፉ ፡ የሚችሉ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ከጭንቅና ፡ ጥርጣሬ ፡ እያደረሱ ፡ የሚያስቸግሩ ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ላይ ፡ ያልተመሠረቱ ፡ በተጥባበ ፡ ሰብእ ፡ ለጊዜው ፡ የቆሙት ፡ ብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ በዓለም ፡ ሞልተዋል ስለምትለው ።

እኒህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የቈጠርኳቸው ፡ በሕሊና ፡ የሚወጡ ፡ የሚወርዱ ሐሳቦችና ፡ ተግባረ ፡ እዶች ፡ ከሃይማኖት ፡ ገብተው ፡ የሚቈጠሩ ፡ ከኾነ ፤ በ ኛም ፡ ሀገር ፡ ያሉ ፡ የልቡና ፡ ሐሳቦች ፡ ባሕረ ፡ ሐሳብ ፡ መቍጠር ፤ ቅኔ መንገር ፤ ተግባረ ፡ እዶች ፤ እርሻ ፡ ማረስ ፤ ቁጢት ፡ መበጠስ ፤ ብረት ፡ መጨ ፍለቅ ፤ ቁርበት ፡ መፋቅ ፤ ጦር ፡ ማሾል ፤ ሰይፍ ፡ መሳል ፤ እኒህን ፡ የመሳሰሉ ሥራዎች ፡ ኹሉ ፤ ሃይማኖት ፡ መኾናቸው ፡ ነው ።

እኔ ፡ የማጭለብለብህን ፡ ብዛት ፡ አይቼ ፡ የቁም ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ መስ ኸኝ ፡ የሃይማኖትና ፡ የምግባር ፡ ስልት ፡ ስልታቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሲኾን ፡ ለምን ተደበላለቁ ፡ ጥቅሶችስ ፡ ለምን ፡ ተዘበራረቁ ፡ ብዬ ፡ ፈርጀብህ ፡ ነበረ ። ለካስ ገና ፡ እህልና ፡ አፈር ፡ ያለየህ ፡ ሕፃን ፡ አእምሮ ፡ ኖረሃል ። እንግዲህ ፡ ምን ይሻላል ፤ እንዳያስተምሩህ ፡ መምህር ፡ ነኝ ፡ አልክ ፤ እንዳይመክሩህ ፡ አዋቂ ነኝ ፡ አልክ ። እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ በዐይነ ፡ ልቡናህ ፡ ላይ ፡ ተመርጎ ለማየት ፡ የከለከለህን ፡ የድንቁርና ፡ ሞራ ፡ ገፎ ፡ ጥሎ ፡ ምሥጢረ ፡ መጻሕፍ ትን ፡ ለማየት ፡ ቃለ ፡ መምህራንን ፡ ለመስማት ፡ ያብቃህ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ላደርግ ፡ እችላለሁ ።

እናንተ ፡ ወንድሞቼ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ሆይ ፡ የልማድና ፡ የድን ርና ፡ መጋረጃ ፡ ገልጾ ፡ ቃሉን ፡ ሊያቀምሳችሁ ፡ ወዶ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ጸጋ ፡ ተቀብላችሁ ፡ ከመንፈስ ፡ የተወለዳችሁ ፡ ኾናችሁ ፡ ከቅዱስ ፡ መጽሐፍ ጋራ ፡ ሊያስተዋውቃችሁ ፡ ያሰበላችሁ ፡ መምህር ፡ የመምህርነቱ ፡ ደረጃ ፡ የት ርቱ ፡ እርምጃ ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ መኾኑን ፡ ከ



ከጻፍኩላችሁ ፡ ከበቶቻችሁ ፡ ከወረሳችኋት ፡ ከተጣራችቱ ፡ ከኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይ ማኖታችሁ ፡ እንዳትነዋወጡ ፡ ከሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳትወጡ ፡ መላ ልሼ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ።

የነፊሎሶፊን ፡ የነአስትሮኖሚን ፤ የነማተማቲክን ፤ የነሳይንስን ፤ የነፖለቲክን ፤ የነራስ ፡ አቶማቲክን ፡ ትርጉም ፡ እንዳልነግራችሁ ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ እናንተ ፡ አብ ልጣችሁ ፡ የምታውቁት ፡ ስለኾነ ፡ የእነዚህን ፡ ትርጉም ፡ ለእናንተ ፡ ለወጣቶች ፡ መንገር ፡ እንደርሱ ፡ መኾን ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አልፌዋለሁ ።

፱ ስለዚህ ፡ በዓይነ ፡ ልቡናህ ፡ ወንፊት ፡ በእዝነ ፡ ልቡናህ ፡ ወንጠፍት ፡ ስካበትና ፡ ኹሉንም ፡ አምላክ ፡ በሰጠህ ፡ ብርሃን ፡ አእምሮ ፡ ነፋፍተህና ፡ አጣርተህ ፡ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ሚክሮስኮብ ፡ ነጽረህ ፡ አይተህ ፡ ኡነቱን ፡ ከሐሰት ፡ ለይተህ ፡ እመን ፡ እንጂ ፡ አዋቂዎች ፡ ነን ፡ እያሉ ፡ ፍሬ ፡ የማይገኝበትን ፡ የማይታይና ፡ የማይጨበጥ ፡ ረቂቅ ፡ ወሬ ፡ ኹሉ ፡ ሳትመረምር ፡ ማመን ፡ ብቻ ፡ አትኹን ፡ ስለምትለው ።

እነሆ ፡ አዋቆች ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ብለህ ፡ መምህራንን ፤ ፍሬ ፡ የማይገኝበት ፡ የማይ ታይና ፡ የማይጨበጥ ፡ ረቂቅ ፡ ወሬ ፡ ኹሉ ፡ ብለህ ፡ መጻሕፍትን ፡ ነቅፈሃቸዋል ፤ አምዘግዝገህ ፡ ጥለሃቸዋል ። እንግዲህ - በዐይነ ፡ ልቡና ፡ የሚደረገው ፡ ወንፊት ፡ በእዝነ ፡ ልቡና ፡ የሚሰካው ፡ ወንጠፍት ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይኾን ? ሴቶች ፡ ከስን ደዶና ፡ ካክርማ ፡ የሰፉት ፡ ወንፊትና ፡ ወንጠፍት ፡ ነውን ፤ ወይስ ፡ ከሸበ ፡ የተ ሠራ ፡ ይኾን ፡ እስኪ እባክህ ፡ ንገረኝ ? እኛስ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚናገሯቸው ፡ መም ህራን ፡ የሚያስተምሯቸው ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ ባይን ፡ የማይታዩ ፡ በእጅ ፡ የማይጨ በጡ ፡ ረቂቅ ፡ ዜናዎች ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢሮች ፡ መኾናቸውን ፡ እናምናለን ፡ ይህ ንም ፡ በሚከተሉት ፡ ነገሮች ፡ አስረዳሃለሁ ።

፩ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ከወኅና ፡ ከመንፈስ ፡ ዳግመኛ ፡ ያልተወለደ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አያይም ፡ ብሏልና ፡ ብትጠመቁ ፡ ከሥላሴ ፡ ረቂቅ ፡ ልደት ፡ ትወ ለዳላችሁ ፡ ብለው ፡ መምህራን ፡ ያስተምራሉ ። ይህ ፡ የማይታይ ፡ የማይጨ በጥ ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። ይህን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አዎን ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ ያልተጠመቀ ፡ ሰው ፡ ክርስቲያን ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

፪ተኛ ፡ ቀሳውስት ፡ መጽሐፍ ፡ ዝኅብስት ፡ ሥጋየ ፡ ውእቱ ፡ ዝጽዋዕ ፡ ደምየ ፡ ውእቱ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፤ ይህ ፡ ኅብስት ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ይህ ፡ ወይን ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያቀብላሉ ፡ ዐይን ፡ የሚያ የው ፡ እጅ ፡ የሚዳስሰው ፡ ኅብስት ፡ ወይን ፡ ሲኾን ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ የክ ርስቶስ ፡ ደም ፡ ነው ፡ ማለት ፡ የማይታይ ፡ የማይጨበጥ ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ፡ ይህን ፡ አዎን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ ካልተቀበሉት ፡ ክርስ ቲያንነት ፡ አይገኝም ።

፫ተኛ መጽሐፍ ፡ ወይወጽኡ ፡ እለ ፡ ሠናየ ፡ ገብሩ ፡ ውስተ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለሕይወት ፡ ወእለሰ ፡ እኩየ ፡ ገብሩ ፡ ውስተ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለደይን ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ መምህራን ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ ከተቀበረ ፡ ከፈረሰ ፡ ከበሰበሰ ፡ በኋላ ፡ ... ተዋሕደውለት ፡ አካል ፡ ገዝቶ ፡ ይነሣል ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ፡ የማይታይ ፡ የማይጨበጥ ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ፡ ይህን ፡ አዎን ፡ እ ነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያላመነ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

ይህነንም ፡ ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ አጕልተው ፡ የሚያሳዩ ፡ መነጽሮች ፡ ለብሉያት ፡ ሐዲሳት ፤ ለሐዲሳት ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ። ብሉያት ፡ ወመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጼልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ።

የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ ይሰፋል ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

ወእነዝኀክሙ ፡ በማይ ፡ ንጹሕ ፡ ኪመ ፡ ትንጽሑ ፡ እምርኵስክሙ ፡ ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፳፭

ከርኵሳችሁ ፡ ትነጹ ፡ ዘንድ ፡ በንጹሕ ፡ ውኃ ፡ ረጫችኋለሁ ፡ ብለው ፡ የተናገ ቸው ፡ ቃላት ፡ በብሉይ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ምሥጢሩ ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ሳይታወቅ ይኖር ፡ ነበረ ፡

ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ዘኢተወልደ ፡ እማይ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይክል ፡ በዊአ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ።

ከውኃና ፡ ከመንፈስ ፡ ያልተወለደ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ሊያይ አይችልም ፡ ብሎ ፡ አጉልቶ ፡ አሳይቷል ።

ይህም ፡ ረቆበት ፡ እንደ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ይህ ፡ ሊደረግ ፡ እንደምን ፡ ይቻላል የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሊቅ ፡ ጾረ ፡ ኃጢአት ፡ ዘአመ ፡ ይህድና ፡ ውስተ ፡ ነቅዐ ጥምቀት፡ አስጠምኩ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

በአይሁዳዊነት ፡ ሳለሁ ፡ ተሸክሜው ፡ የነበረውን ፡ የኃጢአት ፡ ትብትብ ፡ ሸክም በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ተጠምቄ ፡ አውልቄ ጣልኩት ፡ ብሎ ጥምቀት ፡ ከኃጢአት ፡ መለቀቂያ ፡ የልጅነት ፡ ማግኛ ፡ መኾኑን ፡ አጉልቶ ፡ አሳይቷል (ተረ ፡ ቄር ፡ ሳዊሮ) ።

፪ለተኛም ፡ ብሉያት ፡ ቀዳሜ ፡ ሕይወቱ ፡ ለሰብእ ፡ እክል ፡ ወማይ ፡ ወ ወስርናይ ። ሲራ ፡ ፴፱ ፡ ፳፤ ።

የሰው ፡ የሕይወቱ ፡ መጀመሪያ ፡ መገኛ ፡ እኽልና ፡ ውኃ ፡ ስንዴና ፡ ወይን ነው ፡ ሲራ ።

ወወደይከ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ እምፍሬ ፡ ስርናይ ፡ ወወይን ወቅብዕ ። መዝ ፡ ፬ ፡ ፯ ።

ከስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ፍሬ ፡ የተነሣ ፡ በልቡናችን ፡ ደስታ ፡ አሳ ርክብን ፡ ያሉት ፡ ቃል ፡ በብሉይ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ምሥጢሩ ፡ ምን ፡ እንደኾነ ሳይረዱት ፡ ይኖሩ ፡ ነበረ ።

ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ግን ፡ ዝኅብስት ፡ ሥጋየ ፡ ውእቱ ፡ ዝጽዋዕ ፡ ደምየ ፡ ውእቱ ብሎ ፡ አጉልቶ ፡ አሳይቷቸዋል ። ይህንም ፡ በብሉይና ፡ በሐዲስ ፡ የተነገረውን ፡ ረቂቅ ምሥጢር ፡ ሊቅ ፡ አኮ ፡ በከ ፡ በከመ ፡ ትሬእይዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ ከመ ፡ ኅብስ ምድራዊ ፡ አላ ፡ እሳተ ፡ መለኮት ፡ ውእቱ ። አይ ፡ አፍ ፡ ዘይትፌዐም ፡ ዘንተ ፡ ኅ ስተ ፡ ወአይ ፡ አሥናን ፡ ዘየሐይክ ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ ፡ ወአይ ፡ ከርሥ ፡ ዘያገምር



ዘንተ ፡ ኅብስተ ፡ ወይእዜኒ ፡ ንበል ፡ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ ፡ በከመ አበሳነ ። አባ ፡ ሕርያ ።

ይህ ፡ ኅብስት ፡ እሳተ ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደምታዩት ፡ እንደ ፡ ምድ ራዊ ፡ ኅብስት ፡ ብላሽ ፡ አደለም ፤ ይህን ፡ ኅብስት ፡ የሚጐርስ ፡ አፍ ፡ ምን ፡ አፍ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ኅብሰት ፡ የሚያኘክ ፡ ጥርስ ፡ ምን ፡ ጥርስ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ኅብስት ፡ የሚችል ፡ ኾድ ፡ ምን ፡ ኾድ ነው ። ስለዚህ ፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እንደ ፡ ይቅ ርታህ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፤ አጽናን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ኃጢአታችን ፡ ብዛት ፡ አደለም፡ እንበል ፡ በማለቱ ፡ አጉልቶ ፡ አሳይቷል ። የብሉይ ፤ የሐዲስ ፤ የሊቅ ፤ አካሔዳቸው፡ እንዲህ ፡ የተየያዘ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የተለያየ ፡ አይደለም ። ምናልባት ፡ እንዲህ ፡ የተ ያያዙ ፡ አንድ ፡ መኾናቸውን አነጻጽሮ ፡ ሊያይ ፡ የማይችል ፡ ዐይነ ፡ ደካማ ፡ ቢኖርም ፡ ብሉይን ፤ ሐዲስን ፤ ሊቅን ፤ አጠራቅመው ፡ በምዕራፍና ፡ በቍጥር ፡ አገናኝተው ፡ ንባባቸውን ፡ ከንባባቸው ፡ ምሥጢራቸውን ፡ ከምሥጢራቸው ፡ አገናዝበው ፡ አጉል ተው ፡ የሚያሳዩ ፡ ማይክሮስኮፖች ፡ መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡ ተወስነው ፡ አንገታ ቸውን ፡ አቀርቅረው ፡ ዐይናቸውን ፡ አፍዘው ፡ የሚኖሩ ፡ መምህራን ፡ ናቸው ።

ስለዚህ ፡ በእዝነ ፡ ልቡና ፡ የሚሰካው ፡ ወንጠፍት ፡ ቃለ ፡ መምህራን ፤ በዐይነ፡ ልቡና ፡ የሚዘረጋው ፡ ወንፊት ፡ በሰቂለ ፡ ሕሊና ፡ በነቂሐ ፡ ልፁና ፡ ሰምቶ ፡ ማስ ተዋል ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። እነዚህንም ፡ በዓይነ ፡ ልቡናው ፡ ዘርግቶ ፡ በእዝነ፡ ሕሊናው ፡ ሰክቶ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠው ፡ እውቀት ፡ አበጥሮና ፡ አጣርቶ ፡ መጻሕፍትን ፡ የተመለከተ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ፈለከ ፡ ፈለካትን ፡ ዐየረ ፡ ዐየራትን፡ ወደ ፡ ታች ፡ ዕመቀ ፡ ዕመቃትን ፡ መርምሮ ፡ ሊያውቅ ፡ ይችላል ።

እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ መምህራንን ፡ ሊቃውንትን ፡ ነቅፎ ፤ አምዘግዝጎ ፡ ጥሎ ፡ መጻሕፍትን ፡ አተኵሮ ፡ በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ምሥጢረ ፡ መጻሕፍትን ፡ እረዳለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ በከንቱ ፡ ዐይኑን ፡ ያፈዛል ፡ ወረቀቱን ፡ ይቀዳል ፡ እንጂ ፡ የመጻሕ ፍትን ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ሊረዳ ፡ አይችልም ። ይልቁንም ፡ ስንኳን ፡ ተማርኩ ፡ የሚል ፡ ዐዋቂ ፤ ጡተ ፡ ጣል ፡ ሕፃን ፡ የማይናገረው ፤ አስትሮኖሚ፡ ማተማቲክ ፤ ሳይ ንስ ፡ ፖለቲክ ፤ ፊሎሶፍ ፡ አቶማቲክ ፡ ሃይማኖት ፡ ናቸው ፡ ከማለት ፡ ይደርሳል ። በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ሕሊናዬ ፡ የማይደርስበት ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ስለ ኾነ ፡ ከማውቀው ፡ ይልቅ ፡ የማላውቀው ፡ ይበዛል ፡ እንዲሉ ፡ ያደርጋል ። ገጽ ፡ ፷፬ መስ ፡ ፫ ፡ ተመልከት ።

፤ ሌላው ፡ ኹሉ ፡ ይቅርና ፡ ከሰማይ ፡ የወረደችው ፡ የወንጌል ፡ ፀሐያዊት ፡ እምነትም ፡ ብትኾን ፡ የላይ ፡ ብላቷንና ፡ የውስጥ ፡ እንጀቷን ፡ እንብበህ ፡ መርምረህ ፡ ከመጻሕፍተ ፡ ሐሰት ፡ እውነተኝነትዋን ፡ ሳትረዳት ፡ በልማድ ፡ ብታምናት ፡ አትረባህም ፡ ስለምትለው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሊቃውንት ፡ ማይክሮስኮፕነት ፡ የወንጌልን፡ የላይ ፡ ብልቷን ፡ የውስጥ ፡ አንጀቷን ፡ መርምራ ፡ አይታ ፡ ከመጻሕፍተ ፡ ሐሰት ፡ እውነተኝነቷን ፡ ተረድታ ፡ ያመነች ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ በልማድ ፡ ያመነች ፡ አደለችም ፡

www.ethiopianorthodox.org

የወንጌል ፡ ተቃራኒ ፡ የኾኑ ፡ የጥንቈላ ፡ መጻሕፍቶችን ፡ ኹሉ ፡ አጥብቃ ፡ ትቃ ማለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጽሕት ፡ ዘርዕ ፡ ወንጌልን ፡ በ ለም ፡ ላይ ፡ ዘርቶ ፡ ካረገ ፡ በኋላ ፡ የወንጌል ፡ ተቃራኒ ፡ ሐተታ ፡ መናፍስት ፡ የ ባለ ፡ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍ ፡ እንክርዳድ ፡ ወንጌል ፡ በተዘራችበት ፡ ዓለም ፡ ላይ ደርበህ ፡ ስትዘራ ፡ በግልጥ ፡ ትታያለህ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፳፬ ፡ - ፴፩ ፡ ተመልከት ።

ስለዚህ ፡ አንተ ፡ የወንጌልን ፡ የላይ ፡ ብልቷን ፡ የውስጥ ፡ አንጀቷን ፡ አልተ ዳኸውም ፡ ቢባል ፡ እውነት ፡ እንጂ ፡ ሐሰት ፡ አይባልም ። እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ከ ራው ፡ ሳትገኝ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደች ፡ ፀሐያዊት ፡ ወንጌል ፡ እያልክ ፡ ስትሸቅጥ ሰምቶ ፡ ሌላው ፡ በወንጌል ፡ ቢያምን ፡ አንተን ፡ የፋና ፡ የገንዳ ፡ ነገር ፡ ያገኝሃል ፡ እንጂ የሚጠቅመኝ ፡ መሰለህን ?

ፋና ፡ በብርሃኑ ፡ ሌላው ፡ ሲጠቀምበት ፡ እርሱ ፡ አመድ ፡ ኾኖ ፡ ያልቃል ፤ ገ ዳም ፡ እርሱ ፡ ያጠራቀመውን ፡ ውኀ ፡ ሌላው ፡ ጠጥቶ ፡ ሲጠቀምበት ፡ ራሱ ፡ ይ ርቃል ፡ ይበሰብሳል ። አንተም ፡ እንደዚያ ፡ እንዳትኾን ፡ ተው ፡ ተጠንቀቅ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፱ ፡ ፳፯ ።

፲፩ ውድ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ከፉ ፡ ከሚመስልህ ፡ ኹሉ ፡ ሽሽ ፡ ካልከው ፡ ጀምሮ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅ ከተማ ፡ ተጻፈ ፡ እሳከሚለው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ።

የኢትዮጵያን ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖቷን ፡ ሥነ ፡ ምግባሯን ፡ የማይነካ ፡ የ ክር ፡ ቃል ፡ ብቻ ስለኾነ ፡ የምክር ፡ ቃልን ፡ ሰምቶ ፡ የሚቀበል ፡ ይቀበለዋል የሚተው ፡ ይተወዋል ፡ በማለት ፤ መልስ ፡ አልሰጠሁበትም ።

## ምዕራፍ ፬ ቅዱስ መጽሐፍ ።

፩ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ መጽሐፍ ፡ አይደለም ፡ እርሱ ፡ በመለኮታ ጥበቡ ፡ በቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ አድሮ ፡ በመንፈሱ ፡ እየመራ ፡ አስጽፎና ፡ ለዘለዓለም ፡ ጠብቆ ፡ እያስፋፋው ፡ ራል ፡ ፪ ጴጥ ፡ ፩ ፳ ፳፩ ። ፪ ጢሞ ፫ ፲፮ ፲፯ ይህ ፡ መልእክት ፡ ለዘለዓለማዊ ። ሕይወትና ፡ መድኃኒት ፡ ስብ እንዲኾን ፡ ብሎ ፡ ለፍጥረቱ ፡ ኹሉ ፡ ከሀሌ ፡ ኩልንቱ ፡ እንዲገለጽና ፡ ወደ ፡ እውነተኛው ፡ አምልኮ ፡ እ መጣ ። የላከው ፡ መልእክት ፡ ነው ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፲፱ ፳ ። ፩ ጢሞ ፪ ፱ ። ቲቶ ፪ ፲፩ ፲፭ ስለምትለው ።

ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ እግዚአብሔር ፡ በመለኮታዊ ፡ ጥበቡ ፡ በቅዱሳን ሰዎች ፡ አድሮ ፡ በመንፈስ ፡ እየመራ ፡ ማጻፉና ፡ እያስፋፋው ፡ መኖሩ ፡ የማይካድ የታመነ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በገጽ ፡ ኹለት ፡ በመሥመር ፡ ከ፲ - ፲፱ ፡ አባቶቻችን ፡ ፫፻፲ወ፰ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በ፪ተኛው አንቀጽ ፡ መጻሕፍት ፡ ፹ወ፩አምላካውያት ፡ የተዉልን ፡ ጠፍተው ፡ ያልከውንና በገጽ ፡ ፯ በመሥመር ፡ በ፲፯ና ፡ በ፲፯ ፡ አባቶቻችን ፡ ፫፻፲ወ፰ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ የ ዉልን ፡ ፹ወ፩ ብቻ ፡ ይበቁናል ፡ ያልከውን ፡ ዘንግተህ ፡ በገጽ ፡ ፯በመሥመር ፡ ከ - ፯ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ የብሉይ ፡ አዋልድ ፡ አፖክራፌ ፡ ስለኾ ከ፹ወ፩ ፤ ፲፬ቱን ፡ ትሩፋት ፡ ብለው ፡ ለምስክርነት ፡ አይቀበሏቸውም ፡ ያልከውን ብቻ ፡ ተከትለህ ፡ ከ፹ወ፩ ፡ ፲፭ቱን ፡ ገንጥለህ ፡ ጥለህ ፡ ፷፯ቱን ፡ ብቻ ፡ ጠርዞ



መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለትህን ፡ አጥብቄ ፡ እቃወማለሁ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የጻፍከውን ፡ ኹሉ ፡ አልቃወምም ።

ያንተ ፡ ወገኖች ፡ አንዳንድ ፡ ሚሲዮናውያንስ ፡ እንዲያውም ፡ ከነዚኽውም ፡ ከነ፷፯ቱም ፡ ሊቀንሱላቸው ፡ ወደው ፡ ከኒሁ ፡ ከ፷፯ ፡ ውስጥ ፡ ሐሳባቸውን ፡ የሚያፈ ርስ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ የሚቃወም ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ሲገጥማቸው ፡ ይህስ ፡ ሰው ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ አንቀበለውም ፡ የሚሉ ፡ ይገኛሉ ።

አንተም ፡ ምንም ፡ በመለኮታዊ ፡ ጥበቡ ፡ በቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ አድሮ ፡ በመን ፈሱ ፡ እየመራ ፡ አጻፋቸው ፡ ብለህ ፡ ብታምንም ፡ አካሔድህን ፡ አተኵሮ ፡ ሲመለከ ቱት ፡ ከነዚያ ፡ ልዩነት ፡ የለህም ።

ከነዚያ ፡ ልዩነት ፡ የለህም ፡ ያልኩበትም ፡ ምክንያት ፡ ለጊዜው ፡ ሐሳብህን ፡ የሚገድፉልህ ፡ ኾነው ፡ ስታገኛቸው ፡ ፫፻ት ፡ ያልቈጠሯቸውን ፡ መልክ ፡ መልኮችንና ፡ ቅኔዎችን ፡ ያዝማሪዎች ፡ ግጥም ፡ ሳይቀሩ ፡ እየጠቀስክ ፡ ሐሳብህን ፡ የሚቃወሙብህ ፡ ሲኾኑ ፡ ፫፻ት ፡ የቈጠሯቸውንም ፡ የብሉይ ፡ አፖክራፊዎች ፡ ናቸው ፡ ለምስክርነት አይበቁም ፡ በማለትህ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አምላክነት ፡ ከሚናገሩ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ ይህም ፡ አዋልድ ፡ ነው ፡ አልቀበለውም ፡ ማለት ፡ የተሳሳተ ፡ ንግግር ፡ መኾኑን ፡ ትረዳው ፡ ዘንድ ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ አጻጻፍ ፡ ለይቼ ፡ ለይቼ ፡ እጽፍልሃለሁና ፡ በዓይነ ፡ ሥጋህ ፡ ተመልክተህ ፡ በዓይነ ፡ ሕሊናህ ፡ አስተውለው ።

እግዚአብሔር ፡ አድሮ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ያጻፋቸው ፤ የሚያጽፋቸው ፡ ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ ፫ት ፡ ክፍል ፡ ናቸው ፡ በ፫ ፡ ይከፈላሉ ። የጽሑፋቸው ፡ ዓላማም ፡ ፫ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

እኒኽውም ፡ ጸሐፍቱ ፡ ነቢያት ፤ ሐዋርያት ፤ ሊቃውንት ፡ ናቸው ፤ ዐላማቸ ውም ፡ የነቢያት ፡ ትንቢት ፤ የሐዋርያት ፡ ስብከት ፤ የሊቃውንት ፡ ትርጓሜ ፡ ነው ።

### ፩ኛ ፡ ክፍል ።

### ጸሐፍቱ ፡ ነቢያት ፡ የጽሕፈቱ ፡ ዓላማ ፡ ትንቢት ።

አዳም ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በልቶ ፡ ልጅነቱን ፡ አስወስዶ ፡ ሞተ ፡ ሥጋ ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ ከተፈረደበት ፡ በኋላ ፡ ንስሐ ፡ ቢገባም ፡ ቢያለቅስም ፡ በአምስት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ ወዳንተ ፡ መጥቼ ፡ ከልጅ ፡ ልጅህ ፡ ተወልጄ ፡ አድንሃለሁ ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ ከመስማቱ ፡ በቀር ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በአዳም ፡ ፍዳ ፡ ተይዞ ፡ በሠዋው ፡ መሥ ዋዕት ፡ በጸለየው ፡ ጸሎት ፡ መዳን ፤ የኸደች ፡ ልጅነቱን ፡ ማስመለስ ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ክብሩ ፡ መመለስ ፡ ስላቃተው ፡ ኵሉ ፡ ዐረየ ፡ ወኀቡረ ፡ ዐለወ ። አልቦ ፡ ዘይገብራ ፡ ለሠናይት ፡ አልቦ ፡ ወኢአሐዱ ።

ኹሉ ፡ ተካክሎ ፡ በደለ ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ የሚሠራት ፡ አንድ ሰው ፡ ስንኳ ፡ የለም ፡ መዝ ፡ ፲፬ ፡ ፫ ። ወከነ ፡ ጽድቅነ ፡ ከመ ፡ ፀርቀ ፡ ትክቶ ፡ የሠራነው ፡ ትሩ

www.ethiopianorthodox.org

ፋት ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ኾነ ፡ ኢሳ ፡ ፷፬ ፡ ፮ ፡ እያሉ ፡ ይህን
በመሳሰለ ፡ ነገር ፡ ራሳቸውን ፡ እየወቀሱ ፡ እየከሰሱ ፡ እምነታቸውን ፡ በእግዚአብሔር
ላይ ፡ ጥለው ፡ አንሥእ ፡ ኃይለከ ፡ ወነዓ ፡ አድኅነነ ። ፈኑ ፡ ብርሃነከ ፡ ወጽድቀከ
እማንቱ ፡ ይምርሃኒ ፡ ወይሰዳኒ ፡ ደብረ ፡ መቅደስከ ። መዝ ፡ ፵፫ ፡ ፫ ። እያሉ ፡ ይህን
የመሳሰለ ፡ ጸሎት ፡ እያቀረቡ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ በቁመት ፡ ተወስነው
ቢገኙ ፡ በብዙ ፡ ኅብረ ፡ አምሳል ፡ እየታየ ፤ ብዙ ፡ ኅብረ ፡ ትንቢት ፡ እያናገረ ፡ በ
ድኤት ፡ አድሮ ፡ አጽፏቸዋል ።

ኅብረ ፡ አምሳል ፡ ለሙሴ ፡ በአምሳለ ፡ ነበልባል ፡ ወሐመልማል ፤ ለጌዴዎን
በአምሳለ ፡ ፀምር ፡ ወጠል ፤ ለዕዝራ ፡ በአምሳለ ፡ ነፋስ ፡ መፍርህ ፤ ለኢሳይያስ
በአምሳለ ፡ ብእሲ ፡ መከህ ፤ ለዳንኤል ፡ በአምሳለ ፡ ዕብን ፡ ቅውም ፡ መታየት ፡ ነው
ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፪-፮ ። ዘመሳ ፡ ፮ ፡ ፴፮-፵ ። ዕዝ ፡ ፲፫ ፡ ፪-፭ ።

ኅብረ ፡ ትንቢትም ፡ ነቢየ ፡ ያነሥእ ፡ ለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምአኃዊክሙ
ዘከማየ ፡ ወሎቱ ፡ ስምዕዎ ። እግዚአብሔር ፡ ከወንድሞቻችሁ ፡ መካከል ፡ እንደኔ
ያለ ፡ ነቢይ ፡ ያስነሣላችኋልና ፡ እሱን ፡ ስሙት ፡ ዘዳግ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭-፳ ።
ኮከብ ፡ ይሠርቅ ፡ እምያዕቆብ ፡ ወያአትት ፡ ኃጢአተ ፡ እምእስራኤል ። ኮከ
ከያዕቆብ ፡ ይወጣል ፡ ኃጢአትንም ፡ ከእስራኤል ፡ ያርቃል ፡ ዘኍል ፡ ፳፬ ፡ ፲፯ ።

ናሁ ፡ ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡ ወልደ ፡ ወትሰምዮ ፡ ስሞ ፡ አ
ኑኤል ። እነሆ ፡ ድንግል ፡ በድንግልና ፡ ፀንሳ ፡ በድንግልና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ት
ልዳለች ፡ ስሙንም ፡ አማኑኤል ፡ ትለዋለች ። ኢሳ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። ይህን ፡ የመሰለ
ኹሉ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ኹሉ ፡ ትንቢት ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ያ፭ሽ ፡ ፭፻ኛውንም ፡ ዘመን ፡ ሱባዔ
ኄኖክ ፡ በትውልድ ፤ ኤርምያስ ፡ በዕለት ፤ ዳንኤል ፡ በሰንበት ፡ ቈጥረውታል ፡ በ
ቢያት ፡ አድሮ ፡ ያጻፋቸው ፡ የብሉያት ፡ ዐላማቸውና ፡ ግባቸው ፡ ይህ ነው ።

## ፪ተኛ ክፍል ።

ጸሐፍት ፡ ሐዋርያት ፤ የጽሒፈቱ ፡ ዓላማ ፤ የነቢያት ፡ ትንቢት ፡ መፈጸሙን ፡ መግለጽ ነው
(ሀ) ጌታ ፡ ሰው ፡ በሚኾንበት ፡ ወራት ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ልኮ ፡ ኢሳይያስ ፡ ድንግ
በድንግልና ፡ ፀንሳ ፡ በድንግልና ፡ ትወልዳለች ፡ ብሎ ፡ የተናገረላት ፡ ድንግል ፡ ቅ
ስት ፡ ማርያም ፡ መኾኗን ፡ ትፀንሲ ፡ ወትወልዲ ፡ ወልደ ፡ ብሎ ፡ ገልጦታል
ሉቃ ፡ ፩ ፳፮-፴፱ ።
(ለ) በቤተ ፡ ልሔም ፡ በተወለደ ፡ ጊዜም ወትወልድ ፡ ወልደ ፡ ብሎ ፡ ኢሳ
ያስ ፡ የተናገረለት ፡ ልጅ ፡ ከቅድስት ፡ ማርያም ፡ የተወለደ ፡ ክርስቶስ ፡ መኾኑን ፤ ናሁ
ተወልደ ፡ ለክሙ ፡ ዮም ፡ መድኅን ፡ ዘውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ ቡሩክ ፡ በሀገረ
ዳዊት ፡ ብሎ ፡ ለኖሎት ፡ በመንገሩ ፡ ገልጦታል ፡ ሉቃ ፡ ፪ ፲፩ ።
(ሐ) ወደ ፡ ምኵራብ ፡ ገብቶ ፡ መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስን ፡ እንዲያነብ ፡ በሰጡት
ጊዜ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለርሱ ፡ የተናገረለትን ፡ መን...

www.ethiopianorthodox.org



ንቲአሁ ፡ ቀብዐኒ ፡ እዜንዎሙ ፡ ለነዳያን ፡ ፈነወኒ ፡ እስብክ ፡ ሎሙ ፡ ግእዛነ ፡ ለዓ
ዉዋን ፡ ወይርአዩ ፡ ዕውራን ፡ ወአንግፎሙ ፡ ለግፉዓን ፡ ወእስብክ ፡ ዓመተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ኅሪተ ፡ የሚለውን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ አንብቦ ፡ ሲፈጽም ፡ ዮም ፡ በጽሐ ፡
ቃለ ፡ ዝንቱ ፤ መጽሐፍ ፡ ወተሠልጠ ፡ ውስተ ፡ እዘኒክሙ ፡ ብሎ ፡ ነቢያት ፡ ትንቢት ፡
የተናገሩለት ፡ ሱባዔ ፡ የቈጠሩለት ፡ ርሱ ፡ መኾኑን ፡ አስረድቷል ፡ ሉቃ ፬ ፲፰-፳፪ ።

(መ) አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ወአነ ፡ ተፈኖኩ ፡ ብሎ ፡ ነቢያት ፡ ፈኑ ፡ ብርሃነከ ፡ ወጽ
ድቀከ ። ፈኑ ፡ እዴከ ፡ እምዓርያም ፡ እያሉ ፡ የጸለዩት ፡ ጸሎት ፡ ግዳጅ ፡ መፈጸሙን ፡
አስረድቷል ። መዝ ፵፫ ፫ ። ፻፵፬ ፯ ።
(ሠ) ፲፱ቱን ፡ ሐዋርያት ፡ መርጦ ፡ በመሾሙ ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ገብኤ ፡ ሠርቶ ፡
በማስተማሩም ፡ ኤርምያስ ፤ ወይመጽእ ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ዘእኑ ፡ ርኢኩ ፡
ሥግወ ፡ ወይከይድ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወየኀሪ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ ፡ ሐዋርያተ ፡ ብሎ ፡
የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ መፈጸሙን ፡ አስረድቷል ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ነቢያት ፡ ትንቢት ፡ የተናገሩለት ፡ ሱባዔ ፡ የቈጠሩለት ፡ የዓ
ለሙ ፡ መድኃኒት ፡ መሲሕ ፡ ክርስቶስ ፡ ርሱ ፡ መኾኑን ፡ በመለኮታዊ ፡ ኃይሉ ፡ በማ
ይታበል ፡ ቃሉ ፡ ካስረዳቸው ፡ በኋላ ፡ በምሴተ ፡ ኀሙስ ፡ ጰራቅሊጦስን ፡ እሰድላች
ኋለሁ ፡ እኔ ፡ የምሰድላችሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ዛሬ ፡ የነገርኋችሁን ፡
ኹሉ ፡ ያሳስባችኋል ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፳፮ ።

በሞቱ ፡ ዓለምን ፡ አድኖ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃ
ብር ፡ አድሮ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ፵ ቀን ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳንን ፡ አስተምሯቸው ፡ ሲያ
ርግ ፡ አነ ፡ እፌኑ ፡ ተስፋሁ ፡ ለአቡየ ፡ ላዕሌክሙ ፡ አንትሙሰ ፡ ንበሩ ፡ ሀገረ ፡ ኢየ
ሩሳሌም ፤ እስከ ፡ ትለብሱ ፡ ኃይለ ፡ እምዓርያም ። አባቴ ፡ ያናገረላችሁ ፡ ተስፋ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እሰድላችኋለሁና ፡ ሰማያዊ ፡ ኃይልን ፡ ሰማያዊ ፡ ዕውቀትን ፡ ገንዘብ ፡
እስክታደርጉ ፡ ድረስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ኾናችሁ ፡ ደጅ ፡ ጽኑ ፡ ብሏቸው ፡ ዐረገ ።
ዮሐ ፡ ፳፭ ፡ ፳፭ ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፰ ፡ ፵፱ ።

ባረገ ፡ ባሥረኛው ፡ ቀን ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ
ስን ፡ ላከላቸው ። መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብለው ፡ በአእምሮ ፡ ኀለመሱ ፡ በዕውቀት ፡
ታደሱ ፤ በ፸፪ ፡ ቋንቋ ፡ ተናገሩ ፤ ከዚያ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ፃዕፈ ፡ ጸግቡ ፡ እሉ ፡ ወሰ
ክሩ ። ጉሽ ፡ ጠጥተው ፡ ሰክረው ፡ ይቀባጥራሉ ፡ ቢሏቸው ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተነሥቶ ፡
እግዚአብሔር ፡ በኢዩሔል ፡ አድሮ ፡ በሥጋዊ ፡ በደማዊ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስን ፡ አሳድርበታለሁ ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ ልጆቻችሁ ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፡
ራእይ ፡ ያያሉ ፤ ሕልም ፡ ያያሉ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ቢደርስ ፡ ቢፈጸም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
እናንተ ፡ እንደምትሉት ፡ ሰክረው ፡ አደለም ፡ አላቸው ።

ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ ጋኔን ፡ እያወጣ ፡ ድውይ ፡ እየፈወሰ ፡ ሙት ፡ እያነሣ ፡ መለኮ
ታዊ ፡ ሥልጣኑን ፡ ቢያሳያችሁ ፡ እናንተ ፡ ዐምፃችሁ ፡ ኃጥእ ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ስቅላ
... ሁትን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አባቱ ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ አስነሣው ፡

በቀኙ ፡ አስቀመጠው ፤ እግዚእ ፡ መሲሕ ፡ አደረገው ፤ ብሎ ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር እየጠቀሰ ፡ ቢያስረዳቸው ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ አመኑ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፩—፵፩

፪ተኛም ፡ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ ወደምኵራብ ፡ ሲገቡ ፡ ከናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ልምሾ ኾኖ ፡ ተወልዶ ፡ ከምኵራቡ ፡ ደጅ ፡ ወድቆ ፡ ምጽዋት ፡ ሲለምን ፡ ያኖር ፡ የነበረውን በሽተኛ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ የለኝም ፡ ካለኝ ፡ ግን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ በናዝሬቱ ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተነሥ ፡ ብለው ፡ እጁን ፡ ይዘው ፡ አስነሡት ። በሽተኛው ፡ በመዳኑ እየተገረሙ ፡ ሐዋርያትን ፡ በማድነቅ ፡ ሲመለከቷቸው ፡ ሳለ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በእኛ ኃይል ፡ በእኛ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳዳነው ፡ አድርጋችሁ ፡ ለምን ፡ ትመለከቱናላችሁ የአባቶቻችን ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በተአምራት ፡ ቢገልጠው ፡ ነው ፡ እንጂ በእኛ ፡ ኃይል ፡ አደለም ፡ ብሎ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነቱን ፡ ከሙሴ ፡ ከነቢያት ፡ መጻ ፍት ፡ እየጠቀሰ ፡ ቢያስረዳቸው ፡ ፭ሺ ፡ ሰዎች ፡ አመኑ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፫ ፡ ፩—ም ፡ ፬ ፡ ፭

በኹለት ፡ ቀን ፡ ስብከት ፡ ፰ሺህ ፡ ሰዎች ፡ አመኑ ፡ በ፲ ፡ ቤትና ፡ ፲ ፡ ቤት የሚቈጠሩ ፡ በየቀኑ ፡ የሚያምኑትስ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ። እሊህ ፡ ኹሉ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እየኖሩ ፡ እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መከሪ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ኾነው ፡ ቢያስተምሩ ፡ አሪት ፡ እየጠበበች ፡ ወንጌል ፡ እየሰፋች ፡ ሔደች ። ግብ ሐዋ ፡ ፬ ፡ ፴፩—፴፬ ። ፮ ፯ ።

አይሁድ ፡ ግን ፡ ቅናት ፡ ምቀኝነት ፡ ስለያዛቸው ፡ ተስፋ ፡ ያልደረሰውን ፡ ተስፋ ደረሰ ፤ ሥጋ ፡ ያለበሰውን ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፡ ትላላችሁ ፡ ብለው ፡ እስጢፋኖስን ፡ በ ራከሩት ፡ ቀድሞም ፡ አሪትን ፡ ሲማር ፤ ያደገ ፡ ኋላም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የታደለ ስለኾነ ፡ ሱባዔ ፡ ትውልድ ፡ የኄኖክን ፤ ሱባዔ ፡ ዕለት ፡ የኤርምያስን ፤ ሱባዔ ፡ በት ፡ የዳንኤልን ፤ እየቈጠረ ፡ ሱባዔውን ፡ ከዘመኑ ፡ ምሳሌውን ፡ ከግብሩ ፡ ትን ቱን ፡ ከነገሩ ፡ እያስማማ ፡ ቢነግራቸውና ፡ ቢረታቸው ፡ እንዲያውስ ፡ አንተን ፡ ባፍ በመጣፍስ ፡ ማን ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ በደንጋይ ፡ ወግረው ፡ ገደሉ ።

ከዘመነ ፡ አበው ፡ ፭ሺ ፡ ፯ ፡ ፵፱ ፡ አጐደሉ ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ እንደ ወንጌል ፡ አምልተው ፡ አስፍተው ፡ አጕልተው ፡ የሚናገሩ ፡ መጻሕፍትን ፡ እነኄኖክን እነኩፋሌን ፡ እነተረፈ ፡ ኤርምያስን ፡ እሊህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ መጻሕፍት ፡ ገነጣ ለው ፡ ጣሉ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፮ ፡ ፱ ። ፯ ፡ ፩—፰ ። የአለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ መዝ ፈደ ፡ ገጽ ፡ ፶፰ ፡ ተመልከት ።

ስምንቱ ፡ ሺህ ፤ ማኅበርም ፡ በሞተ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ተበተኑ ። በየተሰደዱ ትም ፡ ሀገር ፡ እየተከተሉ ፡ መከራ ፡ ስለአጸኑባቸው ፡ መከራውን ፡ ተሰቀው ፡ ሃይ ኖታቸውን ፡ እንዳይክዱ ፡ ሲያጽናኗቸው ፡ ጴጥሮስ ፡ ፪ ፡ መልእክት ፡ ዮሐንስ ፡ ያዕቆብ ፡ ፩ ፡ ይሁዳ ፡ ፩ ፡ መልእክት ፡ እየጻፉ ፡ ሰደውላቸዋል ።

ጌታም ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ያስተማራቸው ፡ ወንጌልን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሳሰባቸው ፡ ማቴዎስ ፡ ጌታ ፡ ባረገ ፡ በ፱ ፡ ማርቆስ ፡ ጌታ ፡ ባረገ ፡ በ፲፩ ፡ ሉቃስ ጌታ ፡ ባረገ ፡ ፳፩ ፡ ዮሐንስ ፡ በ፴ ፡ ጽፈዋል ።



ሉቃስም ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያትን ፡ ለመኰንነ ፡ እስክንድር ፡ ታዮፊላ ፡ ጽፎ ፡ ሰጥቶታል ።

ዮሐንስም ፡ በደሴተ ፡ ፍጥሞ ፡ ኾኖ ፡ ምሥጢረ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ምሥ ጢረ ፡ ዘመናት ፡ ተገልጾለት ፡ ቀለምሲስን ፡ ጻፈ ።

እኒህንም ፡ መጻሕፍቶች ፡ ሲጽፉ ፡ አይሁድ ፡ ከቍጥር ፡ አውጥተው ፡ ገነ ጣጥለው ፡ ያጠፏቸው ፡ መጻሕፍትን ፡ በቂ ፡ ምስክር ፡ እያደረጉ ፡ ጠቅሰዋቸዋል ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ይሁ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።

ነገር ፡ ግን እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ ሲጽፉ ፡ አይሁድ ፡ ለአሪታቸው ፡ አሕዛብ ፡ ለጣዖታቸው ፡ እየቀኑ ፡ በመቃወማቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፖለቲካ ፡ ትግል ፡ ስለነ በረባቸው ፡ የቃልሥጋ ፡ ከነን ፡ ነገር ፡ ለማስረዳት ፡ ብቻ ፡ ጻፉ ፡ እንጂ ፡ ለጊዜው ፡ አጋጥሟቸው ፡ ከጻፏቸው ፡ አልፈው ፡ አልፈው ፡ ከሚገኙ ፡ ጥቂቶች ፡ ቃላት ፡ በቀር ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አስተዳደር ፡ አልጻፉም ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፭ ፡ ፳፫-፴ ።

ጌታ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ሰው ፡ የመኾኑን ፡ ነገር ፡ የምትናገር ፡ ወን ጌልን ፡ ከስተማረ ፡ በኋላ ፡ ሞቶ ፡ ተነሥቶ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አስተዳደር ፡ በመጽሐፈ ፡ ኪዳን ፡ እንዳስተማረ ፡ ሐዋርያትም ፡ ጉባዔ ፡ አድርገው ፡ ምእመናን ፡ የቃል ፡ ሥጋ ከነን ፡ ምሥጢር ፡ ካመኑ ፡ ከተረዱ ፡ በኋላ ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ሕግና ፡ ሥራት ፡ ወስነዋል ።

ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ ሥርዓተ ፡ ጽዮን ፤ አብጥሊስ ፤ ግጽው ፤ ትእዛዝ ፡ ተብሎ ፡ በ፬ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ፡ ጠቅላላ ፡ ስሙ ፡ ሲኖዶስ ፡ ይባላል ። ፪ኛውም ፡ መጽሐፍ ፡ ዲዲስቅልያ ፡ ይባላል ። ወንጌልን ፡ ከጌታ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የተማሩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ የተቀበሉ ፡ ሐዋርያት ፡ የጻፏቸው ፡ መጻ ሕፍት ፡ እኒህ ፡ ናቸው ።

ጌታ ፡ በጌቴሴማኒ ፡ ባቀረበው ፡ ጸሎት ፡ ወአኮ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ዘእስእለከ ፡ አላ ፡ በእንተሂ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ ብየ ፡ በቃሎሙ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሰጠቱ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ላመኑበት ፡ ለ፻፳ ፡ ቤተ ፡ ሰብአች ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ከነርሱ ፡ ተምረው ፡ ለሚያምኑ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ለሚ ነሡ ፡ ምእመናን ፡ ኹሉ ፡ ስለኾነ ፡ ለአሪት ፡ ቀናሁ ፡ እያለ ፡ ምእመናንን ፡ በዋሉ በት ፡ አላሳድር ፡ ባደሩበት ፡ አላውል ፡ ይል ፡ የነበረ ፡ ጳውሎስ ፤ ጌታ ፡ ባረገ ፡ ባሥራ ፡ ዐራተኛው ፡ ዓመት ፡ በተአምራት ፡ አምኖ ፡ ከ፸ ፡ አርድእት ፡ ባንዱ ፡ በሐናንያ ፡ እጅ ፡ ተጠምቆ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ ሐዋርያት ፡ ከደረሱበት ፡ ማዓርግ ፡ ደርሷል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፩–፳፩ ። ገላ ፡ ፩ ፡ ፲፩-፳ ፡ ከሐዋርያትም ፡ አጻጻፍ ፡ ተረፍ ፡ አድርጎ ፡ ፲፬ ፡ ክታብ ጽፏል ። ስለቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አስተዳደር ፡ ስለጳጳሳት ፡ ስለቀሳውስት ፡ ስለዲያቆናት ፡ ስለዲያቆናዊት ፡ ጽፏል ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩-፲፱ ፡ ፭ ፡ ፱ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፮-፲ ፡ ሐዋርያትም ፡ ሲኖዶስንና ፡ ዲድስቅልያን ፡ ሲጽፉ ፡ በጉባኤው ፡ ተገ ኝቶ ፡ አንደኛ ፡ ኾኖ ፡ አብሮ ፡ ጽፏል ።

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሐዋርያት ፡ ብቻ ፡ የማይወሰን ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ለሚነሡ ፡ ምእመናን ፡ ኹሉ ፡ እየተሰጠ ፡ ሥራ ፡ ሲያሠራ ፡ የሚኖር ፡መኾኑን ፡ አስተውል ።

## የ፫ተኛው ፡ ክፍል ፡ ጸሐፍት ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ።

የጽሒፈታቸውም ፡ ዐላማ ፤ ብሉያትንና ፡ ሐዲሳትን ፡ እያስማሙ ፡ የተሰወረውን ፡ እየገለጹ ፡ አስፋፍቶ ፡ ከብሉያትና ፡ ከሐዲሳት ፡ ግብ ፡ ሳይወጡ ፡ መተርጐም ፡ ነው ። ኹለተኛም ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳደር ፡ ጌታ ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳን ፤ ሐዋርያት ፡ ሲኖዶስንና ፤ ዲዲስቅልያን ፡ እንደጻፉ ። ሊቃውንትም ፡ ጉባኤ ፡ እያደረጉ ፡ ጌታ ፡ በመጽሐፈ ፡ ኪዳን ፤ ሐዋርያት ፡ በሲኖዶስ ፡ ከወሰኑት ፡ ግብ ፡ ሳይወጡ ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳት ፤ ጳጳሳት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ፤ ዲያቆናት ፡ የሚሾሙበትን ፡ የሚሻሩበትን ፡ ሕግ ፡ ማገግ ፤ የአጽዋማትን ፡ የበዓላትን ፡ ሥራት ፡ መደንገግ ፤ በጠቅላላው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትተዳደርበትን ፡ ውስጠ ፡ ደንብ ፡ መወሰን ፡ ነው ።

ይህነንም ፡ ሲሠሩ ፡ ሐዋርያት ፡ ሲኖዶስን ፡ ሲጽፉ ፡ ምናልባት ፡ እኛ ፡ ያጐደልነው ፡ ቢኖር ፡ በኹላችንም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮብናልና ፡ እናንተ ፡ እንደሚገባ ፡ አድርጋችሁ ፡ ፍረዱ ፡ ያሉትን ፡ (ትእዛ ፤ ፷፩) ።

ኹለተኛም ፡ ወለእመ ፡ ተርፈ ፡ እምኔነ ፤ ምንትኒ ፡ ያዘክር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ። ከእኛ ፡ የቀረ ፡ ምንምን ፡ ቢኖር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ይፈጽም ፡ ይሥራ ፡ ያሉትን ። (ትእዛ ፡ ፴፫ ።)

፫ተኛም ፡ ወለእመ ፡ ተርፈ ፡ እምኔነ ፡ ምንትኒ ፡ አፍቁራን ፡ ለዝንቱኒ ፡ ይክሥቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘከነ ፡ ድልወ ፡ ወትትመራህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘ ይደሉ ፡ ኀበ ፡ መርሶ ፡ ወዘህን ።

የተወደዳችሁ ፡ ወንድሞቻችን ፤ ሆይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚገባ ፡ ወደ ፡ ፀጥታ ፡ ወደብ ፡ ትመራ ፡ ዘንድ ፡ (ማለት) ፡ በማይነዋወጽ ፡ ሕግና ፡ ሥራት ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ ከኛ ፡ የቀረ ፡ ምንምን ፡ ሥራት ፡ ቢኖር ፡ ይህን ፡ ከእኛ ፡ የቀረውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ ይግለጽለት ፡ ያሉትን ፡ (ትእዛ ፡ ፺፯ ።)

፬ተኛ ፡ በዲዲስቅልያ ፡ በ፬ተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፤ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ሲጽፉ ፡ እስመ ፡ ለክሙኒ ፡ ይቤለክሙ ፡ እግዚእነ ፡ ዘዐሠርክሙ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ ዕሡረ ፡ በሰማያት ፡ ወዘፈታሕክሙ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ ፍቱሐ ፡ በሰማያት ፡ ወፍትሑ ፡ በሥልጣን ፡ ከመ ፡ አምላክ ።

ጌታችን ፡ እናንተንም ፡ በምድር ፡ ያሠራችሁት ፡ በሰማይ ፡ የታሠረ ፡ ይኹን ፡ በምድር ፡ የፈታችሁትም ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይኹን ፡ ብሏችኋልና ፡ አምላክ ፡ በባሕርይ ፡ ሥልጣኑ ፡ እንዲፈርድ ፡ እናንተም ፡ በጸጋ ፡ ሥልጣናችሁ ፡ ፍረዱ ፡ ያላቸውን ፡ ይዘው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ በድፍረት ፡ አደለም ።



ሐዋርያትም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይህን ፤ ሥልጣን ፡ መስጠታቸው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ ፪ቱ ፡ ፴፫ቱ ፡ ጉብአን ፡ በስምየ ፡ ሀየ ፡ እሄሉ ፡ ማዕከሌሆሙ ።

በኔ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ኾነው ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ከመካከላቸው ፡ እገኛለሁ ፡ ያላቸውን ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳ ።

ወደሰማይም ፡ ሲያርግ ፡ ወናሁ ፡ አነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ በኵሉ መዋዕል ፡ እስከ ሕልቀተ ፡ ዓለም ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ አልለያችሁም ፡ ኹልጊዜ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ፡ ያላቸው ፡ ቃል ፤ እነሱ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ የማይኖሩ ፡ ስለኾኑ ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ስለሚነሡ ፡ መምህራን ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በራሳቸው ፡ ሐሳብ ፡ አደለም ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወለእለሰ ፡ ሤሞሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀዳሚ ፡ ሐዋርያተ ፡ ወዳግም ፡ ነቢያተ ፤ ወሣልስ ፡ መምህራነ ፡ ወእምዝ ፡ ዘትእምርት ፡ ወኀይል ፡ ወእምዝ ፡ ዘአሦት ፡ ወዘረድኤት ፡ ወአምህርት ፡ ወዘነገረ ፡ በሐውርት ።

መጀመሪያ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሾመ ፡ ሐዋርያትን ፡ ነው ። ኹለተኛ ፡ ፸ ፡ አርድእትን ፤ ሦስተኛ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሦስተኛውን ፡ ተራ አስይዞ ፡ ጽፏቸዋል ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰ ።

ድርሰታቸውንም ፡ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ሶበ ፡ ትትጋብኡ ፡ ኵልክሙ ፡ ብክሙ ፡ መዝሙር ፡ ወብክሙ ፡ ትምህርት ፡ ዘከሡተ ፡ አበይኖ ፡ ዘነገረ ፡ በሐውርት ፡ ወዘምድራሳት ።

አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ በተሰበሰባችሁ ፡ ጊዜ ፡ የምትጸልዩት ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ አለላችሁ ፡ በየቋንቋው ፡ ተለይቶ ፡ ተለይቶ ፡ የተገለጠ ፡ ትምህርትና ፡ በየጊዜው ፡ የተደረሱ ፡ ድርሰቶችም ፡ አሉላችሁ ፡ ብሏል ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፳፮ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብክሙ ፡ መዝሙር ፡ ብሎ ፡ ብሉያትን ፤ ብክሙ ፡ ትምህርት ፡ ብሎ ፡ ሐዲሳትን ፤ ወዘምድራሳት ፡ ብሎ ፡ ሊቃውንትን ፡ እንደ ፡ ቈጠረ ፡ አስተውል ።

አንተ ፡ የጠቀስከው ፡ ፪ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮ም ። መጽሐፍ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ተጽፏልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ምእመን ፡ በበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የተሠራ ፡ የተቀጣ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ በምግባር ፡ በትሩፋት ፡ ለመራቀቅ ፡ ይጠቅማል ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ የጠረዝካቸውን ፡ ፳፮ቱን ፡ ብቻ ፡ ለይቶ ፡ አልቈጠረም ። በሮም ፡ ክታቡም ፡ የተጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ኹሉ ፡ እኛ ፡ መጻሕፍት ፡ የነገሩንን ፡ አምነን ፡ መከራውን ፡ በመታገሣችን ፡ ተስፋችንን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ ተጻፈ ፡ ብሎ ፡ ኹሉንም ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ ለይቶ ፡ አልተዋቸውም ።

ስለዚህ ፡ እስመ ፡ ለክሙ ፡ ተውህበ ፡ አእምሮ ፡ ምሥጢራቲሃ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በለው ፡ መሠረት ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ።

ምሥጢረ ፡ መጻሕፍትን ፡ ምሥጢረ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገልጾላቸው ፡ ሊቃውንት ፡ መምህራን ፡ የጻፏቸው ፡ በጉባኤ ፡ የሚነበቡ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሚተረጐሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤ ቄርሎስ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፲፬ቱ ፡ ቅዳሴያት ፤ ፊልክስዩስ ፡ ማሪ ፡ ይስሐቅ ፤ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊም ፡ ፫፻ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ከቈጠራቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኹነው ፡ ይቈጠራሉ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ይባላሉ ፡ ይህ ፡ ምስጋና ፡ አብሮ ፡ ይደርሳቸዋል ። ይገባቸዋል ። እላለሁ ፡ እንጂ ፡ የተናገርከው ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አልቃወምህም ።

፲፪ ቅዱስ ፡ አጎስቲኖስ ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ሕሊናዬ ፡ የማይደርስበት ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ስለኾነ ፡ ከማውቀው ፡ ይልቅ የማላውቀው ፡ ይበዛል ፡ ይላል ፡ ስለምትለው ።

የብሉያትና ፡ የሐዲሳት ፡ ምሥጢር ፡ መክፈቻዎች ፡ እኒህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የቈጠርኩልህ ፡ ሊቃውንት ፡ መኾናቸውን ፡ ተረዳህልኝን ? መጻሕፍተ ፡ ሊቃውንትን ፡ ተመልክቶ ፡ ቢኾን ፡ እንዲህ ፡ ከማለት ፡ በዳነ ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ አጎስቲኖስ ፡ ደግ ፡ እውነተኛ ፡ ሰው ፡ ስለኾነ ፡ እውነቱን ፡ ገልጾ ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ እሊህ ፡ አንተ ፡ ባንድነት ፡ ጠርዘህ ፡ የያዝካቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ ይበቁኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ምሥጢር ፡ በአፍአ ፡ ያለ ፡ መኾኑን ፡ በዚህ ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ።

፲፫ እኔም ፡ ደግሞ ፡ ከማውቃቸው ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ቃላት ፡ አስከትዬ ፡ እጽፋለሁ ፡ ስለምትለው ።

በታላቅ ፡ ቅል ፡ ውሥጥ ፡ እንደ ፡ ተከተቱ ፡ ኹለት ፡ ቅንጣቶች ፡ ኹለት ፡ ቃላት ፡ እያንኳኳህ ፡ የዓለምን ፡ ጆሮ ፡ ከምታደነቁር ፡ በባሕረ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የሚያበሩ ፡ ዕንቍ ፡ ምሥጢራቸውን ፡ ለማየት ፡ እንዳትጠልቅ ፡ በላይ ፡ ያንከረፈህን ፡ ድፍን ፡ ቅል ፡ (ልዩ ፡ ባህል ፡) አውልቀህ ፡ ጥለህ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አስተርጕመው ፡ ባሳተሟቸው ፡ መጻሕፍት ፡ አትዋኝምን ? የሀገርህን ፡ መምህራንና ፡ ሊቃውንት ፡ አትጠይቅምን ? ለምን ፡ በኹለትና ፡ በሦስት ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ ትወሰናለህ ። ይህን ፡ አጻጻፍህንስ ፡ እንደኔ ፡ የተመለከተው ፡ ሰው ፡ ኹለቱና ፡ ሦስቱ ፡ ቃላትም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አሉ ፡ ለማለት ፡ አይደፍርም ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## ስለ ፡ አማላጅነት ።

፩ ወንድሜ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ይህንን ፡ የማያሳስት ፡ እውነተኛ ፡ የሕይወት ፡ መንገድና ፡ እርግጠኛ ፡ አማላጅ ፡ ትተህ ፡ ሌላ ፡ የስርቆሽ ፡ መንገድ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፩ ፡ የማይጠቅም ፡ ንኪር ፡ ባዕድ ፡ የፍጡር ፡ አማላጅ ፡ መፈጠርህ ፡ ምን ፡ ይባል ፡ ይኾን ፡ ስለምትለው ።

የፍጡር ፡ አማላጅነትን ፡ ትነቅፍ ፡ ዘንድማ ፡ ጥንቱንስ ፡ ማማለድ ፡ የፍጡራን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የፈጣሪ ፡ ሥራ ፡ መስሏሃልን ? ፈጣሪስ ፡ መማለድ ፡ እንጂ ፡ ማማለድ ፡ እንደሌለበት ፡ እወቅ ፡ የክርስቶስም ፡ አማላጅነት ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ አይደለም ፡ በቦታው ፡ አመጣልሃለሁ ፡ ይቆይ ።

፪ ንኪር ፡ ባዕድ ፡ አማላጅ ፡ ስለምትለው ።

በእውነተኛው ፡ በሕይወት ፡ መንገድ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመርቼ ፡ የደረስኩባቸውን ፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢይብለክሙ ፡ አግብርትየ ፡ አላ ፡ አዕርክትየ ። ወዳጆቼ ፡ እላችኋለሁ ፡ እንጂ ፡ ባሮቼ ፡ አልላችሁም ፡ ያላቸውን ። አንትሙ ፡ ትነብሩ ፡ ዲበ ፡ ፲ወ፪ ፡ መናብርት ፡ ወትኴንኑ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ። ዛሬ ፡ ሰው ፡ በኾንኩ ፡ ጊዜ ፡ ያመናችሁብኝ ፡ እናንተ ፡ ባሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ትፈርዳላችሁ ። በንፍሐት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳድሮ ፡ እናንተ ፡ ይቅር ፡ ያላችሁት ፡ ኀጢአቱ ፡ ይሠረይላት ፡ እናንተ ፡ ይቅር ፡ ያላላችሁት ፡ ኀጢአቱ ፡ አይሠረይለትም ፡ ብሎ ፡ ለሥልጣኑ ፡ ተካፋዮች ፡ ያደረጋቸውን ፡ ለርሱ ፡ አካል ፡ ማኅበር ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ሐዋርያትን ፡ ፸ ፡ አርድእትን ፡ እነሱን ፡ መስለው ፡ የተገኙ ፡ ቅዱሳንን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ አማላጅ ፡ አልፈጠርኩም ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫ ።

፫ ይህ ፡ ራስህ ፡ የፈጠርከው ፡ ስፊ ፡ ጠማማ ፡ የማያሳልፍ ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ ስሙ ፡ ልንግርህ ፡ ስማኝ ፡ ስሕተት ፡ ክህደት ፡ ድንቁርና ፡ ልማድ ፡ ፍጻሜው ፡ (መድረሻው ፡) የዘለዓለም ፡ ጥፋት ፡ ይባላል ፡ ኤር ፡ ፳ ፡ ፯ ። ፲፯ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ስለምትለው ።

ከኤርምያስ ፡ ለጠቀስካቸው ፡ መልሱን ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ በሚገኙት ፡ መሥመሮች ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ጠብቅ ።

ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ፡ የጠቀስከው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ወደጥፋት ፡ የምትወስድ ፡ ሰፊ ፡ በር ፡ ሰፊ ፡ ጐዳና ፡ አለች ። ወደርሷ ፡ የሚገቡም ፡ እጅግ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ደግሞ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ የምታደርስ ፡ ጠባብ ፡ ጐዳና ፡ አለች ። ወደርሷ ፡ የሚገቡም ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸውና ፡ ሰፊውን ፡ በር ፡ ሰፊውን ፡ ጐዳና ፡ ትታችሁ ፡ ወደ ፡ ጠባቧ ፡ በር ፡ ግቡ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ አልቀረም ። ርሱ ፡ ራሱ ፡ ፊት ፡ ፊታችንን ፡ በጠባቧ ፡ መንገድ ፡ እየሔደ ፡ ወደ ፡ ጠባቧ ፡ በር ፡ ገብቶ ፡ ኑ ፡ በዚች ፡ መንገድ ፡ ተከተሉኝ ፡ ብሎ ፡ ጠባቧን ፡ በር ፡ አሳይቶናል ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሔደባት ፡ ጠባብ ፡ በር ፡ ጠባብ ፡ ጐዳና ፡ ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ ጎጆ ፡ ሳይሠራ ፡ በድንግልና ፡ መኖር ፤ ገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ገብቶ ፡ በተባሕትዎ ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ መጾም ፤ ወዙ ፡ እንደ ፡ ደም ፡ በዝቶ ፡ እስኪወርድ ፡ ድረስ ፡ መላልሶ ፡ መስገድና ፡ ሌሎችንም ፡ እኒህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ትሩፋት ፡ መሥራት ፡ መኾኑ ፡ አይካድም ።

እንግዲህ ፡ ካንተና ፡ ከእኛ ፡ በዚች ፡ ጠባብ ፡ በር ፡ ለመግባት ፡ ጠባቧን ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ በጭር ፡ ታጥቆ ፡ ሲጓዝ ፡ የሚታይ ፡ ማነው ? የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይደለችምን ።

አንተማ ፡ ይህችን ፡ የምታውቁትን ፡ ዓለም ፡ በማታውቁት ፡ ዓለም ፡ ለውጡ ፤ ሥጋዊ ፡ ፍትወታችሁን ፡ በጾም ፤ እግራችሁን ፡ በቀዊም ፤ እጃችሁን ፡ በሰፊሕ ፡ ሥሩ ፡ ቅጡ ፡ የምትል ፤ ጠባቧን ፡ በር ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ትተህ ። ወደ ፡ ግራ ፡ ባለችቱ ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ከገነት ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በሔዱባት ፡ ጾም ፡ የለም ፡ ብሉ ፡ ጠጡ ፤ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ አግቡ ፡ ተጋቡ ፤ በምትሊቱ ፡ በሰፊዋ ፡ መንገድ ፡ ሕግ ፡ ካልተሠራላቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ስትንሸረሸር ፡ የምትታይ ፡ አይደለህምን ።



www.ethiopianorthodox.org

ምነው ፡ ይሉኝታን ፡ እንዲህ ፡ ጨርሰህ ፡ ዕርም ፡ ብለህ ፡ ተውካት ። የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በማጭበርበር ፡ በማስመሰል ፡ የምትገኝ ፡ መሰለህን ። ተው ፡ እባክህ ፡ በነገርህ ፡ እንዲህ ፡ ብል ፡ እንዲህ ፡ ይሉኛል ፡ ማለትን ፡ ጨምርበት ።

እንግዲህ ፡ ስሕተት ፤ ክህደት ፡ ድንቁርና ፤ ልማድ ፤ ፍጻሜው ፡ የዘለዓለም ፡ ጥፋት ፡ ማለት ፡ ይህች ፡ አንተ ፡ የምትኖርባት ፡ ሕግ ፡ መኾኗን ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ።

፬ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ ብታስበውስ ፡ ያንተውን ፡ ዕዳ ፡ ሊከፍል ፡ ብሎ ፡ ኃጢአትህን ፡ ያንተው ፡ መስቀል ፡ በቀራንዮ ፤ ተሸክሞ ፡ አባ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ ብሎ ፡ እየጸለየ ፡ ተሰቅሎልህ ፡ የዋለው ፡ ማን ፡ ይመስልሃል ፡ ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፩—፲፪ ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ፡ ስለምትለው ።

እዝነ ፡ ሥጋ ፡ እንጂ ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፡ የሌለህ ፡ አንተ ፤ እዝነ ፡ ልቡና ፡ ያለን ፡ እኛን ፡ የማናውቅ ፡ የማንሰማ ፡ አስመስለህ ፡ ትጠየቀናልህ ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነሥአ ፡ ደዌነ ፡ ወጾረ ፡ ሕማመነ ።

ደዌያችን ፡ ወሰደ ፡ መከራችንን ፡ ተሸከመ ።

መጽአ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ ይጠባሕ ፡ ወኢይነብብ ፡ በቅድመ ፡ ዘይቀርጾ ።

እንደ ፡ በግ ፡ ሊሠዋ ፡ መጣ ። በግ ፡ ጠጉሩን ፡ ሲሸልቱት ፡ ከቀን ፡ ሐሩር ፡ ከሌሊት ፡ ቁር ፡ የምጠበቅበትን ፡ ጠጉሬን ፡ ምን ፡ ባልኩ ፡ ትሸልቱኛላችሁ ፡ ብሎ ፡ እንደማይናገር ፤ ርሱም ፡ ሲሰቅሉት ፡ ሲቸነክሩት ። ብትራቡ ፡ ኅብስት ፡ አበርክቼ ፡ አበላኋችሁ ፡ ብትታመሙ ፡ ፈወስኋችሁ ፡ ብትሞቱ ፡ አስነሣኋችሁ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ አልኋችሁ ፡ ብሎ ፡ አይናገርም ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ትንቢት ፡ ገና ፡ በትንቢትነቱ ፡ ሳለ ፡ አምነን ፤ ትንቢቱ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፤ ነዋ ፡ ማይ ፡ መኑ ፡ ይከልአኒ ፡ ተጠምቆ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፴፯ ፡ ውኑ ፡ እነሆ ፡ አለ ፡ ብንጠመቅ ፡ ማን ፡ ይከለክለናል ! ብለን ፡ በፈቃዳችን ፡ ያመን ፡ የተጠመቅን ፤ በዕለተ ፡ ዐርብም ፡ አባ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ እስመ ፡ በዘኢየአምሩ ፡ ይገብሩ ። ኃጢአቱን ፡ ባለማወቅ ፡ ይሠሩታልና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ ብሎ ፡ የጸለየልን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ያወቅን ፡ የተረዳን ፡ ሰዎች ፡ ነን ። አንተ ፡ በ፩ሺ፰፻፲፱ ፡ ዓ፡ ም፡ ተነሥተህ ፡ ፩ሺ፩፻፺ ፡ ዘመን ፡ የእምነት ፡ ቅድሚያ ፡ ያለን ፡ እኛን ፡ ትጠይቀን ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ ምጥ ፡ ለእናቷ ፡ አስተማረች ፡ የተባለው ፡ አይኾንብህምን ፡ ሐተ ፡ መና ፡ ገጽ ፡ ፸፬ ፡ ተመልከት ።

፭ አሁን ፡ ግን ፡ እውነተኛው ፡ ዐማላጅ ፡ ማለት ፡ ርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ በፈቃዱ ፡ የወረደው ፡ ከቅድስት ፡ ወንጽሕት ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ የተወለደው ፡ ጻድቁ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፫—፲፰ ። ለሰው ፡ ሰው ፡ ሊያድነው ፡ ስለማይችል ፡ ግን ፡ የሰማዩ ፡ ንጉሥ ፡ ጻድቁ ፡ ለኛ ፡ ለኃጥአን ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ ፍቅሩ ፡ አስገድዶት ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሊወርድ ፡ ግድ ፡ ኾነበት ፡ እንጂ ፡ ከአበው ፡ ኹላቸውም ፡ ይልቅ ፡ አብርሃም ፡ አበ ፡ ምእመናን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ከኹሉ ፡ የበለጠ ፡ ጻድቅ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ጽድቁ ፡ ለሰው ፡ እንደማይተርፍ ፡ አረጋግልጥልሃለሁ ፡ ዘፍ ፡ ፲፰ ፡ ፳ ፡ ዘፀ ፡ ፫ ፡ ፱—፲ ፡ ስለምትለው ።

በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አስታራቂነትና ፡ በቅዱሳን ፡ አማላጅነት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ጠይቆ ፡ መረዳት ፡ ነውር ፡ መስሎህ ፡ ያላአገባብ ፡ አፍህ ፡ እንዳመጣ ፡ እጠቅሳለሁ ፡ እያልክ ፡ መጻሕፍትን ፡ ታምታታቸዋለህ ፡ ታዘባርቃቸዋለህ ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ አደለም ።



እኒህ ፡ አንተ ፡ ለማስመሰል ፡ የጠቀስካቸው ፡ ጥቅሶች ፡ የተጻፉበትን ፡ ምክንያትና ፡ የክርስቶስን ፡ አስታራቂነት ፡ የቅዱሳንንም ፡ አማላጅነት ፡ በረድፍ ፡ በረድፉ ፡ ለይቼ ፡ ለይቼ ፡ እጽፍልሃለሁና ። በማስተዋል ፡ ተመልከት ።

## ፩ኛ ፡ ጥቅሶች ፡ የተጻፉበት ፡ ምክንያት ።

በጥንተ ፡ ተፈጥሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ሲፈጥረው ፡ እንስሳዊ ፡ እውቀት ፡ እንስሳዊ ፡ ግብር ፡ ያላት ፡ በሥራ ፡ እንስሳትን ፡ የምታስመስል ፡ ደማዊት ፡ ነፍስን ፡ አዋሕዶ ፡ ከራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ከፈጠረው ፡ በኋላ ፤ መልአካዊ ፡ እውቀት ፡ መልአካዊ ፡ ግብር ፡ ያላት ፤ መላእክትን ፡ የምታስመስል ፡ ነባቢት ፡ ነፍስን ፡ በንፍሐት ፡ አሳድሮ ፡ በልጅነት ፡ አክብሮ ፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ በጸጋ ፡ አስገዝቶ ፤ ለመንግሥቱ ፡ ተከፋይ ፡ አድርጎት ፡ ነበረ ።

አዳም ፡ ግን ፡ ፈጣሪው ፡ የሰጠው ፡ የጸጋ ፡ ገዢነት ፡ አንሶት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ኾኖ ፡ ለሰማይና ፡ ለምድር ፡ ገዢ ፡ መኾንን ፡ ተመኝቶ ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በመብላቱ ፡ ልጅነቱን ፡ አጣ ፤ ከገነት ፡ ወጣ ፤ ልጅነቱን ፡ አስወሰደ ፤ ከማዕርጉ ፡ ተዋረደ ፤ ከበታው ፡ ተሰደደ ። ሞተ ፡ ሥጋ ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ ተፈረደበት ፤ አዳም ፡ ገብሩ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ሔዋን ፡ አመቱ ፡ ለዲያብሎስ ፡ የሚል ፡ ስመ ፡ ግብርናት ፡ ተጻፈበት ፡ ለዲያብሎስ ፡ መገዛትን ፡ ያህል ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ተጫነበት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አዳም ፡ ባደረገው ፡ ስሕተት ፡ ተጠጥቶ ፡ በንስሐ ፡ ቢያለቅስ ፡ ቢጨነቅ ፡ ቢነሣ ፡ ቢወድቅ ፡ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ክብሩ ፡ መመለስ ፤ የተጻፈበትን ፡ ስመ ፡ ግብርናት ፡ መደምሰስ ፡ አልቻለም ።

ለስሕተቱ ፡ መደበኞች ፡ የኾኑት ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ይቅሩና ፡ ከነሱ ፡ የተወለደ ፡ ኹሉ ፡ የነሱን ፡ መርገምና ፡ ፍዳ ፡ በዘር ፡ ወርሶ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ተገዢ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ በሠዋው ፡ መሥዋዕት ፤ በጸለየው ፡ ጸሎት ፤ ባጠነው ፡ ዕጣን ፡ ባቀረበው ፡ ቍርባን ፡ ከዲያብሎስ ፡ ባርነት ፡ ነፃ ፡ ሊወጣ ፡ አልቻለም ።

ዘመኑም ፡ ዓመተ ፡ ፍዳ ፡ ዓመተ ፡ ኵነኔ ፡ ተባለ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ያሉ ፡ ፍጥረቶች ፡ ኹሉ ፡ በቍራኝነት ፡ ተይዘው ፡ ሞት ፡ ጥላውን ፡ በጣለበት ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ተግዘው ፡ ኖሩ ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ አገዛዝ ፡ ስለጸናባቸው ፡ በሥራቸው ፡ መጽደቅ ፡ ስለተሳናቸው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አኮ ፡ በተንባል ፡ ወኢበመልአክ ፡ አላ ፡ ለሊሁ ፡ እግዚእ ፡ ይመጽእ ፡ ወያድኅነነ ።

ከግብርናተ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነፃ ፡ የሚያወጣን ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አማላጅ ፡ አስነሥቶ ፡ ወይም ፡ መልአክ ፡ ልኮ ፡ አደለም ፡ እያሉ ፡ ክሶ ፡ ማስታረቅ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ የተመደበ ፡ ተግባር ፡ መኾኑን ፡ ተናግረዋል ። እኛም ፡ እንደዚሁ ፡ በክርስቶስ ፡ ካሳ ፡ መዳናችንን ፡ ዐውቀን ፡ እምነናል ።

፮ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ ከነአካቴውም ፡ እስመ ፡ ኢይጸድቅ ፡ ኵሉ ፡ ሕያው ፡ በቅድሜከ ፡ መዝ ፡ ፻፵፪ ፡ ፪ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ መልካም ፡ የሚሠራ ፡ ጻድቅ ፡ ኃጢአትም ፡ የማይሠራ ፡ ሰው ፡ የለም ። መክ ፡ ፯ ፡ ፳ ። ጽድቃችን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ኾነ ፡ ኢሳ ፡ ፷፬ ፡ ፮ ። መኑ ፡ ይነጽሕ ፡ እምኃጢአት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኢመንሂ ፡ ኢዮ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ። እያሉ ፡ አስተካክለው ፡ ይነግሩናል ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በአሚን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ይጸድቃል ፡ እንጂ ፡ ከራሱ ፡ በምግባሩ ፡ ወይም ፡ ከማናቸውም ፡ ፍጡር ፡ ጽድቅ ፡ እንደ ማይገኝ ፡ ኢዮብ ፡ ሲያስረዳ ፡ ሰው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ይጸራ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ከሴት ፡ ከሔዋን ፡ የተወለደ ፡ ጻድቅ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻላል ፡ ይላል ፡ ፲፭ ፡ ፲፬ ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊትም ፡ ኵሉ ፡ ዐረየ ፡ ወኅቡረ ፡ ዐለወ ፡ አልቦ ፡ ዘይገብራ ፡ ለሠናይት ፡ አልቦ ፡ ወኢአሐዱ ፡ ይላል ፡ መዝ ፡ ፲፬ ፡ ፩—፫ ። ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፷፩—፷፰ ፡ ስለምትለው ።

እኒህ ፡ ጥቅሶች ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተነሥቶት ፡ አብዝቶ ፡ ኃጢአት ፡ መሥራቱን ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ ጽድቅን ፡ የሚሠራ ፡ ከተገኘ ፡ ማማለድ ፡ አይችልም ፡ አላሉም ፡ ጽድቅን ፡ የሚሠሯትስ ፡ ሰዎች ፡ በዚያ ፡ ወራትም ፡ ቢኾን ፡ ማማለድ ፡ እንዲቻላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ መስክሮላቸዋል ፤ እነሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲጠፉ ፡ ቊርጥ ፡ ፍርድ ፡ የፈረደባቸውን ፡ ሰዎች ፡ አማልደው ፡ አድነዋል ። ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ የሚከተሉትን ፡ ጥቅሶች ፡ ተመልከት ።

(ሀ) አብርሃም ፡ ሚስቱን ፡ ሣራን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አቤሜሌክ ፡ ንጉሠ ፡ ጌራራ ፡ በተሰደደ ፡ ጊዜ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ስለነበረች ፡ የዚህ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ አንቺን ፡ ሲሉ ፡ እንዳይገሉኝ ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡ በይ ፤ እኔም ፡ እቴ ፡ ናት ፡ እላለሁ ፡ አላት ፤ እሺ ፡ አለች ። ከዚያ ፡ ሲደርሱ ፡ እሱም ፡ እቴ ፡ ናት ፡ አለ ፤ እሷም ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡ አለች ።

አቤሜሌክ ፡ ክእልፍኙ ፡ አግብቶ ፡ እደርስባታለሁ ፡ ቢል ፡ ብልቱ ፡ አበጠ ፡ እጁ ፡ እግሩ ፡ ሰለለ ። እግዚአብሔር ፡ በሕልም ፡ መጥቶ ፡ ይች ፡ ሴት ፡ ባለ ፡ ባል ፡ ናትና ፡ እሷን ፡
መቀማትህ ፡ ሞት ፡ የተፈረደብህ ፡ ነህ ፡ አለው ። አቤሜሌክም ፡ ገና ፡ አልደረሰባትም ፡
ና ፡ እርሱ ፡ እቴ ፡ ናት ፡ ቢለኝ ፡ እርሷም ፡ ወንድሜነው ፡ ብትለኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
፡ አውቄ ፡ አላደረግሁምና ፡ ያለኃጢአቴ ፡ እንደምን ፡ ታጠፋኛለህ ፡ አለው ።

ዚአብሔርም ፡ መልሶ ፡ እኔም ፡ ባለማወቅ ፡ መሥራትህን ፡ አውቄ ፡ ከመድ
ኩህ ፡ አሁንም ፡ ሴቲቱን ፡ ወደ ባልዋ ፡ መልስ ፡ እሱም ፡ ነቢይ ፡ ነውና ፡
ይልኽ ፡ ትድናለህ ፡ ብትመልሳት ፡ ግን ፡ አንተ ፡ እንድትሞት ፡ ያንተ ፡
፡ እንዲጠፉ ፡ እወቅ ፡ አለው ።

ስጠርቶ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ ባልኩህ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መዓት ፡
ጠየቀው ።
፡ ሀገር ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የለምና ፡ አንቺን ፡
ሜ ፡ ነው ፡ በይ ፡ እኔም ፡ እቴ ፡ ናት ፡ እላለሁ ፡ አልኳት ፡

ሞችን ፡ ወንዶችን ፡ ባሮች ፡ ሴቶችን ፡ ባሮች ፡ ለአ
መለሰለት ። ለሣራም ፡ ለፊትሽ ፡ መሸፈኛ ፡ ይኹን ፡
ውን ፡ ልዩ
መጣ ፡ እጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፡ እግዚአብሔርም ፡
እንጂ ፡ ነገሩ ይላል ። ዘፍጥ ፡ ፳ ፡ ፩-፲፰ ።



(ለ) ኢዮብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ ደርሶበት ፡ በሕማም ፡ ሲሠቀይ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ኤልፋዝ ፤ በልዳድ ፡ ሶፎር ፡ የሚባሉ ፡ ወዳጆቹ ፡ ሊጠይቁት ፡ መጥተው ፡ በማረጋጋት ፡ ፈንታ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ተናግረው ፡ ስላሳዘኑት ፡ ኋላ ፡ ከደዌው ፡ በፈወሰው ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኤልፋዝን ፡ አንተና ፡ ኹለቱ ፡ ባልንጀሮችኽ ፡ ስለእኔ ፡ እንደ ፡ ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ቅንነት ፡ አልተናገራችሁምና ፡ ቍጣዬ ፡ በንተና ፡ በኹለቱ ፡ ባልንጀሮችኽ ፡ ላይ ፡ ትነዳለች ።

አሁንም ፡ ፯ ፡ ወይፈንና ፡ ፯ ፡ ደንግሌ ፡ ይዛችሁ ፡ ወደ ፡ ባሪያዬ ፡ ወደ ፡ ኢዮብ ፡ ሒዱና ፡ ስለናንተ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አሳርጉ ። ኢዮብም ፡ ስለናንተ ፡ ይጸልይላችሁ ፡ እኔም ፡ ጸሎቱን ፡ እቀበላለሁ ። ስለእኔ ፡ እንደ ፡ ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ቅንነት ፡ ባለመናገራችሁ ፡ እንደ ፡ ስንፍናችሁ ፡ እንዳላደርግባችሁ ፡ አለው ።

ኤልፋዝና ፡ በልዳድ ፡ ሶፎር ፡ ሔደው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳላቸው ፡ አደረጉ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የኢዮብን ፡ ጸሎት ፡ ተቀበለ ። እግዚአብሔርም ፡ ኢዮብ ፡ ስለወዳጆቹ ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፡ ምርኮውን ፡ መለሰለት ፡ ይላል ። ኢዮ ፡ ፵፪ ፡ ፯–፲፩ ፡ እንግዲህ ፡ መዓትም ፡ ምሕረትም ፡ በእጁ ፡ የኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገሠጻቸው ፡ እነሱም ፡ ከደነገጡበት ፡ በኋላ ፡ ኢዮብ ፡ ይጸልይላችሁና ፡ ይቅር ፡ እላችኋለሁ ፡ ማለቱ ፡ መሐሪነትን ፡ ለርሱ ፤ አማላጅነትን ፡ ለቅዱሳን ፡ መስጠቱ ፡ እንደኾነ ፡ አስተውል ፡ ።

(ሐ) እስራኤል ፡ አሮንን ፡ ፊት ፡ ፊታችንን ፡ እየሔዱ ፡ ጠላት ፡ የሚያጠፉልን ፡ ጣዖታት ፡ ሥራልን ፡ ብለው ፡ ጣዖት ፡ አሠርተው ፡ በሰገዱ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ተቈጥቶ ፡ ሙሴን ፡ ተወኝ ፡ እኒህን ፡ ሰዎች ፡ ላጥፋቸውና ፡ አንተን ፡ በሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እሾምሃለሁ ፡ ቢለው ፤ አቤቱ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አድርገህ ፡ ባሕር ፡ ከፍለህ ፡ ጠላት ፡ አሥጥመኽ ፡ ባወጣሃው ፡ ሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ ለምን ፡ ትፈርድ በታለህ ። ይኽማ ፡ ከኾነ ፡ ግብጻውያን ፡ ለካስ ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ያወጣቸው ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሊያጠፋቸው ፡ ኖሯልና ፡ ይሉኽ ፡ የለምን ? አቤቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ከቍጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ተመልሰኽ ፡ ወገኖችህን ፡ ይቅር ፡ በላቸው ። ልጆቻችሁን ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ኮከብ ፡ አበዛላችኋለሁ ፡ ይህችን ፡ ምድር ፡ ለዘለዓለም ፡ ይወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ለልጆቻችሁ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለኽ ፡ የማልክላቸው ፡ ባሮችህ ፡ አብርሃምን ፡ ይስሐቅን ፡ ያዕቆብን ፡ አስብ ፡ ብሎ ፡ ቢጸልይላቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ከቍጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ተመልሶ ፣ ይቅር ፡ አላቸው ፡ ያደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ የተናገረውንም ፡ ጥፋት ፡ አላደረገባቸውም ፡ ዘፀአ ፡ ፴፪ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ዘዳግ ፡ ፱ ፡ ፲፪–፳፩ ፡ ፳፭ ፡ ተወኝ ፡ ላጥፋቸው ፡ ብሎ ፡ ማማከሩ ፡ ባለሟልነቱን ፡ አማላጅነቱን ፡ ለመግለጽ ፡ አደለምን ? ብታውቅስ ፡ ኖሮ ፡ ለሰው ፡ የተሰጠውን ፡ ክብር ፡ ከማድነቅ ፡ ባላቋረጥክም ፡ ነበረ ።

(መ) እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ በሚያወጣበት ፡ ወራት ፡ በፈርዖን ፡ እንቢተኝነት ፡ ኀጉንቸር ፡ በወረደባቸው ፡ ጊዜ ፡ ፈርዖን ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ጠርቶ ፡ ኀጉንቸሩ ፡ ይርቅልኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩልኝ ፡ እኔም ፡ ሕዝቡን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ልልቀቅ ፡ አላቸው ። ሙሴም ፡ እስራኤልን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትለቀዋለህ ፡ ንገረኝና ፡ ልጸልይልህ ፡ ቢለው ፡ ጓጉንቸሩ ፡ ይልቀቀኝ ፡ እንጂ ፡ ነገ ፡ ይሒዱ ፡ አለው ።

ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ከዚያ ፡ ወጥተው ፡ ጓጉንቸሩ ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመለከቱ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ልመናቸውን ፡ ሰምቶ ፡ ጓጉንቸሩን ፡ ከቤትም ፡ ከደጅም ፡ ከሜዳም ፡ አጠፋላቸው ፡ ይላል ፡ ዘፀአ ፡ ፲ ፡ ፯-፲፩ ።

(ሠ) ፈርዖን ፡ ልቡን ፡ አጽንቶ ፡ ባሮቹን ፡ አልሰድም ፡ ስላለ ፡ ተቈናጣጭ ፡ ዝንብ ፡ በፈርዖን ፡ ቤትና ፡ በወገኖቹ ፡ በምስር ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ላከባቸው ። ፈርዖን ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ጠርቶ ፡ እናንተ ፡ ሒዳችሁ ፡ ለአምላካችሁ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ፡ ለኔም ፡ የውሻው ፡ ዝንብ ፡ ይርቅልኝ ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩልኝ ፡ አላቸው ። ሙሴም ፡ አሁን ፡ መዓቱ ፡ ሲርቅልህ ፡ አንተ ፡ ከድተህ ፡ እስራኤልን ፡ አለቅም ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ እጸልይልሃለሁ ፡ የውሻ ፡ ዝንቡም ፡ ይርቅልሃል ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያመለክት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሙሴን ፡ ጸሎት ፡ ሰምቶ ፡ የውሻ ፡ ዝንቡን ፡ አጠፋ ። ዘፀአ ፡ ፰ ፡ ፳-፴፪ ።

(ረ) ዳታን ፡ አቤሮን ፡ በሙሴ ፤ ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ በምቀኝነት ፡ በተነሡባቸው ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡ ኹሉንም ፡ በንዲት ፡ ጊዜ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከጉባኤያቸው ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፡ ቢላቸው ፤ ሙሴና ፡ አሮን ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፍተው ፡ ወድቀው ፡ አቤቱ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ የሰዉ ፡ ኹሉ ፡ ነፍስ ፡ አምላክ ፡ አደለህምን ? አንድ ፡ ሰው ፡ ኃጢአት ፡ ሠራ ፡ ብለኽ ፡ በማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ትቈጣለኽ ፡ ብለው ፡ ለምነው ፡ ጥፋተኞች ፡ ዳታን ፡ አቤሮን ፡ ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ ተለይተው ፡ ሲጠፉ ፡ ሕዝቡን ፡ አድነዋቸዋል ፡ ዘኍ ፡ ፲፮ ፡ ፳-፴፭ ።

(ሰ) በነጋውም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፤ ላይ ፡ ሕዝቡን ፡ አሰገደላችሁ ፡ ብለው ፡ በደንጋያ ፡ ሊወግሯቸው ፡ ተነሡ ። ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ሸሹ ፡ ዓምደ ፡ ብርሃን ፡ ጋርዶ ፡ አዳናቸው ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ ከዚህ ፡ ከእስራኤል ፡ ፊት ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ በቅጽበት ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ወዲያው ፡ መቅሠፍት ፡ አምጥቶ ፡ ይፈጽማቸው ፡ ጀመረ ። ወዲያው ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ ፲፬ ፡ ሺ ፡ ከ፯፻ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ በግንባራቸው ፡ ወድቀው ፡ ይጸልዩ ፡ ጀመረ ፡ ሙሴም ፡ አሮንን ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰህ ፡ ማዕጠንተ ፡ ወርቅ ፡ ይዘህ ፡ ጸልይላቸው ፡ ኃጢአታቸውን ፡ አስተሥርይላቸው ፡ አለው ።

አሮንም ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖውን ፡ ለብሶ ፡ ማዕጠንተ ፡ ወርቁን ፡ ይዞ ፤ በሙታኑና ፡ በሕያዋኑ ፡ መካከል ፡ እየተመላለሰ ፡ ቢጸልይላቸው ፡ መቅሠፍቱ ፡ ጸጥ ፡ ብሎላቸዋል ፡ ሞት ፡ ተከልክሎላቸዋል ። ዘኍል ፡ ፲፮ ፡ ፵፩-፶ ።

(ቀ) እስራኤል ፡ ተሰብስበው ፡ ሔደው ፡ ኤርምያስን ፡ ጸሎታችን ፡ በፊትህ ፡ ይድረስ ፡ ለኛም ፡ ወደ ፡ አምላክህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይልን ፤ ዐይንህ ፡ እንደሚያየን ፡ ከብዙ ፡ ጥቂት ፡ ቀርተናልና ፡ ቢሉት ፡ እሺ ፡ ወደ ፡ አምላካችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልይላችኋለሁ ። እግዚአብሔርም ፡ የሚሰጣችሁን ፡ መልስ ፡ አል



ደብቃችሁም ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ብሏቸው ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ከጸለየላቸው ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ፡ ከ፲ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡን ፡ ከልሒቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ ሰብስቦ ፡ ጸሎታችሁን ፡ በፊቱ ፡ አቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደርሱ ፡ የላካችሁኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፤ በዚች ፡ ምድር ፡ ብትቀመጡ ፡ እሠራችኋለሁ ፡ አላፈርሳችሁም ፡ እተክላችኋለሁ ፤ አልነቅላችሁም ፤ እናንተ ፡ በሠራችሁት ፡ ኃጢአት ፡ ከደነገጣችሁበት ፡ እኔም ፡ ባደረግሁባችሁ ፡ ክፉት ፡ እጠጠቃለሁና ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ አትፍሩ ፡ ኣላችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነግሯችዋል ። ኤር ፡ ፵፪ ፡ ፩-፲፫ ፡ ይበዛና ፡ ተመልከቶች ፡ ይሰለቹብናል ፡ ብለን ፡ ተውነው ፡ እንጂ ፡ መጻሕፍትን ፡ ኹሉ ፡ ብትመረምር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ታገኛለህ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ በደሙ ፡ ክሶ ፡ ሰውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ገና ፡ ስላላስታረቀው ፡ እሊህ ፡ ኹሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ነቢያት ፡ በጸሎታቸው ፡ የሚጸልዩላቸውን ፡ ሰዎች ፡ በሥጋ ፡ ከሚያገኛቸው ፡ መከራ ፡ አዳኗቸው ፡ እንጂ ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስስ ፡ ስንኳን ፡ ሌሎችን ፡ ሊያማልዱ ፡ ለራሳቸውም ፡ ርደተ ፡ ገሃነም ፡ አልቀረላቸውም ፡ ነበረ ። እኒህም ፡ ዛሬ ፡ የሚደረጉ ፡ አስመስለህ ፡ የምትጠቅሳቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ኹሉ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሰውና ፡ እግዚአብሔር ፡ በተጣሉበት ፡ ወራት ፡ የተነገሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ዛሬስ ፡ በክርስቶስ ፡ አስታራቂነት ፡ ያ ፡ ኹሉ ፡ ቀርቶልናል ፡ መቅረቱንም ፡ ወደፊት ፡ አስረዳሃለሁና ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ ተመልከት ።

## ፪ተኛ ፡ ስለክርስቶስ ፡ አስታራቂነት ።

፩ኛ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ በሠዋው ፡ መሥዋዕት ፡ በጸለየው ፡ ጸሎት ፡ መዳን ፡ እንደተሣነው ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ከታወቀ ፡ ከተረዳ ፡ ለኋላ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ከቅድስት ፡ ማርያም ፡ በድንግልና ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ ተፀነሰ ፤ ዲያብሎስ ፡ በዘር ፡ ምክንያት ፡ በማኅፀን ፡ ይቈራኝ ፡ ነበረ ፡ ቍራኝነት ፡ ቀረ ፤ ካሳ ፡ በማኅፀን ፡ ተጀመረ ። ሰው ፡ ኾነ ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በመንፀፈ ፡ ደይን ፡ ወድቆ ፡ አጋንንት ፡ ይጠቀጥቁት ፡ የነበረ ፡ የአዳም ፡ ባሕርይ ፡ ከወደቀበት ፡ ተነሣ ፡ ከብሴቱ ፡ ታደሰ ፡ ከድካሙ ፡ ተጽናና ፡ በተዋህዶተ ፡ ቃል ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ኾነ ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ተቀመጠ ።

፪ኛ ተወልዶም ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ሲመላው ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ ሲጠመቅ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ተጥሎ ፡ የነበረውን ፡ አዳም ፡ ገብሩ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ሔዋን ፡ አመቱ ፡ ለዲያብሎስ ፡ የሚለውን ፡ ስመ ፡ ግብርናት ፡ ደመሰሰልን ።

፫ኛ ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ የኾነበት ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ዲያብሎስ ፡ በወረወራቸው ፡ በሦስት ፡ ጦሮች ፡ በስስት ፡ በትዕቢት ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ተወግቶ ፡ ወድቆ ፡ ለነበረ ፡ ለአዳም ፡ ባሕርይ ፡ ኃይል ፡ ለመስጠት ፡ ስለኾነ ፡ ሥራውን ፡ በጾም ፡ ጀመረ ።

መጾሙም ፡ በሰውነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በአምላክነቱ ፡ አደለም ። ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ ጾሞ ፡ መዋዕለ ፡ ጾሙ ፡ ሲፈጸም ፡ ተራበ ፤ ረኃቡም ፡ ረኃብ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ረኃብ ፡ ሰይጣናዊ ፡ አደለም ። ርኅብኩ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ አሰማ ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዲያብሎስ ፡ አዳምን ፡ በመብል ፡ ምክንያት ፡ ድል ፡ እንደነሣሁ ፡ ርሱንም ፡ ድል ፡ እነሣለሁ ፡ መስሎት ፡ እኒህን ፡ ደንጋዮች ፡ ዳበ ፡ አድርግና ፡ እንብላ ፡ ብሎ ፡ የስስት ፡ ጦሩን ፡ ወረወረ ።

ክርስቶስም ፡ ሰው ፡ የሚድን ፡ እግዚአብሔር ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኅብስት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ጋሻ ፡ መክቶ ፡ የወረወረውን ፡ የስስት ፡ ጦር ፡ ሰበረበት ።

ኹለተኛም ፡ ዲያብሎስ ፡ ገና ፡ ጦር ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ እንደ ኾነ ፡ አውቆበት ፡ የትዕቢት ፡ ጦሩን ፡ ወደ ፡ አዘጋጀበት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ክምሕዋሩ ፡ ላይ ፡ ቆመ ።

ዲያብሎስም ፡ በትዕቢት ፡ ድል ፡ እነሣዋለሁ ፡ መስሎት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከኾንክስ ፡ በመንገድህ ፡ ኹሉ ፡ መላእክት ፡ እንዲጠብቁህ ፡ ያዝዛችዋል ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለና ፡ መር ፡ ብለህ ፡ ዘለህ ፡ ውረድ ፡ አለው ።

አንባቢ ፡ ሆይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምኛለሁ ፡ ምን ፡ አለብኝ ፡ ብሎ ፡ ከገደል ፡ ልውደቅ ፡ ከባሕር ፡ ልጥለቅ ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፈታተን ፡ ታላቅ ፡ ትዕቢት ፡ እንደ ኾነ ፡ አስተውል ።

ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትፈታተነው ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለ ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ሰጥቶ ፡ የወረወረውን ፡ የትዕቢት ፡ ጦር ፡ እንቅጭ ፡ አደረገበት ።

ሦስተኛም ፡ ገና ፡ ጦር ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ እንደ ኾነ ፡ ዐውቆ ፡ የፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ጦሩን ፡ ወደአዘጋጀበት ፡ ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ወጣለት ።

የዓለምን ፡ ኹሉ ፡ መንግሥታት ፡ ብዕልና ፡ ክብር ፡ እያሳየ ፡ እየው ፡ የኽ ፡ ኹሉ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ አንተ ፡ ለኔ ፡ ብትገዛ ፡ ለኔ ፡ ብትሰግድ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ አስገዛሃለሁ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ አለው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ዕሩቅ ፡ ውዱቅ ፡ ከአጠገቤ ፡ ወግድ ፡ ለፈጣሪህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንድትሰግድ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ እንድታመልክ ፡ ተጽፎአል ፡ ብሎ ፡ በረቂቅ ፡ ጦር ፡ ደረቱን ፡ ቢለው ፡ ክፉኛ ፡ ቄስሎ ፡ የኀፍረት ፡ ደሙን ፡ እያንዠረዠረ ፡ አፍሮ ፡ ተመለሰ ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ በስስት ፡ ቢመጣበት ፤ በትሕርምት ፤ በትዕቢት ፡ ቢመጣበት ፡ በትሕትና ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ቢመጣበት ፡ በጸሊዐ ፡ ንዋይ ፡ ግንባር ፡ ግንባሩን ፡ ብሎ ፡ ድል ፡ ከነሣው ፡ በኋላ ፡ መላእክት ፡ ሊያገለግሉት ፡ መጡ ፡ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፩–፲፪ ፡ ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፩–፲፬ ፡ ድል ፡ ከነሣ ፡ በኋላ ፡ የሚያገለግሉት ፡ መላእክት ፡ መጡ ፡ ማለቱ ፡ እናንተም ፡ ድል ፡ ብትነሡ ፡ መላእክት ፡ ይመጡላችኋል ፡ ድል ፡ ባትነሡ ፡ ግን ፡ አይመጡላችሁም ፡ ማለቱ ፡ እንደ ኾነ ፡ አስተውል ።

፬ተኛ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምድረ ፡ እስራኤል ፤ ገብቶ ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ ጀመረ ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በልጅነት ፡ ልትሰጥ ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነገረ ፤ ኑ ፡ ተከተሉኝ ፡ እኔ ፡ ድል ፡ እንደነሣሁ ፡ እናንተም ፡ ድል ፡ ንሡ ፡ ብሎ ፡ አስተማረ ። ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲፯–፳፫ ። ማር ፡ ፩ ፡ ፲፯ ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፴፱ ።



፭ተኛ ፡ ላመኑበትም ፡ ሰዎች ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ ተስማምተው ፡ በሚሠሩት ፡ በሥጋዊ ፡ በደማዊ ፡ ፍትወት ፡ ያይደለ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተወልደው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።

፮ተኛ ፡ ፲፪ቱን ሐዋርያትም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በልጅነት ፡ ልትሰጥ ፡ ቀርባለች ፡ እያላችሁ ፡ አስተምሩ ፡ ብሎ ፡ በላካቸውም ፡ ጊዜ ፡ ድውያኑን ፡ ፈውሱ ፤ ሙታንን ፡ አስነሡ ፤ ለምጻሞችን ፡ አንጹ ፤ አጋንንትን ፡ አስወጡ ፡ ብሎ ፡ ለሥልጣኑ ፡ ተከፋዮች ፡ አድርጎ ፡ ሾማቸው ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፮ ።

፯ተኛ ፡ ሰማዕያኑ ፡ በዝተው ፡ መምህራኑ ፡ ፲፪ቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ብቻ ፡ መኾናቸውን ፡ አይቶ ፡ ፸ ፡ አርድእትን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በልጅነት ፡ ልትሰጥ ፡ ቀርባለች ፡ እያላችሁ ፡ አስተምሩ ፡ ዱውያን ፡ ፈውሱ ፡ እናንተን ፡ የሰማ ፡ እኔን ፡ መስማቱ ፡ ነው ፡ እኔንም ፡ የሰማ ፡ የላከኝ ፡ አብን ፡ መስማቱ ፡ ነው ። እናንተን ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እኔን ፡ እንቢ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እኔንም ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ የላከኝ ፡ አብን ፡ እንቢ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሾማቸው ።

፰ተኛ ፡ ፸ ፡ አርድእትም ፡ በየተላኩበት ፡ ሔደው ፡ አጋንንት ፡ እንደ ፡ ተገዙላቸው ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ ደብ ፡ እያላቸው ፡ ተመልሰው ፡ አቤቱ ፡ አጋንንት ፡ በስምህ ፡ ተገዙልን ፡ ቢሉት ፡ ሰይጣን ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወድቅ ፡ አየሁት ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ጊንጡን ፡ እባቡን ፡ የዲያብሎስን ፡ ኃይል ፡ ሥልጣን ፡ ኹሉ ፡ ከእግራችሁ ፡ በታች ፡ ትረግጡት ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቻችኋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አጋንንት ፡ ተገዝተውላችኋልና ፡ በዚህ ፡ ደስ ፡ አይበላችሁ ፤ ደስታስ ፡ ስማችሁ ፡ በሰማይ ፡ ተጽፎላችኋልና ፡ በዚህ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ብሎ ፡ የበለጠ ፤ የምሥራች ፡ ነግሯቸዋል ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፩–፲፪ ። ፲፯–፳፩ ።

፱ነኛ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ እነሆ ፡ አቤቱ ፡ ኹሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንህ ፡ እንግዲህ ፡ እኛ ፡ ምን ፡ እናገኛለን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ሰው ፡ በኾንኩ ፡ ጊዜ ፡ የተከተላችሁኝ ፡ እናንተ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ክርስቶስ ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ እናንተም ፡ በ፲፪ት ፡ ወንበሮች ፡ ተቀምጣችሁ ፡ በ፲፪ቱ ፡ ነገደ ፡ እሥራኤል ፡ እንድትፈርዱ ፡ እውነት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ የፍርድ ፡ ተከፋዮች ፡ አድ ጓቸዋል ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ።

፲ኛ ፡ በምሴተ ፡ ሐሙስም ፡ የሞቱን ፡ ነገር ፡ ቁርጥ ፡ አድርጎ ፡ ሲነግራቸው ፡ እንዳ ይሸበሩ ፡ ሲያጽናናቸው ፡ በባቴ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ሀብታት ፡ አሉ ፡ እናንተም ፡ እኔ ፡ ካለሁበት ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ቦታ ፡ ላዘጋጅላችሁ ፡ እሔዳለሁና ፡ ልቡናችሁ ፡ አይሸበር ። በእግዚአብሔር ፡ አብ ፤ በኔም ፡ እመኑ ። በኔ ፡ ያመነ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ይሠራል ፡ እኔ ፡ ከምሠራውም ፡ የበለጠ ፡ ይሠራል ፡ ብዬ ፡ እዉነት ፡ እነግራችኋለሁ ። እኔ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ እሔዳለሁና ፡ አብ ፡ በወልድ ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ አብን ፡ በኔ ፡ ስም ፡ በስቁል ፡ ወልድከ ፡ በቅንው ፡ ወልድከ ፡ ብላችሁ ፡ ብትለምኑት ፡ የለመናችሁትን ፡ ያደርግላችኋል ።

www.ethiopianorthodox.org

እኔንም ፡ በስሜ ፡ አዘተሰቀልከ ፤ አዘተቀኖከ ፡ ብላችሁ ፡ ብትለምኑኝ ፡ ያንን ፡ የለመናችሁኝን ፡ አደርግላችኋለሁ ፡ ብሎ ለምነው ፡ እንዳያፍሩ ፡ ቁርጥ ፡ ቃል ፡ ነግሯቸዋል ። ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፩-፲፫ ።

፲፩ኛ ፡ በ፲፫ኛውም ፡ ምዕራፍ ፡ ወንጌልን ፡ ስለተቀበላችሁ ፡ እናንተስ ፡ ፈጽማችሁ ፡ ንጹሐን ፡ ናችሁ ፡ እናንተ ፡ በኔ ፡ አምናችሁ ፡ ከኖራችሁ ፡ ትምህርቴም ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ ከኖረ ፡ የወደዳችሁትን ፡ ለምኑ ፡ ይደረግላችኋል ፡ ብሏቸዋል ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፫ ፡ ፯።

፲፪ኛ ፡ ከዚህም ፡ አልፍ ፡ ብሎ ፡ ያዘዝኳችሁን ፡ ኹሉ ፡ ከሠራችሁ ፡ ወዳጆቼ ፡ እላችኋለሁ ፡ እንጂ ፡ ባሮቼ ፡ አልላችሁም ፡ ባሪያ ፡ ጌታው የሚያደርገውን ፡ አያውቅም ፡ ለናንተ ፡ ግን ፡ ከባቴ ፡ የሰማሁትን ፡ ነግሬያችኋለሁ ፡ አስተምሬያችኋለሁና ፡ ወዳጆቼ ፡ እላችኋለሁ ፡ እንጂ ፡ ባሮቼ ፡ አልላችሁም ፡ ይህነንም ፡ እኔ ፡ በሔድኩበት ፡ መንገድ ፡ ሔዳችሁ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ፍሬ ፡ ታፈሩ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ መርጨ ፡ ሾምኳችሁ ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ የመረጣችሁኝ ፡ አይደላችሁም ፡ ብሎ ፡ ከግብርናተ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነፃ ፡ ከማውጣቱ ፡ በላይ ፡ አግብርተ ፡ ክርስቶስ ፡ መባል ፡ የክብር ፡ ክብር ፡ ሲኾን ፡ ባሮቼ ፡ አልላችሁም ፡ ወዳጆቼ ፡ እላችኋለሁ ፡ በማለቱ ፡ የበለጠ ፡ የባለሟልነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥቷቸዋል ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬-፲፯ ።

፲፫ኛ ፡ ከዚህ ፡ አልፎ ፡ በሚገኘው ፡ ምዕራፍ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በመቃብር ፡ ተለይቷቸው ፡ ሰንብቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ለነሱ ፡ መታየቱን ፤ ጥቂት ፡ ቀን ፡ አታዩኝም ፤ ደግሞ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ታዩኛላችሁ ፡ እያለ ፡ በረቀቀ ፡ አነጋገር ፡ ቢነግራቸው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አታዩኝም ፡ ደግሞ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ታዩኛላችሁ ፡ የሚለን ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይኾን ፡ እያሉ ፡ ሲያወጡ ፡ ሲያወርዱ ፡ ሐሳባቸውን ፡ አውቆባቸው ፡ የፀነሰች ፡ ሴት ፡ የምትወልድበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ እንድታዝን ፡ እንድትጨነቅ ፤ ከወለደች ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ በመውለዷ ፡ ሕማሟን ፡ ኹሉ ፡ እንድትረሳውና ፡ እንድትደሰት ፡ እናንተም ፡ በኔ ፡ ሕማምና ፡ ሞት ፡ ለጊዜው ፡ ታዝናላችሁ ፡ ተነሥቼ ስታዩኝ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይላችኋል ፡ ከደስታችሁም ፡ የሚለያችሁ ፡ የለም ፡ (ማለት ፡) ለደስታችሁ ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ በነሱ ፡ ከአዳም ፡ እስከርሱ ፡ ያሉ ፡ የአበው ፡ ኹሉ ፤ የመከራቸው ፡ ፍጻሜ ፡ የርሱ ፡ ትንሣኤ ፡ መኾኑን ፡ በምሥጢር ፡ ከነገራቸው ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እኔን ፡ ምንምን ፡ አትለምኑኝም ፤ አብን ፡ በስቁል ፡ ወልድከ ፡ በቅንው ፡ ወልድከ ፡ ብላችሁ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ ብትለምኑት ፡ ኹሉን ፡ እንዲያደርግላችሁ ፤ ያደርግላችኋል ፡ ብዬ ፡ በእውነት ፡ እነግራችኋለሁ ።

እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አብን ፡ ምንምን ፡ ለምናችሁት ፡ አታውቁም ፡ ነበረ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ ተድላ ፡ ደስታችሁ ፡ ፍጹም ፡ ይኾንላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለምኑ ፡ ታገኛላችሁ ። እናንተ ፡ እኔን ፡ ከአብ ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ ፡ ተወልጄ ፡ እንደመጣሁ ፡ አምናችሁ ፡ ስለወደዳችሁኝ ፡ አብ ፡ እናንተን ፡ ይወዳችኋልና ፡ እናንተ ፡ አብን ፡ ትለምኑታላችሁ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አብን ፡ ስለእና



ንተ ፤ የምለምነው ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፡ የአብ ፡ ባለሟሎች ፡ መኾናቸውን ፡ አረጋግጦላቸዋል ፡ ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፲፮-፳፰ ።

፲፬ተኛ ፡ ይህም ፡ መብት ፡ ላመኑበት ፡ እንጂ ፡ ላላመኑበት ፡ አለመሰጠቱን ፡ እኔ ፡ ስለነሱ ፡ እለምንሃለሁ ፡ እንጂ ፡ ስለዓለም ፡ ኹሉ ፡ የምለምንህም ፡ አይደለሁም ፡ ብሏል ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፱ ።

፲፭ተኛ ፡ ከመኑም ፡ ይህ ፡ መብት ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ የማይቋረጥ ፡ መኾኑንም ፡ የምለምንህም ፡ ስለነዚህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ በነርሱ ፡ ቃል ፡ ስለሚያምኑብኝም ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብሏል ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ።

፲፮ተኛ ፡ ከኃያለኛ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚዘርፍ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ ካሠረው ፡ በኋላ ፡ ከቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ገንዘቡን ፡ ይዘርፋል ፡ እንጂ ፡ አስቀድሞ ፡ እጁን ፡ ካልያዘውና ፡ ካላሠረው ፡ ከቤቱ ፡ ሊገባና ፡ ሊዘርፈው ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ በተናገረው ፡ መሠረት ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፳፱ ። ዲያብሎስን ፡ ዐሥሮ ፡ ሲኦልን ፡ በሚበረብርበት ፡ ጊዜ ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፤ ለምንት ፡ ኅደገኒ ፡ የሚል ፡ ድምጽ ፡ አሰማው ።

ዲያብሎስም ፡ ይህን ፡ ሲናገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ መስሎት ፡ በሌሎች ፡ እንደ ፡ ለመደ ፡ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ ለይቶ ፡ ሥጋውን ፡ በመቃብር ፡ ነፍሱን ፡ በሲኦል ፡ ሊቈራኝ ፡ ቀረበ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምሥጢረ ፡ መለኮቱን ፡ ብልጭ ፡ ቢያደርግለት ፡ መላእክት ፡ በመስቀል ፡ ዙሪያ ፡ ወድቀው ፡ ለከ ፡ ኃይል ፡ ለከ ፡ ጽንዕ ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰግኑት ፡ አይቶ ፡ ፈራ ፤ ደነገጠ ፤ ሾልኬ ፡ አመልጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ቢቃጣ ፡ በነፋስ ፡ አውታር ፡ በእሳት ፡ ዛንጅር ፡ አሠረው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ ድል ፡ የነሣኝ ፤ ምእመናንን ፡ ይነጥቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ይህ ፡ ማነው ።

ከኔ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ የኾነ ፡ ነፍሳትን ፡ ከኔ ፡ እጅ ፡ እየማረከ ፡ የሚወስድ ፡ ይህ ፡ ማነው ።

እንደ ፡ ኃጢአተኛ ፡ በመስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ ያለኃጢአት ፡ ሞቶ ፡ የወደድኩትን ፡ እንዳላደርግ ፡ የከለከለኝ ፡ ልቀርበው ፡ የማይቻለኝ ፡ ይህ ፡ ማነው ።

የተሰጡኝን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ ወደ ፡ ልዕልና ፡ ይወሰዳል ፡ እንጂ ፡ በእግሬ ፡ እርግጥ ፡ በእጄ ፡ ጭብጥ ፡ አድርጌ ፡ ይዤቸው ፡ በነበረ ፡ በነፍሳት ፡ ላይ ፡ እንዳልሠለጥን ፡ ያደረገኝ ፡ ይህ ፡ ማነው ።

ለካስ ፡ እኔ ፡ ሳላውቀው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱስ ፡ ሰማያዊ ፡ ኖሯልና ፡ እያለ ፡ ቀባጠረ ። ወይኔ ፡ ጠፋሁ ፡ በለልኩ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በርሱ ፡ ካመኑ ፡ ሰዎች ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ማድረግ ፡ አይቻለኝም ፡ ማነንም ፡ ለመጕዳት ፡ ሥልጣን ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ፈጽሞ ፡ ድል ፡ መኾኑን ፡ መሰከረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታ ፤ ነቢያት ፡ የተናገሩት ፡ ነገር ፡ እኔም ፡ ሰው ፡ የኾንኩበት ፡ ምሥጢር ፡ እንዲህ ፡ ዲያብሎስን ፡ ለማሠር ፡ ነው ፡ ሲኦል ፡ እነሆ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኹሉ ተፈጸመ ፡ ብሎ ፡ ክብርት ፣ ነፍሱን ፡ ከክብርት ፡ ሥጋው ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለየ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ። በአካለ ፡ ነፍስም ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ርሱ ፡ ያሉ ፡ ነፍሳት ፡ ታሥረው ፡ ተግዘው ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ ግእዛንን ፡ ሰብከላቸው ፤ ከቍራኝነት ፡ አስለቀቃቸው ፤ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ቦታቸው ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ መለሳቸው ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፳ ።

በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ ላሉ ፡ ለሐዋርያትም ፡ በዝግ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ? የምሥራች ፡ አስታረቅኋችሁ ፡ አላቸው ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፴፮ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ። ፶ ፡ ቀን ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳንን ፡ አስተማራቸው ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭-፳፯ ፡ ፵፬-፶ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፴ ።

አብ ፡ እኔን ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደላከኝ ፡ እኔም ፡ እናንተን ፡ ወደዓለም ፡ እልካችኋለሁና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበሉ ፡ ብሎ ፡ እፍ ፡ አለባቸው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በንፍሐት ፡ አሳደረባቸው ። እናንተ ፡ ይቅር ፡ ያላችሁት ፡ ኀጢአቱ ፡ ይሠረይለታል ፡ ይቅር ፡ ያላላችሁት ፡ ኀጢአቱ ፡ አይሠረይለትም ፡ ብሎ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ከፀፃዌ ፡ ኖኅት ፡ እስከ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ያለውን ፡ ማዓርገ ፡ ክህነት ፡ ሾሚቸው ፡ ዐረገ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፩-፳፬ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፮-፶ ።

፲፯ተኛ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሰው ፡ በሰማይም ፡ በምድርም ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ሥልጣን ፡ ከሰጠው ፡ ወዲህ ፡ ያ ፡ አንተ ፡ ከብሉያት ፡ እየለቃቀምክ ፡ የምትጠቅስበት ፡ ጥቅስ ፡ ኹሉ ፡ እንደቀረለት ፡ አስተውል ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ የኾነበት ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ በምክረ ፡ ሰይጣን ፡ ተታሎ ፡ በኀጢአት ፡ ተጐሳቍሎ ፡ ኃይሉ ፡ ደክማ ፡ ጸሎቱ ፡ የማይሰማ ፡ ኹኖ ፡ ተፈርዶበት ፡ በመንፀፈ ፡ ደይን ፡ ወድቆ ፡ የነበረ ፡ የአዳምን ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፤ በበደለው ፡ በደል ፡ ኹሉ ፡ ክሶ ፤ የረከሰውን ፡ ቀድሶ ፤ ያረጀውን ፡ አድሶ ፡ የቀደመ ፡ ልጅነቱንና ፡ ኃይሉን ፡ መልሶ ፡ ጸሎቱን ፡ ተሰሚ ፤ መሥዋዕቱን ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ አድርጎ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ እንዲነሣና ፡ እንዲፈረድለት ፡ አደረገው ፤ ከማኅበረ ፡ መላእክት ፡ ጨመረው ፡ ማለት ፤ ነው ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ሰው ፡ ከመኾኑም ፡ አስቀድሞ ፡ ከትንሣኤውም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ እንደ ፡ ጻድቃን ፡ እንደ ፡ ሰማዕታት ፡ ማማለድ ፡ የለበትም ። በክርስቶስ ፡ ካሳ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ሥልጣን ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ተዋርዶ ፡ በመንፀፈ ፡ ደይን ፡ ወድቆ ፡ ጽድቃችን ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ኹኖ ፡ ይል ፡ የነበረ ፡ አንተም ፡ ያነን ፡ ኹሉ ፡ ጥቅስ ፡ የምታንጐደጉድበት ፡ ሰው ፤ ጸሎቱ ፡ ተሰሚ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ ስለኾነለት ፡ ወንሕነሰ ፡ ንተነብል ፡ በአምሳለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይሁበክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍሥሓ ፡ በላዕሌነ ።

እኛ ፡ በክርስቶስ ፡ ፈንታ ፡ ክርስቶስን ፡ መስለን ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ እንለምናለን ፡ እግዚአብሔርም ፣ በእኛ ፡ ስብከት ፡ ልጅነትን ፡ በእኛ ፡ ጸሎት ፡ ተድላ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይሰጣችኋል ፡ ለማለት ፡ በቃ ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፳ ።

፲፰ተኛ ፡ በክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ እንጸልያለን ፡ ብሎ ፡ በቃል ፡ የተናገረውንም ፡ በገቢር ፡ ሲገልጸው ፡ ጌታ ፡ የ፴፰ ፡ ዘመን ፡ በሽተኛ ፡ መፃጉዕን ፡ ተንሥእ ፡ ወንሣእ ፡ ዐራተከ ፡ ወሑር ፡ ተነሣና ፡ ዐልጋህን ፡ ተሸክመህ ፡ ሒድ ፡ ብሎ ፡ እንደፈወሰው ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፰ ። ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፡ ከ ቱ ፡ ማኅፀን ፡ ልምሾ ፡ ኹኖ ፡ ተወልዶ ፡ በምጽ‌ራብ ፡ በር ፡ ወድቆ ፡ ምጽዋት ፡ ሲለምን ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ ኤንያን ፡ ወርቅሰ ፡ ወብሩር ፡ አልብየ ፡ እምዘብየሰ ፡ እሁበከ ፡ ናሁ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ናዝራዊ ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ።

ወርቅ ፡ ብር ፡ የለኝም ፡ ካለኝ ፡ ግን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ በናዝሬቱ ፡ ሰው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተነሣና ፡ ሒድ ፡ ብሎ ፡ አስነሥቶታል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፫ ፡ ፩-፲፪ ።

፲፱ነኛ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባቴ ፤ ሰምተኸኛልና ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ዘወትርም ፡ እንደምትሰማኝ ፡ እኔ ፡ አውቃለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እሊህ ፡ የቆሙት ፡ ሰዎች ፡ አንተ ፡ እንደላከኝ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ እናገራለሁ ፡ ብሎ ፡ አልዓዛርን ፡ እንዳስነሣ ። ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፵፩ ። ጴጥሮስም ፡ ጸሎቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቦ ፡ ተንሥኢ ፡ ጣቢታ ፡ ብሎ ፡ የሞተችቱን ፡ አስነሣ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፴፰-፵፩ ።

፳ኛ ፡ ክርስቶስ ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ ለሰቀሉት ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ ለቸነከሩት ፡ ለአይሁድ ፡ አባ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ እስመ ፡ በዘኢየአምሩ ፡ ይገብሩ ።

አባቴ ፡ ባለማወቅ ፡ ይሠሩታልና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ ብሎ ፡ እንደጸለየላቸው ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ። ከሐዋርያትም ፡ አንዱ ፡ እስጢፋኖስ ፡ በደንጋያ ፡ ለሚወግሩት ፡ ሰዎች ፡ እግዚኦ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ ዘንተ ፡ ኀጢአቶሙ ፡ ወኢተረሲ ፡ ጌጋየ ።

አቤቱ ፡ ይህን ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፤ ዕዳ ፡ በደል ፡ አትበልባቸው ፡ ብሎ ፡ ጸለየላቸው ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፯ ፡ ፷ ።

ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ሐዋርያት ፡ ጌታን ፡ መስለው ፡ ያደረጉት ፡ ተአምራት ፡ ተነግሮ ፡ አያልቅም ፡ ዛሬውንም ፡ በቅዱሳን ፡ ዘንድ ፡ ኹሉ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ። እንግዲህ ፡ ጌታ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ በጸለየው ፡ ጸሎት ፤ ያስታረቀ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ያሉትን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ያሉትንም ፡ እንዳስታረቀ ፡ የማይካድ ፡ ነው ።

በክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ እንለምናለን ፡ ያሉ ፡ ሐዋርያትም ፡ ነፍስን ፡ ከዓለመ ፡ ነፍስ ፡ አምጥተው ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ አዋሕደው ፡ ካስነሡ ፤ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ኹነው ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ላሉት ፡ ማማለድ ፡ እንደተቻላቸው ፡ እወቅ ።

ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ባሉበት ፡ ዓለም ፤ ጻድቃንም ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስ ፡ ኹነው ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ላሉ ፡ ለደቂቀ ፡ አዳም ፡ ስለመጸለያቸው ።

---

ይህነን ፡ ለማወቅ ፡ አስቀድሞ ፡ የሰውን ፡ ተፈጥሮ ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ለተፈጠረ ፡ ሥጋ ፡ የሚያንቀሳቅሱት ፡ ደማዊት ፡ ነፍስና ፡ ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ አሉት ፤ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ደማዊት ፡ ነፍስ ፡ የምትሠለጥንበት ፡ ስለኾነ ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ እንስሳትን ፡ መስሎ ፡ እንዲኖር ፡ በዓ



www.ethiopianorthodox.org

ዐደ ፡ ነፍስም ፡ ዓለሙ ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ፡ ስለኾነ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ መላእክትን ፡ መስሎ ፡ ይኖራል ። ይህነንም ፡ ጌታ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይከውኑ ፡ በሰማያት ።

በሰማይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደሚያገለግሉ ፡ መላእክት ፡ ይኾናሉ ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፳፱-፴ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ ጥቀ ፡ ንኴንን ፡ ኅድጉሰ ፡ ዘገ ፡ ዓለም ።

የዚህን ፡ ዓለምስ ፡ ተዉትና ፡ መላእክትንስ ፡ እንኳ ፡ እንድንገዛ ፡ አታውቁምን ፡ ብሏል ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፫ ።

፳፩ኛ ፡ ከትንሣኤ ፡ አስቀድሞ ፡ ያለውም ፡ ዘመን ፡ በዓለመ ፡ ሥጋም ፡ ቢኾን ፤ በዓለመ ፤ ነፍስም ፡ ቢኾን ፡ የሥራ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ አደለም ።

ይህነንም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ አኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክት ፡ መንፈስ ፡ እሙንቱ ፡ ወይትፌነዉ ፡ ለመልእክት ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይረሱ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ።

መላእክት ፡ ኹሉ ፡ ረቂቃን ፡ ሲኾኑ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስላላቸው ፡ ለተልእኮ ፡ ይላካሉ ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ፡ ዕብ ፡ ፩ ፲፬ ።

ስለዚህ ፡ ጊዜው ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ስለኾነ ፡ ዓለሙም ፡ ሥራ ፡ የሚሠራበት ፡ ዓለም ፡ ስለኾነ ፡ መላእክትና ፡ ጻድቃን ፡ አንድነት ፡ ኾነው ፡ በዓለመ ፡ ነፍስ ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ ላሉት ፡ ለበጎዎች ፡ ይጸልዩላቸዋል ፡ በክፉዎች ፡ ይጸልዩባቸዋል ።

(ሀ) ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ሄኖክ ፡ ዓለመ ፡ መላእክትን ፡ መካነ ፡ ነፍሳትን ፡ እየዞረ ፡ ሲያይ ፡ ይስእሉ ፡ ወያስተበቍዑ ፡ ወይጼልዩ ፡ በእንተ ውሉደ ፡ ሰብእ ፡ ወጽድቅ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ይውኅዝ ፡ በቅድሜሆሙ ።

ስለሰው ፡ ልጆች ፡ መላልሰው ፡ ይጸልያሉ ። ጽድቅም ፡ እንደ ፡ ወኅ ፡ በፊታቸው ይፈሳል ፡ ብሏል ።

ወሣልሰ ፡ ቃለ ፡ ሰማዕኩ ፡ እንዘ ፡ ይስእሉ ወይጼልዩ ፡ በእንተ ፡ ውሉደ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ ውስተ ፡ የብስ ፡ ወያስተበቍዑ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእ ፡ መናፍስት ።

በሦስተኛው ፡ ቃል ፡ በየብስ ፡ ስለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በመናፍስት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ሲጸልዩ ፡ ሰማሁ ።

ወቃለ ፡ ራብዐየ ፡ ሰማዕኩ ፡ እንዘ ፡ ይሰድዶሙ ፡ ለሰይጣናት ፡ ወኢየኀድጎሙ ፡ ይበኡ ፡ ኀበ ፡ እግዚእ ፡ መናፍስት ፡ ከመ ፡ ያስተዋድይዎሙ ፡ ለእለ ፡ የኀድሩ ፡ ውስተ ፡ የብስ ።

ዐራተኛውንም ፡ ቃል ፡ ሰይጣናት ፡ በየብስ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ከመናፍስት ፡ ጌታ ፡ ጋራ ፡ ያጣሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መናፍስት ፡ ጌታ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይገቡ ፡ ሲያባርሯቸው ፡ ሰማሁ ፡ እየሁ ፡ ብሏል ።

(ለ) ዳንኤልም ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ቂሮስ ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ ሳይቀምስ ፡ ሥጋ ፡ ሳይበላ ፡ ወይን ፡ ሳይጠጣ ፡ ዘይት ፡ ሳይቀባ ፡ ሦስት ፡ ሱባዔ ፡ ያህል ፡ ቢያዝን ፡ ቢያለቅስ ፡ ቢጾም ፡ ቢጸልይ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ መጥቶ ፡ ከድ



ከሙ ፡ አጽናንቶ ፡ አንተ ፡ የተወደድክ ፡ ሰው ፡ ዳንኤል ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ወደአንተ ፡ ተልኬ ፡ አለሁና ፡ አትፍራ ፡ የምነግርህን ፡ ነገር ፡ አስተውል ፤ በአምላክህ ፡ ፊት ፡ ልብህን ፡ ለማስተዋል ፤ ሰውነትህን ፡ ለመዋረድ ፡ ከደረግኽበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነገርህ ፡ ተሰማ ፤ እኔም ፡ ልነግርህ ፡ መጣሁ ። የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ አለቃ ፡ (ሰይጣን ፡) ግን ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ተቋቋመኝ ። እነሆ ፡ ከፊተኞች አለቆች ፡ አንዱ ፡ ሚካኤል ፡ ሊረዳኝ ፡ መጣ ። እኔም ፡ ከዚያ ፡ የፋርስን ፡ ነገሥታት ፡ (ሰይጣናትን ፡) ድል ፡ ነሣሁ ። እኔም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ለሕዝብኽ ፡ የሚኾነውን ፡ አስታውቅህ ፡ ዘንድ ፡ መጣሁ ። ስለምን ፡ ወደአንተ ፡ እንደ ፡ መጣሁ ፡ አወቅህን? ፤ አሁንም ፡ ከፋርስ ፡ አለቃ ፡ (ከሰይጣን ፡) ጋራ ፡ እዋጋ ፡ ዘንድ ፡ እመለሳለሁ ፡ እኔ ፡ ስመጣ ፡ የዮናናውያን ፡ አለቃ ፡ (ሰይጣን ፡) ይመጣል ። ነገር ፡ ግን ፡ በእውነት ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ እነግርሃለሁ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከአለቃችሁ ፡ ከሚካኤል ፡ በቀር ፡ የሚረዳኝ ፡ የለም ፡ ይላል ፡ ዳን ፡ ፲፩-፳፩ ። እስራኤልም ፡ ተማርከው ፡ ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ መልአኩ ፡ አቤቱ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ የየሩሳሌምንና ፡ የይሁዳን ፡ ከተሞች ፡ እሊህን ፡ ፸ ፡ ዓመት ፡ የተቈጣሃቸውን ፡ ይቅር ፡ አትላቸውም ፡ ብሎ ፡ ቢጸልይላቸው ፡ እግዚአብሔርም ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በምሕረት ፡ እመለሳለሁ ፡ ቤቴም ፡ ይሠራባታል ፡ ብሎ ፡ መልሶለታል ፡ ዘካ ፡ ፩ ፡ ፲፪—፲፯ ።

እኳዲህም ፡ የሚጸልዩላቸው ፡ ለጊዜው ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠሩ ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ተጠጥተው ፡ ንስሐ ፡ ገብተው ፡ አማልዱን ፡ ብለው ፡ ለሚማፀኑባቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በማይመለሱትስ ፡ ይጸልዩባቸዋል ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ መልአኩ ፡ ለሄኖክ ፡ እየዞረ ፡ መካነ ፡ ነፍሳትን ሲያሳየው ። ወርኢኩ ፡ መናፍስተ ፡ ውሉደ ፡ ሰብእ ፡ እንዘ ፡ ምውታን ፡ ውእቶሙ ፡ ወቃሎሙ ፡ ይበጽሕ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወይሰኪ ። ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ተስእልክዎ ፡ ለሩፋኤል ፡ ዘሀሎ ፡ ምስሌየ ፡ ወእቤሎ ፡ ዛ ፡ መንፈስ ፡ ዘመኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘከመዝ ፡ ቃሉ ፡ ይበጽሕ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወይሰኪ ።

ወአውሥአኒ ፡ ወይቤለኒ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምአቤል ፡ ዘቀተሎ ፡ ቃየል ፡ እኁሁ ፡ ወይሰኪ ፡ ኪያሁ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ይትኀጐሉ ፡ ዘርዑ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፡ ወእምዘርዐ ፡ ሰብእ ፡ ይማስን ፡ ዘርዑ ።

የሰው ፡ ልጆች ፡ በሥጋ ፡ ሞተው ፡ ሳለ ፡ በነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነው ፡ ድምፃቸው ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደርሶ ፡ ሲካሰስ ፡ አየሁ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ሩፋኤልን ፡ እንዲህ ፡ ድምፁ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደርሶ ፡ የሚካሰስ ፡ ይህች ፡ ነፍስ ፡ የማን ፡ ናት ፡ ብዬ ፡ ብጠይቀው ። ይህች ፡ ነፍስ ፡ ወንድሙ ፡ ቃየል ፡ የገደለው ፡ የአቤል ፡ ነፍስ ፡ ናት ፡ የቃየል ፡ ዘሮች ፡ ከሰው ፡ ዘር ፡ ተለይተው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እልም ፡ ድርግም ፡ ብለው ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ እሱን ፡ ትከሳለች ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ፡ ይላል ።

ዮሐንስም ፡ በራእዩ ፡ ወሶበ ፡ ፈትሐ ፡ ኃምሰ ፡ ማኅተመ ፡ ርኢኩ ፡ ታሕተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለእለ ፡ ተቀተሉ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበእንተ ፡ ዘዐቀቦ ፡ [illegible] ፡ ወጸርሑ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ ፡ ወይቤሉ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ እግዚእ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ፡ ወጻድቅ ፡ ኢትትቤቀሎሙኑ ፡ ወኢትኴንኖሙ ፡ በእንተ ፡ ደምነ ፡ እምእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወወሀብዎሙ ፡ አልባሰ ፡ ብሩሀ ፡ ለለአሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ከመ ፡ ያዕርፉ ፡ ዓዲ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትፌጸሙ ፡ እለ ፡ ከማሆሙ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኃዊሆሙ ፡ እለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይትቀተሉ ፡ ከማሆሙ ።

አምስተኛውን ፡ ቍልፍ ፡ በከፈተ ፤ ጊዜ ፡ ከምሥዋዑ ፡ በታች ፡ ሕጉን ፡ ስለጠበቁ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ አየሁ ። እነሱም ፡ እውነተኛ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፡ ደማችንን ፡ በግፍዕ ፡ ያፈሰሱትን ፡ ሰዎች ፡ በምድር ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ለይተህ ፡ አትበቀላቸውምን ? አትፈርድባቸውምን ? እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ትታገሣቸዋለህ ፡ እያሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኹ ። ለያንዳንዳቸው ፡ ብሩህ ፡ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ሰጥተው ፡ እንደነርሱ ፡ በሰማዕትነት ፡ ይሞቱ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ምእመናን ፡ እንደነርሱ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተው ፡ እስኪፈጸሙ ፡ ድረስ ፡ ይታገሡ ፡ ዘንድ ፡ ትንሽ ፡ ታግሣችሁ ፡ ቆዩ ፡ አሏቸው ፡ ብሏል ፡ ራእ ፡ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፱—፲፪ ።

ሄኖክ ፡ ሰማዕኩ ፡ እንዘ ፡ ይሰድዶሙ ፡ ለሰይጣናት ፡ ወኢየኀድጎሙ ፡ ይባኡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ያለውና ። ዳንኤል ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ አለቃ ፡ ሰይጣን ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ተቋቋመኝ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊረዳኝ ፡ መጣ ፤ እኔም ፡ የፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ሰይጣናትን ፡ ከዚያ ፡ ድል ፡ ነሣሁ ፡ ያለው ፡ ቃል ።

፬ተኛም ፡ ሄኖክ ፡ የአቤል ፡ ነፍስ ፡ የቃኤል ፡ ዘሮች ፡ ከምድር ፡ ይጥፉልኝ ፡ ብላ ፡ ስትካሰስ ፡ አየሁ ፡ ያለውና ፡ ዮሐንስ ፡ በግፍዕ ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳት ፡ ደማችንን ፡ በግፍዕ ፡ ያፈሰሱትን ፡ ሰዎች ፡ ተበቅለህ ፡ አታጠፋቸውምን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትታገሣቸዋለህ ፡ እያሉ ፡ ሲጮኹ ፡ ሰማኋቸው ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ አስተውል ።

አንተ ፡ እውነት ፡ የሚነግርህን ፡ አትወድምና ፡ ጠላኸው ፡ እንጂ ፡ ሄኖክ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ቃል ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ እንዳይናገር እወቅ ፡ ተረዳ ።

በዓፀደ ፡ ሥጋም ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስም ፡ ቢኾኑ ፡ ጸሎት ፡ የሚጸለይላቸው ፡ ሰዎች ፡ ገና ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ራሳቸው ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ተጠጥተው ፤ ንስሐ ፡ ገብተው ፡ ኃጢአታችን ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ ጸልዩልን ፡ አማልዱን ፡ ብለው ፡ ለተማፀኑ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኃጢአታቸው ፡ ጸንተው ፡ አንመለስም ፡ ብለው ፡ በዕንቢተኛነት ፡ ለሔዱ ፡ ሰዎች ፡ አደለም ።

በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ጸልዩልኝ ፡ ብሎ ፡ መዳን ፡ እንደሌለስ ፡ በአልዓዛርና ፡ በነዌ ፡ ታውቋል ፡ ሉቃ ። ፲፮ ፡ ፲፱—፴፩ ።

ይኸውም ፡ ምልጃ ፡ የሚደረግበት ፡ ዘመን ፡ እስከ ፡ ዳግም ፡ ምጽአት ፡ ትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቁርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀንስ ፡ ኹሉም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ዋጋውን ፡ ከማግኘት ፡ በቀር ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ማማለድ ፡ እንደሌለ ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ተባብረው ፡ ነግረውና



(ሀ) እኁኒ ፡ ኢያድኅን ፡ እኅዋሁ ፡ ወኢያድኅን ፡ ሰብእ ፡ ወኢይሁብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤዛሁ ፡ ወኢተውላጠ ፡ ሤጠ ፡ ነፍሱ ። ዘፃመወ በዓለም ፡ የሐዩ ፡ ለዝሉፉ ።

ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በበጎ ሥራ ፡ የደከመ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ይድናል ፡ እንጂ ፡ በዚያን ፡ ጊዜስ ፡ ወንድሙን ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ ለወንድሙ ፡ ለውጥ ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቶ ፡ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ አያድንም ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ትፈድዮ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ። ለኹሉም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ትከፍለዋለህና ፡ ብሏል ፡ መዝ ፡ ፷፩ ፲፩፰ ። ፳፪ ፡ ፲፪ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፯ ፡

ዕዝራም ፡ እንደዚሁ ፡ ወእቤሎ ፡ እግዚኦ ፡ እመ ፡ ረከብኩ ፡ ሞገሰ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲከ ፡ ዘንተኒ ፡ ካዕበ ፡ ንግሮ ፡ ለገብርከ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ደይን ፡ ይክሉኑ ፡ ጻድቃን ፡ ሰኢለ ፡ ለኃጥአን ፡ ኀበ ፡ ልዑል ፡ ወአበውኒ ፡ ለውሉዶሙ ፡ ወውሉድኒ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ ወዘመድ ለአዝማዲሆሙ ፡ ወአዕርክት ፡ ለአዕርክቲሆሙ ።

አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ በፊትህ ፡ ባለሟልነትን ፤ አግኝቼ ፡ እንደኾነስ ፡ ለኔ ፡ ለባርያኽ ፡ ይህን ፡ የምጠይቅህን ፡ ንገረኝ ። በቁርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ጻድቃን ፡ ለኃጥአን ፤ አባቶች ፡ ለልጆች ፤ ልጆች ፡ ላባቶቻቸው ፡ ዘመዶች ፡ ለዘመዶቻቸው ፡ ወዳጆች ፡ ለወዳጆቻቸው ፡ ሊለምኑላቸው ፡ ይችላሉን ? ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

ወአውሥአኒ ፡ ወይቤለኒ ፡ እስመ ፡ ረከብከ ፡ ሞገሰ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንትየ ፡ ወዘንተኒ ፡ እነግረከ ። ዕለተ ፡ ደይንሰ ፡ ለምዕር ፡ ይእቲ ፡ ወላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ትእዛዝየ ፡ ማኅተመ ፡ ጽድቅ ፡ ያርእዮ ።

በፊቴ ፡ ባለሟልነት ፡ አግኝተሃልና ፡ ይህን ፡ የጠየቅኸኝን ፡ እነግርሃለሁ ። የቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ ለፍጻሜ ፡ ስለኾነች ፡ ለኹሉም ፡ ትእዛዜ ፡ የተጻፈበትን ፡ የጽድቅ ፡ መዝገብ ፡ ያሳዩታል ።

በከመ ፡ ይእዜ ፡ ኢይፌንዎ ፡ አብ ፡ ለወልዱ ፡ ህየንቴሁ ፡ ወኢወልድ ፡ ለአቡሁ ፤ ወኢእግዚእ ፡ ለገብሩ ፡ ወኢዐርክ ፡ ለዐርኩ ፡ ከመ ፡ ይድወይ ፡ ህየንቴሁ ፡ አው ፡ ይስክብ ፤ አው ፡ ይብላዕ ፤ አው ፡ ይትፈወስ ፤ ከማሁ ፡ ግሙራ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ሰኢለ ፡ ፩ ፡ ለካልኡ ፤ ወአልቦ ፡ መኑሂ ፡ ዘያገብእ ፡ ክበደ ፡ ዚአሁ ፡ ላዕለ ፡ ቢጹ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ጽድቆ ፡ ይጸውር ፡ ወምግባሪሁ ፡ ዘዚአሁ ።

ዛሬ ፡ ሰው ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ አባት ፡ ልጁን ፤ ልጅ ፡ አባቱን ፡ ጌታ ፡ ባሪያውን ፡ ወዳጅ ፡ ወዳጁን ፡ ስለኔ ፤ ፈንታ ፡ ታመምልኝ ፡ ወይም ፡ መድኃኒት ፡ ብላልኝ ፡ ወይም ፡ ታከምልኝ ፡ ወይም ፡ ሙትልኝ ፡ ብሎ ፡ እንደማይልከው ፡ ያን ጊዜም ፡ እንደዚሁ ፡ ኹሉም ፡ ለየራሱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሥራው ያገኛል ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፡ የርሱን ፡ ሸክም ፡ ለወንድሙ ፡ ሊያሸክም ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ አንዱም ፡ ላንዱ ፡ ሊለምንለት ፡ አይችልም ፡ አለኝ ።

ወአውሣእክዎ ፡ ወእቤሎ ፡ እፎኬ ፡ ረከብነ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡ ሰአለ ፡ አብርሃም ፡ [illegible] ሰዶም ፡ ወሙሴ ፡ በእንተ ፡ አበዊነ ፡ አመ ፡ አበሱ ፡ በገዳም ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወዮሴፅ ፡ በእንተ ፡ እስራኤል ፡ አመ ፡ አካን ፡ ወሳሙኤል ፡ በመዋዕለ ፡ ሳኦል ፤ ወዳዊትኒ ፡ በእንተ ፡ ብድብድ ፤ ወሰሎሞንሂ ፡ በእንተ ፡ መቅደስ ፤ ወኤልያስኒ ፡ በእንተ ፡ ዝናም ፡ ወበእንተ ፡ ምውት ፡ ከመ ፡ ይሕየው ፤ ወሕዝቅያስሂ ፡ በእንተ ፡ ሕዝብ ፡ በመዋዕለ ፡ ሰናክሬም ፡ ወብዙኃን ፡ በእንተ ፡ ብዙኃን ። ሶበ ፡ እንከ ፡ ይእዜ ፡ እንዘ ፡ መዋቲ ፡ ይበቍል ፡ ወዓመፃ ፡ ትበዝኃ ፡ ሰአሉ ፡ ጻድቃን ፡ በእንተ ፡ ኃጥአን ፡ በእሮ ፡ እንከ ፡ ኢኮነ ፡ ከማሁ ፡ ይእተ ዓሚረ ።

እኔም ፡ መልሼ ፡ እነሆ ፡ ቀድሞ ፡ አብርሃም ፡ ስለሰዶም ፤ አባቶቻችንም ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ስለነርሱ ፤ አካንም ፡ በበደለ ፡ ጊዜ ፡ ዮሴፅ ፡ ስለእስራኤል ፤ ሳሙኤልም ፡ ስለሳኦል ፤ ዳዊትም ፡ በቸነፈር ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፤ ሰሎሞንም ፡ ስለቤተ ፡ መቅደስ ፤ ኤልያስም ፡ ፫ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ዝናም ፡ እንዳይ ዘንም ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንዲዘንም ፡ የመበለቲቱም ፡ ልጅ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ እንዲነ ሣላት ፤ ሰናክሬምም ፡ በዘመተበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ስለሕዝቡ ፤ እንደዚሁም ፡ ብዙዎች ፡ ጻድቃን ፡ ስለብዙዎች ፡ ኃጥአን ፡ እንደ ፡ ጸለዩላቸው ፡ ተጽፎ ፡ እናገኛለን ፤ እንግዲህ ፡ ዛሬ ፡ ሞት ፡ በሠለጠነበት ፡ ዐመፅ ፡ በበዛበት ፡ ዘመን ፡ ጻድቃን ፡ ስለኃጥ አን ፡ የሚጸልዩላቸው ፡ ከኾነ ፡ ያንጊዜ ፡ ስለምን ፡ እንደዚሁ ፡ አይደረግም ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

ወአውሥአኒ ፡ ወይቤለኒ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ዓዲ ፡ ማኅለቅቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዘይእዜ ፡ ወስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ክሡተ ፡ ዘይነብር ፡ ለዝ ላፉ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ሰአሉ ፡ ጽኑዓን ፡ በእንተ ፡ ድኩማን ። ወዕለተ ፡ ደይንሰ ፡ ማኅለቅቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወቀዳሚሁ ፡ ውእቱ ፡ ለዓለም ፡ ዘይመጽእ ፡ በዘየኃ ልቅ ፡ መዋቲ ፡ ወይቀውም ፡ ዘኢይመውት ። ወእምዝ ፡ ተሥዕረ ፡ ድካም ፡ ወየኃ ልቅ ፡ ተስናን ፡ ወትበቍል ፡ ጽድቅ ፡ ወትጸንዕ ፡ ርትዕ ፡ ወይእተ ፡ አሚረ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ምሒሮቶ ፡ ለዘተመውዐ ፡ በደይን ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ አሕምሞቶ ፡ ለዘሞአ ።

ዛሬ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜው ፡ ገና ፡ ስለኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጌትነቱ ፡ የሚያወርሰው ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖረው ፡ ዕሜተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ገና ፡ ስለኾነ ፡ ብርቱዎቹ ፡ ለደካሞች ፤ ጻድቃን ፡ ለኃጥአን ፡ ይጸልዩላቸዋል ። የቁ ርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ሞትን ፡ የተመላ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ አልፎ ፤ ሞት ፡ የሌ ለበት ፡ የሚመጣው ፡ ዓለም ፡ የሚተካበት ፡ ጊዜ ፡ ስለኾነ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ መውጣት ፡ መውረድ ፡ ድካም ፡ ይቀራል ፤ ፀብ ፡ ክርክር ፡ የለም ፤ ጽድቅ ፡ ትበዛ ለች ፤ ርትዕ ፡ ትጸናለች ፤ ስለዚህ ፡ ያንጊዜ ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ መከራ ፡ ሊያመጣበት ፤ ድል ፡ ተነሥቶ ፡ ገሃነም ፡ ለወረደው ፡ ሰው ፡ ሊለምነለትና ፡ ሊያማልደው ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ። ዕዝ ፡ ሱቱ ፡ ፯ ፡ ፳፯ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ዘረዘር ኩልህ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ከጌታ ፡ ቃል ፡ ሰምታ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ንባባቸ ውን ፡ ከምሥጢራቸው ፡ አስማምታ ፤ ምልጃ ፡ የሚገባቸው ፡ በምን ፡ ግብር ፡ ጸን



ተው ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ መኾናቸውን ፡ ለይታ ፤ ምልጃ ፡ የሚደረግበትን ፡ በታ ፡ ምልጃ ፡ የሚደረግበትን ፡ ጊዜና ፡ የማይደረግበትን ፡ ጊዜ ፡ አጣርታ ፡ ታስተምራ ለች ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ነፋስ ፡ እንደ ፡ በተነው ፡ ነዶ ፡ አለመልኩ ፡ አንዱን ፡ ከንዱ ፡ እያማታህ ፡ እንደምትዘባርቀው ፡ አደለም ።

የሞኝ ፡ ዘፈን ፡ ኹልጊዜ ፡ አበባየ ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ በየደጁ ፡ ምልጃ ፤ ምልጃ ፡ ለምትለው ፡ ጠቅላላ ፡ መልሱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

አንተ ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አንድ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴን ፡ የሚሻ ፡ ሰው ፡ ቸር ፤ ብለው ፡ ቸር ፡ ይለኛል ፡ ብሎ ፡ መጥቶ ፡ ቸሩ መምህር ፡ ሆይ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እወርስ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ልሥራ ፡ ቢለው ፤ አንተ ፡ ሰው ፡ ቸር ፡ ብለው ፡ ቸር ፡ ይለኛል ፡ መስሎህ ፡ ነውን ? ከንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቸር ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ መልስ ።

ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ ኹሉ ፡ በዓመፅ ፡ ተከክሎ ፡ በደለ ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ የሚሠ ራት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ስለዐመፀኞች ፡ ለተናገረው ፡ ቃል ፡ ተመ ሳሳይ ፡ ተጫፋሪ ፡ አድርገህ ፡ በመጥቀስህ ፡ ክርስቶስን ፡ ከቸርነት ፡ አውጥተህ ፡ ለዐ መፀኞች ፡ ተባባሪ ፡ በማድረግህ ፡ እውቀትህ ፡ ባስተዋዮች ፡ ዘንድ ፡ ሲመዘን ፡ ከም ናምን ፡ የቀለለ ፡ ከንቱ ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ።

፳፪ ቸሩ ፡ አምላካችን ፡ ማናቸውም ፡ ፍጡር ፡ የአዳምን ፡ ዕዳ ፡ ከፍሎ ፡ ከጌታው ፡ ጋራ ፡ ለማስታረቅና ፡ አማላጅም ፡ ኾኖ ፡ ፍጡር ፡ ለፈጣሪው ፡ ካሳ ፡ መክስ ፡ እንደማይቻለው ፡ አውቆ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ታራቂና ፡ አስ ታራቂ ፡ አማላጅም ፡ ኾኖ ፡ ዕዳችንን ፡ በመስቀሉ ፡ ከፈለው ፡ እንጂ ፡ የአድኅኖተ ፡ ስብእን ፡ ነገር ፡ ፍጡራንን ፡ ልኮ ፡ እንዳልፈጸመው ፡ አቡሊድስ ፡ ዘሮም ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ በ፳ተኛው ፡ ድርሳኑ ፡ እንደሚከተለው ፡ ቃል ፡ አስረድቷል ።

ኢፈነወ ፡ ሐዋርያ ፡ ወኢነቢየ ፡ አላ ፡ ለሊሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጽአ ፡ ወአድኃነነ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ተስፋነ ፡ በሰብእ ፡ ወኢኾኩን ፡ ርጉማነ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ ርጉም ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘይሴፎ ፡ ሰብአ ፡ ዘወጽአት ፡ ልቡናሁ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ኲኄላ ፡ ወይትነጻሕ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ይብስት ፡ እንተ ፡ ኢትፈሪ ፡ ወኢይሬኢ ፡ ሠናየ ፡ ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፭—፰ ።

አኮ ፡ መልአክ ፡ ወአኮ ፡ ተንባል ፡ አላ ፡ ለሊሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጽአ ፡ ወአድኅነነ ፡ ወሕይወትሂ ፡ ኮነት ፡ ለነ ፡ በእንተ ፡ ቅስብእቱ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ተስፋነ ፡ በሰብእ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ዘየሐዩ ፡ ወኢይሬእያ ፡ ለሞት ፡ ወመኑ ፡ ዘያድኅና ፡ ለነፍሱ ፡ እምእደ ፡ ሲኦል ። እምከመሰ ፡ ኢክህሉ ፡ አድኅኖ ፡ ርእሶሙ ፡ እፎመ ፡ እንከ ይክሉ ፡ አድኅኖ ፡ ኪያነ ፡ እያለ ፡ ደጋግሞ ፡ ተናግሯል ፡ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፵፯ ፡ ፵፰ ፡ ስለምትለው ።

አቡሊድስ ፡ ዘሮም ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በአዳም ፡ በደል ፡ ምክንያት ፡ ከመጣበት ፡ ፍዳ ፡ መርገም ፡ ለማዳን ፡ የሚደረገውን ፡ ካሣ ፡ አንድ ፡ መልአክ ፡ ወይም ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ሐዋርያ ፡ ልኮ ፡ እንዳልፈጸመው ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ እንደፈጸመው ፡ ከመጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ እየጠቀሰ ፡ እኔ ፡ ከላይ ፡ የተረከሁልህን ፡ የመሰለ ፡ ታሪክ ፡ ይተረክልሃል ፡ እንጂ ፡ በሰውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መካከል ፡ ተጋ ርዶ ፡ የነበረው ፡ የጥል ፡ ግድግዳ ፡ በክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ ከፈራረሰ ፡ ወዲህ ፡ ባለ ሟልነትን ፡ ያገኙ ፡ ጻድቃን ፡ የምግባር ፡ ሕጸጽ ፡ ኖሮባቸው ፡ በንስሐ ፡ ለሚለማ መጡ ፡ ኃጥአንን ፡ አያማልዱም ፡ አላለም ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፫ የኢትዮጵያ ፡ ብርሃን ፡ ሊቁ ፡ ጌታዬ ፡ አለቃ ፡ ታዬም ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ለሰው ፡ ማዳን ፡ ሊቻለው ፡ ለየንፍሱም ፡ ማዳን ፡ እንደማይቻለው ፡ ምክሐ ፡ ምእመናን ፡ በተባለው ፡ ድርሰታቸው ፡ ገልጸው ፡ አስረድተውናል ፡

ወላድያኒነ ፡ ቀደምት ፡ ድኅረ ፡ በኃጢአት ፡ ወድቁ ።
ፍትሐ ፡ ሞት ፡ መጽኦሙ ፡ ላዕለ ፡ አዳም ፡ ወደቂቁ ።
እስከነ ፡ ወረዱ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ዕመቁ ።
ኖኅ ፡ ወአብርሃም ፡ ወካልአንሂ ፡ እለ ፡ በግብሮሙ ፡ ተዐውቁ ።
ኢይበቍዖሙ ፡ ጽድቆሙ ፡ ዳዕሙ ፡ በጦርገመ ፡ እዳም ፡ ወሞት ፡ ኵሎሙ ፡ ተሐንቁ ።
በጽድቀ ፡ ርእስከሙ ፡ ቀዊመ ፡ እለ ፡ ትጽሕቁ ።
እምጸጋ ፡ መድኃኒት ፡ ኀበ ፡ ደይን ፡ ከመ ፡ ኢትደቁ ።
መጻሕፍተ ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ በአስተሐይጾ ፡ ጠይቁ ።
እንበለ ፡ ክርስቶስ ፡ ብርእዮሙ ፡ ከመ ፡ ኢድኅኑ ፡ በሕቁ ።
አብርሃም ፡ በምግባሩ ፡ ወኢዮብ ፡ በጽድቁ ። ስለምትለው ።

የቀደሙ ፡ አባቶቻችን ፡ በኃጢአት ፡ ከተሰነከከሉ ፡ በኋላ ፡ በአዳምና ፡ በልጆቹ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈረደባቸው ። በበጎ ፡ ሥራቸው ፡ የታወቁ ፡ ኖኅና ፡ አብርሃም ፡ ሌሎችም ፡ በአዳም ፡ መርገም ፡ ተያዙ ፡ እንጂ ፡ በሥራቸው ፡ ሊድኑ ፡ አልቻሉምና ፡ የራሳችን ፡ ሥራ ፡ ይበቃናል ፡ የምትሉ ፡ ሰዎች ፡ ከክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ እንዳትወድቁ ፤ ያለክርስቶስ ፡ አስታራቂነት ፡ አብርሃም ፡ በሃይማኖቱ ፤ ኢዮብ ፡ በትዕግሥቱ ፡ ሊድኑ ፡ አለመቻላቸውን ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ መርምራችሁ ፡ ተረዱ ፡ እያሉ ፡ እኔ ፡ ከላይ ፡ እንደተረኩልህ ፡ የአቡሊድስን ፡ ንግግር ፡ የመሰለ ፡ ታሪክ ፡ ከብሉያት ፡ አበውን ፡ እየጠቀሱ ፡ ይተርኩልሃል ፡ እንጂ ፤ ሰው ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ ታርቆ ፡ ከጥንተ ፡ ባለሚልነቱ ፡ ከተመለሰ ፡ ወዲህ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በመናቅ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ በመቀበል ፡ ክርስቶስን ፡ መስለው ፡ ተገኝተው ፡ ባለሚልነታቸው ፡ የታወቀላቸው ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ የምግባር ፡ ዳኅፅ ፡ አግኝቷቸው ፡ በንስሐ ፡ ለሚለማመጡ ፡ ኃጥአን ። ከክርስቶስ ፡ አያማልዷቸውም ፡ አላሉም ። እንዲያውም ፡ ጆሮ ፡ ፃማውን ፡ አይሰማም ፡ እንደተባለው ፡ በትሰማ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለቃ ፡ ታየስ ፡ የራሳችን ፡ ሥራ ፡ ይበቃናል ፡ የምትሉ ፡ ሰዎች ፡ ከክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ እንዳትወድቁ ፡ ተጠንቀቁ ፡ በማለታቸው ፡ አንተን ፡ ነክተውሃል ። እኔም ፡ የምግባር ፡ ዳኅፅ ፡ አግኝቷቸው ፡ ንስሐ ፡ ለገቡ ፡ ኃጥአን ፡ ፍጹማን ፡ የኾኑት ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ ከክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ ይለምኑላቸዋል ፡ እላለሁ ፡ እንጂ ፡ ከክርስቶስ ፡ በቀር ፡ ለቤዛ ፡ ዓለም ፡ የተሰቀለ ፡ በሞቱ ፡ ዓለምን ፡ ያዳነ ፡ ሌላ ፡ ጻድቅ ፡ ሰማዕት ፡ ወይም ፡ መልአክ ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ አልናገርምና ፡ አቡሊድስ ፡ ዘሮምና ፡ አለቃ ፡ ታየ ፡ ከተናገሩት ፡ ሌላ ፡ እንዳልተናገርኩ ፡ እወቅ ።

ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ንጹሕ ፡ ለሰው ፡ ሊያጸድቅ ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ ብለህ ፡ የምትቀጥለው ፡ ነገር ፡ የሞኝ ፡ ዘፈን ፡ ኹልጊዜ ፡ አበባዬ ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ ያነኑ ፡ ከመደረት ፡ በቀር ፡ መልስ ፡ የሚሰጥበት ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ የለበትም ። ወደፊትም ፡ የምትቀጥላቸው ፡ ምዕራፎች ፡ የአርእስታቸውን ፡ ስም ፡ ከመለወጥ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምታመጣው ፡ ነገር ፡ እጅግም ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ። አንድን ፡ ነገር ፡ መላልሶ ፡ መጻፍ ፡ ቀለምና ፡ ብርዕ ፡ መጨረስ ፡ የጸሐፊንና ፡ የተመልካችን ፡ ጊዜ ፡ ማባከንና ፡ ማሰልቸት ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ካላገኘሁበት ፡ በቀር ፡ ስላማላጅነት ፡ የምጽፍልህ ፡ የለኝም ።



## ፯ተኛ ፡ ምዕራፍ ።

## ስለፍጡር ፡ ጭከናና ፡ የአምላክ ፡ ርኅራኄ ።

፩ ክርስቶስ ፡ ጨካኝ ፡ ነውና ፡ ቢኾን ፡ ሞግቶ ፡ ባይኾን ፡ ተውሶ ፡ ከኀሃነም ፡ የሚያወጣህ ፡ አንድ ፡ መልአክ ፡ ወይም ፡ ጻድቅ ፡ ወዳጅ ፡ አብጅ ፡ ይሉሃል ፡ ማለትን ፡ አቡሃ ፡ ለሐሰት ፡ ከተባለው ፡ ከሰይጣን ፡ ድምፅ ፡ ሰምተኸው ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባለፈው ፡ እንዳስረዳሁህ ፡ ከክርስቶስ ፡ ያማልዱሃል ፡ በመንፈስ ፡ ይረዱሃል ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ የለም ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

፪ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ አድሮ ፡ አኮ ፡ በመልእክ ፡ ወአኮ ፡ በተንባል ፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ ፡ ጻድቃን ፡ ያማልዳሉ ፡ ማለት ፡ በፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፤ እስከ ፡ ምትለው ፡ ድረስ ፡ የጻፍከው ፡ አርእስቱን ፡ ከመለወጥህ ፡ በቀር ፡ ያኑኑ ፡ ስለአማላጅነት ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ የጻፍከውን ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ መልስ ፡ የተሰጠበትን ፡ ስለኾነ ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ ሲመላልሱ ፡ መኖር ፡ ሞኝ ፡ ሥራ ፡ ፊት ፡ ከማስመሰል ፡ በቀር ፡ ጠቃሚ ፡ አለመኾኑን ፡ ተመልክቼ ፡ አልፌዋለሁ ፡ ቢያስፈልግህም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የጻፍኩልህን ፡ ተመልከት ።

፫ ፍጡር ፡ ጭከናና ፡ ወስላታነት ፡ ካልኾነ ፡ ርኅራኄና ፡ ቅንነት ፡ መሥራት ፡ አይቻለውም ። ፍጡር ፡ ጭከና ካልኾነ ፡ ርኅራኄ ፡ አይገኝበትም ፡ ብለህ ፡ ለዚሁ ፡ ማስረጃ ፡ (ሀ) ሐዋርያት ፡ እንግድነት ፡ አናሳድራችሁም ፡ ያሉዋቸውን ፡ ሰዎች ፡ እንደኤልያስ ፡ እሳት ፡ አዝንመን ፤ እናጥፋቸው ፡ ቢሉ ፡ ክርስቶስ ፡ እናንተ ፡ የየትኛው ፡ መንፈስ እንደኾናችሁ ፡ አላወቃችሁምን ፡ ተዉ ፡ እኔ ፡ ሰውን ፡ ላድን ፡ እንጂ ፡ ላጠፋ ፡ አልመጣሁም ፡ ብሎ ፡ ከለከላቸው ፡ ብለሃል ፡ ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፶፩—፶፭ ።

(ለ) ኤልሳዕ ፡ ኹለት ፡ ድቦች ፡ አስነሥቶ ፡ ፵፪ ፡ ሕፃናት ፡ መስፈጀቱን ።

(ሐ) ኤልያስ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ዝናም ፡ አቁሞ ፡ ሰማይ ፡ ለጉሞ ፡ ሰዎች ፡ በረሃብ ፡ ማለቃቸውን ።

(መ) ፻፲፱ ፡ አለቆችን ፡ ከነጭፍሮቻቸው ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ አውርዶ ፡ ማቃጠሉን ።

(ሠ) ጳውሎስ ፡ የብራየሱስን ፡ ዐይን ፡ በተአምራት ፡ ማጥፋቱን ።

(ረ) ነፍሳት ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ መከሰሳቸውን ፡ ጠቅሰኽ ፡ ስለርኅራኄ ፡ ክርስቶስ ፡ የዕውራንን ፡ ዐይን ፡ ማብራቱን ፡ ድውያንን ፡ መፈወሱን ፡ ጽፈሃል ።

እውነት ፡ ራሷን ፡ ቢይዟት ፡ እግሯ ፤ እግሯን ፡ ቢይዟት ፡ ራሷ ፡ ብቅ ፡ ማለቷ ፡ የማይቀር ፡ ስለኾነ ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በዳዮችና ፡ ቂም ፡ ነገር ፡ የማይገኝባቸው ፡ ናቸው ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ናቸው ፡ ርሳቸውስ ፡ ኹላቸው ፡ በሚዛን ፡ ተመዝነው ፡ ከምናምን ፡ የቀለሉ ፡ ናቸው ፡ ከምትላቸው ፡ ከሰዎች ፡ ወገን ፡ ፈጣሪ ፡ እንጂ ፡ ፍጡር ፡ ሊያደርገው ፡ የማይቻለው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ኃይል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ጻድቅ ፡ የሚገኝባቸው ፡ መኾናቸውን ፡ ከተረዳኽልኝስ ፡ የጭከኔንና ፡ የርኅራኄን ፡ ነገር ፡ ዘርዝሬ ፡ አስረዳሃለሁና ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ ስማ ።

፬ ርኅራኄም ፡ ኾነ ፡ ጭከኔም ፡ ኾነ ፡ ለሰው ፡ የባሕርዩ ፡ ተስማሚ ፡ ግብር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አደለም ። ስለዚህ ፡ ያ ፡ የሚደረግለት ፡ ወይም ፡ የሚደረግበት ፡ ሰው ፡ ኸቶ ፡ ያመጣቸዋል ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ኾነ ፡ ቅዱሳንም ፡ ኾኑ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ያለምክንያት ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የሚያመጧቸው ፡ አደሉም ። ይህንም ፡ በነዚሁ ፡ አንተ ፡ በጠቀስኳቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ማስረዳት ፡ ይቻላል ።

## ፩ኛ ፡ ስለኤልያስ ።

(ሀ) አክዓብና ፡ ኤልዛቤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከድተው ፡ ጣዖት ፡ አቁመው ፡ በ፰፻፶፯ ፡ ካህናተ ፡ ጣዖት ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ እየተመሩ ፡ ቢያስቸግሩ ፡ ኤልያስ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ አምልኮት ፡ ቀንቶ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ዝናም ፡ አቁሞ ፡ ሰማይ ፡ ለጉሞ ፡ እንቢተኞች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አምላክነት ፡ እስኪያውቁት ፡ ድረስ ፡ ቀጣቸው ።

ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልተናወጸች ፡ ያች ፡ መበለት ፡ ግን ፡ ልጅዋ ፡ ቢሞትባት ፡ ሔዳ ፡ ነቢዩ ፡ እግዚአብሔር ፤ ከኃጢአቴ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ አንተ ፡ ከኔ ፡ ቤት ፡ ልትገባ ፡ የማይገባኝን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ልጄ ፡ ሞተብኝ ፡ ብላ ፡ በትሕትና ፡ ብትጮህለት ፡ ልጂሽን ፡ ስጪኝ ፡ ብሎ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ መላልሶ ፡ በጸለየው ፡ ጸሎት ፡ ልጅዋን ፡ ከሞት ፡ አስነሣላት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይህነን ፡ ራብና ፡ ቅጣት ፡ አክዓብና ፡ ኤልዛቤል ፡ ሕዝቡም ፡ በዓመፅ ፡ አንድ ፡ ኹነው ፡ ተካክለው ፡ እንዳመጡት ።

ያች ፡ መበለትም ፡ የልጅዋን ፡ ትንሣኤ ፡ እኔ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነኝ ፡ ነቢዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከቤቴ ፡ ልትገባ ፡ አይገባኝም ፡ ብላ ፡ ራሷን ፡ ዝቅ ፡ በማድረጓ ፡ እንዳመጣችው ፡ አስተውል ። ፩ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯-፳፬ ።

(ለ) ፪ተኛም ፡ አካዝያስ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ንቆ ፡ አቃሎ ፡ ነቢዩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መጠየቁን ፡ ትቶ ፡ ሑሩ ፡ ተሰአሉ ፡ ሌተ ፡ ኀበ ፡ በዓለ ፡ ጽንጽንያ ፡ አምላከ ፡ አቃሮን ፡ ለእመ ፡ አሐዩ ፡ እምዛቲ ፡ ደዌ ።

የአቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ከዚች ፡ ደዌ ፡ እድን ፡ እንደኾነ ፡ ጠይቁልኝ ፡ ብሎ ፡ መላክተኞችን ፡ ቢልክ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ መጥቶ ፡ ኤልያስን ፡ ውጣና ፡ የሠማርያን ፡ ንጉሥ ፡ መላክተኞች ፡ ተገናኛቸውና ፡ የአቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ልትጠይቁ ፡ የምትሔዱ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ የለምን ፤ አሁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተኛህበት ፡ አልጋ ፡ አትነሣም ፡ ትሞታለህ ፡ ብሎሃል ፡ በሉት ፡ በላቸው ፡ አለው ።

ኤልያስም ፡ መልአኩ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ አደረገ ፤ የሠማርያም ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ መኾኑን ፡ አውቆ ፡ ይዛችሁ ፡ አምጡት ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ያምሳ ፡ አለቃ ፡ እስከ ፡ ጭፍሮቹ ፡ ላከ ።

ያምሳ ፡ አለቃውም ፡ ሔዶ ፡ በትሕትና ፡ ሳይኾን ፡ በድፍረት ፡ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፤ ንጉሥ ፡ ይጠራሃልና ፡ ፈጥነህ ፡ ውረድ ፡ ቢለው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ከኾንኩስ ፤ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ትውረድና ፡ አንተን ፡ ከነተከታዮችህ ፡ ትብላህ ፡ አለው ። እንደ ፡ ቃሉ ፡ ተ[illegible]



ኹለተኛውም ፡ ያምሳ ፡ አለቃ ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ በትዕቢት ፡ ታጅሮ ፡ መጣ ፡ እንደዚሁ ፡ ተደረገበት ።

ሦስተኛው ፡ ያምሳ ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ እንደነዚያ ፡ በትዕቢት ፡ ሳይኾን ፡ በትሕትና ፡ ኾኖ ፡ ከኤልያስ ፡ ፊት ፡ በጉልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፤ ነፍሴ ፡ በፊትህ ፡ የከበረች ፡ ትኹን ፡ አብረውኝ ፡ ያሉት ፡ የነዚህ ፡ ያምሳውም ፡ ነፍስ ፡ እንዲሁ ፡ የከበረች ፡ ትኹን ፡ ብሎ ፡ ቢለምነው ፡ እንደነዚያ ፡ እንደፊተኞች ፡ ያምሳ ፡ አለቆች ፡ ሳይኾን ፡ አክብሮ ፡ ተቀብሎታል ፡ ፪ ነገ ፡ ፩ ፡ ፩-፲፰ ።

እንግዲህ ፡ እኒህ ፡ ፫ቱም ፡ ያምሳ ፡ አለቆች ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ዋጋቸውን ፡ አገኙ ፡ እንጂ ፡ ኤልያስ ፤ በግፈኛነት ፡ ወይም ፡ በመድሎኛነት ፡ ያደረገ ፡ አደለም ። ስለዚህ ፡ ጥቅማቸውም ፡ ጉዳታቸውም ፡ በየራሳቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኤልያስን ፡ የሚያስወቅሰው ፡ አደለም ።

ኤልያስስ ፡ እንዲህ ፡ በማድረጉ ፡ ቀናዒ ፡ ለሕገ ፡ አምላኩ ፡ ተብሎ ፡ ተመሰገነበት ፤ በሠረገላ ፡ እሳት ፡ ወደሰማይ ፡ አረገበት ፡ ፪ ነገ ፡ ፪ ፡ ፩-፲፪ ።

## ፪ተኛ ፡ ስለ ፡ ኤልሳዕ ።

(ሀ) ኤልሳዕ ፡ መምህሩን ፡ ኤልያስን ፡ ሸኝቶ ፡ ሀብተ ፡ ኤልያስን ፡ ባጠፌታ ፡ አግኝቶ ፡ ሲመለስ ፡ የኢያሪኮ ፡ ሰዎች ፡ በዚች ፡ ሀገር ፡ መኖር ፡ መልካም ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ውኃዋ ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ሴቶችን ፡ ታመክናለች ፡ ብለው ፡ ቢነግሩት ፡ አዲስ ፡ መንቀልና ፡ ጨው ፡ አስመጥቶ ፡ ይህ ፡ ውኃ ፡ ከምረቱ ፡ ይዳን ፡ ብሏል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ከምንጩ ፡ ላይ ፡ ቢቀብርበት ፡ ውኃው ፡ ከምረቱ ፡ ድኗል ፤ ርጉዞች ፡ ቢጠጡት ፡ የማያስጨንግፍ ፡ ኾኗል ። ለኢያሪኮ ፡ ሰዎች ፡ ያደረገላቸውን ፡ ርኅራኄ ፡ አየህን ?

ለኢያሪኮ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ርኅራኄ ፡ ያደረገ ፡ ኤልሳዕ ፡ ፊሩ ፡ ሲዘል ፡ መጠምጠሚያው ፡ ከራሱ ፡ ቢወልቅ ፡ የራሱ ፡ በራ ፡ ታየ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ አሳዳጊ ፡ የበደላቸው ፡ ሕፃናት ፤ መላጤ ፡ መሊጥ ፡ ቡሄ ፡ ቡሄ ፤ እስኪ ፡ ደግሞ ፡ ዝለል ፡ እያሉ ፡ ቢዘብቱበት ፡ ዐቅማቸውን ፡ ይወቁት ፡ ሲል ፡ ፪ ፡ ድቦች ፡ አስነሥቶ ፡ አስፈጅቷቸዋል ። ፪ ነገ ፡ ፪ ፡ ፲፱-፳፭ ።

(ለ) ደግሞ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ አንዲት ፡ ደኃ ፡ ሴት ፡ መጥታ ፡ ባሌ ፡ ሞተብኝ ፡ ባሌ ፡ የተበደረው ፡ ዕዳ ፡ ነበረበት ፡ ያነን ፡ ዕዳ ፡ መክፈል ፡ ስላልቻልኩ ፡ ልጆቼን ፡ ወስደው ፡ ባሮች ፡ አድርገው ፡ ሊገዟቸው ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ብትጮኽለት ፡ ምን ፡ ላደርግልሺ ፡ ትወጃለሽ ፡ ከቤትሽስ ፡ ምን ፡ አለ ፡ አላት ፡ ከዘይት ፡ ማሠሮ ፡ በቀር ፡ በቤቴ ፡ ምንም ፡ የለ ፡ አለችው ።

ከየጎረቤቶችሽ ፡ ብዙ ፡ ማድጋ ፡ እየተዋስሽ ፡ አምጥተሽ ፡ ያነኑ ፡ ትንሹን ፡ ዘይት ፡ በየማድጋው ፡ ቅጂው ፡ አላት ። እንዳላት ፡ ብታደርግ ፡ ባቀረበችው ፡ [illegible] ዘይቱ ፡ ሞላ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሔዳ ፡ እንዲህ ፡ ተደረገልኝ ፡ ብትለው ፡ ይህን ፡ ዘይት ፡ ሸጠሽ ፡ ዕዳሽን ፡ ከፍለሽ ፡ የተረፈሽን ፡ ከልጅሽ ፡ ጋራ ፡ ተመገቢ ፡ ብሏታል ። ፪ ነገ ፡ ፬ ፡ ፩-፯ ። ኤልሳዕ ፡ ለዚች ፡ ሴት ፡ ያደረገላትን ፡ ርኅራኄ ፡ አየኸን ።

(ሐ) ፫ተኛም ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ኤልሳዕን ፡ ሊገለው ፡ ወዶ ፡ አምጡልኝ ፡ ብሎ ፡ ጭፍራ ፡ ሰደደ ። ኤልሳዕም ፡ እሊያን ፡ ጭፍሮች ፡ ዐይናቸውን ፡ አጥፍቶ ፡ በተአምራት ፡ ማርኮ ፡ ከሠማርያ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ወሰዳቸው ። የሠማርያም ፡ ንጉሥ ፡ ተቈጥቶ ፡ ልግደላቸው ፡ ቢለው ፡ አይኸንም ፡ በሰይፍህና ፡ በቀሥትኽ ፡ የማረከውን ፡ ግደል ፡ እንጂ ፡ ለነዚህስ ፡ የሚበሉት ፡ የሚጠጡት ፡ ስጥተህ ፡ ሸኝተህ ፡ ስደዳቸው ፡ አለው ። እንዳለው ፡ አድርጎ ፡ ሰዷቸዋል ። ፪ ነገ ፡ ፮ ፡ ፱-፳፬ ። ኤልሳዕ ፡ ሊገሉት ፡ ለመጡ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ርኅራኄ ፡ እንዳደረገላቸው ፡ አየህን ?

## ፫ተኛ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ።

(ሀ) ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ የብራየሱስን ፡ ዐይን ፡ ዐጠፋ ፡ ብለህ ፡ ወቅሰኸ ዋል ። ይህ ፡ ብራየሱስ ፡ አሰተኛ ፡ አስማተኛ ፡ ጠንቋይ ፡ ነበረና ፤ ሰርግዮስ ፡ ጳውሎስ ፡ በወንጌል ፡ ሊያምን ፤ ወንጌልን ፡ ሊቀበል ፡ ወዶ ፡ በርናባስንና ፡ ሳውልን ፡ አስጠርቶ ፡ ንገሩኝ ፡ ቢላቸው ፤ ይህ ፡ ብራየሱስ ፡ ዕንቅፋት ፡ እየኾነ ፡ በወንጌል ፡ እንዳያምን ፡ ሲያደርገው ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ሳይኾን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አዝዞት ፡ አንተ ፡ ኃጢአትን ፡ የተመላህ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ ፤ የጽድቅ ፡ ጠላት ፤ የቀናችቱን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ማጣመምን ፡ ተው ፡ ብንልህ ፡ እንቢ ፡ አልክን ? እነሆ ፡ የእግዚብሔር ፡ እጅ ፡ በንተ ፡ ላይ ፡ ናት ፤ ዐይንህ ፡ ይጥፋ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞትህ ፡ ፀሐይን ፡ አትይ ፡ ብሎ ፡ ቅጣቱን ፡ ሰጠው ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፫ ፡ ፮-፲፪ ። እንግዲህ ፡ ብራየሱስ ፡ ይችን ፡ ቅጣት ፡ በእንቢተኛነቱ ፡ ፈልጎ ፡ እንዳመጣት ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሳይታዘዝ ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ደርሶ ፡ እንዳልጫነበት ፡ አስተውል ።

ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍ ፡ በያይነቱ ፡ እያዘጋጀ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚ ያድል ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ አልሠራውም ፡ እያለ ፡ ቢያላግጥም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚሠወር ፡ የለምና ፡ በቀናው ፡ መንገድ ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ሐተታ ፡ መናፍስት ፡ ዐውደ ፡ ነገሥት ፡ የተባሉ ፡ ዕንቅፋቶች ፡ እያኖረ ፡ በማሰናከሉ ከዚህ ፡ ቅጣት ፡ የሚድን ፡ አይምሰልህ ።

(ለ) ምሕረት ፡ ለሚገባቸው ፡ ሰዎችስ ፡ ፩ኛ ፡ ልስጥራን ፡ በምትባል ፡ ሀገር ፡ ከናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ጀምሮ ፡ ልምሾ ፡ ኾኖ ፡ የተወለደውን ፡ ሰው ፡ ተነሥ ፡ ብሎ ፡ እግር ፡ ሰጥቶታል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፬ ፡ ፰-፲፩ ።

(ሐ) ፪ተኛ ፡ ጋኔን ፡ ይሠቀያት ፡ የነበረችቱን ፡ ሴት ፡ አንተ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ይችን ፡ ሴት ፡ ለቀህ ፡ ትሔድ ፡ ዘንድ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አዝዝሃለሁ ፡ ብሎ ፡ አድኗታል ፡ ግ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰ ።



(መ) ፫ተኛ ፤ ርሱ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ሃይማኖት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ ቀደው ፡ ወስደው ፡ ድውያንን ፡ ይፈውሱበት ፡ ነበረ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ። እንዲሁም ፡ ከርኅራኄው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ዘመዶቼ ፡ እስራኤል ፡ የሚድኑልኝ ፡ ከኾነ ፡ ከክርስቶስም ፡ አንድነት ፡ ልለይ ፡ እወዳለሁ ፡ ብሏል ። ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፩-፬ ።

## ፬ተኛ ፡ ስለ ፡ ሐዋርያት ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመሔድ ፡ ፊቱን ፡ መልሶ ፡ ሠማርያ ፡ ሲደርስ ፡ የምናድርበት ፡ ቤት ፡ ፈልጉ ፡ ብሎ ፡ ሐዋርያትን ፡ ላከቸው ። የዚያች ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ አናስገባም ፡ አሏቸው ። የዚያች ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ፊጣሪያቸውን ፡ አንቀበልም ፡ በማለታቸው ፡ ተናደው ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሐንስ ፤ ኤልያስ ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ አዝንሞ ፡ ያምሳ ፡ አለቆችን ፡ እንዳጠፋቸው ፤ እኛም ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ አውርደን ፡ እንድናጠፋቸው ፡ ትፈቅዳለህን ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ እኔ ፡ ሰውን ፡ ላድን ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ ላጠፋ ፡ አልመጣሁምና ፡ አይኾንም ፡ አላቸው ፡ ማለቱ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፶፩—፶፯ ።

ደግሞ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ አንዲት ፡ ከነናዊት ፡ ሴት ፡ በልጅዋ ፤ ቢስ ፡ ጋኔን ፡ ስላደረባት ፡ እየተከተለች ፡ አቤቱ ፡ ልጄን ፡ አድንልኝ ፡ እያለች ፡ ጮኸች ።

ጌታም ፡ ዝም ፡ ብሏት ፡ ሔደ ። ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ቀርበው ፡ አቤቱ ፡ ምነው ፡ ይች ፡ ሴት ፡ እኛን ፡ እየተከተለች ፡ ትጮኻለች ፤ አታሰናብታትምን ፡ ብለው ፡ ማለዱት ።

ጌታም ፤ መምህር ፤ አብነት ፡ አጥተው ፡ ወደ ፡ ተኀዱ ወደ ፡ ቤተ ፡ እስ ራኤል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አልተላኩም ፡ አላቸው ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ እናገኛለን ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፳፩-፳፰ ።

እንግዲህ ፡ ይች ፡ ሴት ፡ የርሱው ፡ ፍጥረት ፡ ስትኾን ፤ ሰው ፡ መኾኑም ፡ ለሕዝቡም ፡ ለአሕዛቡም ፡ ሲኾን ፡ ርሷ ፡ እየተከተለች ፡ ስትጮኽለት ፡ ሐዋርያ ትም ፡ ሲማልዱት ፡ ወደርሷ ፡ አልተላክሁም ፡ በማለቱ ፡ ጌታን ፡ ጨካኝ ፤ ሐዋርያትን ፡ ርኅሩኃን ፡ እንላቸዋለንን ፡ አንላቸውም ።

በሌላም ፡ አንቀጽ ፡ ጌታ ፡ ተቈጥቶ ፡ ሊያጠፋቸው ፡ ሲል ፡ ባለሟሎቹ ፡ ቅዱሳን ፡ ለምነው ፡ አማልደው ፡ ምሕረት ፡ ያስደረጉላቸው ፤ ወይም ፡ እኒህን ፡ ክፉ ዎች ፡ አይኸንም ፡ አልምራቸውም ፡ ብሎ ፡ ቅጣቱን ፡ የፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል ። ኤር ፡ ፯ ፡ ፲፯-፳ ። ፲፬ ፡ ፲፩—፲፰ ። ፡ ዘዳግ ፡ ፫ ፡ ፳፫-፳፯ ፡ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጨካኝ ፤ ቅዱሳንን ፡ ርኅሩኆች ፡ ልንል ፡ እናስባለን ፡ ይኾን ? አና ስብም ። የማናስብበትም ፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ ጥፋት ፡ ሰዎች ፡ በእንቢተኛነታቸው ፡ ፈልገው ፡ ያመጡት ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ኾነ ፤ ከሰውም ፡ ኾነ ፤ ጭካኔም ፡ ርኅራኄም ፡ ቢኾን ፡ ከሚደረግለት ፤ ወይም ፡ ከሚደረግበት ፡ ሰው ፡ ጠባይ ፡ የሚገኙ ፡ መኾና [illegible] ።

www.ethiopianorthodox.org

ለፍጡር ፡ ጭከናና ፡ ወስላቃነት ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ርኅራኄና ፡ ቅንነት ፡ መሥራት ፡ አይቻለውም ፡ ማለትን ፡ ትተህ ፡ ጭከናም ፤ ርኅራኄም ፤ ክፋትም ፤ በጐነትም ፡ ቢኾን ፡ ለሰው ፡ የባሕርዩ ፡ ተስማሚ ፡ ግብር ፡ መኾኑን ፡ ተረዳና ፡ ለፍጡር ፡ ጭከናም ፤ ርኅራኄም ፤ ክፋትም ፤ በጐነትም ፡ መሥራት ፡ የሚቻለው ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ፡

## ፩ተኛ ፡ ስለቅኔዎች ።

፩ ገሠጽኮ ፡ ለዮናስ ፡ በቀሥታመ ፡ ባሕር ፡ ኀበ ፡ ኢዘርዐ ፡ ስብከተ ፡ ኅጠተ ፡ ቃሎ ፡ ዘፉዒ ።
ለምድረ ፡ ነነዌ ፡ ጸርከ ፡ በገራኅተ ፡ እዝና ፡ ሰማዒ ።
ወበቃለ ፡ ረኀብ ፡ ተዛለፍኮ ፤ ለዘኢኅዘነ ፡ ኤልያስ ፡ ቀናዒ ።
በእሳተ ፡ ረኃብ ፡ እንዘ ፡ ያውዒ ፤ ኵሎ ፡ ገዳመ ፡ ቤተ ፡ አክዓብ ፡ ገፋዒ ።
አኮኑ ፡ አምላከ ፡ ፍቅር ፡ እንዘ ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ በላዒ ።
ትቄርር ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ድንጋፄ ፡ ኃጥአን ፡ ሶበ ፡ ትሬኢ ።
ለገብርከኒ ፡ ዓለም ፡ በበትረ ፡ መከራ ፡ በቋዒ ።
ተግሣጸ ፡ ውሉድ ፡ ትጌሥጽ ፡ ወኢትሬስዮ ፡ ከመ ፡ ጸላዒ ።

ኹለተኛም ፡ አሐደ ፡ ዕለተ ፡ እምተፈጸምነ ፡ ለፍጥረትከ ፡ አምላከ ፡ እሙ ፡ አምላክ ፡ ትሬስዮ ።
ትእምርተ ፡ ዝኒ ፡ ነገር ፡ ሶበ ፡ ለነጥበ ፡ ማይ ፡ ቀነዮ ።
ኤልያስ ፡ ዘፍዳ ፡ ሰበኑ ፡ ለኤልሳዕ ፡ ፈደዮ ።
ለፍጥረተ ፡ ዚአከ ፡ ተሐየዮ ፤ ወለፍጥረትከ ፡ ዕፅ ፡ በእሳተ ፡ ረኃብ ፡ አውዐዮ ።
ዳዊትሂ ፡ ዘተሠርገወ ፡ መንግሥተ ፡ ሳኦል ፡ ሎግዮ ።
ግፍዐ ፡ ሳኦል ፡ ተዘከረ ፡ ወጸንዐ ፡ በያርዮ ።
ሚካኤልኒ ፡ ርኅሩኅ ፡ ዘጽጋበ ፡ ምሕረት ፡ ከረዮ ።
ለሙሴ ፡ ኢተራኅራኀ ፡ እንዘ ፡ መቃብረ ፡ ይወድዮ ።

የሚሉትን ፡ ቅኔዎች ፡ ለሰው ፡ ጨካኝነት ፡ ምስክር ፡ አድርገህ ፡ ጠቅሰሃል ።

የቅኔን ፡ ምሥጢር ፡ ውጤት ፡ ባታውቀው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አውቀኸው ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ከላይ ፡ አርእስታቸውን ፡ ከታች ፡ ኅደጋቸውን ፡ ለይተው ፡ ምሥጢራቸውን ፡ አንጠርጥረው ፡ አበጥረው ፡ የሚያስረዱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሊቃውንትን ፡ አልቀበልም ፡ ስትል ፤ ቅኔዎችን ፡ አትጠቅስም ፡ ነበረ ። ቅኔ ፡ የድርሰት ፡ መልመጃ ፤ የሐሳብ ፡ መግለጫ ፤ በኃረግና ፡ በቤት ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜያዊ ፡ ዐጭር ፡ አሳብን ፡ የሚደግፉ ፡ የነገር ፡ ቀጠፋዎች ፡ ተጠረቃቅመው ፡ የሚገኙበት ፡ ማኅሌታዊ ፡ ግጥም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ ከሥር ፡ ገብቶ ፡ አርእስትና ፡ ኅዳግ ፡ ለይቶ ፡ የሃይማኖትንም ፡ የምግባርንም ፡ ምሥጢር ፡ የሚያስረዳ ፡ ድርሰት ፡ አደለም ።

ይህነንም ፡ ወደሌላ ፡ ሳትሔድ ፡ እኒሁኑ ፡ የጠቀስካቸውን ፡ ቅኔዎች ፡ ብትመረምር ፡ ልትረዳው ፡ ትችላለህ ፡

፩ኛ ፡ ኹለቱ ፡ ኹሉ ፡ ቅኔዎች ፡ ኤልያስ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፤ ዝናም ፡ አቁሞ ፡ ሰማይ ፡ ለጕሞ ፡ ሰዉን ፡ በረኃብ ፡ እንደ ፡ ቀጣው ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ያደረገበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምን ፡ እንደኾነ ። ይህንም ፡ በማድረጉ ፡ ምን ፡ ቅጣት ፤ ወይንም ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ እንዳገኘ ፤ ገልጸው ፡ አላስረዱም ።

፪ተኛውም ፡ ባለቅኔ ፡ የሙሴ ፡ አሟሟቱና ፡ መቃብሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ መኾኑን ፤ ሙሴም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ከዚ...



እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሞዓብም ፡ ምድር ፡ በወንዝ ፡ ቀበረው ፡ በቤተ ፡ ፌጎር ፡ ፊት ፡ ለፊት ። የመቃብሩም ፡ ሥፍራ ፡ ወዴት ፡ እንደኾነ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ማንም ፡ አላወቀም ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እያስረዳን ፡ ጊዜያዊ ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲገድፍለት ፡ ሚካኤል ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በጭከኔ ፡ እንደ ፡ ቀበረው ፡ አድርጎ ፡ ተናግሯል ። ዘዳግ ፡ ፴፬ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፤ ባለቅኔ ፡ ጊዜያዊ ፡ ሐሳቡን ፡ ለመደገፍ ፡ መንጦላዕተ ፡ ፍትሕ ፡ ትሰፍሕ ፡ በገጸ ፡ ገፋዒ ፡ መርዓዊ ፡ ተወላጥ ፡ ክርስቶስ ፡ ግፉዕ ፡ እንዘ ፡ ዕሩቁ ።

ወእመ ፡ አኮ ፡ ርቱዕ ፡ ለቤተ ፡ ምኵናንከ ፡ ንድቁ ።
ዳዊት ፡ ወአክዓብ ፡ እለ ፡ ትእዛዘከ ፡ መዝገበ ፡ ሰረቁ ።

ውስተ ፡ ግበ ፡ ኃዘን ፡ ለእመ ፡ ወድቁ ፡ ለዳዊት ፡ ተኀዘነ ፡ ወለአክዓብ ፡ ታስቄቁ ።
አንተሰ ፡ ወዳዊት ፡ እመ ፡ ትትዐረቁ ።
ዳዊት ፡ ወዖርዮ ፡ ነገረ ፡ ቤርሳቤኅ ፡ ኢያሕለቁ ።
አኮኑ ፡ ልቃሐሙ ፡ ፍትሐ ፡ ኢፈደይኮሙ ፡ በሕቁ ።

ለዳዊት ፡ ከመ ፡ ጌጋዩ ፡ ወለዖርዮ ፡ በከመ ፡ ጽዮቁ ፡ ዝሎ ፡ ጊዜያዊ ፡ ስሜቱን ፡ ለመገደፍ ፡ ሲል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተገፋዒ ፡ ለገፋዒ ፡ የሚያደላ ፤ ገፋዒን ፡ የሚደግፍ ፡ አስመስሎ ፡ ተናግሯል ።

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ ተከትለን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገፋዒ ፡ እንልዋለን ? አንለውም ። ስንኳን ፡ እኛ ፡ ባለቅኔውም ፡ ቢኾን ፡ ለጊዜው ፡ የቅኔው ፡ አሰላክ ፡ እንዲያምርለት ፡ ብቻ ፡ አገጣጠመው ፡ እንጂ ፡ ዳዊትና ፡ አክዓብ ፡ በንስሐ ፡ መዳናቸውን ፡ ዘንግቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገፋዒ ፡ ነው ፡ ፍርድ ፡ አያውቅም ፡ ብሎ ፡ አልተናገረውም ።

፫ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ርኅርኅትና ፡ ንጽሕት ፡ ጻድቅና ፡ ቅድስት ፡ ናትና ፡ ክፉ ፡ አትወድም ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሌቦችና ፡ የዘማዊዎች ፡ የገዳዮችና ፡ የሕግ ፡ አፍራሾች ፡ ኹሉ ፡ ዋሻ ፡ ናትና ፡ አማልዳ ፡ ታድናለች ፡ ይላሉ ። ስለምትለው ።

(ሀ) ልጅዋ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግብር ፡ ተቀባይ ፡ ቀራጭ ፡ የነበረውን ፡ ማቴዎስን ፡ አስከትሎ ፡ ከሰምዖን ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ከኃጥአን ፡ ከመጸብሐን ፡ ጋራ ፡ ምሳ ፡ ሲበላ ፡ አይተው ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ ማስተዋል ፡ የሌለባቸው ፡ ድፍረትን ፡ ብቻ ፡ የተመሉ ፡ ፈሪሳውያን ፡ መምህራችሁ ፡ ከኃጥአን ፡ ከመጸብሐን ፡ ጋራ ፡ ለምን ፡ ይበላል ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋቸው ፡ ባለመድኃኒትን ፡ በሽተኞች ፡ ይሹታል ፡ እንጂ ፡ ጤነኞች ፡ አይሹትም ፡ ስለዚህ ፡ እኔም ፡ ኃጥአንን ፡ በንስሓ ፡ ልጠራ ፡ መጣሁ ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ልጠራ ፡ አልመጣሁም ፡ ማለቱን ፡ አልሰማህምን ። ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ፡ – ፲፬ ።

(ለ) ኹለተኛም ፡ በኢያሪሆ ፡ አልፎ ፡ ሲኼድ ፡ ዘኬዎስን ፡ ጠርቶ ፡ ዛሬ ፡ ካንተ ፡ ቤት ፡ ገብቼ ፡ እውላለሁና ፡ ፈጥነህ ፡ ወርደህ ፡ ጕዝጕዝህ ፡ አንጥፈህ ፡ ቈየኝ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ እንዳንተ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ከኃጥእ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ሊውል ፡ ገባ ፡ ብለው ፡ ... እንደ ፡ እኔ ፡ እምሕያው ፡ እኔ ፡ የጠፋውን ፡ ልሻ ፡ የሞተውን ፡ ላድን ፡

www.ethiopianorthodox.org

መጥቻለሁና ፡ አንተም ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ ስለኾንክ ፡ ዛሬ ፡ ለዚህ ፡ ቤት ፡ ሕይወት ፡ ኾነ ፡ ማለቱን ፡ አልሰማኽምን ፡ ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፩ ፡ - ፲ ።

(ሐ) ፫ተኛስ ፡ ማርያም ፡ እንተ ፡ ዕፍረት ፡ በቤተ ፡ ስምዖን ፡ ምሳ ፡ አድርጎ ፡ ሳለ ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ የተገዛ ፡ ሽቱ ፡ ወስዳ ፡ በቀባችው ፡ ጊዜ ፡ የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ስምዖን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ነቢይማ ፡ ከኾነ ፡ ይች ፡ ሴት ፡ ኃጢአተኛ ፡ ዘማ ፡ መኾኗን ፡ ያውቅ ፡ አልነበረምን ፤ ኃጢአተኛ ፡ ዘማ ፡ መኾኗንስ ፡ ካወቀ ፡ እግሩን ፡ ስትዳስሰው ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ ይላት ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ቢጠራጠር ፡ ጌታ ፤ ስምዖን ፡ ስምዖን ፤ ብሎ ፡ ጠርቶ ፤ ላንድ ፡ ሰው ፡ አንዱ ፡ ፭፻ ፡ አንዱ ፡ ፶ ፡ ብር ፡ የሚ ከፍሉት ፡ ባለዕዳዎች ፡ ነበሩት ፡ ኹሉም ፡ የሚከፍሉት ፡ ስላጡ ፡ ለኹለቱም ፡ ዕዳ ቸውን ፡ ፋቀላቸው ፡ ከኒህ ፡ ከኹለቱ ፡ ማንኛቸው ፡ አብልጠው ፡ ሊወዱት ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

፭፻ ፡ ብር ፡ የተወለት ፡ አብዝቶ ፡ ሊወደው ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ። ጌታም ፡ መልካም ፡ ፈርደሃል ፤ ይችም ፡ ሴት ፡ ከቤትህ ፡ ከገባሁ ፡ ጀምራ ፡ እግሬን ፡ በዕንባዋ ፡ ከማጠብ ፤ በጠጒሯ ፡ ከማሸት ፡ ሳታቋርጥ ፤ እግሬን ፡ ስትስም ፡ ታያለህ ፤ ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ በብዙ ፡ ስለወደደችኝ ፡ ብዙ ፡ ኃጢአቷ ፡ ተሠረየላት ፡ ማለቱን ፡ አልሰ ማህምን ፡ ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፴፳ ፡ -፶ ።

እንግዲህ ፡ ኃጢአት ፡ ያልሠሩ ፡ ጻድቃንን ፡ ከመውደድ ፡ ብዙ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ በንስሐ ፡ የሚለማመጡትን ፡ ሰዎች ፡ መውደድ ፡ የበለጠ ፡ ርኅራኄ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ።

እመቤታችንንም ፡ የምንወዳት ፤ ርኅርኅተ ፡ ልብ ፡ ለኃጥአን ፡ ርኅርኅተ ፡ ልብ ፡ ለኀ ዙናን ፡ ቤዛዊተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ እያልን ፡ የምናመሰግናት ፤ ልጅዋን ፡ አብነት ፡ አድ ርጋ ፡ ኃጢአት ፡ ከሌለባቸው ፡ ከጻድቃን ፡ ይልቅ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ በንስሓ ፡ የሚቀጠቀጡትን ፡ ስለምታማልዳቸው ፡ የሃይማኖት ፡ ሕፀፅ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ ስለባሕ ርያቸው ፡ ደካማነት ፡ በየቀኑ ፡ በኃጢአት ፡ የሚሰነካከሉም ፡ ለንስሓ ፡ አብቂን ፡ ብለው ፡ በየጊዜው ፡ የሚያቀርቡላትን ፡ ጸሎት ፡ ሰምታ ፡ ለንስሓ ፡ የምታበቃቸው ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

፮ ፩ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ስደት ፡ ስትሔድ ፡ እንግድነት ፡ አናስገባሽም ፡ ላሏት ፡ ሀገሮች ፡ ረግማ ፡ ዝንጀሮና ፡ ጦጣ ፡ አደረገቻቸው ፡ እያሉ ፡ ጠላቶችዋ ፡ ጽፈዋል ። ስለዚህ ፡ እንወዳታለን ፡ እናከብራታለን ፡ ሲሉ ፡ አስሥራዋ ፡ እየሰጡ ፡ ርስዋ ፡ የማትወደውን ፡ እየሠሩ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ቦታ ፡ የጫጉላ ፡ ቤት ፡ ይመስል ፡ ከንቱ ፡ መናገራቸው ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናል ። ዝንጀሮና ፡ ጦጣ ፡ ሌላውም ፡ እንስሳና ፡ አራዊት ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ በ፮ተኛው ፡ ቀን ፡ እን ደተፈጠሩ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ይነግረናል ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፳፱—፴፩ ። ስለምትለው ።

እመቤታችን ፡ አልተሰደደችም ፡ እንዳትል ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ይመሰክርብሃል ፡ ማቴዎ ፡ ፪ ፡ ፲፫—፳፫ ። በስደቷም ፡ ጊዜ ፡ ክፉም ፡ ኾነ ፡ በጎ ፡ ኹሉም ፡ በያይነታ ቸው ፡ የደረሱባት ፡ መኾናቸው ፡ የማይካድ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ በስደቷ ፡ ጊዜ ፡ የደረሱባት ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ ዝርዝር ፡ በወንጌል ፡ ሳይጻፍ ፡ የስ ደቷን ነገር ፡ በሚናገረው ፡ ነገረ ፡ ማርያም ፡ በተባለ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተጽፏል ።



በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ትዕማን ፡ የምትባል ፡ ግፈኛ ፡ ሴት ፡ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ አልሰጥም ፡ ማለቷ ፡ አንሷት ፡ ጌታን ፡ ከመቤታችን ፡ ክንድ ፡ ነጥቃ ፡ ከድንጋይ ፡ ላይ ፡ ጣለችው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኮቲባ ፡ የተባለችቱን ፡ ባሪያዋን ፡ ምድር ፡ ተከፍታ ፡ ዋጠቻት ፡ ትዕማን ፡ ከቀሩት ፡ ቤተ ፡ ሰብአቿ ፡ ጋራ ፡ ገሚ ሶቹ ፡ ጦጣ ፡ ገሚሶቹ ፡ ዝንጀሮ ፡ እየኾኑ ፡ በረሩ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አንብበን ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ አድርገን ፡ ተቀብለነዋል ።

ብንቀበለውም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ የሚቈጠር ፡ አደለም ።

(ሀ) የማይቈጠርበትም ፡ ምክንያት ፡ ገናናው ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነ ፆር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዘንግቶ ፡ በራሱ ፡ በጉልበቱ ፤ ስለተመካ ፡ ጣዖት ፡ ስላቆመ ፡ ሰው ፡ መኾኑ ፡ ቀርቶ ፡ አውሬ ፡ ኾኖ ፡ እንደበሬ ፡ ሣር ፡ እየበላ ፡ በበረሀ ፡ ከአ ራዊት ፡ ጋራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ መኖሩን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የምናገኝ ፡ ስለ ኾነ ፡ ነው ። ዳን ፡ ፬ ፡ ፩-፴፬ ።

(ለ) ኹለተኛም ፡ ድርጣድስ ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ አርሴማ ፡ የምትባለዋን ፡ ድን ግል ፡ ክርስቲያናዊትና ፡ ሌሎችንም ፡ ደናግል ፡ በሰይፍ ፡ ስላስመታቸው ፡ ከሰው ነት ፡ ወጥቶ ፡ ዕሪያ ፤ ኾኖ ፡ እንደኖረና ፡ ኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ በጸሎቱ ፡ ሰው ፡ ወደመኾን ፡ እንደ ፡ መለሰው ፡ በስንክሣር ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኝ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዓቱ ፡ የራቀ ፡ ምሕረቱ ፡ የቀረበ ፤ መዓቱ ፡ ያነሰ ፡ ምሕረቱ ፡ የበዛ ፤ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ መኾኑን ፡ እናምናለን ፤ ማመናችንም ፡ በእውነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሐሰት ፡ አደለም ።

ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በነናቡከደነፆርና ፡ በነድርጣድስ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ኃይል ፡ ስንመለከት ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽነው ፡ ጭከናም ፡ ርኅራኄም ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ ዘንድ ፡ በአድልዎ ፤ ወይም ፡ በግፈኛነት ፡ ሳይኾን ፡ ከሚደረግባቸው ፡ ወይም ፡ ከሚደረግላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ የሚደረጉ ፡ መኾናቸውን ፡ ከማመ ዛዘን ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ እንላለን ፤ እግዚአብሔርን ፡ ገፋዒ ፡ እንለዋለን ? አንለውም ።

እንደዚህስ ፡ ኹሉ ፡ እመቤታችን ፡ ላመኑባትና ፡ ለተማፀኑባት ፡ አማልዳ ፡ ይቅርታ ፡ ታስደርግላቸዋለች ። ዐመፀኞች ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ቅጣታቸውን ፡ ያገኛሉ ፡ ቢባል ፤ ብርቁ ፡ ድንቁ ፡ ምንድን ፡ ነው ። የጫጒላ ፡ ቤት ፡ ጨዋታ ፡ መምሰሉስ ፡ ምንድን ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ናቡከደነፆርን ፡ ቀድሞ ፡ አነገሠው ፡ ኋላም ፡ አውሬ ፡ አደረገው ፡ ኋላም ፡ ደግሞ ፡ መልሶ ፡ ሰው ፡ አደረገው ፡ ስንል ፡ የጫጒላ ፡ ቤት ፡ ጨዋታ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታልን ? አይገመትም ፡ እየው ፡ ይኸውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

፯ ደግሞ ፡ ጦጣና ፡ ዝንጀሮ ፡ በ፮ኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተፈጠሩ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይነግረናል ፡ ብለህ ፡ እኛ ፡ በ፮ ፡ ቀን ፡ አልተፈጠሩም ፡ እነትዕማን ፡ ጦጣ ፡ በኾኑ ፡ ጊዜ ፡ ተፈ ጠሩ ፡ የምንል ፡ አስመሰለህ ፡ ትናገራለህ ። ይህ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፤ ናቡከደነፆር ፡ ተለ ውጦ ፡ አውሬ ፡ እንደኾነ ፡ እነትዕማንም ፡ ተለውጠው ፡ ጦጣ ፡ ዝንጀሮ ፡ ኾኑ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ እናገኛለን ፡ እንጂ ፡ ያንጊዜ ፡ ተፈጠሩ ፡ የሚል ፡ የለምና ፡ እያስተዋልክ ፡ ተናገር ።

፳ ጻድቃን ፡ ያማልዳሉ ፡ ስማዕታት ፡ ይራራሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ስለኃጥአን ፡ ይሳምናሉ ፡ ማለት ፡ በፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ መጨረሻውም ፡ ከአቤል ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምጽአቱ ፡ በስመ ፡ ክርስቶስ ፡ እየተጠሉ ፡ የሞቱ ፡ ኹላቸው ፡ ጻድቃን ፡ ምስክሮች ፡ ስለኃጥአን ፤ መለመናቸው ፡ ቀርቶ ፡ ምነው ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ቅዱሱ ፡ ለፈሰሰው ፡ ደማችን ፡ በቀል ፡ አትበቀልልንም ፡ ለጠላቶቻችን ፡ አትፈርድባቸውምን ፡ እያሉ ፡ በታላቅ ፡ በሚያስቸኩል ፡ ቃል ፡ ሰውን ፡ ለማጥፋት ፡ በጭከና ፡ እያማረሩ ፡ እየከሰሱ ፡ ኹልጊዜ ፡ እንደሚጮኹና ፡ ርኅሩኅ ፡ አምላክ ፡ ግን ፡ ተዉ ፡ ታገሡ ፡ አርፋችሁ ፡ ቆዩ ፡ ብሎ ፡ እንደሚከለክላቸው ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ በመንፈስ ፡ ራእዩ ፡ አይቶና ፡ ሰምቶ ፡ አስተካክሎ ፡ ነግሮናል ። ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፲ ። ራእ ፡ ፮ ፱—፲፩ ። ዘፍ ፮ ፡ ፭ ። ፪ዜና ፡ ፳፬ ፡ ፲፮—፳፪ ። ራእ ፡ ፲፰ ፡ ፬ ፡ ፯ ፡ ስለምትለው ።

በድቡሽት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሕንፃና ፡ በሐሰት ፡ የተመሠረተ ፡ ነገ ፡ ሌላ ፡ አፍራሽ ፡ ሳይኖረው ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ሲፈርስ ፡ ይገኛል ። በዚህ ፡ አነጋገርህ ፡ ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ ጻድቃን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የሞት ፡ እንቅልፍ ፡ ይዟቸዋልና ፡ ስንለምናቸው ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ሊሰሙን ፡ አይችሉም ፡ ያልከውን ፡ ንግግርህን ፡ እንዳፈረስከው ፡ አወቅህን ? ጻድቃን ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ኾነው ፡ ሥራ ፡ መሥራታቸውን ፡ እንኳን ፡ አወቅኽልኝ ፡ እንጂ ፡ የዚህንስ ፡ መልስ ፡ ለበጎዎች ፡ ይጸልዩላቸዋል ፡ በክፉዎች ፡ ይጸልዩባቸዋል ፡ ብዬ ፡ የጻፍኩልህን ፡ በገጽ ፡ ፻፸፫ ፡ በቍ ፡ ፲፩ ፡ ተመልከት ።

፱ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ባገራችን ፡ የሚታወቁት ፡ እኛ ፡ ጻድቃን ፡ የምንላቸው ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፤ ገሪማ ፤ አባ ፤ ጊዮርጊስ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤ ሌሎችም ፡ የመሰሏቸው ፡ እጅግ ፤ ብዙዎች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ከነርሱ ፡ ባፊት ፡ ለሞቱት ፡ ጻድቃንና ፡ መነኮሳት ፡ ስማዕታት ፡ እርዱን ፡ አማልዱን ፡ እያሉ ፡ ሰዎችን ፡ አምነው ፡ ደግ ፡ ሳይሠሩ ፡ የጻደቁ ፡ ይመስልሃልን ፡ አይደለም ። ኢትትአመኑ ፡ በመላእክት ፡ ወኢበእጓለ ፡ እመሕያው ፡ እለ፡ኢይክሉ ፡ አድኅኖ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ስለተረዱት ፡ እንኳን ፡ ለማዳን ፡ ለመፍጠርም ፡ አጋዥ ፡ የማይፈልግ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ ብቻ ፡ አምነው ፡ ስለአገለገሉት ፡ ጸድቀው ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ለፍጡራን ፡ አምነው ፡ አልጻደቁምና ፡ ገድላቸውም ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ፡ በአሚነ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይላል ፡ መዝ ፡ ፻፵፯ ፡ ፩ ፲ ። ሥራ ፡ ፯ ፡ ፶፱ ፡ ፳ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፭—፵ ። ስለምትለው ።

ሀ ኢትትአመኑ ፡ በመላእክት ፡ ላልከው ፡ በምዕራፍ ፡ ፀዋጅ ፡ በገጽ ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌልሃለሁና ፡ ያንን ፡ ተመልከት ።

ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምልከው ፡ እሱን ፡ አገልግለው ፡ ጸደቁ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሰዎችን ፡ አምነው ፡ ደግ ፡ ሳይሠሩ ፡ ጸደቁ ፡ የሚል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አይገኝም ። ገድላቸውም ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ፡ በአሚነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማለቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ እውነተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እምነታቸው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ኾኖ ፡ ትሩፋት ፡ ለመሥራት ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ የሚያመጣባቸው ፡ ፈተና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስለኾነ ፡ ከሰይጣን ፡ ፈተና ፡ በጸሎታችሁ ፡ እርዱን ፡ በረድኤታችሁ ፡ ደግፉን ፡ ብለው ፡ በቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ መማፀናቸው ፤ ቅዱሳንም ፡ መርዳታቸው ፡ የማይካድ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህነንም ፡ ገድላቸውን ፡ ድርሳናቸውን ፡ ብትመለከት ፡ ትረዳዋለህ ።

ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፡ ገድለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብትመለከት ፡ አቡነ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ወራት ፡ ገና ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ሲባሉ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ከአባታቸው ፡ ከቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ጋራ ፡ ሲሔዱ ፡ መኾቶባቸው ፡



ከንድ ፡ መንደር ፡ ገብተው ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንግዶች ፡ አሳድሩን ፡ ቢሉ ፡ አንድ ፡ ሰይጣን ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ መታቸው ።

ምነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንግዶች ፡ ነን ፡ ብንልህ ፡ በመቀበል ፡ ፋንታ ፡ ትመታኛለህን ፡ ብለው ፡ አልቅሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ የሚገለጽብህ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በኔ ፡ የሠራውን ፡ ግፍ ፡ አታይምን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባለሟሉ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሆይ ፡ የርዳታህን ፡ ኃይል ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አሳየኝ ፡ ብለው ፡ ቢጸልዩ ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ ተናግረው ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ይህ ፡ የመታቸው ፡ ሰው ፡ በዐየር ፡ ተዘቅዝቆ ፡ ተሰቅሎ ፡ ማን ፡ እንደሚገርፈው ፡ ሳይታወቅ ፡ ሲገረፍ ፡ የግርፋቱ ፡ ድምጽ ፡ ይሰማ ፡ ነበረ ።

ርሱም ፡ እናንተ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብላችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉኝ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ፡ ኃጢአቱን ፡ አውቆት ፡ ሥርየት ፡ ከለመነ ፡ በኋላ ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸሎት ፡ ከተሰቀለበት ፡ ወረደ ፡ ከግርፋቱም ፡ ዳነ ፡ ይላል ።

የቅዱሳንን ፤ ገድል ፡ ኹሉ ፡ ብትመለከተው ፡ በወጣኒነታቸው ፡ ከሥዕለ ፡ ማርያም ፡ ወድቀው ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ተማኅጽኖ ፡ አድርገው ፡ ምልክት ፡ አግኝተው ፡ ወደ ፡ ሀገረ ፡ ምናኔያቸው ፡ ሔዱ ፡ የማይል ፡ አታገኛም ።

፲ አልበ ፡ ዘያስተአብዶ ፡ ለእግዚአብሔር ። ለአምላክ ፡ የሚሸነግለው ፡ የማያማክረው ፡ የሚያታልለው ፡ የለም ፡ አይገኝም ፡ እያሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ይነግሩናል ፡ ገላ ፡ ፮ ፯ ። ስለምትለው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ ወንድሞቻችን ፤ ከሃይማኖት ፡ የተናወጠ ፡ ከምግባር ፡ ያዳጠ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸንታችሁ ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፤ ለራሳችሁ ፡ እንዳትስቱ ፡ ተጠንቅቃችሁ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ በገርነት ፡ መንፈስ ፡ አጽናኑት ፤ አጋንንት ፡ መናፍቃን ፡ ያከበዱባቸውን ፡ ሸክም ፡ እናንተ ፡ ተሸከሙላቸው ። ይህን ፡ በማድረጋችሁም ፡ የክርስቶስን ፡ ሕግ ፡ ትፈጽማላችሁ ፡ ብሎ ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ መጸለይ ፡ እንዲገባ ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፤ በጸጋው ፡ ድኛለሁ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ አያሻኝም ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ስሑት ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ አይኑር ። ኹሉ ፡ ሸክሙን ፡ ይሸከማልና ፡ (ማለት) እንደ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ዋጋውን ፡ ያገኛልና ፡ ለሌላ ፡ ያይደለ ፡ ለራሱ ፡ መመኪያ ፡ በሚኾነው ፡ ገንዘብ ፡ ኹሉ ፡ ምግባሩ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ይመርምር ።

ንዑሰ ፡ ክርስቲያንም ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ ሰጊድን ፡ ቁመትን ፡ በጠቅላላው ፡ ትሩፋትን ፡ ኹሉ ፡ ይማር ፡ ብሎ ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ መጸለይ ፡ እንዲገባና ፡ ትሩፋት ፡ መሥራት ፡ እንዲገባ ፡ ተናግሯል ።

ይህን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ከሥራው ፡ ገብቶ ፡ ሳይገኝ ፡ በአፉ ፡ ብቻ ፡ በጸጋው ፡ ድኛለሁ ፡ በስሙ ፡ ተጠርቻለሁ ፤ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብያለሁ ፤ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚሸነግለው ፡ የሚያታልለው ፡ ሰው ፡ የለምና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጸጋው ፡ ድናችኋል ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ አያሻችሁም ፡ የሚሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች ፡ አያስቷችሁ ፡ ሰው ፡ የዘራውን ፡ ይለቅማል ፡ በሥጋው ፡ ላይ ፡ መብላት ፡ መጠጣትን ፡ መደላደል ፡ መቀማጠልን ፡ የሚዘራ ፡ ሰው ፡ ሞትን ፡ ያጭዳል ።

በመንፈስ ፡ ጾምን ፤ ጸሎትን ፤ ሰጊድን ፤ ቁመትን ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ የዘራ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ያጭዳልና ፡ ፍሬውን ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ የምንለቅመው ፡ ስለኾነ ፡ ትሩፋት ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ አንበል ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ የሰማይ ፡ አባቱን ፡ ፈቃድ ፡ ከሚፈጽም ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ የሚለኝ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ፡ በዚያች ፡ ዕለት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አቤቱ ፡ በስምህ ፡ ትንቢት ፡ ተናግረን ፡ አል ነበረምን ? በስምህ ፡ ጋኔን ፡ አስወጥተን ፤ በስምህ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አድር ገን ፡ አልነበረምን ይሉኛል ።

እኔም ፡ ዐመፅን ፡ የምትሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሜ ፡ አላውቃችሁ ምና ፡ ከኔ ፡ ራቁ ፡ እላቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል የመሰለ ፡ ተና ገረ ፡ እንጂ ፤ አንተ ፡ ከላይ ፡ አባቶችን ፡ ከታች ፡ ጎዳጉን ፡ ትተህ ፡ ለአሳ ብህ ፡ እንደሚመችህ ፡ ቀንጭበህ ፡ እንደ ፡ ጠቀስከው ፡ አይደለም ። ገላ ፡ ፮ ፣ ፯ ፡ ማቴ ፡ ፯ ፳፩ ፳፱ ፡ እንግዲህ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ አልበ ፡ ዘያስተአብዮ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ያለ ፡ በጸጋው ፡ ድኛለሁ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ አያሻኝም ፡ ስለሚል ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ለመሥራት ፡ በጸሎታችሁ ፡ ርዱኝ ፡ ብሎ ፡ በቅዱ ሳን ፡ ጸሎት ፡ ስለሚማጠኑ ፡ ሰዎች ፡ አለመኾኑን ፡ አውቀህ ፡ አንተ ፡ ተመክርበት ።

፲፩ ይህ ፡ ነገር ፡ (ትምርት) ፡ አግራምቢጥ ፡ መኾኑ ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ ንብብና ፡ ተቀምጠህ ፡ ተኝተህም ፡ ቢኾን ፡ ሳትቸኩል ፡ ዝግ ፡ ብለህ ፡ ተረድተኸው ፡ ስታበቃ ፡ ልብ ፡ ዳኛ ፡ አድርገህ ፡ እውነትን ፡ ከሐሰት ፡ ለይተህ ፡ ሰው ፡ ይነቅፈኛል ፡ ሳትል ፡ ነፍስ ፡ የምትድንበት ፡ ትልቁ ፡ ነገር ፡ ስለኾነ ፡ በአምላ ክህና ፤ በሰው ፡ ፊት ፡ በድፍረት ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ እንድትፈርድ ፡ እንድትመሰክር ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ በመልካም ፡ ማመን ፡ በመሰከረው ፡ በየሱስ ፡ መድኃኔ ዓለም ፡ እማጽንሃለሁ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፲፫ ፲፮ ፡ ስለምትለው ።

እኔ ፡ በበኩሌ ፡ አንተ ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ጠርተህ ፡ ከማማፀንህ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ነፍሴ ፡ የምትድንበት ፡ ወይም ፡ የምትጎዳበት ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ መኾኑን ፡ አውቄ ፡ መጻሕፍትን ፡ መርምሬ ፡ የረቀቀኝንም ፡ ምሥጢር ፡ ከሊቃውንት ፡ ከመምህራን ፡ ጠይቄ ፡ ተረድቼ ፡ ከመብል ፡ ከመጠጥ ፡ መጾም ፤ በዕረፍት ፡ ከመደላደል ፡ ከመቀማጠል ፡ በትሩፋት ፡ መድከም ፡ እኔ ፡ በሥራዩ ፡ እድናለሁ ፡ አማላጅ ፡ አልሻም ፡ ብሎ ፡ ከመመካት ፡ ራስን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ እኔ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነኝና ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ደማችሁን ፡ ያፈሰሳችሁ ፡ ሰማዕታት ፤ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ በቁመት ፡ የደከማችሁ ፡ ቅዱሳን ፤ አማልዱኝ ፡ ጸልዩልኝ ፡ ብሎ ፡ መማፀን ፡ ከኹሉ ፡ የበለጠ ፡ ፀፀትን ፡ የማያስከትል ፡ ጠቃሚ ፡ እውነተኛ ፤ ነገር ፡ እንደኾነ ፡ የተረዳኹ ፡ መኾኔን ፡ በእውነት ፡ እነግርሃለሁ ።

አንተም ፡ እንዲሁ ፡ እንደኔ ፡ በበኩልህ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ስፉታቸውንና ፡ ምሥጢራቸውን ፡ ከመምህራን ፡ መላልሶ ፡ ጠይቆ



ሲያነቡ ፡ መዋል ፡ ሳይታወቅ ፡ ሰብብሮ ፡ የሚጥል ፡ የግር ፡ ጉድጓድ ፡ መኾኑን ፡ አውቀህ ፡ መምህራንን ፡ ጠይቀህ ፡ እውነተኛውን ፡ መንገድ ፡ ተረድተህ ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ምግባርን ፡ ደርበህ ፡ እንድትድን ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ጠርቼ ፡ እማልድሃለሁ ።

፲፪ ፡እርሱ ፡ የጸጋውን ፡ ብርሃን ፡ ይግለጽልህና ፡ ያቺ ፡ ኹላችን ፡ የምንመኛት ፡ ሀገር ፡ ግን ፡ ፈሪዎችና ፡ ኀፍረተኞች ፡ ተወላዋዮችም ፡ እንደማይገቡባት ፡ አስተውል ፡ ራእ ፡ ፳፩ ፡ ፰ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፳ ፡ ፯ ፡ ፴ ፡ ፯ ። ስለምትለው ።

ያችን ፡ ሀገር ፡ ፈሪዎችና ፡ ኀፍረተኞች ፡ ተወላዋይዎች ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፡ ሃይማኖት ፡ አለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎችም ፡ ቢኾኑ ፡ ምግባር ፡ ከሌላቸው ፡ እንደ ፡ ማይገቡባት ፡ አውቃለሁ ። አንተም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ ጨምረህ ፡ እንደታ ውቅ ፡ አሳስብሃለሁ ።

## ምዕራፍ ፺ ።

### ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ።

፩ ወንድሜ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ የአማላጅነት ፡ ነገር ኹለት ፡ ዐይነት ፡ መኾኑን፡ ልገልጽልህ ፡ እወዳለሁ ፡ ርሱም ፡ ዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ ዐጸደ ፡ ነፍስ ፡ ይባላል ፤ ስለምትለው ።

ምልጃ ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋም ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስም ፡ መኖሩ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ይህን ንም ፡ በምስተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስልት ፡ ስልታቸውን ፡ ለይቼ ፡ ለይቼ ፡ ጽፌልሃለ ሁና ፡ በቍ ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፻፵፫-፻፵፬ ፡ ተመልከት ።

፪ ስለዚህ ፡ አንዳንድ ፡ አውቆ ፡ አበዶች ፡ የሐሰትን ፡ ትምህርት ፡ የተከተከሉ ፡ ሳይሠሩ ፡ በዓላትን ፡ እየቈጠሩ፡ ቦዘን ፡ የሚውሉ ፡ እለ ፡ ከርሦሙ ፡ ያመልኩ ፡ ወአኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተባሉ ፡ በጻድቃንና ፡ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ ስከ ብራቸው ፡ እያልን ፡ አመሃኝተን ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ የሚሉ ፡ ሕዝባቸውን ፡ ስለ ፡ ጭብጥ ፡ ገብስና ፡ ቁራሽ ፡ እን ጀራ ፡ እያታለሉት ፡ የሚኖሩ ፡ ጻድቃን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ብንጠራቸው ፡ ይሰሙናል ፡ ብን ምናቸው ፡ ይሰሙናል ፡ ስለኛም ፡ ሲሉ ፡ ከአምላክ ፡ ምሕረት ፡ ይለምኑልናል ፡ ቢሉህ ፡ ሐስታቸውን ፡ አትመን ፡ ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰ ። ኢሳ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ። ሕዝ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ፡ —፳፫ ። ስለምትለው ።

(ሀ) አውቆ ፡ አበድ ፡ ማለት ፡ ከመብላት ፡ መጾም ፤ ከማድለብ ፡ መመጽወት ፤ እውነተኛ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ መኾኑን ፡ ልብ ፡ እያወቀው ፡ ሰውን ፡ ለማስደሰትና ፡ ወገን ፡ ለማብዛት ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ መርጦ ፤ ጾም ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፡ ብሉ ፤ ጠጡ ፤ ተደሰቱ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጸጋው ፡ ድናችኋል ፡ ምግ ባር ፡ ትሩፋት ፡ አያሻም ፡ ብሎ ፡ ማስተማር ፡ ነው ።

(ለ) የሐሰት ፡ ትምህርትን ፡ መከተል ፡ ማለትም ፡ ይህን ፡ በቂ ፡ ያልኾነውን ፡ ትምህርት ፡ ልቡ ፡ በተፈጥሮ ፡ እውቀቱ ፡ እያወቀው ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ እው ነት ፡ ብሎ ፡ የተከተለ ፡ ነው ።

(ሐ) ቦዘን ፡ የሚውሉ ፡ ስለምትለው ፡ በመቅድሙ ፡ ስለመነከሳት ፡ በጻፍከው ፡ በገጽ ፡ ፶፯ና፶፰ ፡ በቍ ፡ ፳፱ ፡ ጽፌልሃለሁ ፡ ያነን ፡ ተመልከት ።

(መ) እለ ፡ ከርሦሙ ፡ ያመልኩ ፡ ለምትለው ፤ የጾም ፡ ልጓምነትን ፡ በፍጹም ፡ አውል ቀህ ፡ ዘለዓለም ፡ ጠባ ፡ ለሆዴ ፡ መሸ ፡ ለሆዴ ፡ ስትል ፡ የምትኖረው ፡ ሰው ፤ ከ፺ ፡ አጽዋም ፡ ሌላ ፡ የፈቃድ ፡ ጾም ፡ እያለ ፡ የጾም ፡ ልጓም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሳይወልቅለት ፡ በሚኖረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እለ ፡ ክርሦሙ ፡ ያመልኩ ፡ ብሎ ፡ መጥ ቀስ ፡ አውቆ ፡ አበድነቱን ፡ ይመሰክርብኛል ፡ ባለማለትህ ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያመዛዝነው ፡ ብዬ ፡ ትቸዋለሁ ።

(ሠ) አመኻኝተን ፤ እንብላ ፡ ብለው ፡ ሕዝባቸውን ፡ የሚያታልሉ ፡ ለምትለ ውም ፡ ሕዝባቸውን ፡ የሚያታልሉስ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ፡የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮ ሣፍጥ ፡ ሶርያን ፡ ሊወጉ ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፡ እውነተኛው ፡ ነቢይ ፡ ሚክያስ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ሶርያን ፡ እንድትወጉ ፡ አልፈቀደምና ፡ ተዉ ፡ ተመለሱ ፡ ሕዝቡም በየቤታቸው ፡ ይግቡ ፡ ብሎ ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ቢነግራቸው ፤ የሐሰት ፡ ነቢያት ፡ እነሴዴቅያስ ፡ ወልደ ፡ ክህናን ፡ እውነተኛውን ፡ ነቢይ ፡ ሚክያስን ፡ በጥፊ ፡ መተው ፡ የብረት ፡ ቀንድ ፡ በራሳቸው ፡ ሰክተው ፡ እየደነፉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶርያን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ እንድታጠፏት ፡ አዝዟል ፡ ብለው ፡ አታ ለው ፡ አውጥተው ፡ ለሶርያውያን ፡ መጫወቻ ፡ እንዳደረጓቸው ፡ ኹሉ ፤ ዛሬም ፡ ንዑ ፡ ኅቤየ ፡ የሚያሰኝ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ በሚዘራበት ፡ ወራት ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጸጋው ፡ ድናችኋል ፤ ጾም ፤ ጸሎት ፤ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ አያሻችሁም ፡ እያሉ ፡ ሥጋን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መብል ፡ መጠጥን ፡ ብቻ ፡ እያስተማሩ ፡ አስንፎ ፡ አኑሮ ፤ ብራብ ፡ አላበላችሁኝም ፡ ብጠማ ፡ አላጠጣችሁኝም ፤ ብታረዝ ፡ አላ ለበሳችሁኝም ፡ ከኒህ ፡ ከድኖች ፡ ላንዱ ፡ አላማድረጋችሁ ፡ ለኔ ፡ አላማድረጋ ችሁ ፡ ነውና ፡ እናንተ ፡ ርጉማን ፡ ከፊቴ ወግዱ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ የሌለው ፡ የማይረባ ፡ የማጠቅም ፡ ልቅሶ ፡ እያለቀሱ ፡ ወደ ፡ ሥቃየ ፡ ገሃነም ፡ እንዲሔዱ ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ገንዘባችሁ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ እነሱም ፡ በቤታቸው ፡ በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ይቀበሏችሁ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ በኃላፊው ፡ ገንዘባችሁ ፡ ዛሬ ፡ ወዳጅ ፡ ግዙበት ። በተማሪየ ፡ ስም ፡ ጽዋ ፡ ወኅ ፡ ያጠጣ ፡ ዋጋውን ፡ እንዲያገኝ ፡ እውነት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ጢት ፡ ማታ ፡ በመንገር ፡ ምጽዋት ፡ እንዲመጸውቱ ፤ በሐዋርያት ፡ በጅ አርድእት ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ ስም ፡ ዝክር ፡ እንዲዘክሩ ፡ ለተራብ ፡ እንዲያበሉ ፤ ለተጠማ ፡ እንዲያጠጡ ፡ አድርገው ፡ በቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ብራብ ፡ አብልታችሁኛል ፡ ብጠማ ፡ አጠጥታችሁኛል ፡ ከኒህ ፡ ከድኖች ፡ ላንዱ ፡ ማድረጋችሁ ፡ ለኔ ፡ ማድረጋችሁ ፡ ነውና ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የተዘጋጀላችሁ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ኑ ፡ ውረሱ ፡ ለመባል ፡ የሚያበቁ ፡ መምህራን ፡ አታላ ዮች ፡ አይባሉም ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፳፪ ፡ ፩—፶፫ ። ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፩—፵፯ ። ፲ ፡ ፵፩ና ፡ ፵፪ ፡ ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ።

(ረ) ጻድቃን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ይሰሙናል ፡ ስለምትለው ፡ ስለአማላጅነት ፡ በጻፍከው ፡ በ፳ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በቍ ፡ ፬ ፡ ገጽ ፡ ፻፵፮-፻፶ ፡ መልሱ ፡ ተጽፎ ልሃል ፡ ተመልከት ።

፫ ተፈራጆች ፡ ስንኳንስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ሊያማልዱ ፡ [illegible] ውን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ከመማረከና ፡ ለባዕድ ፡ ከመገዛትም ፡ ሊያድኑ ፡ ሊያማልዱም ፡ ቢጸልዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ [illegible]



ርምያስ ፡ አንተ ፡ ስለዚህ ፡ ክፉ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፡ ስለርሳቸውም ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ማማለድም ፡ አታድርግ ፡ አትንገዝንዘኝ ፡ እኔ ፡ አልሰማህምና ፡ ይለዋል ። ኤር ፡ ፯ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ። ፲፬ ፡ ፲፰ ፡ —፲፰ ፡ ስለምትለው ።

አንተንና ፡ እኛን ፡ የሚያጣላን ፡ በፍጹም ፡ ምልጃ ፡ የለም ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ሊጸልይ ፡ አይችልም ፡ ማለትህ ፡ ነበረ ፡ ባሁኑ ፡ አነጋገርህ ፡ ምልጃ ፡ መኖሩን ፡ አምነህ ፡ ልመናህን ፡ አልሰማህም ፡ አለው ፡ ነው ፡ የምትለኝ ፤ ምልጃ ፡ መኖሩን ፡ ስንኳን ፡ አወቅህልኝ ፡ እንጂ ፡ ኤርምያስንስ ፡ ስለዚህ ፡ ክፉ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፡ አልሰማህምና ፡ ማለቱ ፡ ሕዝቡ ፡ ከክፋታቸው ፡ ሳይመለሱ ፤ ኤርምያስንም ፡ ጸል ይልን ፡ አማልደን ፡ ሳይሉት ፡ ርሱ ፡ አበትነቱ ፡ አስገድዶት ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ስለጸለየላቸው ፤ እነርሱ ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ከክፋታቸው ፡ ሳይመለሱ ፡ አንተ ፡ ብትጸልይላቸው ፡ አልሰማህም ፡ ማለቱ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። እነርሱ ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ተጠጥተው ፡ አማልደን ፡ ባሉትስ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ከልሒቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ ሰብስበ ፡ ጸሎታችሁን ፡ በፊቱ ፡ አቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደርሱ ፡ የላከችሁኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ብትቀመጡ ፡ እሠራች ኋለሁ ፡ አላፈርሳችሁም ፡ እተክላችኋለሁ ፡ አልነቅላችሁም ፡ እናንተ ፡ በሠራችሁት ፡ ኃጢአት ፡ ከደነገጣችሁ ፡ እኔም ፡ ባደረግሁባችሁ ፡ ክፋት ፡ እጠጠታለሁና ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥም ፡ ፊት ፡ አትፍሩ ፡ አላችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነግሯቸዋል ። ኤር ፡ ፵፪ ፡ ፪ —፲፫ ።

እኛም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢኸን ፡ ከኃጢአቱ ፡ ተመልሶ ፡ ንስሐ ፡ ገብቶ ፡ ጸል ዩልኝ ፡ አማልዱኝ ፡ ሳይል ፡ እርሱ ፡ በኃጢአት ፡ ባሕር ፡ እየዋኘ ፡ ሌላው ፡ ቢጸል ይለት ፡ ይድናል ፡ ብለን ፡ አናምንም ፡ ለሌላውም ፡ አናስተምርም ።

፬ ኢሳይያስም ፡ የመከረውንና ፡ ያሰበውን ፡ ያስተወው ፡ ይከለክለው ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ ይላል ፡ ኢሳ ፡ ፲፬ ፳፯ ። ረአዬ ፡ ኅቡዓት ፡ ኤር ፡ ፳፫ ፳፫ ፳፬ ። ከሀሌ ፡ ኵሉ ፡ የኾነ ፡ አምላካችን ፡ ሰዎች ፡ በነገሩት ፡ ባስታወሱት ፡ ሰምቶ ፡ አይፈርድም ፡ ባገራችን ፡ ያለው ፡ ሥርዓት ፡ አትመን ፡ ያልኩህ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

ኢሳይያስ ፡ የባቢሎንን ፡ ስም ፤ ዘርዋንም ፡ ትውልዷንም ፡ አጠፋለሁ ፡ የውኅ ፡ መቆሚያ ፡ የአላቅት ፡ መኖሪያ ፡ አደርጋታለሁ ፡ አሶርንም ፡ በምድሬ ፡ እሰብረዋለሁ ። በተራራዬ ፡ እረግጠዋለሁ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ የአሕዛብን ፡ ጥፋት ፡ ከተ ናገረ ፡ በኋላ ፡ ስለነዚህ ፡ ሀገሮች ፡ ቀኖና ፡ ገብቶ ፡ ዕጣን ፡ ዐጥኖ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠውቶ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ተወስኖ ፡ የሚያዝንላቸው ፡ የሚጸልይላቸው ፡ ነቢይ ፡ ካህን ፡ ስለሌለ ፤ ወይም ፡ እነሱ ፡ ከሚያመልኳቸው ፡ ጣዖታት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተወዳዳሪ ፡ ኾኖ ፡ አስገድዶ ፡ የመከረውን ፡ ሊያስተወው ፡ የዘረጋውን ፡ ክንዱን ፡ ሊያጥፈው ፡ የሚችል ፡ ስለሌለ ፡ የመከረውን ፡ ያስተወው ፡ ዘንድ ፡ የተዘረጋችው ንስ ፡ እጁን ፡ የሚመልሳት ፡ ማነው ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ በንጹሕ ፡ የሚያመልኩት ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ቢለምኑት ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ከቁጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ ተመልሶ ፡ አይምርም ፡ አላለም ። ኢሳ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ፡ - ፳፯ ፡ ተመልከት ።

ኤርምያስም ፡ በ፳፫ ም ፡ በ፳፫ ቍ ፡ በውኑ ፡ እኔ ፡ የቅርብ ፡ አምላክ ፡ ነኝን ፡ [illegible] አምላክ ፡ አይደለሁምን ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡

www.ethiopianorthodox.org

በኹሉ ፡ ምሉዕ ፡ የኾነ ፡ እምላክነቱን ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ ቢለምኑት ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፤ ከቁጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ አይመለስም ፡ አላለምና ፡ ይህ ፡ ለማስመሰል ፡ ብቻ ፡ የተጠቀሰ ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

ሰዎች ፡ በነገሩት ፡ በስታወሱት ፡ ሰምቶ ፡ አይፈርድም ፡ ለምትለውም ፡ ለሥልጣኑ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ኾኖ ፡ በግድ ፡ ፍርዱን ፡ ሊያስለውጠው ፡ ትእዛዙን ፡ ሊያስቀርበት ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ፈጣሪነቱን ፡ አምኖ ፤ መዓትም ፡ ምሕረትም ፡ በእጁ ፡ ያሉ ፡ መኾናቸውን ፡ አውቆ ፤ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በድዬሃለሁና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ብሎ ፡ ለሚለምነው ፡ ለሚማልደው ፡ ሰውስ ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ይዳን ፡ በማለት ፡ የሚለውጥ ፤ የቃጣውን ፡ በትረ ፡ መዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ የሚመልስ ፡ ቸር ፡ አምላክ ፡ እንደኾነ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ የሚከተሉትን ፡ ጥቅሶች ፡ ተመልከት ።

(ሀ) ሎጥን ፡ ከሰዶም ፡ ባወጣው ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ግድም ፡ አትገኝ ፡ አየሮጥክ ፡ በፍጥነት ፡ ወደራቀው ፡ ተራራ ፡ ሒደህ ፡ እራስህን ፡ አድን ፡ አለው ።

ሎጥም ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ በፊትህ ፡ ባለሟልነትንስ ፡ ከገኘሁ ፡ ያ ፡ ተራራ ፡ ሩቅ ፡ ነውና ፡ ከዚያ ፡ ድረስ ፡ ሮጦ ፡ መሔድ ፡ አልችልም ፤ ከዚች ፡ ካጠገቤ ፡ ካለችዋ ፡ ተራራ ፡ ኾኜ ፡ እንድድን ፡ አድርገኝ ፡ ብሎ ፡ ቢለምነው ፤ ጌታ ልመናውን ፡ ሰምቶ ፡ እነሆ ፡ ላጠፋት ፡ የነበረችዋን ፡ ይህችን ፡ አንተ ፡ ልዳንባት ፡ ያልካትን ፡ ሀገር ፡ አልገለብጣትም ፡ ወደርሷ ፡ እስክትደርስ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ላደርግ ፡ አልችልምና ፡ ፈጥነህ ፡ ወደዚያች ፡ ሀገር ፡ ሒደህ ፡ ዳን ፡ ብሎታል ፡ ዘፍ ፲፱ ፲፰-፳፫ ።

(ለ) አክዓብም ፡ ናቡቴን ፡ በግፍ ፡ አስገድሎ ፡ ርስቱን ፡ በወረሰ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናቡቴን ፡ ገደልከውን ፤ ርስቱንም ፡ ወረስክን ፤ ውሾች ፡ የናቡቴን ፡ ደም ፡ በላሱበት ፡ ሥፍራ ፡ ያንተንም ፡ ደም ፡ ይልሱታል ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አመጣብሃለሁ ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ኤልያስን ፡ ላከበት ።

አካዓብም ፡ ደንግጦ ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ ፤ ለብሶ ፡ እያለቀሰ ፡ እየጾመ ፡ ቢለምነው ፡ ኤልያስን ፡ ጠርቶ ፡ አካዓብ ፤ እንደ ፡ ደገጠና ፡ በፊቴ ፡ እንደተዋረደ ፡ አየኸን ፡ ብሎ ፡ የፊተኛውን ፡ ቃሉን ፡ መልሶ ፡ በዘመኑ ፡ ክፉ ። አላመጣበትም ፡ ብሎታል ። ነገ ፡ ቀዳ ፡ ፳፩ ፩-፳፱ ።

(ሐ) ሕዝቅያስ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ ትሞታለህ ፡ አትድንምና ፡ ቤትህን ፡ አዘጋጅ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። ሕዝቅያስም ፡ ፊቱን ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሶ ፡ እያለቀሰ ፡ አቤቱ ፡ በፊትህ ፡ በእውነት ፡ እንደ ፡ ሔድኩ ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘኽንም ፡ በፊትህ ፡ እንደ ፡ ሠራሁ ፡ አስብ ፡ ብሎ ፡ ቢያስታውሰው ፤ ወዲያውኑ ፡ ልመናውን ፡ ሰምቶ ። ልመናህን ፡ ሰማሁ ፡ እንባህን አየሁ ፡ እነሆ ፡ በዘመንህ ፡ ላይ ፡ ፲፭ ዘመን ጨምሬልሃለሁ ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ኢሳይያስን ፡ ልኮበታል ። ኢሳ ፡ ፴፰ ፩-፮

(መ) ዮናስን ፡ ለነነዌ ፡ ሰዎች ፡ እስከ ፫ ቀን ፡ ድረስ ፡ ትገለበጣለች ፡ ብሎ ፡ እንዲያስተምር ፡ በላከው ፡ ጊዜ ፡ ዮናስ ፡ እንዲሁ ፡ ብሎ ፡ ቢያስተምራቸው ፡ የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሰው ፡ ከምግብ ፡ ተከልክለው ፡ ቢያለቅሱበት ፡ እግዚ



አብሔር ፡ ከክፉ ፡ መንገዳቸው ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ አየ ፤ ያደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ የተናገረውንም ፡ መከራ ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ አላደረገባቸውም ። ዮና ፡ ፫ ፬-፲ ።

ባገራችን ፡ ያለው ፡ ሥራት ፡ በኒህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በዘረዘርኩልህ ፡ ነገሮች ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አይደለም ፤ እንዲሁ ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲኾን ፡ ይታመናል ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ አይታመንም ።

፳ ከነገደ ፡ እስራኤልም ፡ ፮፻ሺ ፡ እግረኛ ፡ (ጦረኛ) በኃጢአቱ ፡ ምክንያት ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ላይ ፡ ተመቅሠፍት ፡ ሞቶ ሲያልቅ ፡ ኹለቱ ፡ ኢያሱና ፡ ካሌብ ፡ በጽድቃቸው ፡ ምድረ ፡ ከንዓንን ፡ ብቻቸውን ፡ ወረሱ ፡ እንጂ ፡ ባማላጅነታቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ይዘው ፡ እንዳልገቡ ፡ ልትረዳው ፡ የማከተለውን ፡ ጥቅስ ፡ አንብብ ። ዘፀአ ፡ ፲፪ ፴፯ ። ዘኍ ፲፱ ፳፮ ፴፰ ። ዘዳ ፩ ፴፭ ፴፱ ፡ ስለምትለው ።

ዘፀአ ፡ ፲፪ ፴፯ የጠቀስከው ፡ ከራምሴ ፡ ፮፻ሺህ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ የምልጃ ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ የለበትም ። ዘኍ ፲፬ ፳፯-፴፯ ። የጠቀስከው ፡ ሙሴ ፡ ከ፲፪ቱ ፡ ነገድ ፡ ፲፪ ፡ ሰዎች ፡ መርጦ ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ ሰልላችሁ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ ሰልለው ፡ ተመልሰው ፡ ዐሥሩ ፡ ሰዎች ፡ ሀገሪቱ ፡ ጥሩ ፡ ነፀረች ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኃይለኞች ፡ የኤናቅ ፡ ልጆች ፡ አሉበትና ፡ እግዚአብሔር ፡ እኑሱን ፡ አጥፍቶ ፡ አያወርሰንም ፡ ብለው ፡ ሲከዱ ፡ ኢያሱና ፡ ካሌብ ፡ ጥንቱንስ ፡ ከግብጽ ፡ የወጣን ፡ በእግዚአሔር ፡ ኃይል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእኛ ፡ ጉልበት ፡ ኖሯልን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያወርሰን ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ በማመናችው ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ እንደወረሱ ፤ ፯ቱ ፮ሽህ ፡ ሰዎች ፡ በእንቢተኛነታቸው ፡ ወድቀው ፡ እንደቀሩ ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ኢያሱንና ፡ ካሌብን ፡ አማልዱን ፡ አልዋቸው ፡ እነሱም ፡ አማልደው ፡ ሳይኾንላቸው ፡ ቀረ ወይም ፡ አናማልድም ፡ አሉ ፡ የሚል ፡ የለበትም ።

ስለዚህ ፡ ኢያሱና ፡ ካሌብ ፡ በጽድቃቸው ፡ ምድረ ፡ ከንዓንን ፡ ወረሱ ፡ እንጂ ፡ ባማላጅነታቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ይዘው ፡ አልገቡም ፡ ያልከው ፡ እውነትን ፡ ያልጨበጠ ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

እንዲያውም ፡ አንተ ፡ ባታስተውለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እስራኤል ፡ በማንጐራጐራቸው ፡ ተቆጥቶ ፡ ላጥፋቸው ፡ ቢል ፡ ሙሴ ፡ አማልዶ ፡ ይቅርታ ፡ ካስደረገላቸው ፡ በኋላ ፡ ተዉ ፡ አትሒዱ ፡ ቢላቸው ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ ሔደው ፡ በዓማሌቃውያን ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ወደቁ ፡ ዘርዝሮ ፡ ይጽፋል ፡ ዘኁል ፡ ፩ ፡ ፩-፳ ። ፴፱-፵፭ ።

ዘዳግ ፡ ፩ ፡ ፴፭-፴፱ ፡ የጠቀስከውም ፡ ሙሴ ፡ እስራኤልን ፡ ባለፈው ፡ ኃጢአታቸው ፡ ሲወቅስ ፡ እናንተ ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ የሚሰልሉ ፡ ሰዎችን እንላክ ፡ ስላላችሁኝ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ መርጠን ፡ ላክን ።

ሰላዮችም ፡ ተመልሰው ፡ ያዩትን ፡ ቢነግሯችሁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለጠላን ፡ በአሞራውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይጥለን ፡ ዘንድ ፡ ከምስር ፡ አወጣን ፡ ብላችሁ ፡ አንጐራጐራችሁ ።

እኔም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አትፍሩ ፡ ተዉ ፡ አትሸበሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ፊታችሁን ፡ እየሔደ ፡ ይዋጋላችኋል ፡ ብዬ ፡ ብነግራችሁ ፡ አላመናችሁም ።

እግዚአብሔርም ፡ ይህነን ፡ አይቶ ፡ ተቈጣ ፤ ከዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከካሌብና ፡ ከነዌ ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ በቀር ፤ ምድረ ፡ ርስት ፡ የሚገባ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

www.ethiopianorthodox.org

በናንተ ፡ ምክንያት ፡ እኔንም ፡ ተቈጣኝ ፤ ወደ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ አትገባም ፡ አለኝ ፡ እያለ ፡ ያለፈውን ፡ ይተርክላቸዋል ፡ እንጂ ፡ የምልጃ ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ የለበትም ፡ ስለዚህ ፡ የጠቀስከው ፡ ያለአገባብ ፡ ነው ።

፺ ለሙሴም ፡ ስንኳን ፡ ለለሕዝቡ ፡ ለራሱም ፡ ሊያማልድ ፡ ቢጸልይ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ኹለተኛ ፡ እንዳትናገረኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቈጥቶታል ፡ ዘዳግ ፡ ፫ ፡ ፳፫–፳፮ ፡ ስለምትለው ።

እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ተቆጥቶት ፡ አልቀረም ፡ ፌስጋ ፡ ወደሚባለው ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ አውጥቶ ፡ ሊያያቸው ፡ የተመኛቸውን ፡ ሀገሮች ፡ እንዳሳየው ፡ በ፴፬ኛው ፡ ቊጥር ፡ ይነግረናል ፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባለሟሎቹን ፡ ምልጃ ፡ አይሰማም ፡ ለማለት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አይደለም ፡ ቊ ፡ ፫ ፡ እይ ።

፺፩ ትልቆቹ ፡ ሰዎች ፤ እኛ ፡ ጻድቃን ፡ የምንላቸው ፡ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ እንኳንና ፡ ለሌሎቹ ፡ አማልደው ፡ ከሞት ፡ አትርፈው ፡ አጽድቀው ፡ ከነዓን ፡ ገነት ፡ ሊያገቡ ፡ በጉድለታቸውና ፡ በኃጢአታቸው ፡ ምክንያት ፡ ለየራሳቸውም ፡ በድናቸው፡በምድረ ፡ በዳ ፡ ወድቆ ፡ እንደቀረ ፡ መጻሕፍት ፡ ይነግሩናል ፡ ዘኍ ፡ ፳፬ ፡ ፩–፴፪ ፡ ፳፮–፳፱ ። ዘዳግ ፡ ፴፬ ፡ ፩–፯ ። ፴፪ ፡ ፵፰–፶፪ ። ስለምትለው ።

ዘኍ ፡ ፳፬ ፡ ከ፩–፴፬ ፡ የጠቀስከው ፡ ሙሴ ፡ እለምንሃለሁ ፡ እንደ ፡ ምሕረትህ ፡ ብዛት ፡ የዚህን ፡ ሕዝብ ፡ ኃጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ብሎ ፤ ቢጸልይ ፡ እንደ ፡ ነገርከኝ ፡ ይቅር ፡ አልኩ ፡ ብሎታል ፡ ቊ ፡ ፳፱ ፡ ፳ ።

ሕዝቡ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ቢላቸው ፡ ከክፋታቸው ፡ የማይመለሱ ፡ ስለኾነ ፡ እኒህ ፡ እንቢተኞች ፡ በበርሀ ፡ ወድቀው ፡ እንዲቀሩ ፡ ልጆቻቸው ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ እንዲወርሱ ፡ አደረገ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ቅዱሳን ፡ አያማልዱም ፡ አይልም ።

ም ፡ ፳፩–፳፶ኛም ፡ የሚነበበው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰብስበው ፡ ሔደው ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እህል ፡ ወደማይዘራበት ፤ በለስ ፤ ወይን ፤ ሮማን ፤ ወኃ ፤ ወደሌለበት ፡ ሥፍራ ፡ ለምን ፡ አመጣችሁን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሲሞቱ ፡ አብረን ፡ በሞትን ፡ በተሻለ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ ቢበሳጩባቸው ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ደጃፍ ፡ ሔደው ፡ በግንባራቸው ፡ ወድቀው ፡ ቢለምኑ ፡ ወኃ ፡ ከደንጊያ ፡ እንዳፈለቀላቸው ፡ ይነግረናል ፡ እንጂ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ለምነው ፡ እንዳፈሩ ፡ አይነግረንም ።

ዘዳግ ፡ ፴፬ ፡ ፩–፯ ፡ የጠቀስከውም ፡ ሙሴ ፡ ከሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ወደ ፡ ኔቦ ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ጲስጋ ፡ ራስ ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወጣ ። እግዚአብሔርም ፡ የገለዓድን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ የንፍታሌምን ፡ ምድር ፡ የኤፍሬምንና ፡ የምናሴን ፡ ምድር ፡ የይሁዳንም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ባሕሩ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የዐዜብንም ፡ አጠገብ ፡ የኢያሪኮንም ፡ ሜዳ ፡ ስፋት ፡ የተምሩን ፡ አገር ፡ እስከ ፡ ዘዓር ፡ ድረስ ፡ አሳየው ።

ለልጆችህ ፡ አወርሳቸዋለሁ ፡ ብዬ ፡ ለአብርሃም ፡ ለይስሐቅ ፡ ለያዕቆብ ፡ የማልኩላቸው ፡ ምድር ፡ ይች ፡ ባይንህ ፡ ያሳየሁህ ፡ ሀገር ፡ ናት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ። በቍ ፡ ፳፭ ፡ እኔ ፡ ልለፍ ፡ ይህችን ፡ መልካም ፡ ምድር ፡ ልይ ፡ በዮርዳኖስ ማዶ ፡ ይህነን ፡ መልካሙን ፡ ተራራ ፡ ሊባኖስንም ፡ ልይ ፡ ብሎ ፡ የለመነውን ፡ እንደፈጸመለት ፡ ይነግረናል ፡ እንጂ ፡ ቅዱሳን ፡ ሊያማልዱ ፡ አይችሉም ፡ አይለንም ፡



፴፪ ፡ ፵፰–፶፩ ፡ የጠቀስከውም ፡ በሞዓብ ፡ ምድር ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ዐበሪም ፡ ተራራ ፡ ውጣና ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ የምሰጣቸውን ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ እይ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ እንደ ተነገረው ፡ ልመናውን ፡ እንደፈጸመለት ፡ ይነግረናል ፡ እንጂ ፡ ቅዱሳን ፡ አያማልዱም ፡ አይለንም ።

በድናቸው ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወድቆ ፡ ቀረ ፡ ስለምትለውም ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ የባሮችህን ፡ በድን ፡ ለሰማይ ፡ ዎፎች ፡ ምግብ ፡ አደረጉ ፡ የጻድቃንህንም ፡ ሥጋ ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ ምግብ ፡ አደረጉ ፡ ደማቸውን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያ ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ ወኀ ፡ አፈሰሱ ፡ የሚቀብራቸውም ፡ የለ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ይህ ፡ ለጻድቃን ፡ የክብር ፡ ክብራቸው ፡ እንደኾነ ፡ እወቅ ፡ መዝ ፡ ፸፱ ፡ ፪ና ፡ ፫ ።

፺፪ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ አማላጅነታቸው ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ቄሱ ፡ በኛ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ሥረይ ፡ ኃጢአትየ ፡ ወኃጢአተ ፡ ሕዝብከ ፡ ብሎ ፡ እንደሚጸልይልንና ፡ እንደሚያማልደን ፡ የመሰለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይነት ፡ ልመና ፡ አይምሰልህ ፡ ኤር ፡ ፵፪ ፡ ፩–፯ ፡ ተአመኑ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ኃጢአተየሙ ፡ ወጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ ቢጽክሙ ፡ ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ ብዙን ፡ ትረድእ ፡ ጸሎቱ ፡ ለጻድቅ ፡ ትክል ፡ ወታሠልጥ ፡ ከኃጢአታችሁ ፡ እንድትፈወሱ ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ይጸልይለት ፡ ወይም ፡ ይማልድለት ፡ ይላል ፡ ሐዋርያ ፡ ያዕቆብ ፡ ፭ ፡ ፲፫–፳ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ይህን ፡ ማማለድ ፡ (መለመን ፡) ስለዓለም ፡ ኹሉ ፡ ጸሎትን ፡ ዘወትር ፡ እንዲያደርግ ፡ አዝዞታል ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፩–፰ ፡ ሙሴና ፡ ኢዮብም ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ አማልደዋል ፡ ዘኍል ፡ ፲፮ ፡ ፵፬–፵፰ ፡ ዘፀአ ፡ ፴፪ ፡ ፱–፲፬ ፡ ኢዮብ ፡ ፵፪ ፡ ፯–፱ ፡ አብርሃም ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ በበደሉ ፡ ከታዘዘበት ፡ መቅሠፍት ፡ ለአቤሜሌክ ፡ አማልዶ ፡ ጸልዮ ፡ ከሞት ፡ አድኖታል ፡ ዘፍ ፡ ፳፩–፲፰ ። ስለምትለው ።

እውነት ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ ቢኾን ፡ አሸናፊነቷ ፡ የማይቀር ፡ ስለኾነ ፡ ያለ ውድ ፡ በግድ ፡ አፍህን ፡ ከፍታ ፡ ፊትህን ፡ ጸፍታ ፡ እውነትነቷን ፡ አስመሰከረችህ ።

እኛም ፡ እንዲሁ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አረጋግጠው ፡ ስለነገሩን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከልቡናችን ፡ አንቅተን ፡ ቅዱሳን ፡ ያማልዳሉ ፡ አላልንም ።

የልመናውም ፡ ዐይነት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደሚናገሩት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መጻሕፍት ፡ ከሚናገሩት ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ አንልም ።

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ እያወቅህ ፡ ምልጃ ፡ በፍጹም ፡ የለም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ የምትሰብክ ፡ ከኾነ ፡ አውቆ ፡ አበድነት ፡ ያንተ ፡ የግል ፡ ገንዘብህ ፡ መኾኑን ፡ ትረዳው ፡ ዘንድ ፡ አሳስብሃለሁ ።

፺፫ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ኾነ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ማማለድ ፡ ስለማይኾንለት ፡ ለዝያ ፡ ባዕል ፡ (ነዌን ፡) እንኳንና ፡ ከሲኦል ፡ አውጥቶ ፡ አማልዶ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ሊያገባው ፡ አንድ ፡ ጠብታ ፡ ወኀ ፡ ጉሮሮሑ ፡ የሚያጠልበትም ፡ ሊሰጠው ፡ አልቻለም ፡ ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፫–፳፭ ፡ ስለምትለው ።

ባምስተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለአማላጅነት ፡ በሰጠሁህ ፡ መልስ ፡ በቍ ፡ ፬ ፡ ገጽ ፡ ፻፵፱–፻፶፫ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋም ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስም ፡ ቢኾኑ ፡ ጸሎት ፡ የሚጸለይላቸው ፡ ሰዎች ፡ ገና ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ራሳቸው ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ተጠጥተው ፡ ንስሐ ፡ ገብተው ፡ ጸልዩልን ፡ አማልዱን ፡ ብለው ፡ ለተማፀኑ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ [illegible]ታቸው ፡ ሳይመለሱ ፡ በዕንቢተኝነት ፡ ለሔዱ ፡ አደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

በዐፀደ ፡ ነፍስ ፡ ኸኖ ፡ ጸልዩልኝ ፡ ብሎ ፡ መዳን ፡ እንደሌለስ ፡ በአልዓዛርና ፡ በነዌ ፡ ታውቋል ፡ ብዬ ፡ እንዳስረዳሁህ ፡ ነዌ ፡ ያለጊዜው ፡ ያለቦታው ፡ ስለለመነው ፡ ጉድለቱ ፡ ከነዌ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአብርሃም ፡ አደለም ።

አብርሃምን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ማማለድ ፡ ሕልቻለም ፡ ትለው ፡ ዘንድማ ፡ ገና ፡ ጽድቅና ፡ ኃጢአት ፡ በሚፈራረቁበት ፡ በዓለመ ፡ ሥጋ ፤ ፈቃደ ፡ ሥጋና ፡ ፈቃደ ፡ ነፍስ ፡ በሚፈካከሩበት ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፤ አቤሜሌክን ፡ አብርሃም ፡ ካልጸለየልህ ፡ አልምርህም ፤ አብርሃም ፡ ይጸልይልህና ፡ እምርሃለሁ ፡ ብሎ ፡ የጸሎቱን ፡ ተሰሚነት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደመሰከረለት ፡ አታውቅምን ።

እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የመሰከረለትስ ፡ ከኹነ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጽድቅና ፡ ኃጢአት ፡ በማይፈራረቁበት ፡ በዓለመ ፡ ነፍስ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋና ፡ ፈቃደ ፡ ነፍስ ፡ በማይፈካከሩበት ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኸኖ ፡ ያቀረበውን ፡ ጸሎት ፡ አልሰማህም ፡ የሚለው ፡ መሰለህን ፤ ለቅዱሳንስ ፡ በእየቀኑ ፡ ክብር ፡ እየተጨመረላቸው ፡ ይሔዳል ፡ እንጂ ፡ እየተቀነሰባቸው ፡ የሚሔድ ፡ መሰለህን ።

፲ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ እኛ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ያለነው ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ እንደማናውቀው ፡ እንዲሁም ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ያሉት ፡ ሚቾቹ ፡ ባዕዶቹ ፡ ይቅሩና ፡ አባት ፡ እናቶቻችን ፡ እንኳ ፡ ለኛ ፡ በሥጋ ፡ ሳለን ፡ ልጆቻቸውና ፡ ቤተ ፡ ሰብአቻቸውም ፤ ምን ፡ እንደምንኾንና ፡ እንዴት ፡ እንዳለን ፡ ምንም ፡ አያውቁንም ። ኢዮ ፡ ፯ ፡ ፲ ፡ ፱ ፡ ፲፬ ፡ ፳፩ ፡ ስለምትለው ።

ነዌ ፡ ሥቃዩ ፡ ገሃነም ፣ ስለጸናበት ፡ አባቴ ፡ አብርሃም ፡ እባክህ ፡ አልዓዛርን ፡ ላከውና ፡ አንድ ጠብታ ፡ ውኃ ፡ ይስጠኝ ፡ ቢለው ፡ ልጄ ፤ ኹለታችሁም ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ሳላችሁ ፡ አንተ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ስትኖር ፡ አልዓዛር ፡ በጭንቅ ፡ በሥቃይ ፡ በረኃብ ፡ በጽምዕ ፡ ይኖር ፡ ነበረ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ አልዓዛር ፡ ብድሩን ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይኖራል ። አንተም ፡ ብድርህን ፡ በሥቃይ ፡ በሕማም ፡ መኖር ፡ እንዲገባህ ፡ እወቅ ፡ ብሎታል ።

አልዓዛርና ፡ ነዌ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ አብርሃም ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ እንጂ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ አልነበረም ። እንግዲህ ፡ ነፍሳት ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስ ፡ ኹነው ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ የሚሠራውን ፡ ካላወቁ ፡ ኹለቱም ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ የሠሩትን ፡ ጠቅሶ ፡ ሊያስረዳው ፡ እንደምን ፡ ቻለ ።

፪ተኛም ፡ ነዌ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ በጎ ፡ ያልሠራ ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ለምኖ ፡ የማይጠቅም ፡ መኾኑን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፤ አባቴ ፡ አብርሃም ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ፭ ፡ ወንድሞች ፡ አሉኝ ፤ እነሱም ፡ እንደኔ ፡ ይህ ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ እንዳይመጡ ፡ ይነግራቸው ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ እባክህ ፡ አልዓዛርን ፡ ላከው ፡ ብሎ ፡ ለምኖታል ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ኸኖ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ የሚሠሩትን ፡ አውቆት ፡ አደለምን ።

፫ተኛም ፡ አብርሃም ፡ ሕግ ፡ ተሠርቶላቸዋል ፡ መጻሕፍት ፡ ተጽፈውላቸዋል ፡ መምህራን ፡ ተሾመውላቸዋልና ፣ እኒያን ፡ ይስሙ ፡ ቢለው ፤ የለም ፡ አባቴ ፡ አብ



ርሃም ፡ ከሙታን ፡ አንዱ ፡ ተነሥቶ ፡ ሒዶ ፡ ካላስተማራቸው ፡ አይሰሙም ፡ አያምኑም ፡ አይመለሱም ፡ ብሎታል ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ የሚሠሩትን ፡ ቢያውቅ ፡ አይደለምን ።

፬ተኛም ፡ ዮሐንስ ፡ በራእዩ ፡ በግፍዕ ፡ የሞቱ ፡ የሰማዕታት ፡ ነፍሳት ፡ ቅዱስ ፤ ጻድቅ ፡ የኾንክ ፡ አቤቱ ፡ በምድር ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ የምትታገሣቸው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ደማችንን ፡ በግፍዕ ፡ ያፈሰሱትን ፡ ሰዎች ፡ ተበቅለህ ፡ አታጠፋቸውምን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትታገሣቸዋለህ ፡ እያሉ ፡ ሲከሰሱ ፡ አየሁ ፡ ብሏል ፡ ራእ ፡ ፮ ፡ ፱ ።

እንግዲህ ፡ እኒህ ፡ ነፍሳት ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስ ፡ ኹነው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መጸለያቸው ፡ ግፈኞች ፡ ጠላቶቻቸው ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ መኖራቸውን ፡ ከክፋታቸው ፡ አለመመለሳቸውን ፡ አውቀው ፡ አይደለምን ። የሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ የላቸውምና ፡ በእውቀታቸው ፡ ሠርተው ፡ አይጠቀሙበትም ፡ እንጂ ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስስ ፡ ስንኳን ፡ ለጻድቃን ፡ ለኃጥአንም ፡ ቢኾን ፡ እውቀት ፡ አይከፈልባቸውም ፡ ያውቃሉ ።

፲፩ ፡ ጻድቃን ፡ የሞት ፡ ዕንቅልፍ ፡ ይዞዋቸዋልና ፡ ስንለምናቸው ፡ ስለማይሰሙን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ አይቻላቸውም ። ስንጠራቸው ፡ እንደማይሰሙንና ፡ መልስ ፡ እንደማይሰጡንም ፡ ከፀሐይ ፡ በታች ፡ ፈንታ ፡ የላቸውም ። መክ ፡ ፱ ፡ ፫ ፡ ፯ ። እንኳን ፡ እኛ ፡ ስንጠራቸው ፡ ሊሰሙን ፡ ሰማይ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ኹሉም ፡ ተኝተዋልና ፡ ፈጣሪያቸውንም ፡ አያመሰግኑትም ፡ ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪ ፡ ዘአኮ ፡ ሙታን ፡ ይሴብሑከ ፡ እግዚኦ ፡ እንዳለ ፤ ሕዝቅያስ ፡ ንጉሥ ፡ ኢሳይ ፡ ፴፰ ፡ ፲—፲፰ ፡ ስለምትለው ።

የዚህን ፡ ምሥጢር ፡ ለመረዳት ፡ አስቀድሞ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ውኃን ፤ መሬትን ፤ ነፋስን ፤ እሳትን ፤ እኒህን ፡ ዐራቱን ፡ ባሕርያት ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ አምጥቶ ፡ ፈጠረ ።

ኹለተኛ ፡ በዕለተ ፡ ሠሉስ ፤ ምድር ፡ አዝርዕትን ፡ አትክልትን ፡ ዕፀውን ፡ ታብቅል ፡ ብሎ ፡ ቢያዝዝ ፤ ከኒህ ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ አዝርዕት ፡ አትክልት ፡ ዕፀው ፡ ተፈጠሩ ፡ እሊህ ፤ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠሩ ፡ ፍጥረቶች ፡ በውስጣቸው ፡ ያሉ ፡ ዐራቱን ፡ ባሕርያት ፡ የሚያስተካክሉበት ፡ ምግብ ፡ ያሻቸዋል ። ምግብ ፡ ሲመቻቸው ፡ ይለመልማሉ ፡ ያድጋሉ ፡ ይረዝማሉ ፡ ይወፍራሉ ። ምግብ ፡ ሲያጡ ፡ ይደርቃሉ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላሉ ፤ በእሳት ፡ ባይቃጠሉም ፡ ከምድር ፡ ወድቀው ፡ ይበሰብሳሉ ፡ ተመልሰው ፡ ዐፈር ፡ ይኾናሉ ።

እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በምስተኛው ፡ ቀን ፡ ባሕር ፡ በደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ኹነው ፡ የሚኖሩ ፡ ፍጥረታትን ፡ ታውጣ ፡ ብሎ ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ከኒሁ ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ በደማዊት ፡ ነፍስ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ለዕለት ፡ ጥቅማቸው ፡ ሥጋዊ ፡ እውቀትን ፡ ብቻ ፡ ጥቂት ፡ የሚያውቁ ፡ እንስሳት ፡ አራዊት ፡ አዕዋፍ ፡ አንስርት ፡ ተፈጠሩ ። እሊህም ፡ ፍጥረቶች ፡ ደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ስላደረችባቸው ፡ [illegible] ኙትው ፡ የሚያሻቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከመፈለጋቸው ፡ በቀር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ በተገኘው ፡ ተፈጥሯቸው ፡ ከአዝርዕት ፡ ከአትክልት ፡ ልዩነት ፡ ስለሌላቸው ፡ ምግብ ፡ ሲመቻቸው ፡ ያድጋሉ ፡ ይረዝማሉ ፡ ይወፍራሉ ፡ ይሰባሉ ፤ ምግብ ፡ ሲያጡ ፡ ይሞታሉ ፡ ይፈርሳሉ ፡ ይበሰብሳሉ ፡ ዐፈር ፡ ትቢያ ፡ ይኾናሉ ።

እንደዚሁም ፡ በ፮ተኛው ፡ ቀን ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርዓያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤ ሰው ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ዘረዘርናቸው ፡ ፍጥረታት ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያትና ፡ ከደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ተፈጠረ ። ካራቱ ፡ ባሕርያትና ፡ ከደማዊት ፡ ነፍስ ፡ በመፈጠሩ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ተዘረዘሩት ፡ ፍጥረታት ፡ ሲኾን ፡ ከነርሱ ፡ የሚበልጥባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚመስልባት ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ፍጹም ፡ እውቀት ፡ ያላት ፡ ክፋትንም ፡ በጎነትንም ፡ በራሷ ፡ ሥልጣን ፡ መሥራት ፡ የሚቻላት ፡ የማትሞት ፡ የማትፈርስ ፡ የማትበሰብስ ፡ የምታስብ ፡ የምትናገር ፡ ዘወትር ፡ ሕያው ፡ ኾና ፡ የምትኖር ፡ ነባቢት ፡ ነፍስን ፡ አዋሐደው ።

ይህነንም ፡ ሐዋርያት ፡ አመክንዮ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ንለቡ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ውስተ ፡ ሥጋነ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ኢትመውት ፡ ወኢትማስን ፡ ምስለ ፤ ሥጋ ።

እንግዲህ ፡ በሥጋችን ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ የማትሞት ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ የማትፈርስ ፡ የማትበሰብስ ፤ ነፍስ እንዳለች ፡ እናስተውል ፡ ብለዋል ፡ ዲድስ ። ሃይ ፡ አበ ። በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ተመልከት ። ኢዮ ፤ ፴፰ ፡ ፲፩ ።

ይህነንም ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ መቅድመ ፡ ወንጌልን ፡ የጻፉ ፡ አሞንዮስ ፡ አውሳብዮስ ፡ ሥጋ ፡ ዘፍጹም ፡ ቆሙ ፡ ዘቦቱ ፡ ክልኤቱ ፡ ኃይል ፡ ኃይለ ፡ ዘርዕ ፡ ወኃይለ ፡ እንስሳ ።

አካሉ ፡ ፍጹም ፡ የሚኾን ፡ ሥጋ ፡ የዘርዕ ፡ የተክል ፡ ኃይልና ፡ የእንስሳ ፡ ኃይል ፡ ኹለት ፡ ኃይል ፡ አለው ፡ ብለው ፤ ያራቱ ፡ ባሕርያትንና ፡ የደመ ፡ ነፍስን ፡ ተፈጥሮ ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ።

ወዓዲ ፡ አክበሮ ፡ በንፍሐት ፡ ዘይእቲ ፡ ማኅተመ ፡ ሕይወት ፡ መንፈሳዊት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ አክበሮ ፡ እምኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ዘታሕተ ፡ ሰማይ ፤ ወትትዐወቅ ፡ በኃይለ ፡ ንባብ ። ወገብረ ፡ ላቲ ፡ ሥልጣነ ፡ በውስቴታ ፡ ትግበር ፡ በከመ ፡ ኀርየት ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይኬንና ፡ ወዘይኄይላ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እከያቲሃ ፡ ወሠናያቲሃ ፡ በሥምረተ ፡ ሕሊናሃ ፡ በአምሳለ ፡ መላእክት ፡ ብለው ፡ ነግረውናል ። መቅ ፡ ወን ።

እንግዲህ ፡ ሰው ፡ እንስሳትን ፡ የሚመስልበትና ፡ መላእክትን ፡ የሚመስልበት ፡ ኹለት ፡ ጠባይዓት ፡ እንዳሉት ፡ አስተውል ። ኹለት ፡ ጠባይዓት ፡ የተባሉትም ፡ ደማዊት ፡ ነፍስና ፡ ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ናቸው ።

ደማዊት ፡ ነፍስና ፡ ነባቢት ፡ ነፍስም ፡ በፈቃድ ፡ የማይገናኙ ፡ የሚለያዩ ፡ ናቸው ።

የማይስማሙ ፡ የተለያዩ - ስለኾኑ ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሥጋን ፡ ለመማረክ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይዋጋሉ ። ሮሜ ፡ ፯ ፡ [illegible]



ደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ብታሸንፍ ፡ ሰው ፡ እንስሳትን ፡ መስሎ ፡ ይኖራል ። እንስሳትንም ፡ መምሰል ፡ ማለት ፡ ሕግ ፡ እንዳልተሠራላቸው ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ ጊዜ ፡ ሳይወሰኑ ፡ መብላት ፡ መጠጣት ፡ መተኛት ፡ መነሣት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ሥጋን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛትን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ሲሠሩ ፡ መኖር ፡ ነው ፡ መዝ ፡ ፵፱ ፡ ፲፪ ፡ ፳ ።

ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ያሸነፈችና ፡ የማረከችው ፡ እንደ ኾነ ፡ መላእክትን ፡ ታስመስለዋለች ፡ መላእክትን ፡ መስሎ ፡ ይኖራል ። መላእክትንም ፡ መምሰል ፡ ሰው ፡ መፈጠሩ ፡ ለሰማያውያን ፡ መላእክት ፡ ተባባሪ ፡ ተወዳዳሪ ኾኖ ፡ ሰማያዊ ፡ መንግሥት ፡ ሊወርስ ፡ እንጂ ፡ የሌሎች ፡ ፍጥረታት ፡ ተባባሪ ፡ ኾኖ ፡ እንዲቀር ፡ አለመኾኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ ለቁመተ ፡ ሥጋ ፡ ያኽል ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እየተመገቡ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ በቁመት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ተወስኖ ፡ ሰማያዊ ፡ ነገርን ፡ እያሰቡ ፡ መላእክትን ፡ መስሎ ፡ መኖር ፡ ነው ።

ሰው ፡ ኹሉ መላእክትንም ፡ መስሎ ፡ ቢኾን ፡ እንስሳትንም ፡ መስሎ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ሞት ፡ አይቀርለትም ፡ ይሞታል ።

ይሞታልም ፡ ማለት ፡ ነፍስና ፡ ሥጋው ፡ ይለያያሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ ሕይወቱ ፡ ኾና ፡ ታንቀሳቅሰው ፡ የነበረ ፡ ሥጋ ፡ ነፍሱ ፡ ስለተለየችው ፡ ነባቢት ፡ ነፍስን ፡ ከመዋሐዱ ፡ በቀር ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያትና ፡ ከደማዊት ፡ ነፍስ ፡ በመፈጠሩ ፡ ከሌሎች ፡ ፍጥረታት ፡ የሚሻለው ፡ መሻል ፡ ስላሌለው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሬሳ ፡ ኾኖ ፡ ይወድቃል ፤ መሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብእ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ ባለው ፡ ዐዋጅ ፡ መሠረት ፡ በመቃብር ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ ዐፈር ፡ ትቢያ ፡ ኾኖ ፡ ይኖራል ።

ነፍስ ፡ ግን ፡ በባሕርይዋ ፡ መፍረስ ፡ መበስበስ ፡ የለባትምና ፡ በደማዊት ፡ ነፍስ ፡ ኃይል ፤ ተሸንፋ ፡ እንስሳትን ፡ መስላ ፡ ኖራ ፡ እንደኾነ ፡ ከአጋንንት ፡ ጋራ ፡ በመከራ ፡ ቦታ ፡ በሥቃይ ፡ ትኖራለች ።

ደማዊት ፡ ነፍስን ፡ አሸንፋ ፡ መላእክትን ፡ መስላ ፡ ኖራ ፡ እንደኾነ ፡ በዕረፍት ፡ ቦታ ፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ እየተደሰተች ፡ ትኖራለች ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፬–፳፮ ።

ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በሕይወትና ፡ በሞት ፤ በሰማይና ፡ በምድር ፡ አለ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ።

ይኸውም ፡ አልዓዛር ፡ ሞቶ ፡ በመቃብር ፡ አለ ፤ አልዓዛር ፡ ሞቶ ፡ በሕፅነ ፡ አብርሃም ፡ ተቀመጠ ።

ነዌ ፡ ሞቶ ፡ ወደመቃብር ፡ ወረደ ፤ ነዌ ፡ ሞቶ ፡ በሲኦል ፡ ሥቃይ ፡ ተቀበለ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

ሰው ፡ በሞትም ፡ በሕይወትም ፡ የሚገኝ ፡ ስለኾነ ፡ መጻሕፍት ፡ ሰውን ፡ በሥጋ ፡ መደብ ፡ አቁመው ፡ ሲናገሩ ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ እንደጠቀስከው ፡ ደመና ፡ ተበትኖ ፡ እንዲሔድ ፡ እንዲሁ ፡ ወደሙታን ፡ ስፍራ ፡ የሚወርድ ፡ አይወጣም ፡ ወደቤቱ ፡ ደግሞ ፡ አይመለስም ፡ ስፍራውንም ፡ አያውቀውም ። እንዲሁም ፡ ሰው ፡ [illegible] ሬቆምም ፡ ሰማይ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ከእንቅልፋ ፡ አይነቃም ፡

www.ethiopianorthodox.org

አይሰማም ። ልጆቹ ቢከብሩ ፡ ወይም ፡ ቢዋረዱ ፡ አያውቅም ፡ አያስተውልም ፡ እያሉ ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ፡ ኢዮ ፡ ፯ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ፲፬ ፡ ፲፪ ፡ ፳፩ ።

ደግሞ ፡ ሰውን ፡ በነፍስ ፡ መደብ ፡ አቁመው ፡ ሲናገሩ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በብዙ ፡ ዘመን ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ አምላከ ፡ አብርሃም ፡ ወአምላከ ፡ ይስሐቅ ፡ ወአምላከ ፡ ያዕቆብ ።

እኔ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ አምላክ ነኝ ፡ ይላል ። ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፯ ፡ ፴፪ ።

እንዲህ ፡ ባለጊዜ ፡ የሕያዋን ፡ አምላክ ፡ እንጂ ፡ የሙታን ፡ አምላክ ፡ አለመኾኑን ፤ ኢኮነኬ ፡ አምላከ ፡ ምውታን ፡ አላ ፡ አምላከ ፡ ሕያዋን ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕያዋን ፡ በኀቤሁ ።

ኹሉም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሕያዋን ፡ ናቸውና ፡ የሕያዋን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምውታን ፡ አምላክ ፡ አደለም ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ተርጕሞታል ፡ ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፴፰ ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴፪ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ። ወይእዜኒ ፡ ዕበዩ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋየ ፡ እመኒ ፡ በሕይወትየ ፡ ወእመኒ ፡ በሞትየ ፡ አንሰ ። እመኒ ፡ ሐየውኩ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወእመኒ ፡ ሞትኩ ፡ ርቡሕ ፡ ሊተ ። ኃጣእኩ ዘአኅሪ ፡ ለነፍስየ ፡ እምእሉ ፡ ክልኤቱ ፤ ዘያጽሕቀኒ ፡ ፈቂዶቶሙ ። እፈቱሰ ፡ እፍልስ ፡ ወእትፈለጥ ፡ እምዓለም ፡ ከመ ፡ አሀሉ ፡ ኀበ ፡ ክርስቶስ ፡ ወፈድፋደ ፡ ይኄይስ ፡ ወይደሉ ፡ ሊተ ፡ ዝንቱ ። ፊልጵ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

እኔ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ብኖርም ፡ ክርስቶስን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ፤ ብሞትም ዋጋዬ ፡ ይቆየኛልና ፡ በሕይወቴም ፡ ቢኾን ፤ በሞቴም ፡ ቢኾን ፡ የክርስቶስ ፡ ክብሩ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አለ ። እሳቸውን ፡ ከሚያሻኝ ፡ ከነዚህ ፡ ከኹለቱ ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከመኖርና ፤ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ከመኖር ፡ ለሰውነቴ ፡ የምመርጠው ፡ ቸገረኝ ። መውደዱንስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለይቼ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ልኖር ፡ እወዳለሁ ፡ ይልቁንም ፡ ይህ ፡ በሞት ፡ መለየቱ ፡ ይሻላል ። ብሎ ፡ በነፍስ ፡ ሕያው ፡ መኾኑን ፡ አስረድቶናል ።

ይልቁንም ፡ ሰሎሞን ፤ መክብብ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ሙታን ፡ አንዳች ፡ አያውቁም ፤ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ፤ ስማቸው ፡ ተረሥቷልና ፡ ከፀሐይ በታችም ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ለዘለዓለም ፡ ፈንታ ፡ የላቸውም ፡ ብሎ ፡ በሥጋ ፡ የሚደርስባቸውን ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ። ጥበብ ፤ በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ደግሞ ፡ በነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነው ፡ እንዲኖሩ ፤ ሕያዋን ፡ ኾነው ፡ ከመኖራቸውም ፡ በላይ ፡ የኃጥአን ፡ ነፍሳት ፡ ቅጣት ፡ እንዳለባቸው ፤ የጻድቃን ፡ ነፍሳት ፡ በክብር ፡ እየኖሩ ፡ ረሲዓንን ፡ እንዲገዙ ፡ ሲያስረዳ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

ይቤሉ ፡ በርእሶሙ ፡ ኢሐልዮሙ ፡ ርትዐ ፡ እስመ ፡ ኅዳጥ ፡ ውእቱ ፡ ንብረትነ ፡ ወማኅዘን ፡ ወአልቦ ፡ ፈውስ ፡ ለሞተ ፡ ብእሲ ፡ እስመ ፡ በከ ፡ ተፈጠርነ ፡ ለሊነ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ንከውን ፡ ከመ ፡ ዘኢተፈጠርነ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ እስትንፋስ ፡ ውስተ ፡ አንፍነ ፡ ወእምከመ ፡ ጠፍዐ



ወመንፈስነሂ ፡ ይትከዐው ፡ ከመ ፡ ሳሕወ ፡ ደመና ፡ ወስምነሂ ፡ ይትረሳእ ፡ በመዋዕል ፡ ወአልቦ ፡ መኑሂ ፡ ዘይዜክር ፡ ምግባሪተነ ፡ ወየሐልፍ ፡ ንብረትነ ፡ ከመ ፡ ዐሠረ ፡ ሕልፈተ ፡ ደመና ፡ እስመ ፡ ንብረትነ ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ ሐለፈ ። ንዑኬ ፡ ንትፈጋዕ ፡ በዘሀሎ ፡ ሠናያት ፡ ወንግበር ፡ ሐዋዘ ፡ ውስተ ፡ ፍጥረትነ ፡ በአስተሐምሞ ፡ እንዘ ፡ ሀሎነ ፡ በመዋዕለ ፡ ውርዛዌነ ። ወይነ ፡ ብዙኀ ፡ ወዕፍረተ ፡ ምዑዘ ፡ ንትመላዕ ፡ ወኢይሕልፈነ ፡ ጽጌ ፡ ደመና ። ወንትቀጸል ፡ ጽጌረዳ ፡ ሠርፀ ፡ ዘእንበለ ፡ ይፀምሒ ፡ ወኢይኩን ፡ መኑሂ ፡ ዘኢይሳተፍ ፡ እምጽጌ ፡ ትዕቢትነ ፡ ወአልቦ ፡ እምውስቴትነ ፡ ዘኢይደልዎ ፡ እምእንቲአነ ፡ ፍሥሐ ። ጥበ ፡ ፪ ፡ ፳፬–፴፯ ።

የቀናውን ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ አናስብም ፡ ብለው ፡ በራሳቸው ፡ ዓብዝነት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምንኖረው ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡ ያውም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነውና ፡ ለከንቱ ፡ ተፈጥረናልና ፡ ከተፈጠርን ፡ በኋላ ፡ እንዳልተፈጠርን ፡ እንኾናለን ። በፍንጫችን ፡ የሚመላለስ ፡ ትንፋሻችንም ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ነውና ፡ ሥጋችን ፡ ከነፍሳችን ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ አመድ ፡ ትቢያ ፡ ይኾናል ፤ ነፍሳችንም ፡ እንደ ፡ ጉም ፡ ኸንቶ ፡ ይጠፋል ፤ ስማችንም ፡ በሞትንበት ፡ ወራት ፡ ይዘነጋል ፤ ሥራችንን ፡ የሚያስበው ፡ ማንም ፡ የለም ፤ አናዋራችንም ፡ እንደጥላ ፡ ያልፋልና ፡ እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ኑ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ በሕፃንነታችን ፡ ወራት ፡ ከዚህ ፡ ይህ ፡ ቀረ ፡ እያልን ፡ በገንዘባችን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እናድርግበት ፤ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ሰውነታችን ፡ ሳይረግፍ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አይለፈን ፤ ብዙ ፡ ወይንን ፡ እንጠጣ ፡ መልካም ፡ ሽቱ ፡ እንቀባ ፤ በትዕቢታችን ፡ ከምናደርገው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የማይካፈል ፡ እኛ ፡ የምናደርገው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የማይስማማው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ በውስጣችን ፡ አይኑር ፡ ይላሉ ።

ወኢተሰፈዉ ፡ ፀስበ ፡ ጻድቅ ፡ ወኢፈለጡ ፡ ዕበየ ፡ ክብረ ፡ ነፍሳት ንጹሓት ፡ እለ ፡ አልቦን ፡ ነውር ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠሮ ፡ ለሰብእ ፡ እንበለ ፡ ሙስና ፡ ወገብሮ ፡ በአርኣያ ፡ ዚአሁ ፡ ወበቅንዓተ ፡ ዲያብሎስ ፡ ሞት ፡ መጽአ ፡ ወበዐ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወያሜክር ፡ ሰብአ ፡ እለ እሙንቱ ፡ እመክፈልተ ፡ ዝንቱ ።

ከርሱ ፡ ዕድል ፡ ወገን ፡ የሚኾኑትን ፡ ሰዎች ፡ በሚፈታተን ፡ በዲያብሎስ ፡ ተንኰል ፡ ሞት ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ መጣ ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በርሱ ፡ አምሳል ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ እንዲኖር ፡ ስለፈጠረው ፡ ጻድቁ ፡ የሚያገኘውን ፡ ዋጋ ፡ ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለባቸው ፡ ንጹሓት ፡ የሚኾኑ ፡ ነፍሳት ፡ የሚያገኙትን ፡ ክብር ፡ አላወቁምና ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አይለፈን ፡ አሉ ፡ ብሎ የረሚዓንን ፡ ነገር ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ስለጻድቃን ፡ ነፍስ ፡ የሚከተለውን ፡ ተናገረ ።

ነፍሶሙሰ ፡ ለጻድቃን ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢለከሮሙ ፡ ሥቃይ ፡ ወለአዕይንተ ፡ አብዳን ፤ መሰሎሙ ፡ ከመ ዘሞቱ ፡ እሙንቱ ፡ ወተኈለቈ ፡ ፀአቶሙ ፡ ከመ ፡ እከይ ፡ በሙ ፡ ወሕልፈቶሙ ፡ ተመሰለ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ሎሙ ፡ ወእመሂ ፡ ተኰነኑ ፤ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ ተስፋሆሙሰ ፡ ፍጽምት ፡ ሕይወት ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ [illegible] ፡ ሞት ። ወኅዳጠ ፡ ተኰነኖሙ ፡ ዐቢየ ፡ ይዴለዉ ፡ እስመ ፡ እግዚ

www.ethiopianorthodox.org

አብሐር ፡ አመክሮሙ ፡ ወረከበሙ ፡ ድልዋነ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ወርቅ ፡ ዘይትፈተን ፡ በምንሐብ ፡ አመክሮሙ ፤ ወከመ ፡ ጽንሐሐ ፡ ዕጣን ፡ ዘይትዌከፍ ፡ ውኩፈ ፡ ተወከሮሙ ፤ በመዋዕለ ፡ ሕዋጼሆሙ ፡ ይበርሁ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ ወከመ ፡ ቀለምጺጽ ፡ ውስተ ፡ ብርዕ ፡ ይረውጹ ፡ ወይኬንኑ ፡ አሕዛበ ፡ ወይእኅዙ ፡ ሕዝበ ፡ ወይነግሥ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሐር ፡ ለዓለም ። ጥበ ፡ ፩ ፡ ፳–፳፱ ።

የጻድቃን ፡ ነፍስ ፡ በእደ ፡ እግዚአብሐር ፡ ስለተያዘች ፡ ሥቃየ ፡ ገሃነም ፡ አላገኛቸውም ። ላላዋቆች ፡ ግን ፡ የሞቱ ፡ መሰላቸው ፤ ከዚህ ፡ ዓለምም ፡ በሞት ፡ መለየታቸው ፡ ክፋት ፡ እንዳለባቸው ፡ ተቈጠረ ። በጥፋታቸውም ፡ መሰለ ። እነሱ ፡ ግን ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ አሉ ፡ በሰውም ፡ ዘንድ ፡ መከራ ፡ ቢቀበሉ ፡ አለኝታቸው ፡ በእግዚአብሐር ፡ ዘንድ ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ፍጽምት ፡ ሕይወት ፡ ናት ። ጥቂት ፡ መከራ ፡ ተቀብለው ፡ ብዙ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ያገኛሉ ። ወርቅ ፡ ብር ፡ በከውር ፡ እንዲፈተን ፡ እግዚአብሐር ፡ በመከራ ፡ ቢፈትናቸው ፡ እርሱን ፡ ለማገልገል ፡ የተዘጋጁ ፡ ኾነው ፡ አግኝቷቸዋልና ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ተቀበላቸው ። በጸጋ ፡ በክብር ፡ በሚጎበኙበትም ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ያበራሉ ። በብርዕ ፡ የተፈናጠረ ፡ የብረት ፡ ፍንጣሪ ፡ እየሰፋ ፡ እንዲሔድ ፡ በክብር ፡ እየሰፉ ፡ ይሔዳሉ ። በነፍስም ፡ ሕዝቡን ፡ አሕዛቡን ፡ ይገዛሉ ። በርሱ ፡ ያመኑ ፡ ሰዎች ፡ እውነተኛ ፡ ሕጉን ፡ ያውቃሉና ፡ እግዚአብሐር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ይነግሥላቸዋል ።

ወነኪራንሰ ፡ ዘንተ ፡ ርእዮሙ ፡ በሕሊናሆሙ ፡ ኢለበሙም ፡ ወኢያስተጋብኡ ፡ ፍከሬሁ ፡ ለዝ ። እስመ ፡ ፍትሑ ፡ ለእግዚአብሐር ፡ ውእቱ ፡ ለጻድቃኒሁ ፡ ወሕዋጼሁ ፡ በማህል ፡ ይከውን ፡ ላዕለ ፡ ኅሩያኒሁ ። ወብእሲሰ ፡ ጻድቅ ፡ መዊቶ ፡ ይኴንን ፡ ረሚዓነ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ሕያዋኒሆሙ ። ጥበ ፡ ፪ ፡ ፲፰–፳፩ ።

ኃጥአን ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ አላስተዋሉትም ፡ የእግዚአብሐር ፡ ፍርዱ ፡ ለጻድቃን ፡ በይቅርታ ፡ መጐብኘቱም ፡ ለወዳጆቹ ፡ ነውና ፤ ሰው ፡ በሥጋ ፡ ቢሞት ፡ በነፍስ ፡ ሕያው ፡ መኾኑን ፡ የዚህን ፡ ትርጓሜ ፡ አላወቁትም ፡ እንዲያውም ፡ ጻድቅስ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሐርን ፡ የዘነጉትን ፡ ሰዎች ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ይገዛል ፡ ብሏል ። ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የዘረዘርኩልህን ፡ ተመልክተህ ፡ ጻድቃንን ፡ መሳደብህን ፡ እንድትተው ፡ አሳስብሃለሁ ።

፲፪ ፡ ፈጽሞ ፡ ከአዳም ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ጻድቅ ፡ ስለማይገኝ ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉም ፡ ዐመፁ ፡ አንድም ፡ መልካም ፡ የሚሠራ ፡ ጻድቅ ፡ እንኳ ፡ የለም ፡ ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲–፲፰ ። ወኮነ ፡ ኵልነ ፡ ርኵሳነ ፡ ኢሳ ፡ ፷፬ ፡ ፮ ። ከርኩስ ፡ ንጹሕናን ፡ ሊያወጣ ፡ የሚችል ፡ ማነው ፡ አንድም ፡ የለም ፡ ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፬ ፡ ይላሉ ። አትናቴዎስም ፡ በቅዳሴው ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቊ ፡ ፭ ፡ ሰብእሰ ፡ ጽቡረ ፡ ኃጢአት ፡ ውእቱ ፡ ብሏል ። ያዕቆብ ፡ ዘሥሩግም ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቊ ፡ ፳ ፡ አልቦ ፡ ዘተረክበ ፡ ዘኢጎደገ ፡ ለሥርዓትከ ፡ እምቀዳሚ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ይላልና ፡ ይህ ፡ አልቦ ፡ ማለቱ ፡ ፈጽሞ ፡ ከቶና ፡ አካቶ ፡ የሌለ ፡ የማይገኝ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ። ኢሳይ ፡ ፵፭ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ስለምትለው ።

ከኢሳይያስና ፡ ከኢዮብ ፡ የጠቀስከው ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በፊት ፡ የተነገረ ፡ ዛሬ ፡ የተሻረ ፡ መኾኑን ፡ ከሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲–፲፰ ፡ የጠቀስከውና ፡ ከአትናቴዎስ ፡ ከያዕቆብ ፡ ዘሥሩግም ፡ የጠቀስከው ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ እያለ ፡



ያንን ፡ በአሪት ፡ የነበረውን ፡ ፍዳ ፡ መርገም ፡ የሚተርክ ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ የቀረልን ፡ መኾኑን ፡ ታውቅ ፡ ትረዳ ፡ ዘንድ ፡ በ፳ተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለአማላጅነት ፡ በጻፍኩልህ ፡ መልስ ፡ በሰ፫ው ፡ ተጽፎልሃልና ፡ ያንን ፡ ተመልከት ። ዛሬስ ፡ እኔ ፡ ተልእከየን ፡ ፈጽሜያለሁ ፡ የማርፍበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ፡ በጎ ፡ ገድልን ፡ ተጋደልሁ ፡ ቅድድሜንም ፡ ጨረስሁ ፡ ሃይማኖቴንም ፡ ጠበቅሁ ፡ እንግዲህስ ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ እግዚአብሐር ፡ የሚሰጠኝ ፡ ዋጋዬ ፡ ይቆየኛል ፡ ብለን ፡ የምንመካበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯–፰ ።

፲፫ ፡ ወንድሜና ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ ብትበሉ ፡ ብትጠጡ ፡ ወይስ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ብታደርጉ ፡ ኹሉን ፡ ስለእግዚአብሐር ፡ ክብር ፡ አድርጉት ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ስለፍጡራን ፡ ክብር ፡ አድርጉት ፡ አይሉም ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፴፩ ፡ ስለምትለው ፡

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ስሌላው ፡ ዕንቅፋት ፡ ለመኾን ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ አውቆ ፡ መብላት ፡ እንዳይገባ ፡ በጻፈላቸው ፡ አንቀጽ ፡ ለግብዣ ፡ የጠራችሁ ፡ የማያምን ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እናንተም ፡ ብትሔዱ ፡ ይህ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ሳትጠይቁ ፡ ያቀረቡላችሁን ፡ ኹሉ ፡ ብሉ ። ይህ ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢነግሯችሁ ፡ ግን ፤ ለሌሎች ፡ ዕንቅፋት ፡ እንዳትኾኑ ፡ በወንጌል ፡ ማመን ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ለመብላት ፡ ኖሯልን ፡ ብለው ፡ ግእዛነ ፡ ነፍስ ፡ ያገኛችሁበት ፡ ወንጌልንም ፡ እንዳታስነቅፏት ፡ አትብሉ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፤ ስመ ፡ እግዚአብሐር ፡ ጠርቼ ፡ አፀኑ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግሜ ፡ ብበላው ፡ ምን ፡ ይጐዳኛል ፤ ለምንስ ፡ ይነቅፉኛል ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሐር ፡ ገንዘብ ፡ እንደኾነ ፡ ለጣዖት ፡ ገንዘብ ፡ እንደሌለው ፡ አውቃችሁ ፡ ካደረጋችሁትስ ፡ ብትበሉም ፡ ብትጠጡም ፡ ስመ ፡ እግዚአብሐር ፡ ጠርታችሁ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግማችሁ ፡ የምትሠሩትን ፡ ሥራ ፡ ብሎ ፡ ለጣዖት ፡ ስለ ፡ ተሠዋው ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፤ ስለቅዱሳን ፡ መታሰቢያ ፡ ለተራብ ፡ አታብሉ ፡ ለተጠማ ፡ አታጠጡ ፡ አላለም ።

ይህስ ፡ የሚገባ ፡ ሥራ ፡ መኾኑ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ በደቀ ፡ መዝሙሬ ፡ ስም ፡ ጽዋ ፡ ወኀ ፡ ያጠጣ ፡ ዋጋውን ፡ አያጣም ፡ ብሏል ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፵፪ ።

፲፬ ፡ ከጳውሎስ ፡ የበለጠ ፡ እስከ ፡ ፫ተኛ ፡ ሰማይ ፡ የተመሠጠ ፡ ጻድቅ ፡ ወይት ፡ ይገኝ ፡ ይኾን ፡ ምንም ፡ አይገኝም ፡ ለጳውሎስና ፡ ለበርናባስ ፡ ክብርና ፡ ዝክር ፡ መሥዋዕት ፡ ሊኾናቸው ፡ ብለው ፡ ድግስ ፡ ላቀረቡላቸው ፡ ሰዎች ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ አሏቸው ። ወሰሚያሙ ፡ ሐዋርያት ፡ ወይቤልዎሙ ፡ አንትሙ ፡ ሰብእ ፡ ምንትኑ ፡ ዝንገር ፡ አኮኑ ፡ ከማከሙ ፡ ሰብእ ፡ ንሕነ ፡ ዘንመውት ፡ ወንሜሕረከሙ ፡ ከመ ፡ ትኅድጉ ፡ ዘንተ ፡ ከንቶ ፡ ወትትመየጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሐር ፡ ሕያው ፡ ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ወባሕረ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስቴቶሙ ። ለኛ ፡ ለአምላክ ፡ ባሮች ፡ ክብር ፡ አይገባንምና ፡ ይህ ፡ ከንቱ ፡ የኾነ ፡ ሥራችሁ ፡ ለፍጡራን ፡ ማምለክ ፡ ተውት ፤ ሰዎችን ፡ እንደማይጠቅሙም ፡ ኢዘተከለ ፡ ወኢዘሠቀየ ፡ አልቦ ፡ ዘበቊዐ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ዘአልሐቀ ። ሀቡ ፡ ዕበየ ፡ ለአምላክነ ፡ እያሉ ፡ አስተማሩ ፡ እንጂ ፡ ለኛ ፡ ለሐዋርያት ፡ ለጻድቃን ፡ ክብር ፡ ለናንተም ፡ ጽድቅ ፡ ሊቆጠርላችሁ ፡ የኛ ፡ ስም ፡ እንሥታችሁ ፡ ብሉ ፤ ጠጡ ፡ ብለው ፡ አላስተማሩም ፡ የሐዋ ፡ ሥ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ፲ ፡ ፴፩ ፡ ስለምትለው ።

ባለፈው ፡ ንግግርህ ፡ ከአዳም ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ጻድቅ ፡ ስለማይገኝ ፡ ኹሉም ፡ ዐመፁ ፡ አንድም ፡ መልካም ፡ የሚሠራ ፡ ጻድቅ ፡ የለም ። የለም ፡ ማለቱም ፡ ፈጽሞ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከቶ ፡ አካቶ ፡ የሌለ ፡ የማይገኝ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ፡ ብለህ ፡ አስጠንቅቀኸኝ ፡ ነበረ ።

አሁን ፡ ግን ፡ የተናገርከውን ፡ ረስተህ ፡ ከጳውሎስ ፡ የበለጠ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ሰማይ ፡ የተመሠጠ ፡ ጻድቅ ፡ ወዴት ፡ ይገኝ ፡ ይኾን ? አይገኝም ፡ እያልክ ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ ጻድቅነት ፡ ታዳንቃለህ ። እንግዲህ ' ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰው ፡ አይደለምን ። ንግግርህ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ እውነትን ፡ ያልጨበጠ ፡ ገለባ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ። ይህ ፡ የምትናገረው ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ ፡ ሰምተው ፤ ይህ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተቈጡ ፡ ብሎ ፡ አስመስሎ ፡ ከመናገር ፡ ሰምተው ፡ የተቈጡበትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ከፍ ፡ ብለህ ፡ አታመጣውም ፡ ነበርን ? አስመስሎ ፡ በመናገር ፡ ያልተማሩትን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ ጐዳና ፡ ብትመራቸው ፡ ምን ፡ ትጠቀማለህ ።

የተወደዳችሁ ፡ ምእመናን ፡ ሆይ ፡ እውነተኛው ፡ ነገር ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ ተጽፎ ፡ የምናገኘው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ልስጥራን ፡ በሚባል ፡ ሀገር ፡ ከእናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ልምሾ ፡ ኾኖ ፡ የተወለደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሲያስተምር ፡ በሰቂለ ፡ ልቡና ፡ በነቂሐ ፡ ሕሊና ፡ ሲሰማ ፡ አይቶ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ሃይማኖት ፡ ያለው ፡ ነው ብሎ ፡ ተነሣና ፡ ቀጥ ፡ ብለህ ፡ በእግርህ ፡ ቁም ፡ አለው ። ወዲያው ፡ እንዳዘዘው ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆሞ ፡ በእግሩ ፡ ሔደ ። ሕዝቡ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ተአምራት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አማልክት ፡ ሰው ፡ መስለው ፡ ወደኛ ፡ ወረዱ ፡ ብለው ፡ አማልክት ፡ መስለዋቸው ፡ በርናባስን ፡ ድያ ፡ በሚባለው ፡ ጣዖት ፡ ስም ፡ ጠሩት ፤ ጳውሎስንም ፡ የትምህርቱ ፡ መደበኛ ፡ ርሱ ፡ ስለኾነ ፡ አክብረው ፡ በሚያዩት ፡ ሔርሜን ፡ በሚባለው ፡ ጣዖታቸው ፡ ስም ፡ ጠሩት ። በጠቅላላው ፡ ድያና ፡ ሔርሜን ፡ የሚባሉት ፡ አማልክት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ አሏቸው ። በሀገራቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለውን ፡ ድያስ ፡ የሚባለውን ፡ ካህን ፡ ጣዖት ፡ ጠርተው ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ ላም ፡ አቅርበው ፡ ለጣዖታቱ ፡ እንደሚሠዉላቸው ፡ ሊሠዉላቸው ፡ ወደዱ ።

ሐዋርያት ፡ ይህን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ተቈጡ ፤ ልብሳቸውን ፡ ቀደዱ ፤ እኛ ፡ እንደናንተ ፡ የምንሞት ፡ ሰዎች ፡ ነን ፡ እንጂ ፤ እናንተ ፡ እንደምትሉት ፡ አማልክት ፡ አደለንም ፤ የምናስተምራችሁም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ የግብዝነት ፡ ሥራ ፡ ትታችሁ ፡ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፤ እንድታመልኩ ፡ ነው ፡ አሏቸው ፡ ብሎ ፡ ስለአምላክነት ፡ ሥራ ፡ መኾኑን ፡ ለይቶ ፡ ይናገራል ።

እንግዲህ ፡ እኛ ፡ ቅዱሳንን ፡ የክርስቶስ ፡ ባሮች ፡ ብለን ፡ እንወዳቸዋለን ፡ እናከብራቸዋለን ፡ እንጂ ፡ አማልክት ፡ እንላቸዋለንን ? ።

በክርስቶስ ፡ ስም ፡ መከራ ፡ ተቀብለዋል ፡ የክርስቶስን ፡ አምላክነት ፡ መስክረዋል ፡ ብለን ፡ ዘአስተየ ፡ ጽሙዐ ፡ ማይ ፡ ቈሪረ ፡ በስመ ረድእየ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ በስማቸው ፡ ለተራበ ፡ እናበላለን ፡ ለተጠማ ፡ እናጠጣለን ፡ እንጂ ፡ አሕዛብ ፡ ለጣዖታቱ ፡ እንደሚሠዉት ፡ እንደሚያጤሱት ፡ ያለ ፡ ርኩስ ፡ መሥዋዕት ፡ እናቀርብላቸዋለንን ?



የጻድቃንን ፡ የሰማዕታትን ፡ ዕለተ ፡ ዕረፍት ፡ በምናከብርበት ፡ ቀንስ ፤ ቢኾን ፡ የተሠዋውን ፡ መሥዋዕት ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ ብለን ፡ አምነን ፡ እንቀበለዋለን ፡ እንጂ ፡ ያንዱ ፡ ጻድቅ ፡ ወይም ያንዱ ፡ ሰማዕት ፡ ሥጋ ፡ ደም ፡ ብለን ፡ እንቀበለዋለንን ፤ እስኪ ፡ እናንተ ፡ መስክሩ ። በመሥዋዕትና ፡ በዝክር ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ ልዩነት ፡ አስተውሉ ። መሥዋዕት ፡ ማለት ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ መኾኑን ፡ አምነን ፡ የምንቀበለው ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ ፍጡር ፡ አይቀላቀልበትም ።

ዝክር ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ትያጥሮን ፡ በሚባል ፡ ሀገር ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈራ ፡ እግዚአብሔር ፡ እዝነ ፡ ልቡናዋን ፡ ከፍቶላት ፡ ወንጌልን ፡ የምታደምጥ ፤ ስሟን ፡ ልድያ ፡ የሚሏት ፡ ሴት ፡ ነበረች ። በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ከነቤተ ፡ ሰብአቿ ፡ አምና ፡ ተጠመቀች ። እናንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ካደረጋችሁኝስ ፡ ከቤቴ ፡ ገብታችሁ ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ ቅመሱልኝ ፡ ብላ ፡ መላልሳ ፡ ማለደችን ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፲፬-፲፭ ።

የርሷ ፡ እንዳልተነቀፈበት ፡ እንደተወደደላት ፡ እናንተም ፡ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ ለተራበ ፡ ብታበሉ ፡ ለተጠማ ፡ ብታጠጡ ፡ ቅዱሳን ፡ በረድኤት ፡ መጥተው ፡ ቤታችሁን ፡ ይጐበኙላችኋል ፡ ርኅብኩ ፡ ወአብላዕክሙኒ ያሰኛችኋል ፡ እንጂ ፡ አይነቀፍባችሁም ፡ ስል ፡ አሳስባችኋለሁ ።

፲፫ እነርሱስ ፡ አልቦ ፡ ካልእ ፡ ስም ፡ ዘየሐዩ ፡ ለሰብእ ፡ በታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ዘእንበለ ፡ ስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ናዝራዊ ። የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፬ ፡ ፲-፲፪ ፡ ብለው ፡ ናቸው ፡ ያስተማሩ ። ስለምትለው ።

አንተ ፡ እኛን ፡ ሌላ ፡ ለማስመሰል ፡ ከልብህ ፡ እየፈጠርክ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ በማስመሰል ፡ ትጽፋለህ ፡ እንጂ ፡ እኛም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሌላ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ ብለን ፡ አናስተምርም ።

፲፬ ሰዎች ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ለሰዎች ፡ እንደማይረዱ ፡ እንደማያማልዱ ፡ አምላክ ፡ ሕሩ ፡ እምኔየ ፡ ርጉማን ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ዘለዓለም ፡ ብሎ ፡ በቁጣ ፡ ፈርዶ ፡ ካሰናበተም ፡ እንደማይለመን ፡ እበቀላለሁ ፡ ሰውም ፡ አይለምነኝም ፡ ይላል ፡ ኢሳ ፡ ፵፯ ፡ ፫ ፡ ስለምትለው

በ፳ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለአማላጅነት ፡ በጻፍኩልህ ፡ መልስ ፡ ተመልከት ።

፲፭ ደግሞም ፡ በነቢዩ ፡ በሕዝቅኤል ፡ አፍ ፡ ወነበበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤለኒ ፡ ኦወልደ ፡ እጓለ ፡ እመ ሕያው ፡ ምድር ፡ እመ ፡ ዐበሰት ፡ ሊተ ፡ ወስሕተት ፡ ወጌገየት ፡ አነሥእ ፡ እዴየ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወአጠፍዕ ፡ እምኔሃ ፡ ሰብአ ፡ ወእንስሳ ፡ ወለእመ ፤ ሀለዉ ፡ እሉ ፡ ፫ቱ ፡ እደው ፡ ማዕከላ ፡ ኖኅ ፡ ወኢዮብ ፡ ወዳንኤል ፡ ሕያው ፡ አነ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢያድኅኑ ፡ ደቂቆሙ ፡ ወአዋልዲሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ ያድኅኑ ፡ ነፍሶሙ ፡ በጽድቆሙ ፡ ይላል ፡ ሕዝ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪—፳ ፡ ስለምትለው ።

ኖኅ ፡ ኢዮብ ፡ ዳንኤል ፡ በመካከላቸው ፡ ቢኖሩ ፡ በመኖራቸው ፡ ብቻ ፡ አልምራቸውም ፡ አለ ፡ እንጂ ፤ ንስሐ ፡ ቢገቡና ፡ አማልዱን ፡ ቢሏቸው ፡ እነሱም ፡ ቢማልዱላቸው ፡ አልምራቸውም ፡ አላለም ። እኛም ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ በገር ፡ ካለ ፡ በኃጢአተኛ ፡ አይፈርድበትም ፡ አንልም ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፰ ኦልቦ ፡ አሜሃ ፡ ቤዛ ፡ ነፍስ ፡ ወኢተውላጠ ፡ ብእሲ ፡ ለብእሲቱ ፡ አብ ፡ በወልዱ ፡ ወእም ፡ በወለታ ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ይነሥእ ፡ ፍዳ ፡ ምግባሩ ፡ እንዳለ ፡ አትናቴዎስ ፡ ስለምትለው ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ቁ ፡ ፳፩ ፡ ገጽ ፡ ፻፶፩ና ፡ ፻፶፪ ፡ ተመልከት ።

፲፱ ዳዊት ፡ ልበ ፡ አምላክም ፡ ኢትትአመኑ ፡ በመላእክት ፡ ወኢ ፡ በእጓለ ፡ እመሕያው ፡ እለ ፡ ኢይክሉ ፡ አድኅኖ ፡ ስለምትለው ።

ገጽ ፡ ፲፰ ፡ ቁ ፡ ፯ ፡ ተመልከት ።

፳ ትወፅእ ፡ ነፍሶሙ ፡ ወይገብኡ ፡ ውስተ ፡ መሬቶሙ ፡ ውእተ ፡ ዓሚረ ፡ ይጠፍዕ ፡ ኵሉ ፡ ምክሮሙ ፡ መኑ ፡ ሰብእ ፡ ዘየሐዩ ፡ ወኢይሬእያ ፡ ለሞት ፡ ወመኑ ፡ ዘያድኅና ፡ ለነፍሱ ፡ እምእደ ፡ ሲኦል ፡ ይላል ፡ ስለምትለው ።

በቅዱሳን ፡ አማላጅነት ፡ ከሞት ፡ ነፍስ ፡ እንጂ ፡ ከሞት ፡ ሥጋ ፡ መዳን ፡ አለ ፡ ብለን ፡ አናስተምርም ። ይህም ፡ የጠቀስከው ፡ ሞት ፡ ሥጋ ፡ እንጂ ፡ ሞት ፡ ነፍስ ፡ አይደለም ፡ ሲኦልም ፡ መቃብር ፡ ነው ።

፳፩ ስለዚህ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከሲኦል ፡ የማያድኑ ፡ ከኾኑ ፡ የሌሎችን ፡ ነፍሳት ፡ እንዴት ፡ በመሰለ ፡ ዘዴ ፡ ሊያድኑ ፡ ይኾን ፡ ስለምትለው ።

፫ተኛውን ፡ ምዕራፍ ፡ ተመልከት ።

፳፪ ሸክላ ፡ ቢሰበር ፡ ያው ፡ ሠሪው ፡ ካልኾነ ፡ እንደርሱ ፡ ብዙ ፡ ሸክላዎች ፡ ተሰብስበው ፡ መልሰው ፡ ሊሠሩት ፡ ከቶ ፡ አይችሉም ። ስለምትለው ።

ሸክላ ፡ የገዛች ፡ ሴት ፡ የገዛችው ፡ ሸክላ ፡ ቢሰበርባት ፡ መልሳ ፡ ከሸክላ ፡ ሠሪይቱ ፡ ዘንድ ፡ ወስዳ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪይቱን ፡ ለምና ፡ እንድታሳድሰው ፡ እወቅ ።

፳፫ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለህ ፡ የምትተበትበጦ ፡ በ፫ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ የተናገርኩውን ፡ መመላለስ ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ መልሱን ፡ በ፫ስተኛው ፡ ምዕ ፡ ተመልከት ፡ ቢኾንም ፡ አንዳንድ ፡ እንግዳ ፡ እንግዳ ፡ ነገሮች ፡ ሲገኙ ፡ መልስ ፡ ሳልሰጥህ ፡ አላልፍም ።

፳፬ ፍጡራን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ስለሕያዋን ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ማሰብና ፡ መሥራት ፡ ስለማይችሉ ፡ ኤልያስ ፡ ሲያስረዳ ፡ ኤልሳዕን ፡ ካንተ ፡ ከተለየሁ ፡ ልሰጥህ ፡ ወይም ፡ ላደርግልህ ፡ ከቶ ፡ አይቻለኝምና ፡ አሁን ፡ ሳንለያይ ፡ የሚያስፈልግህን ፡ ንገረኝ ፡ አለው ፡ ብለህ ። ስለምትዋሸው ።

በነገሥት ፡ የተጻፈው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ሐለፉ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ይቤሎ ፡ ኤልያስ ፡ ለኤልሳዕ ፡ ሰአለኒ ፡ ዘትፈቅድ ፡ እግበር ፡ ለከ ፡ ዘእንበለ ፡ እዕርግ ፡ እምኅቤከ ። ወይቤሎ ፡ ኤልሳዕ ፡ ለይኩን ፡ ላዕሌየ ፡ ካዕበተ ፡ መንፈስ ፡ ዘዲቤከ ። ወይቤሎ ፡ ኤልያስ ፡ ዕፁብ ፡ ሰአልከ ። ወባሕቱ ፡ ለእመ ፡ ርኢከኒ ፡ እንዘ ፡ አዐርግ ፡ እምኅቤከ ፡ ወአመንከኒ ፡ ለይኩንከ ፡ ከማሁ ፤ ወእመሰ ፡ ርኢከኒ ፡ ወኢአመንከኒ ፡ አይኩንከ ። ወእንዘ ፡ የሐውሩ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ወይትናገሩ ፡ መጽአ ፡ ሠረገላ ፡ ዘእሳት ፡ ወቦአ ፡ ማዕከሌሆሙ ፡ ወዐርገ ፡ ኤልያስ ፡ ከመዝ ፡ በድልቅልቅ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ። ወርእዮ ፡ ኤልሳዕ ፡ ጸርሐ ፡ ወይቤ ፡ አባ ፡ ወአባ ፡ ኃይሎሙ ፡ ወጽንዖሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ወእምዝ ፤ ኢርእዮ ፡ እንከ ፡ ዳግመ ። ወመጠጠ ፡ አልባሲሁ ፡ ወረሰዮሙ ፡ ለክልኤ ፡ ወአውረደ [illegible]



ለቶ ፡ ወወረደ ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡ ለኤልሳዕ ፡ ወገብአ ፡ ኤልሳዕ ፡ ወቆመ ፡ ኀበ ፡ ድንጋገ ፡ ዮርዳኖስ ። ወነሥአ ፡ ሐሜለቶ ፡ ለኤልሳዕ ፡ እንተ ፡ ወረደት ፡ መልዕልተ ፡ ርእሱ ፡ ወዘበጠ ፡ በቲ ፡ ማየ ፡ ወዐበየ ፡ ተግኅሦ ፡ ወይቤ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ አምላከ ፡ ኤልያስ ፡ ወእፎ ፡ ወእምዝ ፡ ዘበጠ ፡ ለማይ ፡ ወተግኅሠ ፡ ወቆመ ፡ እንተ ፡ ለፌኒ ፡ ወእንተ ፡ ለፌኒ ፡ ወኀለፈ ኤልሳዕ ።

ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ሲሔዱ ፡ ኤልያስ ፡ ኤልሳዕን ፡ ካንተ ፡ ተለይቼ ፡ ሳላርግ ፡ የምትሻውን ፡ አደርግልህ ፡ ዘንድ ፡ ለምነኝ ፡ አለው ። ኤልሳዕም ፡ ባንተ ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕጽፍ ፡ ኾኖ ፡ ይደርብኝ ፡ አለው ። ኤልያስም ፡ ልጄ ፡ አስጨናቂ ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ለመንከኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሳርግ ፡ አይተህ ፡ ብታምን ፡ እንደ ፡ ቃልህ ፡ ይደርግልህ ፤ ባታምን ፡ ግን ፡ አይደረግልህ ፡ አለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኹለቱ ፡ እየተነጋገሩ ፡ ሲሔዱ ፡ የእሳት ፡ ሠረገላ ፡ መጥቶ ፡ በመካከላቸው ፡ ገባና ፡ ለያያቸው ። ኤልያስ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኀይልና ፡ ክብር ፡ ወደሰማይ ፡ ዐረገ ። ኤልሳዕም ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ የእስራኤል ፡ አንባቸው ፡ መጠጊያቸው ፤ ጋሻቸው ፤ አባቴ ፡ አባቴ ፡ እያለ ፡ ይጮህ ፡ ጀመረ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ኹለተኛ ፡ አላየውም ። ኤልያስም ፡ ከርሱ ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ መጠምጠሚያውን ፡ ከሦስት ፡ አጥፎ ፡ ቀዶ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ አስቀርቶ ኹለቱን ፡ እጅ ፡ በኤልሳዕ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጣለለት ። ኤልሳዕም ፡ ተመልሶ ፡ ከፈሳሹ ፡ ዳር ፡ ቆመና ፡ ኤልያስ ፡ የጣለለትን ፡ መጠምጠሚያ ፡ አመሳቅሎ ፡ ወኀውን ፡ መታው ፡ አልተከፈለም ። ዳግመኛ ፡ እንዴት ፤ የኤልያስ ፡ አምላኩ ፡ ወደየት ፡ ነው ፡ ብሎ መልሶ ፡ ቢመታው ፡ ወዲህና ፡ ወዲህ ፡ ተከፈለለትና ፡ አልፎ ፡ ሔደ ፡ ይላል ።

እንግዲህ ፡ ኤልያስ ፡ ከኤልሳዕ ፡ ተለይቶ ፡ ካረገ ፡ በኋላ ፤ ላይኑ ፡ ከተሰወረው ፡ በኋላ ፡ መጠምጠሚያውን ፡ ቀዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ከጣለለት ፤ ኹለተኛም ፡ ወኀው ፡ የኤልያስን ፡ ስም ፡ ሳይጠራ ፡ ቢመታው ፡ አልከፈልልለት ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ የኤልያስን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ ቢመታው ፡ ከተከፈለለት ፤ ካንተ ፡ ከተለየሁ ፡ ላደርግልህ ፡ አልችልም ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ መዋሸት ፤ መጽሐፍ ፡ ቅዱስንስ ፡ ማስዋሸት ፡ ይገባልን ፡ አይገባም ።

፳፭ ። ከዚህ ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ የሚከተለውን ፡ የሊበን ፡ ውልታው ፡ ዐጋሚ ፡ ግጥም ፡ ብንጠቅሰው ፡ ይስማማል ። ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ በሞት ፡ ለደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ በ፰ ፡ ወር ፡ ቀድመው ፡ ስለነበር ። (እንጉርጉሮ) ።

ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ አጀቡ ፡ ቢያንሳቸው ።
ጌታየን ፡ አስጠሩት ፡ በሰምንት ፡ ወራቸው ።
ምን ፡ ይረባኝ ፡ ብለው ፡ በሰማይ ፡ አሽከር ።
መገናኘት ፡ የለ ፡ አይረዳ ፡ ምክር ። እያለ ፡ እውነት ፡ የኾነ ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ በጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ አንብበን ፡ ነበረ ። ስለምትለው ።

ሐሰት ፡ ነገር ፡ ዘወትር ፡ እንደ ፡ ዕንቧይ ፡ ካብ ፡ ሲናድ ፡ ከሜኖር ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ጸንቶ ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ፤ አየኸውን ፤ አንተ ፡ የተነሣህ [illegible] ፡ ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ ሰዎች ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቢጠሯቸው ፡ አይሰሙም ፡ አያውቁም ፡ ማለት ፡ ነበረ ፤ ለዚህ ፡ ማስረጃ ፡ የጠቀስ ከው ፡ ጥቅስ ፡ ግን ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ በመቃብር ፡ ከማወቃቸውም ፡ በላይ ፡ አጀብ ፡ አነሰኝ ፡ ብለው ፡ ተቈርቁረው ፡ አሽከር ፡ ልከው ፡ ደጃች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴን ፡ እንዳስጠሯቸው ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ እውነት ፡ የኾነ ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ በጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ አንብበናል ፡ ብለህ ፡ በጽሑፍ ፡ አረጋግጠሃል ።

ሊበን ፡ ወልታ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ተቀምጠው ፡ ባላወቁት ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ይረ ባኛ ፡ ብለው ፡ በሰማይ ፡ አሽከር ። መገናኘት ፡ የለ ፡ አይረዳ ፡ ምክር ፡ ብለው ፡ እንዳሸማጠጡ ፡ ያስረዳል ። ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ከግብሩ ፡ ተገኝተው ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ ሊበን ። ወልታ ፡ ከዚህ ፡ ኸነው ፡ ባሸማጠጡት ፡ ሽሙጥ ፡ ሐሰት ፡ ልን ለው ፡ ይገባልን ፡ አይገባም ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ በሰማይ ፡ የሚላክ ፡ አሽከር ፡ ካለ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉትም ፡ ሰዎች ፡ ንግሥት ፡ ጠርተውሃል ፡ ሲሉት ፡ ደንግጠ ፡ የሚሔድ ፡ ከኾነ ፤ ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ ብንጠራቸው ፡ አይሰሙንም ፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ፋንታ ፡ የላቸውም ፡ እያልክ ፡ የምትቀባጥረው ፡ ኹሉ ፡ ፌራሽ ፡ ነገር ፡ እንደ ኾነ ፡ አስተውል ። ሌላውም ፡ የምትናገረው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ገብቶ ፡ ሲመረምሩት ፡ እንደዚህ ፡ ፌራሽ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ቀዋሚ ፡ ነገር ፡ የለበትም ። እኔ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ሐተታ ፡ ማተቴ ፡ የነገርህን ፡ ፌራሽነት ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመቃ ብር ፡ እገሌን ፡ ጥሩት ፡ ብሎ ፡ ማዘዝና ፡ መታዘዝ ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ ማመኔ ፡ አይደ ለም ፡ የሕያዋንና ፡ የምውታንን ፡ ነገር ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፲፫ተኛ ፡ ቍጥር ፡ በሰፊው ፡ ተጽፎልሃናል ፡ ተመልከት ።

፳፯ ። ፍጡራን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ለሕያዋን ፡ እንደማይረዱና ፡ እንደማይጠቅሙም ፡ ሳኦል ፡ ንጉሠ ፡ እስራኤል ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ ተከበና ፡ ተጨንቆ ፡ ሳለ ፡ በሚርተኞችና ፡ ጠንቋዮች ፡ መንፈስ ፡ ለም ውቱ ፡ ለሳሙኤል ፡ አስቀስቅሶ ፡ ጠላቶች ፡ ሊወጉኝ ፡ ተነሥተውብኛልና ፡ የምሠራውን ፡ ታስታውቀኝና ፡ ትረዳኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ ቢለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላትህ ፡ ከኾነ ፡ ስለምን ፡ ለኔ ፡ ትጠይቀኛለህ ፡ እነሆ እግዚአብሔር ፡ ለጠላቶችህ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጥሃልና ፡ አንተና ፡ ልጆችህም ፡ ትሰየፋላችሁ ፡ ብሎ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ እንረዳዋለን ፡ ሳሙ ፡ ፳፰ ፡ ፩ ' ፲፱ ፴፩ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ። ስለምትለው ።

በዚህም ፡ አጠቃቀስህ ፡ ሳሙኤል ፡ ያች ፡ ዕንዶራዊት ፡ ጠርታው ፡ ተነሥቶ ፡ ሳኦል ፡ ለጠየቀው ፡ መልስ ፡ ከሰጠ ፤ ብንጠራቸው ፡ አይሰሙንም ፡ የምትለው ፡ ፈረ ሰብህ ።

ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ ትረዳኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ አለው ፡ ማለትን ፡ አንተ ፡ ለማስመሰል ፡ ከልቡናህ ፡ ፈጥረህ ፡ ጨምረኸዋል ፡ እንጂ ፡ በመጽሐፍ ፡ አይገኝም ፡ በግእዙ ፡ ወይቤሎ ፡ ሳኦል ፡ እስመ ፡ ተመንደብኩ ፡ ጥቀ ፡ እስመ ፡ ፀብዑኒ ፡ ኢሎፍሊ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ኀደገኒ ፡ ወኢያውሥአኒ ፡ ዳግመ ፡ እንከ ፡ ወኢበእደ ፡ ነቢያት ፡ ወኢበላዕለ ፡ ሐላምያን ፡ ወይእዜኒ ፡ ጸዋዕኩከ ፡ ከመ ፡ ታይድዐኒ ፡ ዘከመ ፡ እገብር ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ከመ ፡ ትርድአኒ ፡ አይልም ።

(አንተ ፡ የምትጠቅሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስም) ፡ ሳኦልም ፡ አለ ፡ እጅግ ፡ ተጨን ቅሁ ፡ ፍልስጥዔማውያን ፡ ይወጉኛልና ? እግዚአብሔርም ፡ ከኔ ፡ ራቀ ፡ በነቢያትም ፡



ቃል ፡ በሕልምም ፡ ሊመልስልኝ ፡ አልወደደም ፡ የማደርገውን ፡ ታስታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠራሁህ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ትረዳኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ፡ አለው ፡ አይልም ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፳፰ ፡ ፲፭ ።

ገና ፡ ለጠማማው ፡ አሳቤ ፡ ይረዳኛል ፡ ብሎ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነገር ፡ ጽፎ ፡ ማሳ ሳት ፡ አይገባም ።

እንግዲህ ፡ ሳሙኤል ፡ ከመቃብር ፡ ተነሥቶ ፡ ሳኦል ፡ ለጠየቀው ፡ ነገር ፡ እው ነተኛ ፡ መልስ ፡ ከሰጠው ፤ ያውም ፡ ከተደረገ ፡ ከተፈጸመ ፡ ቅዱሳን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ሲጠሯቸው ፡ እንዲሰሙ ፡ የለመኗቸውንም ፡ እንዲፈጽሙ ፡ እወቅ ።

፳፯ ወዳጆቹ ፡ ሆይ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ከመልበሱ ፡ በፊትም ፡ ቢኾን ፡ አዳማውያንን ፡ ተልኮ ፡ ለመ ርዳት ፡ የተመደበው ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ በሚከተለው ፡ ስሙ ፡ እንረዳዋለን ፡ መልአክ ፡ ገጸ ፡ እደ ፡ መዝራዕቱ ፤ ኀይሉ ፡ ወጥበቡ ፤ መልአከ ፤ ምክሩ ፤ የዓለም ፡ ካህን ፤ መልአክ ፡ ኪዳኑ ፤ ጻድቅ ባርያው ፡ እያሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ይመሰክሩለታል ። አባታችን ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድም ፡ ሚካኤል ፡ መኑ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብርኤል ፡ ብሂል ፡ ኸኖ ፡ ያወጣቸው ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በባቢሎን ፡ ተማርከው ፡ ሲኖሩም ፡ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ አትላቸውምን ፡ ብሎ ፡ አማልዶ ፡ ያወጣቸው ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ጥቅሶቹን ፡ አስተውለህ ፡ መርምርና ፡ አማላጅነት ፡ የክርስቶስ ፡ የብቻው ፡ ሥራ ፡ መኾኑን ፡ የተረዳሃው ፡ ኹን ። ዘካ ፡ ፩ ፡ ፯—፲፯ ። ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፯—፲፩ ። ዘፀ ፡ ፳፫ ፡ ፳ ። ፴፪ ፡ ፳—፲፫ ። መሳ ፡ ፪ ፡ ፩—፬ ። ኢዮ ፡ ፳፫ ፡ ፳፫ ። ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፲፯—፲፱ ። ዘፍ ፡ ፳፩ ፡ ፲፯—፳ ። ፳፪ ፡ ፲፩ ። ስለምትለው ።

አስቀድመን ፡ ጥቅሶችን ፡ በየተራቸው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እንመርምር ።

(ሀ) ዘካ ፡ ፩ ፡ ፯ | ፲፯ ። የጠቀስከው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፤ አቤቱ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ እስከመቼ ፡ የየሩሳሌምንና ፡ የይሁዳን ፡ ከተሞች ፡ እሊህን ፡ ፸ ዓመት ፡ የተቈጣሃቸውን ፡ ይቅር ፡ አትላቸውምን ፡ ብሎ ፡ ማለደ ። እግዚአብሔርም ፡ ከኔ ፡ ጋር ለሚነጋገረው ፡ መልአክ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ መለሰለት ። ከኔ ፡ ጋር ፡ የሚነጋገረውም ፡ መልአክ ። የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ በኢየሩሳ ሌምና ፡ በጽዮን ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ብቈጣ ፡ አሕዛብ ፡ በክፋት ፡ ላይ ፡ ክፋት ፡ ጨምረ ዋልና ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ የምቈጣ ነኝ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ በምሕረት ፡ እመለሳለሁ ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ አሰምተህ ፡ ተናገር ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ የመልአኩን ፡ አማ ላጅነት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተማላጅነት ፡ የራሱን ፡ ተላኪነት ፡ (ነቢይነት) ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስን ፡ መልአክ ፡ ወይም ፡ አማላጅ ፡ ነው ፡ አይልም ።

(ለ) ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፯—፲፩ ። የጠቀስከውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ ዐጋርን ወደ ሹር ፡ በምትወስደው ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ የውኀ ፡ ምንጭ ፡ አግኝቶ ፡ የሣራ ፡ ባሪያ ፡ ዐጋር ፤ ከወዴት ፡ መጣሽ ፤ ወዴትስ ፡ ትሔጃለሽ ፡ ቢላት ፤ እኔ ፡ ከእመቤቴ ፡ ከሣራ ፡ ፊት ፡ ኰብልያለሁ ፡ አለችው ። የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛም ፡ ወደእመቤትሽ ፡ ተመ ለሺ ፡ ከእጅዋ ፡ በታችም ፡ ተገዢ ፤ ዘርሺን ፡ እጅግ ፡ አበዛለሁ ፤ ከብዛቱም ፡ የተነሣ ፡ አይቈጠርም ፡ አላት ይላል ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የተነጋገራት ፡ መላክተኛ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ አይልም ።

(ሐ) ዘፀአ ፡ ፳፫ ፡ ፳ ። የጠቀስከውም ፤ በመንገድ ፡ ይጠብቅህ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ወዳዘጋ ጀኋትም ፡ ስፍራ ፡ ያገባህ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ መልአኬን ፡ በፊትህ ፡ እሰዳለሁ ፡ ይላል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህም ፡ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ሲወጡ ፡ ፊነሠ ፡ መልአከ ፡ ወእድኅኖሙ ፡ እንዲል ፡ መልአክ ፡ ይመራቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ መልአኪየ ፡ ያለው ፡ ክርስቶስ ፡ እንደኾነ ፡ አያስረዳንም ።

(መ) ዘጸ ፡ ፴ ፡ ፲፫ትም ። የጠቀስከው ፡ እስራኤል ፡ በኮሬብ ፡ ጣዖት ፡ በማቆማቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቈጥቶ ፡ ላጥፋቸው ፡ አንተንም ፡ በሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ልሹምህ ፡ ቢለው ፡ ሙሴ ፡ ለምኖ ፡ አማልዶ ፡ እንዳዳናቸው ፡ ይናገራል እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳማለደ ፡ አይናገርም ።

(ሠ) መሳ ፡ ፪ ፡ ፩—፱ት ። የጠቀስከውም ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገልገላ ፡ ወደ ፡ ቀላዉትሞና ፡ ወጥቶ ፡ እኔ ፡ ከምስር ፡ አውጥቼ ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ ብዬ ፡ ላባቶቻችሁ ፡ ወደማልኩላቸው ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ አገባኋችሁ ። እናንተም ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ኪዳን ፡ አታድርጉ ፤ ጣዖታቸውንም ፡ ስበሩ ፡ ምሥዋዓቸውንም ፡ አፍርሱ ፡ ብያችሁ ፡ ነበረ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ነገሬን ፡ አልሰማችሁም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ ተላከ ፡ የሚል ፡ የለም ።

(ረ) ኢዮ ፡ ፳፫ ፡ ፳፫ ። የጠቀስከውም ፡ ከልብህ ፡ አንቅተህ ፡ ፳፫ ፡ ቊጥርን ፡ ብቻ ፡ ጽፈሃል ፡ እንጂ ፡ በኢዮብ ፡ ፳፫ስተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በ፲፯ ፡ ቊጥር ፡ ይፈጸማል ፡ እንጂ ፡ እስከ ፡ ፳፫ ፡ የሚደርስ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የለውም ።

(ሰ) ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፲፯—፲፱ ። እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ላከኝ ፡ መንፈሱም ፤ ያዳነህ ፡ የተበጀህ ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚረባህን ፡ ነገር ፡ የማስተምርህ ፡ በምትሔድባት ፡ መንገድ ፡ የምመራህ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ ነኝ ፤ ትእዛዜን ፡ ብትሰማ ፡ ሰላምህ ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ጽድቅህም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ሞገድ ፡ በኾነ ፡ ነበር ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ መልአክ ፡ እንደኾነ ፡ አይነግረንም ።

(ቀ) ዘፍ ፡ ፳፩ ፡ ፲፯—፳ ። የጠቀስከውም ፡ እግዚአብሔር ፡ የብላቴናውን ፡ ድምጽ ፡ ሰማ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ ዐጋርን ፤ ዐጋር ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ኾንሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የብላቴናውን ፡ ድምጽ ፡ ሰምቷልና ፡ አትፍሪ ፡ ተነሺ ፡ ብላቴናውን ፡ እጁን ፡ ደግፊሽ ፡ ውሰጂው ፡ ለታላቅ ፡ ወገን ፡ አደርገዋለሁና ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ መልአክ እንደኾነ ፡ አይናገርም ።

(በ) ፳፪ ፡ ፲፩ ፡ የጠቀስከውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። ርሱም ፡ እነሆ ፡ አለሁ ፡ አለ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ መልአክ ፤ ወይም ፡ አማላጅ ፡ እንደኾነ ፡ አይናገርም ። እንግዲህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ኦእግዚኦ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ ይጸልይ ፡ ነበረ ። ጻድቅ ፡ ባሪያው ፡ እያሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ይመሰክራሉ ፡ ማለትን ፡ ከምን ፡ አግኝተህ ፡ ተናገርከው ፡ ይኾን ።

(ተ) ደግሞስ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡ የሚባሉ ፡ መላእክት ፡ በፍጹም ፡ እንደሌሉ ፡ አድርገህ ፡ ሚካኤልም ፡ ገብርኤልም ፡ የሚባል ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ የተናገርክ ፡ ከምን ፡ አግኝተህ ፡ ነው ። እነሆ ...



ሎን ፡ ሲጸልይ ፡ በየዐሙ ፡ ራእይ ፡ ጸሎቴን ፡ ስናገር ፡ ያ ፡ ቀድሞ ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ያየሁት ፡ ገብርኤል ፡ መጣና ፡ ተናገረኝ ፡ ብሎ ፡ ገብርኤልን ።

የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ተቋቋመኝ ፡ እነሆ ፡ ሚካኤል ፡ ከፊተኞች ፡ አለቆች ፡ አንዱ ፡ እኔን ፡ ለመርዳት ፡ መጣ ። ከለቃችሁ ፡ ከሚካኤል ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ማንም ፡ የሚረዳኝ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ የተፈጠሩ ፡ ፍጡራን ፤ ማዓርጋቸውም ፡ ሊቃነ ፡ መላእክት ፤ ግብራቸውም ፡ ሰውን ፡ ለመርዳት ፡ የሚላኩ ፡ መላክተኞች ፡ ለፍጡራንም ፡ ስዒን ፡ ገንዘባቸው ፡ ስለኾነ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚረዳዱ ፡ መኾናቸውን ።

ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩት ፡ ትንቢት ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ የሚፈጸም ፡ የዓለሙ ፡ መድኀኒት ፡ መኾኑን ፤ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትታነጻለች ። ከ፷፪ ፡ ሱባኤ ፡ በኋላ ፡ መሲሕ ፡ ክርስቶስ ፡ ለራሱ ፡ ሳይኾን ፡ ስለምእመናን ፡ ተወግቶ ፡ ይሞታል ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ ብሎ ፡ ለይቶ ፡ ለይቶ ፡ ተናግሯል ፡ ዳን ፡ ፱ ፡ ፳፩ ። ፲ ፡ ፲፫—፳፩ ።

ይልቁንም ፡ ኄኖክ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የመላእክትን ፡ ማዓርጋቸውን ፡ ሥራቸውን ፡ ለይቶ ፡ ለይቶ ፡ ጽፏል ። ያሬድም ፡ ሚካኤል ፡ ብሂል ፡ ዕፁብ ፡ ነገር ፡ ገብርኤል ፡ ብሂል ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለትን ፡ ከኄኖክ ፡ አግኝቶ ፡ ነው ፡ የተናገረው ። እንግዲህ ፡ ነቢያትን ፡ ልታስተባብል ፡ ትችላለህን ።

ከክህደትህ ፡ ከስሕተትህ ፡ ኹሉ ፡ ይህ ፡ ጸና ፤ ክርስቶስ ፡ ክሶ ፡ ሰውን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አስታረቀ ፡ ብለን ፡ የምናምን ፡ በሰውነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመለኮቱ ፡ አይደለም ። በመለኮቱ ፡ ጻድቅ ፡ ባሪያው ፡ ተባለ ፤ ኦእግዚኦ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ ብሎ ፡ ለመነ ፡ የምትለው ፡ ከኾነ ፤ ፍጡር ፡ በመለኮቱ ፡ ማለትህ ፡ አይደለምን ። በጌታና ፡ በባሪያ ፤ በለማኝና ፡ በተለማኝ ፡ በማላጅና ፡ በተማላጅ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መበላለጥ ፡ አታውቅምን ። አርዮስስ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ተናግሯል ፤ ፫፻ ፡ አርዮስ ፡ ውጉዝ ፡ በሰማይ ፡ ወበምድር ፡ ብለው ፡ የለዩት ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ ፍጡር ፡ በመለኮቱ ፡ ቢል ፡ አይደለምን ። እንዲህማ ፡ ከኾነ ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አነ ፡ ወአብ ፡ ፩ ፡ ንሕነ ፡ ያለው ፡ ዮሐ ፲፩ ፱ ፳፩ ።

ሐዋርያትም ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ሠራዊት ፡ ወሢመታት ፡ ወሥልጣናት ፡ ዘሠምረ ፡ ይኩን ፡ ሰብአ ፡ በደኀሪ ፡ መዋዕል ፡ ያሉት ፡ (አመክንዮ ።) ፫፻ትም ፡ ወነአምን ፡ በ፩ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋሕድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ ብለው ፡ ያስተማሩን ፡ ታበለ ፡ ማለት ፡ ነዋ ።

እናንተ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ አደራችሁን ፡ ከዚህ ፡ መርዝ ፡ አጥብቃችሁ ፡ ሽሹ ።

፳፫ ፡ ይልቁንስ ፡ ጳውሎስ ፡ ብርሃና ፡ ለቤተ ፡ ክስቲያን ፤ ወባሕቱ ፡ አንትሙሰ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ ለእመ ፡ መሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዘ ፡ መሀርናክሙ ፡ ንሕነ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡ የሐዋርያት ፡ ... መጽሐፍ ፡ ትምህርትና ፡ ሃይማኖት ፡ እንኳንና ፡ ሰዎች ፡ መላእክትም ፡ ቢኾኑ ፡ ቢና

www.ethiopianorthodox.org

ገሩና ፡ ቢያስተምሩ ፡ እንዳናምናቸውና ፡ እንዳንቀበላቸው ፡ ወግዞናል ፡ ገላ ፡ ፩ ፡ ፮—፲ ፡ ስለዚህ ፡ ያባታችን ፡ የጳውሎስ ፡ ግዝት ፡ ሰምተን ፡ ትምህርቱ ፡ ትእዛዙ ፡ ሃይማኖቱ ፡ መጻሕፍቱ ፡ አይተንና ፡ መርምረን ፡ ኢታምጽኡ ፡ ካልአ ፡ ነኪረ ፡ ትምህርተ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘንን ፡ የኑዛዜ ፡ ቃሉ ፡ ማጽናት ፡ ይገባናል ። ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፱ ።
ስለምትለው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ የጻፈበት ፡ ምክንያት ፡ ገላትያ ፡ ገብቶ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ መኾኑን ፡ ቢነግራቸው ፡ የገላትያ ፡ ሰዎች ፡ አመኑ ፡ ተጠመቁ ። ትምርት ፡ ወዳልደረሰበት ፡ ለማዳረስ ፡ ወጥቶ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ ያሉ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ገብተው ፤ ጳውሎስ ፡ የሚያስተምርለት ፡ ክርስቶስ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ትምርቱን ፡ የተማረ ፡ ከዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነውና ፡ ሊቀበሉት ፡ አይገባም ፡ ቢሏቸው ፡ የገላትያ ፡ ሰዎች ፡ እውነት ፡ መስሏቸው ፤ ከወንጌል ፡ ወደ ፡ ኦሪት ፡ ተመለሱ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ አነክረክሙ ፡ እሮ ፡ ከመዝ ፡ ያፈልሱክሙ ፡ እምሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘጸውዐክሙ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ትምህርት ፡ ዘኢኮነ ፡ ህልወ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘየሐውኩክሙ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ይዕልዉ ፡ ትምህርቶ ፡ ለክርስቶስ ።

በቸርነቱ ፡ የጠራችሁ ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ኾነ ፡ ከማመን ፡ ወጥታችሁ ፡ የክርስቶስን ፡ አምላክነት ፡ ሊለውጡ ፡ ወደው ፡ የሚያውኳችሁ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ በመጽሐፍ ፡ ሳይኖር ፡ ከልባቸው ፡ ፈጥረው ፡ ወደ ሚናገሩት ፡ ክርስቶስ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ ወደማለት ፡ ጨልጠው ፡ ገርኝተው ፡ እንደምን ፡ ወሰዷችሁ ፡ ብዬ ፡ አደንቅባችኋለሁ ።

ወባሕቱ ፡ አንትሙ ፡ ዐሠረ ፡ ዚአነ ፡ ትልዉ ፡ አንትሙሰ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ ለእመ ፡ መሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዝ ፡ መሀርናክሙ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

እናንተስ ፤ እኛ ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ያስተማርናችሁን ፡ ያዙ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ካስተማርነው ፡ ትምርት ፡ ወጥቶ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ ቢያስተምራችሁ ፡ አትቀበሉ ፤ ያስተማራችሁም ፡ የተለየ ፡ ይኹን ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ ለማለት ፡ አልጻፈውም ።

እኛም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ባስተማረን ፡ ጸንተን ፡ ክርስቶስን ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋህድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ፀመለኮቱ ፡ ብለን ፡ እናምንበታለን ፡ እንጂ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቃል ፡ ወጥተን ፡ በመለኮቱ ፡ ያማልዳል ፡ አንለውም ።

አንተ ፡ ግን ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቃል ፡ ወጥተህ ፡ ከልብህ ፡ ፈጥረህ ፡ ሚካኤል ፡ ገብርኤል ፡ የሚባል ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ በመለኮቱ ፡ ኦእግዚኦ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ ያማልድ ፡ ነበረ ፡ እያልክ ፡ ትጽፋለህ ።

እንግዲህ ፡ ከጳውሎስ ፡ ቃል ፡ የወጣኸው ፡ አንተ ፡ በእኛ ፡ ባልወጣኖች ፡ ላይ ፡ ልትጠቅሰው ፡ ይገባልን ፡ አይገባም ፡ ይህ ፡ ጥፋት ፡ የራስህ ፡ ነው ። ሳሙ ፡ ካል ፡ ፲፱ ፡ ፯ ። መዝ ፡ ፹፩ ፡ ፲፩ ።



ምዕራፍ ፡ ፰ ።

ስለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ።

፩ ፡ ወዳጄ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነገርኩህ ፡ አሁንም ፡ እለ ፡ ክርሥሙ ፡ ያመልኩ ፡ ብለህ ፡ የጻፍከው ፡ ያነኑ ፡ መልስ ፡ የተሰጠበትን ፡ ቅዱሳን ፡ አያማልዱም ፡ ማለትን ፡ ሲኾን ፡ ተጨማሪ ፡ አድርገህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጻድቃን ፡ ጻድቀው ፡ ሊያጸድቋችሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብቶላቸዋል ፡ ይላሉ ፡ ብለህ ፡ ሥር ፡ ነገሩን ፡ ተጨማሪ ፡ አድርገህ ፡ ተናግረኸዋል ።

ለሌላው ፡ ንግግርህ ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ መልስ ፡ የተሰጠበት ፡ ስለኾነ ፡ አሁን ፡ የምንነጋገር ፡ ስለቃል ፡ ኪዳን ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ።

እግዚአብሔር ፡ ለጻድቃን ፡ ጻድቀው ፡ ሊያጸድቋችሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብቶላቸዋል ፡ ይላሉ ፡ ብለህ ፡ ነቅፈህ ፡ ለዚሁ ፡ ምስክር ፡ ሕዝ ፡ ፲፫ ፡ ፩-፳፫ ። ፴፬ ፡ ፩—፴፩ ። ሚክ ፡ ፪ ፡ ፰—፲፩ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፵ ። ስለጠቀስከው ።

(ሀ) ሕዝ ፡ ፲፫ ፡ ፩—፳፫ ፡ የጠቀስከው ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ ነቢያተ ፡ ጽድቅን ፡ መምህራን ፡ ሕግን ፡ የሚነቅፉ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ ሲነቅፍ ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቅዱሳንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሲነቅፍ ፡ የጻፈው ፡ አደለም ።

አንተ ፡ ግን ፡ በ፲፱ ፡ ቍጥር ፡ ወአርኰስክናኒ ፡ በኀበ ፡ ሕዝብየ ፡ በሐፍሰ ፡ ሰገም ፡ ወበፍተ ፡ ኅብስት ።

በጭብጥ ፡ ገብስ ፡ በቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ በወገኖቼ ፡ ዘንድ ፡ አስነቀፋችሁኝ ፡ የሚለውን ፡ ንባብ ፤ ጥሬ ፡ ቆልተው ፡ ወኀ ፡ ቀድተው ፡ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ ለድኆች ፡ ስለሚሰጡ ፡ ነቀፋ ፡ የተናገረው ፡ አስመስለህ ፡ ገምተኸዋል ።

ላንተ ፡ መስሎህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አደለም ። ሕዝቅኤልስ ፡ እንደ ፡ ጨሌ ፡ ጣይ ፡ ገብሱን ፡ ቄንጥራችሁ ፡ እንጀራውን ፡ ፈርፍራችሁ ፡ በምታሟርቱት ፡ ሟርት ፡ አስነቀፋችሁኝ ፡ ሲል ፡ የጻፈው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የሚፈጸም ፡ አንተ ፡ ሐተታ ፡ መናፍስት ፡ ብለህ ፡ የጻፍከው ፡ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍን ፡ በሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቅዱሳንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ አደለም ።

ይህ ፡ እኛ ፡ ጥሬ ፡ ቆልታችሁ ፡ ወኀ ፡ ቀድታችሁ ፡ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ ለተራበ ፡ ለተጠማ ፡ ስጡ ፡ የምንለውስ ፤ ዘአስተየ ፡ ጽዋዐ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ፡ ያለው ፡ ትእዛዝ ፡ የሚፈጸምበት ፡ መንገድ ፡ ነው ። ይህነንም ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ይገምተው ።

ይልቁንም ፡ ባሥረኛው ፡ ቍጥር ፡ ወውእቱ ፡ የሐንጽ ፡ ዐረፍተ ፡ ወእሙንቱ ፡ ይመርግዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ሐሠር ።

አንዱ ፡ ግድግዳ ፡ ይገደግዳል ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ገለባ ፡ ጭድ ፡ የሌለው ፡ ጭቃ ፡ ይለስኑታል ፤ ዝናም ፡ በዘነመ ፡ ጊዜ ፡ ያለገለባ ፡ ያለጭድ ፡ የተለሰነው ፡ ጭቃ ፡ ይወድቃል ፡ በማለቱ ፡ በጸጋው ፡ ድኛለሁ ፡ ምግባር ፡ አያሻም ፡ የምትል ፡ አንተን ፡ ነክቶሃል ።

www.ethiopianorthodox.org

እንደምን ፡ ብትለኝ ፡ ነገሩ ፡ የምሳሌ ፡ አነጋገር ፡ መኾኑ ፡ የማይካድ ፡ ነው ። ግድግዳ ፡ የተባለ ፡ ሃይማኖት ፤ ምርግ ፡ የተባለ ፡ ምግባር ፤ ምርጉን ፡ የሚያጸና ፡ ገለባ ፡ የተባለውም ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ምጽዋት ፡ ነው ። ያለገለባ ፡ የተመረገ ፡ ጭቃ ፡ ዝናም ፡ ሲመታው ፡ ይወድቃል ፡ (ማለት ፡) ያለምግባር የተያዘ ፡ ሃይማኖት ፡ ርኀብኩ ፡ ወኢያብላዕክሙኒ ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሊያድን ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

(ለ) ፴፪ ፡ ፳—፴፩ ፡ የጠቀስከውም ፡ ነገሥት ፡ እስራኤል ፡ ከሕዝቡ ፡ ላይ ፡ የሚገባቸውን ፡ ግብር ፡ እየተቀበሉ ፡ በሕግ ፡ ስላልጠበቋቸው ፡ ነገሥታቱን ፡ በኖሎት ፡ ሕዝቡን ፡ በአባግዕ ፡ መስሎ ፡ የተናገረው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቅዱሳንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሲነቅፍ ፡ የጻፈው ፡ አደለም ። ይኸውም ፡ ወአቀውም ፡ ሎሙ ፡ ፩ደ ፡ ኖላዌ ፡ ወይርዕዮሙ ፡ ዳዊትሃ ፡ ገብርየ ፡ በማለቱ ፡ ይታወቃል ።

ሐዋርያት ፡ ደግሞ ፡ ይህነን ፡ ንባብ ፡ ስለ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ አድርገው ፡ በዲዲስቅልያ ፡ ባራተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ጠቅሰውታል ። ቢጠቅሱትም ፡ ዐሥራቱን ፡ በኵራቱን ፡ ተቀብለው ፡ ዝክሩን ፡ ተዝካሩን ፡ በልተው ፡ ሕዝቡን ፡ የማያስተምሩ ፤ ስለሕዝቡ ፡ የማይጸልዩ ፡ ግብዞች ፡ መምህራንን ፡ ሲነቅፉ ፡ ሲገሥጹ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቅዱሳንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሲነቅፉ ፡ አደለም ።

(ሐ) ሚልክ ፡ ፪ ፡ ፰—፲፩ ፡ የጠቀስከው ፡ እላንት ፡ ከመንገድ ፡ ወጣችሁ ፡ በሕግም ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አሰነካከላችሁ ፡ የሌዊን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፈረሳችሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ ብሎ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ተዋዋለ ፡ እንጂ ፡ ለይቶ ፡ መርጦ ፡ ከሙሴ ፡ ከአሮን ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አልገባም ፡ የምትለውን ፡ ተቃውሞ ፤ የቅዱሳንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከማጽናት ፡ በቀር ፡ አልነቀፈም ። በተለየ ፡ ከሌዊ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መጋባቱን ፡ አረጋግጧል ።

ባሥረኛውም ፡ ቍ ፡ ለኹላችን ፡ አንድ ፡ አባት ፡ አይደለውምን ፤ አንድ ፡ አምላክስ ፡ አልፈጠረንምን ፡ ያባቶቻችንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማርከስ ፡ ስለምን ፡ ከኛ ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፤ ወንድሙን ፡ በደለ ፡ ብሎ ፡ ያባቶቻችንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አክብሮ ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የላቸውም ፡ አይልም ።

(መ) ማር ፡ ፡ ፲፪ ፡ ፵ ፡ የጠቀስከው ፡ ጸሎታቸውን ፡ በማስረዘም ፡ ምክንያት ፡ የባልቴቶችን ፡ ገንዘብ ፡ የሚበሉ ፡ ሰዎች ፡ ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ ይቀበላሉ ፡ ይላል ። እርግጥ ፤ ነው ፡ አታላዮች ፡ ይቀጣሉ ፤ አታላዮች ፡ አዩቀጡም ፡ አንልም ። አንተ ፡ ግን ፡ የምትናገረው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቅዱሳን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አልሰጣቸውም ፡ ለማለት ፡ ነበረ ፤ ምኑን ፡ ሊገድፍህ ፡ ጠቀስከው ፤ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ ነው ፡ የጠቀስከው ። ይልቅስ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ በሚገኙት ፡ መሥመሮች ፡ ከቍ ፡ ፵፩—፵፬ ፡ የተጻፈውን ፡ ኹለት ፡ ሻሜ ፡ መሐልቅ ፡ ሰጥታ ፡ የበለጠ ፡ ምስጋና ፡ ያገኘች ፡ የዚያችን ፡ ደኃ ፡ ሴት ፡ ታሪክ ፡ ብትመለከት ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ በጭብጥ ፡ ጥሬ ፡ በጥርኝ ፡ ውኃ ፡ የምትወረስ ፡ መኾኗን ፡ በተረዳህ ፡ ነበረ ።



፱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በቃሉ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ለኹሉ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይላል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ለኹሉ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አትበሉ ፡ ይለናል ብለህ ፡ ለዚሁ ፡ ምስክር ፡ ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፲፪ ። ፴ ፡ ፩ ፡ ጠቅሰሃል ። ኢሳ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ለኹሉ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይላልና ፡ እናንተ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አትበሉ ፤ በፍርሃታችሁ ፡ አትፍሩ ፤ አትደንግጡ ፡ ማለቱ ፡ እስራኤል ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ድል ፡ እናደርጋለን ፡ ብሎ ፡ በመታመን ፡ ፈንታ ፡ ከአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ ርዳን ፡ ብለው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስለተጋቡና ፡ ስለተማማሉ ፡ እነርሱን ፡ ሲወቅስ ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቅዱሳንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ሲነቅፍ ፡ አደለም ።

ይኸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቀድሱት ፤ የሚያስፈራላችሁና ፡ የሚያስደነግጥላችሁ ፡ ርሱ ፡ ይኹን ፡ በማለቱ ፡ ይታወቃል ።

ም ፡ ፴ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ የጠቀስከውም ፡ ከሕግ ፡ ለሚርቁ ፡ ምክር ፡ ለሚያደርጉ ፡ ልጆች ፡ ወዮላቸው ። በኃጢአት ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ ይጨምሩ ፡ ዘንድ ፡ ከኔ ፡ ያይደለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይገባሉ ። በመንፈሴም ፡ አይደለም ፡ ወደ ፡ ምስር ፡ ሊወርዱ ፡ የሚሔዱ ፡ አፌንም ፡ አልጠበቁ ፤ በፈርዖን ፡ ጉልበት ፡ ራሳቸውን ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ በምስርም ፡ ጥላ ፡ ይታመኑ ፡ ዘንድ ፡ በፈርዖን ፡ ጉልበት ፡ መታመን ፡ ኃፍረት ፤ በምስር ፡ ጥላ ፡ መታመን ፡ ስድብ ፡ ይኾንባችኋል ፡ ብሎ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ዘረዘርኩት ፡ መኾኑን ፡ አስረድቶ ፡ አረጋግጦ ፡ ተናግሯል ።

፲ ያገራችን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ግን ፡ ከማናውቃቸው ፡ ፍጡራን ፡ ኃላፊዎች ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መውደቅ ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናልና ፡ ያስፈራል ፡ ዕብ ፡ ፲ ፡ ፳፯—፴፩ ፡ ስለምትለው ።

የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ እያማቱ ፡ እያደበላለቁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መውደቅ ፤ እርግጥ ፡ ነው ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናል ። እኛ ፡ ግን ፡ ይህንኑ ፡ አውቀን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እናንተን ፡ የተቀበለ ፡ እኔን ፡ መቀበሉ ፡ ነው ፤ እኔንም ፡ የተቀበለ ፡ የላከኝ ፡ አብን ፡ መቀበሉ ፡ ነው ፤ በጻድቁ ፡ ስም ፡ ጻድቁን ፡ የተቀበለ ፡ ጻድቁ ፡ የሚያሰጠውን ፡ ዋጋ ፡ ያገኛል ። በተማሪዬ ፡ ስም ፡ ጽዋ ፡ ወኃ ፡ ያጠጣ ፡ ዋጋውን ፡ አያጣም ፡ ብሎ ፡ ለባለሟሎቹ ፡ የሰጣቸውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ብቻ ፡ አምነን ፡ በቅዱሳን ፡ በጻድቃን ፡ ስም ፤ ለተራበ ፡ እናበላለን ፡ ለተጠማ ፡ እናጠጣለን ፡ እንጂ ፡ ከማንም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አንጋባም ።

፲፩ አሁን ፡ ግን ፡ የአምላካችን ፡ እውነተኛው ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ስማኝ ፡ ልንገርህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ልጆች ፡ ለኹላቸው ፡ እስራኤል ፡ ዘመንፈስ ፡ ለኾኑ ፡ (ኹለተኛ ፡ ለተወለዱ ፡ )በጣቱ ፡ ፲ቱ ፡ ቃላትን ፡ ከድንጋይ ፡ ላይ ፡ ጽፎ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ሰጣቸውና ፡ ሰዎቹ ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ሊጠብቁ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰማያዊት ፡ ከነዓን ፡ ገነት ፡ ሊያወርሳቸው ፡ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ተዋዋሉ ፡ እንጂ ፡ ከሙሴ ፡ ከአሮን ፡ ከአልዓዛር ፡ ከፊንሐስ ፡ ከዔሊ ፡ ከሳሙኤል ፡ ከጻድቃንና ፡ ቅዱሳን ፡ ከሰማዕታትና ፡ ከመነኰሴዎች ፡ ብቻ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አልገባም ፤ ዘዳግ ፡ ፳፱ ፡ ፱—፲፭ ። ኵሉ ፡ ቅዱሳን ፡ እስመ ፡ አነሂ ፡ ቅዱስ ፡ አነ ፡ ብሎ ፡ ለፍጥረቱ ፡ ኹሉ ፡ ጠቅልሎ ፡ ኪዳን ፡ ተጋብቶታል ። ሕዝ ፡ ፲፯ ፡ ፶፱—፳፪ ። ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፵፱ ፡ ፀ፩ ፡ አምላካችን ፡ አድላዊ ፡ አደለምና ፡ ስሙም ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ አምላክ ፡ ዘዓመፃ ፡ ያፈቅር ፡ ይባላል ፡ ሥራ ፡ ፲ ፡ ፴፬ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ፡ ስለምትለው ።

እግዚአብሔር ፡ ፲ ፡ ቃላትን ፡ ሠርቶ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከመጋባቱ ፡ በፊት ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርዓያነ ፡ ብሎ ፡ ፈጥሮ ፡ ገነት ፡ አግብቶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ካንዲት ፡ ከዕፀ ፡ በለስ ፡ በቀር ፡ ኹሉን ፡ ብላ ፡ ጠጣ ፡ ብሎ ፡ በሾመው ፡ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ የተፈጥሮ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተጋብቶ ፡ ነበረ ። ሰው ፡ ግን ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ባለመጠበቁ ፡ ሞት ፡ ተፈረደበት ። ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ።

፪ተኛ ፡ ሰብአ ፡ ትክትን ፡ ስለኃጢአታቸው ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ ባጠፋቸው ፡ ጊዜ ፡ ኖኅን ፡ ከነልጆቹ ፡ በመርከብ ፡ አድኖ ፡ ካወጣው ፡ በኋላ ፡ ኖኅ ፤ ሰው ፡ መበደሉን ፡ አይተው ፤ አንተም ፡ መፍረድህን ፡ አትተው ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ ቢሠዋ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ከታናሽነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ክፉ ፡ ስለኾነ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ፍጥረትን ፡ ኹሉ ፡ በንፍር ፡ ወኃ ፡ አላ ጠፋውም ፡ ብሎ ፡ ለፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ የሚኾን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለኖኅ ፡ ሰጠው ። ለዚህ ፡ ምልክት ፡ ዐራት ፡ ኅብር ፡ ያላት ፡ ቀሥተ ፡ ደመና ፡ ተክሎለታል ። በኖኅ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ኹሉ ፡ የሚጠበቅበት ፡ ስለኾነ ፡ ለኹሉ ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ ሳይኾን ፡ በተፈጥሮ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ገንዘቡ ፡ ሲኾን ፡ ለባለሟሎቹና ፡ ለወዳጆቹ ፡ እየለየ ፡ እየመረጠ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብቶላቸዋል ።

(ሀ) ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ተከክሎ ፡ ጣዖት ፡ ያመልክ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ አብር ሃም ፡ አ ምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይዞ ፡ ቢገኝ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ምሳሌ ፡ የኾነች ፡ ከነዓንን ፡ አወርስሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ከሰው ፡ ለይቶ ፡ ምሎለታል ፡ ዘፍ ፲፫ ፩-፫ ፡ ፲፫ ። ፲፯ ፡ ፪-፱ ።

ይህንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ለይቶ ፡ ለይስሐቅ ፡ አጽንቶ ፡ ምሎለታል ፡ ዘፍ ፡ ፳፮ ፡ ፪-፭ ፡ ከይስሐቅም ፡ በኋላ ከኤሳው ፡ ለይቶ ፡ ለያዕቆብ ፡ ምሎለታል ፡ ዘፍ ፡ ፴፭ ፡ ፱-፲፬ ፡ ስለዚህም ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለርሱ ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌሎች ፡ ልጆቹ ፡ ሳይኾን ፡ ከይስሐቅ ፡ ለተወለዱ ፡ ለእስራ ኤል ፡ ብቻ ፡ ከራት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ተፈጸመ ። ይህም ፡ ተስፋ በሚፈጸ ምበት ፡ ወራት ፡ የአብርሃምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ንቀው ፡ አቃለው ፡ አንገባም ፡ ያሉ ፡ ፷ው፼ ፡ ዐጋር ፡ በበረሀ ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ተነጥፈው ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረግፈው ፡ ቀርተዋል ፡ ዘኊልቍ ፡ ፲፬ ፡ ፩-፵፭ ። ያባቶችንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ማቃለል ፡ እንዲ ጎዳ ፡ በዚህ አስተውል ።

(ለ) እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ለይቶ ፡ ለዳዊት ፡ መንግሥት ፡ ከዘርህ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አይሔድም ፡ ብሎ ፡ በሰጠው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መን ግሥት ፡ ከዳዊት ፡ ዘርዕ ፡ ሳይወጣ ፡ ይኖራል ፡ መዝ ፹፱ ፡ ፫ ፡ ፬ ። ፩ ዜና ፡ መዋ ፡ ፲፯ ፡ ፩-፲፭ ፡ ባባቶች ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ልጆች ፡ እንዲጠቀሙ ፡ አስተውል ።

ይህስ ፤ ይቅርና ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ እንኳን በተለይ ፡ ለእስራኤል ፡ ብቻ ፡ ሠራት እንጂ ፡ አሕዛብንስ ፡ ኢይባዕ ፤ ሞዓባዊ ፡ ወአሞናዊ ፡ ብሎ ፡ ከልክሏቸዋል ። ስለዚህ ፡ ለመላው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በተለይ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አልተጋባም ፡ ማለ ትህ ፡ ውሸት ፤ ወይም ፡ አለማስተዋል ፡ ነው ።



(ሐ) ሰው ፡ ኾኖ ፡ ወንጌልን ፡ ባስተማረም ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ ለመረጣቸው ፡ ለሐዋርያት ፡ ለ፸ ፡ አርድእት ፡ እናንተን ፡ የተቀበለ ፡ እኔን ፡ ተቀበለ ፤ እኔንም ፡ የተቀበለ ፡ የላከኝን ፡ አብን ፡ ተቀበለ ፤ በስማችሁ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ለደኅ ፡ ያጠጣ ፡ ዋጋውን ፡ አያጣም ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሰጥቷቸዋል ። ይህም ፡ ለነርሱ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ እነርሱን ፡ መስለው ፡ ለተገኙ ፡ ኹሉም ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ሐዋርያትን ፡ መስለው ፡ ለተገኙ ፡ ቅዱሳን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሰጣቸው ፡ ቢባል ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስሕተት ፡ አይደለም ።

፰ ይህነን ፡ ባገራችን ፡ ያለውን ፡ ሕግ ፡ ካፈረሱ ፡ ድንበር ፡ ለጣሱ ፡ ጽድቅ ፡ ይገኛል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጻድቃን ፡ ጸድቀው ፡ ሊያጸድቋችሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተውላቸዋል ፡ እያሉ ፡ ለሚሰብኩት ፡ ማታለል ፡ ግን ፡ ቁርጥ ፡ የሚናገር ፡ አምላካችን ፡ በኢሳይያስ ፡ አፍ ፡ እናንተ ፡ ፌዘኞች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ ከሞት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርገናል ፡ ከሲኦልም ፡ ጋራ ፡ ተማምለናልና ፡ መቅሠፍት ፡ አይነካንም ፡ ትላላችሁና ፡ ይህ ፡ ከሞትና ፡ ከሲኦል ፡ ጋራ ፡ የተማማላችሁት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይጠፋል ፡ እንጂ ፡ አይጸናላችሁም ። እናንተም ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ የምታፌዙ ፡ በጽኑ ፡ ታሥራችሁ ፡ እየተገረፋችሁ ፡ ለሐፍረትና ፡ ለመረገጫ ፡ ትኾናላችሁ ፡ እያለ ፡ ደጋግሞ ፡ ተናግሮለታል ። ኢሳ ፡ ፳፰ ፡ ፲፬—፳፪ ፡ ፴፩ ፡ ፰ ፡ ፱—፲፯ ። ስለምትለው ።

አንተ ፡ እኛ ፡ የማንለውን ፡ ከልቡናህ ፡ ፈጥረህ ፡ ገነት ፡ ለኃጥአን ፡ ክፍት ፡ ናትና ፡ ኃጢአት ፡ ለመሥራት ፡ አትሰቀቁ ፡ ብቻ ፡ ጠላ ፡ ጥመቁ ፡ ዛሬ ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ይላሉ ፡ ብለህ ፡ እንደምትዋሸው ፡ ሳይኾን ፡ ሕግ ፡ ያፈረሱ ፡ ድንበር ፡ የጣሱ ፡ ሰዎች ፡ ንስሐ ፡ ገብተው ፡ በቅዱሳን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አምነው ፡ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ ለተራብ ፡ ካበሉ ፡ ለተጠማ ፡ ካጠጡ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ክፍት ፡ መኾኗ ፡ አይጠረጠርም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከኃጥአን ፡ ከመ ጸብሓን ፡ ጋራ ፡ ለምሳ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ሐዋርያትን ፤ ፈሪሳውያን ፡ መምህራችሁ ፡ ከኃጥአን ፡ ጋራ ፡ ለምን ፡ ይበላል ፡ ሲሏቸው ፡ ሰምቶ ፡ ባለመድኃኒትን ፡ በሽተኞች ፡ እንጂ ፡ ጤነኞች ፡ አይሹትም ፤ እኔም ፡ ኃጥአንን ፡ ልጠራ ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ልጠራ ፡ አልመጣሁም ። ከመሥዋዕት ፡ ምጽዋትን ፡ እብልጨ ፡ እንድወድ ፡ እወቁ ፡ ያለውን ፡ ተመልከት ። ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲-፲፬ ። ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፪-፲፭ ።

እንግዲህ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመሥዋዕት ፡ አብልጨ ፡ እወደዋ ለሁ ፡ የሚለው ፡ ምጽዋት ፡ ምን ፡ መሰለህ ፤ ምንም ፡ አንተ ፡ ከግብሩ ፡ ገብተህ ፡ ባታውቀው ፡ ይህ ፡ በሀገራችን ፡ በዝቶ ፡ ሲሠራ ፡ የምታየው ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዐቅሙ ፡ እንደፈቀደለት ፡ ጠላውን ፡ ጠምቆ ፡ ጥሬውን ፡ ቆልቶ ፡ በጌታም ፡ ስም ፡ ኾነ ፡ በእ መቤታችንም ፡ ስም ፡ ኾነ ፡ በሌሎች ፡ ቅዱሳንም ፡ ስም ፡ ኾነ ፡ ለነዳያን ፡ የሚያበሉት ፡ ማብላት ፡ የሚያጠጡት ፡ ማጠጣት ፡ አይደለምን ? ይህ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ አይምሰልህ ።

ደግሞ ፡ ለዚህ ፡ ማስረጃ ፡ ከሞት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርገናል ፡ ከሲኦ ልም ፡ ጋራ ፡ ተማምለናልና ፡ መቅሠፍት ፡ አይነካንም ፡ ይላሉ ፡ ብሎ ፡ ኢሳይያስ ፡ ተናገ ረባችሁ ፡ ብለህ ፡ ጽፈሃል ። ያንተ ፡ ሃይማኖትና ፡ ባህል ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፡ ከሽህ ፡ [illegible] ዘመን ። አይቴ ፡ እንከ ፡ ቀኖትከ ፡ ሞት ፡ ወአይቴ ፡ መዊዖትከ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሲኦል ፡ ወለእግዚአብሔር ፡ አኰቴት ፡ ዘወሀበነ ፡ ንግዐ ፡ በእግዚእነ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ፩ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶፭–፶፯ ።

ሞት ፤ ድል ፡ መንሣትህ ወዴት ፡ አለ ፤ መቃብርስ ፤ ይዘህ ፡ ማስቀረትህ ፡ ወዴት ፡ አለ ። በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካሳ ፡ ድል ፡ መንሣትን ፡ የሰጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ ብላ ፡ ለራሷ ፡ የምታምን ፡ ለሌላው ፡ የምታስ ተምር ፡ ኢትዮጵያን ፤ ከሞት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተጋባች ፡ ከሲኦል ፡ ጋራ ፡ ተማ ማለች ፡ ስትል ፡ አታፍርምን ? ሰውንስ ፡ መቸም ፡ ንቀኸዋል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያው ቅብኛል ፡ ይፈርድብኛል ፡ አትለውምን ? ውሸትና ፡ ማስመሰልስ ፡ መቸም ፡ ልማድህ ፡ ነው ፡ ያሁኑ ፡ ደግሞ ፡ እጅግ ፡ በዛ ። እኛስ ፡ ከሞትና ፡ ከሲኦል ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መጋባታችን ፡ ይቅርና ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለወዳጆቹ ፡ ለቅዱሳን ፡ ስማች ሁን ፡ ጠርቶ ፡ ለችጋረኛ ፡ የመጸወተውን ፡ ለተራበ ፡ ያበላውን ፡ ለተጠማ ፡ ያጠጣውን ፡ እምርላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሰጥቷቸዋል ፡ ብለን ፡ በስማቸው ፡ ምጽዋት ፡ እንመጸውታለን ፡ ዝክር ፡ እናዘክራለን ፡ እንጂ ፡ ከቅዱሳንም ፡ ጋራ ፡ ቢኾን ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የለንም ።

፲ ወንድሜ ፡ ሆይ ፤ በወንጌል ፡ ወዘተወክፈ ፡ ጻድቀ ፡ በስመ ፡ ጻድቅ ፡ ዐስበ ፡ ጻድቅ ፡ ይነሥእ ፡ የተባ ለውም ፡ ቃል ፡ በስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ተጠልተው ፡ በመታሠርና ፡ በመገረፍ ፡ ተንገላተው ፡ አምላለ ፡ ሐዋርያት ፡ ኾነው ፡ ቤትና ፡ ንብረትን ፡ ትተው ፡ አገር ፡ ላገር ፡ እየዞሩ ፡ ዘንሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በጸጋ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዛ ቸው ፡ ወንጌልን ፡ ያለዋጋ ፡ ለኹሉ ፡ የሚያስተምሩ ፤ እንኳንና ፡ ጉልት ፡ ቀላድ ፡ ሪም ፤ የመሬት ፡ ሲሶ ፡ አንድ ፡ ማንቲም ፡ ቢኾንም ፡ በኪሳቸው ፡ ለማይቋጥሩ ፡ ዓለመኞች ፡ ጌቶች ፡ ኾነው ፡ ሐርና ፡ ኩፍ ፡ ጫማ ፡ ለብሰው ፡ በዘመን ፡ አመጣሽ ፡ መኪና ፡ ለማይንሸረሸሩ ፡ በእብን ፡ በረድ ፡ የተሠራ ፡ ፎቅ ፡ ቀርቶ ፡ ራሳቸውን ፡ የሚያስጠጉ በት ፡ የያፍ ፡ ጎጆ ፡ የሚያህል ፡ ቤት ፡ ማደሪያቸውን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የማይሠሩ ፤ ንግደ ፡ ኮንኩ ፡ ወተወከፍክሙኒ ፡ ብለው ፡ ለሚያስተምሩ ፡ ዛሬ ፡ ላሉት ፡ ለሚገኙት ፡ ለሕያዋን ፡ አገልጋዮቹ ፡ ተወክፉ ፡ ተቀበሉ ፡ ለድኆች ፡ ወንድ ሞቼ ፡ አጠጡ ፡ አልብሱ ፡ አብሉ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተሰብስባችሁ ፡ የሚያስክር ፡ እየጠጣችሁ ፡ ለማይ ሰሙ ፡ ምውታን ፡ ሬሶች ፡ ስም ፡ ብታነሱ ፡ ትጸድቃላችሁ ፡ አይልም ። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፩–፵፩ ። ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፶፯–፷፪ ። ፊል ፡ ፫ ፡ ፰ ። ዕብ ፤ ፲፩ ፡ ፩–፵ ፡ ስለምትለው ።

በገድልና ፡ በተአምር ፡ ዘጸውዐ ፡ ስመክሙ ፡ ወዘገብረ ፡ ተዝካረክሙ ፡ እምሕር ፡ ለክሙ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ጥንቱ ፡ መሠረቱ ፡ አንተ ፡ አሁን ፡ ዘተወክፈ ፡ ጻድቀ ፡ በስመ ፡ ጻድቅ ፡ ዐስበ ፡ ጻድቅ ፡ ይነሥእ ፡ ብለህ ፡ የጠቀስከው ፡ ንባብ ፡ ነው ። አንተ ፡ ግን ፡ በስመ ፡ ጻድቅ ፡ ያለውን ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ወደማ ለት ፡ ቃጥተኸዋል ፤ ከዚህ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ዘአስተየ ፡ ጽዋዐ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ፡ በስመ ፡ ረድእየ ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ኢየኀጕል ፡ ዐስቦ ፡ ይልብሃል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ረድእ ፡ የተባለ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ትደፍር ፡ ይኾን ፤ አትደፍርም ፤ ብትደፍርም ፡ መምህራችሁ ፡ አንድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ፡ መምህራን ፡ ነን ፡ አትበሉ ፡ ብሎ ፡ ተማሪነትን ፡ ለሐዋርያት ፡ መምህርነትን ፡ ለክርስቶስ ፡ ሰጥቶ ፡ ለይቶ ፡ የተና ገረው ፡ ቃል ፡ ያግድሃልና ፡ የጻድቃን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የታመነ ፡ በወንጌል ፡ የተመ ሠረተ ፡ የማይናወጥ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጥልሃለሁ ።

ዘተወክፈ ፡ ጻድቀ ፡ ያለውንም ፤ ሰው ፡ ለይተህ ፡ መቀበል ፡ የሚገባ ፡ እንዲህ ፡ እን ዲህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ስለምትለውም ፡ [illegible]



መሥመር ፡ አንተው ፡ ራስኽ ፡ አፍቅሩ ፡ ጸላዕተክሙ ፡ ወሠናየ ፡ ግበሩ ፡ ለኵሉ ፡ ብለህ ፡ የጠቀስከው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ያፈርስብሃል ፡ ለምኖ ፡ ሽቶ ፡ ከመጣ ፡ ልብስህ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መከልከል ፡ አይገባም ።

፲፩ ለድኆች ፡ ወንድሞቼ ፡ አብሉ ፡ አጠጡ ፡ አልብሱ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተሰብስባችሁ ፡ የሚ ያስክር ፡ ጠጡ ፡ አላለም ፡ ስለምትለው ።

የሚያጣላን ፡ በጠቅላላው ፡ ዝክር ፡ ተዝካር ፡ የለም ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለድኆች ፡ በሚገባ ፡ መዝከር ፡ እንዳለ ፡ ከመንክልኻስ ፡ እኛም ፡ ምሳ ፡ ዝክር ፡ ባደረግህ ፡ ጊዜ ፡ ነዳያንን ፡ ምስኪናንን ፡ ጥራ ፡ እንጂ ፤ እነሱም ፡ መልሰው ፡ ይጠ ሩህ ፡ ዘንድ ፡ ባለጸጎች ፡ ጐረቤቶችህን ፡ ወዳጆችህን ፡ ዘመዶችህን ፡ ጓደኞችህን ፡ አትጥራ ፡ ያለውን ፡ ሉቃ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪–፲፭ ፡ የምናውቅ ፡ ስለኾነ ፡ ለድኆች ፡ ሽተው ፡ ለመጡ ፡ ስጡ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተሰብስባችሁ ፡ ተሳከሩ ፡ ብለን ፡ አና ስተምርም ፡ እንዲህ ፡ ያለውንስ ፡ ጋሬዳ ፡ ሽርብ ፡ እንለዋለን ፡ እንጂ ፡ ዝክር እንለውም ፡

፲፪ ለማይሰሙ ፡ ምውታን ፡ ሬሶች ፡ ብለህ ፡ ጻድቃንን ስለመስደብህ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በምዕራፍ ፡ ፲ ፡ በጻፍከው ፡ ውስጥ ፡ ምውታን ፡ አለመኾናቸውን ፡ ሕያዋን ፡ መኾናቸውን ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌል ሃለሁና ፡ ያነን ፡ ተመልከት ።

፲፫ ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ ከነመሪዎቹ ፡ ለእውነተኛው ፡ የክርስቶስ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ትቶ ፡ ድርሳንና ፡ ተአምር ፡ ገድልና ፡ መልክዕ ፡ የሚባል ፡ የሐሰት ፡ መጻሕፍት ፡ በራሱ ፡ ፈጥሮ ፡ ወንጌል ፡ ፀባብ ፡ አንቀጽ ፡ ናት ፡ ኢትሥ ርቅ ፡ ኢትቅትል ፡ ኤትዘሙ ፡ ኢትኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ አፍቅሩ ፡ ጸላዕተክሙ ፡ ሠናየ ፡ ግበሩ ፡ ለኵሉ ፡ እያለች ፡ የሰውን ፡ ሕሊና ፡ እያሳቀቀች ፡ ታስቸግራለችና ፡ ለሥጋዊ ፡ ጠባይዕ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስራቂ ፡ ዘማዊ ፡ ሐሳዊ ፡ በላዔ ፡ ሰብእ ፡ ወኵሎሙ ፡ ዓላውያን ፡ ሕግ ፡ ይበውዑ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡

ሌላው ፡ ትንሹ ፡ ኃጢአት ፡ ይቅርና ፡ ፼፼ ፡ ሰው ፡ የሚያህል ፡ አርደውና ፡ ቀቅለው ፡ ቢበሉም ፡ እግዚ አብሔር ፡ ለወዳጆቹ ፡ ለፍጡራን ፡ ቃል ኪዳን ፡ ሰጥቷልና ፡ ገነት ፡ ለኃጥአን ፡ ክፍት ፡ ነው ፡ አትስቀቁ ፡ ብቻ ፡ ጠላ ፡ ጥመቁ ፡ እኛ ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ ዛሬ ፡ ደስታና ፡ ስካር ፡ እናብዛ ፡ እያለ ፡ ራሱን ፡ በማታለልና ፤ ባውቆ ፡ አበድነት ፡ አጉል ፡ በስህተት ፡ ይኖራል ፡ ስለምትለው ።

(ሀ) ፡ የክርስቶስን ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ትቶ ፡ የምትለው ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያንተ ፡ ሃይማኖትና ፡ ባህል ፡ ከመመሥረቱ ፡ አስቀድማ ፡ በወንጌል ፡ የጸናች ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ከወንጌል ፡ የወጣች ፡ አደለችም ።

(ለ) ድርሳን ፤ ወእመኒ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያርኢ ፡ መቅሠፍተ ፡ ኀይሉ ፡ ያመጽእ ፡ መላእክተ ፡ መዓቱ ፡ አርእዮ ፡ ትዕግሥቶ ፡ እለ ፡ ድልዋን ፡ ለአማስኖ ። ወከመ ፡ ያርኢ ፡ ክዕበ ፡ ብዕለ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ያመጽእ ፡ መላእክተ ፡ ምሕረቱ ፡ እለ ፡ ድልዋን ፡ ለሣህል ፡ ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

ከሀሊነቱን ፡ የሚገልጥበትን ፡ መቅሠፍት ፡ ሊያሳይ ፡ ቢወድ ፡ ታግሦ ፡ ታግሦ ፡ ለማጥፋት ፡ ተዘጋጅተው ፡ ያሉ ፡ መላእክተ ፡ መዓትን ፡ ያመጣል ።

ዳግመኛም ፡ የቸርነቱን ፡ ምላት ፡ ስፋት ፡ ሊያሳይ ፡ ቢወድ ፡ ለይቅርታ ፡ ተዘ ጋጅተው ፡ ያሉ ፡ መላእክተ ፡ ምሕረትን ፡ ያመጣል ፡ ተብሎ ፡ የተነገረላቸው ፡ መላ [illegible] ፡ እንደተላኩ ፡ ተልከውም ፡ ምን ፡ እንደሠሩ ፡ ዘርዝሮ ፡ የሚያ

www.ethiopianorthodox.org

ስረዳ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በነኔኖክ ፡ በነዳንኤል ፡ በነሕዝቅኤል ፡ እን ደተጻፈው ፡ ነው ። ሕዝ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ፡ ዳን ፡ ፱ ፡ ፳፩ ፡ ፳፯ ። ፲ ፡ ፲-፳፩ ፡ በመ ጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ታገኛለህ ፡ በወንጌልም ፡ በሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፩-፴ ፡ እንደተጻፈው ፡ ነው ።

(ሐ) ፡ ገድልም ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀለ ፡ ሞቱን ፡ ተሸክሞ ፡ በኋላዬ ፡ ያልተከተለኝ ፡ እኔን ፡ ሊያገለግል ፡ አይችልም ፡ ስላለ ፤ በስሙ ፡ ከተሳለ ፡ ስለት ፡ ከነደደ ፡ እሳት ፡ ገብተው ፡ የሞቱ ፡ የሰማዕታትንና ። እንዲሁም ፡ ያለህን ፡ ኹሉ ፡ ሸጠኽ ፡ ለውጠህ ፡ ለነዳያን ፡ መጽውተህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ ስላለ ፡ ያላቸ ውን ፡ ሸጠው ፡ ለውጠው ፡ መጽውተው ፡ ዳባ ፡ ለብሰው ፡ ከሀገር ፡ ወጥተው ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ ዳዋ ፡ ጥሰው ፡ ጤዛ ፡ ልሰው ፡ ደንጊያ ፡ ተንተርሰው ፡ ጸብዐ ፡ አጋንንትን ፡ ግርማ ፡ ሌሊትን ፡ ድምፀ ፡ አራዊትን ፡ ችለው ፡ ታግሠው ። እኔ ፡ ድል ፡ ነሥቻለሁና ፡ ድል ፡ ንሡ ፡ ባለው ፡ ዐመሠረት ፡ ድል ፡ የነሡ ፡ የጻድቃንን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ የሚነግር ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ።

(መ) ተአምርም ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ታኽል ፡ ሃይማኖት ፡ ካለቻችሁ ፡ ተራራ ፡ ታፈልሳላችሁ ፡ ዛፍ ፡ ትነቅላላችሁ ፡ በስሜ ፡ ላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ይች ፡ ተአ ምራት ፡ ቀጥላ ፡ ቀጥላ ፡ ትደረግላቸዋለች ። በኔ ፡ ያመነ ፡ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ ከዚያም ፡ የበለጠ ፡ ያደርጋል ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ በቅተው ፡ ድውይ ፡ ፈውሰው ፡ ሙት ፡ አንሥተው ፡ ተገኝተው ፡ ለቅዱ ሳን ፡ የተደረገላቸውን ፡ ተአምራት ፡ የሚናገር ፡ ስለኾነ ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያትን ፡ የመ ሰለ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ይህም ፡ ዛሬውኑ ፡ የቅዱሳን ፡ ዐፅማቸው ፡ በተቀመጠበት ፡ ፀበላቸው ፡ በፈለቀበት ፡ ቦታ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ። በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በዝቋላ ፡ ብትሔድ ፡ ዕውር ፡ ሲበራ ፡ ጎባጣ ፡ ሲቀና ፡ አንካሳ ፡ ሲረታ ፡ ታያለህ ። ስለዚህ ፡ እኒህ ፡ መጻሕፍቶች ፡ የወንጌል ፡ ፍሬዎች ፡ የወንጌል ፡ መታወቂያዎች ፡ ይባላሉ ፡ እንጂ ፡ ከወንጌል ፡ ልዩ ፡ ናቸው ፡ አይባሉም ። እንዲህ ፡ በሥራ ፡ ካልተገለጠማ ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ እውነተኛ ፡ መኾኑ ፡ በምን ፡ በታወቀ ፡ ነበረ ።

(ሠ) ፡ ወንጌል ፡ ጠባብ ፡ በር ፡ በመኾኗ ፡ የሰውን ፡ ሕሊና ፡ ስላሰቀቀች ፡ ለሥ ጋዊ ፡ ጠባይዕ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ትምርት ፡ የምታስተምር ፡ አንተነህ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ አደለንም ።

እንደምን ፡ ብትለኝ ። የእኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጾም ፡ በወንጌል ፡ የተሠራ ፡ ሕግ ፡ ነው ፯ቱን ፡ አጽዋማት ፡ ጹሙ ፤ ትሕርምትን ፤ ሰጊድን ፤ ቁመትን ፡ አብዝ ታችሁ ፡ ሥሩ ፡ እያለች ፡ ስታስተምር ፤ አንተ ፡ በወንጌል ፡ ጌታ ፡ ጾመ የሚል ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ ጹሙ ፡ የሚል ፡ የለምና ፡ አትጹሙ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ስትበሉ ፡ ኑሩ ፡ እያልክ ፡ ሥጋን ፡ ደስ የሚያሰኛትን ፡ ትምርት ፡ ታስተምራለህ ። ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፬-፲፰ ።

የኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቃችሁ ፡ ከሴት ፡ ርቃችሁ ፡ ንጽሕ ፡ ጠብቃችሁ ፡ በብሕትውና ፡ በድንግልና ፡ በምንኩስና ፡ ኑሩ ፡ ብላ ፡ ለሥጋ ፡ ጭንቅ ፡ የኾነ ፡ ትምርት ፡ ስታስተምር ፡ አንተ ፡ ይህ ፡ ምንኩስና ፡ በመጽሐፍ ፡ የሌለ ፡ ሰው ፡

www.ethiopianorthodox.org



ሠራሽ ፡ ሕግ ፡ ነውና ፡ ቤት ፡ ሠርታችሁ ፡ ንብረት ፡ ይዛችሁ ፡ ሚስት ፡ አግብታችሁ ፡ ሕፃናት ፡ ወልዳችሁ ፡ ኑሩ ፡ እያልክ ፡ ሥጋን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛትን ፡ ትምርት ፡ ታስ ተምራለህ ። ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲-፲፫ ። ፲፮-፴ ፡ ስለዚህ ፡ የወንጌል ፡ ሕግ ፤ ጭንቅ ፡ የኾነች ብህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ አደለንም ።

(ረ) ፡ ሰራቂ ፤ ሐሳዊ ፤ ዘማዊ ፤ በላዔ ፡ ሰብእ ፡ በሕፍኑ ፡ ማይ ፡ ገነት ፡ ይገባሉ ፡ ያለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ አደለንም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፩-፲፬ ፡ ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፪-፲፩ ። ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩-፳፫ ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ፡ ፬ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፫-፳፩ ። ተመልከት ።

(ሰ) ፹፰ ፡ ሰው ፡ ቀቅለው ፡ ቢበሉ ፡ ስለምትለው ፡ ወንድምህ ፡ አቶ ፡ መንግ ሥቴ ፡ እምሩ ፡ በዛሬይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግንቦት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ሚዛን ፡ አያሸውም ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥቶ ፡ ጠይቆኝ ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌለታለሁና ፡ በግ ንቦትና ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ በ፵፰ ዓ ም ፡ በተጻፈ ፡ ዜና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋዜጣ ፡ ተመልከት ።

ስለዚህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ በ(ሠ)ተራ ፡ ፊደል ፡ እንደ ፡ ዘረዘርኩልህ ፡ ራስን ፡ በማታለል ፡ በአውቆ ፡ አበድነት ፡ የምትኖር ፡ አንተ ፡ መኾንህን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለመኾኗን ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ።

፲ ይህን ፡ የማታለል ፡ አርጌ ፡ ልማድ ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ በወንጌለ ፡ ማቴዎስ ፡ ፳ተኛ ፡ ምዕራፍ ከተናገረው ፡ ቃላት ፡ እንደምን ፡ ሊስማማ ፡ ይችላል ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፬—፲፰ ፡ ኢሳ ፡ ፳፱ ፡ ፲፫ ፡ ፶፯ ፡ ፲—፲፪ ፡ ስለምትለው ።

(፩) ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ በ፳ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ።

(ሀ) ከእውቀት ፤ ከብዕል ፤ ከኃይል ፡ ነዳያን ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሳሉና ።

(ለ) ዛሬ ፡ የሚያለቅሱ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ኋላ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ።

(ሐ) ስለጽድቅ ፡ ብለው ፡ የሚራቡ ፡ የሚጠሙ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ኋላ ፡ ይጠግባሉና ፡ ።

(መ) ስለጽድቅ ፡ ብለው ፡ ከሀገር ፡ ወጥተው ፡ ከዘመድ ፡ ተለይተው ፡ የሚሰ ደዱ ፡ የሚመንኑ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የነርሱ ፡ ናትና ፡ ይላል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ ተስማምታ ፡ ትገኛ ለች ። ያንተ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ያህል ፡ የተራራቀች ፡ ናት ።

(፪ተኛ) ለዚህም ፡ ምስክር ፡ የጠቀስከው ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ፡ ባላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ግብር ፡ አትኑሩ ፡ ይላል ።

(ሀ) ያላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ግብር ፡ ምንድን ፡ ነው ። ጾም ፡ ትሕርምት ፡ ሰጊድ ፡ ቁመት ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ሲፈጽሙ ፡ መኖር ፡ አደለምን ። ይህ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ የለም ። ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ሕግ ፡ ኾኖ ፡ ተይዟል ።

www.ethiopianorthodox.org

(ለ) ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘውም ፡ መሥመር ፡ ክርስቶስን ፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚያደርገው ፡ ማነው ፡ ይላል ። በንተ ፡ ክፍል ፡ በሚገኘው ፡ ዋችታዎር ፡ በሚባለው ፡ ማኅበር ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የመጀመሪያ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፡ ከማለቱ ፡ በላይ ፤ ዛሬ ፡ የሰይጣን ፡ መንግሥት ፡ ነው ። የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ገና ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሰይጣንን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ተካፋይ ፡ አድርጎት ፡ ይገኛል ። አንተም ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ አእግዚአ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ በመለኮቱ ፡ ያማልድ ፡ ነበረ ፡ በማለትህ ፡ በመለኮቱ ፡ ፍጡር ፡ ብለኸዋል ።

በእኛ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ደፍሮ ፡ የሚናገር ፡ ይቅርና ፡ የሚያስብ ፡ የለብንም ፡ ከነወሬውም ፡ በንተ ፡ ጊዜና ፡ በንተ ፡ አንደበት ፡ መሰማቱ ፡ ነው ።

(ሐ) ከዚህም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ታቦተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከቤተ ፡ ጣዖት ፤ አግብቶ ፡ የሚያኖር ፡ ማነው ፡ በማለቱ ፡ ታቦትንና ፡ ጣዖትን ፡ ለይቶ ፡ ተናግሯል ። እኛም ፡ እን ደዚሁ ፡ ታቦትንና ፡ ጣዖትን ፡ ለይተን ፡ እናውቃለን ።

አንተ ፡ ግን ፡ ታቦተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጣዖት ፡ እያልክ ፡ ትሰድባለህ ።

(፫ተኛ) ኢሳ ፡ ፳፪ ፡ ፲፫ ፡ የጠቀስከው ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ሐሜትና ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ ላም ፡ ማረድም ፡ በግ ፡ ማረድም ፡ ሥጋ ፡ መብላትም ፡ ጠጅ ፡ መጠጣትም ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ ይላል ።

በኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ማለትን ፡ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንጹም ፡ እንጸልይ ፡ ማለት ፡ የሚቃወመው ፡ ስለኾነ ፡ ላሞችና ፡ በጎች ፡ የሚታረዱባቸው ፤ ሐሜትና ፡ ደስታ ፡ የሚደረጉባቸው ፡ ቀኖች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ።

በንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ማለትን ፡ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንጹም ፡ ማለት ፡ የማይቃወመው ፡ ስለኾነ ፤ በሕግ ፡ የተፈቀዱ ፡ ላሞችና ፡ በጎች ፡ ይቅሩና ፡ በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ እነ ፡ አሪያና ፡ እነአሳማ ፡ ሳይቀሩ ፡ ችግር ፡ ፈንታ ፡ ካልሰጣቸው ፡ በቀር ፡ ጊዜ ፡ ሳይጋሰን ፡ ካመት ፡ እስካሙት ፡ እየ ታረዱ ፡ ዘወትር ተድላ ፡ ደስታ ፡ ይደረግባቸዋል ። ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፩-፵፯ ።

፵፯ ፡ ፲-፲፪ ፡ የጠቀስከውም ፡ ተመልካቾቹ ፡ ዕውራን ፡ ናቸው ፤ ኹሉ ፡ ሰነፉ ፡ አፍ ፡ የሌላቸው ፡ ውሾች ፡ ናቸው ፡ ይጮኹ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ። ያልማሉ ፤ መኝ ታና ፡ እንቅልፍ ፡ ይወዳሉ ፡ ይላል ። በእኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወተለዐለ ፡ መር ፈቀ ፡ ኖኅት ፡ እምቃል ፡ ዘይኬልሑ ፡ ተብሎ ፡ በኢሳይያስ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ እን ቅልፍ ፡ በሌላቸው ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ መዘም ራንም ፡ አንደበት ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የዜማ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማባታል ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩-፫ ። በንተ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አይሞከርም ፡

፭ተኛ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ መብል ፡ የሚወዱ ፡ ውሾች ፡ ናቸው ፡ ጽጋብ ፡ የማ ያውቁ ፤ ርሳቸውም ፡ ከማስተዋል ፡ የሰነፉ ፡ ጠባቆች ፡ ናቸው ፡ ከፊተኛው ፡ እስከኋ ለኛው ፡ ድረስ ፡ ኹሉም ፡ ወደመንገዳቸው ፡ ወደንፍገቱ ፡ ተመለሱ ፡ ይላል ።



(ሀ) እነሆ ፡ በእኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከጾም ፡ ተከልክሎ ፡ መብልን ፡ ብቻ ፡ መውደድ ፤ ጥጋብን ፡ የማያውቅ ፡ ውሻን ፡ የሚያደርግ ፡ መኾኑ ፡ ታውቆ ፡ ከተወ ሰነ ፡ ሰዓት ፡ በቀር ፡ ኹልጊዜ ፡ መብል ፡ ክልክል ፡ ነው ።

በንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ሌላው ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ ይቅርና ፡ ከ፯ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ በ፩ሰዓት ፡ ወደቤተ ፡ ጸሎት ፡ ስትሔድ ፡ ቁርስ ፡ ሳታደርግ ፡ አት ወጣም ፤

(ለ) በእኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፤ ንፍገት ፡ የተጠላ ፡ የተነቀፈ ፡ ስለኾነ ፡ በጻ ድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ ስም ፡ ድግስ ፡ ደግሶ ፡ ለነዳያን ፡ ዝክር ፡ መዘከር ። ለነፍሳተ ፡ ሙታን ፡ ተዝካር ፡ ማውጣት ፡ የታዘዘ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ በዝቶ ፡ ሲሠራ ፡ ይታያል ።

በንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ንፍገትን ፡ አክብሮ ፡ እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ አስመስሎ ፡ ለመያዝ ፡ እንዲመች ፡ ዝክር ፡ ተዝካር ፡ የተጠሉ ፡ የተነቀፉ ፡ ናቸው ።

እንግዲህ ፡ ከእግርህ ፡ እስከ ፡ ራስህ ፡ የተከናነብከውን ፡ ጉድ ፡ ወደማን ፡ ልት ጥለው ፡ አሰብክ ። ጌታችን ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ በ፳ ፡ ምዕራፍ ፡ ከተናገረው ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ ያንተ ፡ ሕግ ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ። የኛ ፡ ሕግስ ፡ በአን ቀጽ ፡ ብፁዓን ፡ የተመሠረተች ፡ የውጣ ፡ እንተ ፡ አሐቲ ፡ ቅርፀታ ፡ ኢተሐልፍ ፡ እምኦሪት ፡ ወእምነቢያት ፡ የተባለች ፡ እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ ናት ።

፲፩ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ የማታስል ፡ ነገር ፡ አዲስ ፡ እንዳይመስልህ ፡ ከልደት ፡ በፊት ፡ በ፯፻ ፡ ዓመት ፡ በኢሳይያስ ፡ ዘመን ፡ ሕዝቡ ፡ ለተመልካቾቹ ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ከንሕጉ ፡ ወዲያ ፡ ፈቀቅ ፡ አድርጉት ፡ ቅን ፡ ነገርንም ፡ አትዩልን ፡ ለሥጋ ፡ ሐሳባችን ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘን ፡ የጣፈጠውን ፡ ቃላት ፡ ማታለልን ፡ ንገሩን ፡ የሚሉ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ መጻሕፍት ፡ ይነግሩናል ፡ ስለምትለው ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሲመረመር ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ሕጉ ፡ ምን ፡ ይመስ ልሃል ፤ ጾም ፤ ጸሎት ፤ ሰጊድ ፤ ቁመት ፡ ምጽዋት ፡ ነው ፡ እኒህንስ ፡ ወዲያ ፡ ፈቀቅ ፡ ያደረጋቸው ፡ ማነው ? አንተ ፡ አይደለህምን ።

ለሥጋዊ ፡ ሐሳብ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ቃልስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፤ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ጾም ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ሥጋት ፡ ማጥፋት ፡ አደለምን ።

ለዚህስ ፡ ፈጻሚው ፡ አንተ ፡ አይደለህምን ፡ ወደማን ፡ ልታስጠጋው ፡ ትፈቅዳለህ ። እንዲህ ፡ የሚያሳፍር ፡ መጥፎ ፡ ተግባር ፡ መኾኑን ፡ ካወቅኸውስ ፡ አትተወውምን ።

፲፪ ሐዋርያትም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ አስተኞች ፡ መምህራን ፡ በደሙ ፡ የገዛቸውን ፡ ጌታ ፡ የሚክዱ ፡ ከሥጋ ፡ በኋላ ፡ የሚሔዱ ፡ ደፋሮችና ፡ ትዕቢተኞች ፡ ርኩሶችና ፡ ነውረኞች ፡ በማታለላቸው ፡ ራሳቸውን ፡ የሚ ያስወፍሩ ፡ ሴሰኞችና ፡ የተረገሙ ፡ ልጆች ፡ እንደሚነሱ ፡ ጽፈው ፡ ትተውልናል ። ስለምትለው ።

ራስን ፡ ማታለልና ፡ ማስወፈር ፡ ማለት ፡ የጾምን ፡ ሕግ ፤ ሕግ ፡ አደለም ፡ በማለት ፡ ራስንም ፡ ሌላውንም ፡ እያታለሉ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ በመብላት ፤ መወፈር ፡ ነው ፡ ይኸ ውም ፡ ተፈጻሚነቱ ፡ በንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ አሰተኞች ፡ መምሕራን ፡ ይነሣሉ ፡ ብለው ፡ ትንቢት ፡ የተናገሩ ፡ ሐዋርያትም ፡ ጌታ ፤ ሰው ፡ በኾነበት ፡ ባ፳፪ ፡ ፳፱ ፡ ዘመን ፡ ከዚ ያም ፡ በፊት ፡ የተመሠረተውን ፡ ዛሬ ፡ እኛ ፡ የምንገኝበትን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ነው

www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ጥምቀትን ፤ ተባሕትዎን ፤ ምንኩስናን ፤ ተአምኖ ፡ ኃጣውእን ፤ ከዊነ ፡ ሰማዕትን ፡ እኒህን ፡ ፳ቱን ፡ ሕገጋት ፡ ፈጽሞ ፤ እኛንም ፡ ሥሩ ፡ ሲለን ፤ ተዐቀቡ ፡ እምሐሳውያነ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤክሙ ፡ በአልባሰ ፡ አባግዕ ፡ ወእንተ ፡ ውሥጦሙሰ ፡ ተኵላት ፡ መሠጥ ፡ እሙንቱ ፡ ወእምፍሬሆሙ ፡ ተአምርዎሙ ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ።

እነርሱ ፡ የሚነጥቁ ፡ ተኵላዎች ፡ ናቸውና ፡ የበግ ፡ ደበሎ ፡ ለብሰው ፡ (ማለት ፡ )ክህደት ፡ መርዛቸውን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡ በማለት ፡ ደብቀው ፡ ከሚ መጡ ፡ ሐሰተኞች ፡ መምሕራን ፡ ተጠበቁ ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ የመሰለ ፡ ንግግር ፡ ይህን ፡ አንተ ፡ የጠቀስከውንና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመ ሳሰለ ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ።

ጌታ ፡ የሠራቸው ፤ ሐዋርያትም ፡ ያጸኗቸው ፡ ከላይ ፡ የጠቀስኳቸው ፡ ፳ቱ ሕገጋትና ፡ ሌሎቹም ፡ ሕገጋት ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፭፻ ፡ ፲፪ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ዓለም ፡ ተከክሎ ፡ ሲሠራባቸው ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ከ፩ሺ፭፻፲፪–፩ሺ፭፵፯ ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ ዘመ ናት ፡ መካከል ፡ የሐዋርያት ፡ ትንቢት ፡ ተፈጸመ ፡ ቢባል ፡ ይቻላል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መፈጸሙንም ፡ አንተው ፡ ራስህ ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍህ ፡ በ፲፫ተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለማሠርና ፡ መፍታት ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በገጽ ፡ ፸፯ ፡ ሉተር ፡ ጀር መናዊ ፡ የሰውን ፡ ሥርዓትና ፡ የፍጡራን ፡ አማላጅነት ፡ ተባሕትዎና ፡ ምንኵስናም የሚሉት ፡ አንዘግዝጎ ፡ ጥሎ ፡ በምግባር ፡ ሳይኾን ፡ በክርስቶስ ፡ እምነት ፡ ብቻ ፡ የሚገኘውን ፡ የጸጋ ፡ ድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ በድፍረት ፡ ስላስተማረ ፡ እምነትን ፡ ለመጽ ደቂያ ፤ መልካም ፡ ምግባር ፡ ግን ፡ የሃይማኖት ፡ መግለጫ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መስክሯል ፡ በሮማው ፡ ጳጳስ ፡ ሕግ ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ርሱና ፡ ተማሪዎቹ ፡ በምድ ርና ፡ ሰማይ ፡ ጽሉዓንና ፡ ውጉዛን ፡ ዕሡራን ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡ መስክረሃል ።

ይህ ፡ የኛ ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ተቀዳሚ ፤ ሲሠራበት ፡ የኖረ ፡ ኾኖ ፤ ያንተ ፡ ሕግ ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ከ፩ሺ፭፻፲፪ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የተመሠረተ ፡ መኾኑ ንም ፡ ሐተታ ፡ መናፍስት ፡ ብለህ ፡ በጻፍከው ፡ መጽሐፍህ ፡ በ፸፩ ፡ ገጽ ፡ ግብዙ ፡ የጳጳስ ፡ ቀንበር ፡ ሰብሮ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ተፀመደ ፡ በኤሮፓ ፡ የተጋደለና ፡ ስለ ፡ ክርስቶስም ፡ መከራ ፡ የተቀበለው ፤ ማርቲን ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ሥዕሉን ፡ ጨምረህ ፡ ከገለጽከ ፡ በኋላ ፡ እርሱም ፡ በ፩ሺ፬፹፫ ፡ ዓ ም ፡ በስክስን ፡ አገር ፡ አይስሌበን ፡ በምትባል ፡ ከተማ ፡ ተወለደ ፡ ከ፩ሺ፭፲፪ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፭፻፵፯ ፡ ድረስ ፡ አሮጌዋ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በወንጌል ፡ መታደስን ፡ እንደሚገባት ፡ በትጋት ፡ አስተምሮ ፡ በቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ጸንቶ ፡ ልጆች ፡ ወልዶ ፡ ነፍሱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አደራ ፡ ሰጥቶ ፡ በሰላም ፡ ዐረፈ ፡ ብለህ ፡ አስረ ድተሃል ።

እንዲህ ፡ አድርገህ ፡ ትንቢቱንና ፡ ዘመኑን ፡ አስተባ[illegible] ኘው ፡ ሰው ፡ ከሐዋርያት ፡ ሕግ ፡ ባልተናወጽኖች ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ መጥቀስ ፡



በነገሩ ፡ መርምሮ ፡ የሚደርስበት ፡ የለም ፡ መስሎህ ፡ ይኾን ፡ ወይስ ፡ አንተ ፡ በነ ገሩ ፡ ባትደርስበት ፡ ይኾን ።

በእውነቱ ፡ ሳይታወቅህ ፡ መስሎህ ፡ ተናግረኸው ፡ እንደኾነ ፤ የኛ ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀዳሚነቷን ፡ አንተው ፡ መስክረሃል ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ይቺ ፡ የኛ ፡ ሕግ ፡ ከጌታና ፡ ከሐዋርያት ፡ በቀር ፡ እንዳንተ ፡ ሕግ ፤ ሌላ ፡ መሥራች ፡ አላት ፡ ብለህ ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ አልተናገርክ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ የምታመከኝበት ፡ የለህምና ፡ የሐዋርያት ፡ ትንቢት ፡ የተፈጸመ ፡ ባንተ ፡ እንደኾነ ፡ እወቅ ።

አውቀህ ፡ ለማጭበርበርም ፡ ተናግረኸው ፡ እንደኾነ ፡ ማጭበርበር ፡ ማስ መሰል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ እንደኾነ ፡ እወቅና ፡ ተመለስ ።

፲፫ እውነተኛይቱ ፡ ቅንይቱ ፡ የክርስቶስ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ እርሟኛ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ዝሙትና ፡ ርኵሰት ፡ ትዕቢትና ፡ ስስዕት ፡ ሐሰትና ፡ ጥትወት ፡ ስካርና ፡ ቅትለት ፡ ጥንቆላና ፡ ጣዖት ፡ ጠብና ፡ መቃናት ፡ ቁጣና ፡ መለያየት ፡ ገላ ፡ ፭ ፡ ፲፫–፳፮ ፡ የሌለባትና ፡ ነውር ፡ የማይገኝባት ፡ ቅድስት ፡ ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ለክርስቶስ የምትገባ ፡ ወዳ ፡ የታጨችው ፡ በሕገ ፡ ወንጌሉ ፤ ብቻ ፡ የተቀጣችና ፡ ትዛዙንም ፡ በሙሉ ፡ የጠበቀች ፡ ልትኾን ፡ ይገባታል ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፩—፬ ። ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፪– ፴፪ ፡ ስለምትለው ።

አንተ ፡ ባታውቅ ፡ እንግዳ ፡ አስመስለህ ፡ በሕገ ፡ ወንጌሉ ፡ ብቻ ፡ የተቀጣችና ፡ ትእዛዙንም ፡ በሙሉ ፡ የጠበቀች ፡ ልትኾን ፡ ይገባታል ፡ ብለህ ፤ ትናገራለህ ፡ እንጂ ፡ ርሷስ ፡ ሕግ ፡ አፍራሾች ፡ እንዲቀጡ ፡ አውቃ ፡ ሕጉን ፡ ከተቀበለች ፡ ጀምራ ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ ብቻ ፡ የተሠራች ፡ የተቀጣች ፡ ናት ።

፲፬ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ክንቱ ፡ የሆነ ፡ ማታለልና ፡ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ እያልኩኝ ፡ የምነግርህ ፡ ግን ፡ የሐሰት ፡ መምሕራን ፡ የፈጠሩ ፡ መጻሕፍት ፡ ዛሬ ፡ የመጣ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይምሰልህ ፡ ብለህ ፡ ፪ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፩–፳፪ ፡ ለጠቀስከው ፡ መልሱ ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፲፪ ፡ ቍጥር ፡ ተጽፎልሃል ፡ ያንን ፡ ተመልከት ።

፲፭ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ አባቶቻችን ፡ ጣዖት ፡ የሚያመልኩ ፡ በሥዕልና ፡ ምስል ፡ የሚሠኩ ፡ ለሕገ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ የሚቃወሙ ፡ ለእንጨትና ፡ ደንጋይ ፡ የሚሳለሙ ፡ የሚገሉ ፡ የሚሰርቁ ፡ የሚመነዝሩ ፡ እየዋሹ ፡ በዛርና ፡ ጠንቋይ ፡ የሚመሩ ፡ ቢኖሩ ፡ ብለህ ፡ አለ ፡ ሥራቸው ፡ ማዳንን ፡ ለነርሱ ፡ እየሰጠን ፡ አማልክት ፡ ጣዖ ታት ፡ ልናደርጋቸው ፡ አይገባንም ። እስከ ፡ ምትለው ፡ ድረስ ።

ጣዖታት ፡ እያልክ ፡ የምትሰድባቸው ፤ በእኛም ፡ ላይ ፡ አማልክት ፡ ይሏቸዋል ፡ እያልክ ፡ የምታወራ ፡ አንተ ፡ ነህ እንጂ ፡ እኛ ፡ አደለንም ።

እኛስ ፡ የሚገባቸውን ፡ የባለሟልነት ፡ ክብር ፡ እንዳላቸው ፡ እንናገራለን ፤ የሚ ገባቸውን ፡ ክብር ፡ እናከብራቸዋለን ፡ እንጂ ፡ አማልክት ፡ ብለን ፡ አናመልካቸ ውም ፤ ጣዖታትም ፡ ብለን ፡ አንሰድባቸውም ።

ዐዋጅ ፡ ብለህ ፡ ከጀመርከው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ የጻፍከውም ፡ የምትጽፈውም ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። እኔም ፡ መልሱን ፡ በያንቀጹ ፡ እየዘረዘርኩ ፡ ጽፌ ልሃለሁ ፡ [illegible] ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ደግሜ ፡ እንዳልጽፈው ፡ የኔን ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ በማባከኔ ፡ በላይ ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፤ የተመልካቾችንም ፡ ጊዜ ፡ መባከን ፡ ስለኾነ

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## የማይመሰል ፡ ምሳሌ ።

፩ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ እመዐር ፡ ወሦከር ፡ ይጥዕመኒ ፤ ለአፉየ ፡ የተባለው ፡ የመድኃኒ ፡ ዓለም ፡ ቃልና ፡ አማላጅነትም ፡ ስነግርህ ፡ የሌለ ፡ የማይመስል ፡ መራራ ፡ ምሳሌ ፡ ዘተሠርዐ ፡ በምድር ፡ ተሠርዐ ፡ በሰማይ ፡ ተብሏልና ፡ ምንው ፡ በምድራዊ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ሕግ ፡ ያፈረሰ ፡ የሰረቀ ፡ የገደለ ፡ ባማላጆች ፡ ይድናል ፡ ትለኛለህ ። ስለምትለው ።

እኔስ ፡ አንተ ፡ አለ ፡ አገባብ ፡ የጠቀስካቸውን ፡ ጥቅሶች ፡ የተጻፈበት ፡ ምክን ያት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እያልኩ ፡ እየዘረዘርኩ ፡ በማስረዳት ፤ ወይም ፡ አንተ ፡ የጠቀስካ ቸውን ፡ መጻሕፍት ፡እየጠቀስኩ ፡ ከማስረዳትና ፡ ከመርታት ፡ በቀር ፤ አንተ ፡ በልቡ ፡ ምን ፡ አለ ብለህ ፡ ዘተሠርዐ ፡ በምድር ፡ ዘተሠርዐ ፡ በሰማይ ፡ ትለኛለህ ፡ ብለህ ፡ የጠቀስከውን ፤ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ አልጠቀስኩልህ ፡ ወደፊትም ፡ አልጠቅስልህም ። ስለዚህ ፡ አንተ ፡ በግምት ፡ ሳይለኝ ፡ አይቀርም ፡ ብለህ ፡ ለጻፍከው ፡ መልስ ፡ ልሰጥህ ፡ አልፈቀድኩም ።

፪ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ንጉሥና ፡ ጳጳስ ፡ የአምላክ ፡ ምሳሌ ፡ ሊኾኑና ። ሊባሉ ፡ ከቶ ፡ አይገባም ። ስለምትለው ።

ስንኳን ፡ የፍጡርና ፡ የፈጣሪ ፡ ምሳሌነት ፤ የፍጡርና ፡ የፍጡር ፡ ተመሳሳይነት ፡ እንኳ ፡ ቢኾን ፤ እገሌ ፡ እገሌን ፡ ይመስላል ፡ ሲባል ፤ ለተነጋሪው ፡ ልቡና ፡ ግምት ፡ ስሜት ፡ የመስጠት ፡ ያህል ፡ እገሌ ፡ እገሌን ፡ ይመስላል ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ በፍጹም ፡ ተካክሎ ፡ አይገኝም ። ስለዚህ ፡ ምሳሌ ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፡ ዘወትር ፡ ሕፀፅ ፡ መኾን ፡ አለበት ።

እግዚአብሔርም ፡ እንደዚሁ ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከ ለው ፡ የሌለ ፡ ልዑለ ፡ ባሕርይ ፡ ብሑተ ፡ ህሉና ፡ ሲኾን ፡ ለወዳጆቹ ፡ በልዩ ፡ በልዩ ፡ ምሳሌ ፡ ታይቷቸዋል ፤ ራሱንም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምሳሌ ፡ እየመሰለ ፡ ነግሮናል ።

(ሀ) በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርዓያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ በምሳሌው ፡ ፈጥሮታል ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ።

(ለ) ለአብርሃም ፡ መምሬ ፡ በሚባል ፡ ቦታ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ መስሎ ፡ ታይቶ ታል ፤ መብልም ፡ ለባሕርዩ ፡ ተስማሚ ፡ ሳይኾን ፡ እንደሰው ፡ ፡ ሲበላ ታይቷል ፡ ዘፍ ፲፰ ፩ -፱ ።

(ሐ) ያዕቆብን ፡ በመንገድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ ቀርቦ ፡ ታገለውና ፡ በመጨረ ሻው ፡ ባረከው ፡ ዘ ፍ ፡ ፴፪ ፳፬ -፴፪ ።

(መ) ለዳንኤል ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ የራሱ ፡ ፀጉር ፡ እንደ ፡ ነጭ ፡ ፀምር ፡ የኾነ ፡ ሽማግሌ ፡ መስሎ ፡ ታይቶታል ፡ ዳን ፡ ፯ ፡፱ ፲፫-፲፭ ።

(ሠ) ለዮሐንስም ፡ በራእዩ ፡ እንደዚሁ ፡ ጶዴር ፡ የሚባል ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ወገ ቡን ፡ በወርቅ ዝናር ፡ ታጥቆ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መስሎ ፡ በ፯ቱ ፡ የወርቅ ፡ መቅረዞች ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ታይቶታል ፡ ራእ ፡ ፩ ፲፪-፲፯ ።



(ረ) ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ወንጌልን ፡ በስተማረ ፡ ጊዜም ፡ ራሱን ፡ በገበሬ ፤ ወንጌልን ፡ በስንዴ ፡ ቅንጣት ፡ በዘር ፤ ምእመና ንን ፡ በእርሻ ፤ ማቴ ፡ ፲፫ ፩-፲ ። ፲፰ ፳፫ -፴፬ ራሱን ፡ በባለቤት ፤ ወንጌልን ፡ በዐፀደ ፡ ወይን ፤ ምእመናንን ፡ በምንደኛ ፡ ማቴ ፡ ፳ ፡ ፩-፲፯ ፡ ፳፩ ፡ ፴፫-፵፪ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ በንጉሥ ፤ ራሱን ፡ በንጉሥ ፡ ልጅ ፤ ወንጌልን ፡ በሠርግ ቤት ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ፪-፲፭ ራሱን ፡ በሙሽራ ፤ ምእመናንን በደናግል ፤ እየመሰለ ፡ ነግሮናል ፡ ማቴ ፡ ፳፭ ፩-፲፫ እኒህ ፡ ኹሉ ምሳሌዎች ፡ ከላይ ፡ እንዳስታወስኩት ፡ ለሕሊና ፡ ስሜትን ፡ የሚሰጡ ፡ ሕፀፃን ፡ ምሳሌ ዎች ፡ ናቸው ፡ እንጅ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የተካከሉ ፡ ምሳሌዎች ፡ አደሉም ። እነዚህን ፡ ሕፀፃቸው ፡ ከምሳሌነት እንዳልከለከላቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ በባሕርዩ ፡ የሚገዛውን ፡ ዓለም ፡ በጸጋ ፡ የሚገዛ ፡ ንጉሥም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ የሚያሳ ፍር ፡ አይደለም ። እንደዚኾውም ፡ በምድር ፡ ያሠራችሁት ፡ በሰማይ ፡ የታሠረ ፡ ይኹን ፡ በምድር ፡ የፈታችሁት ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ለሥልጣኑ ፡ ተካ ፋይ ፡ ያደረጋቸው ፡ ጳጳሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ናቸው ቢባል ፡ የሚያ ስፈራው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ የጻፍከው ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ከንቱ ፡ ፃማ ፡ ከናፍር ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲

## ንስሐ ፡ ኃዘን ፡ ልቅሶ ።

፩ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እውነተኛው ፡ አማላጅ ፡ ማለት ፡ ፈጣሪህን ፡ መሐሪ ፡ መኾኑን ፡ አምነህ ፡ በንስሐ ፡ በኃዘን ፡ በልቅሶ ፡ ንቅተህ ፡ እንዚህ ፡ ፫ቱን ፡ አማላጆች ፡ አጥብቀህ ፡ ይዘህ ፡ ብትፈልገው ፡ ጎልጎታ ፡ ድረስ ፡ ሳት ደክም ፡ ይቅርታውና ፡ በረከቱን ፡ ከልብህ ፡ ውስጥ ፡ ታገኘዋለህ ፡ ዘፍ ፡ ፴፪ ፡ ፳፬ ፤ ፳፱ ። ዘዳ ፤ ፬ ፳፱—፴፯ ። ስለምትለው ።

አንተ ፡ አንድ ፡ አስመስለህ ፡ ትጠራቸዋለህ ፡ እንጂ ፡ ንስሐና ፡ ኃዘን ፡ ልቅሶ ፡ እየራሱ ፡ ናቸው ፤ ንስሐ ፡ ማለት ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ መጠጠትና ፡ ለመምህረ ፡ ንስሐ - ኃጢአትን ፡ አምኖ ፡ ነግሮ ፡ ቀኖና ፡ መቀበል ፡ ነው ። ኃዘንና ፡ ልቅሶ ፡ ግን ፡ መምህረ ፡ ንስሐ ፡ ያዘዘውን ፡ ቀኖና ፡ እያዘኑ ፡ እያለቀሱ ፡ መፈጸም ፡ ነው ።

፪ የክርስቶስ ፡ ወይም ፡ የሰይጣን ፡ ማኅደር ፡ መኾንህን ፡ ስልብህ ፡ በልብህ ፡ አንተ ፡ እራስህ መር ምረው ፡ መዝነው ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ ፍጡራን ፡ እንኳንና ፡ ቄስ ፡ ጳጳስም ፤ ቢኾን ፡ ምንና ፡ ማንነትህን ፡ አያውቁትም ፡ ምንም ፡ አንተ ፡ ሳታውቅ ፡ ይፍቱኝ ፡ ብትላቸው ፡ እኔ ፡ አልችልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍ ታህ ፡ ይለሃልና ፡ አሣሪና ፡ ፈቺ ፡ ማን ፡ እንደኾነ ፡ አስተውል ። ስለምትለው ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ እንዳልኾነ ፡ ታውቅ ፡ ትረዳ ፡ ዘንድ ፤ በደብረ ፡ ሲና ፡ ለሙሴ ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ሲሠራ ፤ ነፍስ ፡ ለእመ ፡ አበሰት ፡ ያስተሥሪ ፡ ላቲ ፡ ካህን ። ነፍስ ፡ ሳታውቅ ፡ ብትተላለፍ ፡ ብትበ ድል ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ የተከለከለውን ፡ ብታደርግ ፡ ያለእውቀትም ፡ ቢኾን ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነውና ፤ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ዳንግሌ ፡ ለካህኑ ፡ ያቅርብ ፡ ካህኑም ፡ ያስተሥርይለት ፡ ብሏል ። ዘሌዋ ፡ ፬ ፡ ፩-፳፩ ፡ ፳፯-፴፪ ፡ ፴፭ ። ፭ ፭-፯ ፲፱ ።

ይህንም ፡ የኦሪቱን ፡ ሥራት ፡ ኦሪት ፡ ለወንጌል ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ በለ ከነት ፤ ዘለዓለምን ፡ ባዳነ ፡ ጊዜ ፡ ሐር ፡ ወአፍትን ፡ ርእሰከ ፡ ለካህን ።

www.ethiopianorthodox.org

ሔደህ ፡ ራስህን ፡ ለካህን ፡ አስመርምር ፡ ብሎ ፡ አጸናው ፡ እንጂ ፡ አልሻረውም ። ማቴ ፡ ፰ ፡ ፩-፭ ። ማር ፡ ፩ ፡ ፵-፵፬ ። ሉቃ ፡ ፭ ፡ ፲፪-፲፬ ።

በሚያርግበትም ፡ ጊዜ ፡ አብ ፡ እኔን ፡ እንደላከኝ ፡ እኔም ፡ እናንተን ፡ እልካችኋለሁ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ላላችኋቸው ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአታቸው ፡ ይሠረይላቸዋል ፤ ይቅር ፡ ላላላችኋቸው ፡ ግን ፡ ኃጢአታቸው ፡ አይሠረይላቸውም ፡ ብሎ ፡ በንፍሐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአናጕንስጢስነት ፡ እስከ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ያለውን ፡ ማዓርግ ፡ ሾማቸው ፡ ዐረገ ።

ይህንም ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ያዕቆብ ፡ ወእመበ ፡ ዘይደዊ ፡ እምኔክሙ ፡ ለይጸውዕ ፡ ቀሳውስተ ፡ እለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይጸልዩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይቅብዕዎ ፡ ቅብዐ ፡ ጸሎት ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ። ወጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ ያሐይዎ ፡ ለድውይ ፡ ወያነሥኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእመኒ ፡ ቦቱ ፡ ኃጢአት ፡ ይትኀደግ ፡ ሎቱ ፡ ተአመኑ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ኃጢአተክሙ ፡ ወጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ ቢጽክሙ ፡ ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ ብዙኀ ፡ ትረድእ ፡ ጸሎቱ ፡ ለጻድቅ ፡ ትክል ፡ ወታሠልጥ ።

የሃይማኖት ፡ ጸሎት ፡ ድውዩን ፡ ትፈውሰዋለች ፤ ጌታም ፡ ያስነሣዋል ፤ ኃጢአትም ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ኾነ ፡ ትሠረይለታለች ፤ ኃጢአታችሁን ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተናዘዙ ፤ አንዱም ፡ ላንዱ ፡ ይጸልይለት ፡ እንድትፈወሱ ፤ የጻድቅ ፡ ሰው ፡ ጸሎቱ ፡ ታላቅ ፡ ኃይል ፡ ልታደርግ ፡ ትችላለችና ፡ ብሏል ፡ ያዕ ፡ ፭ ፲፬-፲፯ ።

፫ ፡ አባቶቻችን ፡ ዳዊት ፡ በስሕተቱ ፡ ምናሴ ፡ በኃጢአቱ ፡ ጴጥሮስ ፡ በክህደቱ ፡ ለከ ፡ ለባሕቲትከ ፡ አበስኩ ፡ ብለው ፡ ወደርሱ ፡ ቢያለቅሱ ፡ መራራ ፡ ኃዘናቸውንና ፡ ፈሳሽ ፡ ዕንባቸውን ፡ አይቶ ፡ ራርቶ ፡ ሥርየት ፡ ሰጣቸው ፡ እንጂ ፡ በመልአክ ፡ ወይም ፡ በጻድቃን ፡ በፍጡር ፡ አማላጅ ፡ ቀለምና ፡ አልማራቸውም ፡ ስለምትለው ።

ዳዊት ፡ የዖርዮን ፡ ሚስቱን ፡ ቀምቶ ፡ በግፍዕ ፡ ባስገደለው ፡ ጊዜ ፡ በነቢዩ ፡ በናታን ፡ አማሃይነት ፡ ቀኖና ፡ ሰጠው ። ቀኖናውንም ፡ ሲፈጽም ፡ በናታን ፡ አማካይነት ፡ ይቅርታውን ፡ ልከለታል ፡ ሳሙ ፡ ካል ፡ ፲፪ ፡ ፩-፲፬ ።

፪ተኛም ፡ እስራኤልን ፡ ባስቈጠረና ፡ ፫ት ፡ ነገሮች ፡ በታዘዙበት ፡ ጊዜ ፡ በጋድ ፡ አማካይነት ፡ ቍጣውንም ፡ ይቅርታውንም ፡ አግኝቷል ፡ ሳሙ ፡ ካል ፡ ፳፬ ፡ ፲፩-፳ ።

ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ጌታን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ከካደው ፡ በኋላ ፡ ዶሮ ፡ ሲጮህ ፡ ጌታ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ቢያየው ፡ ፫ጊዜ ፡ ትክደኛለህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ ደነገጠና ፡ መሪር ፡ ልቅሶ ፡ አለቀሰ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፷፩ ። ስለዚህ ፡ ቀኖናውን ፡ ከሊቀ ፡ ካህናት ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተቀብሏልና ፡ ሌላ ፡ ካህን ፡ አላሻውም ።

፬ ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ለቄስ ፡ ፡ ንገሩ ፡ አላላቸውም ፡ ስለምትለው ።

ኃጢአትን ፡ ለቄስ ፡ መንገር ፡ አገባብ ፡ መኾኑን ፡ ... ቍጥር ፡ ዘርዝሬልሃለሁ ፡ ከዚህም ፡ ኹለት ፡ ቃላት ፡ አስታውስሃለሁ ።



(ሀ) አቤሜሌክ ፡ ንጉሠ ፡ ጌራራ ፡ ሣራን ፡ የአብርሃምን ፡ ሚስት ፡ በወሰደ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በግሩም ፡ ራእይ ፡ ታይቶ ፡ ሴቲቱንም ፡ ለባሏ ፡ መልስ ፡ ላንተም ፡ አብርሃም ፡ ይጸልይልህ ፡ ትድናለህ ፡ ብሎታል ፡ ዘፍ ፡ ፳ ፡ ፩-፲፯ ።

(ለ) ኢዮብ ፡ ከደዌው ፡ በተፈወሰ ፡ ጊዜ ፡ ኤልፋዝን ፡ በልዳዶን ሶፋርን ፡ ስለእኔ ፡ እንደ ፡ በሪያዬ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አልተናገራችሁምና ፡ በሪያዬ ፡ ኢዮብ ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዋላችሁ ፡ ይጸልያላችሁ ፡ ብሏቸዋል ፡ ኢዮ ፡ ፵፪ ፡ ፯—፲ ።

እግዚአብሔር ፡ ለአቤሜሌክና ፡ ለነኤልፋዝ ፡ ከተገለጸላቸው ፤ ቃል ፡ ለቃል ፡ ከተነጋገራቸው ፡ በኋላ ፡ አብርሃም ፡ ኢዮብ ፡ ይጸልዩላችሁ ፡ ከማለቱ ፡ በነርሱ ፡ ጸሎት ፡ ይቅር ፡ ቢላቸው ፡ ቅርብ ፡ ነገር ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝብ ፡ ለካህን ፤ ኃጥእ ፡ ለጻድቅ ፡ ኃጢአትን ፡ መንገር ፡ እነሱም ፡ ሊጸልዩላቸው ፡ እንዲገባ ፡ ለማስረዳት ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ንገሩና ፡ ይጸልዩላችሁ ፡ እንዳላቸው ፡ አስተውል ።

፭ ፡ ኢሳይያስ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ለማዳን ፡ ዐጭር ፡ አይደለችም ፡ ጆሮውም ፡ ከመስማት ፡ አልደነቆረችም ፡ ይለዋልና ፡ ስለዚህ ፡ በገዛ ፡ እጅህ ፡ አስፈላጊህን ፡ ለርሱ ፡ መንገር ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ ሰማ ፡ በለው ፡ አይፈልግም ፡ ስለምትለው ።

አንተ ፡ ማስመሰልና ፡ ማጭበርበር ፡ ልማድህ ፡ ስለኾነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጁ ፡ ከማዳን ፡ ዐጭር ፡ ናት ፡ ጆሮውም ፡ ከመስማት ፡ የደነቆረች ፡ ናትና ፡ በስማ ፡ በለው ፡ ንገሩልን ፡ ብለን ፡ ለቀሳውስት ፡ ኃጢአታችንን ፡ የምንናገር ፡ አስመስለህ ፡ ትናገራለህ ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ሒር ፡ ወአፍትን ፡ ርእሰከ ፡ ለካህን ፡ ብሎ ፡ ያዘዘንን ፡ ከመፈጸም ፡ በቀር ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ አደለም ።

ይኸውም ፡ ቀሳውስት ፡ ይፍቱኝ ፡ ባሏቸው ፡ ጊዜ ፡ ፈትንሃል ፡ ሳይሉ ፡ ኃይልን ፡ ሥልጣንን ፡ ክሂልን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ሰጥተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍታ ፡ በማለታቸው ፡ ይታወቃል ።

፮ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለህ ፡ የምትጽፋቸው ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ ቅዱሳን ፡ አያማልዱም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ ባለፉት ፡ አንቀጾች ፡ የሰጠሁህን ፡ መልስ ፡ ተመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

## ስለ ፡ መምረጥ ።

፩ ፡ አንባቢና ፡ ሰሚ ፡ ሆይ ፡ ስለአማላጅነት ፡ ነገር ፡ ደግሜ ፡ ደጋግሜ ፡ ልነግርህ ፡ ግድ ፡ ኾነብኝ ፡ ቢኾንም ፤ ለጠቢብስ ፡ እሐቲ ፡ ቃል ፡ ትበቍዖ ፡ የሚባለውን ፡ ምሳሌ ፡ እያሰብክ ፡ ሲነግሩህ ፡ መላ ፡ ጨምር ፡ ስለምትለው ።

የማይሰማ ፡ መቸም ፡ አይሰማ ፤ ለሚሰማስ ፡ ጥቂት ፡ ቃል ፡ እንድትበቃው ፡ ካወቅህ ፡ አንዱን ፡ ቃል ፡ በመመላለስ ፡ ለምን ፡ ደከምክ ፤ ሰውንስ ፡ ለምን ፡ አደከምክ ፤ ያሰኛል ። ደግሞ ፡ በነገሩ ፡ መላ ፡ ብንጨምርበትስ ፡ እግዚአብ

www.ethiopianorthodox.org

ሔር ፡ ለምን ፡ ጾማችሁ ፤ ለምን ፡ በጻድቃን ፡ ስም ፡ ለተራብ ፡ አበላችሁ ፡ ብሎ ፡ ይፈርድብን ፡ ይኾናል ፡ ብለን ፡ እንሰጋ ፡ ይኾን ? ይህ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ይመስላልን ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከኾነስ ፡ አንተ ፡ በሥራህ ፡ ኹሉ ፡ ልብላ ፡ በማለት ፡ ላይ ፡ ልጹምን ፤ ላድልብ ፡ ላኑር ፡ በማለት ፡ ልመጽውት ፡ እያልክ ፡ መላ ፡ ብትጨምርበት ፡ መልካም ፡ ነበረ ።

፸ ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ በጌታ ፡ የሚሞቱ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ምግባራቸውም ፤ ትከተላቸዋለች ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ትፈድዮ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ፡ ብለዋልና ፡ አንተም ፡ ዛሬ ፡ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ቡሩካኑ ፡ ለአቡየ ፡ ትረሱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዘድልው ፡ ለክሙ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ የሚያሰኝህ ፡ እውነተኛውን ፡ የክርስቲያን ፡ ምግባር ፡ መርጠህ ፡ መያዝና ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልግሃል ፡ እንጂ ፡ ስንቅህን ፡ ወደፊት ፡ ካላሳለፍክ ፡ ኋላ ፡ የተውሶ ፡ ጽድቅ ፡ ከቶ ፡ አታገኝም ፡ ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፩ ፵ ። መክ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ስለምትለው ።

እኛ ፡ በበኩላችን ፡ ጌታ ፡ በወንጌለ ፡ ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፱ - ፲፱ ፡ ይህ ፡ ገንዘባችሁ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ነዳያን ፡ በቤታቸው ፡ በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ይቀበሏችሁ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ በኃላፊው ፡ ገንዘባችሁ ፡ ወዳጅ ፡ አድርጓቸው ፡ ባለን ፡ መሠረት ፤ የጌታችንና ፡ የእመቤታችንን ፤ የወዳጆቹ ፡ የቅዱሳንንና ፡ የሞቱ ፡ ዘመዶቻችንን ፡ ስም ፤ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ዝክር ፤ ማኅበር ፤ ተዝካረ ፤ ሰንበት ፤ ተዝካረ ፡ ሙታን ፤ እያልን ፡ በየምክንያቱ ፡ እየደገስን ፡ ለነዳያን ፡ ማብላት ፡ ማጠጣትን ፡ ሕግ ፡ አድርገን ፡ እንሠራዋለን ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የተነቀፈ ፡ ነገር ፡ ነው ።

፸ተኛም ፡ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ለኹለት ፡ ጌታ ፡ ሊገዛ ፡ አይችልም ፤ እናንተም ፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ለገንዘብ ፡ መገዛት ፡ አትችሉም ፡ ባለን ፡ መሠረት ፡ ሸጦ ፡ ለውጦ ፡ መጽውቶ ፡ መመነን ፡ ጠቃሚ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እናስተምራለን ፡ የተቻላቸውም ፡ ሲፈጽሙት ፡ ይታያሉ ፡ ስንቀ ፡ ነፍስ ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ከኃጢአት ፡ ገብቶ ፡ የሚቈጠር ፡ ኾኗል ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ አስቀድመን ፡ እንደናሳለፈው ፡ የምታሳስበን ፡ ስንቀ ፡ ነፍስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ? ዝክር ፤ ተዝካር ፤ ጾም ፤ ትሕርምት ፤ ምናኔ ፤ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማይወደው ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፤ ሕግ ፡ ነው ፤ ድኅነት ፡ በጸጋው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ምግባር ፡ አያሻም ፡ እያሉ ፡ እያማሃኙ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ብቻን ፡ መብላትና ፡ መወፈር ፡ ነው ፡ ይኾን ፡ ? እስኪ እባክህ ፡ ንገረኝ ።

፸፩ እውነተኛው ፡ መድኃኒት ፡ ነፍስ ፡ የኾነ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዛሬ ፡ መርጠህ ፡ ያዝ ፡ ናሁ ፡ ሜምኩ ፡ ቅድሜከ ፡ ሕይወተ ፡ ወሞተ ፡ ወኀረያ ፡ ለከ ፡ ለሕይወት ፡ ከመ ፡ ትሕየው ፡ አንተ ፡ ወዘርዕከ ፡ ብሏልና ፡ ዘዳ ፡ ፴፲፱ ፡ ምሳ ፡ ፩ ፡ ፯—፴፫ ፡ መዝ ፡ ፵፱ ፡ ፯ ፡—፳ ፡ ኤር ፡ ፴፫ ፡ ፲፮ ። ስለምትለው ።

እኛስ ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምረን ፡ ከዓለም ፡ ኹሉ ፡ በፊት ፡ ለእስራኤል ፡ ተከታይ ፡ ኾነን ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፤ ከሕገ ፡ ጣዖት ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅን ፡ መርጠን ፡ ነበረ ። ዛሬም ፡ በዘመነ ፡ ሥጋዌ ፡ ከሕገ ፡ ርትዕ ፡ ከኦሪት ፡ ሕገ ፡ ትሩፋት ፡ ወንጌልን ፤ ከሕገ ፡ ግዝረት ፡ ሕገ ፡ ጥምቀትን ፤ ከመብል ፡ ከመጠጥ ፡ ጾምን ፤ ትሕርምትን ፤ ገንዘብን ፡ ከማድለብ ፤ ምጽዋትን ፡ በጠቅላላው ፡ የትሩፋትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ መርጠን ፡ ሕግ ፡ አድርገን ፡ ይዘናል ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ በዚህ ፡ የሚለወጥ ፡ ሕግ ፡ አያሻንም ፡ ከዚህ ፡ የቀረው ፡ ... ያው ፡ ስለኾነ ፡ መልስ አያሻውም ።



## ምዕራፍ ፲፱ ።

## እውነተኛው ፡ የሚያድን ፡ ተስፋ ።

፩ ምንመን ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ ለአዳም ፡ ሕግ ፡ አቁሞለት ፡ ነበረ ፡ በዲያብሎስ ፡ ስሕተትና ፡ በሥጋ ፡ ደካማነት ፡ ተሸንፎ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ተቀብሎ ፡ ነበረ ። ለዚሁ ፡ አዳም ፡ ላፈረሰው ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ውል ፡ ግን ፡ በአምላክና ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ኹለቱን ፡ ለማስታረቅና ፡ የፈረሰውንም ፡ ሕግ ፡ እንደገና ፡ ለማደስ ፡ የአዳምንም ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ ከአምላኩ ፡ ጋራ ፡ በመዋሐድ ፡ የተቻለው ፡ ከሰማይ ፡ የወረደውና ፡ ከድንግል ፡ ተወልደ ፡ ሰው ፡ የኾነው ፡ አንዱ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፭ ። ስለምትለው ።

አንተ ፡ ከልቡናህ ፡ እየፈጠርክ ፡ ደሙን ፡ አፍሶ ፡ ስለአዳም ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ ክሶ ፡ ያስታረቀ ፡ ሌላ ፡ አለ ፡ የምንል ፡ እያስመሰልክ ፡ ትናገራለህ ፡ እንጂ ፤ እኛም ፡ እንዲሁ ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀር ፡ ከበቱ ፡ ያስታረቀን ፡ ለእኛ ፡ ቤዛ ፡ የሞተ ፡ ሌላ ፡ አለ ፡ አንልም ፤ ለቤዛ ፡ ዓለም ፡ የሞተ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፪ አንዳንድ ፡ ማኅበሮች ፡ አንተ ፡ ኰኵሕ ፡ የሚለውን ፡ ንባብ ፡ ይዘው ፡ ኰኵሕነትን ፡ ለጴጥሮስ ፡ እየሰጡ ፡ በጴጥሮስ ፡ ድኅነት ፡ ነፍስ ፡ እናገኛለን ፡ እያሉ ፡ እንደሚቀላውጡ ፡ አለትነት ፡ እንደኛ ፡ ከጭቃ ፡ ለተፈጠረው ፡ ለምውቱ ፡ ለጴጥሮስ ፡ አንሰጥም ። ስለምትለው ።

ኰኵሕነትን ፡ ለጴጥሮስ ፡ የሰጠው ፡ ገና ፡ በጥንቱ ፡ ስብከት ፡ አንትኑ ፡ ስምዖን ፡ ወልደ ፡ ዮና ፤ አንተኬ ፡ ትሰመይ ፡ ኬፋ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ጴጥሮስ ። የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ? አንተም ፡ ኬፋ ፡ ትባላለህ ፡ ትርጓሜውም ፡ ጴጥሮስ ፡ (ሕንፃ) ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያወጣለት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ኋላም ፡ በፍኖተ ፡ ቂሣርያ ፤ ሰው ፡ ማን ፡ ይለኛል ፡ ብሎ ፡ በጠየቃቸው ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ ሐዋርያት ፡ ዮሐንስ ፡ ነህ ፡ ይሉሃል ፤ ኤርምያስ ፡ ነው ፡ ይሉሃል ፤ እያሉ ፡ ሲሳሳቱ ፤ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ መሲሕ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ አምላክነቱን ፡ ስለመሰከረ ፡ ጌታ ፤ የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፤ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ የሰማይ ፡ አባቴ ፡ ገለጸልህ ፡ እንጂ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ መምህር ፡ አልገለጸልህምና ፡ አንተ ፡ ብፁዕ ፡ ነህ ፤ እኔም ፡ ኰኵሕ ፡ ብየሃለሁ ፡ በዚህችም ፡ ኰኵሕ ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኔን ፡ እሠራታለሁ ፡ የገሃነም ፡ በሮች ፡ አይጐለብቱባትም ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያትንም ፡ መክፈቻ ፡ እሰጥሃለሁና ፡ በምድር ፡ ያሠርከው ፡ በሰማይ ፡ የታሠረ ፡ ይኹን ፤ በምድር ፡ የፈታሃውም ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ እንደሾመው ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ነግሮናል ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫—፳፩ ።

በዚች ፡ ደንጋያ ፡ ላይ ፡ ቤተ ክርስቲያኔን ፡ አንጻታለሁ ፡ ብሎ ፡ የተናገረውንም ፡ ቃል ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ በጥብርያዶስ ፡ ለሐዋርያት ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ ለይቶ ፡ ረዐይኬ ፡ አባግዕየ ፤ ረዐይኬ ፡ መሐስዕየ ፡ ረዐይኬ ፡ አባግዕትየ ።

ወገኖቼ ፡ ምእመናንን ፡ ጠብቅ ፡ ብሎ ፡ በመሾሙ ፡ አጽንቶታል ፡ ።

አንተ ፡ ይህን ፡ አልፈህ ፡ እንደኛ ፡ ከጭቃ ፡ ለተፈጠረው ፡ ለምውቱ ፡ ለጴጥሮስ ፡ አንሰጥም ፡ ትል ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ደፈርክ ፤ ክርስቶስ ፡ የሾመውን ፡ አንተ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ልትሽር ፡ ትችላለህን ፡ ? የክርስቶስ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ኸንክን ፡ ትዕቢትህና ፡ ድፍረትህ ፡ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ አለፈብህ ፡ መዝ ፡ ፹፫ ፡ ፮–፲ ።

ከጭቃ ፡ ለተፈጠረ ፡ ለምውቴ ፡ ብለህ ፡ ትንቀው ፡ ዘንድስ ፡ ይህ ፡ ከጭቃ ፡ የተፈጠረው ፡ የእኛ ፡ ባሕርይ ፡ በተዋህዶተ ፡ መለኮት ፡ ምሉዕ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ ኸኖ ፡ በየማነ ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ እንደተቀመጠ ፡ አታውቅምን ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፳፪ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፳–፳፪ ፡ መዝ ፡ ፻፲ ፡ ፩ ፡ ዕብ ፡ ፩–፲፬ ።

ዳሩ ፡ ግና ፡ አንተ ፡ በመለኮቱ ፡ ማማለድ ፡ አለበት ፡ ባይ ፡ ነህና ፡ ይህን ፡ አታውቅም ፡ ይኸናል ።

፫ በጴጥሮስ ፡ ድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ እናገኛለን ። ይላሉ ፡ ስለምትለው ፡ ግን ፡ በጴጥሮስ ፡ በመምህርነቱ ፡ በስብከቱ ፡ በማላጅነቱ ፡ ሥርየት ፡ በማሰጠቱ ፡ ድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ እናገኛለን ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ በጴጥሮስ ፡ ካሳ ፡ በጴጥሮስ ፡ አስታራቂነት ፡ በጴጥሮስ ፡ ደም ፡ ዳን ፡ አንልም ።

፬ ኵኵሕ ፡ ቢኸንማ ፡ እንደፈከረው ፡ ይፈጽመው ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ መች ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ እየማለ ፡ ፈጣሪውን ፡ ይክድ ፡ ነበረ ። ስለምትለው ።

በዚህ ፡ አያያዝህስ ፡ ወደዚያኛው ፡ ዓለም ፡ በሔድክ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ ማን ፡ አስገባህ ፡ ብለህ ፡ ክንዱን ፡ ይዘህ ፡ የምታወርደው ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ ረዐይኬ ፡ አባግዕየ ፡ ብለህ ፡ ለምን ፡ ሾምከው ፡ ብለህ ፡ የምትወቅሰው ፡ መሰልክ ፡ እንጂ ፡ በጤና ፡ የምትለቃቸው ፡ አልመሰልክም ። በሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ላይ ፡ ለመናገር ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ስትደፍር ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ባንተ ፡ ስድብ ፡ ሊያዝኑ ፡ ሊቈረቈሩ ፡ አይገባም ።

፭ ፔትራ ፡ ደንጋያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ስን ፡ ሲቀጥል ፡ ግን ፡ በጽርዕ ፡ ቃል ፡ ፔትሮስ ፡ የደንጊያ ፡ ነህ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ደንጊያ ፡ ነህ ፡ ማለት ፡ እንዳልኸነ ፡ ሊቃውንት ፡ አስረድተውናል ፡ ስለምትለው ።

እኛ ፡ ሊቃውንት ፡ ብለን ፡ የምንቀበላቸው ፡ በአንቀጸ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደዘረርኩልህ ፡ በሐዋርያት ፡ ያደረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከሐዋርያት ፡ ተያይዞ ፡ እንደ ፡ ፍግ ፡ እሳት ፡ ሳይለያቸው በእሳተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተናደዱ ፡ ብሉያትንና ፡ ሐዲሳትን ፡ የረቀቀውን ፡ አጕልተው ፡ የተሰወረውን ፡ ገልጸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍትንና ፡ ሃይማኖት ፡ አበውን ፡ የጻፉልን ፡ እነአግናጥዮስ ፡ ምጥው ፡ ለአንበሳ ፤ እነአትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፤ እነዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ እነቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፤ ፫፻ት ፤ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

እነርሱ ፡ በጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ የሚያስተባብል ፤ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያትነትን ፡ የሚቃወም ፤ ለተነሳሒያን ፡ አብነት ፡ የኾነበትን ፡ ግብር ፡ ጠቅሶ ፡ ከሀዲ ፡ ብሎ ፡ የሚሰድብ ፡ አንድ ፡ አይገኝም ።

አንተ ፡ የሊቅነትን ፡ ጣዕም ፡ ስለማታውቅ ፡ ኹሉ ፡ ሊቅ ፡ ይመስልሃልና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሊቅ ፡ የሚባል ፡ ከብሉያት ፡ ከሐዲሳት ፡ ግብ ፡ ሳይወጣ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ የወጣስ ፡ መናፍቅ ፡ ከሀዲ ፡ ከመባል ፡ በቀር ፡ ሊቅ ፡ አይባልም ።

በዚያውስ ፡ ላይ ፡ በ፺ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ ብለህ ፡ በጻፍከው ፡ በ፵፰ተኛው ፡ ገጽ ፡ የሐዋርያት ፡ [illegible]



ሐፍ ፡ ትምርትና ፡ ሃይማኖት ፡ እንኳንና ፡ ሰዎች ፡ መላእክትም ፡ ቢኾኑ ፡ ቢነግሩን ፡ ቢያስተምሩን ፡ እንዳንቀበላቸው ፡ ጳውሎስ ፡ ወግዞናል ፡ ያልከውን ፡ ረስተኸው ፡ ነውን ፤ ወይንስ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ፔትሮስ ፡ ማለት ፡ የደንጋያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ደንጋያ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ተረጕመልህ ፡ ከምን ፡ አመጣሃው ፡ እስኪ ፡ ንገረኝ ።

እኛስ ፡ ቀድሞ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፤ ኋላም ፡ በፍኖተ ፡ ቂሣርያ ፤ ፫ተኛም ፡ በጥብርያዶስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መላልሶ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ የሚለውጠውን ፡ ስሑት ፡ መናፍቅ ፡ እንለዋለን ፡ እንጂ ፡ ሊቅ ፡ ብለን ፡ አንቀበለውም ።

፮ ፡ ከዚህ ፡ የቀረው ፡ ጽሑፍህ ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ መልስ ፡ የተሰጠበት ፡ ስለኾነ ፡ ያነኑ ፡ ተመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡

## ስለ ፡ ማሠርና ፡ መፍታት ።

፩ ዘአሠርክሙ ፡ በምድር ፡ ይከውን ፡ ዕሡረ ፡ በሰማያት ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰–፲፰ ፡ ማሠርና ፡ መፍታት ፡ ማለት ፡ ለንጹሐን ፡ ሐዋርያት ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ ይህንኑ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣን ፡ ግን ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ሠሩትና ፡ እንዳስተማሩት ፡ ድውይ ፡ እየፈወሱ ፡ ምውት ፡ እያነሡ ፡ ፊት ፡ እነርሱ ፡ ሕግ ፡ ጠብቀው ፡ ንጹሐን ፡ ስለኾኑ ፡ በሕግ ፡ ለማይሔዱና ፡ ክርስቶስን ፡ ለሚክዱ ፡ ሰዎች ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሥጢራት ፡ ሊወገዱ ፡ ዛሬም ፡ አሠራቸውን ፡ ይዘው ፡ ለሚሔዱ ፡ ካህናት ፡ የተሰጠና ፡ የሚገባም ፡ ነው ፡ ስለምትለው ፡

ማሠርና ፡ መፍታት ፡ ለንጹሐን ፡ ሐዋርያትና ፡ ለተከታዮቻቸው ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ ማለትህ ፡ እውነትህ ፤ ሥልጣነ ፡ ክህነትን ፡ ለተቀበለ ፡ ኹሉ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ።

ድውይ ፡ እየፈወሱ ፡ ሙት ፡ እያነሡ ፡ ማለትህ ፡ ግን ፤ ውሸትህ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ክታቡ ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮባቸው ፡ ሳለ ፡ ገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ባይሰጣቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አላደረብንም ፡ መስሏቸው ፡ ስለተጠራጠሩ ፡ ወንድሞቻችን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ነገር ፡ አላዋቆች ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አንወድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሀብቱ ፡ ብዙ ፡ ስለኾነ ፡ ምሥጢረ ፡ መጻሕፍትን ፡ የማወቅ ፡ ሀብት ፡ የሚሰጠው ፡ አለ ፤ ቋንቋ ፡ የመተርጐም ፡ ሀብት ፡ የሚሰጠው ፡ አለ ።

ድውይ ፡ የመፈወስ ፤ ጋኔን ፡ የማውጣት ፡ ሙት ፡ የማንሣት ፤ ሀብት ፡ የሚሰጠው ፡ አለ ፤ ብሎ ፡ ዘርዝሮ ፡ ዘርዝሮ ፡ እንደተናገረው ፡ በተለይ ፡ የሚሰጥ ፡ እድል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ለያዘ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የሚሰጥ ፡ አደለም ፩ ቆሮ ፲፪ ፩–፲፪ ።

፪ ፊተኞቹ ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታዮች ፡ ሐዋርያት ፡ ግን ፡ ለበደለና ፡ ለተሳሳተ ፡ እንኳንና ፡ ወግዘው ፡ አሥረው ፡ ከማኅበር ፡ ሊለዩ ፡ ታግሠው ፡ በእውቀትና ርኅራኄ ፡ በፍቅር ፡ አስተምረው ፡ አስረድተው ፡ እንዲድኑልን ፡ በማለት ፡ ከኹሉ ፡ ሰው ፡ ጋራ እንደርሱ ፡ ኾነ ፡ እያሉ ደንግፀው ፡ ይመልሷቸው ፡ ስለነበሩ ፡ ብለህ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፱ ፳–፳፫ ። ስለጠቀስከው ።

www.ethiopianorthodox.org

በ፪ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ጻድቃን ፡ የምንላቸው ፡ ሐዋርያት ፡ አንድ ፡ ሌሊት ፡ እንግድነት ፡ አናሳድራችሁም ፡ ቢሏቸው ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ አውርደን ፡ እናቃጥላቸው ፡ አሉ ፡ ብለህ ፡ የነቀፍካቸውን ፡ እረስተህ ፡ እንዲህ ፡ ትላለህ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ብዙዎችን ፡ ወደኔ ፡ ሃይማኖት ፡ እመልሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ከኹሉ ፡ ነፃ ፡ ስኾን ፡ ለኹሉ ፡ ተገዛሁ ፤ አይሁድን ፡ ወደእኔ ፡ ሃይማኖት ፡ እመልሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ለአይሁድ ፡ እንደ ፡ አይሁዳዊ ፡ ኾንኩላቸው ፤ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ያሉትንም ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ እመልሳቸው ፡ ዘንድ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ እንዳለሁ ፡ ኾንኩላቸው ፡ ሕግ ፡ ለሌላቸውም ፡ ሰዎች ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጋሁ ፡ ሳልኾን ፡ ሕግ ፡ እንደሌለው ፡ ሰው ፤ ኾንኩላቸው ፡ ማለቱ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ያላመኑትን ፡ በፍቅር ፡ ለመሳብ ፡ በወንጌል ፡ ለማሳመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወንጌልን ፡ አምነው ፡ ከተቀበሉ ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ ከሥራዋ ፡ ሳይገኙ ፡ ክርስቲያንነን ፡ እያሉ ፡ ለሚዘብቱ ፡ አደለም ።

እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ ሳይኾኑ ፡ ነን ፡ እያሉ ፡ የሚያላግጡትንስ ፡ ኀይላቸውን ፡ ይገልጹብቻዋል ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በሐናንያና ፡ በሚስቱ ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ በብራየሱስ ፡ ያደረጉትን ፡ ተመልከት ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፩–፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፯—፲፫ ።

ለተከታዮቻቸውም ፡ አንገሊገክሙ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መጠውዎ ፤ ለሰይጣን ፡ እያሉ ፡ ሥርዓት ፡ ሠርተዋል ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፬ ።

፫ ኹሉም ፡ አማኞች ፡ ባንዲት ፡ ልብና ፡ እንዳንዲት ፡ ነፍስ ፡ ነበሩ ፡ የሐዋ ፡ ፬ ፡ ፴፪ ፡ እናንባለን ፡ እንጂ ፡ ፲፪ ፡ አይነት ፡ ሰምና ፡ ማኅበር ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡ የሚል ፡ ባንድ ፡ ጽሕፈት ፡ ከቶ ፡ አይገኝም ፡ ስለምትለው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳለ ፡ ፻፳ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችን ፡ ርሱ ፡ ከረገ ፡ በኋላም ፡ ፫ሺህ ፡ ማኅበረ ፡ እስጢፋኖስ ፡ እንዳንድ ልብ ፡ መከሬ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ታናጋሪ ፡ ኾነው ፡ ኖረዋል ። በሞተ ፡ እስጢፋኖስም ፡ በየሀገሩ ፡ ቢበታተኑ ፡ የልብ ፡ አንድነታቸው ፡ ምንም ፡ አልተናወጠም ፡ ነበረ ።

ከ፩ሺ ፡ ፬፻ ፡ ፵፯ ፡ ዓ ም በኋላ ፡ ግን ፡ ከ፲፪ ፡ ዓይነት ፡ የበለጠ ፡ ስምና ፡ ማኅበር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ የወረደበትእ ፡ ምክንያት ልዩ ፡ ዶብዳቤ ፡ ብለህ ፡ በጻፍከው ፤ በ፫ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በ፯ተኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌልሃለሁና ፡ ያነን ፡ ተመልክተህ ፡ ከክልል ፡ ውስጥ ፡ እንድትገባ ፡ አሳስብሃለሁ ።

፬ እንቢ ፡ ብለው ፡ ሥራቸውን ፡ ለማፍረስ ፡ ቢበድሏቸው ፡ እንኳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመልስላቸው ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ፡ ይሉ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ቢኾንም ፡ እንክርዳድ ፡ ኃጥእ ፡ ነህ ፡ ከማኅበራችን ፡ ውጣ ፡ ብለው ፡ ክርስቶስ ፡ ለሞተለት ፡ ኃጥእ ፡ መንጋ ፡ ወግዘው ፡ ለአርዌ ፡ አሳልፈው ፡ አልበጠሱም ፡ አባባረ ሩም ፡ ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፩—፲ ። ስለምትለው ።



ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ወንጌልን ፡ ሲያስተምር ፡ እለእስክንድሮስ ፡ የሚባል ፡ አንጥረኛ ፡ ወንጌልን ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ ቢቃወመው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ይክፈለው ፡ ማለቱ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ከራስጌው ፡ ተሰቅሎ ፡ የነበረው ፡ መዶሻ ፡ ወርዶ ፡ አናቱን ፡ በጥብጦ ፡ እንደ ፡ ገደለው ፡ በገድለ ፡ ሐዋርያት ፡ ተጽፎ ፡ እናነባለን ። አንተ ፡ ግን ፡ ያገዘማሪዎች ፡ ግጥምና ፡ የሚሾ ፡ አውጭዎች ፡ ልቅሶ ፡ ከልኾነ ፡ አልቀበለውም ፡ ሰትል ፡ አትቀርም ፡ ይኸናል ። በዚያውስ ፡ ላይ ፡ እንክርዳድ ፡ ነህና ፡ ከማኅበራችን ፡ ውጣ ፡ አይሉትም ፡ ትል ፡ ዘንድማ ፡ ይሁዳ ፤ ከሐዋርያት ፡ አንድነት ፡ እንደ ፡ ተለየ ፡ አርዮስ ፡ ከ፫፻ ፡ አንድነት ፤ ንስጥሮስ ፡ ከ፪፻ ፡ ሊቃውንት ፤ መቅዶንዮስ ፡ ከመቶ ፡ አምሳው ፡ ሊቃውንት ፡ አንድነት ፡ እንደ ፡ ተለዩ ፡ አልሰማህምን ? ካንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፤ ሦስት ፡ ጊዜ ተመክረው ፡ እንቢ ፡ ቃሉ ፡ ተወግዘው ፡ እንዲለዩ ፡ እወቅ ።

፭ ክርስቶስ ፡ የመጣበት ፡ አይነተኛ ፡ ጉዳዩ ፡ የተበተኑት ፡ በጎች ፡ አርዊ ፡ ዲያብሎስ ፡ እንዳይበላባት ፡ አዝኖ ፡ ካንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ነው ፡ ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፫ ፡ ፴፮ ፡ ስለምትለው ።

ክርስቶስ ፡ የመጣበት ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ መኾኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ዘቅ ፡ የለመዱ ፡ ከብቶች ፡ ቀን ፡ ሲበሉት ፡ የዋሉት ፡ አልበቃቸው ፡ ብሎ ፡ ሌሊት ፡ አጥር ፡ ሰብረው ፡ ወጥተው ፡ ላውሬ ፡ እንደሚኾኑት ፡ ኹሉ ፤ አንዳንድ ሰዎችም ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ተሸንፎ ፡ ጌታውን ፡ የሸጠ ፡ ይሁዳን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ለሆዳቸው ፡ ሲሉ ፡ ከሕገ ፡ ወንጌል ፡ ቅጽር ፡ ወጥተው ፡ ሲገኙ ፡ የዲያብሎስ ፡ ፈንታ ፡ መኾናቸው ፡ አይቀርም ። አታድርስ ! እንዲህ ፡ ከመኾን ፡ አድን ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይባላል ።

፮ የዛሬው ፡ ዘመናችን ፡ ሐዋርያት ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ እኛ ፡ የክርስቶስ ፡ ምስለኔዎች ፡ ስለኾነ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መክፈቻ ፡ በእጃችን ፡ ናት ፡ እኛ ፡ ፈርደን ፡ በምድር ፡ ካሠርነው በሰማይም ፡ ዕሡር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚመኩ ፡ በትዕቢት ፡ ጭቃና ፡ ትምክህት ፡ የተበኩ ፡ ወገነ ፡ ሠራዊትና ፡ መባዕን ፡ ለማብዛት ፡ የሥጋዊ ፡ ጥቅማቸውን ፡ ብቻ ፡ ለማግኘት ፡ እያታለሉ ፡ የሚሰብኩ ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ሞልተዋል ። ስም ፡ በመያዝ ብቻ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በግብራቸውስ ፡ እንኳንና ፡ የክርስቶስ ፡ ምስለኔዎች ፡ የሐዋርያት ፡ ተከታዮች ፡ ለመኾንም ፡ አልበቁም ።

እያልክ ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ መሥመሮች ፡ ሕጉን ፡ ሳይኾን ፡ ሰዎችን ፡ ለመንቀፍ ፡ ለመስደብ ፡ ብዙ ፡ ጽፈሃል ። እኔ ፡ መልስ ፡ የምሰጥህ ፡ ስለሃይማኖትና ፡ ስለምግባር ፡ ስለሕግ ፡ ብቻ እንጂ ፡ ስለ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ተግባር ፡ አደለም ። ስንኳንስ ፡ በማላውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ ተገብቸ ፡ ፈጸሙ ፡ አልፈጸሙም ፡ ብዬ ፡ መልስ ፡ ልሰጥ ፡ እኔንም ፡ ራሴን ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ነህ ብትለኝ ፡ አዎን ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነኝ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምሰጥህ ፡ መልስ ፡ የለኝም ፡ መዝ ፡ ፶፪ ፯ ።

፯ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ለሰው ፡ አፍዓውን ፡ አይቶ ፡ ኃጥእንና ፡ ጻድቅን ፡ ለይቶ ፡ ወግዞ ፡ ፈርዶ ፡ ከሠውነተኛው ፡ ጻድቅ ፡ ፈራጅ ፡ ልብና ፡ ኵላሊት ፡ የሚመረምር ፡ ምን ፡ ሊሠራ ፡ ነው ፡ ይኾን ፤ ፍርዱን ፡ ፍጡራኑ ፡ ከፈጸሙት ፡ ኃጥእና ፡ ጻድቅ ፡ ብለው ፡ ከለያዩ ፡ እርሱ ፡ ለፍርድ ፡ አይመጣም ፡ ለማለት ፡ እያዳግትም ፡ ስለምትለው ።

www.ethiopianorthodox.org

በ፩ኛው ፡ ቍጥር ፡ ማሠርና ፡ መፍታት ፡ ለካህናት ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ኾነ ፡ አረጋግጠህ ፡ የጻፍከውን ፡ ዘንግተህ ፤ ለማጭበርበር ፡ የሰውን ፡ መልኩን ፡ አይተው ፡ አንተ ፡ ኃጥእ ፡ ነህ ፡ አሥረንሃል ፤ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነህ ፡ ፈትንሃል ፡ የሚሉ ፡ አስመስለህ ፡ ትናገራለህ ፡ እንጂ ፤ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ አደለም ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ፲፰ ከ፲፭ ፡ እስከ ፡ ፳፫ ፡ ቍጥር ፡ እንደተናገረው ፡ ነው ።

፲፰ እርሱ ፡ ግን ፡ የማስናበቻ ፡ ቃሉ ፡ እነሆኝ ፡ ለኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣለሁ ፡ ዋጋዬም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ራእ ፡ ፳፪ ፡ ፱ ፲፫ ፡ ይህ ብቻ ፡ ነው ስለምትለው ።

በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ በፈቃደ ፡ ካህን ፡ በምክረ ፡ ካህን ፡ ጸንተው ፡ ለተገኙ ፡ ዋጋቸውን ፤ ለእንቢተኞች ፡ ፍዳቸውን ፤ መስጠት ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ አይካድም ። ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ በሃይማኖት ፡ ማጽናት ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ማሠራት ፡ እንቢተኞችን ፡ አውግዞ ፡ መለየት ፡ የመምህራን ፡ ሥራ ፡ ነው ።

፱ ይህንን ፡ እየተወጋገዙ ፡ ማሠርና ፡ መፍታት ፡ በከንቱ ፡ ነው ፡ ስል ፡ ግን ፡ ለምሳሌ ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ የሰውን ፡ ሥርዓትና ፡ የፍጡራን ፡ አማላጅነት ፡ ተባሕትዎና ፡ ምንኵስናም ፡ የሚሉት ፡ አንዘግዝጎ ፡ ጥሎ ፡ በምግባር ፡ ሳይኾንም ፡ በክርስቶስ ፤ እምነት ፡ ብቻ ፡ የሚገኘውን ፡ የጸጋ ፡ ድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ በድፍረት ፡ ስላስተማረ ፤ እምነትን ፡ ለመጽደቂያ ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ ለሃይማኖት ፡ መግለጫ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መስክሯል ፡ በሮማው ፡ ጳጳስ ፡ ሕግ ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እርሱና ፡ ተማሪዎቹ ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ ጽሉዓንና ፡ ውጉዛን ፡ ዕሡራን ፡ ናቸው ፤ እንዲሁም ፡ ልዮን ፡ የሮማው ፡ ጳጳስ ፡ በእስክንድርያው ፡ ጳጳስ ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ ሕግ ፡ ሥልጣን ፡ ውጉዝና ፡ ዕሡር ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

የዚህን ፡ መልስ ፡ በ፫ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ልዩ ፡ ደብዳቤ ፡ ብለህ ፡ በጻፍከው ፡ በ፯ ፡ ቍጥር ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሬ ፡ ስለጻፍኩልህ ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊ ፡ በ፲፭፻፲፱ ፡ ዓ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ተነሥቶ ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ ከ፫፻ት ፡ የተገኘውን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ሳይኾን ፡ በሕግ ፡ ሳይኾን ፡ በድፍረት ፡ አምዘግዝጎ ፡ መጣሉንና ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ፈቃዳችንን ፡ ኹሉ ፡ እንፈጽም ፡ የምትል ፤ ማነንም ፡ ደስ የምታሰኝ ፡ ሕግ ፡ ማቋቋሙን ፡ ገልጠህ ፡ በመናገርህ ፡ እያመሰገንኩ ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በኋላ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ማድረግን ፡ የሚወዱበት ፤ ኃይለ ፡ ጽድቅ ፡ ምግባርን ፡ ክደው ፡ ጻድቃን ፡ መስለው ፡ የሚታዩበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ።

ትምህርተ ፡ ሕይወት ፡ የሚገኝባት ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ ትተው ፡ ልቡናቸው ፡ በወደደው ፡ ይኖራሉ ፡ ብሎ ፡ ሰጢሞቴዎስ ፡ የነገረው ፡ ትንቢት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መፈጸሙን ፡ ከማስታውስህ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምሰጥህ ፡ መልስ ፡ የለኝም ። ፪ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩–፲ ፡ ፬ ፡ ፫–፭ ።

፲ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ እንደዚህ ፡ እያልኩኝ ፡ ስነግርህ ፡ ግን ፡ ወኢትሑሩ ፡ ውስተ ፡ አርዑተ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ዒኡ ፡ እማዕከሎሙ ፤ ወተፈለጡ ፡ እምኔሆሙ ። ፪ ቆር ፡ ፮ ፲፬–፲፰ ። አእትቱ ፡ እምላዕሌክሙ ፡ እኩየ ፡ ፩ቆሮ ፡ ፭ ፩–፲፫ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የረሳሁኝ ፡ አይምሰልህ ። ተለዩ ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡ ለክርስቶስ ፡ ከማያምንና ፡ የክርስቶስ ፡ ትምርት ፡ ያልኾነ ፡ ሌላ ፡ ትምርት ፡ የመሐመድ ፡ ቍርዓንን ፡ ከሚመስል ፡ ፈጠራ ፡ ተለዩ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ እንደመጣ ፡ ከሚያምን ፡ ወንድም ፡ ተለዩ ፡ አላለም ። ፩ ዮሐ ፡ ፬ ፩-፯ ፡ ፪ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ፡ ስለምትለው ።



፪ ቆሮ ፡ ፮ ፲፬–፲፰ ፡ የጠቀስከው ፡ ጌታ ፡ እስራኤልን ፡ ፯ቱን ፡ ነገሥተ ፡ ከነዓን ፡ አጥፍቶ ፡ ምድረ ፡ ርስትን ፡ ሲያወርሳቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ በእጅህ ፡ በጣላቸው ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመህ ፡ ፍጃቸው ፡ እንጂ ፡ አትማራቸው ። ልጆቻቸው ፤ ሴት ፡ ልጅህን ፡ ለወንድ ፡ ልጃቸው ፡ አታጋባ ፡ ወንድ ፡ ልጅህን ፡ ለሴት ፡ ልጃቸው ፡ ያለውን ፡ ጠቅሶ ፤ ዛሬም ፡ በሐዲስ ፡ ባላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ግብር ፡ አትኑሩ ፡ ማለቱ ፡ እርግጥ ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ አፍርሰኸው ፡ ምግባረ ፡ ወንጌልን ፡ ጨርሰህ ፡ ፍቀህ ፡ ጥለህ ፡ በአሕዛብ ፡ ግብር ፡ ትኖራለህ ። ዘዳግ ፡ ፯ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፩ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፩-፲፫ ፡ የጠቀስከውም ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ካመኑ ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ በምግባር ፡ ተሰነካከለው ፡ ዝሙት ፡ ስለሠሩ ፤ ዓረማውያን ፡ እንኳን ፡ የማይሠሩት ፡ ዝሙት ፡ ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የቀማ ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለ ፡ ይሰማል ። እንዲህ ፡ ያደረገውን ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ አለያችሁትም ፡ እንግዲህ ፡ ወደናንተ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ልመጣ ፡ ትወዳላችሁ ። አሁንም ፡ እንዲህ ፡ ያደረገውን ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ በሥጋዬ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ባልኖር ፡ በመንፈሴ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳለሁ ፡ ኾኜ ፡ እለየዋለሁና ፡ ጉባኤ ፡ አድርጋችሁ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡ ጸኛ ፡ አድርጋችሁ ፤ እኔም ፡ በመንፈስ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ አንዳለሁ ፡ አምናችሁ ፤ ቀሳውስ ዘንድ ፡ ለሰይጣን ፡ አሳልፋችሁ ፡ ስጡት ፡ (ማለት ፡) አውግዛችሁ ፡ ለዩት ፡ ያለ ፤ ከምግባር ፡ ያዳጠውን ፡ እንጂ ፡ ከሃይማኖት ፡ የተናወጠውን ፡ አደለምና ፡ ተለዩ ፡ ማለቱ ፡ እንዳንተ ፡ ካለ ፡ መስሎ ፡ ከሚስብ ፡ አታላይ ፡ መናፍቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሙሐመዳውያን ፡ አደለም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ አስቀድሜ ፡ ምሳሌውን ፡ እነግርሃለሁ ። መጀመሪያ ፡ በኦሪት ፡ የተሠራው ፡ ኹሉ ፡ ለወንጌል ፡ አምሳል ፡ መርገፍ ፡ መኾኑን ፡ እወቅ ።

በኦሪቱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለምጽ ፡ ቢወጣበት ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ወይም ፡ ከካህናቱ ፡ ወዳንዱ ፡ ይወስዱታል ። ካህኑም ፡ ከቤት ፡ አግብቶ ፡ ብቻውን ፡ ከሰው ፡ ለይቶ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ይጠብቀዋል ፤ ከ፯ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የዳነ ፡ እንደ ኾነ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከሕዝብ ፡ እንዲቀላቀል ፡ ይፈቅድለታል ።

ያልዳነ ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ ፪ ፡ ሱባኤ ፡ ፫ ፡ ሱባኤ ፡ ይጠብቀዋል ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ያልዳነ ፡ እንደኾነ ፡ ከሕዝብ ፡ ይለየዋል ፤ ከከተማ ፡ ያስወጣዋል ።

እንዲህም ፡ የሚያደርገው ፡ ጎንብርብሬ ፡ ለምጽ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ነው ። ጎንብርብሬም ፡ ማለት ፡ አልፎ ፡ አካል ፡ አልፎ ፡ ለምጽ ፡ ዝንጉርጉር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ምሥጢሩም ፡ ለምጹን ፡ በልብሱ ፡ ሰውሮ ፡ ደኅና ፡ መስሎ ፡ ሰው ፡ እንዳያበላሽ ፡ ደዌው ፡ እንዳይናኝ ፡ ነው ።

ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ ፍጹም ፡ ለምጽ ፡ ብቻ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ [illegible] ፡ በከተማ ፡ ይኖራል ። ስለምን ፤ ደዌው ፡ የታወቀ ፡ ግልጽ ፡ በመ

ኸኑ ፡ ሰው ፡ ይሸሸዋልና ፡ ማንንም ፡ ሊጎዳ ፡ አይችልም ፡ በማለት ፡ ነው ። ዘሌዋ ፡ ፲፫ ፡ ፩—፵፱ ።

ዛሬ ፡ በሐዲስ ፡ ግን ፡ በለምጽ ፡ ፈንታ ፡ ክህደት ፡ ኑፋቄ ፤ በለምጻሙ ፡ ሰው ፡ ፈንታ ፡ ከሐዲ ፡ መናፍቅ ፡ ተተክቶ ፡ ቀርቷል ።

ቀድሞ ፡ ፍጹም ፡ ለምጽ ፡ የኸነውን ፡ ሰው ፡ በከተማ ፡ ያኖሩት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ ዛሬም ፡ ወንጌልን ፡ ያልተቀበሉ ፡ መሐመዳውያንና ፡ ሌሎችም ፡ እነሱን ፡ የመሰሉት ፡ የታወቁ ፡ በመኾናቸው ፡ ምንም ፡ የማይጎዱ ፡ ስለኾኑ ፡ በውግዘት ፡ ተለዩ ፡ አይባሉም ፡ ከሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ይኖራሉ ።

ለምጹን ፡ ሰውሮ ፡ ሰው ፡ ይጎዳል ፡ ብለው ፡ ጎንብርብሬውን ፡ ለምጽ ፡ ይለዩት ፡ እንደነበረ ፡ ዛሬም ፡ ባፉ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብያለሁ ፤ በክርስቶስ ፡ አምኛለሁ ፡ እያለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ በመለኮቱ ፡ አእግዚአ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ ያማልድ ፡ ነበረ ፡ የሚል ፤ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ክህደት ፡ የሚናገር ፡ መናፍቅ ፤ መስሎ ፡ በማታለል ፡ ወደ ፡ ክህደቱ ፡ እንዳይስብ ፡ ተወግዞ ፡ የሚለይ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

በዚያውስ ፡ ላይ ፡ በአንደኛው ፡ ቍጥር ፡ በሕግ ፡ ለማይሔዱና ፡ ክርስቶስን ፡ ለሚክዱ ፡ ሰዎች ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሥጢራት ፡ ሊወግዱ ፡ ለካህናት ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ነበረ ፡ መሐመዳውያን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሥጢራት ፡ በምን ፡ በኩል ፤ ይሳተፋሉና ፡ ነው ፡ የሚወገዙ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ፡ የምትል ። የምትወገዝ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንጂ ፡ እነርሱ ፡ አደሉም ።

፲፩ ያንዱን ፡ ሰው ፡ ሐሳብና ፡ ትርጓሜ ክንዱ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ማይስማማ ፡ አስቀድሞ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ከመፍረድ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መፍረድ ፡ ይገባዋል ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ ብንፈርድ ፡ ባልተፈረደብንም ፡ ነበረ ። ፩ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፴፩ ። እንዳይፈረድባችሁ ፡ አትፍረዱ ፡ ማቴ ፡ ፯፩—፭ ስለምትለው ።

መጻሕፍት ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ሌላውን ፡ ልትነቅፍባቸው ፡ ልትሰድብባቸው ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ልትሠራቸው ፡ ልትፈጽማቸው ፡ አልተጻፉም ፡ ይኸን ፤ ይህን ፡ ካወቅህ ፡ ካቅምህ ፡ በላይ ፡ ተንጠራርተህ ፡ በሰማይ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክትን ፤ በምድር ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታትን ፤ በጠቅላላው ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለምን ፡ ነቀፍክ ፤ ለምን ፡ ሰደብክ ፤ እየው ፡ አንተ ፡ አስቀድመህ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ባትጽፍ ፡ ይህ ፡ መልስ ፡ ባልተሰጠህም ፡ ነበረ ።

የምታነባቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ለመመርመርና ፡ ለማወቅ ፡ አውቀህ ፡ ለመሥራትና ፡ ለመጠቀም ፡ ያብቃህ ፡ አንባቢ ፡ ኸኖ ፡ ከመቅረት ፡ ያድንህ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

## ስለ ፡ መድኃኒትነቱ ።

፩ በኃጢአት ፤ ቍስል ፡ ለታመመ ፡ ሰው ፡ መድኃኒት ፡ ወይም ... ጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብለህ ፤ እፎየ ፡ ብሎ ፡ አርፎ ፡ ይኖራል ። እስከምትለው ፡ ድረስ ፡ የክርስቶስን ፡



፪ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ የመድኃኒትነቱ ፡ ስም ፡ ስሚ ፡ ብለህ መድኃኒት ፡ ማለት ፡ የቡስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እስከምትለውም ፡ የጻፍከው ፡ እኛን ፡ የማናውቀው ፡ አዲስ ፡ አስመስለህ ፡ በመናገርህ ፡ ከማዘኔ ፡ በቀር ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የምቃወመው ፡ የለኝም ።

፫ ቸሩ ፡ አምላካችንም ዓለምን ፡ ሳይፈጥር ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ በስሕተታቸው ፡ እንደሚወድቁ ፡ አስቀድሞ ፡ ስላወቀ ፡ ለውድቀታቸው ፡ ማንሻ ፡ ለጥንታዊው ፡ ገነታዊ ፡ ንብረታቸውን ፤ መመለሻ ፡ የጠላታቸው ፡ የዲያብሎስን ፡ ራስ ፡ ጨፍልቆ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ በምሕረቱ ፡ አርቆ ፡ ከእሥራታቸውም ፡ በመስቀሉ ፡ ዕዳቸውን ፡ ከፍሎ ፡ የሚያስፈታቸውና ፡ በደሙ ፡ አጥቦ ፡ አንጽቶ ፡ አስታርቆ ፡ ገነት ፡ የሚያገባቸው ፡ አንድ ፡ አማላጅ ፡ ማዕከላዊ ከዓለም ፡ በፊት ፡ ከአባት ፡ ያለ ፡ እናት ፡ ወልድ ፡ ቃል ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ክርስቶስን ፡ መውለዱ ፡ ማዘጋጀቱ ፡ አዳማዊ ፡ ዘር ፡ ኃጥአን ፡ ለኾኑ ፡ ኹላቸው ፡ ለርሱ ፡ በማመን ፡ ብቻ ፡ ድነው ፡ ተፈውሰው ፡ ያምላካዊ ፡ ባሕርይ ፡ ተካፋዮች ፡ እንዲያደርጋቸው ፡ ስላሰበ ፡ ለርሱ ፡ ዓለምን ፡ ሳይፈጥር ፡ አስታራቂና ፡ አዳኝ ፡ መድኃኒት ፡ አድርጎ ፡ አቆመው ። ስለምትለው ።

መጻሕፍት ፡ የክርስቶስን ፡ መድኃኒትነቱን ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ በሦላሴ ፡ ዘንድ መቅደም ፡ መቀዳደም ፤ መከተል ፡ መከታተል ፤ መብለጥ ፡ መበላለጥ ፡ ሳይኖር ፡ አካል ፡ ዘእም ፡ አካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ ፡ የተወለደ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ እንደኾነ ።

አዳምንም ፡ ባንድነት ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ቅደስ ፡ ጋራ ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርዓያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ብሎ ፡ የፈጠረ ።

አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ በድለው ፡ ንስሐ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ወበመንፈቃ ፡ ለዕለት ፡ እመጽእ ፡ ኀቤከ ፡ ወእትወለድ ፡ እምወለተ ፡ ወለትከ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ የሰጠ ።

ትንቢቱንም ፡ በነቢያት ፡ ያናገረ ፡ ምሳሌውን ፡ ያስመሰለ ።

፭ ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ ብሎ ፡ የሰጠው ፡ ቀጠሮ ፡ ሲፈጸምም ፡ በአባቱ ፡ ፈቃድ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ ሰው ፡ የኾነ ።

ኋላም ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ ወንጌልን ፡ አስተምሮ ፡ ለቤዛ ፡ ዓለም ፡ የተሰቀለ ፡ መድኃኒት ፡ እንደኾነ ፡ ይነግሩናል ፡ እንጂ ፤ አንተ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሥልጣን ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ አንድ ፡ ሥምረት ፡ ከመኾን ፡ አውጥተህ ፤ ለልደት ፡ ለጥምቀት ፡ ይኾነኛል ፡ ብሎ ፡ ከበዓሉ ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ አድርጎ ፡ እንደሚያዘጋጁት ፡ በግ ፤ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ እንዲበድሉ ፡ አውቆ ፡ እነሱን ፡ ሊያድንበት ፡ አዘጋጀው ፡ አቆመው ፡ ብለህ ፡ አብን ፡ አዘጋጂ ፡ አድራጊ ፤ ወልድን ፡ ተዘጋጂ ፡ ተደራጊ ፡ አድርገህ ፡ እንደምትናገረው ፡ አደለም ።

እየውማ ፡ ተወግዞ ፡ መለየት ፡ ይገባሃል ፡ ያልኩህ ፡ ፍጡር ፡ ማለትን ፡ መድኃኒት ፡ በማለት ፡ ሰውረህ ፡ ምእመናንን ፡ እንዳትጎዳ ፡ ነው ።

የክርስቶስን ፡ መድኃኒትነት ፡ በእውነተኛ ፡ መንገድ ፡ በተጣራ ፡ አኳኋን ፡ የምታውቁ ፡ ምእመናን ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡ ወጥመድ ፡ እንዳትገቡ ፡ ተጠንቀቁ ።

፬ ከዚህም ፡ ቀጥለህ ፡ ለዚህ ፡ ምስክር ፡ ወውእቱ ፤ ህልው ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ወኵሉ ፡ በቱ ፡ ቆመ ፡ ቈላስ ፡ ፩ ፡ ፲፱—፳፫ ። በከመ ፡ ኀረየነ ፡ ሎቱ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ይረስየነ ፡ ቅዱሳነ ፡

www.ethiopianorthodox.org

(ሀ) ቈላስ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ፡ የጠቀስከው ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ነው ። ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ብሎ ፡ ቀዳማዊ ፡ አምላክነቱን ፡ ይመሰክራል ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ አይናገርም ።

(ለ) ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ የጠቀስከውም ፡ በፍቅር ፡ ኾነን ፡ በፊቱ ፡ ለመቆም ፡ ንጹሐን ፡ ክቡራን ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ለርሱ ፡ አካል ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ አደረገን ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ አይልም ።

(ሐ) ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ የጠቀስከውም ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የታወቀ ፡ ብሎ ፡ ቅድምናውን ። በኋላም ፡ ዘመን ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ብሎ ፡ ሥጋዊውን ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ለአዳም ፡ መድኃኒት ፡ ብሎ ፡ አብ ፡ ወልድን ፡ አዘጋጀው ፡ አይልም ።

፫ የክርስቶስ ፡ ታላቅነት ፡ ፍጡራን ፡ ከተባሉ ፡ ኹሉ ፡ ብልጫው ፡ ግን ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ዘአፈቅር ፡ ወሎቱ ፡ ስምዕዎ ፡ ወሎቱ ፡ ሠመርኩ ።

ፈጽሜ ፡ አከበርሁት ፡ ደግሜም ፡ አከብረዋለሁ ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፫—፴፮ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የመሰከረለት ፡ ከመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ከአሮን ፡ የበለጠ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ የማይሻር ፡ የማይለወጥ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ክህነት ፡ ያለው ፡ እውነተኛ ፡ አዳኝ ፡ አማላጅ ፡ ማለት ፡ የሱስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየንና ፡ አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅን ፡ አለአገባብ ፡ አቆራኝተህ ፡ ከፍጡራን ፡ የሚበልጥበት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብለሃል ። ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ያለው ፤ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ስለተወለደው ፡ ልደት ፡ ነውና ፡ አምላክ ፡ ከፍጡራን ፡ ይበልጣል ፡ ተብሎ ፡ ሊነገር ፡ ሊደነቅ ፡ አይገባም ።

አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ እንደሰውነቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኾኖ ፡ ራሱን ፡ ስለመሠዋቱ ፡ ነውና ፡ ከፍጡራን ፡ ይበልጣል ፡ ማለት ፡ ይህን ፡ ለይቶ ፡ አውቆ ፡ ነው ።

፮ ኃጥእና ፡ ጻድቅ ፡ የሚታየውም ፡ የሊቀ ፡ መላእክት ፡ መለከት ፡ ድምጽ ፡ በምንሰማባት ፡ ከእንቅልፋችን ፡ ተነሥተን ፡ የፈጣሪያችን ፡ ፊት ፤ በምናይባት ፡ ንዑና ፡ ሑሩ ፡ በምንባልባት ፡ በትልቁ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ግን ፡ አብርሃምና ፡ አልዓዛር ፡ ፈያታይ ፡ ዘየማን ፡ ፎቱ ፡ ካልኾኑ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እገሌ ፡ የሚባል ፡ ጻድቅ ፡ ከገነት ፡ ገባ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በመጻሕፍት ፡ የለም ፡ አላየንም ፡ ዳን ፡ ፲፪ ፡ ፩—፲፫ ። ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱—፴፩ ። ፳፫ ፡ ፴፱ ፵፫ ፡ ፊ ፡ ቆሮ ፲ ፮—፲፩ ፡ ስለምትለው ።

አዳምን ፡ በደሙ ፡ አጥቦ ፡ ከሲኦል ፡ እንዳወጣው ፡ ትናገራለህ ፤ ከቀደመ ፡ ቦታው ፡ ገነት ፡ ካላገባው ፡ ወዴት ፡ አድርሶት ፡ ይኾን ፤ እስኪ ፡ ባክህ ፡ ንገረኝ ። ለመከድ ፡ መከድማ ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፱—፵፫ ፡ የጠቀስከው ፡ ፈያታይ ፡ ዘየማንን ፡ ዛሬ ፡ በገነት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንድትኖር ፡ እመን ፡ አለው ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ አገባው ፡ አይልም ።

ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፡ የጠቀስከውም ፡ ነዌ ፡ አልዓዛርን ፡ በአብርሃም ፡ አጠገብ ፡ አየው ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ቦታው ፡ ገነት ፡ እንደኾነ ፡ አይናገርም ፡ ይህንስ ፡ ጨምረህ አትክድምን ።



አብርሃምና ፡ አልዓዛር ፡ ፈያታይም ፡ ያሉ ፡ ገነት ፡ ነው ፡ የምትል ፡ በግምት ፡ ከኾነ ፡ ሌላውንም ፡ እንደዚሁ ፡ ማመን ፡ አለብህ ። ስለነፍሳት ፡ ኹናቴ ፡ በ፯ተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፲፩ ፡ ቍጥር ፡ በሰፊው ፡ ጽፌልሃለሁ ፡ ያንን ፡ ተመልከት ።

፯ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ከኒህ ፡ መልስ ፡ ከጻፍኩልህ ፡ ቃላት ፡ በቀር ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ ጻድቃን ፡ አያማልዱም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ በ፳ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለአማላጅነት ፡ በጻፍከው ፡ የሰጠሁህን ፡ መልስ ፡ ተመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

## የአዳም ፡ መድኃኒት ፡ ከመጽሐፈ ፡ ብሊት ፡

፩ የአዳም ፡ መድኃኒት ፡ በመጽሐፈ ፡ ብሊት ፡ መነገሩ ፡ የማይካድ ፡ ስለኾነ ፡ ሌላው ፡ ጭቅጭቅህ ፡ ሳያንሰኝ ፡ በዚህ ፡ መልስ ፡ ልሰጥህ ፡ አልፈቀድኩም ።

፪ የተወደድህ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ከ፫ቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ክርስቶስ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ መኖሩንና ፡ ለአዳም ፡ አስታራቂ ፡ ለዓለም ፡ መድኃኒት ፡ እንዲኾን ፤ መመደቡ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተመሩ ፡ የተነበዩለትና ፡ የመሰከሩለትን ፡ እንዲረዳህ ፡ ከኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ እስከ ፡ ራዕየ ፡ ዮሐንስ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃላት ፡ በሥጋዊው ፡ ጠባይዕህ ፡ ሳይኾን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሐሳብና ፡ ሕሊና ፡ አስተውለህ ፡ መርምር ። ምሳ ፡ ፰ ፤ ፩—፴፮ ። ፪ ጢሞ ፡ ፫ ፲፯ ። ፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ፡ ስለምትለው ።

ባለፈው ፡ በ፯ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ አእግዚአ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ ለእስራኤል ፡ ያማልድ ፡ ነበረ ፡ ብለሃል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ከ፫ቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ክርስቶስ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ትናገራለህ ። አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ ብሎ ፡ መለመን ፡ ካለ ፡ ትክክልነት ፡ የለም ፤ ትክክልነትም ፡ ካለ ፡ መለመን ፡ ማማለድ ፡ የለምና ፡ ከኹለቱ ፡ አንዱን ፡ መርጠህ ፡ መያዝ ፡ አለብህ ። እንደኔ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ በሥጋዊው ፡ ጠባይዕህ ፡ ሳይኾን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሐሳብና ፡ ሕሊና ፡ አስተውለህ ፤ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ በመለኮቱ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ ያማልድ ፡ ነበረ ፡ ያልከውን ፡ ንግግር ፡ አምዘግዝገህ ፡ ጥለህ ፡ በእሳት ፡ አቃጥለህ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ ማለትን ፡ አጥብቀህ ፡ እንድትይዝ ፡ እመክርሃለሁ ።

፫ ከሥጋ ፡ የተወለደ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ከመንፈስ ፡ የተወለደ ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና ፡ መስሎ ፡ ስለሚታየው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በእምነት ፡ አይቀበለውም ፡ መንፈሳዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ኹሉን ይመረምራል ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ከማንም ፡ አይመረመርም ፡ የሚለውን ፡ ቃላት ፡ አጥብቀህ ፡ መርምረው ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፮ ። ፩ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፲—፲፮ ። ስለምትለው ።

የዚህን ፡ ንባቡን ፡ ከማንበብ ፡ በቀር ፡ ምሥጢሩ ፡ የገባህ ፡ አይመስለኝም ፡ ከሥጋ ፡ የተወለደ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ሥጋዊ ፡ ነገርን ፡ መብል ፡ መጠጥን ፡ በጠቅላላው ፡ ሥጋን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛትን ፡ ነገር ፡ ይወዳል ። ከመንፈስ ፡ የተወለደ ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ ማለትም ፡ መንፈሳዊ ፡ ነገርን ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ ሰጊድን ፡ ቁመትን ፡ በጠቅላላው ፡ መላእክትን ፡ መስሎ ፡ መኖርን ፡ ይወዳል ፡ ማለት ፡ እንደኾነ ፡ አጥብቀህ ፡ መርምረኸው ፡ ወደዚህኛው ፡ ግብር ፡ እንድትመለስ ፡ እሳስብሃለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲፯ ።

### ስለ ፡ ጥምቀትና ፡ ስለ ፡ ቊርባን ።

፩ ጥምቀትና ፡ ቊርባን ፡ ማለት ፡ ብለህ ፡ በወን ፡ የሚደረግ ፡ ረቂቅና ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ፡ እስከ ፡ ምትለው ፡ ድረስ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

፪ ይህንኑ ፡ ምሥጢር ፡ ግን ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ በኃጢአታቸው ፡ ለተናዘዙ ፡ አጥምቆ ፡ ንስሐ ፡ ግቡ ፡ በወንጌልም ፡ እመኑ ፡ እያለ ፡ የጥምቀት ፡ ውል ፡ እየሰበከ ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፡ ተጠማቂዎቹም ፡ ትምህርቱን ፡ ተቀብለው ፡ ሥርየተ ፡ ኃጢአታቸውንም ፡ አምነው ፡ ከሮጌው ፡ የዓለምና ፡ የሥጋ ፡ ልደት ፡ ተለይተው ፡ በነውንና ፡ አዳሱን ፡ የንስሐ ፡ ፍሬ ፡ ለማፍራት ፡ የሚችሉበት ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። ስለምትለው ።

በዚህ ። እነጋገርህ ፡ ልጅነት ፡ በጥምቀተ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደተገኘ ፡ አስመስለህ ፡ ተናግረሃል ፤ ምናልባት ፡ በዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ልጅነት ፡ የተሰጠ ፡ እንዳይመስልህ ፤ የዮሐንስ ፡ ጥምቀትስ ፡ ልጅነት ፡ ለሚገኝበት ፡ ለጌታ ፡ ጥምቀት ፡ የሚያበቃ ፡ ጥምቀተ ፡ ንስሐ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ አስተውል ።

ለዚህም ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ እኔ ፡ ለንስሐ ፡ የሚያበቃ ፡ ጥምቀት ፡ በወኃ ፡ አጠምቃችኋለሁ ፤ ከኔ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣ ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ በእሳት ፡ ያጠምቃችኋል ፡ ያለውን ፡ ብትመለከት ፡ ልትረዳው ፡ ትችላለህ ።

፫ መድኃኒታችንም ፡ ለመጣበት ፡ ጉዳይ ፡ ሥራውን ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ለትስብእቱ ፡ የሚያስፈልገውና ፡ ኃይል ፡ የሚሰጠው ፡ ምሥጢር ፡ ስለ ሆነ ፡ በ፴ ፡ ዓመቱ ፡ በእደ ፡ ዮሐንስ ፡ ስለተጠመቀ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ ነሥቶታል ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፩—፲፯ ። ፬ ፡ ፩—፲፯ ፡ ፩ ዮሐ ፫ ፰ ፡ ስለምትለው ።

በ፴ ፡ ዘመኑ ፡ በእደ ፡ ዮሐንስ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጠመቁ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መጠመቁ ፡ እኮ ፡ ፈቂዶ ፡ ለተጠምቆ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ የሀበነ ፡ ሱታፌ ፡ ንጽሕ ፡ እንዲል ፤ ንጹሕ ፡ እርሱን ፡ ተዋሕደን ፡ ለመኖር ፡ የንጽሕና ፡ አንድነትን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጥቅም ፡ ሽቶ ፡ ሊጠቀምበት ፡ የተጠመቀ ፡ አደለም ።

፬ ኃይል ፡ የሚሰጠው ፡ ምሥጢር ፡ ስለ ሆነ ፡ ማለትህም ፡ ታላቅ ፡ ክህደት ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ለሌላው ፡ ኃይል ፡ ጽንዕ ፡ ከመኾን ፡ በቀር ፡ ለርሱ ፡ ኃይል ፡ ጽንዕ ፡ የሚኾነው ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ እንደሌለ ፡ ባታውቅ ፡ ነው ። ርሱስ ፡ መጠመቁ ፡ እኮ ፡ ዘነሥአ ፡ ጸጋ ፡ በተጠምቆቱ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ያብርህ ፡ ማያተ ፡ ወያኃይል ፡ መከናተ ፡ ለእለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይጠመቁ ፡ ውስቴቱ ፡ እንዲል ፤ በርሱ ፡ አምነው ፡ ለሚጠመቁ ፡ ሰዎች ፡ ለጥምቀት ፡ ኃይል ፡ ለመስጠት ፡ ዮርዳኖስን ፡ ብርሀት ፡ ማኅፀን ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመጠመቁ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ያገኘበት ፡ አደለም ።

ከዮሐንስ ፡ በመጠመቁ ፡ የሚጠቀምበት ፡ ኃይል ፡ የሚያገኝበትስ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ሊጠመቁ ፡ ወደርሱ ፡ የኼዱትን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ለንስሐ ፡ የሚያበቃችኹን ፡ ሥራ ፡ ሥሩ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ተቀበላቸው ፡ ርሱንም ፡ እንደነርሱ ፡ በተቀበለው ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ካንተ ፡ ልጠመቅ ፡ እሻለሁ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ [illegible] ፡ ብሎ ፡ ባልከለከለውም ፡ ነበረ ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፰ ።



፭ ስለተጠመቀ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ ነሥቶታል ፡ ማለትን ፡ አንተ ፡ ከልቡናህ ፡ ፈጥረህ ፡ የምትናገረው ፡ ነው ፡ በመጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ አይገኝም ፤ በመጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ የምናገኘውስ ፡ በገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ ጾሞ ፡ መዋዕለ ፡ ጾሙ ፡ ሲፈጽም ፡ ሰይጣን ፡ መጥቶ ፡ እኒህን ፡ ደንጋዮች ፡ ዳቦ ፡ አድርግና ፡ እንብላ ፡ ቢለው ፡ ሰው ፡ የሚድን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእንጀራ ፡ አደለም ፡ ብሎ ፡ በትዕግሥት ፡ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

ኹለተኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከኾንክ ፡ መላእክትን ፡ እንዲጠብቁህ ፡ ያዝዛቸዋል ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለና ፡ ከምሕዋሩ ፡ ላይ ፡ መር ፡ ብለህ ፡ ውረድ ፡ ብሎ ፡ በትዕቢት ፡ ቢመጣበት ፡ ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትፈታተነው ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ በትሕትና ፡ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፭—፯ ።

ሦስተኛም ፡ አንተ ፡ ለኔ ፡ ብትሰግድልኝ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ቢመጣበት ፡ ለፈጣሪህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልትሰግድ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ እንድታመልክ ፡ ተጽፎብሃልና ፡ አንተ ፡ ሰይጣን ፤ ከኋላዬ ፡ ወግድ ፡ ብሎ ፡ በጸሊዐ ፡ ንዋይ ፡ ፬ ፡ ፰—፲፩ ።

ኋላም ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ ፈጽሞ ፡ ድል ፡ እንደነሣው ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ምሥጢር ፡ ሳታውቅ ፡ ሳትረዳ ፡ ክርስቶስን ፡ እየሰደብክ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ መድኃኒት ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለትህ ፡ እውነተኛ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ መስሎ ፡ በመታየት ፤ ኢይብለክሙ ፡ አግብርተየ ፡ አላ ፡ አዕርክትየ ፡ ያላቸው ፡ ባለሟሎቹ ፡ ቅዱሳንንና ፡ የክርስቶስን ፡ መድኃኒትነት ፡ እንዲህ ፡ ጠንቅቃ ፡ አርጋ ፡ የምታውቅ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከመንቀፍህና ፡ ከመስደብህ ፡ በፊት ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ምሥጢራት ፡ ከመምህራን ፡ ጠይቀህ ፡ ብትረዳ ፤ ኖሮ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ በጠቀመህ ፡ ነበረ ።

፮ ኾኖም ፡ የሕፃናትን ፡ ጥምቀት ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ በ፰ተኛው ፡ ቀን ፡ ግዝረት ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ እንዲሁም ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ መድኃኒታችንና ፡ ሊቀ ፡ ካህናታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢትከልእዎሙ ፡ ለሕፃናት ፡ ከመ ፡ ይምጽኡ ፡ ኀቤየ ፡ ብሎ ፡ እጁንም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ ሲባርካቸውና ፡ ሲጸልይላቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ማቴዎስ ፡ በ፲፱ነኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቍ ፡ ፲፫—፲፭ ፡ ገልጾ ፡ ነግሮናልና ፡ በዚሁ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በሕፃንነት ፡ ጊዜ ፡ ሊጠመቁ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ እንዳንዳንድ ፡ ማኅበሮች ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜዮቸው ፡ ወደርሱ ፡ መጥተው ፡ ጸጋውንና ፡ ሀብተ ፡ ወልድነትን ፡ ሳይቀምሱ ፡ ባዕዳን ፡ ኾነውና ፡ ተከልክለው ፡ ሊኖሩ ፡ ከቶ ፡ አይገባም ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፮—፳፩ ። ስለምትለው ።

እስከ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ አይጠብቅ ፡ በሕፃንነቱ ፡ ይነሣ ፡ በማለትህ ፡ እንስማማለን ፤ ነገርግን ፡ ጊዜ ፡ ባለመወሰንህ ፡ ብቻ ፡ ቅር ፡ ይለኛል ። በኦሪቱ ፡ ወንድ ፡ የወለደች ፡ ሴት ፡ በ፵ ፡ ቀኗ ፡ ሴት ፡ የወለደች ፡ ሴት ፡ በ፹ ፡ ቀኗ ፡ ከርኵሰቷ ፡ ነጽታ ፡ መባዕ ፡ ይዛ ፡ ልጇዋን ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወስዳ ፡ ታስባርክ ፡ እንደነበረ ፤ ዛሬም ፡ የእኛ ፡ ቤተ ፤ ክርስቲያን ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ወንድ ፤ ልጅ ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በ፹ ፡ ቀን ፡ የምታጠምቅ ፡ መኾኗን ፡ እየገለጥኩ ፡ አንተም ፡ ከወገኖችህ ፡ ጋራ [illegible] ፡ ከልቀረ ፡ በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ እንድትስማማበት ፡ አሳስብሃለሁ ። ዘሌዋ ፡ ፲፪ ፡ ፩—፰ ። በቀረው ፡ እንስማማለን ።

www.ethiopianorthodox.org

፺ የመድኃኒትነቱ ፡ ዓላማ ፡ ግን ፡ በበጎ ፡ ሕሊናና ፡ በክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ አምኖ ፡ ከኃጢአትና ፡ ከሥጋ ፡ ፍሬ ፡ ገላ ፡ ፩ ፡ ፲፱–፳፮ ፡ ተለይቶ ፡ ዘወትር ፡ በጸሎትና ፡ ንጽሕና ፡ ነቅቶ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመለመን ፡ ብቻ ፡ ተግተው ፡ ቢያገለግሉ ፡ ነው ። ፩ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ። ስለምትለው ።

አምኖ ፡ ተጠምቆ ፡ ከኃጢአት ፡ ተከልክሎ ፡ ሥራ ፡ ከልሠሩ ፡ ጥምቀት ፡ ብቻ ፡ አይጠቅምም ፡ ማለትህ ፡ እውነትህ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተጠምቆ ፡ ዕለቱን ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ ገዳም ፡ ሔዶ ፡ ሥራውን ፡ በጾም ፡ መጀመሩ ፡ የታመነ ፡ የማይካድ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ሲኾን ፡ ጾምን ፡ ከጸሎት ፡ ለይተህ ፡ በጸሎትና ፡ በንጽሕና ፡ ነቅቶ ፤ በማለትህ ፡ ማዘኔ ፡ አልቀረም ።

አሁንም ፡ እስመ ፡ ጾም ፡ እማ ፡ ለጸሎት ፡ ወእኅታ ፡ ለአርምሞ ፡ ወነቅዓ ፡ ለአንብዕ ፡ ወጥንተ ፡ ኵሉ ፡ ገድል ፡ ሠናይ ፡ (ማሪ ፡ ይስ) ። ጾም ፡ ለጸሎት ፡ እናቷ ፤ ለአርሞሞ ፡ እኅቷ ፤ ለአንብዕ ፡ መፈለቂያዋ ፤ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጥንት ፡ መገኛ ናት ፡ ተብሎ ፡ እንደተነገረ ፤ ያለጾም ፡ መሠረትነት ፡ ምንም ፡ ሊሠራ ፡ የማይቻል ፡ መኾኑን ፡ እያሳሰብኩ ።

ጌታም ፡ ወዝንቱ ፡ ዘመድ ፡ ኢይወፅእ ፡ ዘእንበለ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ፡ ብሎ ፡ ከጸሎት ፡ ጋራ ፡ ያቆራኘው ፡ የትሩፋት ፡ ኹሉ ፡ አበጋዝ ፡ መኾኑን ፡ እየገለጥኩ ፡ ጾምን ፡ ለጸሎትና ፡ ለንጽሕና ፡ መሠረት ፡ እንድታደርገው ፡ አሳስብሃለሁ ። በቀረው ፡ ግን ፡ እንስማማለን ።

፺፩ ቅዱስ ፡ ቍርባን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በግዙፉ ፡ በኅብስትና ፡ በወይን ፡ ቢደረግ ፡ አምነው ፡ ለሚቀበሉት ፡ ኹሉ ፡ ሣክ ፡ ኃጢአትን ፡ አቃጥሎ ፡ የሚያጠፋና ፡ ባሕረ ፡ ሲኦልንም ፡ አሻግሮ ፡ ገነትን ፡ የሚያገባ ፡ መለኮታዊ ፡ የእሳት ፡ መርከብ ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

ስለሃይማኖት ፡ ብለህ ፡ በጻፍከው ፡ በአንደኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለምሥጢረ ፡ ቍርባን ፡ በሰጠሁህ ፡ መልስ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልህ ፡ ኅብስቱ ፡ ተለውጦ ፡ ሥጋ ፡ መለኮት ፡ ወይኑ ፡ ተለውጦ ፡ ደመ ፡ መለኮት ፡ ይኾናል ፡ ማለትን ፡ ስላልደፈርከው ፡ ንግግርህ ፡ ንጹሕ ፡ አልመሰለኝም ። ምናልባት ፡ የሚታየው ፡ ኅብስት ፡ ወይን ፡ ሲኾን ፡ ሥጋ ፡ ደም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ታይቶህ ፡ እንደኾነ ፡ በጥሩ ፡ ወኃ ፡ ተጠምቀን ፡ ከሥላሴ ፡ ረቂቅ ፡ ልደት ፡ ተወለድን ፡ ብለን ፡ ስናምን ፡ ይህ ፡ መወለዳችን ፡ ባይን ፡ የማይታይ ፡ በእጅ ፡ የማይጨበጥ ፡ በልቡና ፡ ብቻ ፡ የሚታመን ፡ ረቂቅ ፡ ነገር ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበ ፡ የሥጋ ፡ ወደሙም ፡ መለወጥ ፡ እንደዚሁ ፡ ባይን ፡ የማይታይ ፤ በልቡና ፡ ብቻ ፡ የሚታመን ፡ ረቂቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ መኾኑን ፡ እስገነዝብሃለሁ ። ዮሐ ፫ ፡ ፲፩ ። ፮ ፡ ፳፯—፷፬ ።

፶ ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በጻፍከው ፡ ኹሉ ፡ እስማማለሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

## ስለ ፡ ተዝካርና ፡ ዝክር ።

www.ethiopianorthodox.org

፩ ወንድሜ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ ለሰብእ ፡ አልቦቱ ፡ ንስሐ ፡ እንዳለው ፡ ግንዘት ፡



ባዕል ፡ ጋራ ፡ ከሕፅነ ፡ ነዌ ፡ በሥቃይ ፡ ቦታ ፡ ገሃነም ፡ ውስጥ ፡ ከገባች ። ከዚሁ ፡ አውጥቶ ፡ አምላክ ፡ የፈረደውን ፡ ገልብጦ ፡ ስፍራ ፡ ሊለውጥላት ፡ የሚችል ፡ ፍጡር ፡ እንደማይገኝ ፡ አስተውል ። ማቴ ፳፭ ፡ ፵፮ ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፭ ፡ አምላክ ፡ ካሠረ ፡ የሚፈታ ፡ ከፈታም ፡ የሚያሥር ፡ ከቶ ፡ እንደሌለ ፡ ዮሐንስ ፡ በራእዩ ፡ ዘኀቤሁ ፡ ይነብር ፡ ኵሉ ፡ መራኁተ ፡ ቤተ ፡ ዳዊት ፡ አልቦ ፡ ዘያርኁ ፡ ወአልቦ ፡ ዘየዐፁ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ብሎታል ፡ ፫ ፯–፲፫ እንዲያውም ፡ ገነት ፡ አጋፋሪና ፡ መዝጊያ ፡ የላትም ። ራእ ፳፩ ፳፭–፳፯ ፡ ስለምትለው ።

ባለፈው ፡ በ፲፩ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ከአብርሃም ፡ ከአልዓዛር ፡ ከፈያታይ ፡ ዘየማን ፡ በቀር ፡ ገነት ፡ የገባ ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ብለህ ፡ ክደህ ፡ ነበረ ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ነፍሳተ ፡ ሙታን ፡ ኹሉ ፡ ወይም ፡ በሕፅነ ፡ አብርሃም ፡ በገነት ፡ ወይም ፡ በሕፅነ ፡ ነዌ ፡ በሲኦል ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ አይገኝላትም ፡ አልክ ፤ እንግዲህ ፡ እውነተኛው ፡ ቃልህ ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ይኾን ፡ እኔስ ፡ መቼም ፡ አውቄሃለሁ ፡ ግድ ፡ የለኝም ፤ እረ ፡ ምን ፡ አልባት ፡ የቁም ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ መስላሃቸው ፡ ሊከተሉህ ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩ ፡ የትኛውን ፡ ቃልህን ፡ እውነት ፡ ብለው ፡ ይይዙት ፡ ይኾን ፤ ካንተስ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ መስክ ፡ ውኃ ፡ በዘው መቅረታቸው ፡ አሳዘነኝ ፤ አንተ ፡ ማጭበርበርና ፡ ማስመሰል ፡ ልማድህ ፡ ስለኾነ ፡ ለማስመሰል ፡ አምላክ ፡ የፈረደውን ፡ ገልብጦ ፡ ስፍራ ፡ ሊለውጥላት ፡ የሚችል ፡ አለ ፡ የምንል ፡ አስመስለህ ፡ ትናገራለህ ፤ እንጂ ፡ እኛስ ፡ በ፳ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በቍ ፡ ፳፩ ፡ ዛሬ ፡ ከምጽአት ፡ አስቀድሞ ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ ያሉት ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስ ፡ ላሉት ፤ በዐፀደ ፡ ነፍስ ፡ ያሉት ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ ላሉት ፤ ይጸልያሉ ፡ ያማልዳሉ ፡ ብዬ ፡ ዘርዝሬ ፡ እንደጻፍኩልህ ፡ እኛ ፡ በሀፀደ ፡ ሥጋ ፡ ያለኖች ፡ በዐፀደ ፡ ነፍስ ፡ ላሉት ፡ ዘመዶቻችን ፡ እንጸልያለን ፡ እንማልዳለን ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ አንተ ፡ እንደምትናገረው ፡ የሚናገር ፡ የሚያስተምር ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ ንስሐ ፡ አለ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ፡ ይድናል ፡ የሚል ፡ የለም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

ስለዚህም ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ አልቦቱ ፡ ንስሐ ፡ ለሰብእ ፡ እምድኅረ ፡ ሞት ፡ አለ ፡ ብለህ ፡ የጠቀስከው ፡ መጽሐፈ ፡ ግንዘት ፡ አንድ ፡ ሃይማኖቱ ፡ የቀና ፤ ምግባሩ ፡ ያልተቃና ፤ በኃጢአት ፡ የሚኖር ፡ ባለጸጋ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ እንዲሁ ፡ በኃጢአቱ ፡ እንዳለ ፡ ሞተ ።

ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ የተሾመ ፡ አንድ ፡ ደግ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ። አባቴ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ከምን ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ግለጽልኝ ፡ ብሎ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በኃዘን ፡ በልቅሶ ፡ ተወስኖ ፡ ቢያመለክት ፡ በሥቃየ ፡ ገሃነም ፡ መኾኑን ፡ በራእይ ፡ ገለጸለት ።

ያም ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ አባቱ ፡ ጥሎት ፡ የሔደውን ፡ ገንዘብ ፡ ለነዳያን ፡ እየመጸወተ ፡ ፍታት ፡ እያስፈታ ፡ ቍርባን ፡ እያስቈረበ ፡ ቢደክምለት ፡ በ፵ ፡ ቀኑ ፡ ከራሱ ፡ እስከትከሻው ፡ ከባሕረ ፡ እሳት ፡ ወጥቶ ፡ ታየው ።

ልመናው ፡ ጸሎቱ ፤ ምጽዋቱ ፡ ከንቱ ፡ እንዳልቀረ ፡ አውቆ ፡ ሥራውን ፡ እየቀጠለ ፡ ሔደ ።

በመንፈቁ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ እስከ ፡ ወገቡ ፡ ድረስ ፡ ወጥቶ ፤ ወዲያውም ፡ ልጄ ፤ ይህ ፡ ሥራ ፡ ለኔ ፡ ጠቃሚኛልና ፡ ይህን ፡ ሥራህን ፡ አታቋርጥብኝ ፡ ሲል ፡

ርሱም ፡ ሥራውን ፡ ቀጠለ ፡ ባመቱ ፡ ፈጽሞ ፡ ከገሃነመ ፡ እሳት ፡ ወጥቶ ፡ በገነት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ በራእይ ፡ ተገለጸለት ፡ እያለ ፡ ይተረካል ፡፡ ይህም ፡ ኀዘኑና ፡ ልቅሶው ፡ ሰውነቱን ፡ ለወንድሙ ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ከመስጠት ፡ የበለጠ ፡ ፍቅር ፡ የለም ፡፡ አባቴን ፡ በኔ ፡ ስም ፡ የለመናችሁት ፡ ቢኖር ፡ ኹሉን ፡ ያደርግላችኋል ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬—፲፯ ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡፡ ሥራ ውም ፡ ከሐዋርያት ፡ ከ፫፻ት ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ የተሠራ ፡ አይምሰልህ ፡፡

፩ኛ ፡ ሐዋርያት ፡ በሲኖዶስ ፡ ወየሀቡ ፡ እምንዋዮሙ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ በእንተ ፡ ነፍሶሙ ፡ ወኢንኤዝዝ ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ዕልዋን ፡ ወመናፍቃን ፡ አላ ፡ ንኤዝዝ ፡ በእንተ ፡ ሰብእ ፡ የዋሃን ፡ በኂሩት ፡ ወበሃይማኖት ፡፡ ወበእንተሰ ፡ ከሀድያን ፡ መሲሐ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ መጽወቱ ፡ ዘምልዐ ፡ ምድር ፡ ወበ ኵሉ ዘውስተ ፡ ዓለም ፡ እምኢበቍዖሙ ፡ ወኢምንተኒ ፡፡

ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ ከገንዘባቸው ፡ ለድኆች ለጠም አዳሪዎች ፡ ይመጽ ውቱላቸው ፤ እንዲህም ፡ አድርጉ ፡ ብለን ፡ የምናዝዝ ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ ለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ መሲሕ ፡ ክር ስቶስን ፡ ለሚክዱ ፡ ሰዎችስ ፡ በዓለም ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ኹሉ ፡ ቢመጸውቱላ ቸው ፡ ምንምን ፤ አይጠቅማቸውም ፡ ብለዋል ፡፡

፪ተኛም ፡ ተዘከሮሙ ፡ ለምውታን ፡ አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ወበ፲ወ፪ቱ ፡ ዕለት ፡ ወበ፴ ፡ ወበ፵ ፡ ዕለት ፡፡ ወአእምር ፡ ወልድየ ፡ ከመ ፡ በ፵ ፡ ዕለት ፡ እምዕረ ፍቱ ፡ ለዘሞተ ፡ ትቀውም ፡ ነፍሱ ፡ ለዘተጠምቀ ፡ ኀጥእ ፡ ወጻድቅ ፡ ቅድመ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይትፌደይ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ፡፡

ሙታንን ፡ በሦስት ፡ ቀን ፤ በአሥራ ፡ ኹለት ፡ ቀን ፤ በ፴ ፡ ቀን ፤ በ፵ ፡ ቀን ፡ ፍታት ፡ በማስፈታት ፡ ቍርባን ፡ በማስቈረብ ፡ ምጽዋት ፡ በመመጽወት ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ በመስጠት ፡ አስቧቸው ፡፡

ልጄ ፡ የተጠመቀ ፡ የክርስቲያን ፡ ሰው ፡ ነፍሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ በክርስቶስ ፡ ፊት ፡ ቆማ ፡ ዋጋዋን ፤ እንድታገኝ ፡ እወቅ ፡ ብለዋል ፡፡

፫ተኛ ፡ ወተዘከሩ ፡ ምውታኒክሙ ፡ በቅዳሴ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ እስመ ፡ ይበቍ ዖሙ ፡ ፈድፋደ ፡ ወያቀርበሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡፡

የሞቱ ፡ ዘመዶቻችሁን ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በቍርባን ፡ በቅዳሴ ፡ አስቧቸው ፡፡ ይህ ፡ እነሱን ፡ እጅግ ፡ ይጠቅማቸዋል ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በክ ብር ፡ በባለሟልነት ፡ ያቀርባቸዋልና ፡ ብለዋል ፡፡

፬ቱ ፡ ፫ትም ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ይህነኑ ፡ የሐዋርያትን ፡ ሲኖዶስ ፡ ጠቅሰው ፡ ወግበሩ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ [illegible]
ታት ፡ በእንተ ፡ ዘተንሥአ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ ወግበሩ ፡ በሳብዕት ፡ ዕለት ፡ ተዝካ

www.ethiopianorthodox.org



ቀዳማውያን ፡ ከማሁ ፡ ኀዘኑ ፡ ሕዝብ ፡ በእንተ ፡ ሙሴ ፡ ወግበሩ ፡ ካዕበ ፡ በፍጻሜ ፡ ዓመት ፡ በአምሳለ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ወሀቡ ፡ ለነዳያን ፡ እምጥሪቱ ፡ ለዘሞተ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተዝካረ ፡ ሎቱ ፡ ወሰበ ፡ ተጸዋዕክሙ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ ብልዑ ፡ በሥ ርዓት ፡ ወበፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡፡

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ እናንተም ፡ ለሞቱ ፡ ዘመዶቻችሁ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ዳዊት ፡ አስደግማችሁ ፡ ፍታት ፡ አስፈትታችሁ ፡ መታሰቢያቸውን ፡ እኽል ፡ ውኃ ፡ ስጡላቸው ፡፡ በ፯ተኛውም ፡ ቀን ፡ ለምውታን ፡ መታሰቢያ ፡ አድርጉላቸው ፡፡ ዳግመኛም ፡ ሙሴ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ እንዳዘኑለት ፡ እንዳለቀሱ ለት ፡ እናንተም ፡ በ፴ቸው ፡ መታሰቢያውን ፡ ስጡላቸው ፡ ዘዳግ ፡ ፴ ፡ ፰ ፡፡

ዳግመኛም ፡ በሠላሳቸው ፡ በዐርባቸው ፡ እንዳደረጋችሁላቸው ፡ በዓመታታቸ ውም ፡ እንደዚሁ ፡ መታሰቢያቸውን ፤ አድርጉላቸው ፡፡ ለሞተው ፡ ሰው ፡ መታሰቢያ ፡ ይኾነው ፡ ዘንድ ፡ ከገንዘቡ ፡ ለነዳያን ፡ መጽውቱለት ፡፡

በዚያም ፡ ቀን ፡ ለግብገ ፡ በተጠራችሁ ፡ ጊዜ ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኾናችሁ ፡ የሞተውን ፡ ነፍሱን ፡ ይማርልን ፡ እያላችሁ ፡ በሕግ ፡ በሥርዓት ፡ ተመ ገቡ ፡ ብለዋል ፡፡

ባስልዮስም ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ያዕርጉ ፡ ቍርባነ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ሞቱ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ ወበሳብዕት ፡ ወበ፲ወ፬ቱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሐቲ ፡ ጉባኤ ፡፡
ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በ፯ተኛው ፡ ቀን ፡ በ፲፬ተኛው ፡ ቀን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊያስቈርቡላቸው ፡ ይገባል ፡ ብሏል ፡፡ በስ ፡ ፴ወ፩
ከ፸ ፡ አርድእት ፡ አንዱ ፡ ቀሌምንጦስም ፡ ወበታስዕት ፡ ዕለት ፡ ወበ፲ወ፪ ፡ ዕለት ፡ ወከማሁ ፡ በ፵ ፡ ዕለት ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ፪ቱ ፡ አውራኅ ፡፡

በ፱ነኛ ፡ ቀን ፡ በ፲፪ተኛ ፡ ቀን ፡ እንደዚኹውም ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ በ፷ ፡ ቀን ፡ ሊያስቈርቡላቸው ፡ ይገባል ፡ ብሏል ፡፡
ወዘተሠርዐሂ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አዕርጎ ፡ ቍርባን ፡ በዕለተ ፡ ተቀብረ ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ወርኅ ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ፮ አውራኅ ፤ ወበተፍጻሜተ ፡ ዓመት ፡ ወፈድፋደሰ ፡ እመ ፡ ተክህሎሙ ፡ ያዕርጉ ፡ ቍርባናተ ፡ ፵ ፡ ዕለተ ፡ እምዕለተ ፡ ተቀብረ ፡ ወየሀቡ ፡ ለነዳያን ፡ ወዘወሰከ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ሎቱሂ ፡ ወለዘሞተሂ ፡ ይፈደፍድ ፡ ዐስበሙ ፡፡

በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ለሙታን ፡ ቍርባን ፡ የታዘዘባቸው ፡ ዕለታት ፡ የሞተበት ፡ ዕለት ፤ በ፴ው ፤ በመንፈቁ ፤ በዓመታቱ ፡ ነው ፡ ይልቁንም ፡ የተቻ ላቸው ፡ ሰዎች ፡ ከሞተበት ፡ ቀን ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ ፵ው ፡ ድረስ ፡ ሳያቋርጡ ፡ ያስቈርቡላቸው ፤ ለነዳያንም ፡ ይመጽውቱላቸው ፡ ከዚህም ፡ አብልጠ ፡ ላደረገ ፡ ለራሱም ፡ ለራሱ ፡ ለሞተውም ፡ ሰው ፡ ዋጋቸው ፡ ይበዛላቸዋል ፡፡

በአምጣነ ፡ ጻሕቅ ፡ ወፍሥሓሁ ፡ ለምጡት ፡ ይከውን ፡ በዝንቱ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ሟቹ ፡ ይህ ፡ ለፍታት ፡ ይህ ፡ ለምጽዋት ፡ ይህ ፡ ለተዝካር ፡ ይህ ፡ ለቊርባን ፡ ይሰጥልኝ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ መናዘዙ ፡ መጠን ፡ ተድላ ፡ ነፍሱም ፡ በዚያው ፡ ልክ ፡ ይደረግለታል ፡ ብሏል ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አንቀጽ ፡ ሙታንን ፡ ተመልከት።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አንተ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ተነሥቶ ፡ ሕገ ፡ አበውን ፡ አምዘግዝጎ ፡ ጥሎ ፡ ሕገ ፡ መብልዕን ፡ ያቋቋመልህ ፡ ሉተር ፡ ጀርመናዊን ፡ አክብረህ ፡ ስትቀበል ፤ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ የተነጋገሩ ፤ ከጌታ ፡ የተማሩ ፡ ሐዋርያትን ፡ ፸ ፡ አርድእትን ፡ ብትነቅፍ ። ያንተን ፡ ነቀፋ ፡ ከምንም ፡ ሳልቈጥር ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰብአ ፡ አርድእትን ፡ ሲመርጥ ፡ የመረጠው ፡ ፸ ፡ አርድእትን ፡ ሲሾም ፡ የሾመው ፡ ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፳፫ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወንጌልን ፡ ዘሮ ፡ ለማስተማሩ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ክታቡ ፡ በም ፡ ፬ ፡ ፫ ፡ የመሰከረለት ፤ መጽሐፉንም ፡ ፫፻ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የቈጠሩለት ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ከጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ያገኘሁትን ፡ እጽፋለሁ ። ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ጽፎ ፡ ለቀሌምንጦስ ፡ የሰጠው ፡ ነው ። መቅ ፡ ፍት ፡ ነገ ፡ ተመልከት ። ርሱ ፡ ስለምውታን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

ወየሀቡ ፡ ምጽዋተ ፡ እምንዋዩ ፡ ለነዳይ ፡ ወይዝክርዎ ፡ በመሥዋዕት ፡ ወቊርባን ፡ እስመ ፡ ትቤ ፡ ነፍስ ፡ አልቦ ፡ ዘበቊዐኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ቊርባን ፡ ወዕጣን ፡ ወመሥዋዕት ። ወእምድኅረ ፡ ወፃእኩ ፡ እምሥጋየ ፡ አልብየ ፡ መንህይ ፤ ወበጊዜ ፡ ቊርባን ፡ ወመሥዋዕት ፡ ወዕጣን ፡ እትፌሣሕ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ አዝማድየ ፡ በከመ ፡ መርዓዊ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ውስተ ፡ ከብካቡ ፡ ከማሁ ፡ ፍሥሐሃ ፡ ለነፍስ ፡ በሰማያት ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ አዝማዲሃ ፡ እመ ፡ ዘከርዋ ፡ በመሥዋዕት ፡ ወቊርባን ፡ ወዕጣን ።

ለሞተ ፡ ሰው ፡ ከገንዘቡ ፡ ለነዳያን ፡ ይመጽውቱለት ፤ ቊርባን ፡ ያስቈርቡለት ፤ ዕጣን ፡ ያሳርጉለት ። ነፍስ ፤ ከሥጋዬ ፡ ከተለየሁ ፡ በኋላ ፡ ከቊርባን ፡ ከዕጣን ፡ ከመሥዋዕት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የረባኝ ፡ የጠቀመኝ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ዕረፍትም ፡ የለኝም ። መሥዋዕት ፡ በተሠዋልኝ ፤ ቁርባን ፡ በተቈረበልኝ ፤ ዕጣን ፡ በታጠነልኝ ፤ ጊዜ ፡ ግን ፤ ከዘመዶቼ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ብላለችና ። ሙሽራ ፡ በሠርጉ ፡ ላው ፡ ከዘመዶቹ ፡ ጋራ ፡ እንዲደሰት ፤ ለነፍስም ፡ ዕጣን ፡ ካሳጠኑላት ፤ መሥዋዕት ፡ ካሠዉላት ፤ ቊርባን ፡ ከአስቈረቡላት ፡ ከዘመዶቿ ፡ ጋራ ፡ በሰማይ ፡ ተድላ ፡ ደስታዋ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

እስመ ፡ በ ፡ ዕፀ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ እለ ፡ ያጸንና ፡ ርእሶን ፡ ለነፍሳተ ፡ ዕጸ ፡ ጻድቃን ፡ ወለለአሐቲ ፡ ጕንድ ፡ በበ፴ወ፩፻ ፡ አዕፁቂሃ ፡ ወለለ፩ ፡ ዐፅቅ ፡ በበ፲፻፻ ፡ ፍሬያቲሃ ፡ ለለአሐቲ ፡ ሕጠት ፡ ፍሬሃ ፡ እንተ ፡ ትንዕስ ፡ በበ፲ወ፪፻ ፡ ነፍሳተ ፡ ጻድቃን ፡ ታስተፌሥሕ ፤ ለእመ ፡ ገብሩ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለለ፩፩ ፡ ነፍሳተ ፡ ጻድቃን ፡ ታጸንን ፡ ርእሳ ፡ ይእቲ ፡ ዕፀ ፡ ገነት ፡ ወትወርድ ፡ ወትትፌሣሕ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ አዝማዲሃ ፡ እለ ፡ ፃመዉ ፡ በገቢረ ፡ ተዝካሮሙ ፡ በአስተፍሥሖ ፡ ካህናት ፡ ወአጽግቦ ፡ ነዳያን ፡ ወአልብሶ ፡ ዕሩቃን ፡ ሕዝ ፡ ፵፯ ፡ ፲፪ ። ራእ ፡ ፪ ፡ ፯ ፡ ፳ ። ፳፪ ፡ ፪ ።



በገነት ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጻድቅ ፡ ነፍስ ፡ ራሳቸውን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ የሚያደርጉ ፡ ዛፎች ፡ አሉ ። ለያንዳንዱም ፡ ዛፍ ፡ ፴፩፻ ፡ ፴፩፻ ፡ አዕፁቅ ፡ አሏቸው ፡ እያንዳንዱም ፡ ዐዕቅ ፡ ሽህ ፡ እልፍ ፡ ፍሬ ፡ ያፈራሉ ። ከፍሬዎቹም ፡ እያንዳንዲቱ ፡ ትንንሽ ፡ ቅንጣት ፡ ዕጣን ፡ የታጠነላቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ የተሠዋላቸውን ፡ ቊርባን ፡ የተቈረበላቸውን ፡ ፲፪፻ ፡ ነፍሳት ፡ ታስደስታለች ። ስለዚህ ፡ ዕጣን ፡ የታጠነላት ፡ ቊርባን ፡ የተቈረበላት ፡ መሥዋዕት ፡ የተሠዋላት ፡ ነፍስ ፡ ይህች ፡ ዛፍ ፡ ራሷን ፡ ዘንበል ፡ አድርጋላት ፡ የተራቡትን ፡ በማብላት ፡ የተጠሙትን ፡ በማጠጣት ፡ የታረዙትን ፡ በማልበስ ፡ ካህናቱን ፡ ደስ ፡ በማሰኘት ፡ ከደከሙላት ፡ ዘመዶቿ ፡ ጋራ ፡ ትደሰታለች ።

ወለእመ ፡ መሐሩ ፡ ሎቱ ፡ አዝማዲሁ ፡ እምንዋዩ ፡ በከመ ፡ ይትቤዘውዎ ፡ ለፄዋ ፡ በንዋይ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ወአዝማዲሁ ፡ ከማሁ ፡ ይትቤዘውዋ ፡ ለነፍሰ ፡ ኃጥእ ፡ ለእመ ፡ ገብሩ ፡ ተዝካሮሙ ፡ በመሥዋዕት ፡ ወቊርባን ፡ ወዕጣን ፡ ወያስተፌሥሕዋ ፡ ለነፍሰ ፡ ጻድቅ ፡ በገቢረ ፡ ተዝካሩ ፡ ለዘእዕረፈ ፡ ግበሩ ፡ ተዝካሮሙ ፡ በንጹሕ ፡ ለአበዊክሙ ፡ ወለአኃዊክሙ ፡ ወለአዝማዲክሙ ፡ ቀደምት ።

ለሞተ ፡ ሰው ፡ ዘመዶቹ ፡ ከገንዘቡ ፡ ከመጸወቱለት ፤ ተዝካር ፡ ካወጡለት ፤ ቊርባን ፡ ካስቈረቡለት ፤ መሥዋዕት ፡ ካቀረቡለት ፤ የተማረከን ፡ ምርኮኛ ፡ እናት ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ ዘመዶቹ ፡ በገንዘብ ፡ እንዲበዡት ፡ እነርሱም ፡ ይበዡታልና ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ ለዘመዶቻችሁ ፡ ንጹሕ ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርቡላቸው።

ወእመሰ ፡ ታፈቅርዎሙ ፡ ጸልዩ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ በንጹሕ ፡ በመሥዋዕት ፡ ወቊርባን ፡ ወዕጣን ፡ ወመንፈሳዊ ፡ በምጽዋት ፡ ለነዳያን ፡ ከመ ፡ ይትዐሠዩ ፡ ዕሤተ ፡ ሠናየ ፡ ዘዐይን ፡ ኢርእየ ፡ ወእዝን ፡ ኢሰምዐ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢተሐለየ ፡ ዘአስተዳለወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ያፈቅርዎ ።

ዘመዶቻችሁን ፡ ከወደዳችኋቸውስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወዳጆቹ ፡ ያዘጋጃት ፡ ዐይን ፡ ያላያት ጆሮ ፡ ያልሰማት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስለነርሱ ፡ ጸልዩላቸው ፡ ንጹሕ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉላቸው ፡ ቊርባን ፡ አስቈርቡላቸው ፡ ለነዳያንም ፡ መንፈሳዊ ፡ ምጽዋት ፡ መጽውቱላቸው ።

ዘንተ ፡ ነገርኩክሙ ፡ ከመ ፡ ትዘከሩ ወትግበሩ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለአበዊክሙ ፡ ወለአኃዊክሙ ፡ ወለውሉድክሙ ፡ ወለቢጽክሙ ፡ ከመ ፡ ትትፈሥሑ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በገቢረ ፡ ተዝካሮሙ ።

ለአባቶቻችሁ ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ ለልጆቻችሁ ፡ ለወገኖቻችሁ ፡ ተዝካር ፡ አውጥታችሁላቸው ፡ ፍታት ፡ አስፈትታችኋቸው ፡ ይህን ፡ በማድረጋችሁ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ አድርጉ ፡ ብዬ ፡ እነግራችኋለሁ ።

ወኢትሑሩ ፡ ወኢትበሉ ፡ ከመ ፡ አሕዛብ ፡ ወዓረሚ ፡ ምንተ ፡ ይበቊዖሙ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ።

እንደ ፡ ዓረማውያንና ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ይረባቸዋል ፡ ምን ፡ ይጠቅማቸዋል ፡ አትበሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘንተሰ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወአልበሙ ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ።

እንዲህም ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፤ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ እንዳለ ፡ የማያምኑ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ፡ (ቀሌምንጦስ ፡ ተመልከት ፡)

ከመጻሕፍት ፡ የተገኘውን ፡ ማስረጃ ፡ እነሆ ፡ በሰፊው ፡ ጽፌልሃለሁ ። እንግዲህ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ አንተ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ሲነግሩህ ፡ መላ ፡ ጨምርበት ፡ ብለህ ፡ እንዳስታወስከኝ ፡ እስኪ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ መላ ፡ እንጨምርበት ። አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያነበብነው ፡ ቃል ፡ ለሙታን ፡ በሚደረገው ፡ መሥዋዕትና ፡ ቍርባን ፤ ተጠቃሚዎቹ ፡ ሙታን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፡ አስቈራቢዎችና ፡ ፍታት ፡ አስፈችዎች ፡ ጭምር ፡ መኾናቸውን ፡ ያረጋግጥልናል ።

ስለዚህ ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ ለሙታን ፡ የማይጠቅማቸው ፡ ቢኾንስ ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ ያሉትን ፡ አስቈራቢዎችንም ፡ አይጠቅማቸውም ፡ ብለህ ፡ ታስባለህ ፡ ይኾን ፤ አታስብም ። እኔ ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ የሰውን ፡ መዳኑን ፡ እንጂ ፡ ጥፋቱን ፡ የማይወድ ፡ ስለኾነ ፡ ስንኳን ፡ በዐፀደ ፡ ሥጋ ፡ ላሉት ፡ በዐፀደ ፡ ነፍሳት ፡ ላሉትም ፡ ቢኾን ፡ ድኅነት ፡ እንዲሰጣቸው ፡ በፍጹም ፡ አምናለሁ ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ በእኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሙታን ፡ የሚደረገው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ምንም ፡ በገንዘብ ፡ ወጭ ፡ በኩል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ቢገመት ፡ በፍጻሜው ፡ ጊዜ ፡ ርህብኩ ፡ ወአብላዕክሙኒ ፡ ፀማዕኩ ፡ ወአስተይክሙኒ ፡ ዐረቁ ፡ ወአልበስክሙኒ ፡ አሰኝቶ ፡ ንዑ ፡ ኅቤየ ፡ ቡሩካኑ ፡ ለአቡየ ፡ የሚያሰኝ ፡ መኾኑ ፡ የማይከድ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ደግሞ ፡ ወዳንተ ፡ ሐሳብ ፡ መለስ ፡ ብለን ፡ መላ ፡ ብንመታ ፡ ይህ ፡ አንተ ፡ ለምውታን ፡ ተዝካር ፡ ማውጣት ፡ ፍታት ፡ ማስፈታት ፡ አይረባም ፡ አይጠቅምም ፡ የምትለው ፡ አስተያየት ፡ ዛሬ ፡ ለጊዜው ፡ ገንዘብ ፡ ለመቈጠብና ፡ ለማድለብ ፡ ጠቃሚነቱ ፤ የማይከድ ፡ ነው ። ፍጻሜው ፡ ግን ፡ እንደዚያ ፡ በሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ በ፲፪ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በ፲፯ኛው ፡ ቍጥር ፡ እንደተጻፈው ፡ ባለጸጋ ፤ ሰውነቴ ፤ ደስ ፡ ይበልሺ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰብስቤልሻለሁ ፡ ብዙ ፡ ድልብ ፡ አድልቤልሻለሁ ፤ የሰበሰብኩልሽም ፡ ገንዘብ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ይበቃሻል ፤ እንግዲህ ፡ ዐርፈሽ ፡ ብዪ ፡ ጠጪ ፡ ደስ ፡ ይበልሺ ፡ እያሉ ፡ ሲዘለሉ ፡ ያልታሰበ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ግብዝ ፤ ሰነፍ ፤ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ነፍስህን ፡ ከሥጋህ ፡ ለይተው ፡ ወደሲኦል ፡ ይወስዷታል ፤ ሥጋህንም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ያወርዱታል ፡ የሚል ፡ ድምጽ ፡ ሰምቶ ፤ በግድ ፡ በጭንቅ ፡ የሚወዱትን ፡ የሚጨነቁለትን ፡ ገንዘብ ፡ ትቶ ፡ ከመሔድና ፤ ኋላም ፡ ርህብኩ ፡ ወኢያብላዕክሙኒ ፡ ጸማዕኩ ፡ ወኢያስተይክሙኒ ፡ ዐረቁ ፡ ወኢያልበስክሙኒ ፡ በሚል ፡ ድምጽ ፡ አስወቅሶ ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ርጉማን ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ዘለዓለም ፡ የሚል ፡ ድምጽ ፡ ከማሰማትና ፡ የዘለዓለም ፡ ልቅሶን ፡ ከማውረስ ፡ በቀር ፡ የሚሰጠ [illegible]



እስኪ ፡ ንገረኝ ። ያው ፡ እሳቱ ፡ ዘኢይጠፍዕ ፡ ዕፄሁ ፡ ዘኢይነውም ፡ የተባለው ፡ ሥቃየ ፡ ገሃነም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ የለውም ።

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከላይ ፡ የተነገረውን ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ተመልክታ ፤

አሁን ፡ የታመተውንም ፡ እምት ፡ አምታ ፤

በሞት ፡ የተለዩ ፡ ዘመዶች ፡ እንደ ፡ አህያ ፡ ሬሳ ፡ ወድቀው ፡ እንደ ፡ ድንች ፡ ተዳፍነው ፡ እንዳይቀሩ ፡ ገምታ ፤

የጻድቅ ፡ ሰው ፡ ሞቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ የተነገረውን ፡ አጽንታ ።

ለሙታን ፡ ቍርባን ፡ ማስቈረብን ፡ ፍታት ፡ ማስፈታትን ፡ ሕግ ፡ አድርጋ ፡ ታስተምራለች ፡ እንጂ ፡ አንተ ፤ እንደምትለው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተዋግቶ ፡ እርሱን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ያሠረውን ፡ ፈቶ ፡ ከሥቃየ ፡ ገሃነም ፡ የሚያወጣ ፡ አለና ፡ ገንዘባችሁን ፡ አምጡ ፡ እያለች ፡ የምታታልል ፡ አደለችም ።

ከማቴዎስ ፡ ወንጌልና ፡ ከሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ከዮሐንስ ፡ ራዕይም ፡ የጠቀስካቸው ፡ ያለቦታቸው ፡ የተጠቀሱ ፡ ናቸው ።

፪ እንደ ፡ አገራችን ፡ መሪዎች ፡ እነ ፡ መምሬ ፡ አታለሉ ፡ ልማድና ፡ ሥርዓት ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ከሞትክ ፡ በኋላ ፡ ወዮላችሁ ፡ እላንተ ፡ የሕዝብ ፡ እረኞች ፡ ጸሎት ፡ አመካኝታችሁ ፡ የምውታንንና ፡ የመበለቶችን ፡ ቤት ፡ ትበላላችሁ ፡ ትውጣላችሁና ፡ ስለዚህ ፡ ከኹሉ ፤ የባስ ፡ የከፋ ፡ ፍርድ ፡ ይፈረድባችኋል ፤ ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፰—፵ ። ብሎ ፡ ጌታ ፡ በቃሉ ፡ ወንጌሉ ፡ የዘለፋቸው ፡ ካህናት ፡ መበለቱ ፡ ወይም ፡ መበለቲቱን ፡ ኃዘናቸውን ፡ በማጽናናትና ፡ ችግራቸውን ፡ ለማቃለል ፡ የምውቱ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ ከረኃብና ፡ ሥቃይ ፡ የሚድኑበት ፡ ሕፃናቱም ፡ የሚያድጉበትን ፡ ዘዴ ፡ በመፍጠር ፡ ፈንታ ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ሟቹ ፡ ከሞተ ፡ በ፯ ፡ ቀኑ ፡ ጀምረው ፡ ሌላው ፡ ይቅርና ፡ በሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ተወስኖ ፡ ለዳነው ፡ ቈራቢ ፡ እንኳን ፡ ለገነት ፤ ወይም ፡ ከገሃነም ፡ ወደ ፡ የትኛው ፡ ቦታ ፡ እንደገባ ፡ ሳያውቁ ፡ የሚያጻድቀው ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍስ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ አለና ፡ ጸሎት ፡ ጸልየን ፡ ዳዊት ፡ ደግመን ፡ ከሲኦል ፡ አውጥተን ፡ አጽድቀን ፡ ገነት ፡ ልናገባላችሁ ፡ የድካማችን ፡ ዋጋ ፡ ዐስበ ፡ ክናፍር ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ማስብና ፡ ማደራጀት ፡ አለባችሁ ፡ (ይገባችኋል ፡ ብለው ፡ ወየዐሥሩ ፡ ጸረ ፡ ዐቢየ ፡ ወክቡደ ፡ ወያስክምዎ ፡ ለሰብእ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡ ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፬ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ አበ ፡ ንስሐው ፡ የኃዘኑ ፡ መጨመሪያ ፡ ክባድ ፤ የብረት ፡ ቀንበር ፡ ለኃዘንተኛው ፡ በጭክና ፡ ይጭኑታል ፡ ስለምትለው ።

ደምህና ፡ ቁርበትህ ፡ ትውልድህና ፡ ዘርህ ፡ አይፈቅድልህም ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያዊነትህን ፡ ለቀህ ፡ የሌላ ፡ ሀገር ፡ ተወላጅ ፡ ልትኾን ፡ ታስባለህና ፡ በምታስበው ፡ ሀገርህ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ አለ ፡ እንደኾነ ፡ አላውቅም ። በእኛ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንስ ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የዘረዘርኩልህን ፡ ሕግና ፡ ሥራት ፡ ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ ከልሒቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ ሴት ፡ ወንዱ ፡ የሚያውቀው ፡ ስለኾነ ፡ ገና ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ገንዘቡን ፡ ይህ ፡ ለምጽዋት ፡ ይህ ፡ ለቍርባን ፡ ለፍታት ፤ ይህ ለልጆች ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ በኑዛዜ ፡ ደልድሎ ፡ ይሞታል ። አበ ፡ ንስሐው ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ኃላፊ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ሥርዓቱስ ፡ ለመዋቲ ፡ ጽንዕት ፡ ይእቲ ፡ ዕብ ፡ ፱ ፡ ፲፯ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ ይፈጸማል ።

ምናልባት ፡ በድንገት ፡ ሳይናዘዙ ፡ የሞቱ ፡ ሰዎችም ፡ ቢገኙ ፡ ልጆቻቸውና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ይህን ፡ የተዘረዘረውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚያውቁት ፡

www.ethiopianorthodox.org

አባታችን ፡ ወይም . . . . አንደ ፡ ድንች ፡ ተዳፍነው ፡ አይቀሩምና ፡ ፍታት ፡ ፍቱልን ፤ ቀዳሴ ፡ ቀድሱልን ፡ መሥዋዕት ፡ አሳርጉልን ፡ ብለው ፡ ሲና ገሩ ፡ እንደጠየቁት ፡ ይፈጸምላቸዋል ።

ደግሞ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የሌላቸው ፡ ሲኾኑ ፡ እንዲያው ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ሥርዓተ ፡ ሙታን ፡ ይፈጸምላቸዋል ፡ እንጂ ፡ ገንዘብ ፡ ከሌላቸው ፡ ተብሎ ፡ ሳይፈቱ ፡ አይቀሩም ።

ለነዚያም ፡ ገንዘብ ፡ እያላቸው ፡ በብላሽ ፡ ቢጸለይላቸው ፡ ወጸሎትየኒ ፡ ገብአ ፡ ውስተ ፡ ሕፅንየ ።

ጸሎቱ ፡ እኔኑ ፡ ወደ ፡ መጥቀም ፡ ተመለሰ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ይኾንባቸዋል ፡ በማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ገንዘባቸውን ፡ በመፈለግ ፡ አደለም ።

ስለዚህ ፡ በኃዘንተኞቹ ፡ በግድ ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ይጭኑባቸዋል ፡ ያልከው ፡ ውሸት ፡ ነው ።

ወዱ ፡ በፈቃዱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ እሰጣለሁ ፡ ካላላቸው ፡ በቀር ፡ ስንኳንስ ፡ ከ፲ ፡ እስከ ፡ ፳፲ ፡ ከአንድ ፡ ብር ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ቢኾን ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ የሚያስገድድ ፡ የለም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

፫ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ ግን ፡ ምውት ፡ እያነሡ ፡ ድውይ ፡ እየፈወሱ ለምጻም ፡ እያነጹ ፡ አንካሳ ፡ እያሮጹ ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ታምራት ፡ ሠርተው ፡ ለሕዝባቸው ፡ ከሥቃይ ፡ እያዳኑ ፡ በእጃቸው ፡ ሠርተው ፡ ይመገቡ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ሲያስተምሩ ፡ የክርስቶስን ፡ ጸጋ ፡ በዋጋ ፡ እየሸጡ ፤ ለሕዝብ ፡ ዕዳ ፡ አይጥሉበትም ፡ የነበሩ ። ወንሠርሕ ፡ እንዘ ፡ ንትቀነይ ፡ ለግብረ ፡ እደዊነ ፡ ታአምሩ ፡ ከመ ፡ ኢተስቁቁ ፡ ንዋየ ክሙ ፡ ኢወርቀ ፡ ወኢብሩረ ፡ ወኢ ፡ አልባሰ ፡ ኢንሣዕኩ ፡ ወኢ ፡ ኀበ ፡ ፩ሂ ፡ እምኔክሙ ፡ እንዳለ ፡ ግብሐዋ ፡ ፳ ፡ ፴፱—፴፮ ። ፩ ቆሮ ፡ ፱ ፱—፲፫ ፡ ስለምትለው ።

ሐዋርያት ፡ አሁን ፡ የጠቀስከውን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ተናግረው ፡ አልቀሩም ። ይህንም ፡ የተናገሩ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ነው ። በሃይማኖት ፡ ወልደው ፡ በምግባር ፡ አሳድገው ፡ በዕውቀት ፡ ፍጹማን ፡ ካደረጓቸው ፡ በኋላስ ፤ ጳውሎስ ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ አስተምሮ ፡ ዋጋ ፡ ይበላል ፡ ብለው ፡ ስላሙት ፤ ወዘኒ ፡ ይፀመድ ፡ ከመ ፡ ይርከብ ፡ ሲሳዮ ፡ መኑ ፡ ዘይተክል ፡ ወይነ ፡ ወኢይበልዕ ፡ ቀምሖ ፡ ወመኑ ዘይርዒ ፡ መርዔቶ ፡ ወኢይሰቲ ፡ ሐሊበ ፡ ቦኑ ፡ ለአድልዎ ፡ ሰብእ ፡ ለላህም ፡ ሶበ ፡ ታከይድ ፡ እክለ ። ላሕምኑ ፡ እንከ ፡ አጽሐቆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘዘንተ ፡ ይጽሕፍ ፤ ወሚመ ፡ በእንቲአነኑ ፡ እንጋ ፡ ይቤ ፡ ወበእንቲአነ ፡ ጸሐፈ ፡ ይድ ፡ እክለ ፡ እንዘ ፡ ሬሴሮ ፡ ምርካበ ፡ የሐርስ ፡ ወዘኒ ፡ ያከ ለክሙ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዐቢይኑ ፡ ውእቱ ፡ ሶበ ፡ ንሕነ ፡ ዘሪዕነ ፡ ዘሥጋ ፡ ሰብእ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፡ ፱ ፯—፲፪ ።

ብላቴና ፡ ሰይፍ ፡ ጫማ ፡ ይዞ ፡ ሲከተል ፡ የሚውል ፡ የዕለት ፡ ምግቡን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ወይን ፡ ተክሎ ፡ አርሞ ፡ ከትኩቶ ፡ ከአዕዋፍ ፡ ጠብቆ ፡ ፍሬውን ፡ የማይመገብ ፡ ማነው ፤ መንጋውንስ ፡ ከአረዊት



ለም ፡ ሣር ፡ ጥሩ ፡ ውኃ ፡ መግቦ ፡ ወተቱን ፡ የማይጠጣ ፡ ማነው ፡ በውኑ ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ በሐሰት ፡ እናገራለሁን ፤ ኦሪትስ ፡ እህልህን ፡ በምታኼድበት ፡ ጊዜ ፡ የላምህን ፡ አፉን ፡ አትሠረው ፡ ብሎ ፡ የለምን ፤ ይህንስ ፤ የተናገረ ፡ ስለኛ ፡ የሚገባ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላም ፡ አሳዝኖት ፡ አትግቶት ፡ ነውን ፤ የሚያርስ ፡ ገበሬ ፡ አምሾውን ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፤ ያርሳል ፤ የሚያኼድም ፡ የቆሎውን ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ያኼዳል ።

እንደዚኸውስ ፡ እኛ ፡ አስተምረን ። አሳምነን ፡ አጥምቀን ፡ አቍርበን ፡ ከአጋንንት ፡ ጠብቀን ፡ ለቁመተ ፡ ሥጋ ፡ ያህል ፡ የዕለት ፡ ዕራት ፡ ብንመገብ ፡ በዛን ? አይበዛም ብሏል ።

ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኙት ፡ መሥመሮች ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ገነውተ ፡ አማልክት ፡ ይሴሰዩ ፡ መበያሙ ፡ ለአማልክት ፡ ወእለኒ ፡ ይፀመዱ ፡ ምሥዋዕ ፡ ይትከፈሉ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወሥዩማን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መባዐ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምርካበሙ ።

ካህናተ ፡ ጣዖት ፡ ለጣዖቱ ፡ የሚገባውን ፡ መባዕ ፡ እንዲመገቡ ፡ አታውቁምን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ካህናትስ ፡ መሥዋዕቱን ፡ ተካፍለው ፡ እንዲመገቡ ፡ አታውቁምን ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለሚያገለግሉ ፡ ካህናትስ ፡ ማግኛቸው ፡ ሰቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚገባው ፡ መባዕ ፡ እንደኾነ ፡ አታውቁምን ።

ወእግዚእነሂ ፡ ከማሁ ፡ አዘዘ ፡ ለእለ ፡ ይሜህሩ ፡ ትምህርተ ፡ ወንጌል ፡ በውእቱ ፡ ምህሮ ፡ ወንጌል ፡ ይኩኖሙ ፡ ምርካበሙ ፡ ለሕይወቶሙ ።

ጌታችንም ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ጊዜ ፡ ወንጌልን ፡ ለሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ማግኛቸው ፡ ወንጌልን ፡ ማስተማር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ይደልዎ ፡ ዐስቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ ብሎ ፡ አዝዟል ፡ እያለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለሚያገለግሉ ፤ ምእመናን ፡ በማስተማር ፡ በማጥመቅ ፡ በማቍረብ ፡ በጸሎት ፡ በፍትሐት ፡ ለሚረዱ ፡ ካህናትም ፡ ዋጋቸውን ፡ ማግኘት ፤ እንዲገባቸው ፡ ጽፏል ።

፴ ለሥጋዊ ፡ ዳኛ ፡ የበደለ ፡ ሕጉንም ፡ ያፈረሰ ፡ ሰው ቢሞት ፡ የበደሉ ፡ ቅጣት ፡ መቀጫ ፡ እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ይማራል ፤ ይቀራል ፡ እንጂ ፡ የሟቹ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ አይጠየቅበትም ። ወንጀለኛ ፡ መቀጫ ፡ ፱ነኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ፻፶፱ኛ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት ፡ መንፈሳውያን ፡ ዳኞች ፡ ያገሬ ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ስለሞተ ፡ የሟች ፡ ዕዳ ፡ ይጥሉበታል ፡ ስለምትለው ።

ሰው ፡ ሲሞት ፤ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ የሥጋ ፡ ዕዳ ፡ ቢፋቀለት ፡ የነፍስ ፡ ዕዳ ፡ የሚፋቀለት ፡ አይመሰልህ ። እንግዲህ ፡ ግበሩ ፡ ለክሙ ፡ አዕርክተ ፡ እምንዋየ ፡ ዓመፃ ፡ በተባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ትቶት ፡ በሔደው ፡ ገንዘቡ ፡ ነዳያንን ፡ ዋጅቶ ፡ የነፍስ ፡ ዕዳውን ፡ ማስፋቅ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ታየህን ? ይህስ ፡ ለክርስቲያን ፡ የተሰጠ ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

፳ ገና ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በክርስቶስ ፡ እመን ፡ ከሞትክ ፡ በኋላ ፡ የምትመገበውን ፡ ስንቅ ፡ ዛሬ ፡ ቋጥር ፤ አምላክህንና ፡ ወንድምህን ፡ አፍቅር ፤ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ምጽዋት ፡ አዘውትር ፡ በሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ [illegible] ውን ፡ የክርስቶስን ፡ ሕግ ፡ ፈጽም ፤ይህን ፡ ካልፈጸምክ ፡ ግን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተከልከል ፡ ብለው ፡ በሥልጣናቸው ፡ አያሥሩትም ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭—፲፰ እኊደ ፡ ታዘዘውም ፡ ወንጌልን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ተግተው ፡ አያስተምሩትም ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፩—፵፪ ። ጽ፰ ፡ ፲፰—፳ ፡ ማር ፡ ፩ ፲፱—፳፩ ። ፩ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፯—፲፮ ፡ ፯ ፡ ፲፫—፳ ። ፪ ፡ ፬ ፡ ፩—፰ ፡ ስለምትለው ።

እኒህ ፤ አሁን ፡ የጠቀስካቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ኹሉ ፡ ለመምህራን ፤ ወንጌልን ፡ ማስተማር ፡ እንዲገባቸው ፡ የሚናገሩ ፡ ናቸው ። አሁን ፡ አንተ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ተነሥተህ ፡ መጽአ ፡ ጸላዒ ፡ ወዘርዐ ፡ ክርዳደ ፡ እንደተባለው ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፳፭ ፡ ጾም ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ሕግ ፡ አደለም ። ሕግ ፡ አልፈጸምክ ፡ ብሎ ፡ ሰው ፡ አውግዞ ፡ መለየትም ፡ አይገባም ፡ ሰዎች ፡ የደነገጉት ፡ ሥራት ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ በምእመናን ፡ ልቡና ፡ የክህደት ፡ የኑፋቄ ፡ እንክርዳድ ፡ እየዘራህ ፡ እንቅፋት ፡ ከመኾንህ ፡ በቀር ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንም ፡ ምእመናን ፡ በሃይማኖት ፡ እንዲጸኑ ፤ በጾም ፡ በጸሎት ፡ እንዲወሰኑ ፡ ተግቶ ፡ ማስተማር ፡ እንቢ ፡ ተኞችን ፡ በቀኖና ፡ መለየት ፡ በክህደታቸው ፡ ቢጸኑ ፡ አውግዞ ፡ መለየት ፡ ነው ።

ይህን ፡ የማይፈጽም ፡ ካህን ፡ ቢገኝ ፡ ግን ፡ በሥጋው ፤ መጥውዎ ፡ ለሰይጣን ፡ በተባለው ፡ መሠረት ፡ ተወግዞ ፡ ይለያል ፤ በነፍስ ፡ ገብር ፡ ሀካይ ፡ ለምን ፡ ኢያገባእከ ፡ ወርቅየ ፡ ተብሎ ፡ ተወቅሶ ፡ ዕሥሩ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ተብሎ ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ቅጣቱን ፡ ይቀበልበታል ፡ እንጂ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይወቀስበትም ።

፮ ለእግዚአብሔር ፡ ለምንን ፡ የሻቱን ፡ ነፍስ ፡ ልናጸድቅላችሁ ፡ እንችላለን ፡ ብለው ፤ የሚጸልዩት ፡ ጸሎትም ፡ ሀቦሙ ፡ በከመ ፡ እከየ ፡ ምግባሮሙ ፡ ፍድዮሙ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ላዕለ ፡ ርእሶሙ ፡ ብለህ ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለው ፡ ሌላውንም ፡ ኹሉ ፡ ነው ፡ ይህንም ፡ መርገም ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ ለጠላቶቹ ፡ የረገመበትን ፡ ብቻ ፡ ሲራገሙ ፡ አድረው ፤ ዘንግእከሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በጸጋ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ጥለው ፤ ዋሽተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለምንን ፡ የሻቱን፡ነፍስ ፡ ከሲኦል ፡ አውጥተን ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ስላገባናት ፡ ዋጋችንን፡ በቶሎ ፡ ስጡን ፡ ይላሉ ። ስለምትለው ።

ልበ ፡ ሕምላክ ፡ የተባለ ፡ አፍቅሮ ፡ ጸላዕትን ፡ የፈጸመ ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ ስለ ራሱና ፡ ስለሌሎችም ፡ ወዳጆቹ ፡ በጎ ፡ ልመና ፡ የሚያቀርብላቸው ፡ ሲኾን ፡ በጠላቶቹ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ እንደጸለየባቸው ፡ እኛም ፡ ወስከሙ ፡ ጌጋየ ፡ በዲበ ፡ ጌጋዮሙ ፡ ወሁከሙ ፡ በመቅሠፍትከ ፡ ምላዕ ፡ ውስተ ፡ ገጸሙ ፡ ኃሣረ ፡ እያልን ፡ ይህነንና ፡ የመሰለውን ፡ ኹሉ ፡ የምንጸልይ ፡ የሕግ ፡ እንቅፋት ፡ በኾንክ ፡ ባንተ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ስለነፍሳተ ፡ ሙታንስ ፡ የምንጸልይ ፤ ለምንት ፡ ትቴክዘ ፡ ነፍስየ ፡ ወለምንት ፡ ተሐውከኒ ። እመኒ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ እገኒ ፡ ሎቱ ። እግዚአብሔር ፡ ያበርህ ፡ ሊተ ፡ ያድኅነኒ ፡ ምንትኑ ፡ ያፈርሃኒ ። እግዚአብሔር ፡ ምእመና ፡ ለሕይወትየ ፡ ምንትኑ ፡ ያደነግፀኒ ። ግብኢ ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍትኪ ። እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረዳኢኪ ። እስመ ፡ አድኀና ፡ ለነፍስየ ፡ እሞት ። ወለአዕይንትየኒ ፡ እምአንብዕ ። ወለእገርየኒ ፡ እምዳኀፅ ። ከመ ፡ አሥምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ ሕያዋን ። እትአመን ፡ ከመ ፡ እርአይ ፡ ሠናይቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ ሕያዋን ። ምንተኑ ፡ አዐሥዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሊተ ። ጽዋዐ ፡ ሕይወት ፡ እትሜጦ ። ወስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጼውዕ ፡ ክቡር ፡ ሞቱ ፡ ለጻድቅ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ። እያልን ፡ ይህነንና ፡ ይህነን ፡ የመሳሰለውን ፡ ኹሉ ፡ ነው ፡ ይህንም ፡ ለመረዳት ፡ እኒህ ፡ የጠቀስኩልህ ፡ ቃላት ፡ ተመርጠው ፡



ተለቅመው ፡ በመጽሐፈ ፡ ግንዘትና ፡ በመዋሥዕት ፡ ተመድበው ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕሊናችን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ወደተጠቀሱት ፡ ቃላት ፡ ያዘነበለ ፡ ሲኾን ፡ ይህን ፡ የጠቀስከውን ፡ የመርገም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ጨምረን ፡ መድገማችንን ፡ በጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ ሲመረምሩት ፡ የአቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ ጸሎትነት ፡ መስሎ ፡ ይገኛል ። እንደምን ፡ ብትለኝ ።

(ሀ) በአቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ውስጥ ፡ መንግሥትህ ፡ ትምጣ ፡ ማለት ፡ ተስፋ ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በታሰበ ፡ ጊዜ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አብቃኝ ፡ ብሎ ፡ የሚጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ ነው ።

(ለ) የዕለት ፡ ምግባችንን ፡ ዛሬ ፡ ስጠን ፡ ማለት ፡ ምግብ ፡ ባስፈለገን ፡ ጊዜ ፡ የሚጸለይ ፡ ጸሎት ፡ ነው ።

(ሐ) እኛ ፡ የበደሉንን ፡ ይቅር ፡ እንደምንል ፡ ኃጢአታችንን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ማለት ፡ ሥርየተ ፡ ኃጢአት ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ የሚጸለይ ፡ ጸሎት ፡ ነው ።

(መ) ከክፉ ፡ ፈተና ፡ አድነን ፡ እንጂ ፡ ወደፈተና ፡ አታግባን ፡ ማለት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የሚጸለይ ፡ ጸሎት ፡ ነው ።

ከነዚህ ፡ ግዳጆች ፡ ባንደኛው ፡ ተይዘን ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ እንጸልይ ፡ በልን ፡ ጊዜ ፡ ጨርሰን ፡ ኹሉንም ፡ እንጸልየዋለን ፡ እንጂ ፡ በከፊል ፡ አንጸልይም ። እግዚአብሔርም ፡ የሕሊና ፡ አምላክ ፡ ስለኾነ ፡ ሕሊናችን ፡ ያዘነበለበትን ፡ ግዳጅ ፡ ይፈጽምልናል ።

እንደዚኹሙም ፡ ነፍሳተ ፡ ሙታንን ፡ ማርልን ፡ ብለን ፡ በምንጸልይበት ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ከላይ ፡ የጠቀስከውን ፡ ቃለ ፡ መርገም ፡ አማልተን ፡ ብናነበው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመለከት ፡ ሕሊናችን ፡ ያዘነበለበትን ፡ ግዳጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማቴ ፡ ፮ ፡ ፱—፲፱ ። እግዚአብሔር ፡ እንዳንተ ፡ አጣሞ ፡ የሚመለከት ፡ አምላክ ፡ አደለም ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ነፍሳተ ፡ ሙታንን ፡ ማርልን ፡ ብለን ፡ በምንጸልይበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳንተ ፡ በግልጽ ፡ የሚቃወሙን ፡ መናፍቃንንና ፡ በሕሊና ፡ የሚዋጉን ፡ አጋንንትን ፡ ድል ፡ ይነሣልን ፡ ዘንድ ፡ ወበከመ ፡ ብዝኀ ፡ ሕብሎሙ ፡ ስድዶሙ ፡ እያልን ፡ እንጸልያለን ።

፯ ደኅሙም ፡ ንዋየ ፡ ዓመፃ ፡ እክለ ፡ ሕማምን ፡ ዘለዓለም ፡ እየበሉ ፡ ፩ ቀን ፡ ስንኳን ፡ ጠግበው ፡ አያውቁም ፡ ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲—፲፪ ፡ ስለምትለው ።

ንዋየ ፡ ዓመፃ ፡ አለመኾኑን ፤ ይደልዎ ፡ ዐስቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ የተባለ ፡ የሚገባ ፡ መኾኑን ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ ከጳውሎስ ፡ ቃል ፡ ጠቅሼ ፡ በሰፊው ፡ አስረድቸሃለሁ ። ደግሞስ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በልተው ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ጠጥተው ፡ ብዙዎቹን ፡ ዕለታትና ፡ ሰዓታት ፡ በጾም ፡ የሚያሳልፏቸውን ፡ ሰዎች ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ጠግበው ፡ አያውቁም ፡ ማለትህ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነውን ፤ አይደለም ። አንድ ፡ ቀን ፡ ጠግበህ ፡ የማታውቅስ ፡ እንደ ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ ሰዴቃ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ከፍህ ፡ ፉርኖ ፡ (ዳቦ) ተለይቶ ፡ የማያውቅ ፡ አንተ ፡ ነህ ። ዘፀአ ፳፰ ፴ ።

፰ ለህብታሙ ፡ እንኳን ፡ አታለው ፡ ቢበሉት ፡ ቢሻው ፡ ከኹሉ ፡ የባሰውና ፡ የከፋው ፡ ግን ፡ የሻቱ ፡ የደ ... ርበት ፡ ለልጆቹ ፡ ማሳደጊያና ፡ ተስፋ ፡ እንዳይኾን ፡ ሕፃናቱ ፡ በዕድላቸው ፡ ያድጋሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በሬው ፡ ለእኛ ፡ ዋጋችን ፡ ስጡን ፡ ብለው ፡ በጭከና ፡ አሳርደው ፡ ሰውየው ፡ ከሞቱ ፡ በ፴ ፡ ወይም ፡ በ፵ ቀኑ ፡ ይበሉትና ፡ ሕፃናቱ ፡ ግን ፡ በረሃብና ፡ ችግር ፡ ሞተው ፡ ያልቃሉ ፡ ስለምትለው ።

የሙት ፡ ልጆች ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለምነው ፡ ከሚያደርጉት ፡ በቀር ፡ የሚያገድዳቸው ፡ አለመኖሩን ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ ዘርዝሬ ፡ አስረድቼሃለሁ ። ኧረ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሞቱ ፡ የሙት ፡ ልጆች ፡ ወዴት ፡ አገር ፡ ነው ፤ እስኪ ንገረኝ ፤ ምነው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ አውቃለሁ ፡ ትላለህ ፡ ኢትኩን ፡ ስምዐ በሐሰት ፡ ያለ ፡ አምላክ ፡ አይፈርድብህም ፡ ይኾን ?

፱ ስለዚህ ፡ ያገሬ ፡ ካህናት ፡ ራሳቸውን ፡ ብቻ ፡ የሚያሰማሩ ፡ በዘመነ ፡ ሕግ ቅኤል ፡ የነበሩ ፡ ካህናትን ፡ ይመስላሉ ፡ ብለህ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የጻፍከው ፡ ካህናትን ፡ ለመስደብ ፡ ብቻ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መልስ ፡ የሚሰጥበት ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ስለሌለበት ፡ ኵሉ ፡ ዘያምዕዕ ፡ እኅዋሁ ፡ በከንቱ ፡ ያለ አምላክ ፡ ዋጋህን ፡ ይከፈልህ ፡ እንጂ ፡ የምሰጥህ ፡ መልስ ፡ የለኝም ። ማቴ ፭ ፳፩ና ፡ ፳፪ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡

## ስለ ፡ በዓላት ።

፩ በዓላት ፡ ማለት ፡ መታሰቢያ ፡ ዝክር ፡ የደስታ ፡ ቀን ፡ ጉባኤ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ዘፀአ ፡ ፲፪ ፩—፲፪ ፡ ዜና ፡ ፰ ፡ ፲፫ ። ነህ ፡ ፰ ፡ ፺—፲፱ ። ይኸውም ፡ በመጽሐፈ ፡ ብሉይ ፡ እንደተጻፈው ፡ የሚዘከረው ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ቀኖቹም ፡ በዓመት ፡ ሦስት ፤ ስማቸውም ፡ ፋሲካ ፤ ሰዊት ፡ መፀለት ፡ ነው ፡ ፪ዜና ፰ ፲፫ ስለምትለው ።

አንተ ፡ ነገር ፤ ቀንጭሮ ፡ መሔድ ፡ ልማድህ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለበዓላትስ ፡ ጥንታቸው ፡ መሠረታቸው ፡ ጌታ ፡ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ ፍጥረታትን ፡ በየወገናቸው ፡ ሲፈጥር ፡ ሰንብቶ ፡ በ፯ተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ስላደረገ ፡ ወእመ ፡ ሳብዕት ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ እግዚእነ ፡ እምኵሉ ፡ ግብሩ ፡ የተባለበት ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ናት ። ዘፍ ፡ ፪ ፩ ፫ ።

ይህችውንም ፡ ለሙሴ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ሕግ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ ከ፲ቱ ፡ ቃላት ፡ አንዲቱ ፡ ርሱዋን ፡ አድርጎ ፡ ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ።

ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራህን ፡ ኹሉ ፡ ሠርተህ ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ትቀድሰው ፡ ዘንድ ፡ አስብ ። ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ የአምላክህ ፡ ሰንበት ፡ ነውና ፡ በርሱ ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ። አንተ ፤ ልጆችህም ፤ አሽከሮችህም ፡ ከብትህም ፤ በደጅህ ፡ ያለ ፡ እንግዳም ፡ ሥራ ፡ አይሥሩ ። እግዚአብሔር ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ ባሕርንም ፡ ያለባቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ፈጥሮ ፡ ስላረፈበት ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ባርኮታል ፤ ቀድሶታልና ፡ ሥራ ፡ አትሥሩበት ፡ ብሎ ፡ ደገኛ ፡ ሕግ ፡ አድርጎ ፤ ቢጠብቁት ፡ ዋጋ ፡ የሚያሰጥ ፡ ባይጠብቁት ፡ የሚያስቀጣ ፡ አድርጎ ፡ ሠርቶታል ። ማስቀጣቱም ፡ በሰለጳዓድ ፡ ታውቋል ። ዘኍል ፡ ፲፭ ፤ ፴፪—፴፯ ፡ ዘፀአ ፡ ፴፭ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ይህ ፡ በ፰ ፡ በ፰ ፡ ቀን ፡ የሚከበር ፡ በዓል ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሠረትነት ፡ በዓመት ፡ የሚከበሩ ፡ አሁን ፡ የቈጠርካቸው ፡ እነበዓለ ፡ ፋሲካ ፡ እነበዓለ ፡ ሰዊት ፤ እነበዓለ ፡ መፀለት ፡ ተጨማሪ ፡ ኾነው ፡ ተሠርተዋል ።



ደግሞ ፡ ከነዚህ ፡ ሌላ ፡ በ፯ተኛው ፡ ዓመት ፡ የሚከበር ፡ ዓመተ ፡ ኅድገት ፡ የተባለ ፡ ስድስቱን ፡ ዓመት ፡ ሠርተው ፡ ሰባተኛውን ፡ ዓመት ፡ በምሉ ፡ እንዲያከብሩት ፡ ታዝዙዋል ።

ደግሞ ፡ ከነዚህ ፡ ሌላ ፡ ዓመተ ፡ ኅድገትን ፡ በሱባዔ ፡ ቈጥሮ ፡ በ፵፱ ፡ ዘመን ፡ የሚከበር ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የተባለ ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ያልካቸው ፡ ፫ቱ ፡ ብቻ ፡ አልነበሩም ።

፪ እንዲሁም ፡ በመጽሐፈ ፡ ሐዲስ ፡ እንደተገለጸውና ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥትም ፡ በ፲፱ነኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደተደነገገው ፡ በዓላተ ፡ ወልድ ፡ የተባለው ፡ በ፩ዓመት ፡ ውሥጥ ፡ ፱ ቀን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

ሠለስቱ ፡ ምዕት ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፱ቱን ፡ በዓላት ፡ ብቻ ፡ ቈጥረው ፡ አልቀሩም ። ወኢትግበሩ ፡ በዕለተ ፡ በዓለ ፡ ሐዋርያት ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ኮኑ ፡ ለክሙ ፡ መምህራነ ፡ ለአእምሮተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወረሰዩክሙ ፡ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ትሳተፉ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ሐዋርያት ፡ እናንተን ፡ መክረው ፡ አስተምረው ፡ ክርስቶስን ፡ ለማወቅ ፡ አብቅተው ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ለመቀበልና ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ለመኾን ፡ ስላበቋችሁ ፡ ያረፉበትን ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አድርጋችሁ ፡ አክብሩ ፡ ብለው ፡ ጨምረው ፡ መሥራታቸውን ፡ አስብልኝ ።

፫ አባ ፡ ገብረ ፡ ወልድና ፡ መምሬ ፡ ተክለ ፡ ዮሐንስ ፡ የተባሉ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ተአምረ ፡ ማርያምና ፡ መርሀ ፡ ዕውር ፡ በሚባል ፡ በ፴፬ ፡ ዓ፡ ም፡ አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ባስጻፉት ፡ መጽሐፋቸው ፡ በገጽ ፡ ፶፳፯ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የሌለውን ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ፵፩ ፡ ቀን ፡ በዓላት ፡ ታዝዙዋል ፡ ብለው ፡ በውሸት ፡ ጽፈዋል ፡ ስለምትለው ።

ምንም ፡ እኒህን ፡ ሰዎች ፡ ባላውቃቸውና ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ባልነጋገራቸው ፡ መቅድመ ፡ ተአምርን ፡ የጻፉልን ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ የተባሉ ፡ ጳጳሳት ። ወለእመ ፡ ተርፈ ፡ እምኔነ ፡ ምንትኒ ፡ ያዘክር ፡ ኢጺስ ፡ ቆጶስ ።

ከኛ ፡ የቀረ ፡ ምንምን ፡ ቢኖር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ያሳስብ ፡ ብለው ፡ ሐዋርያት ፡ በሰጡት ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ እመቤታችን ፡ ለወዳጆቿዋ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሥራ ፡ የሠራችበቻውን ፡ ሰለታት ፡ ቈጥረው ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውሥጥ ፡ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ ፴፫ት ፡ ዕለታት ፡ እንዲከበሩ ፡ አዝዘዋል ፤ ምናልባት ፡ ይህነን ፡ ጠቅሰው ፡ ጽፈው ፡ እንደኾነ ፡ እንጂ ፡ ከልባቸው ፡ አንቅተው ፡ ዶጽፉ ፡ አይመስለኝም ፡

፬ እንደ ፡ ሀገራችን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ ግን ፡ ፻፲፲ወ፰ቱ ፡ ርቱዓን ፡ ሃይማኖት ፡ ያላወጁት ፡ ባንድ ፡ ወር ፤ ፲፰ ፡ ቀን ፡ በዓላት ፡ እየተባለ ፡ የማይሠራበት ፡ ለመላእክት ፡ ለቅዱሳን ፡ ለጻድቃን ፡ ለሰማዕታት ፡ ለአበሆይ ፡ እገሌ ፡ ለእማሆይ ፡ እገሊት ፡ ለክብራቸው ፡ ተብሎ ፡ ተደግሶ ፡ የሚስከርበት ፡ ፈጣሪን ፡ ትቶ ፡ ፍጡር ፡ የሚመለክበት ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ከ፪፻ ፡ ቀን ፡ የሚበዛ ፡ በዓል ፡ ይደረጋል ፡ ስለምትለው ።

(ሀ) አንተ ፡ ቅዱሳንን ፡ ያዋረድኩህ ፡ መስሎህ ፡ አባሆይ ፡ እገሌ ፡ እማሆይ ፡ እገሊት ፡ እያልክ ፡ ትሰድባቸዋለህ ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ ኢይብለክሙ ፡ አግብርትየ ፡ አላ ፡ አዕርክትየ ፡ ተብለው ፡ የተመሰገኑ ፡ ሲኾኑ ፡ ባንተ ፡ አፍ ፡ የሚዋረዱ ፡ አደሉም ። ዋጋህን ፡ ግን ፡ ጴጥሮስ ፡ ለሐናንያ ፤ ጳውሎስ ፡ ለብራየሱስ ፡ እንደ ፡ ከፈሉቸው ፡ ይከፈሉህ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ አልሰጥህም ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፩—፲፩ ። ፲፫ ፡ ፯—፲፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

(ለ) ፫፻ት ፡ ያላወጇት ፡ ስለምትለው ፡ ሐዋርያት ፡ በሲኖዶስ ፡ ወከዕበ ፡ ያዕርፉ ፡ በዕለተ ፡ ተዝካርሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ መምህራኒክሙ ፡ ትእዛዘ ክርስቶስ ፡ ወመለብውያኒክሙ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወከዕበ ፡ ያዕርፉ ፡ በበዓለ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ወቀዳሚሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰማዕት ፡ ከማሁ ፡ ለሰማዕት ፡ ወለኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ይደሉ ፡ ያክብርዎሙ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ እለ ፡ አብደሩ ፡ ፍቅሮ ፡ እምሕይወቶሙ ።

ሐዋርያት ፡ ትእዛዘ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌልን ፡ የሚያስተምሯችሁ ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮባችሁ ፡ እንዳለ ፡ የሚያስገነዝቧችሁ ፡ መምህሮቻችሁ ፡ ስለ ኾኑ ፡ የመታሰቢያ ፡ ቀናቸውን ፡ በዕረፍት ፡ አክብሩ ።

ዳግመኛም ፡ የዲያቆናት ፡ አለቃቸው ፡ የሰማዕታት ፡ ተቀዳሚያቸው ፡ ፊታውራሪያቸው ፡ በሚኾን ፡ በእስጢፋኖስም ፡ በዓል ፡ እንደዚሁ ፡ በዕረፍት ፡ አክብሩ ።

እንደዚኹውም ፡ ከሕይወታቸው ፡ ይልቅ ፡ ፍቅረ ፡ ክርስቶስን ፡ አብልጠው ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ የሰማዕታት ፡ የቅዱሳንን ፡ ኹሉ ፡ በዓል ፡ ማክበር ፡ ይገባል ፡ ብሏዋል ።

ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ወአነ ፡ ጴጥሮስ ፡ እኤዝዞሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ ያዕርፉ ፡ እምግብሮሙ ፡ በመዋዕለ ፡ በዓለ ፡ ሰማዕት ።

እኔ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምእመናን ፡ ሰማዕታት ፡ ባረፉበት ፡ ቀን ፡ ከሥራ ፡ አርፈው ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ አዝዤአለሁ ፡ ብሏል ።

የሐዋ ፡ ሲኖ ፡ ተመልከት ።

ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህን ፡ የሐዋርያትን ፡ የ፫ቱ ፡ ፻ትን ፡ ትእዛዝ ፡ አክብራ ፡ ተቀብላ ፡ በዓለ ፡ ሰማዕታትን ፡ በዓለ ፡ ቅዱሳንን ፡ ታከብራለች ፡ እንጂ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አደለም ።

(ሐ) የሚሰከርበት ፡ ስለምትለው ፡ ለቅዱሳን ፡ መታሰቢያ ፡ ለኃጢአት ፡ ማስተሥረያ ፡ ተብሎ ፡ ይደገሳል ፡ እንጂ ፡ ለመሳከሪያ ፡ ተብሎ ፡ አይደገስም ።

ለበዓሉ ፡ የተጠሩትም ፡ ወሶበ ፡ ተጸዋዕክሙ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ ብልዑ ፡ በሥርዓት ፡ ወበፍርሃት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደተባለው ፡ ዕበያተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየተጨዋወቱ ፡ በቀስታ ፡ በጸጥታ ፡ ተመግበ ፡ ከመለያየት ፡ በቀር ፡ መስከር ፡ በፍጹም ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። ይህን ፡ አልፎ ፡ የሰከረ ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ በሕግ ፡ ተላላፊነት ፡ ይቀጣል ፡ እንጂ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊነቀፍበት ፡ አይገባም ።

(መ) ፍጡር ፡ የሚመለከበት ፡ ያልከው ፡ ፍጹም ፡ ውሸትህ ፡ ነው ፡ ለዚህ ፡ አንድ ፡ ማስረጃ ፡ የለህም ፡ አንተ ፡ እየፈጠርክ ፡ ከማውራት ፡ በቀር ፡ ፍጡር ፡ የሚያመልክ ፡ የለም ።

(ሠ) ባንድ ፡ ዓመት ፡ ከ፫፻ ፡ ቀን ፡ የሚበዛ ፡ በዓል ፡ ይከበራል ፡ ስለምትለው ።

በመሠረቱ ፡ ላይ ፡ በዓል ፡ መከበሩ ፡ ሕግ ፡ መኾኑን ፡ ከተስማማንበት ፡ ሌላው ፡ አያስቸግርም ። በፍትሐ ነገሥት ፡ የተጻፈት ፡ ፱ ፡ በዓላት ፡ ...



ሚከበሩ ፡ የቅዱሳንም ፡ በዓል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ዘረዘርኩልህ ፡ በሐዋርያት ፡ ሲኖዶስ ፡ የታዘዘ ፡ ስለኾነ ፡ ስማቸው ፡ በተጠራበት ፡ ዝክራቸው ፡ በተዘከረበት ፡ ቦታ ፡ ካመት ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ሊከበር ፡ ይገባል ። ሌላው ፡ ግን ፡ አይገደድም ።

(ረ) ደግሞ ፡ በመቅድመ ፡ ተአምር ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ የእመቤታችን ፡ በዓል ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ፴፫ ፡ ቀን ፡ እንዲከበር ፡ አዝዘዋል ። እነርሱ ፡ እንዲህ ፡ ማዘዛቸው ፡ ሐዋርያት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚገባ ፡ ተመርታ ፡ ወደ ፡ ጸጥታ ፡ ወደብ ፡ ትደርስ ፡ ዘንድ ፡ ከእኛ ፡ በኋላ ፡ የሚነሡ ፡ መምህራን ፡ የከበደውን ፡ ሊያቀሉ ፡ የቀለለውን ፡ ሊያከብዱ ፡ የጐደለውን ፡ ሊመሉ ፡ የዘበውን ፡ ሊያቀኑ ፡ ይገባቸዋል ፡ ብለው ፡ በዘዙት ፡ መሠረት ፡ ለጊዜው ፡ አስፈላጊ ፡ ኾኖ ፡ ተገኝቶ ፡ እንዲከበር ፡ አዝዘው ፡ ሲሠራበት ፡ ቈይቶአል ።

ደግሞ ፡ ዛሬ ፡ እንደጊዜው ፡ ለሕዝብ ፡ የሚከብድ ፡ ኾኖ ፡ ሲገኝ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ተመርምሮ ፡ ሊወሰን ፡ የሚቻል ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ።

፳ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ ከንቱ ፡ የኾነ ፡ ስሕተት ፡ ስለተከተልን ፡ ዋጋችንያ ፡ ክፉ ፡ ጠላት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ደመኛ ፡ ማጣት ፡ ወይም ፡ ረሃብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ምሳ ፡ ፯ ፡ ፱—፲፩ ። ፲፫ ፡ ፬ ፡ ፳ ፡ ፲፫ ፡ ስለምትለው ።

አሁን ፡ የጠቀስካቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ሰነፍን ፡ ሲዘልፍ ፡ የጻፋቸው ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በዓል ፡ ስለሚያከብሩ ፡ ሰዎች ፡ አልጻፋቸውም ። ችጋርና ፡ ረሃብም ፡ የሚመጣ ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ በዓል ፡ በመሻር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዓል ፡ በማክበር ፡ አደለም ። ይህም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ እስራኤል ፡ በ፯ ፡ በ፯ ፡ ዓመት ፡ ዓመተ ፡ ኅድገትን ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ዕለት ፡ ያከብሩ ፡ ነበረ ፡ ዘፀአ ፡ ፳፫ ፡ ፲-፲፫ ። ዘሌ ፡ ፲፫—፲፰ ። ዘዳ ፡ ፳፩—፳፫ ። ብላሰ ፡ ዓመተ ፡ ዘዘራዕከ ፡ ወበከልእ ፡ ዘአትረፍከ ፡ ወበሣልስ ፡ ትዘርዕ ፡ ወተዐርር ፡ የተባሉ ፡ እስራኤል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ ሲያከብሩ ፡ ረሃብ ፡ ቸነፈር ፡ የሚመጣባቸው ፡ ሕግ ፡ በመተላለፋቸው ፡ በዓል ፡ ባለማክበራቸው ፡ እንጂ ፡ በዓል ፡ በማክበራቸው ፡ አልነበረም ።

፯ ወዳኛ ፡ ሆይ ፡ ሥራ ፡ ወዳጆች ፡ የኾኑ ፡ ወንድሞቻችን ፡ እስላሞች ፡ ባኑሯቸው ፡ በምግብ ፡ ልብሳቸው ፡ እንዲት ፡ እንዳሉ ፡ እኛ ፡ ሳንሠራ ፡ በዓላት ፡ ስንቈጥርና ፡ ለሚሠሩ ፡ ወንድማችንም ፡ ቡዳ ፡ ፋቂ ፡ ሸማኔ ፡ ቀጥቃጭ ፡ አንጥረኛ ፡ ሸቃጭ ፡ . . . . ብለን ፡ እየተሳደብን ፡ የምንኖር ፡ ሕገ ፡ ክርስቶስ ፡ ስዱስ ፡ መዋዕለ ፡ ተገበር ፡ ተግባረከ ፡ የሚለውን ፡ ሳንፈጽም ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የምንባለው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ኑሮ ፡ እንደምንኖር ፡ ልብ ፡ ያለው ፡ አይስተውም ፡ ዘዳግ ፡ ፳፰ ፡ ፴፫—፴፩ ፡ ስለምትለው ።

ይህ ፡ የጠቀስከው ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ የተሠራልህን ፡ ሕግ ፡ ባትጠብቅ ፡ ባገርህ ፡ የሚቀመጥ ፡ ካንተ ፡ ይበልጣል ፡ አንተ ፡ ዝቅ ፡ ርሱ ፡ ከፍ ፡ ብላችሁ ፡ እርሱ ፡ አበዳሪ ፡ አንተ ፡ ተበዳሪ ፡ ትኾናላችሁ ፡ ይላል ። ከትእዛዛቱም ፡ አንዱ ፡ አክብሮ ፡ በዓል ፡ ነው ። በዓል ፡ ብታከብሩ ፡ ትከብራላችሁ ፡ ባታከብሩ ፡ ትዋረዳላችሁ ፡ ... ፡ አስተውል ። ለሚሠራው ፡ ወንድማችን ፡ ቡዳ ፡ ፋቂ ፡ እያልን ፡ እንሳደባለን ፡ ለምትለው ፡ ነገሩ ፡ ልዩ ፡ ስለኾነ ፡ ከአክብሮተ ፡ በዓል ፡ ጋራ ፡ ተጫ

www.ethiopianorthodox.org

የተከለከለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንሠራበትም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ይቈጠር ፡ እንደኾነ ፡ አርመው ።

ሥራ ፡ ወዳጆች ፡ ወንድሞቻችን ፡ በማለትህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በእስላም ፡ ሕግ ፡ ልትመራት ፡ ማሰብህን ፡ ገልጠሃል ፡ በዚህ ፡ ምኞት ፡ ወገኖችህን ፡ ምራበት ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስንኳንስ ፡ በኑሮዋ ፡ ያላነሰችውን ፤ ብታንስ ፡ ቅሉ ፡ ይኄይስ ፡ ኅዳጥ ፡ ዘበጽድቅ ፤ የምትል ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ የምትቀና ፡ አደለችም ።

ስለበዓላት ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ ሰጥቼ ፡ መላልሼ ፡ አስረድቼሃለሁ ። ከዚህ ፡ ቀጥለህ ፡ የምትጽፈው ፡ ግን ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ ክልቡናህ ፡ ፈጥረህ ፡ ቅዱሳንን ፡ ጣዖታት ፤ እኛን ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ እያልክ ፡ የምትሳደበው ፡ ስድብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ቅዱሳን ፡ ጣዖታት ፡ አለመኾናቸውን ፤ እኛም ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ አለመኾናችንን ፤ ባለፈው ፡ ኹሉ ፡ ጽፌልሃለሁ ፡ ያንን ፡ ተመልከት ። እኔ ፡ እንዳንተ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ አደለሁም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስመላልስ ፡ አልኖርም ።

## ምዕራፍ ፲፱ ።

## ስለ ፡ ምጽዋት ፡ ጸሎት ጾም

፩ ጾም ፡ ማለት ፡ ከምጽዋትና ፡ ጸሎት ፡ ጋራ ፡ የተሰናሰለ ፡ ሦስቱ ፡ የማይለያይ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ምሥጢራዊ ነገር ፡ ነው ። ስለምትለው ፡

ጾም ፤ ጸሎት ፤ ምጽዋት ፤ የተሰናሰሉ ፡ መኾናቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ! ስለዚህ ፡ በእኛ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተያይዘው ፡ ባንድነት ፡ ሲሠሩ ፡ ይኖራሉ ። ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ጾምና ፡ ምጽዋት ፡ በፍጹም ፡ ተሠርዘው ፡ ለጸሎት ፡ ብቻ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ በጅምላ ፡ ስትጓዝ ፡ ትታያለህ ። እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ጾም ፤ ጸሎት ፡ ምጽዋት ፤ የተሰናሰሉ ፡ ናቸው ፡ ማለትህ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽነትህን ፡ ይመሰክርብሃል ፡ እንጂ ፡ የሚጠቅምህ ፡ ምንድን ፡ ነው ። የሦስቱ ፡ ምግባራት ፡ ባንድነት ፡ መገኘት ፡ ጠቃሚነቱን ፡ ከተረዳሃው ፡ የማይረባ ፡ የማይጠቅም ፡ የተውሶ ፡ ባህል ፡ ለቀህ ፡ ወደአባቶችህ ፡ ባህል ፡ ተመለስ ።

፪ የኾውም ፡ ከአምላክህ ፡ ጋራ ፡ በኅቡዕ ፡ የምትነጋገርበት ፡ በተለይ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዘር ፡ የምትዘራበት ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

በእኛ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እኒህ ፡ ሦስቱ ፡ ነገሮች ፡ በግልጽም ፡ የሚሠሩበት ፤ በኅቡዕም ፡ የሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ይኸውም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

(ሀ) ጾም ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የታዘዙት ፡ ፯ቱ ፡ አጽዋም ፡ በግልጽ ፡ በመተባበር ፡ ይጾማሉ ፤ ፍት ፡ ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፫–፲፪ ። ጾመ ፡ ንስሐና ፡ ጾመ ፡ ፈቃድ ፡ ግን ፡ በመምህረ ፡ ንስሐ ፡ አማካይነት ፡ በኅቡዕ ፡ ይጾማል ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፯–፲፱ ።

(ለ) ጸሎት ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚደረግ ፡ ጸሎተ ፡ ማኅበር ፡ በግልጽ ፡ ባንድነት ፡ ይጸለያል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፩ ፡ ፲፫–፲፭ ፩ ቆሮ ፡ ፲፭ ። ፳፯። ሌላው ፡ የሕሊና ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ በኅቡዕ ፡ ይጸለያል ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፭–፲፬ ...



(ሐ) ምጽዋት ፡ በጌታ ፡ በእመቤታችን ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ ስም ፡ የሚዘከር ፡ ዝክር ፡ በግልጽ ፡ ይሰጣል ፡ ሉቃ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪–፲፭ ። ፩ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳ ፡ ፳፪ ። ሌላው ፡ ምጽዋት ፡ ግን ፡ በመምህረ ፡ ንስሐ ፡ አማካይነት ፡ ወይም ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ይሰጣል ማቴ ፡ ፮ ፩–፭ ።

ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ጾምና ፡ ምጽዋት ፡ በፍጹም ፡ ተሠርዘው ፡ ጸሎት ፡ ብቻ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ በጅምላ ፡ ሲሠራ ፡ ይታያል ። እንግዲህ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ፫ቱም ፡ በግልጽ ፡ የማይሠሩ ፡ ከኾነ ፡ ጸሎትንም ፡ በጅምላ ፡ ማድረግ ፡ አልነበረም ፡ ጸሎት ፡ በግልጽ ፡ የሚደረግ ፡ ከኾነ ፡ ጾምና ፡ ምጽዋትም ፡ እንዲሁ ፡ በስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ መደረግ ፡ ነበረባቸው ። የሦስቱ ፡ ትእዛዝ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ወይንም ፡ እንደኛ ፡ ኹሉንም ፡ በግልጽም ፡ በኅቡዕም ፡ ካላደረግህ ፤ ወይም ፡ ጸሎትንም ፡ በኅቡዕ ፡ ብቻ ፡ ካላደረግህ ፡ ሕግህ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ አደለም ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ።

፫ ርሱም ፡ በ፫ት ፡ ይከፈላል ፡ ፩ኛ ፡ በሀገር ፡ ላይ ፡ ዐባር ፡ ቸነፈር ፡ መቅሠፍት ፡ ሲታዘዝ ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ነነዌ ፤ በኢትዮጵያም ፡ ፋሽስት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በዋጅ ፡ አስደርገውት ፡ እንደነበረው ፡ ያለ ፡ ነው ።

፪ተኛው ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተህ ፡ በተለይ ፡ መከራ ፡ በመጣብህ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ከቤርሳቤህ ፡ የወለደው ፡ ልጅ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ እንዳዘነው ፤ ሕዝቅያስም ፡ ሰናክሬም ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳዘነው ፡ ያለ ፡ ነው ።

፫ተኛም ፡ ጴጥሮስ ሐዋርያ ፡ እንደሚነግረን ፡ ዘወትር ፡ ከዲያብሎስ ፡ ጋራ ፡ ለመታገል ፡ በዓለም ፡ ካለው ፡ የከንቱ ፡ ስሕተትና ፡ የጥፋት ፡ ወጥመድ ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ነቅቶ ፡ ኃጢአትን ፡ እየጾሙ ፡ በክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ጐልምሶ ፡ መኖር ፡ ነው ፡ ስላምትለው ።

በአንደኛውና ፡ በኹለተኛው ፡ ቍጥር ፡ የጠቀስካቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍት ፡ በታዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጠ ፡ የሚጾሙት ፡ ጾም ፤ አባት ፡ በልጁ ፡ ላይ ፡ አርጩሜ ፡ በቃጣበት ፡ ጊዜ ፡ ደንግጦ ፡ እንደሚርበደበደው ፡ ያለ ፡ የድንጋጤ ፡ ጾም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሕግ ፡ ጾም ፡ አይደለም ።

የሕግ ፡ ጾምስ ፡ ኸነው ፡ ቢኾን ፡ በአንቀጸ ፡ በዓላት ፡ የተሠሩ ፡ ፱ቱ ፡ በዓላት ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ እንደሚከበሩ ፤ እነዚህም ፡ የዳዊት ፡ ጾም ፤ የሕዝቅያስ ፡ ጾም ፡ እየተባሉ ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ በተጾሙ ፡ ነበረ ። ይኸውም ፡ ከቈጠርካቸው ፡ አንዱ ፡ ጾመ ፡ ነነዌ ፤ ከኾነ ፡ ወዲህ ። ፫፻ት ፡ በሕግ ፡ መጽሐፍ ። ወጾሙ ፡ ሰብአ ፡ ነነዌ ፡ ፫ቱ ፡ ዕለታት ፡ ብለው ፡ ስለቈጠሩት ፡ ሕግ ፡ ኾኖ ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ እንደሚጾመው ፡ ማለት ፡ ነው ።

፫ተኛ ፡ ጴጥሮስ ሐዋርያ ፡ እንደሚነግረን ፡ ብለህ ፡ የጠቀስከውም ፡ ከኃጢአት ፡ ንጹሕ ፡ መኾን ፡ ከኃጢአት ፡ መጠበቅ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ጾም ፡ አይባልም ። ከዓለም ፡ ወጥመድ ፡ ለማምለጥ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ተግቶ ፡ መኖርንም ፡ በአፍ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በገቢር ፡ ለምታሳይ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንተ ፡ ላስተምር ፡ ማለትህ ፡ በተመልካች ፡ ዘንድ ፡ አስገራሚ ፡ ኾኑዋል ።

የሕግ ፡ ጾምስ ፡ ፫፻ት ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የቈጠሩዋቸው ።

፩ኛ ፡ ጾመ ፡ ፵ ዘጾማ ፡ ክርስቶስ ።

፪ኛ ፡ ረቡዕና ፡ ዐርብ ።

www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ ፡ ጾመ ፡ ሰብአ ፡ ነነዌ ።
፬ኛ ፡ ድራረ ፡ ልደትና ፡ ድራረ ፡ ጥምቀት ፡ (ጋድ)
፭ኛ ፡ ጾመ ፡ ነቢያት ።
፮ኛ ፡ ጾመ ፡ ሐዋርያት ።
፯ኛ ጾመ ፡ ፍልሰታ ናቸው ።

ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍህ ፡ ውስጥ ።
1 በገጽ ፡ ፪ ፡ በመሥመር ፡ ፲፯ ።
2 በገጽ ፡ ፬ መሥመር ፡ ፲፰ ።
3 በገጽ ፡ ፯ ፡ በመሥመር ፡ ፪፯ ።
4 በገጽ ፡ ፪፫ ፡ መሥመር ፡ ፳፭ ።
5 በገጽ ፡ ፪፬ ፡ መሥመር ፡ ፬ እጠ ነተኛ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ መኾኑን ፡ የመሰከርክለት ፡ ነው ።

፬ ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ በጾምና ፡ ጸሎት ፡ ጽሙድ ፡ ነኝ ፡ ባይነው ፡ በትምክህቱም ፡ ለዓለም ፡ ኹሉ ፡ የሚተርፍ ፡ መስሎ ፡ ይታየዋል ። በጾሙና ፡ ጸሎቱሳ ፡ የትኛውን ፡ መዓት ፡ መልሶ ፡ ያውቃል ፡ ይኸን ፤ አገራችን ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ከበረድና ፡ አንበጣ ፡ ከዋግና ፡ ቃቂጣ ፡ ከረሃብና ፡ ፈራ ፡ ከችግርና ፡ መከራ ፡ ድኖ ፡ አያውቅም ። እደ ፡ ጸላዒም ፡ ዘወትር ፡ እንዳጠቃውና ፡ ደሙን ፡ እንዳፈሰሰው ፡ ይኖራል ።

ብለህ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከእንግሊዝ ፤ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከግብጽና ፡ ከደርቡሽ ፤ አፄ ምኒልክ ፡ ከኢጣልያ ፤ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከፋሽስት ፡ ጋራ ፡ እየተዋጉ ፡ ድል ፡ እየነሡ ፡ነፃነታቸውን ፡ ጠብቀው የኖሩበትን ፡ ድል ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ አድርገህ ፡ ትናገራለህ ።

እነዚህ ፡ የቈጠርካቸው ፡ ጠላቶች ፡ ኹሉ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ የደረጁ ፡ ብዙ ፡ ፋብሪካዎች ፡ ያዘጋጁ ፡ ሲኾኑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (በእግዚአብሔር ፡ ከመታመንና ፡ ከመንፈስ ፡ ቈራጥነት ፡ በቀር ፡ የበቃ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሳይኖራት ፡ የተነሡባትን ፡ ጠላቶቿን ፡ ኹሉ ፡ አፈር ፡ እያስጋጠች ፡ የምትመልሳቸው ። ይልቁንም ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መቅደላ ፤ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ መተማ ፡ ሲሞቱ ፤ ነፃነቷን ፡ ሳታጣ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ሳትገባ ፡ መቅረቷ ፡ ሥራዋ ፡ ኹሉ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በኀዘን ፡ በልቅሶ ፡ የተመሠረተ ፡ ቢኾን ፡ አደለምን ?

ፋሽስት ፡ በግፈኝነት ፡ ከገባ ፡ በኋላስ ፡ በ፭ት ፡ ዓመት ፡ ድምጥማጡ ፡ የጠፋ ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ትግል ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በኀዘን ፡ በቀኖና ፡ የተመሠረተ ፡ ቢኾን ፡ አይደለምን? ። በዚያውስ ፡ ላይ ፡ ጾመ ፡ ነነዌን ፡ ስትጠቅስ ፡ ፋሽስት ፡ ከመምጣቱ ፡ አስቀድሞ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዐዋጅ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ የተጾመውን ፡ ጾም ፡ ሕገኛ ፡ ጾም ፡ እንደኾነ ፡ ተናግረህ ፡ ነበረ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከመከራ ፡ የማያድን ፡ ጾም ፡ ምን ፡ ጾም ፡ ነው ፣ ስትል ፡ ነቅፈኸዋል ። እንግዲህ ፡ የሚታመን ፡ የትኛው ፡ ቃልህ ፡ ነው ፡ ይኸን ? ። ደግሞ ። አገራችን ፡ ከበረዶና ፡ አንበጣ ፡ ከረሃብና ፡ ከችግር ፡ ድና ፡ አታውቅም ፡ ብለህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለምለም ፡ ፍሬያማ ፡ ኾና ፡ የምትሰጠውን ፡ ፍሬ ፡ ክደሃል ። የኢትዮጵያ ፡ ሰብሏ ፡ ከራሷ ፡ ተርፎ ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ያቆመች ፡ ከምድሯ ፡ [illegible]



አታውቅምን ? ኢትዮጵያ ፡ በኀዘን ፡ በቀኖና ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ መጠቀሟን ፡ ለምለም ፡ ፍሬ የምትሰጥ ፡ መኾኗንም ፡ ዓለም ፡ በሙሉ ፡ ሲያውቀው ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ አለማወቅህ ፡ እጅግ ፡ ታሳዝናለህ ።

፭ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ለማድረግ ፡ የሚገባው ፡ ግን ፡ በምትጾምበት ፡ በምትጸልይበት ፡ ጊዜ ፡ ለዓለም ፡ ከክፉ ፡ ምግባርዋ ፡ ተለይተህ ፡ ሕሊናህን ፡ አንጽተህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚወደውና ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ ባዘዘው ፡ አካሔድ ፡ ልትመላለስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የሰው ፡ ሥርዓት ፤ ለመጠበቅ ፡ ቅቤና ፡ ሥጋ ፡ ጥሉላትን ፡ ከመብላት ፡ ብቻ ፡ ተለይተህ ፡ በእህል ፡ ወጥ ፡ በዘይትና ፡ ዓሣ ፡ እየበላህ ፡ አምላክ ፡ የከለከለውንና ፡ የሚያዝንበትን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እየሠራህ ፡ እጾማለሁ ፡ ማለት ፡ በከንቱ ፡ ሐሰት ፡ ነውና ፡ ጾም ፡ አይባልም ፡ በምትጾምበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ያንተው ፡ ፈቃድ ፡ ትተህ ፡ የአምላክ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ መሥራት ፡ ታዟል ፡ ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፫ ፡ ስለምትለው ።

የሚያጣላን ፡ ጾም ፡ ማለት ፡ ከኃጢአት ፡ መከልከል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መብል ፡ መለጠጥ ከእህል ፡ ከወኅ ፡ መከልከል ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ማለትህ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፤ ጾም ፡ መኖሩን ፡ አምነህ ፡ ከእህል ፡ ከወኅ ፡ እንደ ፡ ተከለከላችሁ ፡ ከቀሩትም ፡ ኃጣውእ ፡ ተከልከሉ ፡ የምትል ፡ ከኾንክስ ፡ እንስማማለን ።

ጾም ፡ የታዘዘበት ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍም ፤ ምጽዋት ፡ የገንዘብ ፡ ግብር ፡ እንደ ኾነ ፡ ጾምም ፡ ሥጋን ፡ መገበር ፡ ማለት ፡ ነው ። በሕግ ፡ ጾም ፡ የታዘዘበት ፡ ምክንያት ፡ ኃይለ ፡ ፍትወት ፡ ደክሞ ፡ ሥጋ ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ትገዛ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አረጋግጦ ፡ ነግሮናልና ፡ ከፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ ኹሉ ፡ መከልከል ፡ የተገባ ፡ ነው ።

፮ ለዘለዓለም ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይነካና ፡ እንዳይበላ ፡ የተከለከለ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ስም ፡ ተጠቅሎ ፡ ኃጢአት ፡ የተባለው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ፪ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ወር ፡ መጾም ፡ የሰው ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

ጌታን ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሲፈታተኑት ፡ እኛና ፡ ፈሪሳውያን ፡ አብዝተን ፡ እንጾማለን ፡ ተማሮችህ ፡ ለምን ፡ አይጾሙም ፡ ብለው ፡ በጠየቁት ፡ ጊዜ ፤ ዛሬ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሳሉ ፡ ሊጾሙ ፡ አይችሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከነርሱ ፡ ለይተው ፡ የሚወስዱበት ፡ ጊዜ ፡ አለና ፡ ያንጊዜ ፡ ይጾማሉ ፡ ማለቱ ፤ ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ። ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሳሉ ፡ ኃጢአት ፡ ይሠራሉ ፡ ከኔ ፡ ሲለዩ ፡ ኃጢአት ፡ አይሠሩም ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ይኸን ? እስኪ ፡ ንገረኝ ፤ ያልኾነ ፡ ነገር ፡ ተናግረህ ፡ እኔን ፡ ጨምረህ ፡ የማይገባ ፡ አናገርከኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈጣሪዬ ፡ ይቅር ፡ ይበለኝ ።

ይህነንስ ፡ እንዳትል ፡ ጾምሰ ፡ ተከልአተ ፡ ብእሲ ፡ እመብልዕ ፡ በጊዜ ፡ ዕውቅ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ እንዘ ፡ ይትኤዘዝ ፡ ለዘሐገጎ ፡ ለሥርየተ ፡ አበሳ ፡ ወብዝኅ ፡ ዕሤት ፡ ፈቂዶ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ያድክም ፡ ኃይለ ፡ ፍትወት ፡ ወትትአዘዝ ፡ ለነፍስ ፡ ነባቢት ።

ጾም ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ሕጉን ፡ ለሠራለት ፡ ለክርስቶስ ፡ እየታዘዘ ፤ ኃጢአቱን ፡ ለማስተሥረይ ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ ሽቶ ፡ የፍትወት ፡ ኃይል ፡ ደክማ ፡ ሥጋ ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ትገዛላት ፡ ዘንድ ፡ በሕግ ፡ በታወቁ ፡ ጊዜያቶች ፡ ከመብል ፡ መከልከል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከመብል ፡ መከልከል ፤ ያውም ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ መኾኑን ፡ ለይቶ ፡ ጽፎብሃል ፡ ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጸ ፡ ጾም ፡ ተመልከት ።

፯ በ፹ወ፩ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ለይቶ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ ጹሙ ፡ ቅቤና ፡ ሥጋም ፡ በሳምንት ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ [illegible]ካዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ባንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ከቶ ፡ የለም ፡ ምንም ፡ አይገኝም ፡ ስለምትለው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ወ፩ ፡ መጻሕፍት ፡ ማለት ፡ በአንቀጸ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደአስረዳሁህ ፡ የሐዋርያት ፡ መጻሕፍት ፡ ሲኖዶስ ፡ ዲዲስቅልያ ፡ ጭምር ፡ ናቸው ፡ ከ፲፡ወ፩ ፡ መጻሕፍት ፡ አንዱ ፡ ወዘኢይጸውም ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ወረቡዕ ፡ ወዐርብ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይትመተር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘሀሎ ፡ ቦቱ ፡ ደዌ ፡ ክሡት ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ይትፌለጥ ።

የታወቀ ፡ ደዌ ፡ ካደረበት ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ጾመ ፡ ፵ንና ፡ ረቡዕን ፡ ዐርብን ፡ የማይጾም ፡ ካህን ፡ ቢኾን ፡ ይሻር ። ሕዝባዊ ፡ ቢኾን ፡ ይለይ ፡ ይላል ። ረሰጠጅ ፡ ፷ ፡ ረሰጠብ ፡ ፵ወ፷ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አለና ፡ ተመልከት ።

፷ እውነተኛ ፡ ጾም ፡ ማለት ፡ ግን ፡ በኀዘን ፡ በልቅሶ ፡ ሥርየት ፡ ዋጋ ፡ ጥቅም ፡ አገኝበታለሁ ፡ ብለህ ፡ በፈቃድህ ፡ ባስፈለገህ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ የሚጾም ፡ እንጂ ፡ ጾሙ ፡ ስለማይል ፡ የትእዛዝ ፡ አደለም ፡ ስለምትለው ።

ጌታ ፡ አሜሃ ፡ ይጸውሙ ፡ ብሎ ፡ በትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ ማዘዙን ፤ ሐዋርያትም ፡ ጾሙ ፡ ብለው ፡ ማዘዛቸውን ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌልሃለሁ ። እንቢ ፡ ብትል ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ በጠቀላላው ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ለእሽተኛው ፡ ዋጋ ፡ በማሰጠት ፡ ለእንቢተኛው ፡ ፍዳ ፡ በማምጣት ፡ እስክትገለጥ ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ መኖር ፡ ስለሚችል ፡ ሌላውንም ፡ ሕግ ፡ እንቢ ፡ ልትል ፡ ትችላለህ ።

፱ እውነተኛ ፡ ጾም ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ዳንኤል ፡ ፲፮ ፡ ፩—፲፬ ፡ እንደ ፡ ዕዝራ ፡ ፰ ፡ ፳፩ ፡ እንደ ፡ ነህምያ ፡ ፩ ፡ ፩—፲፩ ፡ እንደ ፡ አስቴር ፡ ፬ ፡ ፲፮ ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ነነዌ ፡ ፫ ፡ ፩—፲ ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

እኒህ ፡ የጠቀስካቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ኹሉ ፡ ጾዋሚዎች ፡ ከእህል ፡ ከወኀ ፡ ከሥጋ ፡ ከቅቤ ፡ ተከልክለው ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሰው ፡ እንደጾሙ ፡ ይነግሩናል ። አንተ ፡ ግን ፡ ጾም ፡ ከኀጢአት ፡ መከልከል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከመብል ፡ መከልከል ፡ አይደለም ፡ ትላለህ ፡ እንግዲህ ፡ ማንላችሁን ፡ እንቀበል ። እባክህ ፡ ሳትማር ፡ ላስተምር ፡ አትበል ፡ የምትናገረውንም ፡ መርምረህ ፡ ተናገር ።

፲ ያሬድ ፤ አክሱማዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቅ ፡ በጾመ ፡ ድጓ ፤ ስለጾም ፡ ሲናገር ፡ የሚጾመው ፡ ኀጣውእ ፡ የሚጾም ፡ ረቂቁ ፡ ሕዋሳት ፡ መኾኑን ፡ አውቆ ፡ ንጹም ፡ ጾመ ፡ ወናፍቅር ፡ ቢጸነ ፡ ወንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ፡ ዓይን ፡ ይጹም ፡ እምርእየ ፡ ሕሱም ፡ ዕዝን ፡ ይጹም ፡ እምሰሚዐ ፡ ሕሱም ፡ ልሳንኒ ፡ ይጹም ፡ እምተናግሮ ፡ ሕሱም ፡ እያለ ፡ በብዙ ፡ ቃል ፡ አስረድቷል ፡ ስለምትለው ።

ያስቸገረ ፡ እንደ ፡ በሽተኛ ፡ ይህን ፡ እወዳለሁ ፡ ይህን ፡ አልወድም ፡ ማለትህ ፡ ነባረ ፡ እንጂ ፡ ያሬድንስ ፡ ከተቀበልከኝ ፡ ፩ኛ ፡ የሐዋርያውን ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ አከለክሙ ፡ መዋዕል ፡ ዘሐለፈ ፡ ዘተቀነይክሙ ፡ ለግእዝ ፡ ሥጋክሙ ፡ እምይእዜሰ ፡ ጹሙ ፡ ወጻልዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀነዩ ፡ ብሏል ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፩—፬ ።

፪ተኛ ፡ ወዝንቱ ፡ ዘመድ ፡ ኢይወፅእ ፡ ዘእንበለ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ያለውንም ፡ ጠቅሶ ፡ ጾም ፡ ትፌውስ ፡ ቍስለ ፡ ነፍስ ፡ ወታጸምም ፡ ኵሎ ፡ ፍትወታተ ፡ ዘሥጋ ፡ ትሜሕሮሙ ፡ ለወራዙት ፡ ጽሙና ፡ ብሎ ፤ ጾም ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ከመተው ፡ ጋራ ፡ መኾኑን ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ ቀድሱ ፡ ጾመ ፡ ቀድሱ ፡ ጾመ ፡ እስመ ፡ ሙሴኒ ፡ በሲና ፡ ጾመ ፡ እግዚእነ ፡ ጾመ ፡ በእንቲአነ ፡ አርዓያሁ ፡ ከመ ፡ የሀበነ ፡ ብሎ ፡ ሙሴ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ እንደ ፡ ጾመ ፤ ጌታም ፡ ለእኛ ፡ አብነት ፡ ለመኾን ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ መጾሙን ፡ አስረድቶናልና ፡ ጾም ፡ ከምግብ ፡ በመከልከል ፡ አይደለም ፡ ማለትን ፡ ተው ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ስለጾም ፡ መረዳት ፡ ብትፈልግ ፡ የኹግ ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልከት ዘፀአ ፡ ፴፬ ፳፰ ። ማቴ ፬ ፪ ...



ም ዕ ራ ፍ ፡ ፳ ፡

## ስለሚያሰክር ፡ መጠጥ ።

፩ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ መጠጥ ፡ ማለት ፡ ለኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ምንጩ ፡ መፍለቂያው ፡ የበሩ ፡ መክፈቻ ፡ መግቢያው ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ ለሚል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ መጠጥ ፡ ስካርን ፡ ሊጾም ፡ በተገባው ፡ ነበረ ፡ ስለምትለው ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ ስካር ፡ ሰውን ፡ የሚያዋርድ ፡ ከሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያወጣ ፡ በሕግ ፡ የተጠላ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ መጠጥ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መተው ። አይገባም ፡ እንጂ ፡ ከጠጣሁ ፡ ራሴን ፡ መግታት ፡ አይቻለኝም ፡ ብሎ ፡ መተው ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ ነው ።

፪ ስካር ፡ ተከታዩና ፡ ፍሬው ፡ ጥፋት ፤ አሌ ፤ ወዮ ፤ ወዮታ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፲፩—፳፪ ። ወዮታ ፡ ለማነው ፡ ኀዘን ፡ ለማነው ፡ ብለህ ፡ ምሳ ፡ ፳፫ ፡ ፳፱—፴፱ ፡ የጠቀስከው ፡ ኢትስከሩ ፡ ወይን ፡ ብለህ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ፡ ዐቂ ፡ ርእስክሙ ፡ ብለህ ፡ ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፴፬—፴፮ ። ወይእዜኒ ፡ ኢትስተዩ ፡ ወይነ ፡ ወሜሰ ፡ መሳ ፡ ፲፫ ፡ ፯ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ፩ጢሞ ፡ ፫ ፩—፲፯ ፡ ቲቶ ፡ ፩፡፭—፱ ፡ ኢሳ ፳፰፡ ፯ ።

የጠቀስከው ፡ የስካርን ፡ መጥፎነትና ፡ ወይን ፡ መተው ፡ የበለጠ ፡ ትሩፋት ፡ መኾኑን ፡ ይናገራል ። ወይን ፡ ርኩስ ፡ በማለት ፡ ሳይኾን ፡ ያሰክረኛል ፡ ብሎ ፡ ፈርቶ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ለትሩፋት ፡ ብሎ ፡ መተው ፡ የበለጠ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

፫ ወዳጄ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ስማህ ፡ አየህን ፡ ለሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ሐሊብ ፡ አገርዕት ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ደጋግመው ፡ ይነቅፉታል ፡ ሐሊብ ፡ እንስሳት ፡ ግን ፡ ቢጠጡት ፡ ኀጢአት ፡ አይኾንም ፡ የሰው ፡ አእምሮ ፡ የማያዛባና ፡ የማይበጠብጥ ፡ ስለኾነ ፡ መጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ አይከለክሉትም ፡ ያስጸይፋል ፡ ብለውም ፡ አይነቅፉትም ፡ ከቶውም ፡ ለብዙዎች ፡ ልበ ፡ በሽተኞች ፡ ከሞት ፡ ስለሚያድናቸው ፡ የደረቀ ፡ ሕይወትን ፡ የሚያለመልም ፡ ውሳጣዊ ፡ በሽታ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ሲያቃጥል ፡ ጠለ ፡ ሕይወት ፡ ስጥቶ ፡ የሚፈውስ ፡ አምላካችን ፡ በምሥጢሩ ፡ አሰናድቶ ፡ የሰጠን ፡ እውነተኛ ፡ መድኀኒተ ፡ ሥጋ ፡ ስለኾነ ፡ ሊጸምና ፡ ሊታረም ፡ አይገባም ፡ ስለምትለው ።

መጻሕፍት ፡ የነቀፉ ፡ ስካርንና ፡ ጥጋብን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከስነ ፡ ፍጥረት ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ርኩስ ፡ ብለው ፡ አልነቀፉም ። ጥጋብና ፡ ስካርም ፡ በሐሊበ ፡ አገዝርዕት ፡ በጠላ ፡ ባረቂ ፡ በጠጅ ፡ ብቻ ፡ አደለም ፤ በሐሊበ ፡ እንስሳትም ፡ ይመጣል ። ይህንንም ፡ ለመረዳት ፡ ጥጃ ፡ ከማሠሪያው ፡ በተፈታ ፡ ጊዜ ፡ ሜዳ ፡ እስቲጠበው ፡ ድረስ ፡ በመፈናጨዝ ፡ ጥጋቡን ፡ የሚገልጥ ፡ ከእናቱ ፡ ጡት ፡ ያገኘውን ፤ ወተት ፡ ብቻ ፡ ተመግቦ ፡ ነው ። ጠጅ ፡ ዐረቂ ፡ ጠላ ፡ ጠጥቶ ፡ አደለም ።

እንዲዚሁ ፡ ፈረስና ፡ በቅሎም ፡ አውታራቸውን ፡ በበጠሱ ፡ ጊዜ ፡ ሰማይን ፡ በእርግጫ ፡ ለመምታት ፡ እስኪቃጡ ፡ ድረስ ፡ የሚፏልሉ ፡ ሣርና ፡ ጥሬ ፡ በልተው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ገላ ፡ ጠጅ ፡ አረቂ ፡ ጠጥተው ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ምግብ ፡ ቢኾን ፡ ሕግ ፡ በማይፈቅደው ፡ ጊዜ ፡ መከልከል ፡ በሚፈቅድበት ፡ ጊዜ ፡ በመጠን ፡ መመገብ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ዐይነት ፡ ምግብ ፡ ርኩስ ፡ ነውና ፡ ፈጽሜ ፡ እከለክላለሁ ፤ ይህ ፡ ዐይነት ፡ ... ንጹሕ ፡ ነውና ፡ ሰዓት ፡ ሳልወስን ፡ እመገባለሁ ፡ ማለት ፡ አይገባም ።

www.ethiopianorthodox.org

፬ አውሰቦና ፡ መብልዕ ፡ ሊታረም ፡ ይገባል ፡ እያሉ ፡ ለሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ሐሰት ፡ እለ ፡ የሐ ርሙ ፡ አውስበ ፡ ወይከልኡ ፡ መባልዕተ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ፈጠረ ፡ ለምእመናን ፡ ከመ ፡ ይሴሰዩ ፡ ወያእኵቱ ፡ እለ ፡ የአምርዋ ፡ ለጽድቅ ፡ እያለ ፡ ይዘልፋቸዋል ። ስለምትለው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ የጻፈ ፡ ሰብሳብ ፡ ርኩስ ፤ ስነ ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ ስለሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ጾም ፡ ንጽሕና ፡ ይገባል ፡ ስለሚሉ ፡ ሰዎች ፡ አይደለም ። ይህንም ፡ ሲያስረዳ ፡ ያገቡ ፡ እንዳላገቡ ፡ ይኹናሉና ፡ እኔስ ፡ ያለ ፡ ኀዘን ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደኔ ፤ በድንግልና ፡ ሊኖር ፡ እወዳለሁ ።

መብል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ግዳጅ ፡ አይፈጽምልንም ፡ ብንበላም ፡ አይረባንም ፡ አይጠቅመንም ፡ ብንተወውም ፡ አይጎዳንም ፡ ብሏል ። ፩ ቆሮ ፯ ፡ ፯ ፡ ፰ ፴፩—፵ ። ፰ ፰ ።

እኛም ፡ ይህነን ፡ ተመልክተን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ሚስት ፡ ከማ ግባት ፡ በድንግልና ፡ በንጽሕና ፡ መኖር ፤ ከመብላት ፡ መጾም ፡ ይበልጣል ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ግቢ ፡ ርኩስ ፡ ሥን ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ አንልም ።

፫ ጻድቁ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ በአምሳሉ ፡ ለፈጠረው ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ በመጠን ፡ ሊበላና ፡ ሊጠጣ ፡ ሊለመልም ፡ በልቶ ፡ ጠጥቶም ፡ ለሰጪው ፡ ሊያመሰግነው ፡ ብልዑ ፡ ወስግዱ ፡ ኵልክሙ ፡ ጥሉላነ ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ፈጠረው ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ሊኾን ፡ የተመደበው ፡ ሕይወቱን ፡ በረሀብ ፡ ሊያመነምነው ፡ ሊያባላሸው ፡ አላዘዘውም ፡ ስለምትለው ።

ሰውን ፡ በመጠን ፡ ተመገብ ፡ ማለት ፡ በጾም ፡ ልጓም ፡ ይዞ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የጾም ፡ ልጓም ፡ አውልቆ ፡ ስድ ፡ ለቆ ፡ በመጠን ፡ ተመገብ ፡ ማለት ፡ አጋሰስን ፡ ከመስክ ፡ ማሃል ፡ ያለልጓም ፡ ለቆ ፡ በልክ ተመገበሽ ፡ ተዩ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ ነው ።

፯ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ታቦቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አንትሙ ፡ ወመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ወዘሰ ፡ አማሰነ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱኒ ፡ ያማስኖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፩ቆሮ ፡ ፫ ፲፮—፲፯ ፡ ስለምትለው ።

እግዚአብሔር ፡ ኽዱ ፡ የሞላ ፡ ደረቱ ፡ የቀላ ፡ ሰውነቱ ፡ የፋረሰ ፡ ገላው ፡ የለሰለሰ ፡ አይቶ ፡ የሚያድር ፡ ከኾነ ፤ ሳሙኤል ፡ የኤልያብን ፡ ማማር ፡ አይቶ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ልቅበው ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤ እግዚአብሔር ፡ ፊቱን ፡ አትይ ፡ የቁመቱንም ፡ ዘለግታ ፡ ንቄዋለሁና ። እኔ ፡ ሰው ፡ እንደሚያይ ፡ የማይ ፡ አይደ ለሁም ። ሰው ፡ ፊትን ፡ ገጽን ፡ ያያል ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ልብን ፡ ያያል ፡ ማለቱ ፡ ሌሎችንም ፡ ወንድሞቹን ፡ አልፈቀድኋቸውም ፡ ብሎ ፡ ነቅፎ ፡ ወስሕከ ፡ ሥጋየ ፡ በኀጢአ ፡ ቅብዕ ። አንሰ ፡ ዕፄ ፡ ወአከ ፡ ሰብእ ። የሚል ፡ ዳዊትን ፡ የመ ረጠ ፡ ተሳስቶ ፡ ነው ፡ ይኾን ፤ እስኪ ፡ እባክህ ፡ ንገረኝ ? ፩ ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፯-፲፩ ።

እንግዲያ ፡ እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ በቀዊም ፡ በሰጊድ ፡ በትጋሀ ፡ ሌሊት ፡ በረሃብ ፡ በጽምዕ ፤ በውርጭ ፡ በብርድ ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ ፡ ያለ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲያው ፡ ከንቱ ፡ ቀርቷላ ፡ ፪ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫—፴ ። የክርስቶስ ፡ ኀይል ፡ ያድርብኝ ፡ ዘንድ ፡ መከራ ፡ ልቀበል ፡ ወደድሁ ፡ ስለዚህ ፡ አንዱን ፡ መከራ ፡ በተቀበልሁ ፡ ጊዜ ፡ አን ዱን ፡ መከራ ፡ ለመቀበል ፡ ያጸናኛልና ፡ በመሰደብ ፤ ልዩ ...



በመቀበል ፤ ሀገር ፡ ጥሎ ፡ በመሰደድ ፤ ስለክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ በመራብ ፡ በመጠማት ፡ መከራ ፡ ልቀበል ፡ ወደድኩ ፡ ማለቱ ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ ነዋ ። ፪ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ።

ጌታም ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይርህቡ ፡ ወይፀምዑ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ማለቱ ፡ በከንቱ ፡ ነዋ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

ትደንቃለህ ፡ ትገርማለህ ፡ የጾም ፡ ልጓም ፡ አውልቆ ፡ እንደ ፡ አጋሰስ ፡ ስድ ፡ ተለቆ ፡ መብላትስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ለመኾን ፡ ማብቃቱ ፡ ቀርቶ ፡ ሆድን ፡ የእህል ፡ ጉድጓድ ፡ የከብት ፡ መቃብር ፡ ማድረግ ፡ ነው ። በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በልዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ወጸግበ ፡ ከረዩ ፡ ጽጋብ ፡ ለምንዙኅ ። ሰብሐ ፡ ወገዝፈ ፡ ወርኀበ ። ኀደጎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈጣሪሁ ። ወርኀቀ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ሕይ ወቱ ። ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፲፫—፲፯ ።

ያዕቆብ ፡ በላና ፡ ጠገበ ፤ ሆዱ ፡ ሰፋ ፤ አካሉ ፡ ገዘፈ ፤ ልቡናው ፡ በሞራ ፡ ተደ ፈነ ፤ ድልድል ፡ ቅምጥል ፡ ያዕቆብን ፡ ጽጋብ ፡ አቀናጣው ። ስለዚህ ፡ ፈጣሪው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተወው ፤ ሕይወቱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ራቀ ፡ ተለየ ።

ፈጋዕክሙ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወአስተትክሙ ፡ ወተደለውክሙ ፡ ወአስባሕክሙ ፡ ልበክሙ ፡ ከመ ፡ ዘያሰብሕ ፡ ላህመ ፡ ለዕለተ ፡ ጥብሐት ። ያዕ ፡ ፭ ፭ ።

በምድር ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ አላችሁ ፤ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቸል ፡ ብላችሁ ፡ ተደላደላችሁ ፡ ተቀማጠላችሁ ፤ ለበዓል ፡ ቀን ፡ ለመታረድ ፡ ፍሪዳን ፡ ያለልክ ፡ እየመገቡ ፡ እንዲያሰቡት ፡ እናንተም ፡ ልቡናችሁን ፡ እንደዚያ ፡ አሰባችሁት ፡ ያሰኛል ።

በሰማይም ፡ አእምር ፡ ወልድየ ፡ ከመ ፡ ፈጋዕከ ፡ በሕይወትከ ፡ ሉቃ ፲፮ ፲፱-፳፭ ።

ልጄ ፡ በምድር ፡ አንተ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ስታደርግ ፡ ደኃው ፡ ይሠቀይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እወቅ ። ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ደኃው ፡ ብድሩን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያደር ጋል ፡ አንተም ፡ ብድርክን ፡ በሥቃይ ፡ ትኖራለህ ፡ የሚል ፡ ፍርድ ፡ ከማሰማት ፡ በቀር ፡ ምንምን ፡ አይረባም ፡ አይጠቅምም ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ እናንተ ፡ እንደኾናችሁ ፡ አታውቁምን ፡ ያለ ፤ ክርስቶስን ፤ በመሠረተ ፡ ሕንፃ ፤ ምእመናንን ፡ በሕንፃ ፤ መም ሕራን ፡ ሐዋርያትን ፡ ባናጺ ፡ መስሎ ፡ በተናገረበት ፡ አንቀጽ ፡ ስለሃይማኖት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰውነታችሁን ፡ በጾም ፡ አታክሱት ፡ አታጥቁሩት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያድርባችሁ ፡ ሥጋችሁን ፡ አወፍሩ ፡ መልካችሁን ፡ አሳምሩ ፡ ሲል ፡ የጻፈው ፡ አይደለም ።

ከመደላደል ፡ ከመቀማጠል ፡ መራብ ፡ መጠማት ፤ ቤት ፡ ንብረት ፡ አብጅቶ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ከመኖር ፡ የማቅ ፡ ቅዳጅና ፡ የፍየል ፡ ሌጦ ፡ ለብሶ ፡ ዋሻ ፡ ለዋሻ ፡ ፍርኩታ ፡ ለፍርኩታ ፡ እየዞሩ ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ መኾኑን ፡ ሲያ ስረዳ ።

ወዔሉ ፡ በሦቅ ፡ ወበሐሜላት ፡ ወበዘብድወ ፡ ጠሊ ፡ ተፀነሱ ፡ ተመንደቡ ፡ ... እምነቱ ፡ ዘኢይደልዎሙ ፡ ዓለም ፡ ወዔሉ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ውስተ ፡ አድባር ፡ ወበዓታት ፡ ወግበበ ፡ ምድር ፡ ወኵሎሙ ፡ ሰማዕተ ፡ ኮኑ ፡ በሃይማኖት ፡ ብሏል ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፴፯-፴፰ ።

፯ ብልዑ ፡ ወስግዱ ፡ ሊተ ፡ አለን ፡ እንጂ ፡ ጽድቅ ፡ በምትሠሩበት ፡ በምትጾሙበት ፡ ቀን ፡ ጥሉላ ትን ፡ ኢትብልዑ ፡ ብሎ አላዘዘንም፡ ስለምትለው ፡

አንተ ፤ ወይን ፡ በጾም ፡ ሊጠጣ ፡ አይገባም ፡ ያልከውን ፡ ንግግር ፡ ለማጽደቅ ፡ ወኢይደሉ ፡ ይስተይ ፡ መነሂ ፡ እምክህናት ፡ ወይነ ፡ በጾመ ፡ ፵ ፡ ወኢ በጾመ ፡ ረቡዕ ፤ ወዐርብ ፡ ወኢይጸውዑ ፡ ሰብአ ፡ ኀበ ፡ መክነ ፡ ስቴ ፡ ለስታይ ፡ ብሏል ፡ ብለህ ፡ የጠቀስከው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፤ ወእሉ ፡ ይጸወሙ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ መዓልት ፡ ወኢይትበላዕ ፡ በሙ ፡ እንስሳ ፡ ዘይወጽእ ፡ እምኔሁ ፡ ደም ፡ ወኢዘውእቱ ፡ እምእ ንስሳት ።

እሊህ ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ይጾማሉ ። ደም ፡ የሚወጣው ፡ የከብት ፡ ሥጋና ፡ ከላም ፡ የሚገኙ ፡ ወተት ፡ ቅቤ ፡ አጓት ፡ እርጎ ፡ ዕንቊላል ፡ አይበሉባቸውም ።

ወበእሉ ፡ አጽዋም ፡ እለ ፡ ተሠርዑ ፡ ይጹሙ ፡ እስከ ፡ ፱ቱ ፡ ሰዓት ፤ ወኢይ ብልዑ ፡ በሙ ፡ ሥጋ ፡ ዘእንበለ ፡ ዓሣ ።

እሊህን ፡ የታዘዙትን ፡ አጽዋም ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ይጹሙዋቸው ፡ በሚጾሙበትም ፡ ወራት ፡ ከዓሣ ፡ በቀር ፡ ሥጋ ፡ አይብሉ ።

ወዘሰ ፡ አፈድፈደ ፡ ጾመ ፡ እምዝንቱ ፡ ዘተሠርዐ ፡ ይፈደፍድ ፡ ዕሤቱ ።

ከዚህ ፡ ከታዘዘውም ፡ አብልጦ ፡ የጾመ ፡ ዋጋው ፡ ይበዛለታል ።

ወበእሉ ፡ ፯ ዕለታት ፡ ኢይብልዑ ፡ እንበለ ፡ ኅብስት ፡ ወጼው ፡ ወማይ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወእምወይንሰ ፡ ወሥጋ ፡ ተገኃሡ ፡ በእሉ ፡ ዕለታት ።

በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ የጥሬ ፡ ጨው ፡ ጭጣ ፡ በልቶ ፡ ወኃ ፡ ከመጠጣት ፡ በቀር ፡ ሥጋ ፡ አይብሉባቸው ፡ ወይን ፡ አይጠጡባቸው ።

፵ዕለተ ፡ ይጹሙ ፡ ጾመ ፡ በተፀምዶ ፡ ወበትሕትና ፡ ወይደሉ ፡ ተግኅሦ ፡ እም ጥሉላት ።

፵ውን ፡ ቀን ፡ በቀኖና ፡ በትሕትና ፡ ይጹሙት ፡ ከጥሉላት ፡ ከሥጋ ፡ ከቅቤ ፡ መለየት ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ መላልሰው ፡ ጽፈውልናል ።

እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ይሉኝታ ፡ የለህምና ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የኔን ፡ ምኞት ፡ ሲገድፍ ፡ እቀበለዋለሁ ፡ ሐሳቤን ፤ ሲያፈርስብኝ ፡ እነቅፈዋለሁ ፡ ትል ፡ ይኾናል ፡ እነቅፈዋለሁ ፡ የምትል ፡ እንደኾነ ፡ ሰዉ ፡ ኹሉ ፡ ሞተ ፡ ለኹዱ ፡ ኹድ ፡ አምላኩ ፡ መኾኑህን ፡ ይወቅልህ ።

የተቀበልከው ፡ አንደኾነ ፡ ግን ፡ ነገርህ ፡ ኹሉ ፡ ፈራሽ ፡ የእንቧይ ፡ ካብ ፡ መኾኑን ፡ እወቅና ፡ አፍረህ ፡ ተመለስ ።

፰ ስለዚህ ፡ ፈረስን ፡ ልጓም ፡ አልባ ፡ ቢሰቀሉት ፡ ገደል ፡ አገብቶ ፡ እንደሚገድል ፡ እንደዚሁ ፡ ከመጠን ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ እምብዛ ፡ ጥጋብም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ነው ፡ የሚያገባና ፡ ኹል ጊዜ ፡ ዕጉሦች ፡ መጠኞች ፡ በቃኝ ፡ ባዮች ፡ ልንኾን ፡ ይገባናል ፡ እንጂ ፡ ለእኛ ፡ ብሎ ፡ የፈጠረው ፡ በረ ከቱ ፡ ዕርም ፡ ነው ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ልንል ፡ አይገባንም ። አምላካችን ፡ [illegible] የሚታረም ፡ ነገር አይፈጥርምና ፡ አልፈጠረም ፡ ሮሜ ፡ ፲፬ ፡፩—፲፬ ። ስለምትለው ።



እኛ ፡ ይህነን ፡ ዐውቀን ፤ አንተ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስከው ፡ አኵስማዊ ፡ ሊቅ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ጾም ፡ ልጓም ፡ ፍሬሃ ፡ ጥዑም ፤ ትሕተ ፡ ኢናምስላ ፡ ለጾም ፡ ያለንን ፡ ምክር ፡ ሰምተን ፡ ባፋችን ፡ የጾም ፡ ልጓም ፡ አግብተንበታል ።

ወአንተሰ ፡ ቅድመ ፡ አመክር ፡ ርእሰከ ፡ ጹም ፡ ወተቀነይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰብሕ ፡ ወስከ ፡ ዲቤሁ ፡ አፍቅሮተ ፡ ነግድ ፡ እምሲሳይከ ፡ አንኪ ፡ ወአጽግብ ፡ ርሁበ ፡ ወፍታሕ ፡ ለእጓለ ፡ ማውታ ፡ ዝኬ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ለከ ። ያለውን ፡ ምክር ፡ ሰምተን ፡ ፎእጃችን ፡ የምጽዋት ፡ ዛብ ፡ ጨብጠንበታል ።

አንተ ፡ ግን ፡ ከአፍህ ፡ የጾምን ፡ ልጓምነት ፡ አውልቀህ ፤ የምጽዋትን ፡ ዛብነት ፡ ከእጅህ ፡ ለቀህ ፡ ጊዜ ፡ ሳትወስን ፡ ሥጋህን ፡ እየቈረጥክ ፡ ወተትክን ፡ እየጨለ ጥክ እንደ ፡ ጠባ ፡ ጥጃ ፡ ትቀናጣለህ ፤ ይህን ፡ ሳታርም፡ ራስህን ፡ የምታመጻድቅ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትሣለቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ባፈ ፡ ጮሌነት ፡ የሚወረስ ፡ መሰለህን ፡ አይወረስምና ፡ ሕግህን ፡ አርመው ።

፱ መጠጥ ፡ የኃጢአት ፡ ምንጭ ፤ ነውና ፡ ለዘለዓለም ፡ ሊጾም ፡ በተሻለ ፡ ማለታችን ፡ ግን ፡ ዘኢይ በል ፡ ጸዊሮቶ ፡ ባይጠጣው ፡ ቢጾመው ፡ በበለጠ ፡ ባማረ ፡ ነበር ፡ ስንል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ማለታችን ፡ አይደለም ፡ ብለህ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የጻፍከው ።

ባለፈው ፡ ንግግርህ ፡ መጠጥ ፡ የሚያጸይፍ ፡ ነውር ፡ የተመላበት ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ የጻፍከውን ፡ ማሻሻልህን ፡ ይገልጻል ። ስንኳን ፡ አንተ ፡ ንግግ ርህ ፡ ስሕተት ፡ መኾኑን ፡ አውቀህ ፡ ተጠጠትክበት ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ የሚበላውን ፡ የሚጠጣውን ፡ ከመመጠን ፡ የሚበላበትን ፡ የሚጠጣበትን ፡ ጊዜ ፡ ከመወሰን ፡ በቀር ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ የምንለው ፡ የለንም ።

እንዲህም ፡ ስላልኩህ ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋው ፡ ሞቶ ፡ ተገኝቶ ፡ የበከተው ፡ አውሬ ፡ የነከሰው ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ የከለከለው ፡ ዕርያ ፡ አሳማ ፡ እነዚ ህንም ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ አለና ፡ ያ ፡ ኹሉ ፡ ይበላ ፡ ማለታችን ፡ አደለም ፡ የማ ንልበትም ፡ ምክንያት ፡ መጽሐፍ ፡ ስለከለከለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ርኩስ ፡ ብለን ፡ አይደለም ፤ ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፩-፴፯ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፭ ፳፰—፴ ። ፩ ቆሮ ፡ ፰ ፯—፲፫ ። ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጸ ፡ መባልዕት ፡ ተመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ፡

## ስለ ፡ መብልዕና ፡ ትእዛዝ ።

፩ የተወደድህ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ጾም ፡ በኀቡዕ ፡ ያውም ፡ የፈቃድ ፡ የውዴታ ፡ ነው ፡ ብዬሃለሁ ። ስለምትለው ።

አንተ ፡ ከልቡናህ ፡ ፈጥረህ ፡ ጾም ፡ የፈቃድ ፡ ነው ፡ ብትለኝ ፤ እኔም ፡ ከመ ጻሕፍት ፡ አግኝቼ ፡ ከመምሕራን ፡ ሰምቼ ፡ ጾም ፤ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፤ ጌታ ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፤ በቃል ፡ ያስተማሩት ፤ በግብር ፡ የፈጸሙት ፤ ቢጠ ብቁት ፡ ዋጋ ፡ የሚያሰጥ ፡ ባይጠብቁት ፡ ፍዳ ፡ የሚያመጣ ፡ በሕግ ፡ የታዘዘ ፡ [illegible] ፡ ነው ፡ ብዬሃለሁ ፡ በ፲፱ና ፡ በ፳ ፡ ምዕ ፡ ተመልከት ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ እንደዚሁ ፡ መብላትና ፡ መጠጣትም ፡ ባስፈለገህ ፡ ጊዜ ፡ የፈቃድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በግድ ፡ የትእዛዝ ፡ እንዳልኾነ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሲያስረዳ ፤ ወባሕቱ ፡ ለኵሉ ፡ በከመ ፡ አዘዞ ፡ ልቡ ፡ ይላል ፤ ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፩—፭ ። ስለምትለው ።

አንዱ ፡ እንደ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ሥጋንም ፡ ተክልንም ፡ ልብላ ፡ ቢል ፤ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ባንያንና ፡ እንደ ፡ ህንድ ፡ ካንተም ፡ ወገኖች ፡ እንደ ፡ ሚሲስኋይት ፡ ደንብ ፡ ተክልና ፡ እኽል ፡ እንጂ ፡ ሥጋ ፡ አልቀምስም ፡ ቢል ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በመብል ፡ በመጠጥ ፡ አይደለምና ፡ ኹሉም ፡ እንደየፈቃዱ ፡ የወደደውን ፡ ይብላ ፡ ሲል ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ ሐሳብ ፡ ጾምን ፡ ሠርዞ ፡ ባስፈለገው ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ይብላ ፡ ለማለት ፡ የጻፈው ፡ አይደለም ።

፲ ምጽዋትና ፡ ጸሎት ፡ ጾምና ፡ ንጽሕና ፡ ምግበ ፡ ነፍስ ፡ ስለኾኑ ፡ አምልኮ ፡ አለኝ ፡ ለሚል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ያሉ፡ ነገሮች ፡ ረሃብ ፡ ሊገኝበት ፡ ሕሊናው ፤ ያስገድደዋልና ፡ አስፈላጊውም ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

እኛ ፡ ይህነኑ ፤ አውቀን ፡ ሕግ ፡ አድርገን ፡ ይዘነዋል ፡ ራሳችንም ፡ እንሠራዋለን ፡ ለሌላም ፡ እናስተምረዋለን ፡ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ይህን ፡ እያወቅህ ፡ ሳትማር ፡ የተማርክ ፡ ሳታውቅ ፡ ያወቅህ ፡ እየመሰልክ ፡ ምጽዋት ፡ ጾም ፡ የፈቃድ ፡ ነው ።

ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዕንቅፋት ፡ የምትኾን ፡ ስለምንድነው ።

በውነቱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ጥፋት ፡ ግድ ፡ ይመጣል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥፋትን ፡ ለሚያመጣት ፡ ሰው ፡ ወዮለት ፤ በኔ ፡ ካመኑ ፡ ከእነዚህ ፡ ሕፃናት ፡ አንዱን ፡ ከሚያስት ፡ የወፍጮ ፡ ደንጋይ ፡ በንገቱ ፡ ዐሥሮ ፡ ከጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ቢጥሉት ፡ በተሻለው ፡ ነበረ ፡ ብሏልና ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መጥውዎ ፡ ለሰይጣን ፡ ይሥርዎ ፡ ሥጋሁ ፡ ወትድኅን ፡ መንፈሱ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ፡ እንዳለው ፡ ዛሬ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾነህ ፡ ኋላ ፡ ነፍስህ ፡ ከምትጎዳ ፡ ይህን ፡ ባሰብክበት ፡ ቀን ፡ የወፍጮ ፡ ደንጋይ ፡ ባንገትህ ፡ አሥረህ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ብትጠልቅ ፡ በተሻለህ ፡ ነበረ ። ማቴ ፡ ፲፰ ፯—፰ ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፩-፫ ። ፩ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፭ ።

፲፩ ይልቁንም ፡ የእንባ ፡ ጸሎት ፡ ሰማያዊ ፡ ስጥወታን ፡ ጎትታ ፡ አምጥታ ፡ የምታስገኝ ፡ መንገን ፡ ማግኘት ፡ መቃጥን ፡ ስለኾነች ፡ ለውነተኛው ፡ ክርስቲያን ፡ ዋና ፡ መሣሪያው ፡ ለዓለምና ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚያሸንፍበት ፡ ፕንዘቡና ፡ ሕይወታዊ ፡ ምግቡ ፡ ልትኾን ፡ ይገባዋል ፡ ዘፍ ፡ ፴፪ ፳፬—፴ ። ሉቃ ፲፭ ፳—፲፫ ። ፲፰ ፩—፰ ። ስለምትለው ።

ይህ ፡ የማይካድ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጌታ ፡ ከዚህ ፡ ከሚመጣው ፡ ኹሉ ፡ በጸሎታችሁ ፡ ማምለጥ ፡ ትችሉ ፤ ዘንድ ፤ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ትጉ ፡ ያለ ፤ በምድር ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወጥመድ ፡ ድንገት ፡ እንድትወርድባቸው ፡ ያችም ፡ ዕለት ፡ ድንገት ፡ ትደርስባችኋለችና ፡ ልቡናችሁን ፡ በመብላት ፡ በመጠጣት ፡ በመደሰት ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ በማውጣት ፡ በማውረድ ፡ እንዳታደነድኑ ፡ እወቁ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፤ ነው ፡ ሉቃ ፡ ፳፩ ፴፬—፴፮ ።



ስለዚህ ፡ ሊቁ ፡ ይህን ፡ የጌታን ፤ ቃል ፡ ተመልክቶ ፡ እስመ ፡ ጾም ፡ እማ ፡ ለጸሎት ፡ ወእኅታ ፡ ለአርምሞ ፡ ወነቅዓ ፡ ለአንብዕ ፡ ወጥንተ ኵሉ ፡ ገድል ፡ ሠናይ ።

ጾም ፡ ለጸሎት ፡ እናቷ ፤ ለአርምሞ ፡ እኅቷ ፤ ለአንብዕ ፡ መፍለቂያዋ ፤ ለበጎ ፡ ትሩፋት ፡ ኹሉ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ናት ፡ ብሏልና ፡ ከጾም ፡ ተለይቶ ፡ እየበሉ ፡ እየጠጡ ፡ የዕንባ ፡ ጸሎት ፡ የማትገኝ ፡ መኾኑን ፡ አውቀህ ፡ በዚህ ፡ በሐሳብህ ፡ ላይ ፡ ጾምን ፡ ጨምርበት ። እየበሉ ፡ እየጠጡ ፡ የሚያለቅሱትስ ፡ የስካር ፡ እንጂ ፡ የኀዘን ፡ ልቅሶ ፡ አይባልም ።

፲፪ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ሲያዝን ፡ አስቀድማችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥቱን ፡ ጽድቁንም ፡ ፈልጉ ፡ ሌላው ፡ ኹሉ ፡ ይጨመርላችኋል ፡ ይለናል ፡ ማቴ ፡ ፮ ፴፫ ፡ የግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የሚገኘው ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጽድቅ ፡ ደስታ ፡ ሰላም ፡ እየሠሩ ፡ ከፉ ፡ ጠባይን ወደ ፡ በጎ ፡ ለውጠው ፡ ከሰዉ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ በፍቅር ክልኖሩ ፡ መብል ፡ ብቻ ፡ ቢለውጡ ፡ ከቶ ፡ አይገኝም ፤ ሮሜ ፡ ፲፬ ፲፯ ስለምትለው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲህ ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ሰማያዊ ፡ ድልብ ፡ (ምጽዋት ፡ ) አድልቡ ፡ እንጂ ፡ ምድራዊ ፡ ድልብ ፡ አታድልቡ ።

አንድ ፡ ባሪያ ፡ ለኹለት ፡ ጌታ ፡ መገዛት ፡ እንዳይቻለው ፡ እናንተም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለግዚአብሔር ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለገንዘብ ፡ ልትገዙ ፡ አትችሉም ፡ እያለ ፡ ቢያስተምራቸው ፡ ገንዘብ ፡ ካላከማቸን ፡ ምን ፡ እንበላለን ፡ ምን ፡ እንጠጣለን ፡ እንዲሉት ፡ አውቆ ፡ ይህንስ ፡ ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ በአፍዓ ፡ ያሉ ፡ አሕዛብም ፡ ያደርጉታል ፡ ለእናንተስ ፡ ይኸ ፡ ኹሉ ፤ እንዲያሻችሁ ፡ አውቆ ፡ የሰማይ ፡ አባታችሁ ፡ ይሰጣችኋልና ፡ አስቀድማችሁ ፡ መንግሥቱን ፡ ጽድቁን ፡ ሹ ፡ ፈልጉ ። የቀረው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ብዕል ፡ ግን ፡ በዕራት ፡ ላይ ፡ ዳረጎት ፡ እንዲጨመር ፡ ይጨመርላችኋል ፡ ሲል ፡ ነው ።

አንተ ፡ ግን ፡ ተቈርቍረህ ፡ የምታስተምረው ፡ ሕግ ፡ ሰዱሰ ፡ መዋዕለ ፡ ተገብረ ፡ ተግባረከ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ የሚለውን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍርሰን ፡ ዘወትር ባለመሥራታችን ፡ በዓል ፡ በማክበራችን ፤ ቀን ፡ ሳይለዩ ፡ ዘወትር ፡ የሚሠሩ ፡ እስላሞች ፡ በብዕለ ፡ ሥጋ ፡ በለጡን ፡ እያልክ በመቈርቈር ፡ ነው ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ በተከተለ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ያንተ ፡ ትምርት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፤ ያንተንም ፡ ትምርት ፡ በተከተለ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የጌታ ፡ ቃል የለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ቃል ፡ አንተን ፡ ይወቅስሃል ፤ ባንተ ፡ ከማስፈረድ ፡ በቀር ፡ ያንተን ፡ ሐሳብ ፡ መስሎ ፡ አይገኝም ፡ የትኛውን ፡ ሐሳብህን ፡ ሊገድፍልህ ፡ ጠቀስከው ።

ደግሞስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የሚገኘው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጽድቅ ፡ ደስታ ፡ ሰላም ፡ በመሥራት ፡ ነው ፡ ማለትህ ፤ በጀኛው ፡ ምዕራፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ሊኾን ፡ የተመደበው ፡ ሕይወቱ ፡ በረሃብ ፡ ሊያመነምነውና ፡ ሊያበላሸው ፡ አላዘዘም ፡ እንዳልከው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆዱ ፡ በሞላ ፤ ደረቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በቀላ ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ የሚያድር ፡ መሰለህን ። መንፈስ ፡ ቅዱስማ ፡ የሚያድር ፡ በምኑናን ፡ በትሑታን ፡ አይደለምን ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፩ ፳፯–፴ ። ፲፩ ፳–፲፩ ።

ጽድቅ ፡ መሥራትስ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ዘወትር ፡ በመሥራት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ በማድለብና ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ በመብላት መሰለህን ፡

ጽድቅማ ፡ የሚሠራ ፡ ሐር ፡ ወሚጥ ፡ ኰሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ገንዘብን ፡ ሰጥቶ ፡ መጽውቶ ፡ ጮማ ፡ በመቍረጥ ፡ ፍትፍት ፡ በመዋጥ ፡ ጠጅ ፡ ዐረቂ ፡ በመጠጣት ፡ ፈንታ ፤ ጥሬ ፡ በመብላት ፡ ውኃ ፡ በመጠጣት ፡ ሰውነትን ፡ በመቅጣት ፡ አይደለምን ። ማቴ ፡ ፳ ፡ ፫—፲፪ ፡ ዳን ፡ ፩ ፡ ፫-፲፰ ፡ ፳ ፡ ፫– ፡ ፲፪ ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫-፴፩ ። ፲፪ ፡ ፺-፲፩ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስስ ፡ ወፍሬሁሰ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተፋቅሮ ፡ ፍሥሐ ፡ ሰላም ፡ ብሎ ፡ የጠቀሰው ፡ ገላ ፡ ፭ ፡ ፳፪ ፡ አንተ ፡ ተቀን ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ፡ ፋርኖ ፡ እየገመጥክ ፡ ወተት ፡ እየጨለጥክ ፡ ያሳማ ፡ ጮማ ፡ እየቆረጥክ ፡ በሶፋ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በአልጋህ ፡ ላይ ፡ እየተገላበጥክ ፡ የምታደርገውን ፡ ጊዜያዊ ፡ ደስታ ፡ መሰለህን ፤ አይደለም ።

ርሱስ ፡ ደስታ ፣ የሚለው ፤ ስማኝ ፡ ልንገርህ ፤ ቅዱሳን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቀው ፡ አቃለው ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሰጥተው ፡ መጽውተው ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ።

፩ኛ ፡ ከመዓርገ ፡ ሃይማኖት ፡ ይደርሳሉ ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ፩ነት ፡ ፫ትነትን ፡ ማመን ፡ አይደለም ፤ የለመንኩት ፡ ነገር ፡ ይፈጸምልኛል ፡ ብሎ ፡ ግብር ፡ መግባት ፡ ነው ።

ኹለተኛ ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ጽማዌ ፡ ይሰጣቸዋል ፤ ጽማዌ ፡ ማለት ፡ መላእክትን ፡ ለተልእኮ ፡ ሲወጡ ፡ ሲወርዱ ፡ ማየት ፤ ነው ፡ የሚሠሩትን ፡ ግን ፡ አያውቁትም ።

፫ተኛ ፡ በጽማዌ ፡ ላይ ልበዌ ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ከልባዌ ፡ መዓርግ ፡ ሲደርሱ ፡ መላእክትን ፡ ሲወጡ ፡ ሲወርዱ ፡ ያያሉ ፡ የሚሠሩትንም ፡ ያውቃሉ ።

፬ተኛ ፡ በልባዌ ፡ ላይ ፡ ጣዕመ ፡ ዝማሬ ፤ ይሰጣቸዋል ፡ ጣዕመ ፡ ዝማሬ ፡ ማለት ፡ የሚጸልዩትን ፡ ጸሎት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ምሥጢሩን ፡ ማወቅ ፡ ያነኑም ፡ አመስግኖ ፡ አለመጥገብ ፡ አለመሰልቸት ፡ ነው ።

፭ተኛ ፡ በጣዕመ ፡ ዝማሬ ፡ ላይ ፡ አንብዐ ፡ ንስሐ ፡ ይሰጣቸዋል ። አንብዐ ፡ ንስሐ ፡ ማለት ፊታቸውን ፡ ሳይከፋው ፡ እንባቸው ፡ እንደ ፡ ሰን ፡ ወኃ ፡ ሳየቋርጥ ፡ መፍሰስ ፡ ነው ።

፮ተኛ ፡ በአንብዐ ፡ ንስሐ ፡ ላይ ፡ ኵነኔ ፡ ዑቃቤ ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ኵነኔ ፡ ማለት ፡ ሥጋን ፡ ለነፍስ ፡ ማስገዛት ፡ ነው ፤ ዑቃቤ ፡ በዚያው ፡ መጽናት ፡ ነው ፡

፯ተኛ ፡ በኵነኔ ፡ በዑቃቤ ፡ ላይ ፡ ሑሰት ፡ ንጻሬ ፡ ይጨመርላቸዋል ። ሑሰት ከዚህ ፡ ኸኖ ፡ ከኹሉ ፡ መድረስ ። ንጻሬ ፤ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ ኾኖ ፡ መላእክትን ፡ በእየከተማቸው ፡ እየገቡ ፡ ማየት ፡ ነው ።

፰ተኛ ፡ በሑሰት ፡ በንጻሬ ፡ ላይ ፡ ተሠጥሞ ፡ ፍቅረ ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይጨመርላቸዋል ፤ ተሠጥሞ ፡ በ[illegible]



ነው ፡ ፍቅረ ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ሳይለያዩ ፡ አስተካክሎ ፡ መውደድ ፡ ነው ።

፱ነኛ ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ከዊነ ፡ እሳት ፡ ነጽሮተ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ ጦር ፡ ይጠፋላቸዋል ። ፪ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፭–፱ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ፍሥሐ ፡ ሰላም ፡ የሚለው ፡ ይህ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የቆጠርኩልህ ፡ ማዓርግ ፡ ኹሉ ፡ በእየደረጃ ፡ በተጨመረላቸው ፡ ጊዜ ፡ የሚሰማቸውን ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለጊዜው ፡ ሲበሉት ፡ ሲጠጡት ፡ ደስ ፡ እያለ ፡ ገብቶ ፡ ከትንሽ ፡ ሰዓት ፡ በላይ ፡ ተለውጦ ፡ ሸቶ ፡ ልውጣ ፡ ልውጣ ፡ እያለ ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ጊዜያዊውን ፡ ደስታ ፡ አይደለም ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ መብልን ፡ ጣፋጩን ፡ በመራራ ፡ ከፍተኛውን ፡ በዝቅተኛ ፡ እየለወጡ ፡ ከዚያውም ፡ እየቀነሱ ፡ ካልሔዱ ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ እውነተኛው ፡ ጽድቅ ፡ ፍሥሐ ፡ ሰላም ፡ አይገኝም ።

፮ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ግን ፡ ለሥጋዊ ፡ ሕይወት ፡ ብቻ ፡ መቆሚያው ፡ ስለኾነ ፡ ለነፍስ ፡ ምንም ፡ አይደለምና ፡ በጽድቅ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ በታ ላይ ፡ ብንበላ ፡ አንጨምርም ፡ ባንበላም ፡ አንጐድልም ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፰ ። ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ስለ ፡ መብል ፡ ሲናገር ፡ ኹሉ ፡ ተፈቅዶልኛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኹሉም ፡ አይረባም ፡ መብል ፡ ለሆድ ፡ ሆድም ፡ ለመብል ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለሆድና ፡ መብል ፡ ያጠፋቸዋል ፡ ይላል ። ፩ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፪—፳ ። አሁን ፡ ግን ፡ ሥጋችን ፡ ካፈር ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ አፈርም ፡ ይመለሳል ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ሰማይና ፡ ምድርም ፡ ቢኾን ፡ ሐላፊ ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

እኛ ፡ ይህን ፡ አጡቀን ፡ ከማድለብ ፡ መመጽወት ፤ ከመብላት ፡ መጾም ፡ ይበልጣል ፡ እያልን ፡ ለራሳችንም ፡ እንሠራዋለን ፡ ሕግ ፡ አርገን ፡ ይዘነዋል ፡ ለሌላም ፡ እናስተምረዋለን ። አንተ ፡ አታስተምረንም ።

እረ ፡ አንተ ፡ ይህን እያወቅህ ፡ ጾም ፡ ሕግ ፡ አደለም ፡ ዝክር ፡ ተዝካር ፡ አይገባም ፡ እያልክ ፡ ለሕዝቡ ፡ መጥፎ ፡ አርዓያ ፡ ለምን ፡ ትኾናለህ ፡ የሕዝቡን ፡ ሕሊና ፡ ለምን ፡ ታጠራጥረዋለህ ።

፯ የማየልፈው ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ለማግኘት ፡ ብትፈልግ ፡ ግን ፡ በሩ ፡ መክፈቻው ፡ መግቢያ ፡ የሱስ ፡ ብቻው ፡ መኾኑ ፡ አስቀድመህ ፡ ማመን ፡ ያስፈልገሃል ፡ መልካሙ ፡ የጽድቅ ፡ ምግባርህ ፡ ግን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ከእምነት ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡ ይጨበጨባል ። ስለምትለው ።

የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በር ፡ መንገድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ የማይከድ ፡ እውነት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ዮሐንስ ፡ በመልእክቱ ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፮ ፡ በርሱ ፡ አምኜ ፡ እኖራለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ርሱ ፡ እንደሔደው ፡ ሊሔድ ፡ ርሱ ፡ እንደኖረው ፡ ሊኖር ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ነገረን ። ርሱን ፡ መስሎ ፡ ካልኖሩ ፡ ማመኑ ፡ ብቻ ፡ የሚጠቅም ፡ አደለም ።

ማመኑ ፡ ብቻ ፡ የሚጠቅምስ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ያባቴን ፡ ፈቃድ ፡ ከሚፈጽም ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ የሚለኝ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ፡ ባላለም ፡ ነበረ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፩ ።

፰ መልካም ፡ ምግባር ፡ ማለትም ፡ ሃይማኖት ፡ አለኝ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አይሁድ ፡ ዓረሚ ፡ እስ[illegible] ፡ ያዘዘው ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባው ፡ ፲ቱ ፡ ቃላት ፡ ኦሪትንና ፡ ፮ቱ ፡ ቃላተ ወንጌልን ፡ ብቻ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ነው ፡ እንጂ ፤ ሌላውስ ፡ ኹሉ ፡ የሚሠራው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነው ። የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ፍጻሜና ፡ ሕይወታዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ማለትም ፡ እነዚህ ፡ ፲ቱ ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ መኾናቸውን ፡ አስተውል ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ፴፭—፵ ። ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፰—፲ ፡ ስለምትለው ።

የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ፍጻሜ ፡ ይህ ፡ አይደለም ፤ ፍጻሜያቸው ፡ ይህ ፡ ከኾነማ ፡ ያ ፡ ባለጸጋ ፡ ዘንተሰ ፡ ኵሎ ፡ ዐቀብኩ ፡ እምንዕስየ ፡ ምንትኑ ፡ ዘተርፈኒ ።

ይህን ፡ ኹሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሬ ፡ ጠብቄያለሁ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፤ ፍጹም ፡ ልትኾን ፡ ከወደድክስ ፡ አንዲት ፡ ቀርታሃለች ፡ ለምን ፡ አለው ፤ አዎን ፡ ኹሉን ፡ ፈጽመሃል ፡ የቀረህ ፡ የለም ፡ አይለውም ፡ ነበረን ። የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ፍጻሜያቸውስ ፡ ያለህን ፡ ገንዘብህን ፡ ኹሉ ፡ ሸጠህ ፡ ለውጠህ ፡ መጽውተህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ ብሎ ፡ ያስተማረው ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ ነው ። ፍጹም ፡ ልትኾን ፡ ከወደድክስ ፡ ብሎ ፡ ፍጹምነትን ፡ ለሕገ ፡ ምናኔ ፡ እንደሰጠ ፡ አስተውል ። ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፮—፳፪ ።

፲፱ እውነትና ፡ ሐሰት ፡ ብርሃንና ፡ ጨለማ ፡ ጨውና ፡ አልጫ ፡ ጣሙን ፡ ለይተህ ፡ ሳታውቀው ፡ በምግባርህ ፡ ሳይኾን ፡ በፍህ ፡ ብቻ ፡ ሃይማኖት ፡ አለኝ ፡ ማለትህ ፡ ግን ፡ ለባዕድ ፡ መሳቂያ ፡ ለዘመድ ፡ መሰቀቂያ ፡ መኾንህን ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናልና ፡ ያሳፍራል ። አሁን ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ የሚጠቅመው ፡ ሐፍረትና ፡ ይሉኝታ ፡ ነውና ፡ ለጉድለትህ ፡ እፈርበት ፡ እንጂ ፡ አትፈክርበት ፡ ኤር ፡ ፰ ፲—፲፪ ። ራእ ፡ ፫ ፲፬—፲፰ ፡ ስለምትለው ።

እውነትንና ፡ ሐሰትን ፤ ጨለማንና ፡ ብርሃንን ፡ ያለየህ ፤ የጨውና ፡ ያልጫ ፡ ጣም ፡ ያላወቅህ ፡ በምግባር ፡ ሳይኾን ፡ በፍህ ፡ ብቻ ፡ ሃይማኖት ፡ አለኝ ፡ የምትል ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ይህንም ፡ ስልህ ፡ በእውነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሐሰት ፡ አይደለም ።

(ሀ) ፫ቱ ፡ ፶ት ፡ ፹ወ፩ዱ ፡ መጻሕፍትን ፡ እንደተዉልን ፤ ትናገራለህ ። ገጽ ፡ ፪ ፡ መሥ ፡ ፳ ። እልፍ ፡ ብለህ ፡ ደግሞ ፡ ፫ቱ ፡ ፶ት ፡ ከቈጠሯቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ገሚሶቹን ፡ ለምስክርነት ፡ አይበቁም ፡ ብለህ ፡ ገንጥለህ ፡ ጥለህ ፡ ፷፮ቱን ፡ ብቻ ፡ ጠርዘህ ፡ ይዘሃል ። ስለዚህ ፡ እውነትንና ፡ ሐሰትን ፡ አለየህም ፡ ብየሃለሁ ፡ ገጽ ፡ ፮ ፡ መሥ ፡ ከ፫-፰ ።

(ለ) ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ካልክ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ከመኾኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ኦእግዚኦ ፡ መሐርሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ እያለ ፡ በመለኮቱ ፡ ያማልድ ፡ ነበረ ትላለህ ። ገጽ ፡ ፵፩ ፡ መሥ ፡ ፳፮ ፤ በመለኮቱ ፡ ማማለድ ፡ አለበት ካልኩ ፡ ፍጡር ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ያሰኝብኛል ፡ ባለማለትህ ፡ ጨለማና ፡ ብርሃን ፡ ያለየህ ፡ አንተነህ ፡ አልኩህ ።

(ሐ) ለብሉያት ፡ ለሐዲሳት ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ የኾነ ፡ ኄኖክን ፡ ለመጽሐፈ ኄኖክ ፡ ኋደኛውና ፡ ምስክሩ ፡ ቍርዓን ፡ ወይም ፡ ማሕዱስ ፡ የተባለው ፡ የመሐመዳውያን ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ ስላልክ ፡ የጨውና ፡ ያልጫ ፡ ጣዕም ፡ ያለየህ ፡ አንተነህ ፡ ብየሃለሁ ፡ ገጽ ፡ ፰ ፡ መስ ፳፰ ።

(መ) ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ማለት ፡ ጌታን ፡ ሐዋርያትን ፡ መስሎ ፡ መኖር ፡ ነው ። ጌታንም ፡ መምሰል ፡ ተባሕትዎ ፡ ይዞ ፡ በገዳም ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡ ፵ ፡ ሌሊት ፡ መጾም ። ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ ጎጆ ፡ ሳይሠራ ፡ መኖር ። በጠቅላላው ፡ መላ ፡ ዘመንን ፡ መስቀል ፡ ሞትን ፡ ተሸክሞ ፡ መኖር ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የትሩፋት ፡ ሥራዎች ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ መሠራታቸው ፡ ይቅር



ጥረዋል ። ገጽ ፡ ፫ ፡ መሥ ፡ ከ፲፩-፳፯ ። ስለዚህ ፡ በምግባርህ ፡ ሳይኾን ፡ በፍህ ፡ ብቻ ፡ ሃይማኖት ፡ አለኝ ፡ የምትል ፡ አንተነህ ፡ ብየሃለሁ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አንተ ፡ ባታውቀው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለዘመድ ፡ መሰቀቂያ ፡ ለባዕድ ፡ መሳቂያ ፡ ኾነሃልና ፡ በጉድለትህ ፡ እፈርበት ፡ እንጂ ፡ አትፎክርበት ።

፲ ያገሬ ፡ መነኰሴዎች ፡ ከዓለም ፡ ተለይተናል ፡ ብለው ፡ ማር ፡ በሚገኝበት ፡ ዱር ፡ ተቀምጠው ፡ ሥራ ፤ ጠልተው ፡ ለሰው ፡ ሳይረዱና ፡ በሕግ ፡ ሕፃናት ፡ ሳይወልዱ ፡ የሥጋ ፡ ምኞት ፡ ይዘው ፡ መክሊታቸውን ፡ ቀብረው ፡ በዓለም ፡ ዘንድ ፡ ከብረው ፡ እንደሚኖሩት ፡ አይምሰልህ ፡ ስለምትለው ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በገጽ ፡ ፬ ፡ መሥ ፡ ፲፰ ፡ መነኮስ ፡ ዕድሜ ፡ ልኩ ፡ ከተማ ፡ ሳይገባ ፡ በረሃ ፡ ሊኖር ፡ ይገባው ፡ ነበረ ፡ አልፈጸሙትም ፡ ብለህ ፡ ነቀፍካቸው ። ደግሞ ፡ አሁን ፡ ከዓለም ፡ ተለይተው ፡ በበረሃ ፡ ልጅ ፡ ሳይወልዱ ፡ ይኖራሉ ፤ እያልክ ፡ ትነቅፋቸዋለህ ፤ እንግዲህ ፡ የትኛውን ፡ ቃልህን ፡ እንቀበልህ ። ደግሞ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያትን ፡ መስለው ፡ አልኖሩም ፡ ትላለህ ፤ ሐዋርያትን ፡ ለመምሰል ፡ ኹሉን ፡ ጥለው ፡ ሲኾኑ ፡ ልጅ ፡ አልወለዱም ፡ ብለህ ፡ ትነቅፋቸዋለህ ፤ የትኛውን ፡ ቢይዙ ፡ ይሻል ፡ ይኾን ፡ እውነትንና ፡ ሐሰትን ፡ ጨውና ፡ አልጫን ፡ ለይተህ ፡ ያላወቅህ ፡ አንተነህ ፡ የምልህ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ማር ፡ በሚገኝበት ፡ ተቀመጡ ፡ ብለህ ፡ ትነቅፍስ ፡ ዘንድ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅን ፡ ወሲሳዩ ፡ አንበጣ ፡ ወመዓረ ፡ ገዳም ፡ እንዲለው ፡ አልሰማህምን ፡ ማቴ ፡ ፫ ፬ ። አያገኙትም ፡ እንጂ ፡ ካገኙትስ ፡ የርሱን ፡ ያህል ፡ ይበቃቸዋል ። ስለሕገ ፡ ምንኵስና ፡ መቅድም ፡ በገጽ ፡ ፵፪-፶ ፡ በሰፊው ፡ ስለጻፍኩልህ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ደግሜ ፡ ልጽፍ ፡ አላስፈለገም ፡ ያነኑ ፡ ተመልከት ።

፲፩ እኔ ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ እኖራለሁ ፡ የሚል ፡ እንዳለ ፡ ክርስቶስ ፡ በሔደበት ፡ አሠር ፡ ሊከተለው ፡ ይገባዋል ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታይ ፡ ለመኾን ፡ ባካሔድህና ፡ በኑሮህ ፡ ካልተለየህ ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም፡ምን፡ በመሰለ፡ ዘዴ ፡ ከጻድቃን ፡ ጋራ ፡ ትተባበራለህ ፡ ስለምትለው ።

እኒህን ፡ ጥቅሶች ፡ ሌላው ፡ ባንተ ፡ ሊጠቅስብህ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ በሕገ ፡ ዓረሚ ፡ የምትኖር ፡ አንተ ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ልትጠቅሰው ፡ አይገባህም ፡ በእውነቱ ፡ ይህነን ፡ ጥቅስ ፡ ለመጥቀስ ፡ ከፈለግህ ፡ ይህን ፡ የተዋስከውን ፡ መጥፎ ፡ ባህል ትተህ ፡ ወዳባቶችህ ፡ ሃይማኖትና ፡ ባህል ፡ ተመለስ ።

## ምዕራፍ ፤ ፳፪ ።

## ስለ ፡ ልማድ ።

፩ ወንድሜ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ያገራችንና ፡ ያባቶቻችን ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ለቅዱሱ ፡ አምላክ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቃዋሚና ፡ ተጻራሪው ፡ መኾኑ ፡ ልገልጽልህ ፡ እወዳለሁ ፡ ለምሳሌ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሐፈ ፤ ገጽከ ፡ ብላዕ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘውን ፡ ያገሬ ፡ መሪዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ዛሬ ፡ በዓል ፡ ነው ፡ እትሥሩ ፡ ነገ ፡ ጾም ፡ ነው ፡ አትብሉ ፡ እያሉ ፡ ውግዘት ፡ በሚሉት ፡ የሸረሪት ፡ ዘሐ ፡ አጥብቀው ፡ አሥረው ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ፈለጉት ፡ ሲነዱትና ፡ ሲያዞሩት ፡ ይኖራሉ ፡ ስለምትለው ።

እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ያለው ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በበላ ፡ ጊዜ ፡ የምሽትህን ፡ ቃል ፡ ሰምተህ ፡ ከርስዋ ፡ እንዳትበላ ፡ ካዘዝኩህ ፡ [illegible] ምድር ፡ ስላንተ ፡ የተረገመች ፡ ትኹን ፤ ዕድሜህን ፡ ኹሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ክርስዋ ፡ በድኅም ፡ ትበላለህ ፡ ምድር ፡ እሾህ ፡ አሜከላ ፡ ታብቅልብሃለች ፤ የም
ድርንም ፡ ቡቃያ ፡ ትበላለህ ፤ በፊትህ ፡ ወዝ ፡ እንጀራ ፡ ትበላለህ ፡ ወደ ፡ ፈጠ
ርክብት ፡ ምድር ፡ እስክትመለስ ፡ ድረስ ፡ መሬት ፡ ነህና ፡ ወደመሬትም ፡ ትመ
ለሳለህ ፡ ብሎ ፡ ረገመው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ሕግ ፡ ሠራለት ፡ አይባልም ።
ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፯–፳ ።

ሕግ ፤ አድርጎ ፡ የሠራለትስ ፡ አስቀድሞ ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ እንዳይበላ ፡ ያዘ
ዘው ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፡ ዘፍ ፡ ፪ ፲፮–፲፯ ፡ ኹለተኛ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ከ፲ቱ ፡
ቃላት ፡ ጋራ ፤ ተዘክር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበትን ፡ ነው ። ዘጸአ ፡ ፳፰—፲፪ ።

ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ በመፍረሱ ፡ ሕግ ፡ ኾኖ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ከኾነ ፤
ምድርን ፡ አርሞ ፡ ኰትኩቶ ፡ ደስ ፡ የምታሰኝ ፡ የተክል ፡ ቦታ ፤ ወይም ፡
ጨፌ ፡ መስክ ፡ ያደረጋትም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ምድር ፡ ስላንተ ፡ የተረገመች ፡
ትኹን ፡ እሾህ ፡ ደንደሮ ፡ ታብቅል ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍርሷልና ፡ ይቀ
ጣል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ኄኖክና ፡ ኤልያስም ፡ መሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብእ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ ያለ
ውን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍርሰው ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ወጥተዋልና ፡ ይቀጣሉ ።
ማለት ፡ ነው ፡ ዘፍጥ ፡ ፭ ፡ ፳፬ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፭ ። ነገ ፡ ካል ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

ሔዋንንም ፡ ልጅሽን ፡ በፃዕር ፡ በጋዕር ፡ ውለጂ ፡ ብሎ ፡ ረግሟት ፡ ነበር ፡ እነሆ ፡
ዛሬ ፡ ሐኪሞች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ ያለጭንቅ ፡ ሴቶችን ፡ እንዲወልዱ ፡ ያደርጓ
ቸዋል ። ስለዚህ ፡ ሐኪሞች ፡ ሕግ ፡ አፍራሾች ፡ ተብለው ፡ ይቀጣሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

አንተ ፡ ተከብቶች ፡ የማትሻል ፡ መሽ ፡ ለሆዴ ፡ ነጋ ፡ ለሆዴ ፡ ስለኾንክ ፡
ርግማንህን ፡ እንደ ፡ በረከት ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ አድርገህ ፡ ጠብቀው ፡ እንጂ ፡
እኛስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ መጽሐፈ ፡ ዕዳችንን ፡ የደመሰሰልን ፡ መርገማችንን ፡ የፋ
ቀልን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የምትሹኝ ፡ ኅብስት ፡ አበርክቼ ፡ ስላበላኋችሁና ፡
ስላጠገባችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተአምራቱን ፡ ስላያችሁ ፡ አደለም ። ከእንግዲህስ ፡
ወዲያ ፡ ፃሩ ፡ ጋሩ ። ፃሩ ፡ ጋሩም ፡ የምላችሁ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ለሚኖ
ረው ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እኔ ፡ ለምሰጣችሁ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ምግብ ፡
(ሥራ ፡) ነው ፡ እንጂ ፡ ለዚህ ፡ ለሐላፊው ፡ ምግብ ፡ አይደለም ። ይህን ፡ ሐላ
ፊውን ፡ ምግብስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አሳልፎታል ፡ ብሎ ፡ የእርግማናችንን ፡
መሠረዝ ፡ የምሥራች ፡ ስለነገረን ፡ ለዚህ ፡ ለሐላፊው ፡ ምግብና ፡ ሥራ ፡ የም
ንጨነቅለት ፡ አደለንም ። ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፳፮—፳፰ ።

ውግዘትንስ ፡ የሸረሪት ፡ ዘሐ ፡ ብለህ ፡ የምትንቀው ፤ ጌታ ፡ ዘአሠርክሙ ፡
በምድር ፡ ይከውን ፡ ዕሡረ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ ይቆይና ፡ አንተው ፡ ራስህ ፡
በ፲፫ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ማሠርና ፡ መፍታት ፡ ለንጹሐን ፡ ሐዋርያት ፡ የተሰጠ ፡
ሥልጣን ፡ ነው ። ይህነኑ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣን ፡ ግን ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ሠሩትና
እንዳስተማሩት ፡ ድውይ ፡ እየፈወሱ ፤ ሙት ፤ እያነሱ ፤ ፊት ፡ እነርሱ ፡ ሕግ ፡ ጠብ
ቀው ፡ ንጹሐን ፡ ስለኾኑ ፤ በሕግ ፡ ለማይሔዱና ፡ ክርስቶስን ፡ ለማክዱ ፡ ሰዎች ፡
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሥጢራት ፡ ሊወግዱ ፡ ዛሬም ፡ አሠራቸውን ፡ ይዘው ፡ ለሚ



ሔዱ ፡ ካህናት ፡ የተሰጠና ፡ የሚገባም ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ደገኛ ፡ ትእዛዝነቱን ፡
የመሰከርክለትን ፤ ዘነጋኸውን ፡ ምነው ፡ ቃልህ ፡ ባንድ ፡ አልረጋ ፡ አለ ፤ ላንተ ፡
ይብላኝልህ ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከተናገራቸው ፡
ቃላት ፡ አንዲቱ ፡ ታንሳለች ፡ ብለን ለሌላው ፡ እናስተምርም ፡ ለራሳችንም ፡ አን
ሠራም ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።

፪ በዚህ ፡ ክንቱ ፡ ሐሰት ፡ የተደነገገ ፡ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ ግዝት ፡ ሊቁ ፡ የማን ፡ ብርሃን ፡ አበራ ፡
አሮዋ ፡ አባ ፡ ልማድ ተወ ፡ ፍቱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አትገዝቱ ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፤ እየወቀሱ ፡ ይጮኹ
በት ፡ ነበሩ ፡ ስለምትለው ።

የነገሩን ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ዘርዝርህ ፡ ስላላስረዳሃኝ ፡ ሰውየውንም ፡ ስላ
ላወቅኋቸው ፡ ሊቅ ፡ ናቸው ፡ ወይም ፡ አይደሉም ፡ ለማለት ፡ አልቻልኩም ።
ነገር ፡ ግን ፡ በዓል ፡ ማክበር ፡ ሕግ ፡ ሥርዓት ፡ አደለም ፡ ለማለትማ አንድ ፡ ሰው ፡
ብቻ ፡ ከመጥቀስ ፡ እሑድ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አድቢስቲንት ፡ ሚሲዮን ፤
ይሁዲ ፤ ካመት ፡ እስካመት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ መሐመዳውያን ፡ ያሉልህ ፡
አይደለምን ፡ ለምን ፡ ባንድ ፡ ምስክር ፡ ብቻ ፡ ተወሰንክ ።

፫ ወዳጂ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ ግዝት ፡ እጠብቃለሁ ፡ ስትል ፡ ግን ፡ ትልቅ ፡
ዋጋ ፡ ያለው ፡ የአምላክህ ፡ ትእዛዝ ፡ አፍራሽ ፡ ኾነህ ፡ እንዳትገኝ ፤ ተጠንቀቀህ ፡ ማስብ ፡ ያስፈልግሃል ፡
ለሐዋርያትም ፡ በዘመናቸው ፡ የነበሩቱ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ የክርስቶስን ፡ ትእዛዝ ፡ ትታችሁ ፡ እኛ ፡ ያዘ
ዝነውና ፡ የደነገግነው ፡ የወገዝነው ፡ ያቆምነው ፡ የእኛ ፡ ሕግ ፡ ጠብቁ ፡ ስላሏቸው ፡ ወተሠጥዎሙ ፡ ጴጥሮስ ፡
ምስለ ፡ ሐዋርያት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ይኄይስነ ፡ ናድሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምነ ፡ አድልዎ ፡ ለሰብእ ።

እግዚአብሔርን ፡ ከመስማት ፡ ይልቅ ፡ ላንተ ፡ ልንሰማ ፡ የሚገባ ፡ እንደኾነ ፡ እስኪ ፡ እናንተ ፡ ፍረዱት ፡
እኛስ ፡ አይኾንልንም ፡ የአምላካችን ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ካልኾነ የሰውን ፡ ሕግና ፡ አሮጌ ፡ ልማድ ፡ ከቶ ፡
ምንም ፡ ቢኾን ፡ አንጠብቅም ፡ ስላሉ ፡ በዋሾው ፤ ዓለም ፡ ዘንድ ፡ እየተጠሉ ፡ በምጣድ ፡ መከራ ፡ እየተ
ቈሉ ፡ እየታሠሩ ፡ እየተገረፉ ፡ በእደ ፡ አሕዛብ ፡ እየተሰየፉ ፡ በአፈ ፡ አራዊት ፡ እየተጨነገፉ ፡ የዓለም ፡ ጉድ
ፍና ፡ መሳቂያ ፡ የዓረማውያን ፡ መዘበቻና ፡ መሣለቂያ ፡ ኹነው ፡ ስለስሙና ፡ ትእዛዙ ፡ እየተዋረዱ ፡ በአፈ ፡
አንበሳ ፡ ወተኵላት ፡ እየታረዱ ሕይወታቸውን ፡ መንነው ፡ ሰጥተው ፡ ለዋሾው ፡ ዓለም ፡ ድል ፡ ስለነሡት ፡
በእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ እየተመገቡ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ የተጻፈባት ፡ ነጭ ፡
ደንጋያ ፡ (ሉል) ተቀብለው ፡ በእጃቸው ፡ ጨብጠው ፡ ይዘው ፡ ለዘለዓለም ፡ ነግሠው ፡ በደስታ ፡ ይኖራሉ ።
ዳን ፡ ፯ ፡ ፲—፲፯ ። ፲፪ ፡ ፫ ። ሥራ ፡ ፬ ፡ ፲፱—፳፩ ። ፭ ፡ ፳—፳፱ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፩—፵ ። ፩ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፬ ። ፪ ፡
ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፰ ፡ ። ራእ ፡ ፪ ፡ ፯ ፲፯ ፡ ስለምትለው ።

አሁን ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የምትነግረን ፡ በአርእስቱ ፡ እንደገለጽክልን ፡
ዛሬ ፡ በዓል ፡ ነው ፡ አትሥሩ ፡ ነገ ፡ ጾም ፡ አትብሉ ፡ በሚል ፡ ልማድ ፡ ብላዕ ፡
በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ያለው ፡ አምላካዊ ፡ ትእዛዝ ፡ መፍረሱን ፡ ነው ። ለዚሁም ፡
አሥረጂ ፡ ሊቁ ፡ የማን ብርሃን ፡ አበራ ፤ አባ ፡ ልማድ ፡ ተወ ፡ ፍቱ ፡ በሥራ ፡
ላይ ፡ አትገዝቱ ፤ አሉ ፡ ብለህ ፡ ጠቅሰሃል ። ከልብህ ፡ አንቅተህ ፡ ለተናገርከው ፡
ለዚህ ፡ ንግግርም ፡ ማስረጃ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፬ ፡ ፲፱-፳፩ ጠቅሰሃል ።

በዚህ ፡ አጠቃቀስህ ፡ ሐዋርያት ፡ ያስተማሩ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከን ፡ እንደ
ኾነ ፤ ይኄይሰነ ፡ ናድሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምነ ፡ አድልዎ ፡ ለሰብእ ፤ ብለው ፡
በለንጋ ፡ ይተገረፉ ፤ በእደ ፡ አሕዛብ ፡ የተሰየፉ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መኾኑን ፡
ትናገራለህ ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ብለን ፡ እንቀበለው ፤ ይኸን ። እንዲህ ፡ አድ

www.ethiopianorthodox.org

ርገህ ፡ የምትናገረውን ፡ የማትመረምር ፡ የምታኑበውን ፡ የማታስተውል ፡ አንተ ፡ የዘመድ ፡ መሰቀቂያ ፡ የባዕድ ፡ መሳቂያ ፡ ነህ ፡ ብትበል ፡ በዛን ፡ አይበዛም ፡ ሲያ ንስህ ፡ ነው ።

እናንተ ፡ ዐይናሞች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ይህን ፡ ዕውር ፡ መሪ ፡ ተከ ትላችሁ ፡ ገደል ፡ እንዳትገቡ ፡ ሐዋርያት ፡ ይኄይሰነ ፡ ናድሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምነ ፡ አድልዎ ፡ ለሰብእ ፡ ብለው ፡ መከራ ፡ የተቀበሉበትንና ፡ ሉል ፡ የጨበጡበ ትን ፡ ዘርዝሬ ፡ እጽፍላችኋለሁ ። ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ ለጸሎት ፡ ወደምኵራብ ፡ ሲገቡ ፡ ከእናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ልምሾ ፡ ኾኖ ፡ የተወለደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ምጽዋት ፡ ምጽዋት ፡ እያለ ፡ ሲለምናቸው ፤ ወርቅ ፡ ብር ፡ የለንም ፡ ካለንስ ፡ እንሰጥሃለን ፡ ብለው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተነሥ ፡ አሉት ።

ብድግ ፡ ብሎ ፡ እንደነርሱ ፡ እየተራመደ ፡ ሔደ ። ሕዝቡ ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐ ንስን ፡ በአክብሮትና ፡ በአድናቆት ፡ ዐይን ፡ ተመለከቷቸው ።

ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በእኛ ፡ ኃይል ፡ እንደተደረገ ፡ አድርጋችሁ ፡ በአድናቆት ፡ ለምን ፡ ትመለከቱናላችሁ ። ይህ ፡ ታምራት ፡ የተደረገ ፡ እናንተ ፡ ዐምፃችሁ ፡ ሰቅላችሁ ፡ የገደላችሁት ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አብ ፡ በክብር ፡ ቢገልጸው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አምላክነት ፡ አስፍቶ ፡ አጕልቶ ፡ ቢነግራቸው ፤ ፭ሺህ ፡ ሰዎች ፡ በወንጌል ፡ አመኑ ። ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ ይህነን ፡ አይተው ፡ ተከራክሮ ፡ መርታት ፡ ባይቻላቸው ፡ አይኾንም ፤ እንግዲህ ፡ የኢየሱስ ፡ ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ አታስተ ምሩ ። በስሙ ፡ ተአምራት ፡ አትሥሩ ፡ ቢሏቸው ። ሐዋርያት ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከመስማት ፡ ይልቅ ፡ እናንተን ፤ እንሰማ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ልን ፡ እስኪ ፡ እናንተ ፡ ፍረዱት ፡ አሏቸው ፡ ይላል ፡ እንጂ ፤ ርሱ ፡ እንደሚለው ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ሐዋርያትን ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ቀርቶ ፡ በዓል ፡ እንዲከበር ፡ አስተምሩ ፡ አላሏቸውም ፡ ሐዋርያትም ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከን ፡ ለማስተማር ፡ ብለው ፤ ይኄይሰነ ፡ ናድሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምነ ፡ አድልዎ ፡ ለሰ ብእ ፡ አላሉም ፡ ለዚህም ፡ ብለው ፡ መከራ ፡ አልተቀበሉም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ሐሰት ፡ ቅጥፈት ፡ ነው ።

የቀሩትንም ፡ ጥቅሶች ፡ እንዲሁ ፡ እየገባችሁ ፡ ብትመረምሯቸው ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ የተባለውን ፡ ርግማን ፡ የሚደ ግፍ ፡ አንድ ፡ አይገኝም ። ርሱ ፡ ምዕራፍና ፡ ቍጥር ፡ በመደርደር ፡ ብቻ ፡ አሻግሮ ፡ ላየው ፡ ዐይናማ ፡ አስተማሪ ፡ ምሥጢር ፡ መርማሪ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ፡ እንጂ ፡ ቀርቦ ፡ ሲመረምሩት ፡ እንዲህ ፡ ዕውር ፡ ደንቆሮ ፡ ቢከፍቱ ፡ ተልባ ፤ ነውና ፡ ርሱን ፡ ተከትላችሁ ፡ ገደል ፡ እንዳትገቡ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ።

፪ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ እነዚህ ፡ ደጋጎች ፡ ሰዎች ፡ ጻድቀው ፡ ያጸድቁኛል ፡ እኔ ፡ ሳልሠራ ፡ ሳልደክም ፡ የታዘዝሁ ትን ፡ ሳልፈጽም ፡ ፲ቱ ፡ ቃላተ ፡ ኦሪትንና ፡ ፮ቱ ፡ ቃላተ ፡ ወንጌልን ፡ ሳልጠብቅ ፡ በነርሱ ፡ [illegible] ፡ በእ ንተ ፡ ስሙ ፡ ላንድ ፤ ጻድቅ ፡ አንሥቼ ፡ ለጓደኞቼና ፡ አበ ፡ ንስሐየን ፡ [illegible] እገባለሁ ፡ ማለትህ ፡ የልማድ ፡ ቀልድ ፡ ነው ካልከው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የጻፍከው ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ ጻድቃን ፡ አያማልዱም ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፲ቱ ፡ ቃላተ ፡ ኦሪትንና ፡ ፮ቱ ፡ ቃላተ ወንጌልን ፡ ሳንፈጽም ፡ ሳንሠራ ፡ ሳንደክም ፡ በሌሎች ፡ ድካም ፡ እን ጸድቃለን ፡ የሚል ፡ የለም ። በአርእስቱ ፡ እንደገለጽከው ፡ ላንተ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማ ያት ፡ የሚያበቃ ፡ ሥራ ፡ የሚመስልህ ፡ ሠርቶ ፡ መብላት ፡ ብቻ ስለኾነ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ፈረሰ ፡ እያልክ ፡ ትቈረቈራለህ ።

እኛስ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፡ ገጽከ ፡ በተባለው ፡ ቃለ ፡ ተግሣጽ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ በንይዝ ፡ በሥጋችን ፡ ረሃብ ፡ ችግር ፡ ይደርስብናል ፡ ብለን ፤ ሰዱሰ ፡ መዋዕለ ፡ ተግ በር ፡ ተግባረከ ፡ በተባለው ፡ ሥራ ፡ በታዘዝባቸው ፡ ዕለታት ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ እን ይዛለን ፡

ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበትንና ፡ ሌሎችንም ፡ በሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ የታዘዙትን ፡ በዓላት ፡ ብንሽር ፡ በነፍስ ፡ እንዲፈረድብን ፡ አውቀን ፡ በበዓላት ፡ ቀን ፡ ከተግባረ ፡ ሥጋ ፡ አርፈን ፡ ተግባረ ፡ ነፍስ ፡ ይዘን ፡ እንውላለን ፡ ዘፀአ ፡ ፳፫ ። ዘኍል ፡ ፲፰ ፡ ፴፪–፴፯ ።

ይህ ፡ ገንዘባችሁ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱም ፡ በቤታቸው ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማ ያት ፡ ይቀበሏችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ በኃላፊው ፡ ገንዘባችሁ ፡ ነዳያንን ፡ ወዳጅ ፡ ግዙበት ፡ ያለንን ፡ በንፈጽም ፡ ርኅብኩ ፡ ወኢያብላዕክሙኒ ፡ ጸማዕኩ ፡ ወኢያስተይ ክሙኒ ፡ ብሎ ፡ ይፈርድብናል ፡ ብለን ፡ ወጥተን ፡ ወርደን ፡ ያገኘነውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠላ ፡ ጠምቀን ፡ እንጀራ ፡ ጋግረን ፡ ወጥ ፡ ሠርተን ፡ ዐቅማችን ፡ የፈቀደልንን ፡ ያህል ፡ ደግሰን ፡ ከድኆች ፡ ጋራ ፡ እንበላለን ፡ እንጠጣለን ፡ ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፲ ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳–፳፬ ። ፲ ፡ ፵ ። ፲፱ ፡ ፳፩ ።

ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚያበቃ ፤ በጎ ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ ይህና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ኹሉ ፡ ነው ።

ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ እኒህ ፡ ኹሉ ፡ ትእዛዛት ፡ የተሠረዙ ፡ ናቸው ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሕግና ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ሠርዘህ ፡ ብላዕ ፡ በሐፈ ፤ ገጽከ ፡ የተባለ ውን ፡ የርግማን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፤ ተግባር ፡ አድርገህ ፡ የምትኖረው ፡ ሰው ፤ እንዴት ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ልፍረድ ፡ ትላለህ ፡ እስኪ ፡ መልስ ፡ ብለህ ፡ የተከናነብከውን ፡ ጉድ ፡ አስበው ። በእውነቱ ፡ ሥራህን ፡ አከሔድህን ፡ እያሰብክ ፡ ማፈር ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ልትናገር ፡ አይገባህም ።

በል ፡ እንግዲህ ፡ የቅዱሳንን ፡ አማላጅነት ፡ በ፩ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሬ ፡ ስለጻፍኩልህ ፡ ያነኑ ፡ ተመልከት ፡ አንተን ፡ ይመስል ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ በመመላለስ ፡ ወረቀትና ፡ ቀለም ፡ አልጨርስም ፤ ጊዜዬንም ፡ አላጠፋም ፡ ተመልካ ችን ፡ አላሰለችም ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## ስለ ስግደት ።

፩ ስግደት ፡ ወይም ፡ ስጊድ ፡ ማለት ፡ ፈጣሪና ፡ ፍጡር ፤ ጌታና ፡ ሎሌ ፡ ገዢና ፡ ተገዢ ፡ የሚያመልክና ፡ [illegible] አኗኗራቸው ፡ የሚታወቅበት ፡ ሥልጣን ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፡ ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ፡ ስለምትለው ።

ፈጣሪና ፡ ፍጡር ፡ የሚያመልክና ፡ ተመላኪ ፡ ያልከተቸው ፡ ፍጡር ፡ የማይቀላቀልባቸው ፤ በተለይ ፡ ለአምላክ ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቦቹ ፡ ሲኾኑ ፡ ጌታና ፡ ሎሌ ፡ ገዢና ፡ ተገዢ ፡ ያልከተቸው ፡ ነገሮች ፡ ጌትነትና ፡ ገዢነት ፡ ለአምላክ ፡ የባሕርይ ፤ ለሰው ፡ የጸጋ ፡ ገንዘቦች ፡ መኾናቸውን ፡ እንዳትዘነጋ ፡ አሳስብሃለሁ ፡ እንጂ ፡ ሰጊድ ፡ ያክባሪና ፡ የተከባሪ ፡ የገዢና ፡ የተገዢ ፡ ምልክት ፡ መኾኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

፱ ይህ ፡ ስግደት ፡ ግን ፡ ለአምላክ ፤ የብቻው ፡ የባሕርዩ ፡ ገንዘብ ፡ ስለኾነ ፡ ከቶ ፡ ለሌላ ፡ አይሰጥም ። ዘፀአ ፡ ፳፩—፲፯ ። ስለምትለው ።

አምላክ ፡ የባሕርይ ፡ ጌትነትና ፡ የባሕርይ ፡ ገዢነት ፡ ለብቻው ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡ ፡ ሲኾን ፤ የጸጋ ፡ ገዢነትንና ፡ የጸጋ ፡ ጌትነትን ፡ ለሰው ፡ እንደሰጠ ፡ እንደዚሁም ፡ ከመመለክ ፡ ጋራ ፡ የሚኾን ፡ የአምልኮ ፡ ሰጊድ ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡ ፡ ሲኾን ፡ በጸጋ ፡ ከመገዛትና ፡ በጸጋ ፡ ከሚሰጠው ፡ አክብሮት ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ የጸጋ ፡ ሰጊድም ፡ ለፍጡራን ፡ የሚሰጥበት ፡ የሚደረግበትም ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

(ሐ) ለቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ በጸጋ ፡ መስገድ ፡ እንዲገባ ፡ ሲያስረዳ ፡ ኢያሱ ፡ ቅፅረ ፡ ኢያሪኮን ፡ ባፈረሰበት ፡ ጊዜ ፡ በኢያሪኮ ፡ አጠገብ ፡ ሳለ ፡ ዐይኑን ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ ቢመለከት ፡ የተመዘዘ ፡ ሰይፍ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ ቆሞ ፡ አየ ።

ኢያሱም ፡ አንተ ፡ ለእኛ ፡ ነህን ፡ ወይስ ፡ ለጸላቶቻችን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የሠራዊቱ ፡ አለቃ ፡ ነኝ ፡ አንተን ፡ ለመርዳት ፡ መጥቻለሁ ፡ እንጂ ፡ ከጠላቶችህ ፡ ወገን ፡ አይደለሁም ፡ አለው ።

ኢያሱም ፡ በፊቱ ፡ ከምድር ፡ ወድቆ ፡ ሰግዶ ፡ ጌታዬ ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያው ፡ የሚነግረው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አለው ።

የእግዚአብሔር ፡ የሠራዊቱ ፡ አለቃም ፡ ኢያሱን ፡ አንተ ፡ የቆምክበት ፡ ሥፍራ ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፡ ጫማህን ፡ አውልቅ ፡ አለው ። ኢያሱም ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ይላል ። ዘኢያ ፡ ፭ ፡ ፲፫ — ፲፭ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡ አምላክ ፡ አለመኾኑን ፡ መልአክነቱን ፡ እያወቀ ፡ የሰገደለት ፡ የጸጋ ፡ ሰጊድ ፡ እንጂ ፡ የአምልኮት ፡ ሰጊድ ፡ አይደለም ።

መልአኩም ፡ የሚገባው ፡ የጸጋ ፡ ሰጊድ ፡ እንጂ ፡ የአምልኮ ፡ ሰጊድ ፡ አለመኾኑን ፡ ስላወቀ ፡ ጫማህን ፡ አውልቅ ፡ ብሎ ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ ከመጨመር ፡ በቀር ፡ ለምን ፡ ትሰግድልኛለህ ፡ አላለውም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡ ኢታምልክን ፡ አፍርሶ ፡ ጣዖት ፡ ያመለከ ፡ ይመስልሃልን ? መልአኩስ ፡ እንደ ፡ ጣዖት ፡ የተቈጠረ ፡ ይመስልሃልን ? እስኪነገረኝ ። ጣዖት ፡ አመለከ ፡ እንዳትለውስ ፡ እኔና ፡ ቤቴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እና መልካለን ፡ ብሎ ፡ እንደመሰከረ ፡ ዘኢያ ፳፬ ፡ ፲፬—፳፭ ፡ ዘኁል ፲፬ ፡ ፮—፲ ተመልከት ።

(ለ) ፡ ለቅዱሳንም ፡ ስለሚገባ ፤ ሳኦል ፡ ፍልስጥዔማውያን ፡ በተነሡበት ፡ ጊዜ ፡ ዕንዶራዊትን ፡ ጠርቶ ፡ ሳሙኤልን ፡ አስነሺልኝ ፡ አላት ፡ ሴቲቱም ፡ ሳሙኤልን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኻ ፡ ሳኦልን ፡ አንተ ፡ ሳኦል ፡ ስትኾን ፡ ለምን ፡ አታለልከኝ ፡ አለችው ። ንጉሡም ፡ አትፍሪ ፡ ያየሽው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አላት ፡ ሴቲቱም ፡



አማልክት ፡ ከምድር ፡ ሲወጡ ፡ አየሁ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ መልኩ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ አላት ። እርሷም ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ መጐናጸፊያ ፡ ተጐናጽፎ ፡ ወጣ ፡ አለችው ። ሳኦልም ፡ ሳሙኤል ፡ እንደኾነ ፡ አወቀና ፡ በፊቱ ፡ ተጐንበስ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ሰገደ ፡ ሳሙ ፡ ቀዳ ፡ ፳፰ ፭—፲፭ ። ይላል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሳኦል ፡ ለሳሙኤል ፡ ያቀረበው ፡ ሰጊድ ፡ የአክብሮ ፡ የጸጋ ፡ ሰጊድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የአምልኮ ፡ ሰጊድ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ሳሙኤል ፡ ለምን ፡ አወክኸኝ ፡ ለምን ፡ አስነሣኸኝ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ሰገድክልኝ ፡ አላለውም ። ሳኦልም ፡ በሌላው ፡ ኃጢአቱ ፡ ሲወቀስ ፡ በዚህ ፡ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ ተብሎ ፡ አልተወቀሰበትም ።

(ሐ) ፡ ናቡከደነፆር ፡ ግሩም ፡ ራእይ ፡ አይቶ ፡ ሕልሙም ፡ ትርጓሜውም ፡ ተሰወረው ፡ ጠቢባን ፡ ባቢሎንን ፡ ሰብስቦ ፡ ሕልሜን ፡ ከነትርጓሜው ፡ ንገሩኝ ፡ አላቸው ፡ አጡት ። ዳንኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አመልክቶ ፡ ሕልሙ ፡ ንባቡ ፡ ከነትርጓሜው ፡ ተገልጾለት ፡ ቢነግረው ፡ ተነሥቶ ፡ ናቡከደነፆር ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ሰገደለት ። በእውነት ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ለመናገር ፡ ቻችሎሃልና ፡ በእውነት ፡ አምላካችሁ ፡ እርሱ ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፡ የነገሥታትም ፡ ጌታ ፡ ምሥጢር ፡ ገላጭ ፡ ነው ፡ ብሏል ፡ ዳን ፡ ፪ ፡ ፩—፵፱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ናቡከደነፆር ፡ የአምላክ ፡ ባለሟልነቱን ፡ አውቆ ፡ የጸጋ ፡ ሰጊድ ፡ እንደ ፡ ሰገደለት ፡ ስላወቀ ፤ ዳንኤል ፡ ለምን ፡ ትሰግድልኛለህ ፡ አላለውም ። ዳንኤልም ፡ ጣዖት ፡ አልተባለበትም ፡ ናቡከደነፆርም ፡ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ ተብሎ ፡ አልተነቀፈበትም ።

(መ) ንጉሥ ፡ የጸጋ ፡ ገዢ ፡ ስለኾነ ፡ ለንጉሥ ፡ በጸጋ ፡ መገዛት ፡ እንዲገባ ፡ እንዲሁም ፡ በጸጋ ፡ የሚሰገድለት ፡ ስለኾነ ፡ ሳኦል ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡ አማሌቃውያንን ፡ ከመውጋት ፡ ተመልሶ ፡ በሴቄላቅ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሳኦል ፡ ሰፈር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ ትቢያ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነስንሶ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ሰግዶለታል ፡ ሳሙ ፡ ካል ፡ ፩ ፩—፲ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ የማይገባኝን ፡ ለምን ፡ ሰገድክልኝ ፡ አላለውም ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ዳዊት ፡ ጣዖት ፡ ተብሎ ፡ አልተሰደበም ፡ ያም ፡ ሰው ፡ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ ተብሎ ፡ አልተነቀፈም ።

(ሠ) ታናሹ ፡ ለታላቁ ፡ መስገድ ፡ ታናሹ ፡ ታላቁን ፡ ማክበር ፡ የሚገባው ፡ ስለኾነ ፡ ያዕቆብ ፡ ከሶርያ ፡ ሚስቶቹንና ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ ተመልሶ ፡ ከወንድሙ ፡ ከኤሳው ፡ ጋራ ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ፯ት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ከምድር ፡ እየወደቀ ፡ ለኤሳው ፡ ሰገደለት ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ልያ ፡ ከነልጆቿ ፡ ራሔልም ፡ ከዮሴፍ ፡ ጋራ ፡ ባሮቹም ፡ ኹሉ ፡ ለኤሳው ፡ ሰግደውለታል ፡ ዘፍ ፡ ፴፫ ፩—፰ ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያዕቆብና ፡ ሚስቶቹ ፡ ልጆቹና ፡ ባሮቹ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ ተብሉ ፡ ትላለህን ? ኤሳውስ ፡ ጣዖት ፡ ተብሎ ፡ የተነቀፈ ፡ ይመስልሃልን ፡ የለም ፡ እነርሱም ፡ አልተባሉ ። እርሱም ፡ አልተነቀፈም ። ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ እኒህን ፡ ፭ቱን ፡ ብቻ ፡ ከያይነቱ ፡ ጠቀስኩልህ ፡ እንጂ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ብትመለከት ፡ የህን ፡ የመሰሉ ፡ ብዙ ፡ ታገኛለህ ።

www.ethiopianorthodox.org

፫ ከዚህም ፡ አልፎ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ ወንድሜ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ ስጊድት ፡ ያህል ፡ ትልቁ ፡ ነገር ፡ ለአምላክ ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡ ፤ ስለኾነ ፡ እንኳን ፡ ፍጡር ፡ ለፈጠረው ፡ ለኃላፊው ፡ ምናምን ፡ ለሕያዋኑ ፡ ረቂቃን ፡ መላእክት ፡ ቢኾን ፡ ባሮቹ ፡ ስለኾኑ ፡ ሰጊድን ፡ እንደማይገባቸው ፡ ቢሰግዱላቸውም ፡ እንደሚያስቆጣቸው ፡ ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፩ ፲ና ፡ ፳፪ ፯ ፱ ፡ ብታነብ ፡ እንደእኔ ፡ ትረታለህ ፡ ብለህ ፡ ጠቅሰሃል ።

አንተ ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ለማየት ፡ ዐቅምህ ፡ በይፈቅድልህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ የትሕትና ፡ አነጋገር ፡ ነው ። ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ በምኵራብ ፡ ደጅ ፡ ወድቆ ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ በሽተኛ ፡ ባዳኑት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በአክብሮ ፡ ዐይን ፡ ቢመለከቷቸው ፡ እኛ ፡ በሥልጣናችን ፡ በኃይላችን ፡ እንዳዳነው ፡ አድርጋችሁ ፡ አክብራችሁ ፡ ለምን ፡ ታዩናላችሁ ፡ እንዳሉት ፡ ያለ ነው ። መልአኩም ፡ ለዮሐንስ ፡ ወደፊት ፡ የሚደረገውን ፡ ምሥጢር ፡ ስለነገረው ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በትሕትና ፡ ቢሰግድለት ፡ መልአኩም ፡ መልሶ ፡ ስለትሕትና ፡ እኔ ፡ እንዳንተና ፡ እንደ ፡ ወንደሞችህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነኝ ፤ አንተም ፤ እኔም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንስገድ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ትሰግድላኛለህ ፡ ብሎ ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ ጥቀ ፡ ንኄንን ፡ ኅድጉሰ ፡ ዘዝ ፡ ዓለም ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አጽድቆ ፡ የሐዋርያትን ፡ ክብር ፡ መሰከረ ፡ እንጂ ፡ ለፍጡራን ፡ ሰጊድ ፡ አይገባም ፡ ሲል ፡ የጻፈው ፡ አደለም ። መላእክትን ፡ ያስቆጣቸዋል ፡ ማለትንም ፡ አንተ ፡ ከልብህ ፡ ፈጥረህ ፡ ትናገራለህ ፡ እንጂ ፡ መጽሐፉ ፡ አላለም ። ዮሐንስ ፡ ለመልአኩ ፡ መስገዱ ፡ ዕዳ ፡ ኾኖበት ፡ ተቈጣው ፡ የምትል ፡ ከኾነማ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደዘረዘርኩልህ ፡ ኢያሱ ፡ ለመልአኩ ፤ ሳኦል ፡ ለሳሙኤል ፤ ናቡከደነፆር ፡ ለዳንኤል ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ለዳዊት ፡ በሰገዱ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ትሰግዱልናላችሁ ፡ ብለው ፡ ተቈጡ ፡ አይልምና ፡ እነርሱም ፡ አምላክነት ፡ ሸቷቸዋል ፡ የኸውም ፡ ዕዳ ፡ ኾኖባቸዋል ፡ ማለትህ ፡ እንደኾነ ፡ አስተውል ።

፬ አምላካችንም ፡ ይህ ፡ አምልኮና ፡ ስግደት ፡ ለሌላ ፡ ለሥዕልና ፡ ለምስል ፡ ወይም ፡ ለማናቸውም ፡ ፍጡር ፡ ቢኾን ፡ እንደማይገባውና ፡ እንዳንሰጥለትም ፡ በጣቱ ፡ ጽፎ ፡ አስጠንቅቆ ፡ ሲያዝን ፡ ሲከለክለን ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ፡ ወኢትግበር ፡ ለከ ፡ ሥዕለ ፡ ወአምሳለ ፡ ኢትስግድ ፡ ሎሙ ፡ ወኢታምልኮሙ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ቀናዒ ፡ ወእሳት ፡ በላዒ ፡ እያለ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ግርማ ፡ ባለው ፡ በሚያንቀጠቅጥ ፡ ድምጽ ፡ ቃሉ ፤ አውጀልናል ፡ ዘዳ ፬ ፳—፳፬ ። ፭ ፯—፱ ። ስለምትለው ።

ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ፡ ዲያብሎስ ፡ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ በቦታ ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ መኾኑን ፡ አይቶ ፡ ከበታቹ ፡ ያሉ ፡ መላእክትን ፡ እኔ ፡ ፈጥርኳችሁ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ የአዳም ፡ ልጆችም ፡ እውነት ፡ መስሏቸው ፡ ከሴሩህ ፡ ወዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ዕንጨት ፡ ጠርበው ፡ ደንጊያ ፡ አለዝበው ፡ ቤል ፡ ፌጎር ፡ ዳጎን ፡ አጽሎን ፡ እያሉ ፡ የአጋንንትን ፡ ስም ፡ እየጻፉ ፡ ስለአመለኳቸው ፡ ስለሰገዱላቸው ፡ እነዚያን ፡ ሲከለክል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ኢትስግድ ፡ ሎሙ ፡ ወኢታምልከሙ ፡ ብሎ ፡ በማቆራኘቱ ፡ ይታወቃል ።

ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከአንድ ፡ እስከ ፡ [illegible] የጸጋ ፡ ሰጊድማ ፡ የሚነቀፈው ፡ ከኾነ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጻፉ ፡ በፊት ፡ ያዕቆብ ፡



ለኤሳው ፡ የሰገደለት ፡ ይቅርና ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከተጻፈ ፡ ወዲህ ፡ ኢያሱ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለመልአኩ ፤ ሳኦል ፡ ለሳሙኤል ፤ ያ ሰው ፡ ለዳዊት ፤ ናቡከደነፆር ፡ ለዳንኤል ፤ ሲሰግዱ ፡ ለምን ፡ አልነቀፋቸውም ፤ ለአምልኮት ፡ ቀናዒነቱን ፡ ለምን ፡ ተወው ፤ ፈርቷቸው ፡ አፍሩዋቸው ፡ ነው ፡ ይኸን ፡ እስኪ ፡ ንገረኝ ።

አንተ ፡ ያገርህን ፡ መምህራን ፡ አባቶችህን ፡ ጠይቆ ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ መረዳት ፡ ሲቸግርህ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አስተናግር ፡ ቡቃያ ፡ ሲጨቡጡት ፡ ተመንግሎ ፡ የሚወድቅ ፡ የድቡሽት ፡ ቡቃያ ፡ ባህል ፡ ተውሰህ ፡ አገኝ ፡ አጣህን ፡ ትቀባጥራለህ ፡ እንጂ ፡ ኢታምልክንስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተውሰ ፡ ባህል ፡ ከመመሥረቱ ፡ አስቀድማ ፡ በሽህ ፡ በሚቆጠሩ ፡ ዘመናት ፡ ውስጥ ፡ ተጠንቅቃ ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ብሌኔ ፡ ስትጠብቀው ፡ ኖራለች ፤ ዛሬም ፡ በመጠበቅ ፡ ላይ ፡ ናት ፤ ወደፊትም ፡ እንዲሁ ፡ እስከ ፡ መቸም ፡ ድረስ ፡ ስትጠብቀው ፡ የምትኖር ፡ ናት ።

፭ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ሰውን ፡ ያህል ፡ በአምላክ ፡ አርዓያና ፡ ምሳሌ ፡ የተፈጠረው ፡ ትልቁ ፡ የፍጡራን ፡ ንጉሥ ፡ በእጁ ፡ ዕንጨትን ፡ ጠርቦና ፡ ደንጋያ ፡ አለዝቦ ፡ ቀለም ፡ በጥብጦ ፡ ለሐሳቡ ፡ የሚስማማውን ፡ ሥዕል ፡ ሥሎ ፡ ለማይሰማውና ፡ ለማይጠቅመው ፡ ለከንቱ ፡ መስገዱ ፡ ጣዖት ፡ ማምለኩ ፡ አይደለምን ፤ ከኹሉ ፡ የከፋ ፡ ከንቱ ፡ የኾነ ፡ አርጌው ፡ የጣዖት ፡ ልማድ ፡ ግን ፡ በሚጸለይበት ፡ ቦታ ፡ የማያድን ፡ ሥዕለ ፡ አድኅኖ ፡ እየተባለ ፡ የማያሸተውን ፡ ዕጣን ፡ እየታጠነ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦ ፡ የጸሎት ፡ ሐሳቡን ፡ በምድር ፡ ባለው ፡ ራሱ ፡ በፈጠረው ፡ ሥዕልና ፡ ምስል ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ መወሰኑ ነው ። ስለምትለው ።

በታቦተ ፡ እግዚአብሔርና ፡ በጣዖት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ባታውቅ ፡ እንዲህ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ ከእንጨት ፤ ታቦት ፡ እንዲቀረጽ ፡ ያዘዘ ፡ እግዚአብሔር ነው ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ከልቡናችን ፡ ፈጥረን ፡ ያደረግነው ፡ አደለም ። ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ዘፀአ ፡ ፳፭ ፲-፵ ፡ ብትመለከት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ታቦት ፡ ቀረጽ ፡ ርዝመቱን ፡ ኹለት ፡ ክንድና ፡ እኩል ፡ ወርዱን ፡ ክንድና ፡ እኩል ፤ ቁመቱንም ፡ ክንድና ፡ እኩል ፡ አድርገው ፡ እያለ ፡ ስለታቦት ።

በማስተሥርያው ፡ መክደኛ ፡ ላይ ፡ ኹለቱን ፡ ኪሩቤል ፡ ከወርቅ ፡ በተቀረፀ ፡ ሥራ ፡ አድርግ ፡ ብሎ ፡ ስለሥዕል ።

ከዚያም ፡ ወዳንተ ፡ እመጣለሁ ፡ ከምስክሩ ፡ ማጥን ፡ መክደኛ ፡ ላይ ፡ በኹለቱ ፡ ኪሩቤል ፡ መካከል ፡ ኾኜ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ታወጣው ፡ ዘንድ ፡ የማዝዝህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እነግርሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ከሥዕለ ፡ አድኅኖ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ በመጸለይ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ በሰፊው ፡ ያስረዳሃል ።

ይህም ፡ ቢኾን ፡ አንተ ፡ አንገተ ፡ ደንዳና ፡ ነህና ፡ ያችኑ ፡ አንዷን ፡ ታቦት ፡ ብቻ ፡ ቀረጽ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ሌላ ፡ ቀረጽ ፡ አለው ፡ እንዳትል ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ የሰጠው ፡ ፪ቱ ፡ ጽላቶች ፡ ከተሰበሩ ፡ በኋላ ፡ የፊተኞችን ፡ አስመስለህ ፡ ኹለት ፡ ጽላቶች ፡ ከደንጋያ ፡ ቀረጽ ። እኔም ፡ በሰበርካቸው ፡ ጽላቶች ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ እጽፍባቸዋለሁ ፡ እንዳለውና ፤ ሙሴም ፡ እስ[illegible]ጸ ፤ ቃላቱንም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደጻፈለት ፡ ዘፀአ ፡ ፴፬ ፡ —፳፱ ፡ ብትመለከት ፡ ትረዳዋለህ ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ የሚጠበቁበትን ፡ ስሙ ፡ የተጻፈበትን ፡ ጽላት ፡ ለእስራኤል ፡ ሰጥቷቸዋል ፡ በጽላቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲሰግዱ ፡ አዝዞዋቸዋል ።

እኛም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ በተጻፈበት ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንሰግዳለን ፡ እንጂ ፡ በእጃችን ፡ የቀረጽነው ፤ ዕንጨት ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አናምንም ።

ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መስገድ ፡ የሚገባ ፡ መኾኑንም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ብርከ ፡ መላእክት ፡ ብርከ ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፤ በምድርም ፡ በሰማይም ፡ በወንዞች ፡ ውስጥ ፤ ከምድር ፡ ውስጥም ፡ ያለው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፤ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ከስም ፡ ኹሉ ፡ የበለጠ ፡ ስም ፡ ሰጠው ፡ ብሏል ። ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

በቅዱሳን ፡ ወይም ፡ በጌታችን ፡ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ በተሣለው ፡ ሥዕለ ፡ አድኅኖ ፡ ፊት ፡ ቆመን ፡ ፡ ስንጸልይ ፡ ጌታችንን ፡ እመቤታችንን ፡ ወይም ፡ ሥዕሉ ፡ የተሠየመበትን ፡ ጻድቅ ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፤ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ እናስታውስበታለን ፡ እንጂ ፡ በእጃችን ፡ የሣልነውን ፡ ሥዕል ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አናመልከውም ፡ ወይም ፡ እገሌ ፡ የተባለው ፡ ጻድቅ ፡ የኽ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አናምንበትም ።

ይህንንም ፡ ለማስረዳት ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ በ፲፰፻፴፫ ፡ ዓመት ፡ ቅርጣግና ፡ በምትባል ፡ ሀገር ፡ ፊልጶስ ፡ የተባለ ፡ ቄስ ፡ ከእስላም ፡ ሙፍቲና ፡ ቃዲ ፡ ጋራ ፡ በልሳነ ፡ ዐረቢ ፡ ስለክርስቲያን ፡ ሃይማኖትና ፡ ስለእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ የተከራከሩት ፡ ክርክር ፡ በፍራንስ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፎ ፡ ሲኖር ፡ አባ ፡ ዮስጦስ ፡ የተባለ ፡ ሊቅ ፡ በ፲፰፻፵፬ ፡ ዓ፡ ም፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ተርጒሞት ፡ በ፲፱፻፳፫ ፡ዓ፡ ም፡ ፕሮፌሶር ፡ ሜትቦሕ ፡ የተባለ ፡ ሊቅ ፡ በበርሊን ፡ ከተማ ፡ በጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ባማርኛ ፡ ካሳተመው ፡ መጽሐፈ ፡ ተክህዶ ፡ በሃይማኖት ፡ ከተባለ ፡ መጽሐፍ ፡ ጠቅሼ ፡ ትንሽ ፡ ልጽፍልህ ፡ እወዳለሁ ። ርሱ ፡ በገጽ ፡ ፴፯ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

ሙፍቲ ፡ ፊልጶስን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችሁ ፡ ፊት ፡ ባለፍሁ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ዕንቅፋት ፡ የሚኾንብኝን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ አየሁ ፡ አለው ።

ቀሲስም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለሚፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ዕንቅፋት ፡ የሚኾን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ የለም ፤ ያየኸው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አለው ።

ሙፍቲ ፡ ለሥዕላትና ፡ ለመስቀል ፡ ሕዝቡ ፡ ሲሰግዱ ፡ አየሁ ፡ ይህ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ አይኾንምን ፡ አለው ።

ቀሲስ ፡ እኔም ፤ በመስጊዳችሁ ፡ ባለፍሁ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ ለርሳቸው ፡ ሲሰግዱ ፡ ከብሔረ ፡ ቍርዓን ፡ የሚገኝን ፡ ጽሕፈት ፡ ያዲስ ፡ ጨረቃን ፡ ሥዕል ፡ በደጁ ፡ ላይ ፡ አየሁ ። በእስላም ፡ መስጊድም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ መካ ፡ ላለ ፡ ሚራብ ፡ ሲሰግዱ ፡ አየሁ ። እናንተ ፡ የቍራንን ፡ ጽፈት ፡ የጨረቃን ፡ ሥዕል ፡ ሚራብን ፡ ታመልካላችሁ ፡ ይኸን ፤ ታመልኩ ፡ እንደኾነ ፡ መምለክያ ፡ ወይ... ፡ አለው ። ሚራብ ፡ ማለት ፡ ወደ ፡ መካ ፡ የሚያሳይ ፡ መስኮት ፡ ማለት ፡ ነው ።



ሙፍቲ ፡ እኛስ ፡ አደለንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቍራንን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ አላህ ፡ ቃል ፡ እናከብራለንና ፡ ጽፈቱን ፡ ስናይ ፡ የሚናገራቸውን ፡ ምሥጢራት ፡ እናስባለን ፡ ያዲስንም ፡ ጨረቃ ፡ ሥዕል ፡ ስናይ ፡ ሲድ ፡ መሐመድ ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ እናስባለን ፡ ለሚራብም ፡ የምንሰግድ ፡ መካ ፡ ቅድስት ፡ ሀገር ፡ ናትና ፡ ፊታችንን ፡ ወደ ፡ ርስዋ ፡ መልሰን ፡ ልንሰግድ ፡ ነቢይ ፡ ስላዘዘን ፡ ነው ፡ አለው ።

ቀሲስ ፡ እኛም ፡ እንዲህ ፡ እናደርጋለን ፡ መስቀልና ፡ ሥዕላት ፡ ሕዝብ ፡ እንደሚያነቧቸው ፡ ንባባቸውን ፡ የሚሰሙ ፡ ምሥጢራትን ፡ ፈጥነው ፡ እንደሚያስተውሉባቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ምልክት ፡ ይኾኑልናል ። የቅዱሳንንም ፡ ሥዕል ፡ ስናይ ፡ ያደረጉትን ፡ ገድል ፡ እናስባለን ። መስቀልንም ፡ ስናይ ፡ ኢየሱስ ፡ ስለእኛ ፡ በእርሱ ፡ ተሰቅሎ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ እናስባለን ፡ አለው ።

ሙፍቲ ፡ እንዲህስ ፡ የምታደርጉ ፡ ከኾነ ፡ ስሑታን ፡ አደላችሁም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከእስላሞች ፡ ወገን ፡ የሚበዙት ፡ እናንተ ፡ ጣዖት ፡ እንደሚያመልኩ ፡ ናችሁ ፡ ይላሉ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሐሰት ፡ እንደኾነ ፡ ዛሬ ፡ አወቅሁ ። እንግዲህም ፡ እናንተ ፡ ሥዕላትን ፡ ምሥጢራትን ፡ ለማሰብ ፡ ምልክት ፡ እንድታደርጓቸው ፡ እንጂ ፡ እንዳታመልኳቸው ፡ ለባልንጀሮቼ ፡ እነግራቸዋለሁ ፡ አለው ።

ቀሲስ ፤ ክርስቲያን ፡ አዋቂ ፡ እንደኾነ ፤ ጣዖት ፡ የሚያመልክ ፡ ግን ፡ ደንቆሮ ፡ እንደኾነ ፡ ትናገራላችሁ ፤ እውቀት ፡ ካለን ፡ ጣዖትን ፡ ልናመልክ ፡ እንዴት ፡ ይቻለናል ፤ ይህንንስ ፡ እንዳናደርግ ፡ እናንተ ፡ እስላሞች ፡ መጽሐፈ ፡ ብርሃን ፡ የምትሉት ፡ መጻፋችን ፤ ለእግዜር ፡ ብቻ ፡ ልንሰግድ ፤ ስግደታችንም ፡ በእውነት ፡ በመንፈስ ፡ ሊኾን ፡ ያዘናል ። እኛም ፡ እንዳዘዘን ፡ እናደርጋለን ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ስናደርግ ፡ ጣዖትን ፡ ያመልካሉ ፡ ብትሉ ፡ ታላቅ ፡ ሐሰት ፡ ትናገራላችሁ ፤ በእኛም ፡ ምክንያት ፡ በደለኞች ፡ ትባላላችሁ ፡ አለው ።

ሙፍቲ ፡ መምሮቼ ፡ ስለናንተ ፡ ብዙ ፡ ሐሰት ፡ እየነገሩኝ ፡ ባለማወቁ ፡ እጅግ ፡ በድያለሁ ፤ ተወኝ ፤ ተወኝ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ አንተን ፡ መርምሬ ፡ እናንተ ፡ እንደኛ ፡ አንድ ፡ አምላክን ፡ እንድታመልኩ ፡ እንጂ ፡ ፫ ፡ አማልክትን ፡ እንዳታመልኩ ፡ አውቃለሁ ። ዳግመኛም ፡ ሲድ ፡ ኢየሱስ ፡ የአላህ ፡ ቃል ፡ እንደኾነ ፤ የአላህ ፡ መንፈስ ፡ እንዳልኾነ ፡ ስለ ፡ ሰውም ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ አወቅሁ ። ፫ተኛም ፡ እናንተ ፡ ጣዖትን ፡ እንዳታመልኩ ፡ አወቅሁ ። ለእኔ ፡ የሚበጀኝን ፡ ይህነን ፡ ኹሉ ፡ ስላሰማኝ ፡ እልሐምዲሊላሂ ፡ አለው ። ይህም ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሔድ ፡ በሰላም ፡ ኑር ፡ አለው ። ቀሲስም ፡ በሰላም ፡ ሒድ ፡ አለው ፡ ይላል ።

በ፬ተኛውም ፡ ገጽ ፡ ሙፍቲና ፡ ቃዲ ፡ የዚህኑ ፡ ነገር ፡ አንሥተው ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ሙፍቲ ፡ ለቃዲ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥዕልንና ፡ መስቀልን ፡ ስለምን ፡ ያመልካሉ ፡ ብዬ ፡ ቀሲስን ፡ ጠየቅሁት ። ቀሲስም ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ጣዖት ፡ ሥዕልንና ፡ መስቀልን ፡ እንዳያመልኩ ፡ ነገረኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ እኛ ፡ በመስጊዳችን ፡ የም

www.ethiopianorthodox.org

ናደርጋቸው ፤ የቍራን ፡ ጽሬት ፡ ያዲስ ፡ ጨረቃ ፡ ሥዕል ፡ ሚኅራብ ፡ ቅዱሳት ፡ ምሥጢራትን ፡ ለማሳሰብ ፡ ምልክት ፡ ሊኾኑን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልናመልካቸው ፡ እን ዳልኾነ ፡ ክርስቲያን ፡ መስቀልንና ፡ ሥዕልን ፡ የሚያደርጉ ፡ ቅዱሳት ፡ ምሥጢራ ትን ፡ ለማሳሰብ ፡ ምልክት ፡ ሊኾኗቸው ፡ ነው ፡ አለው ።

ቃዲ ፤ ክርስቲያን ፡ ለባውያን ፡ ናቸውና ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልኩ ፡ አይመስለ ኝም ፡ አለው ።

ሙፍቲ ፤ ቍራን ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ብሎ ፡ የሚዘልፋቸው ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ አለው ።

ቃዲ ፤ ቁራንን ፡ ያልተቀበሉ ፡ ጣጉት ፡ የሚባል ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልኩ ፤ መርዋ ፡ ሳፋ ፡ በሚባሉ ፡ ኮረፍቶች ፡ የሚሠዉ ፤ ያዛ ፡ መናት ፡ የሚባሉንም ፡ ጣዖ ታት ፡ አዋልደ ፡ አላህ ፡ ብለው ፡ የሚያመልኩ ፡ የዓረብ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ አለው ።

ሙፍቲ ፤ እስላሞች ፡ ክርስቲያንን ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ በሚልዋቸው ፡ ጊዜ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ በደል ፡ እንዲያደርጉ ፡ እውነት ፡ ልንናገር ፡ ይገባል ፡ አለው ።

ቃዲ ፤ አላህ ፡ መሀሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ የሚከራ ከረውን ፡ ቄስ ፡ ባይ ፤ ክርሱም ፡ ጋራ ፡ ብነጋገር ፡ እወዳለሁ ፡ አለው ።

ሙፍቲ ፤ ቀሲስ ፡ ወደእኔ ፡ በሚመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ና ፡ ብዬ ፡ እልክብሃለሁ ፡ አለው ፡ ቃዲ ፤ እሺ ፡ በሰላም ፡ ኑር ፡ አለው ። ሙፍቲ ፡ በሰላም ፡ ሒድ ፡ አለው ፡ ያላል ።

እንግዲህ ፡ ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ በአፍዓ ፡ ያሉ ፡ ሙፍቲና ፡ ቃዲ ፡ የሥዕ ልንና ፤ የመስቀልን ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ተረድተውት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ክርስቲያኖችን ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ውሸትና ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሲመሰክሩ ፤ አንተ ፡ በሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ አምኛለሁ ፡ ስትል ፡ ክርስቲያን ለታቦት ፡ ለሥዕል ፡ ለመስቀል ፡ ከሰገደ ፡ ጣዖት ፡ ያመልካል ፡ ብትል ፡ አሬምደህ ፡ ምሥጢር ፡ ማየት ፡ የማትችል ፡ ዕውር ፡ መኾንህን ፡ ከመመስከር ፡ በቀር ፡ እንዳንተ ፡ ዕውር ፡ ካልኾነ ፡ እውነት ፡ ብሎ ፡ የሚቀበልህ ፡ የለም ።

፩ ኅሡራንኬ ፡ እሙንቱ ፡ ወበውስቶ ፡ ምግባርኒ ፡ ምውታን ፡ ተስፋሆሙ ፡ እለ ፡ ጸውዑ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ዕብእ ፡ አማልክተ ፡ ዘወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ገብርዎሙ ፡ በተኬንዎ ፡ ዘይበቍዕ ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ ዘትካት ፡ ወእመ ኒበ ፡ ፀራቢ ፡ ዘይፀርብ ፡ ዕፀ ፡ ዘሠናየ ፡ ሠረፀ ፡ ወፀረበ ፡ በሥነ ፡ ኪኑ ፡ ኰሎ ፡ ቅርፍቶ ፡ ወገብሮ ፡ ዘይበቍዕ ፡ ንዋየ ፡ ለመልእክተ ፡ ሕይወት ፡ ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ ዘይደሉ ፡ ቤተ ፡ ዘወቅሮ ፡ ወውስተ ፡ ዐረፍት ፡ አጥበቆ ፡ ወአጽ ንዖ ፡ በሐጺን ፡ ወአስተሐመመ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ኢይደቅ ፤ አእሚሮ ፡ ከመ ፡ ኢይክል ፡ ርእሶ ፡ ረዲአ ፡ ወያስተበ ቍዖ ፡ ኀቤሁ ፡ በእንተ ፡ ጥሪቱ ፡ ወብእሲቱ ፡ ወውሉዱ ፡ ወኢየኃፍር ፡ እንዘ ፡ ይትናገር ፡ ምስለ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ወበእንተ ፡ ሕይወቱኒ ፡ ምውተ ፡ ይስእል ፡ ወያስተበቍዖ ፡ ኀበ ፡ ዘአልቦቱ ፡ አእምሮ ፡ ጥበ ፡ ፲፫ ፲–፲፱ ስለምትለው ።

ከዚያም ፡ አልፈህ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ኢትግበር ፡ ለከ ፡ ሥዕለ ፡ ወአምሳለ ፡ ኢበአምሳለ ፡ ብእሲ ፡ ወኢበአምሳለ ፡ ብእሲት ፡ ኢትስግድ ፡ሎሙ ፡ ወታምልኮሙ ፡ ወኢትስ ግድ ፡ ለአምላክ ፡ ነኪር ። አቅንዑኒ ፡ በዘኢኮነ ፡ አምላክ ፡ ወአምዕዑኒ ፡ በአማልክቲሆሙ ፡ ብለህ ፡ ዘዳግ ፡ ፱ ፡ ፲፮–፳፱ የጠቀስከው ።



ከዚያም ፡ ኢይሁብ ፡ ክብርየ ፡ ለባዕድ ፡ ወስብሐትየ ፡ ለግልፎ ፡ ብለህ ፡ ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፰ ። ከዚህ ፡ አያ ይዘህ ፡ ነቢያት ፡ ስለጣዖት ፤ የተናገሩትን ፡ ኢሳ ፡ ፵፭ ፲፰—፳፮ ። ኤር ፡ ፲ ፡ ፩–፲፩ ። ኢሳ ፡ ፵፬ ፰–፳ ፡ ፵፮ ፡ ፩—፱ ። ፪ ፳ ። ኤር ፡ ፫ ፮—፲፮ ። ፲ ፡ ፩—፲፩ ። ፪ ፩—፳፰ ። ፲፩ ፱—፲፮ ። ዕንባ ፡ ፪ ፲፰—፳ ። ጠቅሰሃል ።

ያለአገባብ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ከመጠትወት ፡ አስቀድሞ ፡ በታቦተ ፡ እግዚ አብሔርና ፡ በጣዖት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ማወቅ ፡ በተሻለ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔር ፡ ቀድሞ ፡ ሰውን ፡ ሲፈጥረው ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ አውቆ ፡ ስሙን ፡ ሊቀድስ ፡ ክብሩን ፡ ሊወርስ ፡ ፈጥሮት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ሕጉንና ፡ ሃይማኖቱን ፡ በብ ራና ፡ በቀለም ፡ ሊጽፍና ፡ ሊይዝ ፡ አልነበረም ። ይህ ፡ ባይቻለው ፡ ግን ፡ ሕግ ፡ ተሠርቶለታል ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎለታል ፡ ይህንም ፡ የሚያስረዳ ። ኄኖክ ፡ ሰብእሰ ፡ ኢተፈጥሩ ፡ ለዝ ፡ ከመዝ ፡ ከመ ፡ ያጽንዑ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ በረቅ ፡ ወበቀለም ፡ አላ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይግበሩ ፡ ወይንበሩ ፡ ንጹሓነ ፡ ወቅዱሳነ ።

ሰው ፡ ሲፈጠር ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ አውቆ ፡ ንጹሕ ፡ ቅዱስ ፡ ኾኖ ፡ ሊኖር ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ሃይማኖቱን ፡ በብራና ፡ ጽፎ ፡ ለመያዝ ፡ አልነበረም ፡ ብሏል ፡ ፲፱ ፡ ፳፬ ።

ማር ፡ ይስሐቅም ፡ ሕግሰ ፡ ጠባይዐዊ ፡ ተውህበ ፡ ለሰብእ ፡ እምኀበ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ቀዲሙ ። ወዘተጽሕፈሰ ፡ መጽአ ፡ እምድኅረ ፡ ተዐድዎ ፡ ሕግ ።

ለሰው ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ የሚታወቅ ፡ ሕግ ፡ አስቀድሞ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበረ ። በብራና ፡ የተጻፈው ፡ ሕግስ ፤ ትእዛዝ ፡ ከማፍረስ ፡ በኋላ ፡ መጣ ፡ ብሏል ። ፪ ፡ ፩ ።

እንደዚሁም ፡ ከአዳም ፡ ፲፰ተኛ ፡ ትውልድ ፡ ሴሩህ ፡ በሞተበት ፡ በልጁ ፡ በብኑ ፡ አምሳል ፡ በቀረፀው ፡ እንጨት ፤ ሰይጣን ፡ አድሮ ፡ ድምፅ ፡ በመስጠቱ ፡ ምክንያት ፡ አምልኮ ፡ ጣዖትን ፡ አስፋፍቶ ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ ጨልጦ ፡ ገርኝቶ ፡ ስለወሰደው ፤ ሰውም ፡ የሚያየውን ፡ ግዙፍ ፡ ነገር ፡ ፈልጎ ፡ ወደ ፡ ጣዖት ፡ ስለተሳበ ፤ አይተው ፡ ይመኑበት ፤ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ይጠበቁበት ፡ ብሎ ፡ ለአምላክነቱ ፡ ምስክር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ስሙን ፡ በጽላት ፡ ላይ ፡ ጽፎ ፡ ለሙሴ ፡ ሰጠው ።

ለጽላቱም ፡ ማደሪያ ፡ ማስቀመጫ ፡ (ሣጥን) ፡ ታቦት ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ቅረጽ ፡ በመግጠሚያውም ፡ ላይ ፡ ኹለቱን ፡ ኪሩቤል ፡ ሳልበት ። የምስክሩን ፡ ጽላት ፡ በውስጡ ፡ አኑረው ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ መጥቼ ፡ በኹለቱ ፡ ኪሩቤል ፡ መካ ከል ፡ ከምስክሩ ፡ ሣጥን ፡ መክደኛ ፡ ላይ ፡ ኾኜ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ትነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ የምነግርህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እነግርሃለሁ ፡ ብሎታል ። ዘፀአ ፡ ፳፭ ፡ ፱–፳፫ ።

ሙሴም ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ፡ እስራኤል ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ለታቦተ ፡ ጽዮን ፡ በመስገድ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየመሰከሩ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ተጠብቀው ፡ ኖረዋል ። አሁን ፡ የጠቀስካቸው ፡ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ለታቦተ ፡ ጽዮን ፡ በመስገድ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየመሰከሩ ፡ ጣዖታትን ፡ ሲነቅፉ ፡ ይህን ፡ የጠቀስከውን ፡ ኹሉ ፡ ተናግረዋል ።

ስለታቦተ ፡ ጽዮንስ ፡ ያደረጉትን ፡ ክብር ፡ የተናገሩትን ፡ ነገር ፡ ልትረዳ ፡ ብት
[illegible] ፡ ፲፰ ፡ ፴፬ ፡ ፩–፭ ፡ ፳፰ ። ዘኢያ ፡ ፫ ፡ ፫–፲፯ ። ፩ ፡ ፩–፲፱ ። ፩ ነገ ፡ ፪ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሸ፮ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ፡ ፮ ፡ ፲፱ ። ፰ ፡ ፩–፲ ፡ ፳፩ ። ዜና ፡ መዋ ፡ ካል ፡ ፭ ፡ ፩–፲፬ ። ፮ ፡ ፲፩ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ፡ መዝ ፡ ፻፴፪ ፡ ፰ ፡ ተመልከት ። ይህንንም ፡ በማስተዋል ፡ ተመልክተህ ፡ በታቦትና ፡ በጣዖት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ተረዳና ፡ ለጣዖት ፡ የተነገረውን ፡ ለታቦት ፡ እያስመሰልክ ፡ መዘብረቅህን ፡ ተው ።

፭ ከማይነቅዝ ፡ ዕንጨት ፡ ተመርጦ ፡ ከዱር ፡ ተቈርጦ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የተጠረበው ፡ ታቦት ፡ እንኳንና ፡ ለሰው ፡ ሊያድን ፡ በአምላክ ፡ እጅ ፡ ተጽፎ ፡ ሙሴ ፡ የተቀበለው ፡ ጽላትም ፡ ቢኾን ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ሕጉን ፡ ስላፈረሱለት ፡ አምላክ ፡ ተቈጥቶ ፣ ፴ሽ ፡ ወታደር ፡ ለጠላት ፡ ሰይፍ ፡ አሳልፎ ፡ ለጣቸውና ፡ የሚመኩበትም ፡ ታቦት ፡ ጭምር ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ ተማርኮ ፡ ሔደ ፡ እንጂ ፡ ሊያድናቸው ፡ አልቻለም ፡ ፩ ሳሙ ፡ ፬ ፩—፲፩ ፡ ስለምትለው ።

ጽላት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተጻፈበት ፡ አምላክነቱ ፡ የሚመሰከርበት ፡ ከዕንጨት ፡ የተቀረጸ ፡ ሰሌዳ ፡ እንደ ኾነ ፤ ርሱ ፡ ራሱ ፡ አምላክ ፡ እንዳልኾነ ፡ መላልሼ ፡ ነግሬሃለሁ ። ስለዚህ ፡ እኛን ፡ ለመስደብ ፡ ብለህ ፡ የቃጣሃው ፡ ንግግር ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመንቀፍ ፡ እንዳደረሰህ ፡ አስተውል ።

ታቦተ ፡ ጽዮንስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ያምላክነቱ ፡ መገለጫ ፡ ምስክር ፡ ስለኾነች ፡ በጣዖታቱ ፡ ላይና ፡ በፍልስጥዔማውያን ፡ ላይ ፡ አምላከዊ ፡ ኃይል ፡ ገልጻ በክብር ፡ ተመልሳለች ። ይህንንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትወድ ፡ ሳሙ ፡ ቀዳ ፡ ፭ ፬ ፡ ብትመለከት ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወስደው ፡ ዳጎን ፡ ከሚባለው ፡ ጣዖት ፡ ቤት ፡ አግብተው ፡ ከጣዖቱ ፡ ባጠገብ ፡ አቆሙት ። በማግስቱ ፡ ማልደው ፡ ቢሔዱ ፡ ዳጎን ፡ ከታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ፊት ፡ ወድቆ ፡ አገኙት ። መልሰው ፡ በሥፍራው ፡ አድርገውት ፡ ሔዱ ። ዳጎን ፡ በግንባሩ ፡ ወድቆ ፡ ራሱም ፡ እጁም ፡ ተቈራርጦ ፡ ወድቆ ፡ አገኙት ። የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በአሸደድ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ጸናች ፡ አጠፋች ፡ አሸደድንና ፡ ድንበራቸውንም ፡ በጽኑ ፡ ዕባጭ ፡ መታቻቸው ። የአሸደድም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ እንደ ኾነ ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ እጅ ፤ በላያችንና ፡ በአምላካችን ፡ በዳጎን ፡ ላይ ፡ ጠንክራለችና ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ አትቀመጥ ፡ አሉ ። ፍልስጥዔማውያን ፡ በጉባኤ ፡ መክረው ፡ ጋት ፡ ወደ ፡ ሚባል ፡ አገር ፡ አዞሯት ። ቢያዞሯትም ፡ የጋትን ፡ ሰዎች ፡ ከታናሹ ፡ እስከ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ እበጥ ፡ ወጣባቸው ፤ በመዓት ፡ ቀሠፋቸው ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ዔቅሮን ፡ ወሰዷት ፡ የዔቅሮንም ፡ ሰዎች ፡ እኛንና ፡ ሕዝባችንን ፡ ሊያጠፉ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ አመጡብን ፡ ብለው ፡ ጮኹ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የፍልስጥዔም ፡ ሰዎች ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ እኛንና ፡ ሕዝባችንን ፡ ጨርሶ ፡ እንዳያጠፉን ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ይመለስልን ፡ አሉ ። ከዚህ በኋላ ፡ በፍልስጥዔማውያን ፡ አለቆች ፡ ቍጥር ፡ ፭ የወርቅ ፡ እበጥ ፤ ፭ የወርቅ ፡ አይጥ ፤ አሠርተው ፡ አዲስ ፡ ሠረገላ ፡ አሠርተው ፤ ፪ት ፡ የጊደር ፡ በካሮች ፡ ጭነው ፤ አምስቱን ፡ የወርቅ ፡ ዕበጥና ፡ አምስቱን ፡ የወርቅ ፡ አይጥ ፡ ጨምረው ፡ በሠረገላው ፡ አድርገው ፤ ጥጆቻቸውን ፡ አስቀርተው ፤ እንግዲህ ፡ ጊደሮች ፡ ታቦቱን ፡ ይዘው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ብሔረ ፡ እስራኤል ፡ የሔዱ ፡ እንደ ኾነ ፡ በመቅሠፍት ፡ የመታን ፡ እግዚአብሔር ፡ መኾኑን ፡ እናውቃለን ፡ ወደሌላ ፡ የሔዱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ መቅሠፍቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አለመኾኑን ፡ እናውቃለን [illegible]



ጥታ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ እስራኤል ፡ ስለሔዱ ፡ ሌዋውያን ፡ በክብር ፡ ተቀብለው ፡ አኑረዋታል ፡ ፍልስጥዔማውያንም ፡ በታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ያደረ ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ቀሠፋቸው ፡ አወቁ ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ፡ ሳሙ ፡ ቀዳ ፡ ፭ ፩–፲፪ ። ፮ ፩–፳፩ ። ፯ ፩–፫ ።

ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ እንዲህ ፡ አድርጋ ፡ በፍልስጥዔማውያንና ፡ በጣዖታቸውም ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ኃይል ፡ አሳይታ ፡ በታላቅ ፡ ኃይል ፡ ወደ ፡ ቦታዋ ፡ ከተመለሰች ፡ ጥንቱንም ፡ የሔደች ፡ ከጣዖታት ፡ በላይ ፡ ያለች ፡ እውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ መኾኗን ፡ ለመግለጽ ፡ ሔደች ፡ ከማለት ፡ አልፎ ፡ ስንኳን ፡ ለሰው ፡ ሊያድን ፡ ራሱም ፡ ታቦቱ ፡ ተማረከ ፡ ብለህ ፡ የምትናገረው ፡ የብልግና ፡ ንግግር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕጋዊ ፡ ንግግር ፡ አደለም ።

፮ ርሕገ ፡ ኦሪትም ፡ ታቦት ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዙን ፡ በደንጋያ ፡ ጽላት ፡ ላይ ፡ ጽፎ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ የተዋዋለበት ፡ ዘፀአ ፡ ፴፩ ፡ ፲፰ ። ዘዳ ፡ ፴፩ ፡ ፳፮ ። ውል ፡ ፊርማ ፡ ክቡር ፡ ቃሉ ፡ የሚኖርበት ፡ ማጥን ፡ ማኅደር ፡ ስለኾነና ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደርሱ ፡ መጥቶ ፡ በላዩ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚናገራቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አከበሩት ፡ እንጂ ፡ ለመንበሩ ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡ ይሰማናል ፡ ብለው ፡ ከቶ ፡ አልሰገዱለትም ። ዘፀአ ፡ ፳ ፳፬። ፳፭ ፲፮—፳፪ ስለምትለው ።

እኛም ፡ እንዲሁ ፡ አንተ ፡ እንደተናገርከው ፡ እግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ በተጻፈበት ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ አምነን ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንሰግዳለን ፡ እንጂ ፡ ታቦቱን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አናመልከውም ። በማጥኑ ፡ መክደኛ ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ በኹለቱ ፡ ኪሩቤል ፡ መካከል ፡ ኾኜ ፡ እነግርሃለሁ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ በታቦቱ ፡ አድሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰማናል ፡ ብለን ፡ በታቦት ፡ በሥዕል ፡ ፊት ፡ ልመናችንን ፡ እናቀርባለን ፡ እንጂ ፡ ራሱ ፡ ሥዕሉ ፡ ወይም ፡ ታቦቱ ፡ ይሰማናል ፡ ብለን ፡ የምንጸልይ ፡ አደለንም ። ዘፀአ ፡ ፳፭ ፳፩ና ፳፪ ።

፯ ታቦት ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ ለሰው ፡ ሊጠቅምና ፡ ሊያድን ፡ ሙሴ ፡ ተቈጥቶ ፡ በጣዖት ፡ በወርቅ ፡ ጥጃ ፡ ላይ ፡ ሲጥለው ፡ ኹለቱም ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ስለኾኑ ፡ ተያይዘው ፡ ደቂት ፡ ኾነው ፡ ጠፉ ፡ እንጂ ፡ ራሳቸውም ሊያድኑ ፡ አልቻሉም ፡ ስለምትለው ።

በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የተቀረፀውን ፡ ጽላት ፡ ግብረ ፡ እደ ፤ ሰብእ ፡ ስለኾነ ፡ ተሰበረ ፡ ብለሃል ፤ በመሰበሩ ምክንያት ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ የሚባል ፡ ከኾነ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ኃላፊ ፡ ጠፊ ፡ ነውና ፡ ኹሉም ፡ የሰው ፡ ሥራ ፡ መኾኑ ፡ ነዋ ።

እነሆ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ መኾኑን ፡ ጽፈሃል ። ጽላት ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የተቀረፀ ፡ ሲኾን ፤ ኹለቱም ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ስለኾኑ ፡ ያልከውን ፡ አልቀበልም ፡ እንጂ ፤ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ነው ፡ ያልከውን ፡ እኔም ፡ አልክድም ። ሰውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በመኾኑ ፡ ከሞት ፡ አይድንም ፡ ይሞታል ። ስለሞተም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ከመኾን ፡ የሚያግደው ፡ የለም ።

እንደዚኽውስ ፡ ራሱ ፡ ሊጠቀም ፡ ሳይኾን ፡ ሰው ፡ ሊጠቀምበት ፡ በእግዚአ[illegible]ተቀረፀ ፡ ታቦት ፡ ቢሰበር ፡ ብርቁ ፡ ድንቁ ፡ ምንድን ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በፊተኛው ፡ አስመስለህ ፡ ቅረጽ ፡ ብሎት ፡ ቢቀርጽ ፡ በፊተኛው ፡ ጽላት ፡ የነበረው ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጣት ፡ ተጽፎበት ፡ ከተገኘ ፤ በዚህም ፡ ጽላት ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንቅ ፤ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ ካደረገ ፡ ታቦት ፡ የሚነቀፍበት ፡ ምንድን ፡ ነው ? እስኪ ፡ ንገረኝ ።

ሰውን ፡ መሞቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ከመኾን ፡ እንዳላገደው ፡ የቀደሙት ፡ የሙሴ ፡ ጽላቶች ፡ መሰበርም ፡ የተከታዩን ፡ ታቦት ፡ ክብር ፡ የሚቀንስ ፡ አደለም ።

፰ በዚሁም ፡ ጠንቅ ፡ እስራኤል ፡ ለግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ስለሰገዱ ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡ ተቈጥቶ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ፫ሺ ፡ ሰዎች ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ሰይፍ ፡ ታረዱ ። ዘፀአ ፡ ፴፪ ፳—፴፭ ፡ ስለምትለው ።

እኒህ ፡ ሰዎች ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ሰይፍ ፡ የታረዱ ፤ ለጣዖት ፡ በመስገዳቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በዚህ ፡ ጠንቅ ፡ ለታቦት ፡ ጽዮን ፡ ስለሰገዱ ፡ አደለም ፤ አንድ ፡ ማስረጃ ፡ የሌለው ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

፱ ኾኖም ፡ ዛሬ ፡ በዘመን ፡ ሐዲስ ፡ ታቦት ፡ እንደማያስፈልግና ፡ እንደማይደረግም ፡ ነቢያት ፡ አስቀድመው ፡ ተናግረውለታል ። ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ መዋዕል ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እወዲ ፡ ሕግየ ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡ ወእጽሕፎ ፡ ውስተ ፡ ሕሊናሆሙ ። ኤር ፡ ፴፩ ፴፩—፴፱ ። ወእሁቦሙ ፡ መንፈሰ ፡ ሐዲስ ፡ ወአአትት ፡ ልበ ፡ እብን ፡ እምሥጋሆሙ ፡ ወእሁቦሙ ፡ ልበ ፡ ዘሥጋ ፡ ሕዝ ፡ ፲፩ ፲፱ ፡ ስለምትለው ።

ለቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ የተሰጣቸው ፡ መንፈስ ፡ ረድኤት ፡ ስለነበረ ፡ የተጻፈውን ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ አቅቷቸው ፡ ወደአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ይሳቡ ፡ ነበረ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ የተሰጠን ፡ መንፈሰ ፡ ልደት ፡ ስለኾነ ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ሕግ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ተቀርጾለት ፡ ወደአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ የሚሔድ ፡ አይገኝም ። ስለዚህ ፡ የቀደመውን ፡ ልበ ፡ እብን ፤ የዛሬውን ፡ ልበ ፡ ሥጋ ፡ በማለት ፡ ተናገረው ፡ እንጂ ፤ የቀደመውን ፡ ሕግ ፡ ሲነቅፍ ፡ የጻፈው ፡ አደለም ።

የቀደመውንስ ፡ እንዳልነቀፈ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ። ኦሪትንና ፡ ነቢያትን ፡ ልፈጽማቸው ፡ እንጂ ፡ ላሳልፋቸው ፡ አልመጣሁም ። ሰማይ ፡ ምድር ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ቅርጿ ፡ ወይም ፡ ጽሕፈቷ ፡ አንዲት ፡ የኾነች ፡ የውጣ ፡ አታልፍም ፡ ከኒህም ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲትን ፡ የሻረ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይወጣል ። የሚጠብቃቸው ፡ ግን ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መደበኛ ፡ ይኾናል ፡ ብሏል ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ ከናንተ ፡ አስቀድመው ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ አትግደሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችሁ ፡ ነበረ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ መግደሉ ፡ ይቅርና ፡ ያልኾነ ፡ ነገር ፡ ተናግሮ ፡ ወንድሙን ፡ ያሳዘነ ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድበታል ፡ እያለ ፡ በጽላተ ፡ ሙሴ ፡ ለይ ፡ የተጻፉትን ፡ ፲ሩን ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ አጽንቷቸዋል ። ማቴ ፡ ፭ ፲፯—፵፰ ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ በላዩ ፡ የተጻፉትን ፡ ቃላቱን ፡ ሲያጸና ፡ የተጻፉበትን ፡ ሰሌዳውን ፡ ለይቶ ፡ እንዳጠፋው ፡ የሚያስረዳ ፡ ጽሑፍ ፡ አናገኝም ።

ስለዚህም ፡ ታቦት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ስሙ ፡ ተጽፎበት ፡ እንደ ፡ ዛሬውም ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋው ፡ እየተፈተተበት ፡ ደሙ ፡ እየተቀዳበት ፡ ክብሮ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ አልተነቀፈም ።



ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወመኑ ፡ ዘይዴምር ፡ ታቦተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ብሎ ፡ አጽንቶታል ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፯ ፲፯ ።

፫ቱ ፡ ፺ትም ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ወይኩን ፡ ታቦት ፡ ዘይፈልስ ፡ እመካን ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ብለው ፡ አጽንተውታል ።

፲ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ፈጽሞ ፡ በዘመን ፡ ሐዲስ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስና ፡ ታቦት ፡ ኾኖ ፡ እንዲኖር ፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደንጊያ ፡ ተጽፎ ፡ በአፍአ ፡ ሳይኾን ፡ በሰው ፡ ሕሊናና ፡ ልብ ፡ ሊያድር ፡ እንደሚገባ ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ታቦቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አንትሙ ፡ ወመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ፩ ቆሮ ፡ ፫ ፲፯ ። ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ማኅደሩ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንትሙ ፡ ፮ ፲፱ ። እስመ ፡ እንተ ፡ ውሥጡ ፡ ለሰብእ ፡ የኀድር ፡ ክርስቶስ ፡ በሃይማኖት ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ፡ በተፋቅሮ ፡ ኤፌ ፡ ፫ ፲፯ ። ብሏል ፡ ጌታም ፡ የሚወደኝ ፡ ቢኖር ፡ ቃሌን ፡ ይጠብቃልና ፡ አባቴ ፡ ይወደዋል ፡ ወደርሱ ፡ መጥተን ፡ እናድርበታለን ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፳፫ ፡ ብሏል ፡ ስለምትለው ።

ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ መኾኑ ፡ ርግጥ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ለመኾን ፡ የሚበቃው ፡ በቈሱ ፡ አማካይነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ሃይማኖቱን ፡ መስክሮ ፡ በጥምቀት ፡ ሀብተ ፡ ልደትን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ሃይማኖት ፡ የሚመሰከርበት ፤ በጥምቀት ፡ ሀብተ ፡ ልደት ፡ የሚገኝበትም ፡ ቦታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይባላል ።

ስለዚህ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደላባ ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ በራእዩ ፡ የወርቅ ፡ መሰላል ፡ ያየበትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምጽ ፡ የሰማበትን ፡ ቦታ ፤ በእውነት ፡ እኔ ፡ አላውቅም ፡ ነበርሁ ፡ ለካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚህ ፡ ነውን ፤ ይህ ፡ ስፍራ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ይህም ፡ የሰማይ ፡ ደጅ ፡ ነው ፡ ብሏል ፡ ዘፍ ፡ ፳፰ ፲፩—፳፪ ።

(ለ) ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አሠርቶ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ ከዚያ ፡ አግብቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ወደባርያህ ፡ ጸሎትና ፡ ወደልመናው ፡ ተመልከት ። ባርያህ ፡ በፊትህ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎት ፡ ስማ ። ስሜ ፡ ከዚያ ፡ ይኾናል ፡ ወዳልከው ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ዐይኖችህ ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ የተገለጡ ፡ ይኹኑ ። በዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልዩትን ፡ ጸሎት ፡ ኹሉ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ። ሰምተህም ፡ ይቅር ፡ በል ፡ ብሎ ፡ ቢጸልይ ፤ እግዚአብሔር ፡ ተገልጦ ፡ ጸሎትህን ፡ ሰማሁ ፡ ለዘለዓለም ፤ ስሜ ፡ ከዚያ ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ የሠራኸውን ፡ ቤት ፡ ቀደስሁ ። ዐይኔም ፡ ልቤም ፡ ዘመኑን ፡ ኹሉ ፡ ከዚያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ብሎታል ። ነገ ፡ ቀዳ ፡ ፰ ፩—፳፯ ። ፱ ፩—፯ ።

ይህም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በዔዋዌ ፡ ፈርሶ ፡ ሲኖር ፡ እስራኤል ፡ በዘሩባቤልና ፡ በዮሴዴቅ ፡ መሪነት ፡ ተመልሰው ፡ ቤታቸውን ፡ ሠርተው ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ ስላሉ ፡ በሐጌ ፡ አድሮ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ዘመኑ ፡ አልደረሰም ፡ ይላል ። በውኑ ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ፈርሶ ፡ ሳለ ፡ እላንተ ፡ በተሸለመ ፡ ቤት ፡ ለመኖር ፡ ጊዜ ፡ አላችሁን ፤ ወደተራራ ፡ ውጡ ፡ ዕንጨትም ፡ ተሸከሙ ። ቤቱንም ፡ ሥሩ ። እኔም ፡ እወድላችኋለሁ ። ቤቴ ፡ ስለፈረሰ ፡ እላንተም ፡ ኹሉ ፡ ኹላችሁ ፡ ወደቤታችሁ ፡ ስለሮጣችሁ ፡ በላያችሁ ፡ ያሉ ፡ ሰማዮች ፡ ጠል ፡ [illegible] ፡ ቡቃያዋን ፡ እንዳትሰጥ ፡ ከለከለች ፡ ብሏል ፡ ሐጌ ፡ ፩ ፩—፲፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

በዳዊትም ፡ አድሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ ማደሪያው ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ስለ መረጣት ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ማረፊያዬ ፡ ይች ፡ ናት ፡ መርጫታለሁና ፡ ከዚህ ፡ አድሬ ፡ እኖራለሁ ፡ ብሏል ። መዝ ፡ ፻፴፪ ፡ ፲፫–፲፭ ። በዮሐንስ ፡ ወንጌልም ፡ ቤቴ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ይባላል ። ያባቴን ፡ ቤት ፡ ገባያ ፡ አታድርጉት ፡ ብሏል ፡ ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፵፮ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፲፫ ።

ስለዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰው ፡ ጸሎቱን ፡ መሥዋዕቱን ፡ ቍርባኑን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርብባት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ናት ።

ታቦትም ፡ ሰው ፡ ያቀረበውን ፡ ጸሎት ፡ የሠዋውን ፡ መሥዋዕት ፡ አድሮ ፡ የሚቀበልበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ነው ።

ሰው ፡ ግን ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብቶ ፡ ከታቦት ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ሃይማኖቱን ፡ መስክሮ ፡ በጥምቀት ፡ ባገኘው ፡ ልጅነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ኾኖ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ሲገኝ ፡ የክብሩ ፡ ወራሽ ፡ ይኾናል ።

ስለዚህ ፡ በታቦትና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ቢኾን ፤ በሰውም ፡ ቢኾን ፡ አድሮ ፡ የሚሠራውን ፡ ምሥጢር ፡ ለይቶ ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ነው ፤ ታቦት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ነው ፤ ሰውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ የሚያስነቅፍ ፡ አደለም ።

፲፩ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ራሱ ፡ በሠራው ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ይኖራልና ፡ ያድራል ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ በታቦትና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደማያድር ፡ በውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይቀመጣልን ፡ እነሆ ፡ ሰማይ ፡ የሰማያትም ፡ ሰማይ ፡ ይይዝህ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ፪ ዜና ፡ ፮ ፡ ፲፰ ። ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነው ፡ ምድርም ፡ የእግሬ ፡ ድኳ ፡ ናት ፡ እናንተ ፡ የምትሠሩልኝና ፡ እኔ ፡ የማርፍበት ፡ ቤትስ ፡ እንዴት ፡ የመሰለ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፩ ። እሱ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ ነውና ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ በሠራው ፤ መቅደስ ፡ ከቶ ፡ አይኖርም ፡ የሰው ፡ እጅም ፡ አያገለግለውም ፡ የሐዋ ፡ ፯ ፵፯–፶ ። ፲፯ ፡ ፲፬–፴ ። ስለምትለው ።

እኒህ ፡ ጥቅሶች ፡ እግዚአብሔርን ፡ በባሕርዩ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዙፋን ፡ ወንበር የማይችለው ፤ ቤት ፡ የማይወስነው ፡ ምሉዕ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ መኾኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የተነገሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የፍጥረቱን ፡ ጸሎት ፡ የሚሰማበት ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ የሚቀበልበት ፡ ልዩ ፡ ቦታ ፤ ቤተ ፡ መቅደስ ፤ አድሮ ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራበት ፡ ታቦት ፡ የለውም ፡ ለማለት ፡ አልተነገሩም ። ይህንም ፡ ለመረዳት ፡ ዜና ፡ መዋ ፡ ቀዳ ፡ ፲፫ ፡ ፩–፲፬ ። ኢሳ ፡ ፪ ፡ ፪–፫ ። ፳፯ ፡ ፲፫ ። ፴፯ ፡ ፩ ። ፰ ፡ ፲፫ ። ፰፫ ፡ ፲፰ ። ፰፬ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። ፰፮ ፡ ፯ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፪ ፡ ፵፫ ፡ ተመልከት ።

፲፪ እናንተ ፡ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ልጆች ፡ በሕያው ፡ አምላክ ፡ መንፈስ ፡ እንጂ ፡ በቀለም ፡ ያልተጻፈች ፡ በልብ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዕንጨት ፡ ወይም ፡ በደንጊያ ፡ ጽላት ፡ ያልኾነች ፡ የክርስቶስ ፡ ደብዳቤ ፡ መኾናችሁ ፡ በኹሉም ፡ ዘንድ ፡ የተገለጸ ፡ ነው ፡ ተብሏል ፡ ፪ ቆሮ ፡ ፫ ፩–፲ ፡ ፲፩ ፡ ስለምትለው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህንን ፡ የጻፈ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴን ፡ የማይሻ ፡ ስለኾነ ፡ እናንተን ፡ አስተምረን ፡ አሳምነን ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በደንጋይ ፡ ጽላት ፡ ሳይኾን ፡ በልቡናችሁ ፡ ሰሌዳነት ፡ ስለቀረፅነው ፡ እኛ ፡ ራሳችንን ፡ እያመሰገን ፡ ልንጽፍላችሁ ፡ ወይም ፡ እናንተ ፡ መምሮቻችን ፡ አዋቆች ፡ ጠንቃቆች ፡ ናቸው ፡ ብላችሁ ፡ ልትጽፉልን ፡ አንሻም ። ለእኛስ ፡ ፳መክሊት ፡ ሰጥተኸኝ ፡ ነበረ ፡ ወጥቼ ፡ ወርጀ ፡ ፳ ፡



ጨምሬ ፡ ፲ር ፡ አድርጌያቸዋለሁ ፡ ብለን ፡ በምናበረክትበት ፡ ጊዜ ፡ በክርስቶስ ፡ ዘንድ ። መታወቂያችን ፡ ደብዳቤዎቻችን ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ፡ ሲል ፡ የጻፈው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጽላትን ፡ ሲነቅፍ ፡ የጻፈው ፡ አደለም ።

፲፫ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ያገራችን ፡ ልማድ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ የምውታንና ፡ የፍጡራን ፡ ስም ፡ ተሰጥቶት ፡ ቢሰየም ፡ አለእውቀት ፡ የተደረገ ፡ ስሕተት ፡ ስለ ኾነ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ የምታመልከውና ፡ የምትሰግድለት ፡ በሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ኾኖ ፡ ሲሠለስና ፡ ሲቀደስ ፡ የሚኖረው ፡ አንዱ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ ቤቱም ፡ አንተ ፡ መኾንህን ፡ አስተውል ፡ ስለምትለው ፡

እንደ ፡ ሀገራችን ፡ ሕግና ፡ ልማድ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ታቦተ ፡ ማርያም ፤ ታቦተ ፡ ሚካኤል ፡ ታቦተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እየተባሉ ፡ በቅዱሳን ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢሳይያስ ፡ አድሮ ፡ ጃንደረባ ፡ እኔ ፡ የደረቅሁ ፡ ዛፍ ፡ ነኝ ፡ አይበል ፤ ለጃንደረቦች ፡ ሰንበቴን ፡ ለሚጠብቁ ፡ እኔ ፡ የመረጥሁትንም ፡ ለሚመርጡ ፡ ሥርዓቴንም ፡ ለሚይዙ ፡ በቤቴ ፡ በቅጽሬ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ ከወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ የሚበልጥ ፡ ለዘለዓለም ፡ የማይጠፋ ፡ ስም ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ ስላለ ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፶፮ ፡ ፫–፮ ።

አሁን ፡ ኢሳይያስ ፡ ኅዕዋን ፡ ያላቸው ፡ ስለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ ኅዕዋን ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ የተነገረላቸው ፡ ስለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ብለው ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ጣዕሙን ፡ ፍቅሩን ፡ ንቀው ፡ አቃለው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለገሉ ፡ ቅዱሳን ፡ መኾናቸውን ፤ በቤቴ ፡ በቅጽሬ ፡ ውስጥ ፡ ከወንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ የበለጠ ፡ የማይጠፋ ፡ ስም ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ ያለም ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታቦተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ታቦተ ፡ መርቆሬዎስ . . . እየተባሉ ፡ የሚጠሩት ፡ መጠራት ፡ እንደኾነ ፡ አስተውል ፡ ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ።

ሀገር ፡ ሲያረጅ ፡ ጃርት ፡ ያፈራል ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ አንተ ፡ ተነሥተህ ፡ የሀገርህን ፡ ስሟን ፡ ልታጠፋ ፡ ከልብህ ፡ እየፈጠርክ ፡ መጥሮ ፡ ስም ፡ ትሰጣታለህ ፡ እንጂ ፡ የሀገርህስ ፡ ሕጓና ፡ ሥርዓቷ ፡ እንዲህ ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተመሠረተ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ያለዕውቀት ፡ በስሕተት ፡ የምትናገርም ፡ አንተ ፡ መኾንህን ፡ እወቅ ።

፲፬ ከዚህ ፡ አያይዞህ ፡ የምትናገረው ፡ ኹሉ ፡ ለጣዖት ፡ የተነገረውን ፡ ለጽላት ፡ ለታቦት ፡ እየሰጠህ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ንግግር ፡ ነው ። በጽላትና ፡ በጣዖት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌልሃለሁና ፡ ያነኑ ፡ ተመልከት ፡ መርምር ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፳፬ ።

## አድራጊ ፡ ማድረጊያ ፡ ተደራጊ ።

፩ ከአገራችን ፡ ባስሕተትና ፡ በልማድ ፡ ፍጡር ፡ ለፈጠረው ፡ ለግብረ ፡ እድ ፡ ይሰገድበታል ፡ ይኸውም ፡ ከንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ታቦት ፡ ነው ። ይህ ፡ ታቦት ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ከዱር ፡ ተቈርጦ ፡ መጥቶ ፡ ሕዝብ ፡ በዋጋ ፡ ተስማምቶ ፡ አናጢ ፡ ጠርቦ ፡ አበጃጅቶ ፡ ሰው ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ [illegible] ፡ ኵሐ ። ያማረና ፡ የለሰለሰ ፡ የማይነቅዝ ፡ ዕንጨት ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከማይነቅዝ ፡ እንጨት ታቦት ፡ እንድንቀርጽ ፡ ያዘዘን ፡ እግዚአብሔር ፡ መኽ ኑን ፡ ከአሪት ፡ ዘጸአ ፡ ምዕ ፡ ፳፭ ፡ ቍ ፡ ፲-፳፫ ፡ ጠቅሼ ፡ ባለፈው ፡ አንቀጽ ፡ አስረድቼሃለሁና ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ ነገር ፡ አትየው ።

፪ ይህን ፡ ዕንጨት ፡ ግን ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ጠረጴዛ ፡ መንበር ፡ ወይም ፡ ስደቃ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ያልኾነ ፡ ያው ፡ አምላክ ፡ በዝናቡ ፡ አብቅሎ ፡ ያሳደገው ፡ የዱር ፡ ዕንጨት ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፵፬ ፡ ፱—፳ ። ኤር ፤ ፲ ። ፩—፳ ፡ ስለምትለው ።

እኛም ፡ ታቦትን ፡ የምናከብረው ፡ ስሙ ፡ ተጽፎበታል ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ ይፈ ተትበታል ፡ ስለዚህ ፡ በታቦቱ ፡ አንጻር ፡ ቆመን ፡ ያቀረብነውን ፡ ጸሎት ፡ የሠዋን ውን ፡ መሥዋዕት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀበለናል ፡ ብለን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዕንጨት፡ መቀረጹን ፡ ዘንገትን ፡ ዓለምን ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፤ ነው ፡ ብለን ፡ አደለም ።

፫ መሪዎቻችን ፡ ግን ፡ የእገሌ ፡ ሀገር ፡ ታቦት፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷል ፡ ተአምራትም ፡ አሳይቷልና ፡ ስጊድ ፡ ይገባዋል ፡ በገንዘባቸው ፡ ገዝተው ፡ የእንጨት ፡ የብረት ፡ የወርቅ፡ መስቀል ፡ አሠርተው ፡ ሕይወት ፡ ለሌለው ፡ ለም ውቱ ፡ ነገር ፡ ሕያዋን ፡ ሊስሙትና ፡ ሊሰግዱለት ፡ ይላሉ ። ዘፀአ ፴፪ ፩—፰ ስለምትለው ።

ዘፀአ ፡ ፴፪ ፩-፰ ፡ እስራኤል ፡ አሮንን ፡ አስገድደው ፡ ስላሠሩት ፡ ጣዖት ፡ የተነገረ ውን፡ንባብ ፡ ያለቦታው ፡በእግዚአብሔር ፡ትእዛዝ ፡ ከሕዝብ ፡ ገንዘብ፡ ተለይተው፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ገንዘቦች ፡ በኾኑ ፡ ንዋያተ ፡ ቅድሳት ፡ ላይ ፡ በመጥቀስህ ፡ የራስህን ፡ ዕውርነትና ፡ ድንቁርና ፡ ትመሰክራለህ ፡ እንጂ ፡ እኛን ፡ መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ የሚያ ሰኘን ፡ አደለም ። እኒህም ፡ ገንዘቦች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለዩ ፡ ንዋያተ ፡ ቅድሳት ፡ መኾናቸውን ፡ ትረዳ ፡ ዘንድ ፡ ዘፀአ ፳፭ ፡ ፩-፱ ፡ ብትመለከት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እስራኤል ፡ የስለት ፡ ገንዘብ ፡ ይሰጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ንገራቸው ፡ ስለት ፡ የምትቀበላቸ ውም ፡ ገንዘብ ፡ ወርቅ ፤ ብር ፤ ናስ ፤ ሰማያዊ ፤ ወይም ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ የገባ ፡ ፈትል ፤ ሻሽ ፤ የፍየል ፡ ጠጕር ፤ የዳንግሌ ፡ ቍርበት ፤ ቀይ ፤ ወይም ፡ ሰማያዊ ፡ ዓረብ ፡ የግ ራር ፡ ዕንጨት ፤ የመብራት ፡ ዘይት ፤ ለሚቀቡት ፡ ሽቱ ፡ ለመዓዛ ፡ ዕጣን ፤ ዕንቍ ፡ በቀሚስ ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሳንቃ ፡ የሚኾን ፡ ጌጥ ። መቅደስም ፡ ሥሩልኝ ፡ በመሃከላቸው ፡ አድራለሁ ፡ አለው ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚ ያድርባቸው ፡ መኾናቸውን ፡ አውቀን ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ እንሰጣቸዋለን ፡ እንጂ ፡ ንዋያተ ፡ ቅድሳቱን ፡ አማልክት ፡ የምንላቸው ፡ አደለንም ።

፬ የአዳምን ፡ ሕይወት ፡ ለማዳን ፡ የቻለውን ፡ ግን ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ የፈሰሰው ፡ መለኮታዊ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ክብሩ ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመስቀያው ፡ በደረቁ ፡ ዕንጨት አደለም ፡ ስለምትለው ።

የአዳምን ፡ ሕይወት ፡ ለማዳን ፡ የቻለው ፡ መለኮታዊ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ በመ ስቀል ፡ ላይ ፡ የፈሰሰው ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ አለው ፡ ብለን ፡ የምናምን ፡ አደለንም ።

፭ አድራጊ ፡ ማድረጊያ ፡ ተደራጊ ፡ የተሰቀለውንና ፡ መስቀያውን ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ ይገባናል ፡ ስለምትለው ።

አድራጊም ፡ ለቤዛ ፡ ዓለም ፡ ሰው ፡ ስለኾነ ፡ ክርስቶስን ፡ ኃጥእ ፡ ብለው ፡ የሰ ቀሉት ፡ አይሁድ ፤ ተደራጊም ፡ ለቤዛ ፡ ዓለም ፡ የተሰቀለ ፡ ክርስቶስ ፤ ማድረጊ ያም ፡ የተሰቀለበት ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ መኾኑን ፡ ለይተን ፡ ያወቅን ፡ ነን ፡ እንጂ ፡ እንዳ... ፡ እንደመትጠመው... ፡ አደለንም ።



፮ ለምሳሌ ፡ በየቤታችን ፡ የምንሰቅለው ፡ ሥጋ ፡ ቋንጣውን ፡ ብቻ ፡ እንበላለን ፡ እንጂ ፡ መስቀልያውን ፡ ሕይወት ፡ ስለሌለው ፡ አይበላምና ፡ በልተነው ፡ አናውቅም ፡ ስለምትለው ።

ባሁኑ ፡ አነጋገርህ ፡ ከለማስተዋልህ ፡ ብዛት ፡ የተነጣ ፡ መስቀልን ፡ የምንበላው ፡ አስመሰልህ ፡ ትናገራለህ ። እኛስ ፡ ሥጋን ፡ የምንሰቅልበትን ፡ ኩላብ ፤ ወይም፡ ቋንጣ ፡ የሰቀልንበትን ፡ ገመድ ፤ ለጊዜው ፡ ከሠራንበት ፡ በኋላ ፡ ለሌላውም ፡ ጊዜ፡ እንደሚያስፈ ልገን ፡ አውቀን ፡ እንዳይቆሽሽ ፡ በንጹሕ ፡ እንደምናስቀምጠው ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ የከበረ ፡ መስቀልንም ፡ በእየጊዜው ፡ አጋንንትን ፡ ድል ፡ የምንነሣበት ፡ መሣሪያችን ፡ መኾኑን ፡ አውቀን ፡ እናከብረዋለን ፤ የሚገባውን ፡ ስጊድ ፡ እናቀርብለታለን ፡ እንጂ ፡ የምንበላው ፡ አደለንም ።

የምናቀርብለት ፡ ክብርም ፡ ከጣዖታት ፡ የተለየ ፡ መኾኑን ታመዛዝንበት ፡ ዘንድ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ሊቃውንት ፡ የተደረሰ ፡ አንድ ' ዋዜማ ፡ ቅኔ ፡ እጽፍልሃለሁ ።
እሰግድ ፡ በብረክየ ፡ ወበልብየ ፡ እንጂ ፡ ለዕፀ ፡ ቅዱስ ፡ መስቀል ።
እስመ ፡ ተቀደሰ ፡ በደሙ ፡ ለቃል ።
ኤፍሬምስ ፡ ለዕፀ ፡ ገዳም ፡ ወሐቅል ።
መንፈቆ ፡ ይወዲ ፡ ውስተ ፡ ነበልባል ።

ወመንፈቆ ፡ አምላኪየ ፡ ይብል ፡ ብለዋል ። ምቀኝነት ፡ አሳውሮህ ፡ ዐይነ ፡ ልቡናህን ፡ ካልጋረደብህ ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንዋያተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታቦትን ፡ መስቀልንና ፡ ጣዖታትን ፡ ለይታ ፡ ያወቀች ፡ መኾኗን ፡ በዚህ ፡ ቅኔ ፡ አመዛዝነህ ፡ ልታውቅ ፡ ትችላለህ ።

፯ መስቀሉ ፡ ታቦቱ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አሳይቷል ፡ ቢሉም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ ሲያወጣቸው ፡ ታላቁ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራንም ፡ ከፍሎ ፡ ሲያሻግራቸው ፡ በበትረ ፡ ሙሴ ፡ ተአምራት ፡ አድርጎ ፡ ነው ። ዘፀአ ፡ ፬ ፩—፲፯። ፲፬ ፩—፴፩ ፡ ስለ ምትለው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀድሞ ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ጀምራ ፡ እስ ራኤል ፡ የነፍሳት ፤ ኤርትራ ፡ የባሕረ ፡ እሳት ፤ በትረ ፡ ሙሴ ፡ የመስቀለ ፡ ክርስ ቶስ ፡ ምሳሌ ፡ መኾኑን ፡ አውቃ ፡ በተስፋ ፡ ስትጠባበቀው ፡ ኖራለች ።

ከልደተ ፡ ክርስቶስም ፡ ወዲህ ፡ ምሳሌው ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ አውቃ ፡ ባሕረ ፡ እሳትን ፡ የተሻገረችበትን ፡ መስቀለ ፡ ክርስቶስን ፡ ታከብራለች ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ አትሠራም ።

፰ እንኳንና ፡ ሕያዋን ፡ በያዙቱ ፡ ማድረጊያ ፡ ምውቱ ፡ የነኤልሳዕ ፡ አጥንቶም ፡ ከመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ምውት ፡ አንሥቶ ፡ ተአምራት ፡ አሳይቷል ፡ ፪ ነገ ፡ ፲፫ ፳ ስለምትለው ።

በመንፈሰ ፡ ረድኤት ፡ መለኮታዊ ፡ ኃይል ፡ ያገኘ ፡ የኤልሳዕ ፡ ዓፅም ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ መለኮታዊ ፡ ኃይል ፡ ማድረግ ፡ ከቻለ ፤ በመንፈስ ፡ ልደት ፡ የከበሩ ፤ የቅዱሳ ንማ ፡ ዐፅም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ኃይል ፡ ማድረግ ፡ የሚቻላቸው ፡ መኾኑን ፡ አውቀን ፡ ብንማፀንባቸው ፡ የሚያስነቅፈን ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ እስኪ ፡ ንገረኝ ።

... ...ቀው ፡ አጥንት ፡ ባኽያ ፡ መንጋጋ ፡ ሽህ ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡ ለጠላቶቹ ፡ ድል ፡ ነሥቷል ፡ መሳ ፡ ፲፭ ፲፬—፳ ። የነጳውሎስ ፡ የልብሳቸው ፡ ቍራጭ ፡ በድውያን ፡ ላይ ፡ ቢያኖሩት ፡ እያዳነ ፡ ብዙ ፡ ተአም ራት ፡ አሳይቷል ...

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰውነታቸው ፡ አልፎ ፡ በለበሱት ፡ ልብስ ፡ በጨበጡት ፡ በትር ፡ በያዙት ፡ መሣሪያ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ኃይል ፡ የሚያደርግላቸው ፡ ባለሟሎቹ ፡ መኾናቸውን ፡ ካወቅህ ፡ እኛን ፡ ምን ፡ በሉ ፡ ትለናለህ ፤ ይህነኑ ፡ አውቀን ፡ ለእኛም ፡ አስደርጉልን ፡ ብለን ፡ እንማፀንባቸዋለን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ አርገናል ? አማልክት ፡ ናችው ፡ ዓለምን ፡ ፈጠሩ ፡ ብለን ፡ አምልከናቸዋልን ፡ ምን ፡ አርጋናል ።

፲ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ታላላቅ ፡ ተአምራት ፡ ከዚህም ፡ የበላጠ ፡ ቢሠራ ፡ ግን ፡ ምስጋናና ፤ ስጊድ ፡ ለማይመስነው ፡ መለኮትና ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ኃይል ፡ ላለው ፡ ካልኾነ ፡ ለኃላፊና ፡ ጠፊው ፡ ለማይጠቅም ፡ ዕንጨትና ፡ አጥንት ፡ ብረትና ፡ አጭርቅት ፡ መስጠት ፡ ክፉ ፡ የማይገባና ፡ ለአምላካችንም ፡ የሚያስቀናውና ፡ የሚያሳዝነው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ስለምትለው ።

ስለሰጊድ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ መላልሼ ፡ አስረድቸሃለሁና ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገም ፤ ምስጋና ፡ እንዲገባቸው ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማይታበል ፡ ቃሉ ፡ ብፁዓን ፡ ብፁዓን ፡ እያለ ፡ ያመሰገናቸው ፡ ቅዱሳንን ፡ እኛስ ፡ የሚገባቸውን ፡ ምስጋና ፡ ብንሰጣቸው ፡ ነውሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ማቴ ፡ ፭ ፫–፲፪ ። ሉቃ ፲፰–፳፬ ። ፲፮ ፴፯ ፴፰ ፵፫ ።

ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ በአፍኣ ፡ ያሉ ፡ ሙሐመዳውያን ፡ ሙፍቲና ፡ ቃዲ ፡ ካንተ ፡ አስተያየት ፡ የበለጠ ፡ አስተያየት ፡ አግኝተው ፡ አምልኮታችን ፡ እውነተኛ ፡ መኾኑን ፡ ተረድተውት ፡ ክርስቲያን ፡ ጣዖት ፡ ያመልካል ፡ ማለት ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሲመሰክሩ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ የምትለው ፡ አንተ ፡ እኛን ፡ ጣዖት ፡ ያመልካሉ ፡ ለማለት ፡ ጽላተ ፡ ሙሴን ፡ ያከብሩ ፡ የነበሩ ፡ ነቢያት ፡ ጠንቀቀው ፡ ለይተው ፡ ስለጣዖታት ፡ የጻፉትን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ለታቦት ፡ እየሰጠህ ፡ በመጥቀስህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጣዖት ፡ ከማለት ፡ የሚያደርስህ ፡ መኾኑን ፡ አለማወቅህ ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናል ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ በአምልኮታችን ፡ ውስጥ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያሳዝንና ፡ የሚያስቈጣ ፡ ነገር ፡ የለበትም ።

፫ ባገራችን ፡ ባድዋ ፡ ሲልቨስትሪ ፡ የተባለ ፡ ፈረንጅ ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ፡ ም፡ የወፍጮ ፡ መኪና ፡ ለማበጀት ፡ ብሎ ፡ የወንዙ ፡ አስምን ፡ ወኃ ፡ ሽቅብ ፡ ለማውጣት ፡ ግንብ ፡ ሲገነባ ፡ ያገሬ ፡ ሰዎች ፡ እንአቶ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ አይወዱ ፡ ተሰብስበው ፡ ይህ ፡ ወንዝ ፡ ያባ ፡ ገሪማ ፡ ነው ፡ ተቈጥተው ፡ ያፈርሱብሃልና ፡ ባትሠራ ፡ ይሻልሃል ፡ አሉት ። እ ሱም ፡ ፍጡራን ፡ ኃይል ፡ እንደሌላቸው ፤ ሲያስረዳ ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ ድሮ ፡ የሞቱትን ፡ ያገሬ ፡ መነኰሴ ፡ መቸ ፡ ወኃ ፡ ለመፍጠር ፡ ቻሉና ፡ ግንብ ፡ ለማፍረስ ፡ በቂ ፡ ስንት ፡ ሺ ፡ የሚኾን ፡ ኃይልና ፡ ወታደርስ ፡ ይኖራቸዋል ። አትዋሹ ፡ ሠሪና ፡ አፍራሽ ፡ በሰማይ ፡ የሚኖረው ፡ ፩ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ካልኾነ ፡ ሌላ ፡ የማውቀው ፡ ነገር ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ተቆገራቸው ። ኤር ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ፡ ኢሳ ፡ ፵፬ ፡ ፳ ። ስለዚህ ፡ ሥራው ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ያልተመሠረተና ፡ አምላክም ፡ ያልፈቀደው ፡ ስለኾነ ፡ በሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ፡ ም፡ በመርቆሬዎስ ፡ ቀን ፡ ብርቱ ፡ ዝናም ፡ ከምድራዊው ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ ሳይኾን ፡ እርሱ ፡ እንዳለው ፡ ከሰማይ ፡ ዘንሞ ፡ ግንቡን ፡ አፈረሰበት ። ሕዝባችን ፡ ግን ፡ ውሸቱን ፡ የማጋነን ፡ ሲል ፤ በሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ በሚዘከሩበት ፡ ቀን ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ በተአምራት ፡ አፈረሱት ፡ እያለ ፡ ያወራል ፡ በ፳፩ መርቆሬዎስ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ፈረሰ ፡ ግን ፡ ጌታዬ ፡ የማን ፡ ብርሃን ፡ አባራ ፡ ኪዳኑ ፡ ዐድዋ ፡ በተቀኙት ፡ ቅኔ ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ።

መ ወ ድ ስ ።

በመጽሔት ፡ ማይ ፡ ርእይዎ ፡ ለመርቆሬዎስ ፡ ጠቢባን ፡ ዕርዕ ፡ ዘገብሩ ፡ በዓለ ፡ ተሐውሶ ፡ በማይ ።
ወእመ ፡ ሕፍነ ፡ ማይ ፡ ከልእዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነዳይ ።
ወድቀ ፡ እመንበሩ ፤ ዘተሐንፀ ፡ በእብነ ፡ ሕንደኬ ፡ ሰናዖር ፡ ዐቢይ ።



ርደተ ፡ ማየ ፡ ዐይኅ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ መንጠላዕተ ፡ ማይ ፡ ዘሰፍሐ ፡ እደ ፡ ሰብአ ፡ ግብጽ ፡ ጠዋይ ።
ተወለጠ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍቱ ፡ ርእየተ ፡ መልክዑ ፡ ሠናይ ።
ለገዝንቱ ፡ እብነ ፡ ህንደኬ ፡ ወሰገ ፡ ዕንቈ ፡ ባሕርይ ።
አምጣነ ፡ ጠፈሩ ፡ ገዝናም ፡ ወመሠረቱ ፡ ቀላይ ፡
ለዘገብረ ፡ ተአምረ ፡ መርቆሬዎስ ፡ በሰማይ ። ስለምትለው ።

(ሀ) ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፍከው ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ፡ ም፡ ሲኾን ገና ፡ ትደርስበት ፡ አትደርስበት ፡ ባልታወቀው ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ፡ ም፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ተሠራ ፡ ብለህ ፡ ጽፈሃል ። የስሕተትም ፡ እንዳይኾን ፡ በዚሁ ፡ በ፻፵፯ኛው ፡ ገጽ ፡ በመሥመር ፡ ፲፭ና ፡ ፳፬ ፡ መላልሰህ ፡ አረጋግጠሃል ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ፡ ም፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያላለፈ ፡ ገና ፡ ወደፊት ፡ ፵፰ ፡ ዘመን ፡ የቀረው ፡ ሲኾን ፡ እንዳለፈና ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ተሠራበት ፡ አድርገህ ፡ ከተናገርክ ፡ የስሕተት ፡ የድፍረት ፡ ነቁ ፡ ምንጩ ፡ እንደ . . . . አንተ ፡ መኾንህን ፡ እወቅ ፡ ተረዳ ። ሌላውም ፡ ተመልከች ፡ ሌላው ፡ ነገርህ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መኾኑን ፡ ይመዝንበት ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ጽሑፍህን ፡ ሚዛን ፡ አድርጌ ፡ አቅርቤ ለታለሁ ።

(ለ) እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ተአምራት ፡ ምናልባት ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ፡ ም፡ ተጀርጎ ፡ ይኾናል ፡ ብለን ፡ ገምተን ፡ ወደ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ እንራመድ ።

የሀገርህ ፡ ሰዎች ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ ተቈጥተው ፡ ያፈርሱብሃልና ፡ ባትሠራው ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ትንቢት ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፤ ግንቡን ፡ የሚያፈርሱበትን ፡ ዕለትና ፡ ወር ፡ አልወሰኑም ፤ መሣሪያውንም ፡ ለይተው ፡ አልተናገሩም ።

ፀመፀኛው ፡ ሲልቨስትሪ ፡ ግን ፡ የነገሩትን ፡ አልሰማም ፡ ብሎ ፡ በእንቢተኝነት ፡ ቢሠራው ፤ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ተኻክል ፡ ሃይማኖት ፡ ካላችሁ ፡ ያችን ፡ ሾላ ፡ ዛፍ ፡ ከሥርሽ ፡ ተንቅለሽ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ተተከይ ፡ ብትሏት ፡ ትታዘዝላችኋለች ፡ ከተባለት ፡ አንዱ ፡ አባ ፡ ገሪማ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ሳያደርሱ ፡ በሰኔ ፡ ፳፫ ፡ ኃይለኛ ፡ ዝናም ፡ አስነሥተው ፡ አፈራርሰው ፡ ሲጥሉለት ፡ ጊዜ ፡ ያገርህ ፡ ሰዎች ፡ ትንቢት ፡ መፈጸሙን ፡ ከማድነቅ ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ አለበት ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፮ ። ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ። ፳፩ ፡ ፳፩ ። ዮሐ ፡ ፲፬ ፲፪ ፡

(ሐ) ለቅዱሳንም ፡ ዝናም ፡ ለማቆም ፡ ወይም ፡ ለማዝነም ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ በኤልያስ ፡ ታውቋል ፡ ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፩–፲፰ ፡ ፵፩–፵፯ ፡ ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፯–፲፱ ፡ ተመልከት ።

(መ) ደግሞ ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልተመሠረተ ፡ አምላክ ፡ ያልፈቀደው ፡ ስለኾነ ፡ ብለህ ፡ ለተአምራቱ ፡ ሌላ ፡ አስተያየት ፡ ልትሰጠው ፡ ቃጥተሃል ። ሲልቨስትሪ ፡ ሠሪና ፡ አፍራሽ ፡ በሰማይ ፡ የሚኖረው ፡ አንዱ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እምነቱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያጸና ፡ ሲኾን ፡ አምላክ ፡ ያልፈቀደበት ፡ ምክንያት ፡ ገብር ፡ ኄር ፡ ወምእመን ፡ ዘበኅዳጥ ፡ ምእመነ ፡ ኮንከ ፡ ዲበ ፡ ብዙኅ ፡ እሠይመከ ፡ ባእ ፡ ውስተ ፡ ፍሥሐሁ ፡ ለእግዚእከ ፡ ብሎ ፡ የሾማቸው ፡ ደገኛውን ፡ ጻድቅ ፤ ድሮ ፡ የሞቱ ፡ ያገሬ ፡ መነኰሴ ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ ግንብ ፡ ለማፍረስ ፡ ስንት ፡ ሺህ ፡ ወታደር ፡ አላቸው ፡ ብሎ ፡ በማቃለሉ ፡ እንደኾነ ፡ አስተውል ።

www.ethiopianorthodox.org

(ሠ) ከምድራዊው ፡ ከባ ፡ ገሪማ ፡ ሳይኸን ፡ በመርቆሬዎስ ፡ ቀን ፡ ከሰማይ ፡ ብርቱ ፡ ዝናም ፡ ዘንሞ ፡ አፈረሰበት ፡ ሕዝባችን ፡ ግን ፡ ውሸቱን ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ በተአምራት ፡ አፈረሱበት ፡ እያለ ፡ ያወራል ፡ ብለህ ፡ ተአምራቱ ፡ ላባ ፡ ገሪማ ፡ መኾኑን ፡ ክደህ ፡ ለመርቆሬዎስ ፡ መኾኑን ፡ አምንሃል ፡ ለዚኸውም ፡ ምስክር ፡ ለዘገብረ ፡ ተአምረ ፡ መርቆሬዎስ ፡ በሰማይ ፡ የሚል ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ ጠቅሰሃል ።

የነገርህ ፡ ከታች ፡ መነሻው ፡ ከላይ ፡ መድረሻው ፡ በጠቅላላው ፡ ቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ የደረቁ ፡ የሰለቱ ፡ ሬሶች ፡ ናቸው ፡ ምንምን ፡ ሊሠሩ ፡ አይችሉም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ መርቆሬዎስ ፡ ይበልጣል ፡ ገሪማ ፡ ያንሳል ፡ በማለት ፡ የቅዱሳንን ፡ ክብር ፡ በማበላለጥ ፡ አይደለምና ፡ መርቆሬዎስም ፡ ኸነ ፡ ገሪማም ፡ ኸነ ፡ ቅዱሳን ፡ መለኮታዊ ፡ ተአምራት ፡ ማድረጋቸውን ፡ ካመንክልኝ ፡ ነገርህ ፡ ኹሉ ፡ ፍሬ ፡ የማይገኝበት ፤ ውርጭ ፡ ብርድ ፡ ያስቀረው ፤ አገዳ ፡ መኾኑን ፡ አውቀህ ፡ ተረታልኝ ። አልረታም ፡ ብትልም ፡ ነገርን ፡ ኹሉ ፡ አንጠርጥሮ ፡ አበጥሮ ፡ ተመልካቹ ፡ ወጣት ፡ ይፍረደኝ ።

፬ ኸኖም ፡ ታማኞች ፡ ቅዱሳን ፡ አገልጋዮቹ ፡ እንዲመሰገኑ ፡ ብሎ ፡ በእጃቸውና ፡ በሚዘከሩበት ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ቢሠራ ፡ ሠሪው ፡ መለኮታዊ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ሊመሰገን ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ እነርሱስ ፡ ማድረጊያዎች ፡ ስለኾኑና ፡ የታዘዙትንም ፡ ተልከው ፡ ስለሠሩ ፡ የታዘዛችሁትን ፡ ኹሉ ፡ ባደረጋችሁ ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ የማንጠቅም ፡ ባሮች ፡ ነን ፡ ልንሠራው ፡ የሚገባንን ፡ ስለ ፡ ሠራን ፡ ምስጋና ፡ አይገባንም ፡ እንዲሉ ፡ ታዝዘዋልና ፡ ላድራጊ ፡ እንጂ ፡ ለማድረጊያስ ፡ ክቶ ፡ ምስጋና ፡ አይገባውም ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፯—፲ ። ስለምትለው ።

አፍህና ፡ ልብህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አብረው ፡ ሠርተው ፡ አያውቁምና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲመሰገኑ ፡ ብሎ ፡ በእጃቸውና ፡ በሚከበሩበት ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ካደረገላቸው ። እኛም ፡ የተደረገላቸውን ፡ ተአምራት ፡ አይተን ፡ ብናከብራቸው ፡ ብናመሰግናቸው ፡ ነውሩ ፡ ምንድ ነው ፤ ይከበሩ ፡ ይመስገኑ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተእዛዝ ፡ ፈጸሙ ፡ ያሰኘናል ፡ እንጂ ፡ ያስነውረናልን ፡

አግብርት ፡ ጽሩዓን ፡ ንሕነ ፡ በሉ ፡ ብሏቸዋል ፡ የምትለውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በወጣኒነት ፡ ሳሉ ፡ ጦር ፡ ሳይጠፋላቸው ፡ ዲያብሎስ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ጦር ፡ ይዋጋቸው ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በትዕቢት ፡ ጦር ፡ እንዳይዋጋቸው ፡ ነበረ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ሠርተናልና ፡ አክብሩን ፡ አመስግኑን ፡ ሳይሉ ፡ አግብርት ፡ ጽሩዓን ፡ ንሕነ ፡ እያሉ ፡ በትሕትና ፡ ሠርተው ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ፈተና ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ መሰወር ፡ የማይቻላቸው ፡ የተራራ ፡ ላይ ፡ መንደር ፡ የመቅረዝ ፡ ላይ ፡ መብራት ፡ ኾነዋል ፡ ማቴ ፡ ፩ ፡ ፲፬-፲፯ ። ማር ፡ ፬ ፡ ፳፩-፳፫ ፡ ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፲፬-፲፯ ።

ብፁዓን ፡ እሙንቱ ፡ አግብርት ፡ እለ ፡ ይረክቦሙ ፡ እግዚአሙ ፡ መጺኦ ፡ እንዘ ፡ ከመዝ ፡ ይገብሩ ፡ ወይትግሁ ፡ ተብለው ፡ ተመስግነው ፡ የዐረቦኑን ፡ ክብር ፡ ወርሰዋል ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፴፯ ። ከዚህኛው ፡ ዓለም ፡ ወደዚያኛው ፡ ዓለም ፡ ተሸጋግ



ረው ፡ የክርስቶስን ፡ ፊት ፡ አይተው ፡ ተሠየም ፡ ዲበ ፡ ፲ቱ ፡ አህጉር ፤ ተሠየም ፡ ዲበ ፡ ፭ቱ ፡ አህጉር ፡ ከተባሉ ፡ በኋላ ፡ አግብርት ፡ ጽሩዓን ፡ ንሕነ ፡ ማለት ፡ የለባቸውም ።

ደግሞስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ታሃክል ፡ ሃይማኖት ፡ ካለቻችሁ ፡ ተራራ ፡ ታፈልሳላችሁ ፡ ዛፍ ፡ ትነቅላላችሁ ፡ አላቸው ፡ እንጂ ፡ ማድረጊያ ፡ ትኾኑኛላችሁ ፡ አላላቸውም ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፳ ። ፳፩ ፳፩ ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፯ ። በዮሐንስ ፡ ወንጌልም ፡ በእኔ ፡ ያመነ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ይሠራል እኔ ፡ ከምሠራውም ፡ የበለጠ ፡ ይሠራል ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ማድረጊያ ፡ ይኸናል ፡ የሚል ፡ የለም ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪ ፤ ማድረጊያ ፡ ናቸው ፡ ማለትን ፡ ከምን ፡ አግኝተህ ፡ ተናገርከው ? እስኪ ንገረኝ ፡ ጠላቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፡ የሚሰድቧችሁን ፡ መርቁ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዳጆቹ ፡ ባለሟሎቹ ፡ ቅዱሳንን ፡ ሰደብክልኝ ፡ ብሎ ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጥህ ፡ መሰለህን ፡ ኧረ ፡ እስኪ ፡ የምትሠራውን ፤ ድፍረት ፡ የምትናገረውን ፡ ስሕተት ፡ መለስ ፡ ብለህ ፡ ተመልከተው ። ዐውታሯን ፡ እንደ በጠሰች ፡ በቅሎ ፡ ፋነህ ፡ በጥጋብህ ፡ ገደል ፡ መግባትህን ፡ እወቀው ።

፭ ዓለምን ፡ ከፈጠሩት ፡ ጀምረው ፡ እስኪአሳልፉት ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ደቂቃ ፡ እንኳ ፡ ተአምራት ፡ ከመሥራት ፡ በዝነው ፡ የማያውቁት ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ ከ፫ጀ፰፰ ፡ ያመት ፡ ቀኖች ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ኹሉ ፡ ተራ ፡ ደርሷቸው ፡ ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ባቢሎንን ፡ (ጥቅመ ፡ ሰናዖር) ፡ ያፈረሱበት ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ተብለው ፡ ይከብራሉ ፡ ስለምትለው ።

አንተ ፡ ከልቡናህ ፡ ሳይኾን ፡ በምላስህ ፡ ላይ ፡ ያገኘኸውን ፡ የማይረባ ፡ የማይጠቅም ፡ ነገር ፡ መናገር ፡ ልማድህ ፡ ስለኾነ ፡ እንዲህ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፤ የመላእክትን ፡ ድርሳናቸውን ፤ የቅዱሳንን ፡ ገድላቸውን ፡ ብትመለከት ፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ብሎ ፡ ሲጀምር ፡ ታገኘዋለህ ። ከዝርዝሩም ፡ ነገር ፡ ገብተህ ፡ ብትመለከት ፡ ሰማዕታት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማመን ፡ ጸንተው ፡ መከራ ፡ ለመቀበል ፡ ጨክነው ፡ ቢገኙ ፤ እግዚአብሔር ፡ ነበልባል ፡ አበረደላቸው ፤ አንበሳ ፡ አሰገደላቸው ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ፡ ዳን ፡ ፫ ፩-፳፯ ። ፯ ፩-፳፬ ።

ገድለ ፡ ቅዱሳንንም ፡ ብትመለከት ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ ዳበ ፡ ለብሰው ፡ ዳዋ ፡ ጥሰው ፡ ፀብዐ ፡ አጋንንትን ፡ ግርማ ፡ ሌሊትን ፡ ድምፀ ፡ አራዊትን ፡ ችለው ፡ ታግሠው ፡ ቢገኙ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈቀ ፡ ኅብስት ፡ እንዲወርድላቸው ፡ ዛፍ ፡ እንዲያፈራላቸው ፡ ቁራ ፡ እንዲታለብላቸው ፡ አደረገ ፡ ሲል ፡ ታገኘዋለህ ።

የመላእክትን ፡ ድርሳን ፡ የቅዱሳንን ፡ ገድልና ፡ ተአምር ፡ ኹሉ ፡ ብትመለከት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈጣሪነት ፡ የቅዱሳንን ፡ ፍጡርነት ፤ የእግዚአብሔርን ፡ አምላክነት ፡ የቅዱሳንን ፡ አምልኮት ፤ የቅዱሳንን ፡ ተጋድሎ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ረድኤት ፡ የሚናገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንዱን ፡ ጻድቅ ፡ አምላክ ፡ የሚል ፡ አይገኝምና ፡ ለሥላሴም ፡ እንደ ሌሎቹ ፡ ኹሉ ፡ ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ደርሷቸዋል ፡ በማለትህ ፡ የተሳሳትክ ፡ አንተ ፡ መኾንህን ፡ እወቅ ።

፮ በኔ ፡ ተጣበቅ ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ አምልክ ፡ ፍራ ፡ አክብር ፡ የሚል ፡ ቃሉ ፡ እንዳይፈርስብን ፡ ለሥራውና ፡ ለመለኮቱ ፡ ሽሪክና ፡ ረዳት ፡ እንዳንጨምርበት ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባናል ፡ ዘዳግ ፡ ፲ ፳ ። ፴፪ ፡ ፲፪ ፡ ስለምትለው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከላይ ፡ እንደገለጥኩልህ ፡ በኔ ፡ ያመነ ፡ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ ከዚያም ፡ የበለጠ ፡ ያደርጋል ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ የፈጣሪያቸውን ፡ ያሃክል ፡ ተአምራት ፡ ማድረግ ፡ ይቻላቸዋል ፡ ብለን ፡ ብናመሰግናቸውም ፡ ብናከብራቸውም ፡ በመለኮቱ ፡ ድካም ፡ ኖሮበት ፡ ቅዱሳን ፡ የሥራ ፡ ረዳቶችና ፡ ሽሪኮች ፡ ይኾኑታል ፡ ብለን ፡ አናምንም ። እርሱ ፡ ፈጣሪ ፡ እነሱ ፡ ፍጡራን ፡ እርሱ ፡ ተመላኪ ፡ እነርሱ ፡ አምላኪ ፡ መኾናቸውን ፡ የምንዘነጋ ፡ አደለንምና ፡ በዚህ ፡ ጥርጥር ፡ አይግባህ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## ጠቅላላው ፡ ማስረጃ ።

፩ የተወደድክ ፡ አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ በዚህ ፡ ክንቱ ፡ የከንቱ ፡ ከንቱ ፡ የተባለው ፡ በኃላፊ ፡ ዓለም ፡ ያለውን ፡ አግራምቢጥ ፡ የኾነ ፡ የሰው ፡ ልማድና ፡ ግዝት ፡ መጠበቁ ፡ አይገባህም ። ስለምን ፡ ብትለኝ ፡ አምላክ ፡ ያላዘዘው ፡ ስለኾነ ። ኤር ፡ ፳፫ ፳፩—፴፪ ። መክ ፡ ፲፪ ፰ ፡ ስለምትለው ።

አንተ ፡ አብሾ ፡ ወይም ፡ አልኮል ፡ ጠጥቶ ፡ ወይም ፡ አእምሮ ፡ የሚለውጥ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ አድሮበት ፡ የተናገረውን ፡ እንደማያውቅ ፡ እብድ ፤ የኾነውንም ፡ ያልኾነውንም ፡ ትቀባጥራለህ ፡ እንጂ ፡ ስለ ውግዘት ፡ በ፲፫ተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ከ፯-፲፩ በ፳፪ተኛ ፡ ምዕ ፡ ከ፩—፪ ፡ በሰጠሁህ ፡ መልስ ፡ በሰፊው ፡ ጽፌልሃለሁና ፡ ያንን ፡ ተመልከት ።

፪ እኛ ፡ ግን ፡ ለቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የመሠረታቸው ፡ ሙሴና ፡ የፈጸማቸው ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ኹለቱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተመርተው ፡ ከዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቶ ፡ አንዳች ፡ አትጨምሩ ፡ ወይም ፡ አታጕድሉ ፡ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ግራ ፡ አትፀኡ ፡ ብለው ፡ እንዳስተማሩን ፡ አጠረ ፡ ብለን ፡ ልንቀጥልለት ፡ ረዘመ ፡ ብለን ፡ ልንቀንስለት ፡ ከቶ ፡ የማይገባና ፡ ሐሳባችንም ፡ ያይደለ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ዘዳ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ፲፪ ፡ ፴፪ ፡ ኢያ ፡ ፩ ፡ ፩—፱ ። ምሳ ፡ ፴፰ ፡ ፮ ። ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፳፩ ። ራእ ፡ ፳፪ ፡ ፲፰—፳፩ ፡ ስለምትለው ።

ፊትም ፡ ሐዋርያት ፡ ኋላም ፡ ፫፻ ፲፰ት ፡ ቈጥረው ፡ ያስረከቡን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ሰማንያ ፡ አንድ ፡ ናቸው ። ፹፩ ፡ መኾናቸውንም ፡ አንተ ፡ በገጽ ፡ ፪ መሥመር ፡ ፲፱ና ፡ ገጽ ፡ ፯ መሥ ፡ ፲፯ ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በብዙ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ አረጋግጠህ ፡ ጽፈሃል ።

እነዚኽውም ፡ በእየጊዜው ፡ በእየዘመኑ ፡ የተጻፉ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በንድ ፡ ዘመን ፡ በንድ ፡ ጊዜ ፡ የተጻፉ ፡ አደሉም ።

አንተ ፡ ግን ፡ ከ፹፩ ፡ መጻሕፍት ፡ ፲፯ቱን ፡ ገንጥለህ ፡ ፷፬ቱን ፡ ብቻ ፡ በጥራዝ ፡ አገናኝተህ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እኒህ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ የምትለውን ፡ ስሕተትና ፡ ውሸት ፡ ለማጽደቅ ፤ ሊቀ ፡ ነቢያት ፡ ሙሴና ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ተባብረው ፡ መክረው ፡ ከ፷፬ ፡ በላይ ፡ አትጨምሩ ፡ ከ፷፬ትም ፡ አታጕድሉ ፡ አሉን ፡ ብለህ ፡ ትዋሻለህ ።

(ሀ) ለውሸትህም ፡ ማስረጃ ፡ ሙሴ ፡ በ፫ሺ ፡ ፪፻፹፫ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ተወልዶ ፡ በ፫ሺ ፡ ፫፻፷፫ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፤ በተወለደ ፡ በ፻፳ ፡ ዓመቱ ፡ ሞቷል ።

ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድም ፡ በ፭ሺ ፡ ፭፻፬ ፡ ... በ፭ሺ ፡ ፮፻፬ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ሞቷል ።



ሙሴ ፡ ከተወለደበት ፡ ዮሐንስ ፡ እስከ ፡ ተወለደበት ፡ ፪ሺ ፡ ፪፻፺፩ ፤ ሙሴ ፡ ከሞተበት ፡ ዮሐንስ ፡ እስከ ፡ ሞተበት ፡ ፪ሺ ፡ ፪፻፵፩ ፡ ዘመን ፡ ይገኛል ።

ይህን ፡ ያህል ፡ ዕረፍተ ፡ ዘመን ፡ የጋረዳቸውን ፡ ሰዎች ፡ ፪ቱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተመርተው ፡ ከ፷፬ ፡ መጽሐፍ ፡ በቀር ፡ አትጨምሩ ፡ አታጕድሉ ፡ ብለው ፡ ወሰኑ ፡ ደነገጉ ፡ ማለት ፡ ምንም ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ውሸት ፡ ነው ።

(ለ) ዘዳግ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ የጠቀስከው ፡ ባዘዝኋችሁ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አትጨምሩ ፡ ከርሱም ፡ አታጕድሉ ፡ ይላል ። ሙሴ ፡ በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ትውልደ ፡ አበውን ፡ ቈጥሮላቸዋል ፤ ዜና ፡ አበውን ፡ ተርኮላቸዋል ። በኦሪት ፡ ዘፀአት ፡ ፲ቱ ፡ ቃላትንና ፡ ሌሎችንም ፡ ትእዛዛት ፡ ጽፎላቸዋል ። በኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፡ የሌዋውያን ፡ ሥርዓት ፡ የመሥዋዕቱን ፡ የቍርባኑን ፡ ሕግ ፡ አቋቁሞላቸዋል ። በኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ ትውልድ ፡ ከትውልድ ፡ ነገድ ፡ ከነገድ ፡ እንዳይፋለስ ፡ እስራኤልን ፡ በእየወገን ፡ በእየወገናቸው ፡ ቈጥሮ ፡ የቤት ፡ አለቃ ፡ ሾሞላቸዋል ፡ የሚጓዙበትን ፡ ተራ ፡ የሚሰፍሩበትን ፡ ቦታ ፡ ወስኖላቸዋል ። በኦሪት ፡ ዘዳግም ፡ ባለፈው ፡ ያዘዛቸውን ፡ እየተረከ ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ ባዘዝኋችሁ ፡ ላይ ፡ አትጨምሩ ፡ ከርሱም ፡ አታጕድሉ ፡ አላቸው ፡ እነርሱም ፡ ትእዛዙን ፡ ፈጽመዋል ፡ እንጂ ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ አይጻፍ ፡ አላለም ።

አይጻፍ ፡ አለማለቱም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ሙሴ ፡ አትጨምሩ ፡ አትክፈሉ ፤ ብሎ ፡ ጽፎ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በኢያሱ ፡ ዘመን ፡ ፳፬ ፡ ምዕራፍ ፤ በየጊዜው ፡ ስለተነሡ ፡ መሳፍንትም ፡ ፳፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ ፡ ሩትም ፡ ፬ ፡ ምዕራፍ ፡ መጻሕፍት ፡ ቢጻፉ ፡ እስራኤል ፡ ተቀብለው ፡ ሙሴ ፡ ከጻፋቸው ፡ ከ፭ቱ ፡ ብሔረ ፡ ኦሪት ፡ ጋራ ፡ ቈጥረው ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ሲሠሩባቸው ፡ ኖረዋል ፡ እንጂ ፡ ሙሴ ፡ አትቀበሉ ፡ ብሎናል ፡ ብለው ፡ አንቀበልም ፡ አላሉም ።

በምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ በቍ ፡ ፴፪ም ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ የማዝዝህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርሱን ፡ ጠብቅ ፡ በርሱ ፡ ምንም ፡ አትጨምርበት ፡ ከርሱም ፡ አንዳች ፡ አታጕድል ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ አይጻፉ ፡ አላለም ። ስለዚህ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በእየጊዜው ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ተጽፈዋል ።

(ሐ) ፡ ኢያሱ ፡ ፩ ፡ ፩—፱ ፡ የጠቀስከውም ፡ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾንኩ ፡ እንዲሁ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለሁ ፡ አልጥልህም ፡ አልተውህም ፡ በማለቱ ፡ እስከ ፡ መቸም ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ለመኾን ፡ በቅቶ ፡ ከተገኘ ፡ በማንም ፡ ሰው ፡ አድሮ ፡ ሥራ ፡ የሚያሠራ ፡ መኾኑን ፡ ከማረጋገጥ ፡ በቀር ፡ ከኦሪት ፡ ዘዳግም ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ አትጻፉ ፡ አላለም ።

(መ) ምሳ ፡ ፴፫ ፡ ፮ ፡ የጠቀስከው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ፈጽማ ፡ የተፈተነች ፡ ናት ፡ እርሱ ፡ ለሚታመኑበት ፡ ጋሻ ፡ ነው ፡ እንዳይዘልፍህ ፡ አሰተኛም ፡ እንዳትኾን ፡ በነገሩ ፡ አንዳች ፡ አትጨምር ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ኢታምልክን ፡ የሚያጸኑ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከነን ፡ የሚተረጕሙ ፡ መጻሕፍት ፡ አይጻፉ ፡ አላለም ።

... ፡ አንዳች ፡ መጨመርስ ፡ ሐተታ ፡ መናፍስት ፤ ዐውደ ፡ ነገሥት ፡ እያሉ ፡ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍ ፡ እየጻፉ ፡ ለሕዝብ ፡ ማደል ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

(ሥ)ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፳፭ ፡ የጠቀስከው ፡ ጆሮዎችሽም ፡ በኋላሽ ፡ ይህች ፡ መንገድ ፡ ናትና ፡ ሒዱባት ፡ ቀኝም ፡ ግራም ፡ አትበሉ ፡ የሚሉሺን ፡ ነገር ፡ ይሰማሉ ፡ ይላል ። ይህ ፡ ቃል ፡ በዌዋዌ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ እስራኤልን ፡ ማርከው ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ እየነዱ ፡ እንደ ፡ ወሰዷቸው ፡ ያስረዳል ፡ አንጂ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻፍት ፡ ፷፰ ፡ ብቻ ፡ መኾናቸውን ፡ አያስረዳም ።

ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፪ ፡ ፲፰–፳፭ ፡ የጠቀስከውም ። ዮሐንስ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ወንጌል ፡ ፫ቱን ፡ መልእክታት ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ በደሴተ ፡ ፍጥሞ ፡ ሳለ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚደረገው ፡ ምሥጢር ፡ ኹሉ ፡ ተገልጾለት ፡ ራእየ ፡ ዮሐንስ ፡ ወይም ፡ ቀለምሲስ ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲጽፍ ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ትንቢት ፡ የሚፈጼምበት ፡ ዘመኑ ፡ ቅርብ ፡ ነውና ፤ የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ትንቢት ፤ ንባቡን ፡ የሚያነበው ፤ ምሥጢሩን ፡ የሚመለከተው ፤ ጊዜውን ፡ የሚጠብቀው ፡ ሰው ፤ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በአርእስቱ ፡ እንዳስጠነቀቀ ፡ ራእ ፡ ፩ ፡ ፫ ። በመጨረሻውም ፡ የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ከዚህ ፡ ያል ተጻፈ ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ቢጨምርበት ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውን ፡ መቅሠፍት ፡ እንዲጨምርበት ። ከዚህ ፡ ከተጻፈውም ፡ ቢከፍልለት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከተጻፈ ፡ ከዕፀ ፡ ሕይወት ፡ እንዳይከፍለው ፡ ከቅድስት ፡ ሀገር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊትም ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ጽዋ ፡ ተርታ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ እኔ ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ምትዋሸው ፡ በየጊዜው ፡ ዘመን ፡ ከማይገጥማቸው ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተጻፉ ፡ ፷፰ት ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ጠርዞ ፡ ከ፷፰ ፡ አትለፉ ፡ ከ፷፰ ፡ አታትርፉ ፡ ሲል ፡ የተናገረው ፡ አደለም ።

ስሕተትህን ፡ ክህደትህን ፡ የሚመሰክሩብህ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ከምስክርነት ፡ ለማውጣት ፡ ይመቸኛል ፡ ብለህ ፡ እንዳስፋልት ፡ መንገድ ፡ ወለል ፡ ባለው ፡ በተጣራው ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ያልተማሩትን ፡ ሰዎች ፡ ለማሰናከል ፡ እሾህ ፡ ብትከሰክስበት ፡ ዕንቅፋት ፡ ብታኖርበት ፡ ምን ፡ ትጠቅማለህ ። በእኔ ፡ ካመኑ ፡ ከእኒህ ፡ ከትንንሾች ፡ አንዱን ፡ ያሳተ ፡ ባንገቱ ፡ የመኪና ፡ ወፍጮ ፡ አስሮ ፡ ቢጥሉት ፡ በተሻለው ፡ የለ ፡ ርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይይልህ ፡ ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፮ ። ማር ፡ ፱ ፡ ፵፪ ፡ ሉቃ ፤ ፲፯ ፡ ፩ ።

፫ ከዚህ ፡ አያይዘህ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ነቢያት ፤ ሐዋርያት ፤ ራሳቸው ፡ ሠርተው ፡ ሥሩ ፡ ለማለት ፡ የጻፉትን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ አንተ ፡ ከሥራው ፡ ሳትገኝ ፡ እየመረጥክ ፡ ጽፈኸዋል ፤ ምዕራፉንና ፡ ቍጥሩን ፡ ደርድረኸዋል ። ልሙትልህ ፡ የምትለውን ፡ በሆድህ ፤ የምትወደውን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ዋሾው ፡ ዓለም ፡ ከንቱ ፡ የከንቱ ፡ ከንቱ ፡ የኾነው ፡ ዓለም ፡ እያልክ ፡ በአፍህ ፡ ታማዋለህ ፡ ትጠላዋለህ ፤ በሥራህ ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ አንተ ፡ ትንቀው ፡ የሚንቁትንም ፡ ትንቃቸዋለህ ፡ ትነቅፋቸዋለህ ፡ ምዕ ፡ ፳፭ ፡ ቍ ፡ ፲ ።

እንዲሁም ፡ ስንኳን ፡ በርሱ ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ [illegible] መቀጠል ፡ የማገባውን ፡ መጽሐፈ ፡ ጥንቆላ ፡ ዘኢያ ፡ ፮ ፡ ፲፰–፳፮ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፱ ፡ በመሸጥ ፡ የሕዝብን ፡ ገንዘብ ፡ እየሸለግህ ፡ መንኖ ፡ ጥሪት ፡ ያለህ ፡ ለመምሰል ፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ለገንዘብ ፤ ልትገዙ ፡ አትችሉም ። ለኃጢአት ፡ ኹሉ ፡ ሥሩ ፡ ምንጩ ፡ አፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ ትጠቀሳለህ ።



ከሥራው ፡ ሳትገኝ ፡ በፍህ ፡ ብቻ ፡ ይህን ፡ ብትወተውት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያፍ ፡ ዘመድ ፡ ተገባያም ፡ አይገድ ፡ ይልሃል ፡ ብዬ ፡ እፈራልሃለሁ ፡ እንጂ ፡ የመጻሕፍቱ ፡ ቃልስ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምሰጥህ ፡ መልስ ፡ የለኝም ።

በል ፡ ደኅና ፡ ኹን ። አንተ ፡ ዕውሩን ፡ ሀይናማ ፡ ነህ ፡ ቢሉት ፡ ዐይናማ ፡ ላይኾን ፡ የተሰበረውንም ፡ ደኅና ፡ ነህ ፡ ቢሉት ፡ ደኅና ፡ ላይኾን ፤ የንብላውን ፡ ሕግ ፡ እውነተኛ ፡ ለማስመሰል ፡ በጻፍከው ፡ ስሕተት ፡ የምእመናንን ፡ ልቡና ፡ ይኹንን ፡ አይኹንን ፡ ከሚል ፡ ጥርጥር ፡ ላይ ፡ ስለጣልከው ።

እኔም ፡ ይነግረው ፡ ያጣ ፡ ያሙኝ ፡ አይመስለውም ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ ዝም ፡ ብንልህ ፡ ጥፋትህን ፡ እየቀጠልክ ፡ ስለሔድክ ፡ ለምእመናን ፡ ነገርህ ፡ እውነት ፡ ይመስላቸዋል ፡ በማለት ፤ ገሥጽ ፡ ወተዛለፍ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ እያጽናናኝ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፪ ፡ መልሱን ፡ ስጽፍልህ ፡ ያመላለሱ ፡ ዘዴ ፡ እያስገደደኝ ፡ በማደርገው ፡ ንግግር ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ባርክዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይረግሙክሙ ፡ የተባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይፈርስብኝ ፡ የቀረ ፡ አይመስለኝምና ፡ የሰውን ፡ መዳኑን ፡ እንጂ ፡ መጎዳቱን ፡ የማይወድ ፡ ቸሩ ፡ አምላክ ፡ ኹላችንንም ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ ያገናኘን ።

አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳያዳክም ፡ የፊልጶስን ፡ ቃል ፡ ተቀብሎ ፡ ተጠምቋል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፳፮—፴፱ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ የተወለዱ ፡ አብርሀ ፡ ወአጽብሐም ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባዔ ፡ ያውቁ ፡ ስለነበሩ ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባዔ ፡ ሳያፋልሱ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ የዓለም ፡ ነገሥታት ፡ የመምህራኑ ፡ ወንጌልን ፡ ደም ፡ ሳያፈሱ ፡ በፈቃዳቸው ፡ መምህር ፡ አስመጥተው ፡ ሕገ ክርስትናን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዘረጉ ። እነሆ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በፊት ፡ አምልኮ ፡ ጣዖትን ፡ ንቃ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተቀበለችበት ፡ ቀድሚያ ፡ ፲፱፻፹፱ ፡ ዓመት ፡ አላት ፡ ይህን ፡ ፲፱፻፹፱ትን ፡ ዓመት ፡ ከ፩ሺ፲፱፻፺፬ ፡ ዓ. ም. ፡ ጋራ ፡ ቢገጥሙት ፡ ፫ሺ፲፱፻፹፫ ፡ ዘመን ፡ ይኾናል ። እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከያዘች ፡ አምልኮ ፡ ጣዖትን ፡ ከናቀች ፡ ፫ሺ፲፱፻፹፫ ፡ ዘመን ፡ መኾኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ለሃይማኖተ ፡ አሪት ፡ ለሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ መደበኞች ፡ መኾናችሁን ፡ ከማርት ፡ ከጣዖት ፡ የፈለሳችሁ ፡ የሃይማኖት ፡ እንግዶች ፡ አለመኾናችሁን ፡ አውቃችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ ኩራት ፡ ይደርባችሁ ። እንግዲህ ፡ ወደ አቶ ፡ ዘመንፈስ ፡ አስተያየት ፡ እንመለስ ፡ አቶ ፡ ዘመንፈስ ፡ በትውልዱና ፡ በነገዱ ፡ የዚህ ፡ ዕድል ፡ ተካፋይ ፡ ሲኾን ፡ ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ጽንሱ ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ ፴፯ ። ልደቱ ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ ሦስት ፡ ዘመን ፡ በላይ ፡ ዕድሜ ፡ የሌለው ፤ መስሎ ፡ መታየትን ፡ ለተጐናፀፈ ፡ ለንብላው ፡ ባህል ፤ አዲስ ፡ አማኒ ፡ ቅኝ ፡ ኾኖ ፡ ጥንታዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሲነቅፍ ፡ አባቶቹን ፡ አያቶቹን ፡ ቅድመ ፡ አያቶቹን ፡ ሲሰድብ ፡ ሲዘልፍ ፡ ይታያል ፡ ይልቁንም ፡ መጻሕፍት ፡ የመሰከሩለት ፡ ርእሰ ፡ አበው ፡ ኄኖክንና ፡ ከጌታ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ወንጌልን ፡ የተማረ ፤ በጌታ ፡ ቃል ፡ የተሾመ ፡ ቀሌምንጦስን ፡ ነቅፎ ፡ በ፲፭፻ ፡ ዓ. ም. ፡ የተነሡና ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የገለባበጡ ፡ እነ ሉተርን ፡ አክብሮ ፡ ተቀብሏል ፡ ግብዝነቱን ፡ ለማወቅ ፡ ይኽ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ምስክር ፡ ነው ። በዚሁም ፡ ላይ ፡ የርሱ ፡ ጥፋት ፡ አንሶት ፡ እናንተም ፡ ብኵርናችሁን ፡ እንደ ፡ ዔሳው ፡ ለመብል ፡ ሸጣችሁ ፡ እንድርሱ ፡ ለዚሁ ፡ ለወጣቱ ፡ ባህል ፡ ቅኝዎች ፡ አዲስ ፡ አማኒዎች ፡ እንድትኾኑ ፡ ይጎተጉታችኋል ።

በሃይማኖት ፡ በሕግ ፡ ቅድምና ፡ አለኝ ፡ የማይል ፡ ሕዝብ ፡ መቸም ፡ ያው ፡ ቅኝ ፡ ስለኾነ ፡ የሚቀበለውን ፡ የሃይማኖቱንና ፡ የሕጉን ፡ ደግነት ፡ ከማመዛዘን ፡ በቀር ፡ ክብሬ ፡ ይነካብኛል ፡ ከመዓርጌ ፡ እዋረዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ስጋት ፡ የለበትም ።

ኢትዮጵያማ ፡ በዚህ ፡ እንዳትታሰብ ፡ ለአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥንቱ ፡ መሠረቱ ፡ በአብርሃም ፡ መሪነት ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ስትኾን ፤ ኹለተኛዋ ፡ ተከታይዋ ፡ በንግሥተ ፡ አዜብ ፡ መሪነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ አይደለችምን ።

በሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ ወገን ፡ መለያየት ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖተ ፡ አሪት ፡ ኢይባዕ ፡ ሞዓባዊ ፡ ወአሞናዊ ፡ እስከ ፡ ዓልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ፡ ማለት ፡ ኖሮ ፡ ቢኾን ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ መሲሕ ፡ ክርስቶስን ፡ አልቀበልም ፡ በማለቷ ፡ እንደዔሳው ፡ በኵርነቷን ፡ ለቃ ፡ ከተስፋ ፡ ስትወጣ ፡ ይህን ፡ በኵርነት ፡ [illegible] ፡ መውረስ ፡ የሚገባት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነበረች ።



ነገር ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ መድሎ ፡ የሌለበት ፡ ትክክለኛ ፡ ሕግ ፡ ስለኾነች ፡ አኀዝ ፡ እምድኅርት ፡ እስከ ፡ ቀደምት ፡ እያለች ፡ ለኹሉም ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ጽናት ፡ እንደ ፡ አእምሮው ፡ ስፋት ፡ ዋጋውን ፡ ታድለዋለች ፡ እንጂ ፡ በቀዲመ ፡ ዓመታት ፡ ለማንም ፡ አታደላምና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የእምነት ፡ ቀድሚያ ፡ አለኝ ፡ ብላ ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ አትመካም ፡ ማቴ ፡ ፳ ፡ ፫ ።

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ለሚኰራበት ፡ ለሚመካበት ፡ ለመንግሥቱና ፡ ለነፃነቱ ፡ ደሙን ፡ ለማፍሰስ ፡ ቈራጥ ፡ እንደኾነ ፡ በሃይማኖትም ፡ ረገድ ፡ ተቀዳሚና ፡ መደበኛ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ከእውነተኛነት ፡ ጋራ ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቈጠር ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ ጥንታዊ ፡ ሃይማኖቱንና ፡ ባህሉን ፡ ለዚህ ፡ ያምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ዕድሜ ፡ ለሌለው ፡ የእንብላው ፡ ሕግ ፡ ጥገኛ ፡ ወይም ፡ ቅኝ ፡ ሀገር ፡ አድርጎት ፡ እንዳይገኝ ፡ መጠንቀቅ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

በ፳፫ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ ስግደት ፡ በሰጠሁት ፡ መልስ ፡ ለማስረጃ ፡ ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ። በአፍዓ ፡ ያሉ ፡ ሙፍቲንና ፡ ቃዲን ፡ እንደ ፡ ጠቀስኩ ፡ ከዚህም ፡ የሀገሩ ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ከሚያቃጠለው ፡ ከማኅተማ ፡ ጋንዲ ፡ ንግግር ፡ ባጭሩ ፡ ልጠቅስላችሁ ፡ እወዳለሁ ።

የሀገሩ ፡ ልማድ ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ እሳት ፤ የሚያቃጥለው ፡ ሕንዳዊው ፡ ማህአትማ ፡ ጋንዲ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ላላስተማሩት ፤ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ለማያውቁት ፡ ሃይማኖቱና ፡ ሕጉ ፤ ተቈርቋሪ ፡ ይህን ፡ ጉዳት ፡ የሌለበትን ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ ለጊዜው ፡ አትንኩብኝ ፡ አታናውጡብኝ ፡ ይኑር ፡ እንዳለ ፡ ብሏል ።

በጥብቅ ፡ እንዲከበሩለት ፡ ከሚያሳስባቸው ፡ ልማደ ፡ ሀገሮችም ፡ አንዱ ፡ ሥጋዋን ፡ ሊበሏት ፡ ወተቷን ፡ ሊጠጧት ፡ ለተፈጠረች ፡ ለላም ፡ ከመጠኗ ፡ በላይ ፡ የሚደረግላት ፡ ክብር ፡ ነው ።

ይህም ፡ ልማድ ፤ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ ጥንት ፡ ከነበረው ፡ አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ የተወረሰ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ መገመቱ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ርሱ ፡ ግን ፡ የጣዖታት ፡ አምልኮ ፡ የጣዖታት ፡ መንፈሳዊ ፡ አክብሮ ፡ ከእኔ ፡ ከጋንዲ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ፡ ብላችሁ ፡ ብትፈልጉ ፡ ድካማችሁ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ጣዖት ፡ አላመልክም ፡ ብሎ ፡ ጣዖት ፡ አለማምለኩን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ መንፈሳዊ ፡ አክብሮን ፡ ለምስል ፡ ለሥዕል ፡ መስጠት ፡ በጋንዲ ፡ ዘንድ ፡ በሕንድ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ የመንፈስ ፡ ደካማነት ፡ እንጂ ፡ አምላክን ፡ መካድ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ሥዕልንና ፡ ምሳሌን ፡ የሚያከብር ፡ ሰው ፡ ስላከበረ ፡ ሊቀለድበትና ፡ ሊናቅ ፡ አይገባም ።

ተመልካቹም ፡ በሥራው ፡ ባይስማማበትም ፡ አክብሮ ፡ ሊያየው ፡ ይገባል ።

እኛ ፡ መመልከት ፡ ያለብን ፡ የሥዕልንና ፡ የምሳሌን ፡ አክባሪን ፡ ሰው ፡ ዋና ፡ አሳቡን ፡ ዓላማውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዋናው ፡ አሳቡ ፡ ከዓላማው ፡ ለመድረስ ፡ የሚከተለውን ፡ ምክንያትና ፡ መንገድ ፡ አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህማ ፡ ከኾነ ፡ ተመልካቾችም ፡ አእምሯችን ፡ ግዙፍ ፤ መኾኑን ፡ መሰከርን ፡ ማለት ፡ ነው ። ፎቶ ፡ ግራፍ ፡ ሳያይ ፡ ያሉትም ፡ የሞቱትም ፡ ቢኾኑ ፡ ዘመዶቹና ፡ ወዳጆቹ ፡ ደግ ፡ ሥራቸውም ፡ ትዝ ፡ የሚለው ፡ አለ ።

ደግሞ ፡ ስለአእምሮው ፡ ደካማነት ፡ ሥራቸውን ፡ አብልጦ ፡ ለማሰብ ፡ ፎቶ ፡ ግራፋቸውን ፡ ለማየት ፡ የሚገደድ ፡ አለ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ዘመድህ ፡ የወረቀቱ ፡ የቀለሙ ፡ ፎቶ ፡ ግራፍ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አንደፍርም ።

እንዲሁም ፡ በአምልኮ ፡ ተግባር ፡ ሥዕልና ፡ ምስል ፡ ያስፈለገውን ፡ ሰው ፡ አምላኮችህ ፡ ወረቀት ፤ ዕንጨትና ፡ ደንጋይ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ አይገባንም ፡ ብሎ ፤ ኄኖክ ፡ ሰብእሰ ፡ ኢተፈጥሩ ፡ ለዝ ፡ ከመዝ ፡ ከመ ፡ ያጽንዑ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ በረቅ ፡ ወበቀለም ፡ አላ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይግበሩ ፡ ወይንበሩ ፡ ንጹሓነ ፡ ወቅዱሳነ ፡ ያለውን ፡ ፲፱ ፡ ፳፪ ።

ኢሳይያስም ፡ እስመ ፡ ሕገ ፡ ወሀበ ፡ ለረድኤት ፡ ያለውን ፳ ፡ ፳ ።

ማር ፡ ይስሐቅም ፡ ሕግሰ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ተውህበ ፡ ለሰብእ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዲሙ ፡ ወዘተጽሕፈሰ ፡ መጽአ ፡ እምድኅረ ፡ ተዐድዎተ ፡ ሕግ ፡ ያለውን ፡ የመሰለ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ተናግሯል ፡ ፪ ፡ ፩።

እኒህም ፡ በግዕዝ ፡ የጠቀስኳቸው ፡ ኃይለ ፡ ቃሎች ፡ ወደ አማርኛ ፡ ሲተረጐሙ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ መርምሮ ፡ ፈጣሪውን ፡ አውቆ ፡ ሊኖር ፡ ሕገ ፡ ልቡና ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበረ ፤ ስለ መንፈሱ ፡ ደካማነት ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ተመራምሮ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ ቢሳነው ፡ ለልቡናው ፡ አጋዥ ፡ ረዳት ፡ ሊኾን ፡ በቃል ፡ ያጠናውን ፡ አይቶ ፡ ሊረዳበት ፡ መልክዐ ፡ ፊደል ፡ ተቀረፀለት ፤ መጻሕፍት ፡ ተጻፉለት ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ ተሠሩለት ፤ በጽሑፍ ፡ የተሰጠውንም ፡ ዓላማ ፡ በማየት ይደርስበት ፡ ዘንድ ፡ ጽላትን ፡ ሥዕልን ፤ መስቀልን ፤ የመሳሰሉ ፡ መታሰቢያዎች ፡ ተዘጋጁለት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህች ፡ ካባቶቻችሁ ፡ የወረሳችኋት ፡ ሃይማኖትና ፡ ሕግ ፡ ቀድሞ ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ከሃይማኖተ ፡ ኦሪት ፡ በአፍዓ ፡ የነበሩ ፡ እነ በለዓም ፡ እነ ንዕማን ፡ ሶርያዊ ፡ እንደ ፡ መሰከሩላት ፡ ዛሬም ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ በአፍዓ ፡ ያሉ ፡ እነ ሙፍቲ ፡ እነ ቃዲ ፡ እነ ማህአተማ ፡ ጋንዲ ፡ ሳይቀሩ ፡ የመሰከሩላት ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ በአቶ ፡ ዘመንፈስ ፡ ያደረ ፡ መንፈሰ ፡ ጽርፈት ፡ እንደ ፡ ሚለፈልፈው ፡ አይደለችምና ፡ አትጠራጠሩ ፡ አትሸበሩ ።

የጥንተ ፡ ተገዥ ፡ የአብርሃም ፡ የጥንተ ፡ ተገዥ ፡ የንግሥተ ፡ አዜብ ፡ የቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የሌሎቹም ፡ አግአዝያን ፡ ዘሮች ፡ መኾናችሁን ፡ አውቃችሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ ኩራት ፡ ይደርባችሁ ።

ዕንቢያችን ፡ አቅኚነታችንን ፡ በቅኚነት ፡ ጌትነታችንን ፡ በባርነት ፡ ቀዳማዊነታችንን ፡ በደኃራዊነት ፡ አንለውጥም ፡ በሉት ።

ያባቶቻችንን ፡ ምክር ፡ የምንሰማበት ፡ ርኅው ፡ጆሮ ፡ የምናመዛዝንበት ፡ ረቂቅ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኹላችን ፡ ይስጠን ፡ አሜን ።


| ተራ ቁ | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | መቅድም ፡ ከመልስ ፡ ሰጭው ፡ | ፭ |
| ፪ | መግቢያ ። | ፲፩ |
| ፫ | ጸሎት | ፲፫ |
| ፬ | ተግሣጽና ፡ ምክር ። | ፲፭ |
| ፭ | ዐዋጅ ፡ | ፲፯ |
| ፮ | ማስጠንቀቂያ ። | ፳፩ |
| ፯ | መግቢያ ። | ፳፫ |
| ፰ | መቅድም ። | ፴፪ |
| ፱ | ልዩ ፡ መግለጫና ፡ ምክር ፡ | ፺፪ |
| ፲ | ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ትርጓሜ ። | ፺፱ |
| ፲፩ | ማይ ፡ ንዝጸምዐ ። | ፻፲፰ |
| ፲፪ | ልዩ ፡ ደብዳቤ ። | ፻፲፰ |
| ፲፫ | ስለ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ። | ፻፳፯ |
| ፲፬ | ስለ ፡ ዐማላጅነት ። | ፻፴፬ |
| ፲፭ | ስለ ፡ ፍጡር ፡ ጭከናና ፡ የአምላክ ፡ ርኅራኄ ። | ፻፶፭ |
| ፲፮ | ሕያዋንና ፡ ምውታን ፡ አይተዋወቁም ፡ | ፻፰፯ |
| ፲፯ | ስለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ። | ፻፺፩ |
| ፲፰ | የማይመስል ፡ ምሳሌ ። | ፪፻፬ |
| ፲፱ | ንስሐ ፡ ኀዘን ፡ ልቅሶ ። | ፪፻፭ |
| ፳ | እውነተኛ ፡ የሚያድን ተስፋ ። | ፪፻፱ |
| ፳፩ | ስለ ፡ ማሠርና ፡ መፍታት ። | ፪፻፲፩ |
| ፳፪ | ስለ ፡ መድኃኒትነቱ ። | ፪፻፲፯ |
| ፳፫ | ስለ ፡ ጥምቀትና ፡ ቍርባን ፡ | ፪፻፳ |
| ፳፬ | ስለ ፡ ተዝካርና ፡ ዝክር ። | ፪፻፳፪ |
| ፳፭ | ስለ ፡ በዓላት ፡ | ፪፻፵፬ |
| ፳፮ | ስለ ፡ ምጽዋት ፡ ጸሎት ፡ ጾም ። | ፪፻፵፰ |
| ፳፯ | ስለሚያሰክር ፡ መጠጥ ። | ፪፻፶፫ |
| ፳፰ | ስለ ፡ መብልዕና ፡ ትእዛዝ ። | ፪፻፶፯ |
| ፳፱ | ስለ ፡ ልማድ ። | ፪፻፷፫ |
| ፴ | ስለ ፡ ስግደት ። | ፪፻፷፯ |
| ፴፩ | አድራጊ ፡ ማድረጊያ ፡ ተደራጊ ። | ፪፻፸፩ |
| ፴፪ | ጠቅላላው ፡ ማስረጃ ። | ፪፻፸፰ |
| ፴፫ | ማስገንዘቢያ ። | ፪፻፹፪ |


www.ethiopianorthodox.org

| ገጽ | መሥመር | ግድፈት | ዕርም |
|---|---|---|---|
| ፲፫ | ፳፩ | ከተሰዳቢ | ከተሳዳቢ |
| ፲፰ | ፴፪ | » » | ፲፯ ፯ |
| ፲፱ | ፫ | ኩሉ | ኵሉ |
| ፳፫ | ፲፰ | አሳነማህ | አስነማህ |
| ፳፮ | ፯ | እንዳይደርበት | እንዳይደርስባት |
| ፳፱ | ፴፬ | ከመጻፋ | ከመጻፉ |
| ፶፩ | ፲፬ | ትሬ | ፊት |
| ፶፰ | ፩ | ሰው | ከሰው |
| ፷፩ | ፴ | የመለሰ | የመሰለ |
| ፷፰ | ፲፯ | ይደድኑ | ይከድኑ |
| ፸፩ | ፱ | ዝክቲ | ዝክቱ |
| ፸፬ | ፲፫ | ወድሰሙን ለእደው | ንወድሰሙ ፤ ለእደው |
| ፸፯ | ፴፱ | ርቅው | ርቀው |
| ፸፱ | ፱ | በመሲሔ | በመሲሑ |
| » » | ፳፪ | የእስማዔላውንን | የእስማዔላውያንን |
| ፹፰ | ፲፯ | አለመኸንቸውንም | አለመኾናቸውንም |
| ፺ | ፳፬ | እናገኛለን | እንገናኛለን |
| ፺፫ | ፲፪ | የሚያመልጠን | የሚያመጣልን |
| ፺፯ | ፫ | በማለቻቸው | በማለታቸው |
| ፻፲፫ | ፴፯ | አይናግርም | አይናገርም |
| ፻፳፩ | ፲፰ | እያለችሁ | እያላችሁ |
| ፻፵ | ፳፪ | አሰገደላችሁ | አስገደላችሁ |
| ፻፵፫ | ፴፯ | ሲአል | ሲል |
| ፻፷፬ | ፱ | ነገ | ነገር |
| » » | ፲፰ | አባ | አበ |
| ፻፺ | ፴፪ | ዘኢጎደገ | ዘኢጎደጎ |
| ፻፺፫ | ፱ | ከፍቶለት | ከፍቶላት |
| ፪፻፴ | ፳፰ | አነኑ | አኮኑ |
| ፪፻፴፱ | ፳፯ | ወጸሙ | ወጸመ |
| ፪፻፶፰ | ፴ | ያላዘነ | ያሳዘነ |
| ፪፻፺ | ፲ | የሚፈሄምበት | የሚፈጸምበት |
| » » | ፳፯ | የለ | ያለ |

www.ethiopianorthodox.org